# ኢሕአፓ እና ስፖርት

ክውነተኛ ታሪክ




ክፍል ሁለት

፪

ገነነ መኩሪያ (ሊብሮ)

# ኢህአፓና ስፖርት

## ቅጽ 3

አዘጋጅ ገነነ መኩሪያ(ሊብሮ)

2012 ዓ.ም

© ገነነ መኩሪያ(ሊብሮ)
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ሕትመት - 2012 ዓ.ም

## ማውጫ

1/የኢህአፓ ውሾች .......... 1
2/ የአንቱን ልጅ .......... 19
3/ የጎበዝ አለቃ .......... 48
4/ የቁራው ሰው .......... 53
5/ ዘበኛው ያላወቀው ግብ ጠባቂ .......... 114
6/ ራሳ እስመሳጩ .......... 128
7/ አሮስቶው .......... 146
8/ የተደበቁት ገዳዮች .......... 157
9/ሚኒቹ ገዳይ .......... 176
10/ የሞቃዲሾ ሰው .......... 195
11/ ፈላጊና ተፈላጊ .......... 238
12/ የፍየል ወጠጤ .......... 250
13/ ሽልንጊን .......... 273
14/ እደፍርስ .......... 301
15/ የአጥሩ ገዳይ .......... 328
16/ ተካሹ ቆርቆሮ .......... 332
17 / በቀዳዳ የታየው ልጅ .......... 353
18/ ለቅሶ ቤት .......... 356
19/ መኩርያ .......... 360
20/ ሆያ ሆዬ .......... 371
21/ የበረቱ ግብ ግብ .......... 383
22/ የመሸሸጊያ ከተማ .......... 390
23/ የቤት ሰራተኛዋ .......... 398

## መግቢያ

እነሆ ቁጥር ሶስት ኢህአፓና ስፖርት ወደናንተ አድርሻለሁ። ሶስተኛው መጽሀፌ አዲስ አበባና አንዳንድ ከተሞች ያጠነጥናል። ከቁጥር ሁለት ያላለቁ ጥቂት ነገሮች በስተመጨረሻ ተጨምረዋል። እንደተለመደው ባለቤቴ አስቴር እየለ በጥንካሬ ከጎኔ አለች። መረጃ በማሰባሰብ አበበ ማንደፍሮ ተሳትፏል። መልካም ንባብ።



ምእራፍ 1

## የኢህአፓ ውሾች

ወደ ቶጎ የሚሄደው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የምእራብ አፍሪካን ሰማይ እየቀደደ በመጓዝ ላይ ነው። ጉዞው አሰልቺ በመሆኑ ሁሉም ቶሎ መድረስ ፈልገዋል።በአንደኛው ጥግ የተቀመጡትሁለት ሰዎች ግን የጀመሩትን ወሬ ባለመጨረሳቸው አውሮፕላኑ በማንኛውም ሰአት ቢደርስ ለእነርሱ ችግር አልነበረውም። አውሮፕላኑ ውስጥ የነበሩት ተሳፋሪዎች ስፖርተኞች ይበዙበታል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች ናቸው። ለአስራ አራተኛው አፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ የመጨረሻውን ፍልሚያ ለማድረግ እየሄዱ ነው። ህዝቡ የእነርሱን ውጤት በጉጉት እንደሚጠብቅ ያውቃሉ። ተጫዋቾቹ ጭንቀት ላይ ቢሆኑም አንዱ ተጫዋች ብቻ ዘና ብሎ ሌሎቹን እያዋራቸው ነው።

ዘና ባዩ ተጫዋች ለብሄራዊ ቡድን ሲመረጥ የመጀመሪያው ቢሆንም ልክ ብዙ ልምድ እንዳለውእንደሲኒየር ተጫዋች ነበር የሚሆነው ።ከሁሉም ጋር ይግባባል።አሁን ለረጅሙ የምእራብ አፍሪካ ጉዞ አብሮት የተቀመጠው ተጫዋች በሚያወራው ወሬ ተገርሞ ስለቱ እልም እያለ ነው።የጀመሩትን ወሬ ሳይጨርስ አውሮፕላኑየቶጎን መሬት እንዲነካ አልፈለገም።ሲኒየሩ ተጫዋች በወጣቱ ወሬ ተገርሞ የነገሩን መጨረሻ ለማወቅ እየጠየቀው ነው።ሲኒየሩ ተጫዋች ተገርሞ‹‹ሀይሌ!! ››አለው

‹‹አቤት››

‹‹በጣም የሚገርም ታሪክ ነው››

‹‹የትኛው?››

‹‹የውሾቹ››

‹‹ምኑ ነው የገረመህ?››

‹‹23 ውሻ ያለው ታዳጊ አይቼም ሰምቼም አላውቅም››

‹‹የገረመህ የቁጥሩ መብዛት ነው?››

‹‹አይ!!››

‹‹እና››

‹‹የምትግባቡበት መንገድ››

‹‹ይሄ ነው ያስገረመህ እንዴ››

‹‹እሱ ብቻ ሳይሆን እንዴት ታስተዳድራለህ?››

‹‹ችግር አልነበረውም››

‹‹በምን ነበር የምትግባቡት?››

‹‹የራሳችን ዘዴ አለን››

‹‹መጨረሻቸው ምን ሆነ?››

‹‹የማን››

‹‹የውሾቹ››

ሀይሌ ለጓደኛው መልስ ቶሎ መስጠት አልቻለም፡፡ ውሾቹን ስለሚወዳቸው እንዲህ አይነቱ ጥያቄ ለመመለስ ስሜቱ ይረበሻል፡፡ እናም ይሄን ጉዳይ ላለማስታወስ ወሬውን ተሻግሮ መሄድ ቢፈልግም የነገሩን መጨረሻ ለማወቅ የፈለገው ተጫዋች እዚሁ ጥያቄ ላይ ተጣብቆ ቀረበት፡፡

## እንደገና ወደ ኋላ

ጎህ ሳይቀድና ሰማዩ አይኑን ሳይከፍት ገና በሌሊቱ ቁጥራቸው 23 የሚሆኑ ውሾች በር ላይ ተሰብስበው ዝቅ ባለ ድምጽ ይጮሀሉ፡፡ሌባ አይተው አልነበረም፤ ጅብም አልመጣም ወይም ደግሞ ምግብ ፍለጋ እያሸረገዱ አይደለም፡፡እዚህ በር ላይ መገኘታቸው አቤቱታ ለማቅረብ እንደሆነ የሚያውቀው አንድ ሰው ብቻ ነበር፡፡ አሁንም ድምጻቸውን አሰባስበው እያፈራረቁ የሚጮሁት ሰውየው ቶሎ እንዲመጣላቸው ነው፡፡ 23 የሚሆኑ ውሾች አንድ ቤት በር ላይ መገኘታቸው ለሚያየው ሰው አስገራሚ ቢሆንም ለቀበሌው አብዮት ጠባቂዎች ግን ጥርጣሬ የሚጥል ነበር፡፡ውሾቹ በሌሊት አንድ ላይ ግር ብለው ሲመጡ አሰሳ ለማድረግ ለሚመጡ ሰዎች አስቸጋሪ ነበሩ፡፡፡ በአካባቢው ለሚንቀሳቀሱ የኢህአፓ አባላት ደግሞ ወረቀት ለመበተንና የስኳድ ስራ ለመስጠት ለሽፋንነት የሚጠቀሙባቸው ነበሩ፡፡





ደግሞም ውሾቹ ዋነኛ አገልግሎታቸው ምሽት ላይ ኢህአፓ የሚበትናቸውን በራሪ ወረቀቶች በንቃት መጠበቅ ነው፡፡ አሁን ድቅድቅ ጨለማ በሸፈነው ሌሊት ቤቱን ሳይሳሳቱ መጥተው ለፈርተኛውን ሳይረብሹ ባላቤታቸው በሚሰማቸው ያህል ነበር የሚጮሁት፡፡ አሁን ግን ድምጻቸው እየጨመረ ሄደ፡፡ ሰውየው መምጣታቸውን አውቆ ከመኝታው ብድግ ብሎ ወደውጭ ወጣ፡፡እሱን ሲመለከቱት ጭራቸውን እያራገቡ ለፈሩን ለቀው ወደ ካስ ሜዳ መሄድ ጀመሩ፡፡ሰውየውና ውሾቹ የሚግባባቡ በፉጨት ነው፡፡ቀጭን ፤ አጭር፤ ወፍራም፤ ረጅም የፉጨት አይነቶችያሰማል፡፡በእነዚህ ጩኸቶች ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ይነግራቸዋል፡፡እነዚህ ውሾች ቤታቸው እዚህ አይደለም፡፡ ግማሽ ኪሎ ሜትር ይርቃል፡፡እዚህ እንዲመጡ ባለቤቱ አይፈቅድላቸውም፡፡እነርሱም መምጣት አይፈልጉም፡፡እዚህ የሚገኙት ሲቸግራቸውና ከአቅማቸው በላይ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ዛሬ እዚህ የተገኙት ቀፏቸው ነው፡፡ሞት አጠገባቸው እንደመጣ አውቀዋል፡፡ዛሬ ሊገላቸው የሚፈልግ አካል በራቸው ላይ እንደመጣ ስሜታቸው የነገራቸው ይመስላል፡፡ነገሩ ሲጀመር እንደዚህ ነው,-፡

ደርግ በጣም እየተቸገረ ነው፡፡፡በቅስቀሳና በብልሃት ኢህአፓን ማቆም አልቻለም፡፡በግድያም ሞክሮታል፡፡ይሄም መፍትሄ አላመጣም፡፡ ሰሞኑን የሚበተነው ወረቀት ህዝቡን የሚያነቃና በደርግ ላይ እንዲነሳ የሚያሳስብ ነው፡፡ ሀይሌ ካሴ ኳስ በጣም የሚወድ ታዳጊ ነው፡፡ኳስ መውደዱን የሚውቁት የአባቱን ስም ካሴ የሚለውን ኳሴ አስኝተው ሀይሌ ኳሴ ይሉታል፡፡ከሌሊቱ 11 ሰአት ኳስ ሜዳ የሄደ እሱን አያጣውም፡፡ ሀይሌ የኢህአፓ ታዳጊ ሊግ አባል ነው፡፡ኢህአፓ የሚበትናቸውን ወረቀቶች ተረክቦ የሚያስበትነው እርሱ ነው፡፡ ወረቀቶቹን ሀይሌ አይጽፍም፡፡ የእሱ አለቃ ከሆነው ሰው ጋር ነው የሚቀባበሉት፡፡ በተለመደው ቦታ ይቀጣጠራሉ፡፡ አለቃው ለሀይሌ‹‹ዛሬ ወሳኝ ነገር ይጠብቅሀል ››አለው

‹‹ምንድነው?››

‹‹ትልቅ መልእክት ይተላለፋል››

‹‹የት ነው?››

‹‹እውቶብስ ተራ››
‹‹ምኑ ጋር?››
‹‹በሩ አካባቢ››
‹‹እዛ ብቻ ነው?››
‹‹አዎ ለመንገደኞች ነው››
‹‹ለየትኞቹ?››
‹‹ክፍለሀገር ለሚሄዱት››
‹‹ይሄ ብቻ ነው?››
‹‹አዎ ግን....››
‹‹ግን ምን››
‹‹ተጠንቀቅ››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ወረቀቶቹ አንድ ቦታ እንዳይሆኑ በደንብ ይበታተኑ››
‹‹ሌላስ!!››
‹‹ንፋሱ ወደ መንገዶቹ እንዲወስድ ተደርጎ ይበተን››
‹‹ችግር የለም››
‹‹ወረቀቶቹን በጥንቃቄ አስቀምጥ››
‹‹ቢሮ ነው የምደብቃቸው››
‹‹ቢሮ ሰው ይገባል እንዴ?››
‹‹እኔ ብቻ ነኝ የምገባው››
‹‹ሌሎች አይመጡም?››
‹‹ቢመጡም ወደ ውስጥ ዘልቀው አይገቡም ጥበቃ አለ››
‹‹ማነው የሚጠብቀው?››
‹‹የእኛ አባሎች አሉ››

ሀይሌ ወረቀቱን ተረክቦ ሄደ፡፡ወደ ቤቱ አልገባም፡፡ ወደ ቢሮ ነው የዘለቀው፡፡ ቢሮው ዋሻው ውስጥነው፡፡ የእሱ ጓደኞች ቢመጡም ወደ ውስጥ አይገቡም፡፡ውሾቹም አያሳልፏቸውም፡፡ ከእሱ ፈቃድ ውጭ ማንም ሰው ወደ ውስጡ እንደማይገባ ያውቃል፡፡ ውሾቹ የተደበቀውን ወረቀት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠብቃሉ፡፡ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ወረቀቱም ሲበተን በእጀባ ያገለግላሉ፡፡ ወረቀቱ ተበትኖ ሲያልቅ ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ ለእሁድ ጨዋታ ቅዳሜ ሌሊት የመጫወቻ





ሜዳውን ዙርያ ጥበቃ ያደርጋሉ፡፡ኖራ ይዘው የሚመጡ ልጆች አሉ፡፡ በትልቁ ሜዳው ላይ በኖራ ኢህአፓ ያሸንፋል ብለው ይጽፋሉ፡፡ህዝቡ ጨዋታውን ከመጀመሩ በፊት በደምብ ያነበዋል፡፡ ኖራ ቀቢዎቹ ሌላም ስራ አላቸው፡፡መቀመጫ ድንጋዮች ስር ወረቀት ያስቀምጣሉ፡፡ ለሌሎች አባላት የሚተላለፍ መልእክት ነው፡፡መልእክት ተቀባዮቹ የትኛው ድንጋይ ስር እንዳለ ይነገረዋል፡፡ ሰው ሳይሰበሰብ በቅድሚያ መጥተው ድንጋዩ ላይ ተቀምጠው በዘዴ ወረቀቱን ይዘው ጨዋታውን አይተው ይሄዳሉ፡፡ሌላ ቦታ የሚበተነውም ወረቀት አንዳንዴ ትልቁ ድንጋይ ስር ይደረጋል፡፡

የቀበሌው ታጣቂዎች ወረቀት እየበተነ አካባቢውን የሚያምሰውን ሰው ከነወረቀቱ በእስቸኳይ በቁጥጥር ስር ማድረግ አለባቸው፡፡ ቢሮዎቹ ተፈትሸው ይሄን ስፍራ ለምን ተግባር እንደሚጠቀሙበት ሲያውቁ ምን ያህል እንደተታለሉ የተረዱት ያን ግዜ ነበር፡፡ ዋሻው ውስጥ ተደብቆ ይሆናል ብለው የጠበቁትን አላገኙትም፡፡ ተፈላጊው እንዳያመልጣቸው በፍጥነት ወደ ቤቱ ሄዱ፡፡ ቤቱን ከበቡ፡፡ ማምለጥ የለበትም፡፡ ኢህአፓ በታዳጊዎች ምን ያህል እንደሚጠቀም ቢያውቁም የዚህ ታዳጊ አገልግሎት ግን አናደዳቸው፡፡ አፍንጫቸው ስር ሆኖ ይሄን ሁሉ ነገር ሲፈጽም መሸወዳቸው አበሳጭቷቸዋል፡፡ ጉዳዩን ሰምተው እንዳረጋገጡ በፍጥነት ለማነቅ ድንገት ቤቱ ደረሱና አገኙት ‹‹ሀይሌ አንተ ነህ?››አሉት

‹‹አዎ››
‹‹እጅ ወደላይ››
‹‹ምን አደረግሁ?››
‹‹ደግሞ ምን አደረግሁ ትላለህ?››
‹‹እንዴት››
‹‹አንተ ዋናው ኢህአፓ ሆነህ...››
‹‹እኔ ህጻን ነኝ ኢህአፓ የምትሉትን አላውቅም››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ስራዬ ኳስ መጫወት ብቻ ነው››
‹‹ሌላ ምንም አልሰራህም?››
‹‹ሰፈር ውስጥ ማንንም ጠይቁ››

ሀይሌ ምንም እያገኙብኝም ብሎ ተስፋ አድርጓል። እጅ ከፍንጅ አልተያዘም። አለቃውም እንደማይጠቀምበት ያውቃል። ግን ግርፋቱና ሲቆጥ አንዳንዶቹን ወጣቶች እንዲያጋልጡ እንዳደረጋቸው አልተረዳም ነበር። ኢህአፓም ይሄ እንደሚመጣ ስለሚያውቅ ከአራት ሰው በላይ እንዳይተዋወቁ አድርጓል። ሀይሌ እየተነዳ ወደ እስር ቤት ሄደ። ከግርፊያው በፊት ጥያቄ ተጀመረ ‹‹ወረቀቶቹ የት ነው ያሉት?››አሉት

‹‹የምን ወረቀት?››

‹‹የምትበትኑት››

‹‹እኔ ወረቀት የሚባል ነገር አላውቅም››

‹‹እርግጠኛ ነህ?››

‹‹አዎ››

‹‹ሌሊት ወጥተህ አልበተንክም?››

‹‹እረ በፍጹም››

‹‹እውነቱን አትነግረንም?››

‹‹ስለምን››

‹‹ሌሊት ስለምበትነው ወረቀት››

‹‹እኔ በእርግጥ ሌሊት ወጣለሁ››

‹‹ለመበተን››

‹‹አይደለም››

‹‹እና ››

‹‹ኳስ ለመጫወት ነው››

‹‹ሌሊት 11 ሰአት?››

‹‹አዎ››

‹‹ከመቼ ወዲህ ነው ሌሊት 11 ሰአት ኳስ ያለው››

‹‹በመንገድ መብራት ነው የምጫወተው››

‹‹ብቻህን ነው?››

‹‹አዎ››

‹‹ብቻህን ከሆነማ በደምብ ለወረቀት ብተና ነው የምትወጣው››

‹‹አይደለም››

‹‹ሲሊት እንደምትወጣ ተናግረሃል››





‹‹አዎ››

‹‹ሌሎች ወረቀት ሲበትኑ አይተሃል ማለት ነው››

‹‹አላየሁም››

‹‹ አንተ ካልሆንክ ታዲያ ማነው ወረቀት የበተነው?››

‹‹እኔ እንጃ››

‹‹እርግጠኛ አንተ አልበተንኩም ብለሃል››

‹‹አዎ››

‹‹ምጣጭን ታውቀዋለህ?››(ቅጽል ስሙ ነው)

‹‹አዎ››

‹‹አለቃህ ነው አይደል?››

ሀይሌ አሁን የተጠራውን ስም ሲሰማ ደነገጠ። በእርግጥም አለቃው ነው። እሱ ነው የሚበተነውን ወረቀትና ሌላም ትዕዛዝ የሚሰጠው። ከእዚህ በኋላ መዋሸት እንደሌለበት አውቋል ግን አንዳንዴ የውሸት እንደሚያናዝዟቸው ሰምቷል። ያሁኑ ግን የውሸት እንዳልሆነ በሚቀርበው መረጃ እያረጋገጠ ነው። ሁሉንም ነገር ካልተናዘዘ እጣ ፈንታው ምን እንደሚሆን አልጠፋውም። ከምጣጭ ጋር ትልቅ ቃል ኪዳን እንዳላቸው ያውቃል። እንዴት ሊያጋልጠው እንደቻለ አልገባውም። ቢያገኘው ምን እንደሚያደርገው ግራ ቢገባውም ቃል ኪዳን በማፍረሱ ቢገድለው ደስ ባለው ነበር።

ምጣጭ እዚህ እስር ቤት የሆነ ክፍል እንደሚገኝ ያውቃል። እንዳገኘው ለምን ይሄን እንዳደረገ ይጠይቀዋል። መጣላትም ካለበት ይፋለመዋል። ሌላው ቢቀር እስከ ህይወቱ ፍጻሜ ድረስ እንደሚቀየመውና አጠገቡ እንደማይደርስ ሊነግረው እንደሚፈልግ ተዘጋጅቷል። የቸኮለውም እሱን ለማግኘት ነው። ምን ብሎ እንደነገራቸውም ማወቅ ይፈልጋል። ደግሞም እኮ እሱ ነው ‹‹አንዳችን ሌላችንን አሳልፈን እንዳንሰጥ ቃል እንግባ›› ያለው። ሀይሌ ግን ምንም ሚስጥር ማውጣት አልፈለገም ሌሎችን ሚስጥራዊ ነገሮች እንደተደበቁ ማቆየት እንዳለበት ያውቃል። መጀመርያ ግን አግኝቶት ስለእሱና ስለሚስጥራዊው ቀሻ ምን እንደነገራቸው ማወቅ

ይኖርበታል፡፡ ከእሱ በእድሜ ተለቅ ቢልም ይሄን ነገር ማድረግ እንደሌለበት ያምናል፡፡

ምጣጭ አሁን እስር ቤት ውስጥ እንደሚገኝ ሰምቷል፡፡ እሱን በቶሎ ማግኘት አለበት፡፡እስር ቤት ውስጥ የምጣጭ ጓደኞች ይገኛሉ እነርሱን ማናገር አለበት፡፡ አንድ የእሱን ጓደኛ ማውራት ጀመረ፡፡ ይሄኛው ልጅ የትኛው ሴል ውስጥ እንዳለ ባያውቅም ኢህአፓ ተብሎ ተይዟል፡፡ምናልባት ስለእሱ ያውቅ ይሆናል፡፡አሁን የሚፈልገው ምጣጭ የት እንዳለ ማወቅና ማግኘት ነው፡፡ እነርሱ ቀድመው ስለታሰሩ ብዙ መረጃ እንዳላቸው ያውቃል፡፡ ሁለቱ ብቻ ቁጭ ብለው ማውራት ጀምረዋል፡፡ አሁን ያገኘው ልጅ ከምጣጭ ጋር በደምብ ስለሚተዋወቁ ነው ማናገር የፈለገው፡፡ እንዴት ስለሁኔታው እንደሚነግረው እያሰላሰለ ትንሽ ቆየ፡፡ ሀይሌ ልጁን ተጠጋውና ‹‹ሰው ማመን አስቸጋሪ ነው››አለ

‹‹ምን ገጠመህ?››

‹‹ቃል የተገባባነው ሰው ካደኝ››

‹‹ምን ስለሆነ?››

‹‹ይሄ ድርጅት የተናጋው በከሀዲዎች ነው››

‹‹እውነትህ ነው››

‹‹መጀመርያ ራሳችን ሳናጠራ መንግስትን መቃወም የለብንም››

‹‹ሁሉም ሳይሆን ጥቂቶች የፈጠሩት ነው››

‹‹የኔ ከጥቂቶቹ አንዱና ዋናው ከሀዲ ነው››

‹‹እንዲህ ካንገበገበህ አንተ በጣም ተጎድተሃል ማለት››

‹‹ተጎድተሃል ብቻ አይገልጸውም››

ሀይሌ አሁን የካደውን ሰው ስም ለሁሉም ሰጥቶ በእስር ቤት ውስጥም ማንም እንዳይቀርበው ማድረግ ነው፡፡ ይሄ ብቻ አይበቃም ከማንም ጋር ምግብ መብላት የለበትም፡፡ ሁሉም እክ እንትፍ ብሎ እንዲተፋው ማድረግ አለበት፡፡ እስካሁን ምን እንደነገራቸው አያውቅም፡፡ ይሄን ይጠይቀዋል፡፡ ስለዋሻው ከነገራቸው ድርጅቱን ይጎዳል፡፡ ምክንያቱም የኢህአፓ ንብረቶች እዚያ ነው ያሉት፡፡ ወሳኝ ስብሰባ የሚደረገውም እዚያ ነው፡፡ ቢያንስ እስከ 7 ሰው ለሚሆን ሰው





ዘና አድርጎ እንዲሰበሰቡ ያደርጋል፡፡ ወረቀት፣ ማባዣ፣ ቀለሞችና ሌሎችም ይገኛሉ፡፡ በጣም ተፈላጊ ኢህአፓ እዛ ተደብቆ ያሳልፋል፡፡ እነዚህን ነገሮች ከሀይሌ ውጭ በደምብ የሚያውቀው እሱ ነው፡፡ ምጣጭ ሲታሰር ስለሀይሌ ሲናገር አብሮ የዋሻውን ሚስጥር ማውጣቱ አልቀረም፡፡ አሁንም ሀይሌ ንዴቱን ይዞ ከልጁ ጋር ማውራት ጀምሯል፡፡ ጥያቄውን በድጋሚ ማንሳት ጀመረ ‹‹ምጣጭ እዚህ እስር ቤት አለ አይደል!!!!››አለው

‹‹ለምን ፈለግከው?››

‹‹ለጉዳይ››

‹‹ለእኔ ልትነግረኝ ትችላለህ?››

‹‹እሱን ማግኘት ነው ያለብኝ››

‹‹እዚህ የለም››

‹‹አልታሰረም እንዴ!!!!!!››

‹‹ታስሮ ነበር ››

‹‹እና››

‹‹አሁን አታገኘውም››

‹‹ለምን?››

‹‹የለም››

‹‹ሌላ እስር ቤት ነው?››

‹‹አይደለም››

‹‹አልታሰረማ!!!!››

‹‹ታስሮ ነበር አልኩህ››

‹‹ታድያ የት ወሰዱት?››

‹‹የማይደረስብት ቦታ ››

‹‹የት ነው?››

‹‹ተሸኝቷል››

‹‹ወደየት?››

‹‹ወደመቃብር››

ሀይሌ ደነገጠ፡፡ ምጣጭ ከተገደለ እሱን አይለቁትም፡፡ ምጣጭ ሁሉን ነገር ከዘከዘከ ዋሻው ሲፈተሽ የኢህአፓ ጉድ እዚያ ይገኛል እናም አለቀለት፡፡ ገና ታዳጊ ቢሆንም ስራው ግን ለመንግስት አስቸጋሪ

ስለነበር አይለቁትም፡፡ ገዳዮቹ አብዮት ጥበቃዎች የቀበሌውን ሊቀመንበር ትእዛዝ ብቻ ነው የሚጠብቁት፡፡ በሌላ ግዜ አሰሳ ሲደረግ የዋሻው ጉድ ተጋለጠ፡፡ ሀይሌ ሊቀመንበሩ ጋር ቀረበ፡፡ ሊቀመንበሩ ‹‹ሀይሌ››አሉት

‹‹አቤት››

‹‹ዋሻው ያንተ ነው?››

‹‹አዎ››

‹‹ለምን ተሰራ?››

‹‹ለውሻ ማሳደጊያ››

‹‹ውሾቹ ምን ያደርጉልሃል››

‹‹ሜዳው ሀይወቴ ነው››

‹‹እና››

‹‹ሰዎች ሜዳው ላይ ይጸዳዳሉ››

‹‹አንተ አትከለክልም እንዴ››

‹‹ሞክሬ ነበር››

‹‹እና ››

‹‹ህጻን ስለሆንኩ አይፈሩኝም ውሾች ግን ስለሚያባርሯቸው አይመጡም››

‹‹ለዚህ ብቻ ነው ውሻ የምትጠቀመው?››

‹‹አዎ››

‹‹ሌላ ስራ የላቸውም?››

‹‹ምንም››

‹‹የኢህአፓን ንብረት ይጠብቃሉ አይደል››

‹‹እረ በፍጹም ››

‹‹ወረቀት ተገኝቷል እኮ››

‹‹እኔ ሳላውቅ ደብቀው ነው››

ሊቀመንበሩ ኳስ ይወዳል፡፡ ሀይሌን ደግሞ በችሎታው ያደንቀዋል፡፡ ወደፊት ብሄራዊ ቡድን ትደርሳለህ እያለ ተስፋ ያደርግበታል፡፡ በእዚህ የተነሳ ሀይሌ የሚያስገድል ጥፋት ቢኖርበትም ግድያ ሊስት ውስጥ እንዲገባ ስላልፈለገ ከጥፋተኛነት እያወጣው ነው፡





‹‹ሀይሌ እኛ ሁሉን ነገር እናውቃለን ከእንግዲህ ከእነርሱ ጋር ምንም እንዳትሰራ፡፡ አሁን ዋሻውን እናፈርሰዋለን››አለው፡፡

## አንድ ቀን

‹‹ፍሮም ቪክትሪ ቱ ቪክትሪ›› የተባለውን የቻይና ፊልም ሀይሌ በጣም ይወደዋል፡፡ ሀይሌ ብቻ ሳይሆን በወጣቶች ተደናቂ ፊልም ነው፡፡ ሁሌም ሲታይ አዳራሹ በተመልካች እንደተጨናነቀ ነው፡፡ ሀይሌ ይሄን የቻይና ፊልም ከተከታተለ በኋላ ጉድጓድ አስቆፈረ፡፡ ጉድጓዱ ብቻውን ትርጉም የለውም፡፡ ማንም የማይጠረጥረው ቦታ በመሆኑ ኢህአፓ በድብቅ ይሰበሰብበታል፡፡ ከባድ ውሳኔ ያሳልፍበታል፡፡ ሀይሌ ቦታውን ከእሱ ውጭ ወይም እሱ ከሚፈቅደው በስተቀር ማንም ሰው ወደ ዋሻው መግባት ስለሌለበት አንድ ነገር ማድረግ ፈለገ፡፡ ግን ምንም ውጥን አልነበረውም፡፡ አንድ ቀን ድንገት የሆነ ሀሳብ መጣለት፡፡ ሰዎች ውሻቸው ስትወልድ እነዚያን ቡችሎች ሁሉ መቀለብ ስለማይችሉ ውሻ ለሚፈልጉ ነዋሪዎች ይሰጣሉ፡ እንዲህ አይነቱ ነገር ብዙ ግዜ የተሳካ አይሆንም፡፡

ስለዚህ ቡችሎችን እያመጡ ኳስ ሜዳ ይጥሏቸዋል፡፡ እነዚህ ውሾች በአካባቢው የሚያልፍ ሰው ውሻ ከሌለው ይወስዳቸዋል፡፡ ወይም ጅብ ከመጣ ለቅሞ ያጠናቅቃቸዋል፡፡ የውሻ ባለቤቶች በሌሊት መጥተው ነው የሚጥሉት፡፡ በዚህ ሰአት ደግሞ ሀይሌ ኳስ ሜዳ ጋር እየተጫወተ ጓደኞቹን የሚጠበቅበት ሰአት ነው፡፡ አንድ ቀን የሆነ የሰፈሩ ሰው ሁለት ቡችሎች ጥሎ ሄደ፡፡ የዚህን ግዜ ነው ሀይሌ ሀሳቡ የመጣለት፡፡ እነዚህን ውሾች ወደመደበቂያው ዋሻ ወሰዳቸው፡፡ በጎጃም በረንዳ የሚገኘው ጎንደር ጠጅ ቤት የእነርሱ ነው፡፡ጠጅ ቤቱ በስፋቱ ከአዲስ አበባ ተወዳዳሪ የለውም፡፡ በዘልማድ ስፋቱን ለመግለጽ ‹‹ኑ ካምፕ ነው›› የሚሉት፡፡ ኑ ካምፕ ትልቅ ስጋ ቤት በውስጡ ይበዛል፡፡ ከዚህ ስጋ ቤት ከቅንጣቢ ጀምሮ ለውሻ የሚያስፈልግ ምግቦች በብዛት ማምጣት ጀመረ፡፡ ለውሾቹ የሚፈልጉት ምግብ በሰአቱ ይመጣላቸዋል፡፡ ሰዎች ቡችላ እያመጡ በተለያየ ግዜ ሲጥሉ ሀይሌ እየለቀመ ዋሻው ውስጥ ሲያሳድጋቸው ቁጥራቸው 23 ደረሰ፡፡ ሀይሌ እንዴት እንደሚንቀሳቀሱና በምን ሁኔታ እንደሚገባቡ ስላስተማራቸው ለመደማመጥ ችግር አልነበረባቸውም፡፡



ሀይሌ ካሴ ኳሴ በወጅነቱ

በአብዛኛው በፉጨት ነው መልእክት የሚያስተላልፈው፡፡ ምሽት ላይ ወረቀት ለመበተንና አምፖል ለመስበር የእጀባ አግልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ጠመንጃ የያዙ ሰዎች ክርቅት ሲመለከቱ በጩኸት ምልክት ሲሰጡ ወረቀት በመበተን ግርግዳ ላይ መፈክር በመጻፍና አምፖል በመስበር ላይ የሚገኙ ወጣቶች ይደበቃሉ፡፡ ከዚህ ስራ መለስ ደግሞ ጉድጓዱ ውስጥ ያለውን የኢህአፓን ንብረት ይጠብቃሉ፡፡ወሳኝ ስብሰባ ጉድጓዱ ውስጥ ሲደረግ ምግብ ለመለቃቀም እንኳን አይሄዱም፡፡ ስለተለማመዱ አባላቱ ከእዚያ እስኪሄዱ ዙርያውን ይጠብቃሉ፡፡ የእጀባ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ይሄ ሁሉ የሚከናወነው ፉጨቱን ተከትለው ነው፡፡ የዋሻው ባለቤት እዛ ውስጥ የሚገቡትን የኢህአፓ አባላት አያውቃቸውም፡፡ ማወቅም አይገባውም፡፡ ከእሱ የበላይ የሆነ ሰው ብቻ ነው የሚያውቃቸው፡፡ ትእዛዝ ሲደርሰው ውሾቹን ያዘጋጃቸዋል፡፡ ሰዎቹ ተበታትነው ነው የሚገቡት፡፡ በፉጨት ምልክት ሲሰጥ የተፈቀደለት ሰው እንደገባ ያውቃሉ፡፡ አካባቢውን በመውረር ሰዎች ወደዛ ቦታ ድርሽ እንዳይሉ ያደርጋሉ፡፡





ምግባቸውን ከጠጅ ቤቱ ከሚመጣው በተጨማሪ ቅርብ ከሆነው አውቶብስ ተራ የዶሮ ስጋ ይመጣላቸዋል፡፡ ከተለያየ ክፍለሀገር የሚመጡ አውቶብሶች ማራገፊያቸው አውቶብስ ተራ ነው፡ ዶሮዎች እቃ መጫኛ ላይ ወይም በአውቶብሱ ኪስ ተደርገው ነው የሚመጡት፡፡ አንዳንዶቹ ይሞታሉ፡፡ የዶሮዎቹ ባለቤቶች የሞቱትን እዛው አውቶብስ ተራ ጥለዋቸው ይሄዳሉ ፡፡ሀይሌ እነዚህን የሞቱ ዶሮዎች አሰባስቦ ያመጣላቸዋል፡፡ ከሌላው ስጋ ይልቅ ዶሮው በጣም ጣፈጣቸው፡፡ እናም በህይወት ያለ ዶሮ ሰፈር ውስጥ ማባረር ጀመሩ፡፡ ዶሮ አምልጦ ሲሄድ ከባለቤቱ ጋር አብረው ያባርራሉ፡፡ ቀድሞ የያዘ ዶሮዋን ይወስዳል፡፡ ውሻው ቀድሞ ይዞ ባለቤቱ ደርሶ ሊያስጥል ሲሞክር ሁሉም ግር ብለው ስለሚያጅቡ ከሀያ በላይ ውሻ ሲከበው የዶሮው ባለበት በፍራቻ ትቶ ይሄዳል፡፡ አንዳንዴ ሴት ዶሮ ሲያባርሩ እንቁላል ጣይ በመሆኗ ሀይሌ በፉጨት ይመልሳቸዋል፡፡ ፉጨቱን እንደሰሙ በሩጫ ላይ ካሉ ተቀይሰው ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳሉ፡፡ የዶሮ እንደሰሙ በሩጫ ላይ ካሉ ተቀይሰው ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳሉ፡፡ የዶሮ አደኑ ነገር ከጎዳና ላይ ወደ ሰፈር ውስጥም ዘለቀ፡፡ ቤት ለቤት አደን ተጀመረ፡፡ የዶሮ ባለቤቶች ተማረሩ፡፡ የውሾቹ ባለቤት ማን እንደሆነ አወቁ፡፡ አንድ ቀን ሶስት ዶሮ የተጠለፈበት ሰው ሀይሌ ጋር መጣና‹‹ምን እያደረግክ ነው››አለ

‹‹ምን››

‹‹ዶሮዎቼ ተወሰዱብኝ››

‹‹ማን ወሰደብህ?››

‹‹ያንተ ናቸዋ››

‹‹የኔ ምን››

‹‹የአንተ ውሾች››

‹‹የእኔ ውሻ ቤት ነው ያለው ከግቢ አይወጣም››

‹‹እነዛ ታድያ የማናቸው››

‹‹የትኞቹ››

‹‹23ቱ››

‹‹እነርሱማ ያንተ ናቸው››

‹‹ምን እያልክ ነው››

‹‹ቡችላ እያሉ አንተ አይደለህ እዛ የጣልካቸው››

‹‹መቼ››

‹‹በልጅነታቸው ሁለት ግዜ አምጥተህ ስትጥል አይቸሃለሁ››

‹‹እና››

‹‹ጠብቀው ተበቀሉህ››

‹‹እንዲህ ነው ነገሩ!!››

‹‹አዎ››

‹‹ከእንግዲህ ዶሮየን አንድ ውሻ ቢነካ እገድለዋለሁ››

‹‹የቱን?››

‹‹አባራሪውን››

‹‹ብዙ ናቸው እኮ››

‹‹ቢሆኑስ››

‹‹ከእንግዲህ ለዶሮ ሳይሆን ላንተም ፍራ››

‹‹ምን ልታደርግ?››

‹‹አይለቁህም››

የስፈሩ ሰዎች ስጋት አደረባቸው፡፡ ውሾቹ እየጠነከሩና እየተደራጁ ሀይለኛ ሆነዋል፡፡ ከዋሻው ጥበቃ አገልግሎት መልስ በየመንደሩ ቅኝት በሚያደርጉበት ግዜ አንድ አይነት አደጋ ለማድረስ ነው በሚል ብዙዎቹ ስጋት ላይ ወደቁ፡፡ሁሉም መጥፊያቸውን ይፈልግ ነበር፡፡ አንድ ቀን ነገሩ ሲጋለጥ የኢህአፓ ጥበቃ ቡድን አባላት መሆናቸው ተደረሰበት፡፡ የአብዮት ጥበቃዎች ከፍተኛ ዝግጅት አድርገው ፈጁዋቸው፡፡ ባለቤቱም ወደ እስር ቤት ተወረወረ፡፡

## እንደገና በሌላ ቀን

የስፈራቸው ቡድን ጠንካራና ሀይለኛ ነው፡፡አጥቂውና አማካዩ ለተጋጣሚ አስቸጋሪ ቢሆንም ተከላካይ መስመሩ ግን ቀዳዳ የበዛበትና እንደወንፊት አሾላኪ ነው፡፡ተከላካዩ ይሄ ችግር ቢኖርበትም ቀዳዳዎቹ የሚሸፈኑት በግብ ጠባቂው ይልማ ስዩም ነው፡፡እሱ በሩ ላይ ባይኖር ቡድኑ የግብ ጎተራ ይሆን ነበር፡፡ቡድኑ ቡድን ቢሆንም ዝም ብሎ እግር ኳስ የሚጫወት አይደለም፡፡ ለኢህአፓ ስራ አግልግሎት የሚሰጥ ነው፡፡ በወቅቱ ማንኛውም ወጣት ሁለት ሆነው አንድ ቦታ መታየት የለበትም ፡፡ህጉ ይከለክላል፡፡የሆነ ነገር እያሰቡና እየዶለቱ





ነው በሚል ያስቀጣቸዋል፡፡ብቸኛው አብሮ መሰባሰቢያ እግር ኳስ ነበር፡፡ ከየትም ቀበሌ ይምጣ ተሰባስበው በጋራ ማውራትና መንቀሳቀስ ይቻላል፡፡እዚህ ቀበሌ የሚገኘው ቡድን መረጃ አቀባይ፣ወረቀት በታኝና ተያያዥ ስራ የሚያከናውን ነው፡፡ ሌላ ቦታ የሚገኙት የእግር ኳስ ቡድኖች ግን አብዛኛውን ስኳዶች የተሰባሰቡበት ነው፡፡ለእግር ኳስ ጨዋታ በየቦታው መንቀሳቀስ ስለሚችሉ ተፈላጊውን ሰው ሰፈሩና እቤቱ ድረስ ሄደው መግደል ይችላሉ፡፡ ይሄኛውም የእግር ኳስ ቡድን አንዳንዶቹ ሌሎች ቦታ እንደሚደረገው ደረጃቸውን ለማሳደግ እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡

ቡድኑ የሚሰባሰበው መሳለሚያ ሞቢል አካባቢ ነው፡፡ ከተሰባሰቡ በኋላ ተያይዘው ወደ ኳስ ሜዳ ይሄዳሉ፡፡ የቡድኑ አባላት ሲሟሉ ብቻ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ያልመጣ ሰው ካለ አስር ደቂቃ ይጠብቁታል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን አይታገሱም ትተውት ይሄዳሉ ፡፡ ተሰላፊ ከሆነ በእርሱ ቦታ ሌላ ሰው እንዲገባ ይደረጋል፡፡ዛሬ ግን ከአስር ደቂቃ ባለፈ መጠበቅ ነበረባቸው ፡፡ህጉ ማንም ይሁን ማን ካረፈደ አይጠበቅም፡፡ዛሬ ግን ለመቆየት ተገደዱ፡፡ያረፈደው ግብ ጠባቂው ይልማ ነው፡፡በእሱም ላይ ህጉ መስራት አለበት ሌላ ግብ ጠባቂ ስላለ በእሱ መተካት ነው ፡፡ነገር ግን ይሄን ሀሳብ ለማንሳትና ለመወሰን ማንም አልደፈረም፡፡ይልማን ትቶ መሄድ ለተጋጣሚ ‹‹ና አሸንፈኝ›› ብሎ እጅ መስጠት ነው፡፡ይልማ አንድም ቀን ቀርቶ አያውቅም፡፡ አርፋጅም አይደለም፡፡ሌላውተጫዋች ቢቀር ቀዳዳው ይሸፈናል ፡፡የይልማን ቦታ ግን ማንም አይሸፍንም፡፡ እሱ የሚተካ ስላልሆነ ለመጠበቅ ተገደዋል ፡፡ስአቱ ከአስር ወደ አስራ አምስት ከዚያም ወደ ሀያ እንዲህ እያለ የደቂቃው ቁጥር ከፍ አለ፡፡ሁሉም ትእግስቱ ተሟጠጠ፡፡ ዛሬ ደግሞ አደገኛ ጨዋታ ስላላቸው ይሄን ውጤት ይፈልጉታል፡፡ ይህን ጨዋታ ያለ ይልማ የሚደፈር ባይሆንም አሁን ግን መድፈር አለባቸው ፡፡ስአቱም ስለሄደ ይልማን ትተውት ሄዱ፡፡ ቡድኑ በስንልቦና እንደተጎዳ ወደ ግጥሚው ሄደ፡፡ በመንገድ ላይ በንዴት መነጋገር ጀመሩ‹‹ምን ማድረጉ ነው ግን..››አለ

‹‹ማን?››

‹‹ይልማ ነዋ››

‹‹ምን አውቅለታለሁ››
‹‹እያወቀ!!››
‹‹ምኑን?››
‹‹ዛሬ ከባድ ጨዋታ እንዳለን››
‹‹እሱ አይደል እንዴ የሚገርመው››
‹‹ለምኑኝ ለማለት ነው?››
‹‹ተው ባክህ››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ማንንም አንለማመጥም››
‹‹እውነትህን ነው››
‹‹ሌላ ኀበዝ በረኛ መፈለግ አለብን››
‹‹ግን››
‹‹ግን ምን ?››
‹‹እቤቱ ብንሄድስ››
‹‹ለምን እንሄዳለን››
‹‹በጣም ያስፈልገናል››
‹‹ጨዋታ እንዳለን ያውቅ የለ››
‹‹አዎ››
‹‹ገንዘብ ተቀብሎ ይሆን እንዴ››
‹‹ከማን››
‹‹ከተጋጣሚያችን››
‹‹ለምን?››
‹‹እሱ ከሌለ እንድምንሸነፍ ካወቁ ይከፍሉታል››
‹‹ሊሆን ይችላል››
‹‹ምን አልክ››
‹‹እንዳውም ነው ግን…››
‹‹ግን ምን››
‹‹ቤቱ ብንሄድስ››
‹‹ሆን ብሎ ከቀረ ለምን ቤቱ መሄድ አስፈለገ ››
‹‹ ግን እንሞክር!››
‹‹እና ቤቱ እንሄድ?››





‹‹አዎ››
‹‹ከዚያ ልንለምነው ነው››
‹‹እንጠይቀዋለን››
‹‹ባክህ ተወው ይቅር››
‹‹ግድ የለም ቤቱ ካለ እናናግረውና የሚፈልገው ነገር ካለ…››

ተጫዋቾቹ ወደ ቤቱ ሄዱ፡፡ ወደ ቤቱ ለመሄድ ብቻ ፈልገው አልነበረም፡፡ ሜዳው በዚያ በኩል የሚያወጣ መንገድ ስላለው እንዲመቻቸው ብለው ነው፡፡ሁሉም ተናደዋል፡፡ ካገኙት እስኪበቃው ነው የሚሰድቡት፡፡ መጣላትም ካለባቸው እንደዚሁ፡፡ ማንም ሰው ከቡድኑ በላይ መሆን የለበትም የሚል አቋም አላቸው፡፡ እንደበሸቁና እንደተንጨረጨሩ ተጫዋቾቹ ወደ ሰፈሩ ደረሱ ፡፡ቤቱ ጋር ተጠጉ ፡፡ ይልማን በሩ ላይ አገኙት፡፡ በረኛው እዚሁ ሰፈር ሆኖ ለምን እንደቀረባቸው አሁን አወቁ ፡አንድም ቀን ቀርቶና አርፍዶ የማያውቅ ልጅ በእንዲህ አይነት ቦታ እናገኘዋለን ብለው አልገመቱም፡፡

ሁሉም ተጫዋች ከተሰባሰቡበት ቦታ እዚህ እስኪደርሱ ድረስ እያሙት፤ እየወቀሱትና እያወገዙት መጥተው በሩ ላይ ሲደርሱ ሁሉም ‹‹ይቅር ይበለን›› ማለት ጀመሩ፡፡ በርግጥም ሌላ በረኛ መፈለግ አለባቸው ወይም ቡድኑ ከእንግዲህ በተጠባባቂ በረኛ ነው መቀጠል ያለበት፡ ተጫዋቾቹ እንደተቀጡ እንደተናደዱ ወደ ቤቱ ሲጠጉ ይልማን ወድቆ አገኙት፡፡ ሰውነቱ በጥይት ተበሳስቷል፡፡ የቀበሌው ደህንትና አብዮት ጥበቃዎች በረኛቸውን በሩ ላይ ደፍተወት ሄዱ፡፡ ሀይሌ ካሴ ‹‹...ይልማ ኀበዝ በረኛ ነበር፡፡ትልቅ ደረጃ ይደርሳል ተብሎ የሚጠበቅ ነው ግን በሩ ላይ ገድለውት ሄዱ››ይላል፡፡ይሄ ቀበሌ በዚህ ሳምንት ለግድያ ታጥቆ የተነሳ ነው፡፡እዚህ ቡድን ላይ ግቡን ከሚጠብቀው ከአንድ ቁጥሩ ጀመሩ፡፡ ቀስ እያሉ ወደ ተከላካዮቹ አለፍ ሲልም ወደ አማካዩ እየዘለቁ ይሄዳሉ፡፡

እርግጥ ነው ሰሞኑን በቀበሌው ብቻ ሳይሆን በከፍተኛውም የግድያ ሳምንት ነው፡፡ ወቅቱን ሀይሌ እንዲህ ያስታውሳል‹‹.....እኔ በደምብ የማስታውሰው የነደብረወርቅን ነው፡፡ እሷ፤ብርየና ሉሉ ዋጋው የተባሉት ልጆች ተይዘው መሳለሚያ መስጊዱ ጋር ሰበሰቧቸው፡፡ እዛ ያመጧቸው ህዝብ በብዛት እንዲመለከታቸው ነው፡፡

ኢህአፓ የሚጠቀምበትን ማባዣ ማሽን ጭምር ይዘዋል። እንዳያመልጡ ዙርያውን መሳርያ በያዙና መያዝ ብቻ ሳይሆን በደንኑ አብዮት ጥበቃና ወታደሮች ተከበዋል። ህዝቡ ካያቸው በኋላ ወደ እስር ቤት ተወሰዱ። ደብረወርቅ ታመልጣለች ተብሎ በአይነ ቁራኛ ይጠብቋት ነበር። ልጅቷን በጣም ይፈሯት ነበር። ሲኒማ ራስ የኢህአፓ አባላት ቤቱን ከበው ሲኒማ አስቁመው መፈክር ባሰሙበት ግዜ ድርጊቱን ከፈጸሙት አንዷ እንደሆነች ይነገርላታል። ዝናዋ በጣም ላቅ ብሎ ነበር። ብዙ ግዜ እየፈለጉ እያሰሱ ሊያገኟት አልቻሉም ነበር። አሁን ግን እጃቸው ገባች። ተከበው የሚመለከተው ሰው በእሷ መያዝ በጣም ነው የተቆጨው። ለህዝብ ከታዩ በኋላ ወደ እስር ቤት ተወሰዱ ።

ሌሊት እኔ ወደ ኳስ ሜዳ ስሄድ ድምጽ የሰማሁ መሰለኝ ውሾቹ ግን አውቀው ወደዚያ እየሮጡ ሄዱ። ሁሉም ሰው ቀን ያያቸው ግዜ ደርግ እንደሚገድላቸው አውቋል። ወደተተኮሰበት ቦታ ስደርስ ሶስቱም ወድቀዋል። ያለማጋነን ከሁለት እና ሶስት መቶ በላይ ጥይት የተኮሱባቸው ይመስለኛል። እኔ ቦታው ላይ ስደርስ ማንም አልነበረም። ሰውነታቸውን ስመለከት ወንፊት ሆኗል። ስጋቸው በትንንሹ ተቦጫጭቆ ተበታትኗል። በልብሳቸው ነው የለየኋቸው። ሰዎቹ በቅርብ ገድለዋቸው እንደሄዱ የሚያሳየው የጥይቱ ባሩድ ሽታ ትኩስ እና በጣም ይሸት ነበር››ይላል። ሀይሌ አሁን ኑሮውን በአሜሪካ አድርጓል።





## ምእራፍ 2

## የአጎቱ ልጅ

ትንሹ ልጅ በሳምንቱ መጨረሻ ደስታው በፍጹም ይጨምራል። ምክንያቱ ደግሞ በልሁ(ስሙ የተቀየረ) እቤታቸው ይመጣል። ምንግዜም ስጦታ ያመጣለታል። እርካታ የሚሰጠው በስጦታው ብቻ አልነበረም። ልዩ ልዩ ጨዋታ ያጫውተዋል።እቤታቸው ግቢ ባለው ባህር ዛፍ ላይ ዥዋዥዌ ሰርቶ የሚያንዠዋዥወው እርሱ ነው። እነርሱ ጋር ከመጣ ጀምሮ ብዙ ግዜውን የሚያጠፋው ትንሹን ልጅ በመንከባከብና ፍላጎቱን ጥግ በማድረስ ነው።ከቤት ውጭ ቆይታቸው ደግሞ ያማረና አስደሳች ነው ።ፊልም ቤት ይወስደዋል፤የእነበልሁ ቡድን የእግር ኳስ ግጥሚያ ባለው ግዜ ራቅ ያለ ሰፈርም ቢሆን ይዞት ይጓዛል ።እናትና አባቱ የማያደርጉለትን እንክብካቤ ከእርሱ ያገኛል።የትንሹ ልጅ አባት ለበልሁ አጎት ነው።

ከሰኞ እስከ አርብ ለትንሹ ልጅ ድብርት ነው ።አርብ ማታ ቅዳሜን ይናፍቃታል።በልሁ ያልመጣ ቀን በር ላይ ቆሞ ምሽት ድረስ ይጠብቃል።ያላገኘው ግዜ ያለቅሳል፤ ቤተሰቡን ያስቸግራል ።በጥቅሉ በልሁ ለትንሹ ልጅ ሱስ ሆኖበታል።አንድ እለት የትንሹ ልጅ አባት ህይወቱ አለፈ። በልሁ ግን ለቅሶው ላይ አልተገኘም። ጭራሽ ወደ ቤታቸውም አልመጣም። የደረሰበት አልታወቀም። ትንሹ ልጅ በልሁንም እንደአባቱ እንደገደሉት ነው የተገነዘበው። ከግዜ በኋላ በልሁ መታሰሩን ትንሹ ልጅ ሰማ። ከእናቱ ጋር እየሄዱ ይጠይቀው ጀመር። ከሁለት አመት በኋላ በልሁ ከእስር ተፈትቶ ወደ ቤት መጣ። የአጎቱን ለቅሶ ተቀመጠ። ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ቤቱ ውስጥ እንደ አዲስ ለቅሶ ተጀመረ፡ እርሙንም አወጣ።

ትንሹ ልጅ አሁን አባት የለውም።አባቱ ከሞተ ጀምሮ በልሁም በመታሰሩ ህይወት መጥፎ ሆኖበት ነበር። ነገር ግን በልሁ ተስፋ ሰጠው። እንደ አባት ሆኖ ምንም ሳይጎድለው አሳደገው።

ትምህርቱን በደምብ እንዲከታተል ይቆጣጠረዋል። እቤት እየመጣ ያስጠናዋል። አንድ ቀን ትንሹ ልጅ ‹‹ማነው ያሳሰረህ?›› አለው

‹‹ወቅቱ ነው››
‹‹ወቅቱ ማነው?››
‹‹ወቅት ማለት ግዜ ነው››
‹‹አልገባኝም››
‹‹አንድ ሰው ተገደለ››
‹‹እና ››
‹‹ገዳዮቹ አመለጡ››
‹‹እሺ››
‹‹እኔ ተያዝኩ››
‹‹ለምን?››
‹‹መንገድ ላይ ቆሜ ነበር››
‹‹ምን እያደረግክ››
‹‹ታክሲ እየጠበቅሁ››
‹‹ታድያ ታክሲ መጠበቅ ያሳስራል እንዴ››
‹‹ወጣት በመሆንህ ትታሰራለህ››
‹‹ለምን?
‹‹ግዜው ነው ያልኩህ ይሄንን ነው››

በልሁ ለዚህ ታዳጊ እንዴት አድርጎ ማስረዳት እንዳለበት ቸገረው። ደግሞም አንድ ነገር ከጠየቀ አይለቅም ችክ ይላል። የታሰረበት ጉዳይ አሁን ለትንሹ ልጅ እንደሚነግረው አልነበረም፡ የመኢሰማ ሊቀመንበር ቴዎድሮስ የተገደለ ቀን ነበር የተያዘው። የደህንነት ሰዎች ተባባሪ ነህ በሚል ነው በቁጥጥር ስር ያዋሉት። በኋላ ግን ትክክለኛ ገዳዮቹ ተያዙ። አንድ ሳምንት ሙሉ ያለእረፍት በልሁን ገረፉት። በመጀመርያው ቀን‹‹ገዳዮቹን ታውቃቸዋለህ አይደል?››አሉት

‹‹አላውቃቸውም,,
‹‹ሽፋን ሰጥተሃል››
‹‹የምን ሽፋን?››
‹‹ገዳዮቹ እንዲያመልጡ››





‹‹እኔ ግድያ መኖሩንም አላወቅሁም››
‹‹የቴዎድሮስ ቢሮ በሩ ላይ ምን ታደርጋለህ?››
‹‹ትምህርት ቤት እየሄድኩ ነው››
‹‹የት››
‹‹ቦሌ››
‹‹ተማሪ ትምህርት ጀምሮ በዛ ሰአት አንተ.....››
‹‹አርፍጄ ነው››
‹‹ለምን አረፈድክ?››
‹‹ለገሃር መንገድ ተዘግቶ ነው››
‹‹ለምን?››
‹‹እነዛ ኢህአፓ የሚባሉት››
‹‹እና››
‹‹ወታደሮች ለመያዝ ከበዋቸው መንገድ ተዘጋ››
‹‹አንተ እኮ የተያዝክ ቀን ከታክሲ መያዣ በተቃራኒው ነው የነበርከው››
‹‹መጀመርያ በዛኛው ነበርኩ››
‹‹እና ››
‹‹ግርግር ሲነሳ መንገድ ተሻገርኩ››

ሰዎቹ በልሁን አላመኑትም።የቴዎድሮስ መሞት ደርግን አንገብግቦታል።ኢህአፓ መኢሰማን ለመያዝ እየተሟሟተ ነበር። የቴዎድሮስ ግድያ በሌሎችም አመራር ላይ ስጋት ጥሎ የላባደሩ ሀይል በኢህአፓ እጅ እንዳለ ለማሳየት ነው በመባሉ ነው።ገራፊዎቹ ይሄንን ግድያ ማን እንዳቀነባበረና ማን እንደመራ ማወቅ ይፈልጋሉ። የወታደር ልብስ ያደረጉ ሰዎች ናቸው ጥበቃውን አሳምነው ገብተው ሊቀመንበሩን የገደሉ።ስትራቴጅው ከደህንነቱ አቅም በላይ ነበር።ደርግ በቴዎድሮስ ግድያ የተጣራ ነገር ይፈልጋል።እነዚህን ነገሮች የሚያገኙት ከበልሁ እንደሆን ያውቃሉ።እናም እስኪበስልና እስኪሽረካከት ድረስ ገረፉት። ሆኖም ምንም ጠብ የሚል ነገር አላገኙም። በኋላ ግን በልሁ የተሳሳተ ሰው እንደሆነ አወቁ። በመደብደብ ግዜያቸውን ስላባከኑ ተናደዱ።

ገራፊዎች በምርመራ ወቅት ብዙ ግዜ የሚያበሳጯቸው ምንም የሌለው ላይ በድብደባ ግዜ አሳልፈው በኋላ ግን ባለጉዳዩ ሌላ ሰው ሆኖ ሲገኝ ይናደዳሉ። የሚያበሳጫቸው የእነርሱ መልፋት ብቻ ሳይሆን ከአለቆቻቸው የሚደርስባቸው ቁጣ ነው።ለዚህም ነው በበልሁ ማውጣጣት ምንም ባለመገኘቱ የተበሳጩት።እውነቱ ግን እንዲህ አልነበረም።የግድያውን ስትራቴጂ ሁለተኛ ሰው ሆኖ የቀየሰው እርሱ ነው።በር ላይ ሆኖ ሽፋን የሰጠው ራሱ በልሁ ነበር።ገዳዮቹ እንዴት መግባት እንዳለባቸው ጥቃቱን ፈጽመው እንዴት መውጣት እንዲሚኖርባቸው ነድፎ፣ አሰማርቶና አስፈጽሞ ያጠናቀቀው እርሱ ነው። እንደሚይዙት አውቆ ከመንገዱ ተሻግሮ መሳርያውን ጢሻ ውስጥ በዘዴ ደብቆ ብቅ አለ። እንቅስቃሴውን አይተው በጥርጣሬ ያዙት ግን ምንም አላገኙበትም። ከሁለት አመት በኋላ ተፈታ።

በልሁ ከትንሹ ልጅ ጋር ሲሆን አስልቺ የሚሆንበት የማያልቅ ጥያቄውንና ስለአባቱ እያነሳ የሚጠይቀው አስቸጋሪ ጉዳይ ነው።ትንሹ ልጅ ‹‹አስለአባቴ ንገረኝ››አለው

‹‹ምን ልንገርህ››

‹‹እንዴት አይነት ሰው ነው››

‹‹ጎበዝ››

‹‹ጎበዝ ስትል!!!››

‹‹ለአላማው የቆመ ነው››

‹‹ማነው የገደለው?››

‹‹ተገድሎ ነው እንዴ?››

‹‹አዎ››

‹‹ማን ነገረህ?››

‹‹እናቴ››

‹‹እኔ እንኳን አላውቅም››

‹‹አልሰማህም ማለት ነው››

‹‹እኔ ታስሬ ነበር ››

‹‹የታጠቁ ሰዎች ናቸው የገደሉት አሉ››

‹‹መንገድ ላይ ነው?››

‹‹አይደለም ቢሮ ድረስ ገብተው ነው››





‹‹አልተያዙም››

‹‹በመኪና አመለጡ አሉ››

‹‹ቶሎ ነው የሞተው?››

‹‹አይደለም ሆስፒታል ገብቶ ትንሽ ቆይቶ ነው››

‹‹እንደርሱ ነው እንዴ?››

‹‹አዎ ቶሎ ህክምና ቢያገኝ ይተርፍ ነበር።ግን....››

‹‹ግን ምን?››

‹‹ሀኪሞች አልነበሩም አሉ››

‹‹ማለት? ››

‹‹ብዙ ጎበዝ ሀኪሞች ወታደሩን ለማከም ወደ ጦር ሜዳ ሄደዋል››

‹‹አዎ ያኔ በእርግጥ የሱማሌ ወረራ ጦርነት ነበር››

‹‹እናቴም እንደነገረችኝ ለማጅ ሀኪሞች ናቸው የነበሩት››

‹‹ያሳዝናል››

‹‹ያማል እንጂ››

‹‹ቶሎ አልሞተም አልከኝ?››

‹‹አዎ እናቴ አግኝታው ነበር››

‹‹የት?››

‹‹ሆስፒታል››

‹‹ሳይሞት?››

‹‹አዎ››

‹‹ምን አላት››

‹‹ልጆቼን አደራ አላት››

‹‹ወይኔ አጎቴ!!!››

‹‹ያሳዝናል አይደል?››

‹‹አዎ፣ከመሞቱ በፊት ሌላስ ምን አላት?››

‹‹እናቴን ለምን አትጠይቃትም››

‹‹ምኑን?››

‹‹በዛን ቀን የነበረውን ሁኔታ››

‹‹በዚህ ጉዳይ እንኳን አላወራትም››

‹‹ለምን?››

‹‹መጥፎ ስሜት ውስጥ ልከታት አልፈልግም››
‹‹ምን ችግር አለው?››
‹‹አንተም ቢሆን አታውራ››
‹‹ምነው››
‹‹ትምህርትህን ይረብሽብሃል››
‹‹ግድ የለም እናቴን ጠይቃት››
‹‹ምኑን?››
‹‹ሆስፒታል ስለነበረው ሁኔታና ሲሞት ምን እንዳላት››
‹‹ለምን?››
‹‹እኔም ማወቅ የምፈልገው ነገር አለ››
‹‹አልገባኝም››
‹‹የዚያን ግዜ የነበረውን ሁኔታአልነገረችኝም››
‹‹ቅድም ነገረችኝ አላልከም እንዴ››
‹‹በግልጽ አልነገረችኝም››
‹‹ለምን?››
‹‹ላንተ አይሆንም አለች››
‹‹ምንድነው ላንተ የማይሆነው››
‹‹ማወቅ የሌለብህ ነገር አለ አለችኝ››
‹‹እኔም በናትህ ሀሳብ እስማማለሁ››
‹‹እኔ ግን አልቀበለውም››
‹‹ምን?››
‹‹ገዳዮቹንም እኮ ነግሯት ይሆናል››
‹‹አንተ ልጅ ይሄ ነገር ይቅርብህ››
‹‹ለምን?››
‹‹ሊያስገድልህ ይችላል››
‹‹እንዴት››
‹‹አንተ ገዳዮቹን አታውቅም አይደል››
‹‹አዎ››
‹‹እነርሱ ግን ያውቁሃል››
‹‹ቢያወቁኝስ?››
‹‹ለመበቀል መዘጋጀትህን ካወቁ ቀድመው ያጠፉሃል››





‹‹እኔ እኮ ላንተ በሚስጥር ነው የነገርኩህ››
‹‹ሚስጥር ለሰው አይነገርም››
‹‹እንዴት?››
‹‹ከባለቤቱ ከወጣ ይዛመታል››
‹‹አንተ አባቴ ስለሆንክ ነው የነገርኩህ››
‹‹በቀልን ከውስጥህ አውጣ››
‹‹አንተ ግን ሰዎቹን አታውቃቸውም?››
‹‹እነማንን››
‹‹ኢህአፓ የተባሉት ናቸው እኮ አባቴን የገደሉት››
‹‹አላውቃቸውም››
‹‹አንተ ኢህአፓ ተብለህ አይደል የታሰርከው››
‹‹ተባልኩ እንጂ አይደለሁም››
‹‹ግን ኢህአፓ የተባሉትን አልወዳቸውም››
‹‹እኔም አልወዳቸውም››
‹‹እኔ ግን ስለነርሱ ማወቅ እፈልጋለሁ››
‹‹ስለማን?››
‹‹ኢህአፓ ስለተባሉት››
‹‹ለምን?››
‹‹አልነግርህም››
‹‹አሁን ነገሩ አልቋል እነርሱም የሉም››
‹‹በል ሁ››
‹‹አቤት››
‹‹በጣም እወድሃለሁ››
‹‹እኔም››
‹‹በልደቴ ምን ታደርግልኛለህ?››
‹‹አልነግርህም››
‹‹ለምን?››
‹‹ሌላም ቀን እኮ ነግሬህ አላውቅም››
‹‹እሽ ጠብቃለሁ››
‹‹ለመሆኑ ስንት አመት ሆነህ››
‹‹16 ሆነኝ››

በልሁ ሁሌም ይሄን ልጅ ይከታተለዋል፡፡ከማን ጋር እንደሚውልም ያጣራል፡፡ ከመስመር ለቆ እንዳይሄድም ይገድበዋል፡፡በዋናነት የአባቱን ገዳዮች እንዳያጣራና አጣርቶም እንደይከታተል ያደርገዋል፡፡ምክንያቱም ማጣራቱን በጀመረ በአጭር ግዜ ሰዎቹ ላይ ሳይደርስባቸው እንደሚገድሉት ይገምታል፡፡መገመት ብቻ ሳይሆን ያውቃል፡፡በተቻለ አቅም የአባቱን ገዳዮች እንዳያጠያይቅ ይቆጣጠረዋል፡፡ትንሹ ልጅ ‹‹አባቴን ትወደዋለህ አይደል››አለው

‹‹አዎ፤እሱ ነው እኮ ያሳደገኝ››

‹‹እውነት!!››

‹‹አባቴ በሞተ ግዜ ለአባትህ አደራ ልጆቼን ብሎት ነበር››

‹‹አባትህ ምን ሆነው ሞቱ››

‹‹በበሽታ››

‹‹ያሳዝናል ››

‹‹እኔ ግን ስለ አባቴ ማንሳት አልፈልግም››

‹‹ለምን?››

‹‹መጥፎ ስሜት ውስጥ እገባለሁ››

‹‹እኔ ግን እንዳንተ አይደለሁም››

‹‹እንዴት?››

‹‹ስለአባቴ ሁሌም ማንሳት ፈልጋለሁ››

‹‹እሱ ያንተ ምርጫ ነው›

‹‹ግን አንተ በትክክል አባቴን ትወደዋለህ?››

‹‹አዎ አልኩህ እኮ››

‹‹ግን ለምን ዝም አልክ››

‹‹ምኑን?››

‹‹ገዳዮቹን››

‹‹አላውቃቸውም አልኩህ እኮ››

‹‹ብትጠይቅ ትደርስባቸው ነበር››

‹‹ምን ማለት ነው››

‹‹የእኔ ጓደኞች የአባታቸውን ገዳይ ተበቅለዋል››

‹‹ባንተ እድሜ ያሉ?››





‹‹ታላቅ ወንድሞቻቸው ናቸው››

‹‹እኔ አላውቃቸውም ፤በዛ ላይ የት አገኛቸዋለሁ››

ስለአባቱ እንዳያነሳበት ብዙ ግዜ ነግሮታል፡፡ ግን ትንሹ ልጅ ዛሬ ትልቅ ቢሆንም በሆነ ወሬ ውስጥ ዘሎ ገብቶ ይጀምረዋል፡፡በብዙ መንገድ ሊርቀው እየፈለገ ልጁን ይወደዋል፡፡በተለይ አባቱን ካጣ በኋላ ተቆጣጥሮ የማሳደግ ሀላፊነት እርሱ ላይ ወድቋል፡፡ እዳ እየከፈለ ያለ ይመስለዋል፡፡ አባቱ ስላሳደገው እርሱ ደግሞ ልጁን ተንከባክቦ የማሳደግ ሀላፊነት ላይ ወድቋል፡፡በልሁ የትንሹን ልጅ አባት ማን እንደገደለበት ያውቃል፡፡ መንገር ግን አይፈልግም፤ ሊነግረውም አይገባም፤መንገርም የለበትም፡፡ልጁ ግን ችክ ብሏል‹‹አባቴ ሲሞት አልመጣህም››አለው

‹‹እኔ?››

‹‹አዎ››

‹‹ታስሬ ነበር እኮ››

‹‹ከዛ በፊትም አትመጣም ነበር››

‹‹ከፍለሀገር ሄጄ ነበር››

‹‹ግን ሰዎቹን ለማጣራት አትችልም››

‹‹እነማን››

‹‹የአባቴን ገዳዮች››

‹‹ምን ያደርግልሃል?››

‹‹ለማወቅ››

‹‹አጣራልሃለሁ››

‹‹አባቴ በጥይት ብዙ ቦታ ተበሳስቶ ወንፊት ሆኖ መሞቱን ሰምተሃል?››

‹‹ ይሄን ደግሞ ማን ነገረህ?››

‹‹ሆስፒታል የወሰደው ሰው ነገረኝ››

‹‹ማነው?››

‹‹ያኔ ቀበሌ ከአባቴ ጋር ይሰራ የነበረ ሰው ነው››

‹‹ማንነቱን አታውቀውም እንዴ››

‹‹ወፍጮ ቤት ሀላፊው››

‹‹ቀዩ ሰውዬ!!!››

‹‹እዎ››
‹‹አወቅሁት፤ሌላስ ምን አለህ?››
‹‹ብዙም አልነገረኝም››
‹‹ለምን?››
‹‹ሌላ ቀን እቤቱ ሄጄ ጠይቀዋለሁ››
‹‹ይቅርብህ››
‹‹ማጣራት አለብኝ››
‹‹አንተ ወሬ በስማህ ቁጥር…››
‹‹ግን አሁን የነገርኩህን ታደርጋለህ?››
‹‹ምኑን?››
‹‹ማጣራቱን››
‹‹እዎ ግን….››
‹‹ግን ምን?››
‹‹ላንተ በቀል ጥሩ አይደለም››
‹‹ለምን?››
‹‹ወደፊት ትምህርትና ስራህ ላይ ነው ማተኮር ያለብህ››
‹‹እሱ ችግር የለውም››
‹‹ ወደ በቀል ከገባህ በሰላም አትኖርም እኮ››
‹‹እንዴት››
‹‹ቤተሰብ ትመሰርታለህ፤ ልጆች ይኖራሉ፤ እነርሱ አደጋ ላይ ይወድቃሉ››
‹‹ለዚያ ነገር እንኳን እጠነቀቃለሁ››

ትምህርት ቤት ሁለት ልጆች ያስቸግሩት ነበር። አንድ ቀን በመጥፎ ሁኔታ ደበደቡት። በልሁ ነገሩን ሰምቶ ተናደደ ።ሁለቱንም መንገድ ላይ አግኝቶ ቀጠቀጣቸው። በሌላ ቀን ከትንሹ ልጅ ጋር ማውራት ጀመሩ‹‹አሁን ያስቸግሩሃል እንዴ?››አለው

‹‹ማን?››
‹‹ልጆቹ››
‹‹እረ ይፈሩኛል››
‹‹ለመሆኑ በምንድነው ጸባችሁ››
‹‹ዝም ብሎ ነው››





‹‹ባለፈውም እንዲህ አልከኝ››
‹‹ነው ግን ››
‹‹እኔ እኮ አባትህ ነኝ አትደብቀኝ››
‹‹አውቃለሁ››
‹‹እና››
‹‹የሆነች የሴት ጓደኛ ነበረችኝ››
‹‹ገባኝ ጸቡ በምን እንደሆነ››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ተወው››

ሁለቱም በግልጽ ተወያዩ። ልጅቷን እንደሚወዳት አስረግጦ ነገረው። እሷን ማጣት አይፈልግም። ማንም ሰው በእሷ ቢመጣበት ቀድሞ እንዲነግረው አስረዳው። ግን ደግሞ ከትምህርቱ በፍቅር እንዳይዘናጋ ነገረው። በዚያኑ አመት ጥሩ ውጤት ስላመጣ ስእት ገዛለት።ልጁ እያደገ እየጎረመሰ ሲሄድ በልሁ እየራቀው ነው።ግን ርቆ አልራቀም። የሆነ ነገር እየጎተተው እንደገና አመጣው ።ከልጅነቱ ጀምሮ እንደአባት እያሳደገው ነው። አሁን ግን ልጁ ሀይለኛ አስቸጋሪ ሆኗል ።እናቱ የምትለውንም አይሰማም ።።ግን በልሁን ይፈራዋል። እሱ ባይኖር ዱርዬነቱን አጠናክሮ ትምህርቱን በማቋረጥ ወደ አደገኛ ቀጠና ይሄድ ነበር።ለተወሰነ ቀን ትንሹ ልጅ ስላልመጣ ስጋት አደረበት። ስለምኑም ነገር መከታተል አለበት። በሳምንቱ መጣ‹‹የት ነበርክ ሰሞኑን››

‹‹ላይብራሪ››
‹‹መጽሀፍ ለማንበብ ነው
‹‹እዎ››
‹‹የትምህርት ነው››
‹‹ሌላ››
‹‹ስለምን?››
‹‹ስለኢህአፓ››
‹‹ምን ያደርግልሃል?››
‹‹ለማወቅ››

‹‹ግዜው ጥሩ ስላልነበር ስለዚያ ነገር ማወቅ ምን ያደርግልሃል?››
‹‹ ይሄኛውን ሰዎች ናቸው የሰጡኝ››
‹‹ማናቸው››
‹‹የአባቴ ጓደኛ የነበሩ››
‹‹ለምን ሰጡህ?››
‹‹የአባቴ ስም ስለተጠቀሰ››
‹‹ምን ተብሎ?››
‹‹በኢህአፓ መገደሉን››
‹‹የአንተ አባት ብቻ ነው?››
‹‹አይደለም››
‹‹እና››
‹‹ የብዙ ሰዎች ስም ነው››
‹‹ስለ አባትህ ምን ተጽፏል?››
‹‹መገደሉን ብቻ ነው››
‹‹በቃ እርሳው››
‹‹እንዴት እረሳለሁ››

በተገናኙ ቁጥር ስለአባቱ ሳያነሳበት አያልፍም፡፡ትንሹ ልጅ እንደርሱ አባታቸው ከሞተባቸው ሁለት ልጆች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ ስለአባቶቻቸው ገዳዮች እንደሚወያዩ በልሁ ደረሰበት ፡፡አሁን ትልቅ ክትትል ማድረግ እንደሚገባው አመነ፡፡ይሄን ነገር ችላ ማለት የለበትም፡፡እነዚህ ልጆች ከአባቶቻቸው ጋር ቀበሌ ይሰሩ የነበሩ ሰዎች ግር ግንኙነት እንደጀመሩ ደርሶበታል ፡፡የተሳሳተ ሰው ጠቋሞዋችው አደጋ ላይ ሊጥሏቸው ይችላሉ፡፡ትክክለኛውን የአባቶቻቸውን ገዳዮች አውቀው ከነገሩዋቸው እነዚህ ሰዎች በቅርብ ስላሉ ቀድመው በልጆቹ ላይ እርምጃ እንደሚወስዱባቸው ያውቃል፡፡ በልሁ ለትንሹ ልጅ ‹‹የአባትህን ገዳይ ብታገኝ ምን ታደርጋለህ?››አለው
‹‹እገለዋለሁ››
‹‹በምን?››
‹‹እሱን ለእኔ ተወው››
‹‹ብትገድለው ትታሰራለህ እኮ››





‹‹ተደብቄ ነው››
‹‹ላትገድለው ትችላለህ››
‹‹እንዴት››
‹‹እሱ ቢገድልህስ፣ ሁለት ጉዳት ነው እኮ››
‹‹እና››
‹‹ይሄን ነገር እርሳው››
‹‹ለምን››
‹‹እኔ እንድትሞትብኝ አልፈልግም፣ እንድትማርና እናትህን እንድትረዳ ፈልጋለሁ››
‹‹እናቴ እኮ ትቀሰቁሰኛለች››
‹‹እንድትበቀል?››
‹‹አይደለም››
‹‹እና››
‹‹ስለአባቴ እያነሳች››
‹‹ታድያ ስለአባትህ መንገር ተበቀለው ማለት ነው እንዴ››
‹‹አሟሟቱንና በደም ጨቅይቶ ማየቷን ስትነግረኝ ምን ማድረግ ነው ያለብኝ?››
‹‹እኔ ነግራታለሁ››
‹‹ይሄን እንዳትነግራት››
‹‹የቱን?››
‹‹አሁን በዝርዝር የነገርኩህንና ስለበቀሉ››

በልሁ ሁል ግዜ ሲያገኘው የሚከነክነው ነገር አለ፡፡ግን ምንም ሊያነሳበት አይፈልግም፡፡ ትንሹ ልጅ ባህሪው ሁሉ እንደአባቱ እየሆነ ነው፡፡ ከእናቱ የወረሰው ምንም ነገር የለም፡፡ቁመቱ ፣መልኩ፣ አረማመዱ፣ አነጋገሩና ግልፍተኝነቱ ሳይቀር አባቱን ይመስላል፡፡ ከእሱ ጋር ሲከራር ከአባቱ ጋር የሚያወራ ነው የሚመስለው፡፡ አንዳንድ ግዜ ሳይታሰብ ሲገናኙ ድንግጥ የሚያደርገው ነገር አለ፡፡ ሲያጠፋ ይቆጣዋል እንጂ አይቀጣውም፡፡አንድ ቀን ብቻ ነው በጥፊ የመታው‹‹ለምን መታኸኝ?››አለው
‹‹እየተበላሸክ ነው››
‹‹አባቴ እኮ መትቶኝ አያውቅም››
‹‹እኔ ግን ቀጣሃለሁ››

ከመታው በኋላ በጣም ተጸጸተ። እንደሚወደው ያውቃል ። ድንገት ስለተናደደ ነው የመታው።ከመታው በኋላ እልሁና ግልፍተኝነቱ ሲመለከት አባቱን የመታው ነው የመሰለው። ትንሽ ቆይቶ ትንሹ ልጅ‹‹ቅዳሜ ቤት እንዳትቀር››አለው

‹‹ለምን?››

‹‹የአባቴ ሙት አመት ነው››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ዘንድሮ አመቱ ይከበራል››

‹‹ከዚህ በፊት ይከበር ነበር እንዴ?››

‹‹አይደለም››

‹‹እና››

‹‹ዘንድሮ 20ኛ አመት ስለሆነ ነው››

በልሁ ቅዳሜ ወደ ቤት ሄደ። ከዚህ በፊት በሁለትና በሶስት ወር ነው ብቅ የሚለው። ብዙ ግዜ በልሁ ቤት ወይም ስራ ቦታ ነው ከልጁ ጋር የሚገናኙት።አሁን ግን ለሙት አመት ተብሎ ሲመጣ ግር አለው። የእንቱ ፎቶ በትልቁ ታጥቦ ሳሎን ተቀምጧል።በልሁና እንቱ ፊት ለፊት ተያዩ። እንቱ ‹‹በልሁ!!!››አለው

‹‹አቤት እንቴ›››

‹‹ምን ታደርጋለህ እዚህ ቤት?››

‹‹አንተ ስለሌለህ›.....›

‹‹እና››

‹‹ልጅህን ማሳደግ አለብኝ››

‹‹ልትገድለው ነው ልታሳድገው?››

‹‹ላሳድገው››

‹‹እኔ አላምንህም፤ቤተሰቤን....››

‹‹እንቴ ሙት የልጅህን ነገር ለኔ ተወው››

‹‹ደግሞም......››

‹‹ደግሞም ምን

‹‹ማን እንደገደለኝ ለባለቤቴ ንገሪያታለሁ››

‹‹የት?››

‹‹ሆኪም ቤት መጥታ››





ከፎቶ ጋር ብዙ ተወቃቀሱ። በልሁ ስሜቱ ጥሩ ስላልሆነ ምክንያት ፈጥሮ ቶሎ ለመሄድ ፈለገ። ሚስቱ ግን እንዲቆይ እየነገረችው ነው።ሁለቱም ማውራት ጀመሩ።‹‹እንዴት አስታውስሽ ለማክበር ፈለግሽ?››አላት

‹‹እሱ ነው››

‹‹ማን ››

‹‹ወንዱ ልጄ››

‹‹ለምን?››

‹‹መከበር አለበት ብሎ አስቸገረ››

‹‹ግን አንች ትዳር ለምን አትይዥም?››

‹‹ልጄ ነዋ››

‹‹እና››

‹‹ትዳር ይዞ ቤቱን ሲለቅ እኔም አስብበታለሁ››

‹‹ተነጋግራችኋል››

‹‹እሱ አባቱን በጣም ስለሚወድ ትዳር እንድይዝ አይፈልግም››

‹‹በእርግጥ የአባቱ ነገር አይሆንለትም››

‹‹ሁሌም እንደጨቀጨቀኝ ነው››

‹‹ስለምን?››

‹‹ስለማንነቱ ፤ስለስራው፤በተለይ.....››

‹‹በተለይ ምን?››

‹‹ስለ አሟሟቱ››

‹‹ምን ያደርግለታል?››

‹‹እኔ አላውቅም ››

‹‹ግን አንድ ነገር ልጠይቅሽ?››

‹‹ምን?››

‹‹ከመሞቱ በፊት አይተሽው ነበር?››

‹‹አዎ››

‹‹የት?››

‹‹ሆስፒታል››

‹‹አናግሮሽ ነበር?››

‹‹የተወሰነ...››

ከዚህ በኋላ ርቆ መሄድ አልፈለገም:: ጥያቄውን እዚህ ጋር ማቆም አለበት።ስታወራ በጥልቅ አተኩሮ ይመለከታት ነበር።ፊቷ ላይ የነበረውን ስሜት ለማጥናት ሞከረ:: ከባሏ ጋር እንደማይዋደዱ ያውቃል:: ብዙ ግዜ ይደበድባት ነበር:: ተጣልተውም ከቤት አባሯት ነበር።ለልጃቿ ስትል በሽማግሌ ለምና ነው የተመለሰችው:: ባል እንድታገባ ሲገፋፋት የነበረውም አጎቱን ከውስጧ አውጥታ አዲስ መንገድ እንድትጀምርም ነው።ሌላ ቀን ግን ሙት አመት ብለው ማክበር እንደሌለባቸው ነግሯት ሄደ:: መንገድ ላይ ብዙ ነገር አሰበ:: ይሄን ቤተሰብ መለየትና መለያየት ነው ያለበት፡ወደራሱ ህይወት ማተኮር ይኖርበታል።በተለይ ትንሹ ልጅ ብዙ ነገር እየወሰደበት ነው:: የጉሮውን ግማሹን ነገር ስለቦጨቀበት አንድ ቦታ ማቆም እንዳለበት ራሱን ማሳመን አለበት።ትንሹ ልጅ ከጎረመሰ በኋላ ከጓደኞቹ ጋር በግሩፕ ተጣልቶ በመታሰሩ ለማስፈታት ብዙ ደክሟል:: ጉዳት ስላደረሰ ካሳ ከፍሎ በሽምግልና ለመጨረስ ጣጣውን አይቷል::

## እንደገና ወደ ኋላ

ወደ ቀበሌው ግቢ የገባው የላንድሮቨር መኪና አንድ ጥግ ላይ እንዳቆመ ወታደሮቹ በፍጥነት ወረዱ:: መሳርያ ታጥቀዋል:: ደግሞም ተጣድፈዋል።ሹፌሩ ጮክ ብሎ‹‹ሻለቃ!!›› አለ

‹‹አቤት››

‹‹ሞተሩን ላጥፋው?››

‹‹እንዳታጠፋው››

‹‹ቤንዚኑን ይጨርሳል እኮ››

‹‹ቶሎ ነው የምንሄደው ››

እዚህ ቀበሌ ወታደሮች በተለየያ ግዜ ይመጣሉ ::ዋና አመጣጣቸው በጣም አስፈላጊና የተመራበት አደገኛውን እስረኛ ለመውሰድ ነው።ከ20 ደቂቃ በፊት ከደርግ ጽህፈት ቤት ተደውሎ ወታደሮች እንደሚመጡና ስማቸው የተጠቀሱት እስረኞችን በአስቸኳይ እንዲልኩ መልክእት ተላልፎላቸው ነበር:: ወታደሮቹ እዛ ግቢ በመጡ ግዜ ለማረጋገጥ በሚል የቀበሌው ሊቀመንበር ስልክ





ለመደወል እጀታውን አነሳ:: ለግዜው ስልኩ አይሰራም:: ደጋግሞ ሞከረ።ስልኩ ከጥቂት ደቂቃ በፊት እየሰራ አሁን ጸጥ ስላለበት ግራ ተጋብቷል:: ሊቀመንበሩ ችግር ካለ እንዲደውል ከደርግ ጽህፈት ቤት ቅድም የተሰጠው ስልክ ነበር::

አሁንም ስልኩ እንቢ አለው።ወታደሮቹ ወደ ግቢ በገቡበት ሰአት አንድ ሰው ከግቢው በጀርባ በኩል ባለው የስልክ እንጨት ላይ ወጥቶ የሚሰራውን ማንም ልብ አላለውም! አልተመለከተውም:: ሻለቃው ከሰው ጋር በር ላይ ቆሞ እያወራ ነበር:: ሹፌሩ በድጋሚ ‹‹ሻለቃ!!››አለ

‹‹አቤት››

‹‹እንፍጠን እንጂ››

‹‹ምን አልክ?

‹‹ሰአት የለምን እኮ››

‹‹ይገባኛል ቶሎ እንሄዳለን››

ወታደሮቹ ተጣድፈዋል:: ሻለቃው ከቀበሌው ዋና ጸሀፊ ጋር እያወራ ነው‹‹አሁን ስንመጣ ችግር ነበር ››አለ

‹‹የት?››

‹‹መንገድ ላይ ››

‹‹ምንድነው?››

‹‹ኢህአፓ መንገድ ዘግታ እስረኛ ልታስመልጥ.....››

‹‹እና››

‹‹ድራሿን አጠፋናት››

‹‹እነርሱ እኮ....››

‹‹ግን አንድ ጓዳችን ሳይገደል አይቀርም››

‹‹ማለት ››

‹‹በጥይት ተመትቶ ሆስፒታል አስገብተውታል ››

‹‹ከእናንተ ላይ ነው ሊያስመልጡ የፈለጉት?››

‹‹ሌሎች ጓዶቻችን ይዘው ሲሄዱ እኛ አጃቢ ነበርን››

‹‹እና››

‹‹እነርሱ አሁን ተፈላጊውን ሰው ወስደውታል::››

‹‹አሳስመሰጡማ!!››
‹‹አዎ ››
‹‹የታባታቸው››
‹‹አሁን እኛ ከዚህ ቶሎ ይዘን መሄድ አለብን››
‹‹እነማንን ነው የምትወስዱት?››
‹‹ቅድም ተደውሎላችሁ ነበር አይደል››
‹‹ለእኛ?››
‹‹አዎ››
‹‹አላውቅም››
‹‹ሊቀመንበሩ አንተ ነህ?››
‹‹አይደለሁም ››
‹‹ማነው ?››
‹‹ውስጥ ነው››

ወታደሮቹና ጸሀፊው ወደ ውስጥ ተያይዘው ገቡ፣ ሰዎቹ ተጣድፈዋል። ደግሞም በቅድሙ ተከስ ነው መሰል ተደናብረዋል። ወደ ሰውዬው እየተመለከቱ ‹‹አንተ ነህ ሊቀመንበሩ?››አሉ
‹‹አዎ››
‹‹እኔ ሻለቃ በትሩ እባላለሁ››
‹‹ስምህ ቅድም ተነግሮኛል››
‹‹የታሉ ልጆቹ››
‹‹እነማን››
‹‹የምንወስዳቸው እስረኞች››
‹‹ውስጥ ናቸው››
‹‹ተዘጋጅተው ይጠብቁችኋል ተብለን ነበር››
‹‹እስረኛ አውጥተን በር ላይ አናስቀምጥም››
‹‹ይገባናል ቢሆንስ ስለምንቸኩል ሰአት ለመቆጠብ እዚሁ በር ማድረግ ትችሉ ነበር››
‹‹ይቅርታ አድርጉልንና ግን....››
‹‹ግን ምን?››
‹‹እንደገና ማረጋገጥ እንፈልግ ነበር››
‹‹የትን? ››





‹‹ደርግ ጽፈት ቤት››
‹‹ደውልና አረጋግጥ ››
‹‹ስልክ እምቢ አለን››
‹‹እሱ የእናንተ ችግር ነው፤ ካልሰጣችሁን››
‹‹ካልሰጠናችሁ ምን? ››
‹‹ትተን እንሄዳለን››
‹‹እንደርሱ ለማለት አይደለም››
‹‹እንዳውም እራሳችሁ አምጡ፤ቢያመልጡ ግን...››
‹‹አንድ ግዜ እንገባ››
‹‹ምን እንገባለን ፤በየቦታው ኢህአፓ ተሰግስጎ እኛን እያስገደሉ››
‹‹እባክህ ያልሆነ ስም አትስጠን››
‹‹እናንተን ማለቴ አይደለም....››

ሻለቃው እምባርቆና አስፈራርቶ ትቶ ወደ መኪናው ሄደ። ሊቀመንበሩ ተከትሉ ሄዶ ይቅርታ ጠየቀው። እስረኞቹን ቶሎ አምጥተው መኪና ላይ ለመጫን አዘጋጁ። ሊቀመንበሩ ‹‹መውሰዳችሁን እዚህ ላይ ትፈርሙ?›› አለ
‹‹ምን አገባን እኛ....››
‹‹ደንቡ ነው››
‹‹እሽ አምጣ››
‹‹ግን በምን እናረጋግጣለን?››
‹‹ምን አያልክ ነው››
‹‹ችግር ካለ ደውሉ ተብለን ነበር››
‹‹መድረሳቸውን ለማወቅ ነው?››
‹‹አዎ››
‹‹ከእናንተ አንድ ሁለት ሰው ይሄድ››
‹‹እሺ››
‹‹ማነው የሚሄደው?››
‹‹ምክትሉና ጸሀፊው››
‹‹መሳርያ እንዳትይዙ ››
‹‹ለምን? ››

‹‹ቤተመንግስት ነው የምንሄደው››
‹‹ምን ችግር አለው››
‹‹ውስጥ አይገባም በዚያ ላይ….››
‹‹በዚያ ላይ ምን?››
‹‹ዘቦቹ ሲቀያየሩ መሳርያችሁን ላታገኙት ትችላላችሁ››
‹‹እንደዚህ ከሆነ ባንሄድ ይሻላል››
‹‹እሱ የእናንተ ምርጫ ነው››

‹‹ለማንኛውም ይሄን ስልክ ያዙ። እኔ የምሰራበት ክፍል ነው። እስከ 5 ሰአት ወደውል ትችላላችሁ›› በሚል ሻለቃው ስልኩን ሰጥቶ ሶስቱን እስረኞች ይዘው ሄዱ።ከመሄዳቸው በፊት የቀበሌው ሰዎች ግራ ስለተጋቡ ለማንኛውም አንድ የአብዮት ጥበቃ ሰው አብሮ እንዲሄድ አደረጉ።ሰውየው በጣም ገራፊና በእስረኞች የተነከሰ ነበር። በሽራ የተሸፈነችው ላንደሮቨር ተንቀሳቀሰች ።እስረኞቹና ሶስቱ ወታደሮች እንዲሁም አብዮት ጥበቃው ከኋላ ሽራውን ገልጠው ወደ ውስጥ ገቡ።መኪናው ከቀበሌው ሁለት ኪሎ ሜትር እንደራቀ የአብዮት ጠባቂው‹‹ወደየት ነው የምንሄደው?››አለ

‹‹ወደ ደርግ ጽፈት ቤት››
‹‹መንገዱን የተሳሳታችሁ መሰለኝ››
‹‹አልተሳሳትንም››
‹‹ይሄ እኮ ወደ ሌላ ቦታ የሚወስድ ነው››
‹‹አንድ ነገር ታውቃለህ?››
‹‹ምን››
‹‹እኛ እነዚህን እስረኞች እንደምንወስድ ኢህአፓ መረጃ ሊኖራት ይችላል››
‹‹እና››
‹‹ዋናው መንገድ ላይ ለማስመለጥ ትጠብቀናለች››
‹‹እንደዚህ ነው!!!››
‹‹እኛም ከእነርሱ የባስን ብልሆች ነን››
‹‹በዚህ መንገድ አልገባኝም ነበር››
‹‹ባላሰቡበት መንገድ መሄድ አለብን››





‹‹ጥሩ ዘዴ ነው››
‹‹በስፈር ጉራንጉር አድርገን እንደርሳለን››

ወታደሮቹ መሳርያቸውን እስረኞቹ ላይ እንደደገኑ ነው። እጃቸውን ቢታሰሩም አያምኗቸውም። አንደኛው ወታደር ከፊት ለፊቱ ያለውን እስረኛ‹‹ምናለ ብትተውት››አለ

‹‹ምኑን?››
‹‹ግድያውን››
‹‹እኔ ምንም አላደረግሁም››
‹‹ከጥፋታችሁ የባሰው ደግሞ መካዳችሁ ነው››
‹‹ማለት››
‹‹ድርጅታችሁ ከስሮ ለባዶ አላማ ትሞታላችሁ››
‹‹እኔ…››(ዝምታ)
‹‹ለምን እንደተጠራችሁ ታውቃላችሁ?››
‹‹አናውቅም››
‹‹እርምጃ ሊወሰድባችሁ ነው››
‹‹ምንም ሳናደርግ››
‹‹የሰው ህይወት ከማጥፋት በላይ ምን ልታደርጉ ፈለጋችሁ››

ልጆቹ በወታደሩ ንግግር ተቆጡ። እልህ ፊታቸው ላይ ይነበባል ።አንደኛው ልጅ ወታደሩ ላይ ተፋበት።‹‹ፋሽስት ነህ›› ብሎ ሰደበው። ወታደሩ ግን ያሁኑን ንግግር በቁጣ ደገመው። የአብዮት ጥበቃው መሀል ገብቶ ለወታደሩ ‹‹ተዋቸው››አለ

‹‹ምን አልክ?››
‹‹እነዚህ ደረቆች ናቸው፤ ምንም አያምኑም››
‹‹እዛ ሲደርስ ልክ ይገባል››
‹‹እዚህም እኮ እስኪበቃቸው ተገርፈዋል››
‹‹ጥሩ ገራፊ አለ እንዴ እናንተ ጋ››
‹‹አዎ፤እኔም ስቃያቸውን አሳይቻቸው ነበር፤ ግን ምንም አያምኑም››
‹‹ጎድ!!አንተም ገራፊ ነህ እንዴ?››
‹‹አዎ››

‹‹ስልጥነሃል››

‹‹15 ቀን ሚሊተሪዎች አስተምረውናል››

‹‹ግን ደርግ ጽፈት ቤት እንዲህ አይደለም››

‹‹እዛ የተለያ መግረፊያ አለ እንዴ?››

‹‹አዎ››

‹‹ባየው ጥሩ ነው››

‹‹ከፈለግህ እነርሱን እዛ እናስገባና እናሳይሃለን››

‹‹ደስ ይላል››

‹‹ዝም ብሎ ግርፍያ መሰለህ››

‹‹እና››

‹‹እንደስጋ ነው የሚሰቀሉት››

‹‹እንዴት?››

‹‹ስጋ ቤት ሽንጥ እንዴት እንደሚንጠለጠል አይተሃል››

‹‹አዎ››

‹‹እንደርሱ ሰውየው በጋንች ተንጠልጥሎ ነው የሚገረፈው››

‹‹መሆን ያለበት እንደዚህ ነው››

‹‹ለማንኛውም ፍታቸው››

‹‹ምኑን?››

‹‹ካቴናውን ››

‹‹ይሻላል?››

‹‹አዎ››

‹‹ከተፈቱ እኮ ችግር ይፈጥራሉ››

‹‹መሳርያ እኮ ነው የያዝነው››

የአብዮት ጥበቃው በያዘው ቁልፍ ካቴናውን ፈታላቸው። የሶስተኛውን ፈትቶ እንደጨረሰ ገና ቀና ሳይል ከፊት ለፊቱ ያለው ወታደር በግንባሩ ጥይት ለቀቀበት። እስረኞቹ ግራ ተጋቡ። ደነበሩ፤ ተደናገጡ፤ ተርበተበቱ። ወታደሩ አንዱን እስረኛ በኰድ ስሙ‹‹ጣሰው ነው የምትባለው አይደል?››አለው

‹‹አዎ››

‹‹ሁለቱ ካንተ ጋር ይሆናሉ››

‹‹ማለት››





‹‹አንድ መደበቂያ ቤት እናደርሳችኋለን››

‹‹የት ነው?››

‹‹ቅርብ ነው››

‹‹እና››

‹‹ትእዛዝ ይመጣልሃል››

‹‹ዛሬ ነው?››

‹‹አዎ ኮድ ይሰጥሃል››

‹‹እሺ››

‹‹ትእዛዝ ግን አክብሩ››

‹‹ግድ የለም፤ግን....››

‹‹ግን ምን?››

‹‹የምንረዳችሁ ነገር አለ?››

‹‹እኛን ከዚህ በኋላ አታገኙንም››

‹‹በቃ!!››

‹‹አታውቁንም አናውቃችሁም››

‹‹ገባኝ››

‹‹ይሄን ሰውዬ ግን.....››

‹‹የቱ ?››

‹‹ይሄ ሬሳ››

‹‹ምን ሆነ?››

‹‹ይሄን ያህል ጥሩ እድል ማግኘት አልነበረበትም››

‹‹እንዴት?››

‹‹ተሰቃይቶ መሞት ነበረበት››

‹‹ለምን?››

‹‹በነፍሳችን ነው የተጫወተው››

‹‹ኢህአፓ እንደደርግ አያሰቃይም ቶሎ መሸኘት ነው››

‹‹እናንተ ግን.....››

‹‹እኛ ግን ምን?››

‹‹እኛንም....አሳሳታችሁን››

‹‹እንዴት?››

‹‹ትክክለኛ ወታደር ነው የምትመስሉት››

‹‹ተው እንጂ!!!››

‹‹በተለይ ሻለቃ ፤አስር አለቃ ስትባባሉ…››

‹‹ምን ይደረግ››

‹‹እኛ በቃ አለቀልን ብለን ነበር››

‹‹እንዴት?››

‹‹በትክክል ወታደር ሆናችሁ ደርግ ጽፈት ቤት እንደምንሄድ….››

‹‹ቢጋንች እንደ ስጋ ልትንጠለጠሉ….››

‹‹ብዙ ነገር እያሰብን ነበር››

‹‹ሰው ያለቀኑ አይሞትም ይሄ አብዮት ጥበቃ  ግን ቀኑ ዛሬ ሆነ››

‹‹እውነት ነው፡፡

‹‹ግን….››

‹‹ግን ምን?››

‹‹ተፋህብኝ እኮ››

‹‹ከዚያም ሊብስ ነበር ››

‹‹ምን?››

‹‹እንደተፈታን እየተጠቃቀስን ነበር››

‹‹ምን ለማድረግ?››

‹‹ትንሽ ቆይተን ተናንቀን ግብግብ ለመግጠም››

‹‹ይሄማ ጨዋታውን አበላሽታችሁት ነበር››

‹‹ሻለቃ››

‹‹አቤት››

‹‹አንድ ነገር ልጠይቅህ?››

‹‹ምን››

‹‹ይሄ ማዕረግህ››

‹‹የቱ››

‹‹ያደረግከው››

‹‹እና››

‹‹የሻለቃ ሳይሆን የሻምበል ማእረግ ነው››

‹‹ነው እንዴ››





‹‹አዎ››

‹‹እንዴት አወቅክ?››

‹‹ከሚሊተሪ ቤት ከድቼ እኮ ነው ኢህአፓን የተቀላቀልኩት››

‹‹ማእረጌን ሻምበል በሚል አስተካክለዋለሁ

‹‹እንደርሱ ቢሆን ጥሩ ነው››

ወታደሮቹ ሶስቱን ልጆች አውርደው ዛሬውን የሚጨርሱት ስራ ስላለ በፍጥነት ወደ ሌላ ቦታ ሄዱ፡፡አንድ ሰው መንገድ ላይ ተቀላቀላቸው፡፡ቅድም ቀበሌ በገቡ ግዜ በንሮ መስመር የሚያልፈውን ስልክ እንጨት ላይ ወጥቶ ገመዱን የቆረጠውና ስልኩን ያቋረጠው እሱ ነው፡፡ሁሉም ተያይዘው  ወደ አንድ ቦታ ሄዱ፡፡የሚፈልጉበት ቦታ ደረሱ፡፡ይሄም የቀበሌ ጽፈት ቤት ነው፡፡በሩ ላይ ያለው ወጣት ወታደሮቹን እያናገረ ነው‹‹ምን ነበር?››አለ

‹‹በእፈላማ የታሰሩት ከብቶች ፈልገን ነው››

‹‹ከብቶቹ የሉም››

‹‹የት ሄዱ?››

‹‹ወጥተዋል››

‹‹ማን አለ?››

‹‹እረኛቸው አለ››

‹‹የት ነው?››

‹‹ውስጥ ነው››

‹‹ብቻውን ነው››

‹‹አንድ ሰው አለ››

‹‹ስንት ቁጥር?››

‹‹አራት››

ሹፌሩና ሁለቱ ወታደሮቹ ወደ ውስጥ ገቡ፡፡ አራት ቁጥር የተጻፈበትን ቢሮ አገኙት፡፡ ጽሁፉን ተመለከቱት ‹‹የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር›› ይላል፡፡ ሹፌሩ ይሄን ነገር በጣም ይፈልገው ነበር፡፡ቤቱ ከሌሎቹ ቢሮ ገንጠል ያለና ፊቱን በተቃራኒ ያዞረ ነበር፡፡በር ላይ ያለው ወጣት እዚሁ ቀበሌ የሚሰራ የኢህአፓ አባል ነው፡፡አሙቺውን ሰአት አይቶ ነው የቀጠራቸው፡፡ ሹፌሩ ለሁለቱ ወታደሮች

ሊቀመንበሩን ለእሱ መስጠት እንዳለባቸውና ሌላው ላይ እነርሱ እንዲያተኩሩ አሳስቧቸዋል።ወታደር ተብዬዎቹ በቀዳዳ ተመለከቱና በሩን በርግደው ገቡ። ስብሰባ ላይ ያሉት ሶስቱ ሰዎች ደነገጡ። እንደገቡ ነው የደገኑባቸው ።ሊቀመንበሩ ደንግጦ‹‹በልሁ !!››አለ

‹‹እቤት አጎቴ!!!››

‹‹ምን እያደረግክ ነው››

‹‹ምን ላደርግ የመጣሁ ይመስልሃል››

‹‹ልትገለኝ ነው?››

‹‹አንተ ነህ እንጅ ቀድመህ የገደልከኝ››

‹‹እኔ?!!››

‹‹አዎ››

‹‹እረ እኔ.....!!!!!››

‹‹በእኔና በሁለት ጓደኞቼ የፈረምክበትን ወረቀት ልስጥህ?››

‹‹እኔ አይደለሁም››

‹‹ፈርመሃል እኮ››

‹‹አሁን ልትገድለኝ ነው?››

‹‹ለምን የመጣሁ ይመስልሃል››

‹‹ስጋህ እኮ ነኝ››

‹‹ዝም በል!!!!!!!››

‹‹እኔ አሳድጌህ››

‹‹ጉዳዩ የእኔ አይደለም››

‹‹ማለት ››

‹‹ድርጅቱ ነው የወሰነው››

‹‹አንተ ኢህአፓ ነህ እንዴ?››

‹‹በሊስት ላይ ማን ብለህ ነው የመዘገብከኝ››

‹‹በአባትህ ይገፍሃለሁ››

ይሄን አባባሉን አሟልቶ ለመናገር አላስጨረሰውም። የያዘውን ጥይት ግንባሩን ብሎ ቀሪውን ሰውነቱ ላይ አርከፈከፈበት። አብረው የነበሩትን ሌሎቹ ሰዎች ወታደሮቹ ደግነውባቸው ስለነበር በልሁ አጎቱ ላይ ሲተኩስ እነርሱም ረሽነው ቶሎ ወጡ። ተኩስ የሰሙ ሰዎች ወደ ቦታው መጥተው ነበር። ነገር ግን ገዳዮቹን





አልደረሱባቸውም። እዛ የነበሩት የኢህአፓ አባላት የሄዱበትን አቅጣጫ የተሳሳተ መረጃ ስለሰጡ እነርሱን የሚከተላቸው አልነበረም።

የበልሁ አጎት እዚህ ቀበሌ ብዙ የኢህአፓ አባላት አስይዞ አስገርፏል። እንዲረሸኑም አድርጓል። ከእዚህ አልፎ ከአጎራባች ቀበሌ እያሳደነ አምጥቶ አሳራቸውን በማሳየት የሚታወቅ ነው። ኢህአፓ ከአንድም ሁለቴ አስጠንቅቃዋለች። ሰውየው ግን ጭራሽ ማሳደዱን ቀጠለ። መጨረሻ የወንድሙን ልጅ የጥቃት መዝገብ ውስጥ አስገባው። ያን ግዜ በልሁ እንዲበቀል ተነገረው።ከጥቂት ግዜ በኋላ ሶስቱ ጓደኞቹ የወታደር ልብስ ለብሰው ሌላ ቀበሌ እስረኛ ለማስፈታት ሲገቡ ተደርሶባቸው ተገደሉ። በልሁ ግን አልነበረም ።በሌላ ቀን በቴዎድሮስ ግድያ ተጠርጥሮ ታሰረ።

## እንደገና ወደ ኋላ

በቀበሌው ጽፈት ቤት ኢህአፓን ለመመንጠር በተደረገው ስብሰባ የአብዮት ጥበቃው ሊቀመንበር አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ የሚታሰሩና ርምጃ የሚወሰድባቸውን ዝርዝር እያቀረበ ነው። ለወትሮው የቀበሌው ህዝብ ደህንነት አባል ባለበት ነበር የሚያቀርበው፡ ነገር ግን የህዝብ ደህንነት አባሉ ከሶስት ቀን በፊት ተገደለ።ገዳዮቹ እነማን እንደሆኑ አይታወቁም። በጥርጣሬ የተያዙ ሰዎች አሉ።አሁን ርምጃ ለመውሰድ የተዘጋጁት ለበቀል ነው።እርምጃው አፋጣኝ መሆን እንዳለበት ተነግሯል። ይሄንን ግድያ የሚያቀነባብረውና የሚያስፈጽመው የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበሩ ነው። ሊቀመንበሩ ስብሰባው ላይ ሰዎች እርምጃ እንደሚወሰድባቸውና የት እንደሚመቱ እያብራራ ነው‹‹3 ሰዎች ናቸው የሚመቱት ››አለ

‹‹እነማን ናቸው?››

‹‹ታመነ››

‹‹እሸ››

‹‹በልሁ››

‹‹ቀጥል››

‹‹ገዛኸኝ››

‹‹እሱማ ዋነኛው ነው››

ከመሀላቸው አንደኛው ሰርጎ የገባ ኢህአፓ መሆኑን ሳያውቁም፣ ፡ሌሎችም መጨመር አለባቸው ብሎ ሲከራከር ነበር፡፡ የበልሁ ግን በደምብ መጣራት እንዳለበት አስረዳ፡፡ ግን ከሲቀመንበሩ ያገኘው ምላሽ ጥሩ ስላልነበር መከራከር አልፈለገም፡፡ሲቀመንበሩ የወንድሙን ልጅ እንዲገደል አዘዘ፡፡ በአስቸኳይ ድርጅቱ ለበልሁና ለሌሎች ገዳዮች በተደበቁበት ቦታ የበለጠ እንዲደበቁና እንዳይንቀሳቀሱ ተነገራቸው፡፡ እነዚህ ተደባቂ ወጣቶች አንድ ጠንካራ ቡድን ሰርተው ሀይለኛ ስኳድ ወጣቸው፡፡በሌላ ቀበሌ ሄደው የእግር ኳስ ግጥሚያ ያደርጉ ነበር፡፡ አሁን ግን ተሸሸጉ፡፡ይሄ የስኳድ ቡድን የወታደር ልብስ አድርገው እስረኛ በማስፈታት በመሳርያ ዘረፋ ላይ ተሰማሩ፡፡ አጎቱንና አንድ የህዝብ ደህንነት አባል እንዲገደሉ ኢንተር ዞን ኮሚቴ ወሰነ፡፡ ግድያውን የነበልሁ ቡድን እንዲፈጽም ታዘዘ፡፡አጎቱን ለምን እንደገደለ ሲያስታውስ‹‹....ግዜው የመጨካከን ወቅት ነው፡፡እኛ ራሳችን እየተከላከልን ነው፡፡ ቀበሌው ውስጥ ሁለት ሰዎች አስቸገሩ፡፡ ጓደቻችንን እየለቀሙ አሰሩ፡፡ ገሚሱን ገደሉ፡፡ ድርጅቱ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ትእዛዝ አስተላለፈ፡፡ ግድያው ለኛ ቡድን መጣ፡፡ የድርጅቱ ትእዛዝ በመሆኑ መፈጸም ነበረብኝ፡፡ እኔ ባላደርገውም ትእዛዝ ስለሆነ ሌላው ስኳድ ይፈጽመዋል፡፡ያን ግዜ ድርጅቱ ካዘዘን ለምን ብለን አንጠይቅም፡፡ አጎቴ እኔ እንድገደል ትእዛዝ አስተላልፏል፡፡ እኔ የቀደምኩት በእኔ ላይ ስለወሰነ አይደለም ድርጅቱ ስላዘዘኝ ነው››ይላል

## እንደገና የሆነ ቀን

ከዩንቨርስቲ የሚመረቀው ተማሪ እንደ አባቱ ሆኖ ያሳደገውን ሰው ለማመስገን ቃላት አጥሮታል፡፡ ለምረቃ የሚሆነው ሱፍ ልብስ ያሰራለት እርሱ ነው፡፡በልሁ አንድም ቀን እንዲህ ያማረና ሰውነትን የሚሞላ ሱፍ ልብስ ኖሮት አያውቅም፡፡ትንሹ ልጅ ‹‹እንዴት አድርጌ እንደማመሰግንህ አላውቅም››አለ

‹‹እኔ ነኝ የማመሰግንህ››

‹‹ለምን?››

‹‹ምክሬን ሰምተህ ትምህርት ላይ ማተኮርህ››





‹‹መማር ነበረብኝ እኮ››

‹‹እነኛ ዱርዬ ጓደኞችህ ጋር ተቀላቅለህ አስቸግረህ ነበር››

‹‹እሱ ልክ ነህ በግዜ መለስከኝ››

‹‹እናትህንም አመስግናት››

‹‹ያንተ ይበልጣል››

‹‹እንዴት? ››

‹‹አባቴ ሞቶ ሳትስለች...››

‹‹አደራ ስላለብኝ ነው››

‹‹የማን?››

‹‹የአባትህ››

‹‹ነግሮህ ነበር››

‹‹በህይወት እያለ አንድ ነገር ብሆን ልጄን እንደአባት ተንከባከብ ነው ያለኝ››

‹‹እንደሚሞት ያውቅ ነበር?››

‹‹ግዜው እኮ አስቸጋሪ ነበር››

‹‹አባቴ እንዴት እንደተገደለ ሰማሁ››

‹‹ማን ነገረህ››

‹‹የቀበለው ዘበኛ የነበሩት ለእናቴ ሲናገሩ አዳመጥኩ››

‹‹የሰው ወሬ አትስማ››

‹‹አንድ ቀን የአባቴን ገዳይ እንደሌሎቹ ሳልበቀል....››

‹‹እኔም የአባትህን ገዳይ ባገኝ አለቀውም››

ከ20 አመት በፊት ትንሹ ልጅ ወደ አሜሪካ አቀና፡፡ በልሁም አንድ እግሩ እዚህ አንድ እግሩ አውሮፓ አድርጓል፡፡ ከዚያ በኋላ ተገናኝተው አያውቁም፡፡፡

## ምእራፍ 3

### የጎበዝ አለቃ

የፋብሪካው ሰራተኞች ወደ ስራ ለመግባት እያመነቱ ነው፡፡ አንዳንዱ ፍቃድወስዶ ቀርቷል፡፡ ሌላው ደግሞ ፍቃድ ከወሰደ በኋላ ከከተማው ለቆ ሄዷል፡፡ ሱማሌ ጅጅጋ ገብታለች ስለተባለ በጥቂት ግዜ ውስጥ ድሬዳዋ ላይ ትከሰታለች፡፡ የትኛውን ቦታ እንደምትመታና እንደምታፈራርስ እየተነገረ በመሆኑ የጨርቃ ጨርቅ (ኮተኒ)ፋብሪካ ዋናው ታርጌት መሆኑ ብዙዎቹ ሰግተዋል፡፡ ፋብሪካው ከ7 ሽህ በላይ ሰራተኛ የሚያንቀሳቅስ ነው፡፡ይሄ ደግሞ በሀገሪቱ ፋብሪካ ታሪክ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ነው፡፡ ይሄ ፋብሪካ ተዘጋ ወይም በሱማሌ ታንክና መድፍ ተመታ ማለት በሀገሪቱ ምርት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ የሚያደርስ ነው፡፡ የሱማሌ እየገሰገሰ መምጣት ደግሞ ለድሬዳዋ ብቻ ሳይሆን ለአዲስ አበባም ሆነ ለናዝሬት ከፍተኛ ጉዳት የሚያመጣ ነው፡

የሱማሌ ጦር ድሬዳዋ ገብቶ አውሮፕላን ሜዳውን ከተቆጣጣረ ትልቅ ችግር ይፈጥራል፡፡ አውሮፕላኖቻቸው ቤዛቸውን ድሬዳዋ አደረጉ ማለት ከዚህ እየተነሱ አዲስ አበባን በአውሮፕላን በመቀጥቀጥ ዋና ከተማውን ለማፈራረስ አቅም ይፈጥራሉ፡፡ እናም ዋናው ነገር የድሬዳዋ አየር ሀይልና አውሮፕላን ሜዳዎች ናቸው፡፡ የከተማው ሰው የጎበዝ አለቃ እየመረጠ ተደራጅቶ ህጻናት አሮጊትና ሽማግሌዎችን ከከተማው እያራቀ ነው፡፡ ብዙ ሰው ዱላ እንጅ መሳርያ የለውም፡፡ መሳርያ እንኳን ለነዋሪው ለሰራዊቱም በበቂ ሁኔታ የለም፡፡ ዛሬ ወይም ነገ ሱማሌ ወደ ድሬ ስለሚገባ ሁሉም ምን ይፈጠር ይሆን? በሚል ሰግቷል፡፡ እንደገና እዚሁ ከተማ ሌላ ተጋጣሚዎች አሉ፡፡

በየቦታው የደርግ ደህንነትና አብዮት ጥበቃ ጨምሮ ከኢህአፓ ጋር እየተታኮሱ በመጋደል ላይ ናቸው፡፡ ከኮተን ፋብሪካ ኢህአፓ ናቸው ተብለው ተወስደው የታሰሩ የተገደሉ አሉ፡፡ ሀሙስ እለት ወደ





ፋብሪካው የገቡት ደህንነቶች ግቢውን ከበቡት፡፡ ጥበቃው ላይ የነበረውን ሰው ‹‹ሀይሉን አይተሃል?››አለው

‹‹የቱ ሀይሉ‹‹

‹‹ማሽን ላይ የሚሰራው››

‹‹ይሄ ረጅሙ››

‹‹አይደለም››

‹‹እና››

‹‹አጠር ያለው››

‹‹እኔ አሁን ስመጣ አይቼዋለሁ››

‹‹ስራ ላይ ነው?››

‹‹አይደለም››

‹‹እና ››

‹‹ወደ ክበብ ነበር የሄደው››

ሰዎቹ ወዲያውኑ ወደ ክበብ ሄዱ፡፡ ቦታውን ከበቡ ነገር ግን ሀይሉ እየተመለከታቸው ነበር፡፡ እሱ መጀመርያም ክበብ አልነበረም፡፡ ጥበቃው አካባቢ የነበረው ሰው የኢህአፓ አባል ስለሆነ ሊያስመልጠው ነው፡፡ ከግቢው በመውጣት ላይ እንዳለ አንድ ሰው ተመለከተው ‹‹ሀይሉ››አለው

‹‹አቤት(በዝግታ)

‹‹የት እየሄድክ ነው?››

‹‹መጣሁ(በምልክት)

‹‹አሁን ፈልጌህ ነው››

‹‹ቶሎ እመለሳለሁ››

ሀይሉ ፈጠን እያለ ወደ በሩ ሄደ፡፡ ግን ሰወዬው ለብርቱ ጉዳይ እየፈለገው ስለነበር ‹‹ሀይሉ!!!!››ብሎ ተጣራ፡፡ ይሄኔ በየቦታው ለመፈለግ የተሰማሩት ሰዎች ይሄን ስም ከፍ ብሎ ሲጠራ ሰሙት ፡፡ ያን ግዜ ሀይሉን ተመለከቱ፡፡ እየሮጡ ወደ እርሱ ሄዱ ፡፡እሱም በፈጣን ርምጃ በሩን አለፈና መሮጥ ጀመረ፡፡ በር ላይ የነበሩት ዘበኞች ብዙዎቹ ተደናግጠው አብዮት ጥበቃዎቹን ለመተባበር ተዘጋጁ፡፡ ግን ተፈላጊው ሰው ከግቢው ርቋል፡፡ ዋናው አስፓልት ይዞ

ሄደ። አሁን ቁርጡ ታወቀና መታከስ ተጀመረ። አሳደው ያዙት…ምን ፈለጋችሁ ነው?››አለ

‹‹አታመልጠንም››

‹‹ምን እያላችሁ ነው››

‹‹ግድያ ላይ ተሳትፈህ…..››

‹‹እረ እኔ ሰላማዊ ነኝ››

‹‹ይሄን መሳርያ ይዘህ እንዴት ሰላማዊ ነኝ ትላለህ ?››

‹‹መሳርያውን ሰው ነው ያስታጠቀኝ››

‹‹እኮ ማነው ያስታጠቀህ?››

‹‹እኔን?››

‹‹አዎ፤ እንድትገድል የላኩህ ናቸው አይደል ያስታጠቁህ?››

‹‹አዎ››

‹‹እኛም የፈለግንህ ማን አስታጥቆ ለግድያ እንዳሰማራ እንድትነግረን ነው››

‹‹እነማን እንደሆኑ ነግራችኋለሁ››

‹‹አሁን እንሂድ ቀጥል››

‹‹የት?››

‹‹ ያስታጠቁህ ሰዎች ጋር››

‹‹እሺ››

‹‹የት ናቸው?››

‹‹ሰፈር ናቸው››

‹‹ለመሆኑ እነማን ናቸው?››

‹‹እነባሻ ናቸው››

‹‹ባሻ ጡረተኛው?››

‹‹አዎ››

‹‹እሳቸው ኢህአፓ ናቸው እንዴ››

‹‹እረ!! አይደሉም ።እሳቸው በሰፈራችን የጎበዝ አለቃ ሆነው ተመርጠዋል››

‹‹አሁን አንተን ያስታጠቁህ በትክክል እነማን ናቸው››

‹‹የሰፈር ሰዎች››

‹‹እንዴት አስታጠቁህ››





‹‹ሱማሌ ወደ ከተማው ልትገባ ስለሆነ አካባቢን ለመጠበቅ ነው››

‹‹እነርሱ ሱማሌን ለመውጋት አስታጠቁህ፤ አንተ ግን ቢህአፓነትህ እየተጠቀምክበት ነው››

‹‹ተሳስታችኋል››

‹‹ታድያ ለምን አመለጥክ?››

‹‹የሱማሌ ሰርጎ ገብ ፋብሪካ ውስጥ አሉ››

‹‹እና››

‹‹እኛን የህዝብ ሰዎች እየመረጡ እያስገደሉን ነው››

‹‹ታድያ ለምን ትሸሻለህ?››

‹‹እነርሱን መስላችሁኝ ነው››

‹‹እኛ?››

‹‹አዎ አሁንም የመንግስት ሰዎች ናችሁ ብዬ ስለማላምን……››

‹‹ተው እንጂ!!!››

‹‹እርግጠኛ ነኝ ሰርጎ ገብ ሱማሌ ናችሁ››

ሰዎች እየተሰበሰቡ መጡ። አብዮት ጥበቃዎቹ ግራ ተጋቡ። ሰርጎ ገብ ናችሁ ከተባለ ለእነርሱም ጥሩ እንደማይሆን አውቀውታል። እናም አሁን የያዙት ሰው ቀንደኛ ኢህአፓ እንደሆነ ነው። ደግሞም እየሸሸ ያለው ከሱማሌ ሰርጎ ገቦች ከሆነ እኛ ተሳስተናል ወደሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ። መሳርያውን ነጠቁና እንዲሄድ አደረጉት። ግን እሱ ‹‹መሳርያዬን አምጡ››አለ

‹‹እኛ ጋር ይቆያል››

‹‹በምን ልዋጋ ነው?››

‹‹ይሄ ባይኖርህስ››

‹‹እንደሌላው በእጠና ወይም ባገኘሁት ነገር እታገላለሁ››

‹‹በቃ አጠና ፈልግ››

‹‹ይሄ እኮ የሰዎቹ ነው››

‹‹የማን?››

‹‹የጎበዝ አለቆቹ››

‹‹ግን እነርሱ ከየት አመጡ?››

‹‹ብዙዎቹ ወታደሮች ናቸው››
‹‹እነርሱ ነው የሰጡህ?››
‹‹አዎ ሄደን ማረጋገጥ ትችላላችሁ››

ለማረጋገጥ መንገድ ጀመሩ ነገር ግን ሌላ ስራ ስላለባቸው አምነውት ይሁን ተሰላችተው መሳርያውን ሰጥተው ሸኙት፡፡ ነገር ግን ምሽት ላይ እሱ ላይ ያነጣጠረውን የደህንነቱን ሰው ወደ ቤቱ ሲገባ ገደለው፡፡ በእርግጥም ሀይሉ ዋናው ሰኳድ ነበር፡፡ በነጋታው ማን እንዳደረገ ተደረሰበት፡፡ ሀይሉ ከመስርያ ቤቱ ከሀገሩም ተሰወረ፡፡ ከፋብሪካ ውስጥ ጥብቃዎችን ሳይቀር ሌሎች ሰዎች ታፈሱ፡፡





## ምእራፍ 4

### የቁራው ሰው

ከኮልፌ አውቶብስ ተራ ለመድረስ መንገዱ ረዘመባት፡፡ ውስጧ ያለው ነገር ሊዘረገፍ ትንሽ ቀርቶታል፡፡ ይሄ ከመሆኑ በፊት ሰፈሯ መድረስ አለባት፡፡ ከማስመሰስ በማይተናነስ ሁኔታ እየታገላትና እየተናነቃት ነው፡፡ ነገሩ ዝርግፍ ብሎ ሊወጣ ከውስጧ እየገፈተራት ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ነገር ደግሞ ሰፈሯ ውስጥ መከሰት የለበትም፡፡ አሁን ሰፈሯ ደርሳ አቋራጩን ይዛ ወደ ቤት ለመድረስ እየገሰገሰች ነው፡፡ እየተናነቃት ያለው ነገር እዚህ ሰፈር ውስጥ ተዘርግፎ መውጣት የለበትም፡፡ ‹ልዘረገፍ ነው እና አትዘረገፍም ትንሽ ታገስ› በሚል ሁኔታ ትግል ላይ ናቸው፡፡ በህይወቷ እንዲህ አይነት ነገር ገጥሟት ስለማያውቅ የሚታገላትን ነገር ለማቆም ተቸግራለች፡፡ እንደምንም ብላ እቤት እንደደረሰች የአጥሩን በር በርግዳ ገብታ ወደ ቤት ውስጥ ዘለቀች፡፡ ወደሳሎኑ እንደገባች መሬት ላይ ወድቃ ‹‹ወይኔ ወንድሜ!!! ወንድሜ!!!››እያለች ማልቀስ ጀመረች፡፡ ወድቃም ዝም አላለችም፡፡ እየተሽከረከረች በመንከባለል ‹‹ወንደሜ፤ ብቸኛው ወንድሜ!!!!›› እያለች ሰው ባይኖርም ለያዥ ለገላጋይ በሚመስል ሁኔታ ተንፈራፈረች፡፡ ወንድሟ መሞቱን ካወቀች ሰአት ጀምሮ ለማልቀስምንም አጋጣሚ አላገኘችም፡፡ ላልቅስ ብትልም ችግር ውስጥ ትገባለች፡፡ ፋንቱ(ስሟ የተቀየረ) የወንድሟ ሞት እንደ እግር እሳት እየለበለባት ነው፡፡ነገሩ ሲጀመር እንዲህ ነበር፡፡

ወታደራዊ መንግስትን ካስቸገሩትና ካጨናነቁት ቦታዎች ዋናዎቹ መርካቶ፤ አውቶብስ ተራና ሰባተኛ አካባቢ ነበሩ፡፡ በአካባቢው ብዙ ሰው የሚንቀሳቀስ ስለነበር ለቁጥጥርም አስቸጋሪ ከመሆኑ ሌላ ለኢህአፓ ጥሩ መሸሸጊያ ነበር፡፡ ከየቦታው የተሳደዱ አባላት መደበቂያቸው እዚሁ መርካቶ ነው፡፡መሸሸግ ብቻ ሳይሆን ጥቃት የሚፈጽሙትም ከዚሁ ቦታ ተነስተው ነው፡፡በህዳር 1969 አካባቢ የኢህአፓ እንቅስቃሴ በአካባቢው በጣም የተጠናከረበት ግዜ በመሆኑ

ይሄን ጥንካሬያቸውን ለመበታተንና ሁሉን ነገር በእጁ ለማስገባት የሚሟሟትበት ግዜ ነበር፡፡በዚሁ ወር የኢህአፓን እንቅስቃሴ ለመበታተን ትልቅ እርምጃ ለመውሰድ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ወቅቱ ደርግ የቀን፤ ምሽት ደግሞ ኢህአፓ ነበሩ አካባቢውን የሚያስተዳድሩት፡፡ ግድያዎች በሁለቱም በኩል ነበሩ፡፡

ደርግ ቦታዎችን ለመቆጣጠር የመጨረሻ ርምጃ መውሰድ ጀምሯል፡፡በዚሁ ወር አጋማሽ ብዙ አብዮተኞች እየተገደሉ ነበር፡፡ ለዚሁ ምላሽ ለመስጠት የአብዮት ጥበቃዎችና የአካባቢው ህዝብ ደህንነት ታጣቂዎች የመልስ ምት እየሰጡ ነው፡፡ረቡእ ጠዋት ስራቸውን በካባዱ ጀምረዋል፡፡ ምሽት ከየሰፈሩ ያፈሷቸውን ወጣቶች አውቶብስ ተራ አምጥተው በሌሊት ረሸኗቸው፡፡ሬሳዎቹ በተለምዶ እስከ 4 እና ግፋ ካለ እስከ 5 ሰአት እዛው እንደተሰጡ ያቆዩዋቸዋል፡፡ ከዚያ በኋላ አንስተው በጅምላ ይቀብሯቸዋል፡፡

ሬሳዎቹ ከመነሳታቸው በፊት እንደተዘረጉ በአካባቢ የሚተላለፈውን መንገደኛ ሰብስበው መፈክር እንዲያሰሙና ኢህአፓን እንዲያወግዙ ያደርጓቸዋል፡፡ ይሄን ሁሉ የሚያደርጉት ህዝቡ እንደተቀበላቸው ለማሳየት ነው፡፡ እዚያ ቦታ መጥተው መፈክር የሚያሰሙት ሰዎች እዛ ጋር የወደቁትን ሰዎች በአብዛኛው ያውቋቸዋል፡፡ አንዳንዴም ቤተሰብ ሳይቀር አምጥተው ያስፎክሯቸዋል፡፡

የከፍተኛ ስድስት የኪነት ቡድን በስሩ ባሉት ቀበሌዎች ያቋቋማቸው የኪነት ቡድኖች በየቦታው እየተጠሩ አብዮታዊና ቀስቃሽ ዜማ በማሰማት ተጠምደዋል፡፡ የኪነት ቡድን ሰባተኛ አካባቢ የቅስቀሳ ዜማዎችን አሰምቶ በቀጣዩ ወደተጠራበት ወደ ኮልፌ ሲያመራ አውቶብስ ተራ አካባቢ እንዲቆሙ ተደረገ፡፡የህዝብ ደህንነት ካድሬው የኪነት ቡድኑ ከጭነት መኪናው ላይ እንዲወርዱ አዘዙ፡፡ወደሬሳዎቹ ጋር እንዲመጡ ተደረገ ፡፡እንዲህ አይነቱ ነገር አዲስ አይደለም፡፡ አልፎ አልፎ ይደረጋል፡፡እነርሱም ለምን ወደ ሬሳዎቹ ጋር እንደተጠሩ አውቀውታል፡፡ካድሬው የቀበሌያቸው ፈላጭ ቆራጭ ነው፡፡እናም ትእዛዙ የተከበረ ነው፡፡ሬሳዎቹ ጋር ተሰብስበው መፈክር የሚያሰሙት ሰዎች ቦታዎችን ከፊት እንዲያደርጉ ተነገራቸው፡ከሬሳዎቹ ፊት





በነበረው ሰፊ ቦታ የኪነት ቡድኑ‹‹ወዮልሽ ኢህአፓ…መጨረሻሽ ሞት ነው….እንዲህ መዘርጋት ነው……ወዮልሽ ኢህአፓ ከአፈር ተደባለቅሽ………››እያሉ ይዘምራሉ፤ ያቅራራሉ፤ ይፎክራሉ፡፡ የተሰበሰበው ሰውም ከእነርሱ ጋር ያቅራራል፡፡

ከፊት ሆነው አብዮታዊ መዝሙር ከሚያሰሙት አንዷ በደምብ እየተውረገረገች ታቅራራለች፡፡ እንደገናም ትዘምራለች፡፡፡እየዘመረች በጥግ ካለው ሬሳ አጠገብ የሚገኘውን ልጅ አየችው፡፡እስካሁን እንዴት እንዳላየችው አስደንቋታል፡፡በርግጥ እነዚህ ሁለት ሬሳዎች ከሌሎቹ ከስድስቱ ተገንጥለው ራቅ ብለው የተጋደሙ ናቸው፡፡አብላጫው ሰው የሚመለከተው ስድስቱን ነው፡፡ልጅቱ አይኗን ከስድስቱ ላይ ነቅላ እየተወረገረገች ወደሁለቱ ተመለከተች፡፡እየተመለከተች ድንገት ቀጥ አለች፡፡መሬቱ ተሰንጥቆ ቢውጣት በመረጠች ነበር፡፡ወንድሟ ነው፡፡ ወዲያው ነው ያወቀችው፡፡ሬሳው በደረቱ ነው የተደፋው፡፡እንኳን እሷ ማንም ሰው ሊለየው ይችላል፡፡ያደረገው ጃኬት የተለየ ነው፡፡ወጣቱ ይሄን ጃኬት ከሁለት አመት በላይ ለብሶታል፡፡እንኳን እንዲህ ከቅርብ ቀርቶ ከርቀትም ቢሆን እሱነቱን የአካባቢው ሰው በልብሱ ለይቶ ያውቀዋል፡፡

ፋንቱ እስክስታ እየወረደች ነው ሬሳውን ያየችው፡፡ በጣም ደነገጠች፡፡ ልትጮህ ምንም አልቀራት፡፡ እዛው ባለችበት ሁሉም ነገር ጠፋባት፡፡ መዝሙሩ በህብረት የሚሰራ በመሆኑ ባያጋልጣትም እንደዞረባት ጨረሰችው፡፡ ደግነቱ ወዲያው አጠናቀው ወደ ኮልፌ አመሩ፡፡ ወንደሟን አንድቀን እንደሚገዱሉት ታውቅ ነበር፡፡እናም ያቀን ዛሬ ሆነ፡፡

ፋንቱ ከኮልፌ እንደተመለሰች አሁንም መሬት ወድቃ መንከባለሏን ቀጥላለች፡፡ ውስጧ ሲታገላት ታምቆ የነበረው የልቅሶ ሁኔታ ብትንከባለልም ሊወጣላት አልቻለም፡፡ ድምጽዋን ከፍ አድርጋ ‹‹ወይኔ ወንድሜ!!!!››በሚል እያለቀሰች ሳለ ሰራተኛቸው ከኩሽና በቅ ብላ እየተንከባለለች እሪ የምትለዋን የቤቱን ዋናዋን ልጅ ተመለከተች፡፡ ወድቃ መንከባለሏን ስታይ ግራ ተጋብታ እየተጣደፈች ከመሬት እያነሳቻት ‹‹ምን ሆንሽ …..ምንሆንሽ!!!!!!››አለቻት

‹‹ምንም››

‹‹ታድያ እንዲህ ወድቀሽ ለምን ታለቅሻለሽ?››
‹‹ዘረፉኝ››
‹‹ምን አልሽ››
‹‹ብሬን ዘረፉኝ››
‹‹ማነው››
‹‹ሌቦች››

ወይኔ ብሬ....ወይኔ ገንዘቤ!!!!ስንት ያጠራቀምኩትን ብር እንዲህ በሌባ ልዘረፍ!!አብዮቱ ሌባን እንኳን አያጠፋልንም? ወይኔ ብሬ!!!››እያለች ስታለቅስ ሰራተኛዋ ከመሬት ጎትታ አንስታ ወንበር ላይ እያስቀመጠቻት ‹‹ስንት ብር ነውየወሰዱብሽ?››አለቻት

‹‹100 ብር››
‹‹100 ብር?
‹‹እዎ››
‹‹100 ብር እንዴት ትይዣለሽ?››
‹‹50 ብሩ የእኔ ነው፤ሌላው ጓደኞቼያስቀመጡት ነው››
‹‹100ብር ሙሉ ወሰዱብሽ?››
‹‹እዎ፤ወይኔ ብሬ!!!!››
‹‹የት አካባቢ ነው?››
‹‹ኮልፌ አውቶብስ ውስጥ ሆኜ ነው››
‹‹100ብር!!!!!!!!!ወይ ጉድ!!!!››
‹‹ወይኔ ብሬ!!››
‹‹አይዞሽ››
‹‹ምን አይዞሽ ትይኛለሽ››
‹‹ምንልበል ታድያ››
‹‹ይሄ ሁሉ እንዴት ይወስዱብኛል››
‹‹ሌቦቹን አይተሻቸዋል?››
‹‹ተዘናግቼ ነበር፤ስወርድ ነው መወሰዱን ያውቅሁት››
‹‹የት ጋር ነበር ያደረግሽው?››
‹‹በሱሪው የኋላ ኪስ ነው››
‹‹እንዴት እዛ አደረግሽው?››
‹‹ከፊት ያለው ኪስ ቀዳዳ ነበር››





‹‹ሁሉንም ይዘሽ መሄድሽ ስህተት ነው››
‹‹ወይኔ ብሬ!!!አንድ ነገር በይን እንጂ››
‹‹ምን ልበልሽ››
‹‹አንቺማ ምንም አይሰማሽም››
‹‹ምን ላድርግ?››
‹‹ምንም አታለቅሽም?››
‹‹ባለቅስ ምን አመጣለሁ፤ይልቅስ በመልክ ካወቅሻቸው እዛው ኮልፌ እንሂድ››
‹‹አሁንማ እዛ ምን ይሰራሉ?››
‹‹ታድያ ምን ይደረግ››
‹‹ወይኔ ብሬ!!››

እንደገና መሬት ወድቃ መንከባለል ጀመረች።ሰራተኛዋ ግራ ተጋባች። ከወደቀችበት ብታነሳትም ተመልሳ መሬት ትዘረገፋለች ‹‹ወይኔ ወንድሜ.....ወይኔ ብሬ›› እያለች እያፈራረቀች ታለቅሳለች ።ድንገት ለቅሶዋን ገታ አድርጋ ‹‹እማዬ የት ነው ያለችው?››አለች

‹‹እትዬ እንትና ቤት ሄደዋል››(ስማቸውን ነገረቻት)
‹‹የት?››
‹‹መንገድ ተሻግሮ ያለው ቤት››
‹‹ምን ታደርጋለች?››
‹‹ለቅሶ ለመድረስ መሰለኝ››
‹‹ነግራሻለች?››
‹‹አይደለም ከጎረቤታችን ሴትዮ ጋር ሲያወሩ ሰምቼ ነው››

አሁንም ከመሬት አልተነሳችም።ሰራተኛዋ አንስታ ወንበር ላይ ስታደርጋት እየተንሸራተተች መሬት ትነካና ቁጭ ብላ እንደገናም መሬት ተኝታ ታለቅሳለች። እናትየዋ ለቅሶ ቤት መሄዷን ሰራተኛዋ ማወቋ ደስ አላላትም። እናትየዋና ጎረቤቷ ማውራታቸውን ተንጠራርታ ወይም ተደብቃ መስማቷን እያረጋገጠች ነው። የዚህች ሰራተኛ ወንድም እዚሁ ቀበሌ አብዮት ጥበቃ ነው።ይህችን የቤት ሰራተኛ ከቤት አባረዋት ትልቅ ጣጣ ነው ያመጣባቸው ።የአብዮቱ ደጋፊ ሆና የፊውዳል አፍቃሪ በሆኑ አሰሪዎች ነው የተባረረችው በሚል 3 ብር ደሞዝ አስጨምራ ችግር ልትፈጥርብን ነው በሚል

ወደ ቤት ሰራተኛነት ተመልሳለች። ሰፈሩ ውስጥ መረጃ በማቀበል ትታወቃለች። ሁለት ወጣቶች ከተደበቁበት የተያዙትም በእርሷ ጥቆማ መሆኑን እውቀዋል። ቤት ውስጥ ዘመድ ሲመጣ አሳፊ ንግግር እንዳያደርግ መንግስትን የሚቃወም ምንም ነገር እንዳይተነፍስ በቅድሚያ ተነግሮት ነው ወደ ቤት የሚገባው። እሷም በፈቃዷ ሰቃ አትሄድም እነርሱም አይሸኟትም። ምግብ ስታቀርብ ወይም እዛው ሳሉን ቡና ስታፈላ አብዮቱን የሚደግፍ ወሬ ብቻ ነው የሚያወሩት። እሷ ወደ ኩሽና ስትሄድ በሹክሹክታ ነው አብዮቱን ቡጭቅ የሚያደርጉት።

የቤቱ ዋናዋ ልጅ ፋንቱ አብዮቱን ተቀብላ በቀበሌው ኪነት ውስጥ ስለምትሳተፍ ትንሽ የቤቱን ነገር ባላንስ እያደረገች ይመስላል። በቤት ሰራተኛቸው የተነሳ ቀበሌው በአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበሩ ትልቅ ማስጠንቀቂያ ስለተሰጣቸው በራሷ ፍቃድ ትታ እስካልሄደች ድረስ መሰናበት ቀርቶ በርበሬ እንዴት አለቀ? ቅቤ የት ሄደ? ብለው እንኳን መጠየቅ አይችሉም። የአብዮት ጥበቃው ወንድሟ ከሁለት ባልደረቦቹ ጋር እቤት መጥቶ በጥሩ ሁኔታ የተሰራ ምሳ በልቶ ሲሄድ ቤተሰቡ ዝም ነው ያለው። እነርሱ ቤት የመጡት አብዮታዊ እህታችን ያለችበትን ሁኔታ ለመመልከት ነው በሚል ነበር።

አሁን ፋንቱ በሰራተኛቸው ፊት በኢህአፓነት ለተገደለው ወንድሟ ማልቀስ ከባድ ዋጋ እንደሚያስከፍላት አውቃለች።በዚያ ላይ እሷ የቀበሌው ኪነት አባል ነች። ኪነቱ አብዮታዊ ውዝዋዜ በማቅረብ ነው የሚታወቀው። ማንነቷ ተበርዟል መጣራት አለበት በሚል እየተገመገመች ሳለ ለወንድሟ ስታለቅስ ብትገኝ ሰርጎ ገብ ኢህአፓ ነች በሚል እንደምትታሰርና ርምጃም እንደሚወሰድባት ታውቃለች። ሰራተኛቸው ለአብዮቱ የቆመች በመሆኗ አሳልፋ እንደምትሰጣት አይጠፋትም። እናም በእርሷ ፊት ስለወንድሟ ማልቀስ የሚከተለውን ስለምታውቅ ድንገት የፈጠረችውን የገንዘቡን ጉዳይ አጠናክራ ይዛለች፡ ሰራተኛዋ ወደ ውስጥ ገባ ብላ እስክትመለስ ‹‹ወይኔ ወንድሜ!!!›› እያለች እፈራርቃ ታነፈርቃለች።እንደገናም ሰራተኛዋ ባለችበት ‹ወይኔ ብሬን› ድምጿን ከፍ አድርጋ ትለዋለች። በውስጥ ደግሞ ‹‹ወይኔ ወንድሜ!!! የሚለውን እያፈራረቀች ነው።ፋንቱ ሰራተኛዋን ትኩር ብላ





ተመለከተቻት። የሆነ ነገር ጠርጥራለች ድንገት ቆጣ ብላ ‹‹አንቺ›› አለቻት

‹‹አቤት››
‹‹አንቺ ነሽ አይደል ያስገደልሽው?››
‹‹ማንን?››
‹‹ወንድሜን››
‹‹የት?››
‹‹እዛ ሜዳ ላይ ገድለው ጥለውታል››
‹‹ሞተ እንዴ?››
‹‹እም!!!››
‹‹ወይኔ ወንድሜ››
‹‹ዝም በይ››
‹‹ምነው››
‹‹ደግሞ ስታለቅሽ አታፍሪም እንዴ››
‹‹ለምን››
‹‹አንቺ ነሽ ጠቋመሽ ወንድሜንና ጓደኞቹ የተገደሉት››
‹‹እረ ተይ እንዴት እኔ አስገድለዋለሁ››
‹‹ድሮም አትወጅም አስበላሽው››

ለመናገር የፈለገችው ይሄንን ነበር። ግን የሚመጣው የመጨረሻ መልስ እጨራረሱ እሷንም እንደሚያስጨርሳት አልጠፋትም። እናም ቶሎ ብላ ለመናገር ያሰበችውን ዋጠችና ‹‹አንቺ››አለቻት

‹‹አቤት››
‹‹ብቃ ዝም ትያለሽ?››
‹‹ምን ልበል››
‹‹100ብር እኮ ነው የጠፋብኝ››

‹‹ወይኔ ብሬ!!!!›› እንደገናም በውስጧ ‹‹ወይኔ ወንድሜ!!!››እያለች ሰራተኛዋ እስክትሄድላት እየጠበቀች ነው ።እሷ ግን ለማስተዛዘን ቆማ እያባበለቻት ነው። ያልጠፋው ብር እንዴት እንደሚገኝ እየተመካከሩ ነው።አሁንም ውስጧ ያለውን መንጨርጨር አውጥታ ማልቀስ ፈልጋለች። የወንድሟ ነገር እንዲህ በቀዘቀዘ ስሜት

ውስጥ ማሳለፍ የለባትም። ትዝ ሲላት አንድ ሀሳብ መጣላት ።እናቷ ለቅሶ ቤት መሄዷን ሰራተኛዋ ነግራታለች። እዛ ሄዳ በደምብ ማልቀስ ትችላለች። እዚህ ከቆየች አምልጧት ወይኔ ወንድሜ ማለቷ አይቀርም። እንዲህ ከሆነ ጉዷ ነው። ይሄ ከመሆኑ በፊት መሄድ አለባት።በቤቷ ማልቀስ ያለመቻሏ አናደዳት።‹‹ሰው እንዴት በቤቱ ሀዘኑን አይገልጽም››?በሚል ተናደደች።

ሰራተኛዋ ከፊቷ እስከትሄድላት እየተናነቃት ነበር።ሲቃዋና ስቅስቅታዋ እየመጣባት ነው። ለቅሶ ቤት ሄዳ በደምብ ልትለቀው ፈልጋለች። አሁን ለቅሶዋ በብሩ ሳይሆን በወንድሟ መሆኑን ትንሽ ፍንጭ ከታየባት አስቸጋሪ እንደሚሆን ታውቃለች። ወንድሟ መሞቱን ሰራተኛዋ ካወቀች‹‹ጸረ አብዮተኞችን በመደገፍ እርር ብላ እያለቀሰች ነው›› በሚል ለአብዮት ጥበቃ ወንድሟ ትነግረዋለች። ያን ግዜ ሰርጎ ገብ ናት በሚል ኢላማ ውስጥ ትገባለች። ኢህአፓ ተብሎ ለተገደለ ሰው ሀዘንን ለመግለጽ ቀርቶ ጥቁር ልብስ እንኳን በማይደረግበት ግዜ እንዲሁ እየተብከነከኑ ሬሳውን መንገድ ላይ እያዩ ዝም ከማለት በስተቀር አማራጭ ባልነበረበት ግዜ ይህች ለአብዮቱ ሙያዋን የሰጠች የቀበሌው ኪነት ተወዛዋዥ የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ አይነት ሆኖባታል።

ሰራተኛዋ ፊት ጉዷ ከሚወጣ ለመሄድ ተዘጋጀች ‹‹ወይኔ ብሬ›› ብላ አምባረቀች።‹‹ወይኔ ወንድሜ!!›› የሚለውን ውስጥ ለውስጥ እያለችው ነው። ድንገት ከቤት ስትወጣ ሰራተኛዋ ‹‹የት ልትሄጂ ነው?››አለቻት

‹‹እዚህ ቁጭ ብዬ ምን አደርጋለሁ››

‹‹ምሳ እንኳን አትበይም?››

‹‹ቀልደኛ ነሽ››

‹‹እንዴት››

‹‹ብሬ ጠፍቶ ምሳ በላለሁ››

‹‹እሽ ትንሽ አረፍ በይ››

‹‹መሄድ አለብኝ››

‹‹የት ነው የምትሄጅው?››

‹‹ጓደኞቼ ጋር››





‹‹ምን ታደርጊያለሽ?››

‹‹ልነግራቸው ነዋ››

‹‹ብሩ መጥፋቱን››

‹‹አዎ፤ግማሹ የእነርሱ እኮ ነው››

‹‹በኋላ አትነግሪያቸውም››

‹‹በትኩሱ ነው እንጂ ዘግይቶማ ምን ያደርጋል››

ከቤት ወጥታ የታችኛውን አቋራጭ ይዛ በፍጥነት ተራመደች። መሄድ ያለባት የላይኛውን አቋራጭ ይዛ መሆን ነበረበት። ነገር ግን ሰራተኛዋ ከበር ወጥታ እያየቻት ስለነበር ነው ቁልቁል የወረደችው። እርግጥ ነው ጓደኞቿ ያሉት አሁን በምትሄድበት መንገድ አቅጣጫ ነው። እርሷ ግን በትክክል መሄድ የፈለገችው እናቷ ሄደች ወደተባለበት ለቅሶ ቤት ነበር። እዛ ማንም አያግዳትም። ለሟቹ አስመስላ ለወንድሟ በደምብ ታለቅሳለች።አንደኛውን አቋራጭ ጨርሳ ሁለተኛው መንገድ ውስጥ ገብታ ነው ጓደኞቿ ቤት የምትደርሰው። ነገር ግን አንደኛውን አቋራጭእንደጨረሰች በሌላ በኩል አድርጋ እንደገና ወደ ላይ ተመለሰች። እየተመለሰች አንድ ሀሳብ መጣላት። ጓደኞቿ ወደቤት ሲመጡ ሰራተኛቸው ልትጠይቃቸው ትችላለች። ወሬኛ ነገር ስለሆነች ሁሌም ጨዋታዋ አንድ ነገር በማውጣጣት ላይ ያተኮረ ነው። ስለዚህ እንደገና ተመልሳ ወደ ጓደኞቿ ሄደች። ፊቷ እንደበለዘ እህቷን አገኘቻት‹‹ምን ሆንሽ?››አለች

‹‹ምን ሆንኩ››

‹‹አይንሽ ቀልቷል አልቅሰሻል››

‹‹ብሩ ጠፋ››

‹‹የቱ ?››

‹‹እኔ ጋር ያለው››

‹‹መቼ ?››

‹‹ዛሬ ››

ጓደኛዋ አዘነች። ከእነርሱ ይልቅ የእሷ 50 ብር ከባድ እንደሆነ አውቃለች። አብራት ማልቀስ ጀመረች ‹‹አይዞሽ ነገ ገንዘቡ ይገኛል››አለቻት

‹‹በጣም የሚያናድድ እኮ ነው››

‹‹ግን ለገንዘቡ ነው ይሄ ሁሉ ያለቀስሽው?››
‹‹አዎ ደግሞ ተጣላሁ››
‹‹ከማን?››
‹‹ከእንዱ››
‹‹መታሽ ››
‹‹አዎ››
‹‹ታውቂዋለሽ››
‹‹በአይን ነው››
‹‹ቀበሌ ንገሪያቸው››
‹‹ስንቱን ነገር ለቀበሌ ነግረሽ ትችያለሽ››

አሁን ያሉበት ክፍል ማንም የለም፡፡ እናትና አባቷ የመንግስት ሰራተኛ ናቸው፡፡እስከ 11 ሰአት አይመጡም፡፡እዚህ የተመቻቸ ቦታ በመሆኑ የተወሰነ ደቂቃ እንኳን ለማለቀስ ትችላለች፡፡ደግሞም ጓደኛዋ በማላቀሱ ከተባበረቻች በደምብ ከውስጧ ሊወጣላት ይችላል፡፡ፋንቱ ‹‹እኔ የምልሽ››አለች

‹‹እሺ››
‹‹እህቶችሽ.....››
‹‹እዚሁ ጎረቤት ናቸው››
‹‹አንድ ነገር ላማክርሽ ፈልጌ ነው››
‹‹ምንድነው››
‹‹ለሰው የሚነገር አይደለም››
‹‹ምንድነው ንገሪኝ››
‹‹እንደምታውቂው ወቅቱ የፈጠረው ነገር...››
‹‹ምን!!!!?››
‹‹ወንድሜን እኮ ገደሉት››
‹‹መቼ!!!?››
‹‹ዛሬ ሌሊት››
‹‹የት ?››
‹‹መንገዱ ዳር››
‹‹ወይኔ!!!! ወይኔ››





እራሷን ይዛ ጮኸች፡፡ ከእሷ የበለጠ እስካቸው፡፡ ግን ደግሞ ቶሎ ዋጥ አደረገችና ተቃቅፈው ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ማልቀስና መላቀስ ጀመሩ‹‹ትላንት እኮ አግኝቸው ነበር››አለቻት

‹‹ማታ እቤት ስላልመጣ ጠርጥሬ ነበር››
‹‹ማን ነገረሽ ሞቱን››
‹‹ጠዋት ከሌሎች ጋር ተገድሎ አየሁት››
‹‹እሱ ብቻነው››
‹‹ምን አልሽ?››

ይህችኛዋ እንደገና ደነበረች፤የእሷም ታላቅ ወንድም ታስሯል፡፡ ከእናቷ ጋር ቁርስ ለማድረስ ጠዋት ሲሄዱ እርሱ አልተቀበላቸውም ፡፡ጓደኛው ነው፡፡ እናትየው‹‹የለም እንዴ?››አሉ

‹‹አሞት ተኝቷል››
‹‹ምን ሆኖ?››
‹‹ሆዱን ነው››

እሁን ግን ይሄን አባባል አልተቀበለችም፡፡ እውነቱን ጓደኞቻቸው አይናገሩም፡፡ በቃ ወንድሟም እንተደገደለ ነው የገመተችው ፡፡አሁን ማልቀስ ያለባት ስለጓደኛዋ ወንድም ሳይሆን ስለራሷም ቤተሰብ መሆን አለበት፡፡ ከቤቷ ገስግሳ የመጣችው ልጅ ጥሩ ማልቀሻ ቦታ ስላገኘች እዚሁ ለመላቀስ ተመቻቸች፡፡ ደግሞም ነገሩ ስታስበው ወንድሟና ይህች ልጅ ይግባባሉ ፡፡መግባባት ብቻ ሳይሆን መንገድ ላይ እየተቀጣጠሩ ሲያወሩ አይታለች፡፡ ፍቅረኛዋ ሊሆን ይችላል፡፡ ለማንኛውም ጥሩ ቦታ ነው ፡፡ከውስጧ ያለውን የታመቀ ነገር አውጥታ ለማልቀስ ጥሩ ስፍራ ነው ፡፡ተመቻችተው ለመላቀስ በተዘጋጁበት ግዜ ትልቋ እህቷ ሰተት ብላ ገባች፡፡አሁን ነገሩ ጥሩ እንደማይሆን ገመተች፡፡ለወንድሟን ሞት ለማልቀስ በየቦታው መንከራተትዋ አንሶ ሌላ ጣጣ ማስከተል አልፈለገችም፡፡ ደግሞም አሁን የገባችው ልጅ ከእርሷ ጋር ጥሩ አይደሉም፡፡ ወሬውን በእንዴ ታራባዋለች፡፡ ግን ማልቀሷ ያስታውቅባታል፡፡ታላቅ እህቷ‹‹ምን ሆና ነው››አለቻት

‹‹ገንዘብ ጠፍቷት ነው››
‹‹መቼ ?››
‹‹ዛሬ››

ሁለቱ ስለጠፋው ገንዘብ ሲያወሩ እሷ አጎንብሳ ‹‹ወይኔ ወንድሜ›› ትላለች፡፡ እዚህ ክፍል በምትፈልገው መልኩ ለማልቀስ ብትመጣም አልሆነም፡፡ ግን አሁንም የሚተናነቃትን ነገር በደምብ አውጥታ መጨረስ ባለመቻሏ ቤቱን ለቃ መሄድ ፈለገች፡፡ የጠፋውን ገንዘብ እንደምትከፍላት ነገረቻት፡፡ ገንዘቧን ብዙ ግዜ ከቤቷ ስትወጣ ኪሷ ነው የምታደርገው፡፡ሰራተኛዋን አታምናትም ፡፡የገንዘቡም መጥፋት አጋናዋለች‹‹ግን ይሄ ለሳቢ ጠፍቶ ቢሆንስ››ብላ በቀሚሷ እጇን አሾልካብሩ መኖሩን አረጋገጠች፡፡

በእርግጥም በህይወት አለ፡፡ ጠፋ የተባለውን ብር ከየቦታው ተበዳድራ እንዳመጣች አድርጋት መልስላቸዋለች፡፡ እቤት ሲመጡ ሰራተኛቸው ስለብሩ መጥፋት ስትጠይቃቸው በእርግጥም እውነት መሆኑን ስለሚያሳምኗት ይሄን ይመሰክራሉ፡፡ የወንድሟ መሞት በቶሎ ላይታወቅ ይችላል ፡፡ ከታወቀም የእዛን ቀን ለቅሶዋ የገንዘቡ መሆኑን ሰራተኛዋ ታምናለች፡፡ እናም አሳልፋ አትሰጣትም፡፡ ይሄን በዚህ ቋጭታ እናቷ ወደምትገኝበት ቦታ መሄድ ጀመረች፡፡ በመንገድ ላይ የወንድሟን አሟሟት እንዴት እንደሆን በአይነህሊናዋ መጣባት፡፡ አወዳደቁን አይታ የት ቦታ ፤እንዴት እንደተኮሱበት፤ ምኑ ቦታ እንደመቱት፤ ህይወቱ እንዴት እንዳለፈ ሀሳቧ ላይ ወደቀ፡፡

ከአስራ አምስት ቀን በፊት በአስቸኳይ መድረክ ላይ የሚቀርብ አብዮታዊ ዜማ ለመለማመድ በቀበሌው አዳራሽ እየተውረገረጉ ሳለ ጩኸትና ግርግር ይሰማሉ፡፡ በተከፈተው መስኮት ሲመለከቱ ታስረው የመጡ እስረኞች መሳርያ ነጥቀው ለማምለጥ ሲታገሉ እዛው አይታለች፡፡በጥይት እየተመቱ እንዴት እንደወደቁና ደጋግመው እዛው በተኙበት በፍጥነት አከታትሉ በሚተፋ ጥይት ሲረሸኑ ተመልክታለች፡፡ ጥይቱ ሰውነታቸውን ወንፊት ነው ያደረገው፡፡ ደማቸው ፈሶ መሬቱን በክሎታል ፡፡የእዛን ቀን የልጆቹን አሟሟትና እየጮሁ እንደወደቁ ለሳምንት ሙሉ ከህሊናዋ አልጠፋ ብሎ ነበር፡፡ አሁን ያንን ፊልም እንደገና ወደ ኋላ አጠነጠነችው፡፡





ፊልሙን ከመጀመርያ አንስቶ ማየት ጀመረች፡፡ የልጆቹ መልክ አልጠፋትም፡፡ በተለይ ከፊት ያለው አንደኛው ልጅ ብዙ ጥይት የተርከፈከፈበት እሱ ነበር፡፡በጣም የገረማት ያ ሁሉ ጥይት ገብቶበት ቶሎ ህይወቱ ያለመውጣቱ ነው፡፡ በወደቀበት ሲወራጭ እንደገና ሌላ ተከታታይ ጥይት እየተተኮሰበት ነበር፡፡ተኩሱ ሲጀመር መስኮቱን ዘግተው በሰፊው ቀዳዳ መመልከት ጀመሩ፡፡ይሄንን ፊልም አጠንጥና ስትመለከት ወንድሟ እዚህ ፊልም ውስጥ ታያት፡፡ከፊት ሆኖ ሲርከፈከፍበት የነበረው ልጅ ወንድሟ እንደሆን አድርጋ ተመለከተች፡ ፡በኢህአፓ ሜቾች ላይ የሚርከፈከፈው ጥይት ተመሳሳይ በመሆኑ የወንድሟ አሟሟት እንዲህ እንደሆን ገመተች፡፡ብዙ ጥይት ሰውነቱ ላይ ተሰግስጎ አልሞት ብሏቸው እንደገና ተጨማሪ ጥይት ሲረጩበት እየተርገበገበ ሲወድቅ በአይነ ህሊናዋ መጣ፡፡

ፋንቱ አሁን ስሜቷን መቋቋም አልቻለችም፡፡ መንገድ ላይ እያለቀሰችና እየነፈረቀች ሄደች፡፡ የወንድሟ ሬሳ በደረቱ ወድቆ ነው ያየችው፡፡ እንዴት ተኩሰው እንደመቱት ተርገፍግፎ ሲወድቅ‹‹እናቴ ድረሺልኝ›› እያለ እየጮኸ በአፍጢሙ ክንብል ሲል ታያት ፡፡ልጆ እያለም አባቱ ሲገርፈው እንዲህ ነበር የሚለው፡፡እናቷ የልጇን መሞት ሳትሰማ የሌላው ለቅሶ ለማድመቅ መሄዷ የወጣቶች ሞት ምን ያህል በከተማው እንደተንሰራፋ የገባት አሁን ነው፡፡ደግሞም እዛ በደረሰች ግዜ እንዴት አድርጋ ነው የወንድሟን መሞት ለእናቷ የምትነግራት፡፡ይሄን ሁሉ እያሰላሰለች የወንድሟን አሟሟት በልቅሶ እያጀበች ፊቷን በሻርፕ ሸፍና ፍጥነቷን ጨምራ እናቷ ትገኝበታለች ወደተባለው ለቅሶ ቤት ደረሰች፡፡ደርሳም ወደ ውስጥ ገባች፡፡አሁን ነጻ ቦታ ስላገኘች በደምብ ማስነካት ነው ያለባት፡፡

እዚህ ግቢ ውስጥ ‹እህህ....›እየተባለ ነው የሚለቀሰው ፡፡ ለሚች ኢህአፓዎች ጮክ ብሎ ለቅሶ ስለማይፈቀድ በእህህ ተጀምሮ በመነፍረቅ ያበቃል፡፡ ሴትዮዋን ታውቃቸዋለች፡፡ ሟቹንም እንደዚሁ፡፡ ለቅሶው ድብቅ ስለሆነ በዋናው ቤት አይለቀስም፡፡ በግቢው በዋናው ስፍራም አይሆንም፡፡ አመቺው ቦታ በግቢው በጓሮ በሚገኘው ቦታ ነው፡፡ ድንገት ያልታሰበ ሰው በዋናው በር እንኳን ቢገባ ለቅሶውን ወደ

ጨዋታ ወይም ወደ ሌላ ነገር ለመቀየር እድል ይገኛል በሚል ነው። እናም ለለቅሶ እመቺ ነው በሚባለው ስፍራ ገብታ ቦታዋን ያዘች ። በአይኗ እናቷን መፈለግ ጀመረች።አላገኘቻትም። ያለውም ሰው ጥቂት በመሆኑ ቶሎ መለየት ችላለች።መኖርያ ቤት ውስጥ ልትሆን ትችላለች ብላ አሰበች።የቤቱን ሰው መጠየቅ ፈለገች። ግን ለግዜው አጠገቧ የመጣ ሰው አልነበረም። የምትጠይቀው ሰው እስከታገኝ ድረስ የወንድሟ እሚሟት ፊቷ ድቅን ስላለባት እንባዋን ለቀቀችው።እዚህ ቤት ውስጥ ሟች ቢኖርም አሁን የራሷን ለቅሶ ነው የያዘችው። ለቅሶውም የሚመራው በራሷ ስሜትና ፍላጎት ነው።እየተብከነከነች ‹‹አንዱና ብቸኛው ወንድሜ ››እያለች ማልቀሷን ተያያዘችው። በርግጥም እነርሱ ቤት ውስጥ ሁለቱ ብቻ ነው ያሉት። ፋንቱ ብቸኛ ወንድሟ በመሆኑ በጣም ነው የምትወደው። ከእንግዲህ ወንድም አይኖራትም። ብቻዋን ጥሏት ነውየሄደው።

በወቅቱ በነበረው የለቅሶ ህግ እህህ..እያለች በውስጧ የተቃጠለ ስሜቷን እያወጣች ታለቅሳለች። እንደገናም እናቷን በአይኗ ትፈልጋለች። ደግሞም ያለችበትን ቦታ የሚነግራት ሰው እያሰሰች ነው።ሁለት ወጣቶች ከፊት ለፊቷ ራቅ ብለው እየተመለከቷት ነው። የቤተሰቡ አባላት ባይሆኑም ዘመድ ናቸው። እነርሱ ግን እንደርሷ ተብከንክነው እያለቀሱ አልነበረም።በእርግጥ ሀዘን ላይ ናቸው።እዚህ ግቢ ውስጥ በአሁን ሰአት እርሷ ብቻ ናት ኮከብ አልቃሽ።እነርሱ ጋር መሄድ አልፈለገችም።እያለቀሰች በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለባት እያወጣች እያወረደች ነው።በለቅሶዋ መሀል አንድ ሰው ከኋላ እጇን ጉተት አደረጋት።ጉተታው ለቅሶውን አቁሚ ወይም ዝም በይ የሚልነው። እሷ ግን ስሜት አልሰጣትም።ከዚህ ጉተታ በፊትም አንድ ሰው መጥቶ ‹‹ቀስ በይ››ብሏታል።እሷ የመጣችው ለእነርሱ ለቅሶ ባለመሆኑ በዚህ ቤት የለቅሶ ህግ አትወሰንም። ማንም ምንም ቢል ለቅሶዋ እስከወሰዳት ድረስ የእህህን ህግ ጠብቃ ብቻ ትሄዳለች እንጂ ለቅሶዋን አታቆምም።

እሷም ብትሆን እስከስንት ሰአት እንደምታለቅስ አልወሰነችም፡ ፡የሚያዩዋት ሰዎች ከሟች ጋር በፍቅር ጓደኝነት እንዳላቸው





አድርገው ገምተዋል። ምክንያቱም ከሁሉም በበለጠ አልቃሽና ተንጨርጫሪዋ እርሷ ነበረችና። ደግሞም አንዳንዱ ግራ ገባው። እርሷ በኪነት በኩል የአብዮቱ ወገን ሆና እንዲህ ማልቀሷ ለማስመሰል እንደመጣች ገምተዋል። ዘመድ፤ ቤተሰብ ፤አልቃሽና ሀዘንተኛ መስለው እየሰለሉ ለቀበሌው ሹሞችና ለአብዮት ጥበቃዎች መረጃ የሚሰጡ አሉ።ይህችም ከነዚህ አስመሳዮች አንዷ እንደምትሆን የሚገምቱም አልጠፉም።ለእሷ ግን ከሌላው ቦታ እዚህ ተመችቷታል። እስካሁን ምንም አልወጣላትም ።ገና ከእናቷ ጋር ለቅሶውን ከፍ አድርጋ ትወስደዋለች።እስከዚያ ለብቻዋ ትወጣዋለች‹‹ወይኔ ወንድሜ!!!!!›› እያለች አሁንም ትብከነከናለች። ለቅሶው በጨመረ ቁጥር ፊቷ ተንሳቁሏል።አብዮቱ ወንድሟን ገድሎበታል።

ከእንግዲህ በጭካኔ ወንድሟን የወሰደባትን አብዮት ማገልገል ሞኝነት ሆኖ ታያት። ግን አብዮቱን ትታ የትም መሄድ አትችልም። ቀበሌ ኪነት ስትገባ ለመዝፈን ብቻ መስሏት ነበር።በኋላግን በየቦታው እየተጠሩ ኢህአፓን ማውገዝ ፤ስለአብዮቱ መዝፈን ፤ቅስቀሳ ማድረግ፤ በኢህአፓ ሬሳ ላይ እየተገኙ ሰውን መቀስቀስና መዝፈን ሆነ።ከዚያም አልፎ በአካባቢያቸው የሚያዩትን ጸረ አብዮት ተግባር ለቀበሌው ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።እየቆየ ሄዶ የስለላ ተግባር እንዲያከናውኑ ተነገራቸው።ይሄ ነገር ሾልኮ ወጥቶ ፋንቱ በአስጠቋሪነት ነው የምታትወቀው። እሷ ግን በዛ ደረጃ ሰው እንደሚገምታት ወይም እንደሚያውቃት አታውቅም። ለዚህ ነው አሁን ፊት ለፊቷ የሚገኙት ሁለት ሀዘንተኛ ወጣቶች በትዝብት የሚመለከቷት። አሁን ግን ከአብዮቱ ካምፕ መውጣት አለባት። ወጥታ ግን የት ነው የምትሄደው? እስከመቼ ነው ለእነርሱ እየቀሰቀሰች የምትዘልቀው?። ይሄው ዛሬ እንኳን በወንድሟ ሬሳ ላይ ቆማ መፈክር እንድታሰማ አድርገዋታል።

ደግሞም ሰሞኑን ጀመሩት። በኢህአፓ ሬሳ ላይ ተጠርተው መንገደኛውን ሰብስበው ‹‹ኢህአፓ ወዮልሽ፤መጨረሻሽ ሞት ነው›› እያሉ ይዘምራሉ፤ መፈክር ያሰማሉ። ወንድሟን ተደፍቶ ያገኘችው በእንዲህ አይነቱ የቅስቀሳ ቦታ ነው። መጨረሻ እሷ ላይ መጥቶ እንደ አይኗ ብሌን የምታየው ወንድሟን ወስደባታል።እናም አንድ የእሷ

ነፍስ ብቻ ነው የቀራት። የቀበሌውን ኪነት በቃኝ ብላ ወሰነች።በዚህ ስአት መቅረቷምን እንደሚስከፍል ገብቷታል። የቀረችው በወንድሟ ሞት የተነሳ ነው ።ስለዚህ በአንድ ኢህአፓ ሞት አብዮቱ ላይ አኮረፈች ተብሎ የሚመጣው ነገር ዋጋ ያስከፍላታል። ‹‹ወይኔ ወንድሜ!!!››አለች።

በዚህ ስአት ግን የሚያላቅሳት ሰው ትፈልጋለች።አሁንም መንስቅስቋን አልተወችም ።ከኋላዋ የሚመጣው ድምጽ ‹‹እረ ዝም በይ›› ቢላትም ግድ አልሰጣትም።ደጋግሞ ስለተናገራት ዞር ብላ በጥፊ ብትለው ደስ ባላት ነበር።የወንድም መሞት ምን ያህል እንደጎዳት ያላወቀ ሰው ነው እንዲህ የሚለው ብላ አሰበች።ምን አልባት ነገ በእሱ ላይ ሲደርስበት በደምብ ያውቀዋል ብላ ወሰነች።አሁንም ከኋላ ድምጹ ስለመጣ ያልከኝን ሰምቻለሁ ከእንግዲህ እንዳትናገረኝ ብላ መልስ ለመስጠት ፈልጋለች ግን ሁኔታው አልተመቻትም።

አሁን ከኋላ ከሚናገሯት ጋር ውዝግብ ብትፈጥር ከዚህ ግቢ ልትባረር ትችላለች። ቀኑን ሙሉ ማልቀሻ አጥታ ስትንከራተት የነበረውን አስታውሳ ከኋላ ያሉትን ጎንታዮቿን መልስ ሳትሰጥ ለቅሶዋ ላይ ብቻ ማተኮር እንዳለባት ለራሷ አሳመነች። ከፊት ያሉት ሁለት ወጣቶች አንዱ ለሌላው በጆሮው የሆነ ነገር እየነገረው ወደ እርሷ ይመለከታሉ። እሷን በሀሜት እየገሸለጧት እንደሆነ አልጠፋትም። ምንም ቢሉ ምንም ሞሯሷን የሚነካ ድርጊት ቢፈጽሙም ለቅሶዋ ላይ ብቻ አተኮረች።

ወደ ኋላ ዞራ ላለማየት ትኩረቷን አንድ ቦታ አደረገች።ዝም በይ የሚለው ነገር አሁንም መጥቷል።ቢቃ ስምታዋለች ማልቀስ የእሷ መብት ነው።ሰው ዝም ብሎ ከመሬት ተነስቶ እንዴት ‹‹ዝም በይ›› ይላል ብላ አሰበች።ምን ያህል እንደተጎዳች ያለማወቁ ነው እንጂ እንዲህ ባላላት ነበር።አብዮቱ ከመጣ ጀምሮ ብዙ ችግሮችን አይታለች፣ ፤እንደዛሬ ግን አብዮቱን ጠልታ አታውቅም።በርግጥ የአብዮቱ ጉዞ ከባድና አስቸጋሪ ነው። ሰዎች ሲያማርሩ ‹‹ምን ይደረግ አብዮት ነው››ትል ነበር። ዛሬ ግን አብዮቱ እሯሷ ቤት ሲመጣ ጥልትአደረገችው ፡፡አንገሸገሻት። ከእንግዲህ ወዲህ ቀበሌ ሄዳ ኪነት ምናንም ላለማለት ማለች። ቅድም ወስና ነበር። አሁን ግን ውሳኔዋን





በመሀላ አረጋገጠች። የፈለገ ይምጣ ብላ ራሷን አሳምናለች። የመጨረሻው ነገር ሊገድሏት ቢችሉ ነው ።አሁን ግን ሞትን አልፈራችም ።ወንድሟም መከተል ስለፈለገች ይሄን ታደርገዋለች።

ወንድሟን አብዮቱ ስለማይመልስላት እዚህ ባለችበት መለያየቷን አበሰረች። ‹‹ወይኔ ወንድሜ!!!!›› እየተብከነከነች ነው። ድምጿ እየጨመረ ሄደ። እንደገናም ትንሽ ከፍ አለ፤ይሄን ግዜ የሰዎችን ትኩረት ሳበች።ወደ እሷ እየተመለከቱ ነው።ለብቻዋ ተነጥላ ነው የቆመችው።ልትሰልል ነው የመጣችው በሚል የተጠጋት ሰው የለም። እዚህ ቤት ላሉት ሰዎች ቅርበት ቢኖራትም መገኘት የለባትም በሚል እየገላመጧት ነው።የሟች ጓደኞች እዚህ መኖሯን አልወደዱም።ሟቹ ኢህአፓ ነው፤እሷ ደግሞ አብዮቱን ታገለግላለች። መረጃ ልትለቃቅም እንደመጣች ነው የጠረጠሩት። ከመጠርጠርም በላይ ደምድመዋል። ቤቱ ውስጥ ድንገት ዘው ብላ ነው የገባችው። ከውጭ ሰው ቢኖር ኖሮ አያስገባትም ነበር።አሁን ግን ቦታው ላይ ተገኝታለች።ወጣቶች ግን እየሸሹዋት ነው።አንዳንድ ሰው ሲመጣ ወደ መኖርያ ቤት ሲያስገቡት አይታለች እርሷን ግን ግቢ አላሏትም።እንዳውም እዛው ግቢ ውስጥ ተቀመጭ እንኳን ብሎ የጋበዛትየለም። ከቤተሰቡ አባላት እንኳን ተቀመጭ የሚላት ቀርቶ አብሯት ለማልቀስ የመጣ የለም። ከሟች ጋር ሰላምታ እንጂ የረባ ንግግር እንኳን የላቸውም።

ይሄ ሁሉ ለሰዎች እንጂ ለእርሷምንም አይፈይድም።አለቃቀሷን አይተው አስመሳይ ነች በሚል የፈረዱባት ተናግረው ከዚህ ሊያስወጧት ቢፈልጉም ለቀበሌ ትነግራለች ብለው የሰጉ ይመስላል። አላወቁትም እንጂ እርሷ አብዮቱን ከድታ ከእነርሱ ሀሳብጋር ተሰልፋለች። እሷም ብትሆን እዚህ በመገኘቷ ምን ስም እንደሚሰጧት አልጠፋትም።የፈለገ ቢሉም የለቅሶ ሜዳ ፈልጋ እንጂ ከእነርሱ ምንም እንደማይገኝ አውቃለች። እናም የእርሷ ተግባር ለቅሶዋን ማካሄድ ብቻ ነው።‹‹ወይኔ ወንድሜ!››አለች።

አሁን እናቷን ማግኘት አለባች። የለቅሶ አጣማሪ ትፈልጋለች። ምናልባት እናቷ ሳታያት በዋናው በር ወደ ቤት ተመልሳ ሄዳ ይሆን እንዴ?።እንደዛ ከሆነ ደግሞ ጥሩ አይደለም።ወደ ቤት ከሄደች ማልቀስ አትችልም። ጥሩ ቦታ ይሄ ነው። ወደ ቤት ከሄደችና እናቷ የልጇን

መሞት ካወቀች የመጣ ይምጣ ብላ ታለቅሳለች፡፡እሷ ግን በሰራተኛዋ ፊት አታደርገውም፡፡ ለካ ከአብዮቱ መጣላቷን ቅድም ወስናለች፡፡ እዚህ ግቢ ውስጥ ትልቁ ችግሯ ለማላቀስ አጣማሪ ማጣቷ ነው፡፡ጭራሽ ቤተሰቡ ስታለቅስ እየገረመማት ነው፡፡ደግሞም ከኋላ የሚመጣው ድምጽ አሁንም እየረበሻት ነው‹‹ዝም በይ››የሚለውቅድም በትህትና ነበር፡፡አሁን ግን‹‹ዝም በይ››የሚለው በቁጣ መልክ ሆኗል፡፡እሷ ግን እስኪ ስታቆመኝ አይሃለሁ አይነት እየነፈረቀች ለቅሶዋን ተያዘችው፡፡

ከኋላ ካለው ሰው ጋር እልህ ውስጥ የተጋቡ ይመስላል፡፡አሁንም ለቅሶዋን ካቆመችበት እያስቀጠለች ሳለ ከኋላ ያለው ሰው ‹‹ዝም በይ እንጂ››ብሎ እጇን ጎተታት‹‹ምን አገባህ›› አለችው(ሞቅ ባለ ንዴት)

‹‹ምን አልሽ››!!!!(በቁጣ)

‹‹አያገባህም››

‹‹ምንካሽ?››

‹‹አንተ!!!!......››

ይሄን ቃል ግን አልጨረሰችውም፡፡ ዝም በይ ብሎ ወደጎተታት ሰው ዞራ ተጨማሪ ስድብ ልትለቅበት ነው፡፡እንደገናም በቁጣ ለመሳደብ እየተዘጋጀች ሳለ ጎታቹ ልጅ በቁጣ እየተናገራት ነው፡፡ ሁለቱም ፊት ለፊት ተያዩ፡፡ እሱ ምንም አልመሰለውም፡፡እሷ ግን ያየችውን ማመን አቃታት፡፡ አይኗ በለቅሶ ስለበለዘ በትክክል ሰው ለመለየት አቃታት እንጂ አፏን ከፍታ ነው የቆመችው፡፡ የጨነበሰው አይኗ ለማረጋገጥ እንዳላስቻላት ስለገባት ይሄ ነገር ውሸት እንዳይሆን አይኗን በለበሰችው ሻርፕ መጥረግ ጀመረች፡፡ አጠራረጓ በፍጥነትና በሀይል ነው፡፡እሷ ተገድላ መሆን አለበት እንጅ በምድር ላይ እያለች እንዲህ አይነት ነገር ለማመን አቅቷታል፡፡አይኗን እያሻሸች ‹‹ዝም በይ›› ብሎ የተቆጣትን አየችው፡፡ነገሮች በተገረመና ባለተገረመ ሰው መከከል ያለ ፍጥጫ ሆነ፡፡አሁን እያየች የነበረውን ነገር አረጋገጠች፡፡ ለቅሶ በሸፈነው ፊቷ ውስጥ ፈገግ ለማለት ሞከረች፡፡ ግን የማግጠጥ ያህል እንጂ በሳቅና ባለመሳቅ መካከል አልነበረም፡፡ ወደ ጎተታት ሰው በፍጥነት እየተመለከተችው ‹‹አንተ !!!!!››አለች

‹‹አቤት››

‹‹አንተ ነህ እንዴ?››

‹‹ምን ማለት ነው?››





‹‹አይኔ ነው ወይስ.....››

‹‹እየቀለድሽ ነው?››

‹‹ወንድሜ!!!!!››

‹‹ምንካሽ?››

‹‹ማለት››

‹‹አምሻል እንዴ?››

‹‹ምን እያልክ ነው››

‹‹አንቺ እኮ ነው እየተናገርሽ ያለሽው››

‹‹ምን ላድርግ››

‹‹እንዴት››

‹‹ሞተሃል......››

‹‹ማነው ሞቷል ያለሽ?››

‹‹ማንም አልነገረኝም››

‹‹እና››

‹‹እኔ ነኝ ያየሁት››

‹‹ሳልሞት ምን አየሽ?››

‹‹አይደለም››

‹‹ምንድነው የምትይው.....››

‹‹ጠዋት ያንተን ጃኬት የለበሰ...››

‹‹ተይው አውቅሁት››

‹‹ምንድነው?››

‹‹ጓደኛዬ ነው፤ የእኔን ጃኬት ለብሶ ነበር ማታ የወሰዱት››

‹‹አንተ ባለመሆንህ ደስ ብሎኛል››

‹‹ገና ነው እኮ››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹ወደእኔ እየመጡ መሆኑን ነግረውኛል››

‹‹አሁን ወደ ቤት እንሂድ››

‹‹ወደ ቤት ከእንግዲህ አልሄድም››

‹‹ለምን?››

‹‹እዛ ነው የሚጠብቁት››

‹‹ እንዳውም ነይ እንሂድ››

‹‹የት?››

‹‹የሆነ ቦታ››

ሁለቱ ተያይዘው ወደ ጓደኛቸው ቤት ሲሄዱ ጓደኛዋ ሱቅ ጋር ቆማ አገኘቻት፡፡ ርቀት ቢኖራትም ወደ እርሷ መሄድ አልፈለገችም፡፡ ጓደኛዋ ድንገት በመገረም አተኩራ ስታያት ሰላምታ ሰጠቻት፡፡ከአንድ ሰአት በፊት ወንድሜ ሞቷል ብላ ስታላቅሳት አሁን ደግሞ ሞተ ከተባለው ሰው ጋር ስትሄድ ስትመለከት ተገረመች፡፡ከጥቂት ሰአታት በኋላ ጓደኛዋ ወደ ቤት መጣች‹‹አንቺ!!!››አለች

‹‹አቤት››

‹‹ምን ማድረግሽ ነው?››

‹‹ምኑ?››

‹‹ወንድሜ ሞቷል ብለሽ አስለቅሰሽኝ....››

‹‹ለእኔም ግራ ገብቶኛል...››

‹‹በእኔ ላይ ቲያትር እየሰራሽ ነው?››

‹‹እንደርሱ አይደለም..››

‹‹ንገሪኛ››

‹‹አትቆጭ››

‹‹እኔን ጠርጥረሽኛል?››

‹‹ለምን?››

‹‹ደብዛን ለማጥፋት››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹አሁን በቅርቡ የተጀመረውን አልሰማሽም››

‹‹ምኑን?››

‹‹አከሌ ጠፍቷል ተብሎ እንዳይፈለግ ትኩረት ይደረጋል››

‹‹አላውቅም››

‹‹እኔ በየሰፈሩ እየዞርኩ ወንድምሽ መሞቱን እንዳወራልሽ ነው››

‹‹እረ እንደዛ አይደለም››

‹‹ነው እንጂ››

‹‹ሌላ ነገር አታስቢ››

‹‹ወንድምሽ የሆነ ነገር አስቧል ማለት ነው››





ወንድሟን በማግኘቷ ብትደሰትም ከቤት መራቁ ሌላ ሰቀቀን ውስጥ ከተታት፡፡ጓደኛው በመገደሉ ስጋት ውስጥ ገብቷል፡፡ ከመገደሉ በፊት የእሱን ስም ሳይሰጣቸው እንዳልቀረ ነው፡፡ ከበላይ የመጣው ትእዛዝ ይሄን ያመላክታል፡፡ዛሬ የደረሰው ትእዛዝ ቶሎ እንዲደበቅ ነው፡፡ መደበቂያውን ካገኘ በኋላ የሚፈልገውን እቃ ከቤት የሚያመጣለት ሰው ሲፈልግ እህቱ ወደለቅሶ ቤት እንደገባች ጓደኞቹ ነግረውት ነበር የመጣው፡፡ እህቱ‹‹አሁን የት ነው የምትሄደው?››አለች

‹‹ጓደኛዬ ቤት››

‹‹የትኛው ጓደኛ?››

‹‹አታውቂውም››

‹‹እኔ የማላውቀው ያንተ ጓደኛ አለ እንዴ?››

‹‹ምን ማለት ነው››

‹‹አንተ ሄደህ የምታድርበት ቤት በጣም የሚቀርብህ መሆን አለበት››

‹‹ነው ግን..››

‹‹ለኔ ላለመንገር ፈልገህ ነው››

‹‹እንደሱ ሳይሆን ሁለት ጓደኞቼ ጋር ነው የምሄደው››

‹‹ማለት››

‹‹አንዱ ጋር አድራለሁ››

‹‹እና››

‹‹ገና አልወሰንኩም ማለት ነው››

‹‹እንዴት ላውቅ እችላለሁ››

‹‹እልክብሻለሁ››

‹‹በማን››

‹‹በድሉ››(ስሙ የተቀየረ)

‹‹እርግጠኛ ነህ››

‹‹አዎ››

የሚደበቅበትን ቦታ ለማንም እንዳይናገር ድርጅቱ ያዘዋል፡፡ እናም እህቱን ቢወዳትም የት እንደሚሆን ሊነግራት አልቻለም፡፡ በድሉ ጓደኛው ነው፡፡ እርሱ እራሱ መደበቂያውን አያውቅም፡፡ ፋንቱ ከለቅሶ ቤት መልስ በነጋታው ቀበሌ ተጠራች፡፡ የቀበሌው የህዝብ

ደህንነት ካድሬ በጣም የሚያንቀጠቅጥ ነው፡፡ ወጣቶችን እሳደ እያስረና እየገደለ የቀበሌውን የኢህአፓ እንቅስቃሴ ያሽመደመደ ነው ይሉታል፡፡ ገና ወደ ቢሮው እንደገባች ‹‹የእኛ ኪነት!!!!››አለ

‹‹አቤት››

‹‹ለአብዮቱ ትዘፍኚያለሽ ለኢህአፓ ታገለግያለሽ››

‹‹እረ እኔ....››

‹‹ዝም በይ››

‹‹ምን አጥፍቼ ነው?››

‹‹ወንድምሽ ሞቷል አይደል?››

‹‹አልሞተም››

‹‹ከሞት ተነሳ እንዴ››

‹‹ምን ማለት ነው››

‹‹ሞቶ ስታለቅሽ አልነበር ››

‹‹እኔ?››

‹‹አዎ››

‹‹የት?››

‹‹የት ነው የሚለቀሰው››

‹‹እኔ....››

‹‹መዋሸትሽ አብዮቱን እየቦረቦርሽ ለኢህአፓ እንደምትሰሪ የሚያረጋግጥ ነው››

‹‹እኔ ለኢህአፓ አልሰራሁም››

‹‹አላለቀስኩም ብለሽ ዋሸሽ››

‹‹ውሸት አይደለም››

‹‹ጓደኛሽ ቤት ሄደሽ አለቀስሽ››

‹‹እሷነው ያላቀሰችን››

‹‹ወንድምሽ ግን ሞቷል?››

‹‹በስህተት ነው››

‹‹ስህተትም ቢሆን ለሞተ ኢህአፓ ነው ያለቀስሽው››

‹‹ድንገት የተፈጠረ ነገር ነው››

‹‹ግን ወንድምሽ አልሞተም?››

‹‹አዎ››





‹‹አስወሪልኝ ብሎሽ ነው››

‹‹እንደዛ አይደለም››

‹‹እንዳንፈልጋቸው ሞተ ብለው ያስወራሉ››

‹‹እረ እኔ እንደዛ ለማስወራት አይደለም››

‹‹አንድ ነገር ልንገርሽ?››

‹‹ምን››

‹‹እውነተኛውን ሞት ዛሬ ማታ እናደርገዋለን››

‹‹በማን ላይ?››

‹‹በወንድምሽ››

‹‹የእኔ ወንድም?››

‹‹አዎ፤ አስገረመሽ እንዴ››

‹‹እንደዛ ለማለት አይደለም››

‹‹አሁን አንድ ነገር ጠይቅሻለሁ››

‹‹ምን››

‹‹ወንድምሽ የት ነው ያለው?››

‹‹የት እንዳለ አላውቅም››

‹‹ብትነግሪኝ ይሻላል››

‹‹አላውቅም አልኩህ››

‹‹ትላንት አብረሽ ነበርሽ››

‹‹አዎ ግን ከዚያበኋላ አላገኘሁትም››

‹‹እቤትም ማታ አላደረም አይደል!!!››

‹‹አዎ››

‹‹የት እንዳለ አንቺ ብቻ ነሽ የምታውቂው››

‹‹ነበረ ግን ዛሬ አላገኘሁትም››

‹‹አንቺ የአብዮቱ ልጅ ነሽ አይደል››

‹‹አዎ››

‹‹በዚያ ላይ በአብዮታዊ ግልጋሎትሽ ተሸልመሻል››

‹‹ልክ ነህ››

‹‹ታድያ ወንድምሽም ለአብዮቱ ብትሰጭ ይከፋሻል?››

‹‹አይከፋኝም ግን የት እንዳለ አላውቅም››

‹‹አሁን ወደ ቤት ሂጂ እንደመጣ ለእኛ ንገሪን››

‹‹እሺ›

ገና በክበሩ ወጥታ የቤቷን አቅጣጫ ለመያዝ ስትንደረደር የሆነ ሰው ሲጠራት ሰማች፡፡ የህዝብ ደህንነት ሰራተኛ ነው፡፡ እዚሁ ቀበሌ በብዙ ስራ ይተዋወቃሉ ‹‹ፈለግሽኝ እንዴ?››አለችው

‹‹አዎ››

‹‹ምንነበር?››

‹‹ከእኛ ጋር እንድትመጪ››

‹‹ለምን?››

‹‹ለትንሽ ጉዳይ ነው ቶሎ ትመለሻለሽ››

‹‹አሁንማ ወደ ቤት እየሄድኩ ነው››

‹‹በኋላ ትሄጃለሽ››

‹‹እቸኩላለሁ››

እንቀው ሊወስዷት ፈለጉ፡፡ሀሳባቸው ለማስፈራራት ነው፡፡ ነገር ግን ሁኔታው ስላልተመቻቸው ወደ ቤት እንድትሄድ ፈቀዱላት፡፡ ይሄው የደህንነት አባል ከሁለት ቀን በኋላ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ወደ ቤቷ ሄደ፡፡ አላገኛትም፡፡ነገር ግን መንገድ ላይ ከሱቅ ስትመለስ ፊት ለፊት ተገጣጠሙ፡፡ አመጣጣቸው አስፈርቷታል ፡፡ፊታቸው ላይ ትልቅ ቁጣ ይነበብባቸዋል፡፡ የሆነ ችግር ሊፈጥሩባት እንደፈለጉ የገባት ይመስላል፡፡ ከደህንነቱ ጋር አብሮት አንድ ሰው ነበረ፡፡ እንጠልጥለው መኪና ውስጥ አስገቧት፡፡እዛው ቀበሌ እስር ቤት ወረወሯት፡፡ ቤቱ ግርግዳው በደም ተልቅልቋል፡፡እዚህ ሰው ሲገረፍ እንደነበረ ነገሯት፡፡ እሷ ግን ሲገረፍ ሳይሆን ሲታረድ እንደነበር የቤቱ ሁኔታ፣ መሬትና ግድግዳ ላይ ያለው ደም ይመሰክራል፡፡ደህንነቱ እየጮኸ ያንባርቅባት ነበር፡፡ምን እንደተፈጠረ ግራ ቢገባትም የሆነ ነገር እንደተከሰተ ስሜቷ ነግሯታል፡፡ስለዚህ ቤት ዝና ሰዎች እያንሾካሾኩ ሲያወሩ ሰምታለች፡፡የሆነ ከባድ ችግር ባይፈጠር እዚህ እንደማያመጧት ታውቃለች፡፡ወንድሟ ፊቷ ድቅን አለ፡፡

የፈራችው አልቀረም፡፡ የዚያኑ ቀን ወንድሟ የህዝብ ደህንነቱን ሊቀመንበር ገድሎ አመለጠ፡፡ይሄን በሰማች ግዜ ለምላ ሲያስቡን ለቁርስ ዳረግናቸው አይነት ነው የሆነባት፡፡ ሊቀመንበሩ ወንድሟን እንደሚገድለው እሷም ይሄንኑ መልእክት ለወንድሟ ተጠንቀቅ ብላ





ልካበታለች፡፡ዛሬ ከጠዋት ጀምሮ ወንድምየውን ሁሉ ቦታ አስሰው ሊያገኙት አልቻሉም፡፡ የት እንዳለ በትክክል የምታውቀው እሷ ብቻ ናት፡፡ አብርሀም (ስሙ የተቀየረ) የመኢሶን አባል ሲሆን በቀበሌው ውስጥ የታወቀ ገራፊ ነው፡፡ውጭ ሀገር ድረስ ግርፊያ ተምሮ እንደመጣና ሌሎችንም እንዳስተማረ ይነገርለታል፡፡ እስረኛውን አብርሀም ያናግረዋል ከተባለ ገና ሳይመታ ሁሉንም ነገር ዝርግፍ አድርጎ ይናገራል፡፡

ፋንቱ ወደ እስር ቤት ከመጣች በኋላ ሁለት ሰዎች ገብተው እየተፈራረቁ ወንድሟ የት እንደሚገኝ ጠየቋት፡፡ ተለማመጧት፣ ለመኗት፣ አስቸገሯት፣ ዛቱባት፣ አስፈራሯት …ሁሉንም ነገር ሞከሩ እሷ ግን ወንድሟ የሚገኝበትን ልትነግር ቀርቶ ፍንጭ ልትሰጣቸው አልቻለም፡፡ እናም ወደአብርሀም እንድትሄድ ወሰኑ፡፡ይሄ ከመሆኑ በፊት ስለአብርሃም ማንነት ነገሯት፡፡ ምንም አልደነቃትም ፡፡እሷ የአብዮቱ ሰው እንደሆነችና ወንድሟን በዚህ ሰሞን እንዳላገኘችው ብቻ ነገረቻቸው፡፡ መግረፊያ ክፍል እንዳስገቧት አንድ ሰው መጣ‹‹አብርሀም አባላለሁ››አላት

‹‹እኔም ፋንቱ እባላለሁ››

‹‹ኪነት ነሽ አይደል››

‹‹አዎ››

‹‹እዚህ በደምብ ትዘፍኛለሻ››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹ጨዋታ እንጀምራለን ማለት ነዋ››

በመጀመርያ ቀን በግርፍያ ብዙ አስቃዩዋት፡፡ የምትበገር አልሆነችም፡፡ ገራፊው‹‹ወንድምሽ የት እንዳለ ካልነገርሽኝ መግረፍ ብቻ ሳይሆን ዘለዝልሻለሁ››አላት፡፡ እሷ ግን የት እንዳለ አስረግጣ ነገረቻቸው፡፡ እርሷ ግን የት እንዳለ ታውቃለች፡፡

ያን ቀን ከለቅሶ ቤት እንደወጡ ወንድሟ ለፋንቱ እውነቱን ነገራት፡፡ ሰሜን ሸዋ የሚገኙት የእናቱ ታናሽ ወንድሞች ጋር ሄዶ እንደሚደበቅ አስረዳት፡፡ በክረምት እዛ ይሄድ ስለነበር አካባቢው ለመደበቅ አመቺ እንደሆን ያውቀዋል፡፡ የእናቱ ወንድም አዲስ አበባ በመጣ ግዜ በለጠን(ስሙ የተቀየረ) እዛ ለማሳደግና አብሯቸው

እንዲናር ብዙ ግዜ እናትየውን ይጠይቃት ነበር፡፡የትምህርቱ ጉዳይ ሆኖበት እንጂ እሱም ቢሆን እትቱን በጣም ስለሚወደው እዛ መሆን ይፈልግ ነበር፡፡እትቱ ሴት ልጆች ብቻ ስላሉት እሱን እንደወንድ ልጇ ነበር የሚቆጥረው፡፡ በለጠ እትቱን በስሙ አይጠራውም ‹‹አቡቴ›› ነበር የሚለው፡፡አሁን በለጠ ከተማውን ለቆ አቡቴ ጋር መሄድ አለበት፡፡ ለእሷም እንደነገራት ድንገት አንድ ነገር ተፈጥሮ እዚህ ከተማ ውስጥ ካጣችው አቡቴ ጋር እንደሚሄድ ነግሯታል፡፡፡በችግር ግዜ መደበቂያው እዛ ነው፡፡‹‹አንድ ወቅት በሰፈር ድብድብ ተነስቶ አንዱን በስለት ወግቶት ከሰፈሩም ከመንደሩም ጠፍቶ ሄደ፡፡እትቱ እሱ ጋር እንደተደበቀ ላከብንና ተረጋጋን ፡፡አባቱ ሽምግልና ጠርቶ እርቅ ተደርጎ ነገሩ ከበረደ በኋላ እንዲመጣ መደረጉን አስታውሳለሁ››ትላለች ፋንቱ፡፡

አሁን ፋንቱ ወንድሟ የት እንዳለ ታውቃለች፡፡ከእሷ በስተቀር ማንም አያውቅም ፡፡እናትየው እንኳን ትገምታለች እንጂ እዛ መደበቁን አልተነገራትም፡፡አካባቢው ለወታደራዊ መንግስት አስቸጋሪ የሆነበት ወቅት ስለነበር እዛ መደበቁ ቢታወቅ እንኳን ከቦታው አስቸጋሪነት ለማግኘት አዳጋች ነበር፡፡እሷ ወደ አካባቢ ደጋግማ ስለሄደች ለወንድሟ ከዚህ የተሻለ መደበቂያ እንደሌለ አምናለች፡፡አሁን በዚህ ሰአት ምን እየሰራ ይሆን ብላ አሰበች፡፡አካባቢውን በአይነ ህሊና ቃኘችው ፡፡ፈላጊ ቢመጣ እንኳን የቱ ጋር መደበቅ እንዳለበት ታውቃለች፡፡ግርፍያው ሁለመናዋን ለብልቧታል ብቻ ሳይሆን ሰውነቷን ሰነጣጥቋታል፡፡

የመንግስት ሰዎች ወንድሟን ካላገኙና እዚህ አደባባይ ረሽነው ለሰው እስካላሳዩ ድረስ በተሸናፊት እንደሚቆጠሩ ነው የገመቱት፡፡የት እንደሚገኝ የምታውቀው እህቱ ብቻ ስለሆነች እሷ ላይ አፍጥጠዋል፡፡ በለጠ የት እንዳለ እንድትነግራቸው እስኪበቃት ቀጥቅጥዋታል፡፡ግን ለግርፍያ የምትበገር አልሆነችም፡፡ የእነርሱ ግምት ወይ ያለበትን አታውቅም አለበለዚያ አሳልፋ መስጠት አልፈለገችም፡፡ ገራፊዎቹ ሁለተኛው ሀሳብ ላይ አርፈዋል፡፡ማንም ሰው ዱላ ሲቋቋም ይችላል ግን የሆነ ግዜ ስሜቱ ይታጠፍና እጅ መስጠቱ አይቀሬ ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ለገራፊዎቹ የተሰጠው ትእዛዝ በአስቸኳይ ገዳዩ ተይዞ መምጣት እንዳለበት ነው፡፡የትም ቦታ መገደል የለበትም፡፡ ከእነህይወቱ ተይዞ እዚሁ ቀበሌ መረሸን ነው ያለበት፡፡እሱን ለመያዝ





ሰዎች ተመድበዋል ፡፡ሰዎቹ ደግሞ ልጁ ያለበትን ቦታ ማወቅ ይፈልጋሉ ፡፡ልጁ ያለበትን የምታውቀው ፋንቱ ነች፡፡ እሷ ደግሞ በገራፊዎቹ እጅ ናት ያለችው፡፡ ለገራፊዎቹ የተሰጠው ትእዛዝ ሰውዬውን ገርፈውም ሆነ በጣጥሰው መረጃውን ማግኘት ብቻ ነው፡፡

ፋንቱ አንደኛው ዙር ጨርሳለች፡፡አንደኛው ዙር ግርፍያ ነው፡፡ ሁለተኛው ዙር ስራ ላይ ሊገቡ ነው፡፡ቀጣዩ ስራ ምን እንደሆን መገመት ባትችልም ከባድ ነገር እንደሚመጣ አውቃለች፡፡ ለዚህም ዝግጁ መሆን አለባት፡፡ሰአቱ አሁን ወደ መምሽቱ ተቃርቧል፡፡ ወንድሟ ከአጎቱ ጋር በዚያ በረጅሙ እንጨት ገበጣ እየተጫወቱ እንደሆን ትገምታለች፡፡በክረምት ከወንድሟ ጋር አብረው ወደ ገጠር ሲሄዱ ሁለቱ በዚህ ሰአት ጥሬ እየበሉ ገበጣ እስኪመሽ ይጫወታሉ፡፡ በአሁን ሰአት ገጠር ገበጣ እዚህ ደግሞ ግርፍያ እየተካሄደ ነው፡፡8 ቁጥር በሚሉት ሲስተም ገልበጠው ነበር የገረፏት፡፡ ይሄንን ድብደባ እንዳገባደዱ ከተሰቀለችበት አውርደው ወንበር ላይ አስቀመጧት፡፡ እጇን ወደ ኋላ አሰሯት፡፡ እግሯንም እንዳይንፈራገጥ አድርገው ጠፈሩት፡፡ ምን ሊያደርጉኝ ነው ብላ አሰበች፡፡ እግሯ በደምብ መሬት መርገጥ አይችልም፡፡ ገልብጠው በዱላ ቀጥቅጠው ደም ቋጥሮ ለመራመድ አይቻላትም ነበር፡፡ ገራፊዎቹ ሶስት ናቸው፡፡ ስራውን በአግባቡ የሚሰራውና ታታሪ ሆኖ የሚቀጠቅጠው አንደኛው ነው፡፡እሱ መረጃውን ለማግኘት በጣም ተጣድፎ የማወጣጫ ግርፍያውን ተያይዞታል፡፡

ታታሪው ገራፊ ሁለተኛው ዙር የማውጣጫ ስራ ሊጀምር ነው፡፡መሬት ላይ ቁጢጥ አለ፡፡ ጣቶቿን መደባበስ ጀመረ፡፡ለጓደኛው ምልክት ሰጠና ከተንጠለጠለው ኮሮጆ መሳይ ነገር አንዱን መርጦ እንዲሰጠው ነገረው፡፡ ቁጢጥ ያለው ታታሪ ገራፊ የእግሯን ጣቶች እየተመለከተ‹‹አሪፍ ጣቶች አሉሽ››አለ

‹‹ምን ማለትህ ነው?››

‹‹የእኔ ዱልዱምና አስጠሊታ ናቸው››

‹‹እና››

‹‹የአንቺ አለንጋና ውብ ናቸው››

‹‹አልገባኝም የምትለው››

‹‹ውበትአላቸው››

‹‹አሁንም አልገባኝም››

‹‹ብጥሩ ሁኔታ ነው የያዝሻቸውለማለት ነው››

‹‹አሁን ስለ እግሬጣት ለምን ማንሳት ፈለግህ?››

‹‹የጣቶችሽ አድናቂ ነን››

‹‹ምን ያደርጉልሃል››

‹‹ግን ጣቶችሽን ትወጃቸዋለሽ?››

‹‹አባባልህ ግልጽ አልሆነልኝም ››

‹‹ትወጃቸዋለሽ ወይ ነው ያልኩሽ››

‹‹ለምን አልወዳቸውም››

‹‹ጣቶችሽ በኢህአፓና በአብዮቱ ይመስላሉ››

‹‹ምን እያልክ ነው››

‹‹ወንድምሽ ያለበትን ከጠቆምሽን ጣቶችሽ አብዮታዊ ናቸው እንዳማረባቸው ያቆያሉ››

‹‹እና››

‹‹ወንድምሽን ካልጠቆምሽ ጣቶችሽ ኢህአፓ ናቸው፤ዋጋቸውን ያገኛሉ››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹የኢህአፓ ጣት አብዮታዊ ሴት እግር ላይ ምንም አይሰራም››

‹‹ምን ልታደርግ ነው››

‹‹እኔ ብሆን ይሄን ጣት ከእኔ እንዲለይ አልፈልግም››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹ምንም አላልኩ፤ጉብቶሽ ከሆነ ተባበሪን››

ታታሪው ገራፊ ከኪደኛው ሜንጦ መሳይ መቁረጫ ተቀበለ ፡፡አፏ ውስጥ ጨርቅ እንዲወትፍ አዘዘ፡፡ የመጨረሻ እግር ጣቷን ለብቻ ፈልቀቅ አድርጎ ነጠለውና መቁረጫው አፍ ውስጥ ከተተው ፡፡ቀና ብሎ ተመለከታት ‹‹ትናገርያለሽ ወይስ ልቁረጠው?›› አይነት ምልክት ሰጣት፡፡ ለመናገር ከፈለገች ሌባ ጣቷን ማውጣት እንዳለባት ተነግሯታል፡፡ ግን ሌባ ጣቷን ስላላወጣች ትንሿን ጣቷን ልታጣ ነው፡ ‹‹.....ልቆርጥ ነው አንድ.....ልቆርጥ ነው ሁለት፤ ልቆርጥ ነው





ሶስት....›› ብሎ ቀና ብሎ አያት ሌባ ጣቷን ስላላወጣች ትንሿን ጣቷን በመቁረጫው መንጭቆ በጠሳት፡፡ ፋንቱ ለማስፈራራት እንጂ ያደርገዋል ብላ ስላልገመተች አልተዘጋጀችም፡፡ ነገር ግን ጣቷ ከእግሯ ላይ ተበጥሶ ሲሄድ ድምጿ ተውጦ ቢቀርም እሪ ብላ ጮኸች፡፡ ተንጨረጨረች፡፡ ሰውነቷ እንደእሳት ተለበለበ ፡፡ጣቷን በመቁረጫው ላይ እንዳደረገ ከተቀመጠበት ተነሳና አይኗ ስር አስጠግቶ የእግሯን ጣት እንድትመለከት አደረጋት፡፡ ጨኸቷ ከአፏ ውስጥ ስላልወጣ የአንገቷ ደም ስር ተገታትሮ ሌላ ሰው አስመሰላት፡፡በዚህ ሰአት መናገር እንደምትችል ስላወቁ ከአፏ ጨርቅ ሲወጣ እሪታዋን አቀለጠችው‹‹ለምን ትጮሂያለሽ››አላት

‹‹አንተ ውሻ!!!!››

‹‹እኔ?›››

‹‹አዎ፤ጣቴን ልትበላ ነው የወሰድከው?››

‹‹እኔ ሽሮ እንጂ ስጋ አልበላም››

‹‹ሞትኩኝ!!!!!!››

‹‹ምን አልሽ?››

‹‹ተቃጠልኩኝ!!!!አረርኩኝ››

‹‹ምን ሆነሽ ነው እሪ የምትይው?››

‹‹ልሞት ነው››

‹‹ገና መጀመራችን ነው እኮ››

‹‹ምኑን››

‹‹የአሁኑን አይነት ስራ››

‹‹ስለፈጠራችሁ ተውኝ››

‹‹ደሙ እንዲቆም መድሃኒት እናምጣልሽ?››

‹‹አዎ በናትህ በፈጠረህ አምጣልኝ››

‹‹ወንድምሽ ያለበትን ንገሪንና››

‹‹የት እንዳለ አላውቅም አልኳችሁ››

‹‹እኛም መድሃኒት የለንም መቁረጡን ግን እንቀጥላለን››

‹‹እንደገና ሌላ ጣት ልትቆርጡ ነው?››

‹‹እንቆርጥም››

‹‹እንቆርጣለን አልክ እኮ››

‹‹አንቺ ነሽ የምትወስኚው››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹ወንድምሽ ያለበትን ካልተናገርሽ……››

‹‹እና››

‹‹እስር ጣትሽን ተረክበን ባዶሽን ትወጫያለሽ››

ማንም ባይደርስላትም ተንጨርጭራ ማልቀስ ጀመረች፡፡እነዚህ ሰዎች እውሬ መሆናቸውን አውቃለች፡፡ሰዎቹን ታውቃቸዋለች፡፡እዚሁ ቀበሌ ነው ያሉት፡፡ በተደጋጋሚ ኪነት ሲያቀርቡ እዚሁ የሚታደሙ ናቸው ፡፡አንድ ላይ ሆነው ስለአብዮቱ ሲዘምሩ የነበሩት አሁን ገራፊና ተገራፊ ሆነዋል፡፡ ጣቷን በክር አስረና ግድግዳ ላይ በምስማር አንጠልጥሎት እሷ እንድታየው አደረገ፡፡ ከዚያም አንድ ክፍል ወስደው አስቀመጧት፡፡መጀመርያ ከሌሎች እስረኞች ጋር ነበረች፡አሁን ሌላ ክፍል አስገቧት፡፡የተቆረጠው ጣቷ ደሙ ባይቆምም የለበሰችውን ሹራብ ቀርጣ አሰረችው፡፡ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ ተጋባች፡፡ ክፍል ውስጥ አንዲት ሴት ተኝታለች፡፡ ይህች ልጅ ተገርፋ እንደመጣች ነው ያወቀችው፡፡እንዴት እንዳደረጓት ካየች በኋላ ልጅቷ ነገሩ አስለቀሳት፡፡ ምንም ማድረቂያ ነገር ስላላገኙ ግራ ተጋቡ፡፡ የምግብ ሰሀኑን መክደኛው አውጥታ ሽንቷን ሸናችና ቀስ እያለች ትኩሱን ሽንት ቁስሏ ላይ አፈሰሰችባት፡፡ ይሄን ግዜ የባሰ እግሯን አቃጠላት‹‹እረ ተቃጠልኩኝ!!! ››አለች

‹‹አይዞሽ ያደርቀዋል››

‹‹እነዚህ አውሬዎች…››

‹‹ተይው በቃ እንደገና ከሰሙ ሌላ ጣጣ ነው››

‹‹ወይኔ እግሬ!!!››

‹‹በምን ቀረጡት?››

‹‹ምን አልሽኝ››

‹‹በጥርሱ ነው የበጠሰው?››

‹‹በመቁረጫ ነው››

‹‹መቁረጫ››

‹‹አዎ››

‹‹መቁረጫም አላቸው እንዴ!!››

‹‹እንደዛ ነው››





‹‹እኔንም ሊቆራረጡኝ ነው እዚህ ያደረጉኝ?››

‹‹እንጃልሽ››

‹‹ምን አልሽ››

‹‹ጣቱን በጠሱኝ ወይኔ!!!!ወይኔ››

‹‹አይዞሽ አልኩሽ እኮ››

‹‹እዚህ ለምን አመጡኝ?››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ይሄ ሌላ ማሰቃያ ቤት ነው?››

‹‹አልመሰለኝም››

‹‹እኔ ሌላ ክፍል ነው የነበርኩት››

‹‹እዛ ሰው ሞልቶ ሊሆን ይችላል››

‹‹የሚበላ ነገር አለሽ?››

‹‹አለ ልስጥሽ››

‹‹ተይው በቃ››

‹‹ለምን ጠየቅሽኝ?››

‹‹እኔ ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም››

‹‹አይዞሽ››

‹‹እንዴት እንዳቃጠለኝ ብታይ››

‹‹አይዞሽ! ግን ምን አድርገሽ ነው?››

‹‹ምንም››

‹‹ታድያ እንዴት እግር እስከመቁረጥ ይደርሳሉ››

‹‹ወንድሜን ፍለጋ ነው››

‹‹ወንድምሽ ምን አድርጎ ነው?››

‹‹ምን አውቃለሁ››

‹‹የደህንቱን ሰው ገደለ የተባለው ነው?››

‹‹ይላሉ እሱ ግን የለበትም››

‹‹አንቺ ያለበትን ታውቂያለሽ እንዴ?››

‹‹አላውቅም››

‹‹እኔ ልምከርሽ››

‹‹ምን?››

‹‹ምንም እንዳትነግሪያቸው››

አብራት የታሰረቸው ልጅ ገራፊዎቹ ልከዋት መሆኑን የተረዳቸው ዘግይታ ነው። ለገራፊዎቹ እንዳትናገሪ ብላ ወንድሟ የት እንዳለ በዘዴ እያውጣጣቻት ነበር።ለሽንት ስትወጣ ጓደኞቿ በትንሽ ወረቀት ‹‹ልጅቷን ተጠንቀቂ ››ብለው ነገሯት።በሁለተኛው ቀን ፋንቱ ተጠራች መልሷ ስላልተሻሻለ ሁለተኛው ጣቷን ቆረጧት።ሁለተኛውም ጣት በክር ተቋጠረና ከሌላው ወንድሙ ጋር ግድግዳ ላይ ተንጠለጠለ፡ ሁለቱም ወገኖች ስቃይ ላይ ነው ያሉት ።ገራፊዎቹ መረጃውን ቶሎ ባለማምጣታቸው አለቆቻቸው እያብጠለጠሏቸው ነው።እሷ ደግሞ ጣቷን አጥታ እየተንገበገበች ነው።የተቆረጠው እግሯ ሳይጠግ ምሽት ላይ ተጠራች።ጣቷን የሚቆርጠውን ሰው ‹‹የቁራው እራጅ ነው›› የምትለው።እንደተቀመጠች ፊት ለፊት ተያዩ።ከእሷ ይልቅ እነርሱ የበገኑ ይመስላል ፡የቁራው ሰው በቁጣ‹ሶስተኛው ጣት ልንወስድ ነው››አለ

‹‹ኧረ!! በፈጠረህ››

‹‹እኛ ምን እናድርግ ንገሪንና አንቆርጥም››

ሁሉም ነገር ዝምታ ሆነ። እንደታሰረች በረጅሙ አሰበች። እነዚህ ሰዎች የሚፈልጉትን ካላገኙ የእግሯን ጣቶች ቆራርጠው እንደሚጨርሱት አልጠፋትም።ንዴት በላያቸው ላይ የተደፋው ሰዎች ብሽቀታቸው ጨምሯል።የተገደለው ሰው በቀበሌው ከፍተኛ ስልጣን ያለው በመሆኑ ገዳዩን ካላገኙ ለእነርሱ እንደሸነፈት ነው የቆጠሩት። አንደኛው ሰው ሁለት ክር አወጣና አሳያት።ሁለት ጣት ለመበጠስ እንደተዘጋጁ ነው።ወዲያውኑ አፏ ውስጥ ጨርቅ ጨመረና ሶስተኛውን ጣቷን መበጠስ ጀመረ። ገና በመቁረጥ ላይ እያለ እየተንፈራገጠች ሌባ ጣቷን አወጣች።በመቆረጥ ሂደት ላይ ያለችው ጣትዋ እንደተንጠለጠለች ከገራፊነት ወደቆራጭነት የተሸጋገረው የቁራው ሰው ከተቀመጠበት ተነስቶ በመኩራራት ‹‹ዘረ ቂላቂል›› ብሎ ተሳደበና ‹‹ለዚህ ነው ያስለፋሽን?›› አይነት ቁልቁል እየተመለከታት ጨርቁ ከአፏ ውስጥ እንዲወጣ አዘዘ‹‹ወንድምሽ የት ነው ያለው?››አለ በንዴት መልክ

‹‹እሺ ልንገራችሁ››

‹‹አሁን ጥሩ ተግባባን ማለት ነው››





‹‹ብነግራችሁ አትገድሉትም?››

‹‹ጫፉን አንነካውም››

‹‹እርግጠኛ አትገሉትም?››

‹‹አንነካውም አልንሽ››

‹‹በምን ላረጋግጥ››

‹‹እሱ ታዛዥ ነው››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹እሱ ታዝዞ ነው የገደለው››

‹‹አልገደለም አልኳችሁ››

‹‹ምን እያልሽ ነው?››

‹‹ገደለ ካላችሁ ትገድሉታላችሁ››

‹‹እሱ ታዝዞ ነው አልንሽ››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹እሱ ባይገድል ይገድሉታል››

‹‹ማን ?››

‹‹አለቆቹ››

‹‹እና››

‹እሱ ጥፋት የለበትም››

‹‹ታድያ ጥፋት ከሌለበት ለምን ፈለጋችሁት?››

‹‹እሱ እንዲገድል ያዘዙትን ነው የፈለግነው››

‹‹ስለዚህ እሱ ጥፋት የለበትም?››

‹‹ያዘዘውን ሰው ከነገረን እንለቀዋለን››

ያለበትን ቦታ ልትነግራቸው ተዘጋጀች። ለመጀመርያ ግዜ ወንድምዋን የከዳቸው መሰላት። አንድም ቀን በምንም ነገር አሳልፋ እንደማትሰጠው እርግጠኛ ነበረች።ግርፍያው በበረታና ባሰቃይዋት ግዜ እንኳን ‹‹ይግደሉኝ እንጂ አልናገርም›› ብላ ነበር። ሁለት ጣቷንም ወስደው ወንድሟን አሳልፋ እንደማትሰጥ እርግጠኛ ነበረች። ከነገረቻቸው እንደሚገድሉት አይጠፋትም። እሷ ደግሞ ያለ እሱ እንደማትኖር ታውቃለች።አሁን ግን ሶስተኛው ጣት መቆረጥ ሲጀምር ተሸነፈች።ሰዎቹ እርስ በእራስ እየተያዩ ለአለቆቻቸው ዋናውን ዜና ለማድረስ ተቻኮሉ።

የእግሯ ደም እየፈሰሰ ነው፡፡እዚህ ቤት በመጣች ቁጥር ደሟን እያፈሰሰች መሄድ ልማዷ ሆኗል፡፡ለመናገር መፈለጓን በተሰማ ግዜ ትንሽ ፋታ ሰጧት፡፡ የተቆረጡ ጣቶቿን ከግድግዳ ላይ ቶሎ አነሱት ፡፡ እሷን ማባበልና መንከባከብ ያዙ፡፡ተቆርጦ ያላለቀውና የተንጠለጠለው ጣትዋን ቶሎ ብለው በጨርቅ ሸፈኑት፡፡ ሀኪም እንዲጠራ አዘዙ፡፡ አይዞሽ ባዩዋ በዛ፡፡አሁን የእነርሱ ለመሆን ተዘጋጀች፡፡ ከአጎቱ ጋር ቁጭ ብሎ ሲያወራ ሄደው እንደሚይዙትና እንዴት እንደሚያሰቃዩት ፊቷ ላይ መጣባት፡፡እሱ ከተያዘ እሷ እንደጠቀመች እርግጠኛ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ለምን መደበቂያ ቦታውን ነገረኝ ብላ ተጸጸተች፡፡ ባይነግራት ስቃይዋን ዋጥ አድርጋ የመጣው መጥቶ ይለይለት ነበር፡፡

ወሳኙ ሰአት ደረሰ፡፡ የት እንደሚገኝ ልትነግራቸው ነው፡፡አሁን የወንድሟ ገዳይ እሷ እንደሆነች ተሰማት፡፡ ምን ታድርግ!!!! እንዴት እንደተሰቃየች ቢያውቅ ኖሮ ይሄን መወሰኗ ላያስገርመው ይችል ነበር፡ አሁን የተማመነችበት ነገር ቢኖር እንደማይገድሉት ቃል ገብተዋል፡፡ እዚህ አምጥተው መግረፋቸው አይቀሬ ነው፡፡ወንድሟ ግትር ስለሆነ ትእዛዝ የሰጠውን ሰው ቶሎ ሊነግራቸው አይችልም ፡፡ምናልባት ከእሷ በበለጠ ቁጥር እየቆራረጡ የእግር ጣት አልባ እንደሚያደርጉት ገመተች፡፡ እንደማይገድሉት ግን እርግጠኛ ሆነች፡፡ ዋናው ነገር ያለመገደሉ ነው አለች፡፡ ውሃ ጠይቃቸው ነበር፡፡ ቶሎ አመጡላት፡፡ ሚሪንዳም ጨመሩላት፡፡ ውሃ እየጠጣች ስቃዩዋን እየታገለች ትንሽ ቆየች፡፡ አንድ ነገር ትውስ አላት፡፡

ከተማው ውስጥ በየእለቱ የሚወራው ወሬ ስለግድያ፣ ግርፍያና ስለማውጣጣት ነበር ፡፡ከብዙ ቀን በፊት አንድ ወሬ ሰምታለች፡፡ልጁ ታስሮ እየተገረፈ ነው፡፡ ስቃዩንም አበዙበት፡፡ እሱ ምንም ውስጥ የለበትም፡፡ተፈላጊው ታላቅ ወንድሙ ነው ፡፡ታላቅ ወንድሙ ያለበትን ቦታ እንዲነግራቸው ነው የሚቀጠቅጡት፡፡ዱላ ሲበዛበት ያለበትን እንደሚነግራቸው ቃል ገባላቸው፡፡ ዋስትና እንዲሰጡት ጠየቃቸው፡፡ ወንድምየውን ምንም እንደማያደርጉት ነገሩት፡፡መንገር ብቻ ሳይሆን ቃል ገቡለት፡፡ ቦታውን ጠቆመ ፡፡ወንድሙ ተይዞ መጣ፡፡የዛኑ ቀን እፊቱ ገደሉት፡፡ ወንድምየውን ጨርሰው እሱንም አሰናበቱት ፡፡ይሄ





ነገር እፊቷ ላይ መጣ ፡፡ወንድሟ ሰው ገድሏል ብለው ደምድመው ካገኙት እንደማይለቁት አሰበች፡፡ይሄ ሀሳብ ያለምክንያት ዛሬ አልመጣም ብላ አመነች፡፡

ይሄን ሀሳብ እያላመጠች ባለችበት ሰአት ጨርቁ ከጣቷ ላይ ተፈትቶ የመጣው ሀኪም እግሯን እያከመላት ነው፡፡ የተንጠለጠለውን ጣቷን ወደ ቦታው ለመመለስ እያስተካከለ ነው፡፡ህመም የሚባል ነገር ከሰውነቷ እየጠፋ መሆኑን የተረዳችው በዚህን ግዜ ነበር፡፡ የመጀመርያ ቀን ጣቷን ሲወስዱ ነበር ብዙ የተሰቃየቸው ፡፡አሁን ግን የለመደችው ይመስላል፡፡ሁሉም ከንፈሩን እየመጠጠ ‹‹አይዞሽ›› በሚል እያበረታቷት ነው፡፡ወሳኙ ሰአት ደረሰ፡፡ዋናው ጣት ቆራጭ ዞር እንዲል ተደርጎ ትህትና ያለው ሰው ከፊት ለፊቷ ወንበር ስቦ ቁጭ አለ ‹‹አመመሽ?››አለ

‹‹በጣም››

‹‹አይዞሽ ሆስፒታል እንወስድሻለን››

‹‹እሺ››

‹‹ግድግዳ ላይ የነበሩት ጣቶችሽም በኦፐራስዮን እንዲያያዙ እናደርጋለን››

‹‹አመሰግናለሁ››

‹‹እኔ አሁን ነው የሰማሁት››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹ይሄን ባውቅ ኖሮ እንዲህ አያደርጉሽም ነበር››

‹‹በጣም ጎዱኝ እኮ››

‹‹ያልታዘዙትን ነው ያደረጉት››

‹‹ምን እያልክ ነው››

‹‹ጣት እንዲቆርጡ ማንም አልፈቀደላቸውም››

‹‹ያኛው ጥሩ ሰው አይደለም››

‹‹እሱን ለእኛ ተይው››

‹‹ማለት››

‹‹ሪፖርት ተደርጎ ከፍተኛ ቅጣት እንዲቀበል እናስደርጋለን››

አሁን እያናገራት ያለው የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር ነው፡፡ ከቆራጩ የባሰ አረመኔ ሆኖ በብዙ ሰው ዘንድ የተፈራ ነው፡፡

መረጃውን ለማግኘት ስለፈለገ ብቻ ትሁት የሆነ ይመስላል፡፡ በተረጋጋ ሁኔታ እያወራ አጠገቡ ለነበረው ረዳት ነገር ‹‹ጣቷን የቆረጠው ሰው በአስቸኳይ እንዲታሰር አድርግልኝ››አለው፡፡ ወደ እርሷ ፊቱን አዙሮ‹‹ባንቺ ላይ ሌላ ነገር የፈጸመ ሰው አለ?››አለ

‹‹ማለት››

‹‹ከግርፍያ ሌላ››

‹‹የለም››

‹‹የጎዱሽ እነማን እንደሆኑ ትነግሪኛለሽ››

‹‹እሺ››

‹‹በይ አሁን በጥሞና አዳምጭኝ››

‹‹እየሰማሁህ ነው››

‹‹ወንድምሽ የት ነው ያለው?››

‹‹አትባራ ነው››

‹‹አትባራ?››

‹‹አዎ››

‹‹አትባራ የት ነው?››

‹‹በጌምድር››

‹‹በጌምድርና ጎንደር?››

‹‹አዎ››

ሰዎቹ በጣም ተደሰቱ፡፡ ከበላይ እያጣደፉ እያሯሯጡ አስቸግረዋቸው ነበር፡፡ አሁን በአስቸኳይ ማድረስ አለባቸው፡፡ የበጌምድርና ጎንደር ክፍለሀገር ለሱዳን ድንበርተኛ ነው፡፡አትባራ የተባለው ከተማ በጌምድር ክፍለሀገር እንደሚገኝ ነው ያወቁት፡፡ ከተማው ከታወቀ በኋላ በአሰሳና በደፈጣ የሰለጠኑ ሙያተኞች ይመደባሉ፡፡ተፈላጊውን ሰው አንቀው የመያዝ ችሎታ ያላቸው ሰው ተፈልጎ በፍጥነት ወደ ቦታው ይላካል፡፡በቅድሚያ አትባራ በምትባለው ከተማ አስተዳዳሪውና የህዝብ ድርጅት ካድሬ አባላት መረጃው ይነገራቸዋል፡፡ከዚያም ታዳኙ ወጣት ጥብቅ ቁጥጥር ይደረግበታል፡፡ ተፈላጊውን ልጅ በቶሎ በማምጣት ህዝብ በተሰበሰበበት እንዴት ዘልዝለው እንደሚሰቅሉት እያሰቡ ነው፡፡ ዋናውን ካድሬና ለደርግ ቀኝ እጅ የሆነውን ሰው ነው የገደለባቸው፡፡ እንኳን እርሱን ተባባሪ





የተባሉትንም አውጥተው ለመረሸን እየዛቱ ነው፡፡እስካሁን ከአስር ሰው በላይ ገድለዋል፡፡ዋናውን ገዳይ ከአትባራ እስኪመጣ ተቻኩለዋል፡፡

በሁለት ጣት ተኩል አትባራ ተገኝታለች፡፡ሁለት ቆረጡ፤ አንዱን እንጠለጠሉት፡፡ ተንጣልጣዩም ቢሆን እንደተቆረጠ ነው የሚቆጠረው፡፡ እስኪነጋ ቆዩና መረጃውን ተለዋወጡ፡፡ ወደ ስፍራው የሚሄዱት ሳተና ሰዎች ተዘጋጁ፡፡ከሰአት በኋላ ወደ ክፍሏ በርግደው የገቡት ሰዎች የትላንቶቹ ናቸው፡፡ለምን እንደመጡ አልጠፋትም ፡፡ ቆራጩ ሰው ተንደርድሮ መጣ፡፡ ተንጠልጥላና በህክምና ተያይዛ የነበረችውን ጣት በጥሶ ጣላት፡፡አንከብክቦ ወደ መግረፊያ ክፍል ወሰዳት፡፡ በጣም ተቻኩለዋል፡፡ አራተኛውን ጣቷን በሜንጦ በጥሶ ጣለው፡፡በዚህ ብቻ አላበቃም፡፡ እሪ የምትለውን ልጅ እንደገና እጇን አሳሰረና የእግሯን ትቶ ከግራ እጅ አንድ ጣቷን በጠሰላት፡፡ ቤቱ በእሪታ ተሞላ፡፡ደሟ እዚህም እዚያም ይረጭ ጀመር፡፡ ‹‹ይሄን ነው የፈልግሽው?››አላት

‹‹እረ አትግደሉኝ››

‹‹መቼ በቀላሉ ትሞቻለሽ ተሰቃይተሽ ቆራርጠን ነው የምንጨርስሽ››

‹‹በናታችሁ!!!!››

‹‹ልትጫወችብን ነው የፈለግሽው አይደል!!!››

‹‹እንደዛ አይደለም››

‹‹አልተማሩም ብለሽ ነው?››

‹‹በፍጹም››

‹‹አትባራ አልሽን እኮ››

‹‹እንደዛ አይደለም››

‹‹ደምሽ አያባራም ታያለሽ››

‹‹በናታችሁ ተውኝ››

‹‹ዛሬ አንድም ጣት አይተርፈንም››

ይሄ ሁሉ ጣጣ የመጣው ቅድም በሀሳቧ ብቅ ያለው ነገር ነው፡፡ እየተገረፈ የነበረው እስረኛ ወንድሙ ያለበትን ከነገረ እንደማይገድሉት ቃል ገብተው በኋላ ግን ቃላቸውን አጥፈው ረሸኑት ፡፡እሷም ወንድሟ ያለበትን ለመናገር ተዘጋጅታ ሀሳቧን ቀይራ ቦታውን ላለማሳየት

ወሰነች።የት እንዳለ ስትጠየቅ ድንገት አንድ ነገር መጣላት። ትምህርት ቤት ስለድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ስትማር ስለአባይ ወንዝ አስተማሪው ብዙ ግዜ የሚናገረው ትዝ አላት።አባይ ሱዳን ሲደርስ አትባራ....በሚል ያወራው ሁሌም ከአእምሮዋ አይጠፋም ነበር።እናም ገራፊዎቹ ሲያስቃዩዋት ወዲያውኑ የዚህን ከተማ ስም ጠራች ። በነጋታው እንደተሸወዱ ሲገባቸው ዋናውን ቆራጭ ልከው ስቃይ ውስጥ ከተቱዋት። የቆራው ሰው እጇን ለመቁረጥ እየተዘጋጀ በተቀደደው ሸሚዟ ውስጥ ጡቷን ተመለከተ፡ይሄን ግዜ ደንግጣ እሪ ብላ ጮኸች።

አሁንም በጣት ቆረጣ አልረኩም።ልብሷን አስወለቁ ከወገብ በላይ ራቁቷን አደረጓት። ጉች ጉች ያለውን ጡቷን ተመለከተ። አይኗ እያየ ጡቷን በካራ መሰል ትልቅ ስለት መገዝገዝ ጀመረ።ቅድም የፈራችውም ነገር ይሄንኑ ነበረ።አሁን እራሷን ስታ እዛው ባለችበት ተዝለፈለፈች ።ከዚያ በኋላ ምን እንዳደረጓት አታስታውስም።ከአምስት ቀን በኋላ እናትዋ እንድትጎበኛት ተፈቀደላት።

እናትየው የሆነውን ማመን አልቻለችም። በከፍተኛ ሀዘንና የለቅሶ ስሜት‹‹የታሉ ጣቶችሽ?››አለች

‹‹እኔ እንጃ››

‹‹ምን ማለት ነው እኔ እንጃ››

‹‹ወሰዷቸው››(እራሷን እንደመሳት አደረጋት)

‹‹እነማን?››

‹‹እነዚህ...››.

‹‹ወይኔ ልጄ!!!››

‹‹አታልቅሽ››

‹‹ለምን አላለቅስም››

‹‹ገና አልጨረሱም እኮ››

‹‹ሌላም ፈለጉ?!!!!!!››

‹‹አዎ››

‹‹ምንድነው ጉዳዩ››

‹‹ቼቼን ፈልገው ነው››

‹‹የት [illegible]ው ያለው?››





‹‹አላውቅም››

‹‹ገድለውት ይሆናል››

‹‹ተይ እንጂ››

ብዙ ነገር አወሩ ።ድንገት የሆነ ነገር ሲስፈነጠር ሰሙ። እናትየው ዝቅ ብላ ተመለከተች። ቴፕሪከርደር ጠረጴዛው ስር መቀመጡን አሁን አስተዋሉ።እናትየው ልጇን ለመጠየቅ ብዙ ሞክራ አልቻለችም። ነገር ግን ድንገት ተፈቀደላትና አንድ ክፍል ሰው በሌለበት እንዲገናኙ ተደረገ።ያለምክንያት ለብቻቸው እንዲያወሩ እንዳልፈቀዱላቸው ገመቱ። ድንገት ሁለቱ ለብቻቸው ሲሆኑ የበለጠ የት እንዳለ ይነጋገራሉ በሚል የተዘጋጀላቸው እንደሆን ዘግይተው አውቀዋል።የልጆች ሞት ለእናቶች ዱብ እዳ ሆኗል።በቤት ስሙ ቼቼ ብለው የሚጠሩት በለጠ ሊሞት እንደሚችል እናትየው ታውቃለች። አንድ ቀን በሯ ላይ ደፍተው እንደሚጥሉላት ትጠብቃለች።እንኳን ቼቼ ፋንቱም ቢሆን በህይወት ከእዚህ እንደማትወጣ ገምታለች።

እናቶች ሰቆቃ ውስጥ ነው ያሉት። ፋንቱ ነገሮችን እንዲህ ታስታውሳለች ‹‹....ለአብዮት ጥበቃዎቹ መግደል ቀላል ነገር ሆኗል። ለእናቴ ሁለታችን ብቻ ነን ያለናት።አንድ ቀን ሬሳችን በራችን ላይ እንደሚጣል ትገምታለች...እናቴ ጎረቤት ካሉት ሴትዮ ጋር ጥብቅ ጓደኛ ናቸው።ሴትየዋ የምትወደው ልጇን በራፍ ላይ ገድለው ሬሳውን ጥለውት ሄዱ።እናትየው ሮጣ ልጇ ሬሳ ላይ ተደፋች ።አብዮት ጠባቂዎቹ መጥተው በስደፍ በመምታት አስነሷት።ማልቀስ እንዳትችልም ተነገራት።አባትየውን ከቤት አውጥተው ሬሳው ፊት አብዮታዊ መፈክር እንዲያሰማ አደረጉት።ሴትየዋን ግን ከግቢ እንዳትወጣ አደረጓት።

እናትየው እስከ ከሰአት ሬሳው በሯ ላይ ተጥሎ መንገደኛውን እያመጡ ሲያስፎክሩ ቤቷ አጥር ስር ሆና ሁሉንም ታያለች።አስር ቀን በማይሞላ ግዜ ውስጥ ሌላኛው ልጇ ተገደለ። ይሄኛው ልጅ በቀበሌ ውስጥ የሚሰራ የመኢሶን አባል የነበረ ነው። እሱ ከአብዮቱ ወገን ስለነበረ ሬሳው በክብር እቤቷ መጥቶ በከፍተኛ የቀብር ስነስርአት ተካሄደ።ጉንጉን አበባ በሳጥኑ ላይ ተደረገ።እድሩ በቀብሩ ላይ ነበሩ።በርካታ ከፍተኛ ገንዘብ ሰጣት።የደርግ አባሎች በቀብሩ ላይ ነበሩ።በርካታ

የቀበሌው ነዋሪ በሀዘኑ ላይ ተገኝ።ወደ ቀብሩ ሲሄዱ እናቴ ነበረች የምታስተዛዝናት።ሴትየዋ የምታለቀሰው የዚያኛውን ስም እየጠራች ነው።በሯ ላይ ገድለውት የት ወስደው እንደቀበሩት የማታውቀው ልጇ በክብር ስላልቀበረቸው ሀዘኑ ውስጧን ቦርቡሮታል። ደጋግማ ስሙን እየጠራች ስትጮህ እናቴ ‹እረተይ እኛንም ታስጨርሽናለሽ› በሚል እየተከታተለቻት ብትናገራትም እሽ እያለች የልጇ ሬሳ ግብአቱ ሲፈጸም እንኳን የዚያኛውን ስም መጥራቷን አልተወችም ነበር።› ትላለች

እናቶች ያልቀበሯዋቸውን ልጆቻቸውን ለማስታወስ በሌላ ሰው ቀብር ላይ እየሄዱ እስከማልቀስ ጀምረው ነበር።የፋንቱም እናት አንድ ቀን ልጇን በሯ ላይ አምጥተው እንደሚጥሉ እየጠበቀች ነው። ፋንቱ ከዚህ በኋላ የምትወደውን የመረብ ኳስ ስፖርት አትጫወትም። ለቡድኗ ኮከብ ናት። ተጫዋቾቹ በእሷ ትልቅ እምነት አላቸው።ስርብና ማቀበል ጎበዝ ነች ።አሁን የምስርብበትም ሆነ የምትደፍቅበት ጣት የላትም።ወንድሟና ጓደኞቹ የእግር ኳስ ቡድን አላቸው ።ግን የፋንቱ አድናቂዎች ናቸው። ቹቹ ካድሬውን ከገደለ በኋላ እሱ የነበረበት ቡድን ተጫዋቾች ማንነታቸው ስለተደረሰበት ታሰሩ አንዳንዶቹም ተገደሉ።

## እንደገና በመጨረሻ

ሰውየው እዚህ ከቆመ 30 ደቂቃ አልፎታል።ለቀጠሮ ትልቅ ቦታ አለው።ነገር ግን የሚጠብቀው ሰው በሰአቱ ካልመጣ ጥሎት ይሄዳል። ይሄን ጓደኞቹ ስለሚያውቁ በሰአቱ ቦታው ላይ ይገኛሉ። አርፍደው ከመጡ በቦታው አያገኙትም ።ይሄ ዋነኛ ባህሪው ነው።ዛሬ ግን ችግር ስለገጠመው የቀጠረው ሰው ስአቱ ቢያልፍም ህገ ደንቡ ተጥሶ እየጠበቀው ነው።እነሆ 5 ደቂቃ አልፏል።የቀጠረው ሰው እስካሁን አልመጣም።አምስት ደቂቃውም አልፎ ሌሎች ደቂቃዎች ተጨመሩ ።እንዲህ እያለ 30 ደቂቃ አለፈው ።አሁንም የቀጠረው ሰው አልመጣም።ይሄኔ ሌላ ግዜ ቢሆን ኖሮ ሁለትና ሶስት ደቂቃ ካለፈ በኋላ ትቶ ሄዶ ሰፈሩ ደርሶ ነበር።

ከርቀት አጭር ሰው ባየ ቁጥር የቀጠረው ሰው እንደሆነ በማመን ተስፋ ያደርግና ተዘጋጅቶ ሲጠብቅ እሱ ሳይሆን ይቀራል።





ትቶ መሄድ ቢፈልግም ለመሄድ የሚያስችለው ምንም ነገር አላገኘም። ቢሄድ የሚጎዳው እርሱ ነው። ይሄን እድል ከእንግዲህ ፈጽሞ አያገኘውም።ይሄ ቀጠሮ ወሳኝ ነው።ወሳኝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አንገብጋቢም ነበር።ችግሩ ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ሊፈታና ሊፍታታ ነው።የቀጠረው ሰው ዘግይቶም ቢሆን መጣ።ለችግሩ ግዜ ደራሽ በመሆኑ ደስ አለው።አሁን ወደጉዳያቸው መሄድ እንዳለባቸው ተነጋገሩ።አብርሃም ትምህርት ቤት መቀየር ስለሚፈልግ የቀጠረው ሰው ዛሬ ይሄን ጉዳይ ይጨርስለታል።

ከሞትና፤ ከስቃይና ከግርፋት የተረፉት ወጣቶች ተሰባስበው ቡድን ሰርተዋል።ቡድናቸው ራስን ለመከላከልና ለመረዳዳት የተሰባሰቡ ናቸው።መነሻቸው በአብዮቱ ወቅት ከደርግ ወገን የነበሩ ጠቋሚዎቻቸውን እያጠቁ ነው በሚል በመወራቱ እንዲህ አይነቱ ነገር ወደ እነርሱ ከመጣ ተሰባስበው ራሳቸውን ለመጠበቅ የተደራጁ ናቸው፡ ፡መጀመርያ አራት ነበሩ ።በፍጥነት ሲደራጁ ከደርዘን በላይ መድረስ ችለዋል።መረጃ የሚያሰባስብ፤የሌሎችን እንቅስቃሴ የሚያጠና፤አጥቂ ወገን የሚባሉት የት እንደሚገኙ የመሳሰሉትን ሰብስበው ይወያዩበታል።ወቅቱ ወታደራዊ ደርግ የተንገዳገደበት ግዜ በመሆኑ ምን እንደሚመጣ ስላላወቁ ቶሎ መሰባሰብን መርጠዋል።አንድ ሰው በእነርሱ አካባቢ የሚገኝ ቤተሰብን ከጠየቀ ለምንድነው ያጠያየቀው ?በሚል ይከታተሉታል።ከደርግ ወገን ከሆነ በምንም መንገድ ችላ የማይሉት ጉዳይ ነው።ጠያቂው ሰው ሰላማዊ ከሆነ በሰላም ያስተናግዱታል።

አሁን ተሰባስቦ የተደራጀው ቡድን በአብዮቱ አፍላ ወቅት የገረፏቸውን ያሰቃዩዋቸውን ቤተሰባቸውን የገደሉባቸውን ሰዎች ምን እናድርጋቸው በሚል ብዙ ተወያይተዋል።መበቀልን የፈለጉ ቢኖሩም እኛም ቤተሰባችን በሰላም እንዲኖር ከፈለግን በቀልን ትተን በሰላም እንዲኖሩ አድርገን እኛም ለቤተሰባችን ሰላም እንስጥ በሚል በቀል እንዳይኖር ቡድኑ ወስኗል። ግን ለአንድ ሰው ብቻ ይሄን እድል መስጠት እንደሌለባቸው ተነጋግረዋል፤‹‹የቁራውን ሰው መተው የለብንም ››በሚል ተማምነዋል።አብርሀም(ስሙ የተቀየረ) የፋንቱን እግርና እጅ ቆርጧል፤ ከዚያም ባለፈ ልጅ እንዳትወልድ ሞራሏን

የነካበትን ድርጊት ፈጽሟል፡፡መግረፍና ማስቃየት የደርግ ትእዛዝ ቢሆንም የቁራው ሰው ግን ጣትና ጡት ሲቆርጥ የነበረው ራሱ የእንስሳነት ባህሪ ስላለበት ነው በሚል አምነዋል፡፡አብርሀም ሁሉም ጨከነበት፡፡ፋንቱ ከተፈታች በኋላ እሱን ሳለማየት ሰፈሩን ለቃ ሄዳለች፡፡

የተደራጀው ቡድን በስውር የቁራ ሰው የት እንዳለ፤ ምን እንደሚሰራ፤አጠገቡ እነማን እንዳሉ መረጃ አሰባሰቡ፤ስራውን ለማከናወን አንድ ግቢ ውስጥ ቤት ተከራዩ ፡፡ከአከራዩ በስተቀር እዛ ግቢ ሰው አይኖርም ፡፡አከራይዋ ሴትየዋ ብቻቸውን ነው የሚኖሩት፡፡ ወደገበያና ቤተክርስቲያን ሲሄዱ እነርሱ(ተከራዮቹ) ከሌሉ ግቢውን ቆልፈው ነው የሚሄዱት፡፡አብርሀም መምህር ነው፡፡አቃቂ አካባቢ ነው የሚያስተምረው፡፡ የሚኖረው ደግሞ አዲስ ከተማ ነው፡፡ የሚያስተምርበት ከሚኖርበት ቦታ ሩቅ ስለሆነበት በተደጋጋሚ የሚቀይረው ፈልጎ አልተሳካለትም፡፡አንድ ሰው እንዲተዋወቀው ተደረገ፡፡አንዱ እንደጓደኛው ሆኖ ለብዙ ሳምንታት አብሮ አሳለፈ ፡፡ አንድ ቀን መንገድ ላይ አገኘው ፡፡ተንደርድሮ አቀፈውና‹‹እንኳን ደስ አለህ››አለው

‹‹ምን ተገኘ››

‹‹ያ ነገር እኮ ተሳካ››

‹‹የቱ?››

‹‹ስትፈልገው የነበረው ቅያሬ››

‹‹እውነትህን ነው››

‹‹አዎ ››

‹‹እንዴት ተገኘ?››

‹‹ትምህርት ቢሮ ለሚሰራ ጓደኛየ ነግሬው ትላንት ደወለልኝ››

‹‹ቅያሬ ፈላጊውንስ አገኘኸው?››

‹‹አዎ››

‹‹የት ነው?››

‹‹አዲስ ከተማ ነው የሚያስተምረው››

‹‹እና››

‹‹ሳሪስ የቤተሰቦቹን ቤት ወርሶ ገብቷል››





‹‹መቼ?››

‹‹አምስት ወር ሆነው››

‹‹ጥሩ እድል ነዋ››

‹‹በጣም እንጂ››

‹‹የነገረኝን ጓደኛዬን እንጋብዘዋለን››

‹‹በደምብ እንጅ››

‹‹ግን አንድ ነገር አለ››

‹‹ምን?››

‹‹ገንዘብ ሊሰጠን ይገባል››

‹‹ማን? ››

‹‹ቀያሪው››

‹‹ለምን?››

‹‹የእኛን ችግር አያውቀውም››

‹‹ስለዚህ››

‹‹እሱ ነዋ የፈለገው››

‹‹እንዴት ይደረግ?››

‹‹ገንዘብ ከፍሎ እናቀያይረዋለን››

‹‹ይሄ ነገር ቢቀርስ››

‹‹ለምን?››

‹‹እድሉ እንዳያመልጠን ምክንያቱም በትራንስፖርት ወጪ እየተሰቃየሁ ነው››

‹‹እሽ አንተ እንዳልክ››

‹‹ግን እርግጠኛ ነክ?››

‹‹እንዴት?››

‹‹ጓደኛህ አሳስቶ እንዳልነገረክ››

››በጣም እርግጠኛ ነኝ››

‹‹ቶሎ ሰውየውን ማግኘት አለብን››

‹‹ችግር የለውም››

‹‹እንደርሱ አይደለም››

‹‹ማለት››

‹‹በመሀል ሰው ገብቶ ሊከሽፍ ይችላል››

‹‹እንዲህ አይነት ነገር አለ እንዴ››

‹‹አዎ፤ብዙ መምህር በዚህ የተነሳ ችግር ላይ ስላለ እንደኔ አይነቱ ሌላ ሰው ሊጠልፍ ይችላል››

‹‹እንዴት እናድርግ ታድያ››

‹‹ሰውየውን አገናኘኝ››

‹‹ትንሽ የጤና ችግር አለበት››

‹‹ምን ሆነ?››

‹‹ብርድ ነው፤ እስኪሻለው ትንሽ ግዜ እንጠብቅ››

‹‹ሆስፒታል ነው ያለው?››

‹‹አይደለም፤ቤቱ ነው››

‹‹ቤቱ እንሂድ?››

‹‹ይቻላል››

‹‹ትተዋወቃላችሁ እንዴ››

‹‹አጋጣሚ ሆኖ የማውቀው ሰው ነው››

ሰውየው ወጥመድ ውስጥ ሰተት ብሎ መግባቱ አስገርሞታል። እውነትም ትልቅ ሀጢያት አለበት ብሎ አሰበ፡፡ቤቱ ያከራዩት ሴትዮ ብቻቸውን ነው ያሉት፡፡ወደ ገበያ ወይም ወደቤተክርስትያን ሲሄዱ የግቢውን በር ቆልፈው ነው፡፡ ተከራዮቹ ቤቱን እየተመላለሱ ያድሩበታል፤ ይውሉበታል፤ የእነርሱ የሆነ እንግዳ ሲመጣ ያሳርፉበታል፡፡ሴትየዋ ራቅ ብለው የሚሄዱበትን ግዜ ያውቃሉ፡፡ግን ማረጋገጥ ፈልገዋል ፡፡አንደኛው ተከራይ‹‹ደህና ዋሉ እትዬ››አለ

‹‹ደህና››

‹‹ነገ እቤት ይቆያሉ እንዴ››

‹‹አዎ፤ ምነው?››

‹‹ዘመዴ ከክፍለ ሀገር ይመጣል››

‹‹ቁልፍ አለህ አይደል››

‹‹አዎ››

‹‹ታድያ ምን ችግር አለ ከፍቶ ይግባ››

‹‹አካባቢውን ስለማያማቀው….››

‹‹ሰፈሩ አያሳስትም እኔ ወጥቼ እጠብቀዋለሁ››

‹‹ልክ ነዎት››





‹‹ለመሆኑ ጓደኛህ ነገ ነው የሚመጣው?››

‹‹ስነሳ እነግርሀለሁ ነው ያለኝ፤ ነገ ካልሆነ ከነገወድያ ነው የሚመጣው››

‹‹ከነገወዲያ እኔ አልኖርም››

‹‹ቀኑን ሙሉ››

‹‹አዎ ማታ ነው የምመጣው››

‹‹ነው እንዴ!!››(ቢንጎ)

‹‹አዎ››

‹‹እንግድያውስ ሰፈሩን ስለማያውቅ እኔ እዚሁ ልጠብቀው››

‹‹ይሻላል፤እንግዲህ ነገ ከሆነ ንገረኝ ፤እኔ ጠብቀዋለሁ ››

ለአብርሃም ነገ ስራ ስላለብኝ አይመቸኝም ብሎ ነገረው፡፡ ከነገወዲያ ተቀጣጠሩ፤በተባለው ሰአት ተገናኙና ወደግቢው ሄዱ፡፡ወደ ውስጥ ዘለቁ፡፡ቤቱን አንኳኩ፡‹‹ግቡ›› የሚል ድምጽ ሰማ፡፡መኝታ ላይ ተከናንቦ የተኛው ህመምተኛ ተደጋግሞ እያሳለው ነው፡፡ወደ ውስጥ የገቡት አቀያያሪውና እንግዳው ሰው ወንበር ስበው ለመቀመጥ እየፈለጉ ነው፡፡አብርሃም ተቀመጠ፡፡አቀያያሪው ሰው አልጋው ጫፍ አጮልቆ ተቀመጠ፡፡ተከናንቦ የተኛው ሰው በብርድ ልብሱ ጫፍ እየተመለከተ ነው፡፡ወንበር ላይ ተዝናንቶ ሲቀመጥ የባሰ አናደደው፡፡ ንዴት ብቻ ሳይሆን እሳት የሚተፋ ብስጭት በውስጡ መጣበት፡፡ እንደዚህ በቅርብ ያየው መቼ እንደሆነ አስታወሰ፡፡ያን ግዜ ከታሰረበት ክፍል ደጋግሞ እያወጣ ሲገርፈውና ገላው ላይ ሲጋራ እየተረኮሰ ሲያስቃየው የነበረውን አስታወሰ፡፡እየተናደደና እያሳለ ብርድ ልብስ ውስጥ ሆኖ ግደለው ግደለው አይነት ስሜት መጣበት፡፡እሱን ለመግደል ስልጣን የለውም፡፡ ለዚህ የተቋቋመ ኮሚቴ ስላለ እነርሱ ናቸው መደረግ ያለበትን የሚወስኑት፡፡ አሁን የእሱ ስራ እያሳለና እያቃሰተ እእእ…. እያለ ማንቋረር ብቻ ነው፡፡ዋናዎቹ ሰዎች እስኪመጡ የቁራውን ሰው ቶሎ ከክፍሉ እንዳይወጣ ማቆየት ነው ያለበት፡፡ ግዜው ደርግ ሊወድቅ አስር ሳምንት ያህል ይቀር ነበር፡፡ አልጋው ላይ የተቀመጠው ሰው‹‹አቤ እንዴት ነህ?››አለ

‹‹ምንም አልልም››

‹‹አልተሻለህም››

‹‹ዛሬ ብሶብኛል››
‹‹ባለቤትህ የት ሄደች?››
‹‹ፋርማሲ መድሃኒት ልታመጣ ነው››
‹‹ትቆያለች?››
‹‹አላውቅም፤ሻይ ይፈላላችሁ?››
‹‹ችግር የለም፤እኔ የምልህ....››
‹‹እሺ››
‹‹ያልኩህ መምህር እሱ ነው››
‹‹ነው እንዴ?››
‹‹አዎ››
‹‹እዚህ ድረስ ለምን ታስለፋዋለህ››

አብርሃም ቶሎ ብሎ በአስተዛዛኝ መልኩ መንከባከብ በሚመስል ሁኔታ ወደወሬው መግባት በመፈለጉ ‹‹እኔ ነኝ እንሂድ ያልኩት››አለ

‹‹ተሸሎኝ እስክነሳ መጠበቅ አትችሉም ነበር?››
‹‹እንችላለን››
‹‹እና››
‹‹ታሚል ሲለኝ ለመጠየቅም ጭምር ነው የመጣሁት››
‹‹የታመመን መጠየቅ ጥሩ ነው፤እግዜር ይስጥህ››
‹‹አመሰግናለሁ፤ምን እንርዳህ››
‹‹ምንም ፤ ትንሽ በሩን ከፈት አድርጉት››
‹‹እሺ››
‹‹የት አካባቢ ነው የምታስተምረው››
‹‹አቃቂ ነው፤ያንተስ የት ነው?››
‹‹አዲስ ከተማ፤ያንተ ግን በጣም እሩቅ ነው››
‹‹ችግር ውስጥ ገባሁኝ››
‹‹ካንተ በኋላ ሌላ በጣም የተቸገረ ሰው ጠይቆኝ ነበር››
‹‹እኔ ነኝ የቀደምኩት እባክህ ተባበረኝ››
‹‹እተባበራለሁ ሰውየው አሁን ይመጣል››
‹‹የቱ?››
‹‹ቀይረኝ ያለው››





‹‹እና ለእሱ ልትሰጠው ነው››
‹‹አይደለም››
‹‹እና››
‹‹አንተ ችግርህን ትነግረዋለህ እኔም አስረዳዋለሁ››
‹‹ግን ነገሩ ወደእርሱ እንዳያመዝን››

ለዚህ መልስ ሳይሰጠው አንድ ሰው አንኳኩቶ ወደ ቤቱ ገባ፡፡ ቅያሬውን የሚፈልገው ሰው እንደሆነ ገመተ፡፡ አብርሀም አሁን የመጣውን ሰው ያውቀዋል፡፡ ግን የት እንደሚያውቀው ግራ ገባው ‹‹አንተን ግን የማውቅህ መሰለኝ›› ብሎ ተናግሮ ለዚህ መልስ እየጠበቀ ባለበት ግዜ ከጀርባው መቀመጫ ፍሰጋ የዞረ የሚመስለው ሰው በካቦርቱ ሽሽንት በነበረው አጭር የብረት ዘነዘና ማጅራቱን ሲለው ከወንበሩ ላይ ተዘቅዝቆ መሬት ድፍት አለ፡፡ ወዲያውኑ በሽተኛ ተብየው ፍንጥር ብሎ ተነሳና ብርድ ልብስ ውስጥ ይዞት የነበረውን ገመድ አወጣና አሰረው፡፡ አቀያያሪውና አልጋው ጫፍ ላይ የተቀመጠው ሰው ከፍራሹ ስር ገለጥ አድርጎ ያስቀመጠውን ጨርቅ አውጥቶ አፉ ውስጥ ወተፈበት፡፡ ይሄ ነገር አስተማማኝ ባለመሆኑ አፉን በገመድ አሰሩት፡፡ ለጥያቄያቸው መልስ ለመስጠት እንዲያስችል ተብሎ እያላሉ የሚጠቀሙበትን ነገር አመቻቹ፡፡ ስራውን ቶሎ መጀመር አለባቸው አብርሃም‹‹ምንድነው እሱ?››አለ

‹‹የቱ?››
‹‹እየጎዳችሁኝ እኮ ነው››
‹‹ተረጋጋ››
‹‹መምህር አይደለህ እንዴ?››
‹‹አዎ››
‹‹ለመቀያየር አይደል እንዴ ያመጣችሁኝ››
‹‹ነበረ ግን ሀሳባችንን ቀየርን››
‹‹ዘራፊዎች ናችሁ?››
‹‹አይደለንም››
‹‹ብትሆኑም እኔ ምንም ገንዘብ የለኝም››
‹‹ገንዘብ ችግር ካለብህ እኛ እንሰጥሃለን››
‹‹እና ለምን ትመቱኛላችሁ?››

‹‹መቼ መታንህ››
‹‹ማጆራቴን ብላችሁ ጣላችሁኝ››
‹‹ይህች ምን አላት››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹መቼ ተጀመረ››
‹‹አሁን ልቀቁኝና ልሄድ››
‹‹እኛ የማሰር እንጂ የመልቀቅ ስልጣን የለንም››
‹‹ማነው ታድያ….››
‹‹ምኑ?››
‹‹ባለጉዳዩ››
‹‹አሁን ተረጋጋ እናም ዝም በል››
‹‹ከእኔ ምን ፈለጋችሁ?››
‹‹የሚያናግርህ ሰው አለ እሱ ነው ባለጉዳዩ››
‹‹ማነው እርሱ?››
‹‹ትንሽ ጠብቅ ባለጉዳዩ ሲደርስ እናገናኝሃለን››

ሁሉም ተረጋግተው ቁጭ አሉ። ለአብርሀም ‹‹ብትጮህ፣ ብትነቃነቅ፣ ብትንፈራገጥ በዚህ ዘነዘና እናትህ ይብረቀሳል፤ዘነዘናው ልክ ካላገባህ በዚህ ማፈኛ ባለው ሽጉጥ ለመጨረሻ ግዜ እንሸኝሃለን›› አለው።ለሽጉጡ ማፈኛ ባይኖረውም ድምጽ ሳይሰማ እንተኩሳለን የሚለውን እንዲያስብ ለማድረግ ነው።በሽተኛ መስሎ የተኛው ሰው እስካሁን ከኋላው ሆኖ በማሰርና መጋደሚያውን ቦታ በማመቻቸት እንጂ ወደ ፊት ለፊቱ ብቅ አላለም ነበር።አሁን ግን ከፊቱ ተገኝቶ‹‹ምነው አተኩረህ አየኸኝ›› አለው

‹‹አንተን የማውቅህ መሰለኝ››
‹‹ማወቅ ብቻ!!››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ከእኔ የበለጠ የምታውቀውን ሰው እናገናኝሃለን››
‹‹መምህር ነበርክ?››
‹‹አይደለሁም››
‹‹ቀበሌ ትሰራ ነበር?››
‹‹እዛም አልነበርኩም››





‹‹ታድያ የት ነው የማውቅህ?››
‹‹ለምን እኔን የምታውቅበትን ቦታ ለማወቅ ፈለግህ?››
‹‹እዚህ ያለውን ነገር ለመገመት ነው››
‹‹ባታውቅ ይሻልሃል››
‹‹ግን የፈለጋችሁትን ብትነግሩኝ ጥሩ ነበር››
‹‹ምን ቢሆን ጥሩ ነው ብለህ ትገምታለህ?››
‹‹ለመገመት አስቸግሮኛል››

ከውጭ በሩ የተንኳኳ መሰለ።ምናልባት የእሱ ሰው ድንገት እዚህ ሲገባ አይቶት የተከተለ ከሆነ ለማጣራት በመስኮት ቀዳዳ ተመለከተ። ምንም ሰው የለም። ከጠላፊዎቹ አንዱ‹‹እንግዳችን ቀረ እንዴ››አለ

‹‹እንዴት ይቀራል የእሱ ጉዳይ አይደል››
‹‹ስንት ሰአት ነው ድረስ ያልከው››
‹‹እዚሁ ቅርብ ነው››
‹‹ለምን አልገባም››
‹‹ነገሩ እስኪረጋጋ ለመቆየት የፈለገ ይመስላል››
‹‹እንዴት?››
‹‹ከእኔ ጋር ተከታትሎ ላለመግባት የፈለገ መሰለኝ››

ወዲያውኑ የግቢው በር ሲከፈት ተሰማቸው።በቀዳዳ ሲመለከቱ እንግዳው ነው።ከእንግዳም በላይ ዛሬ የክብር እንግዳ ነው‹‹ቤቶች››አለች

‹‹ግቢ››
‹‹እንዴት ናችሁ››
‹‹አለን በስራ ተጠምደን››

አብርሀም አሁን የገባውን ሰው ትኩር ብሎ ተመለከተ።ፊቷ ላይ የሆነ ነገር አይቷል ።እንደሚያውቃት ገምቷል።የታሰረው በእሷ ትእዛዝ መሆኑ ተነግሮታል። እንዲፈታ ወይም የዱላ እርምጃ እንዲወሰድበት የምታደርገው እሷ መሆኑን ተረድተቷል።በቅርቡ አንድ ነገር ሰምቷል። ሴቶችም ያሉበት አፋኝ ቡድን አገታ ያደርጉና አንድ ቦታ አስቀምጠው ገንዘብ መውሰድና ከሌለውም ቤተሰቡ የተቀጣጠሩበት ቦታ እንዲያመጣ አድርገው በዘረፋ ስራ ይሰማራሉ።፡፡ ይሄም ቡድን ከእነርሱ አንዱ ነው ብሎ ገመተ ።ግን በትንሽም ቢሆን የሚያውቀው ፊት ስላለበት ነገሩ ግራ አጋባው። አሁን ወደ ቤቱ

ዘሌታ የገባችው ሴት የታሰረውን ሰው በስሙ ጠራችውና ‹‹ከወትሮ...
አለች

‹‹ቀኖቹ ቢሆንም ፊትሽ አልጠፋኝም››
‹‹ፊቴን እንኳን አይመጣልህም››
‹‹እና በምን ለስታውስሽ››

ሴትየዋ ሚማዋን ማውለቅ ጀመረች። የእጇንም ጓንት ... አወጣችው። ወንበር ላይ ቁጭ ብላ‹‹ይሄን የእግር ... ታስታውሳለህ?››አለች

‹‹ምን ሆኖ ነው?››
‹‹እኔ አገኘ››
‹‹ማለት››
‹‹ምን እንደሆነ እኔ አላስታውስም››
‹‹አልገባኝም››
‹‹ምን ሆኖ እንደተቆረጠ የሚነግረኝ ሰው ሳፈላልግ ነበር››
‹‹እና››
‹‹አንተ ታውቃለህ አሉ››
‹‹እረ እኔ አላውቀውም››
‹‹እርግጠኛ ነህ?››
‹‹አዎ፤የምታውቂውን ልትነግሪኝ ትችያለሽ››
‹‹የሆነ ሰው ወስዶብኝ ነው››
‹‹ማነው?››
‹‹እሱን እየፈለግሁት ነው››
‹‹ለምን ወሰደ?››
‹‹ስርቆኝ ነዋ››
‹‹ጣት ይሰረቃል እንዴ?››
‹‹ቢሆን ነዋ፤ደግሞ...
‹‹ደግሞ ምን?››
‹‹ጣቶቼን የት እንዳደረጋቸው ማወቅ እፈልጋለሁ››
‹‹ሰውየውን ካገኘሽውማ መጠየቁ ጥሩ ነው››

ሴትየዋ ተናዳ በተቀጣጠፈው እጇ በጥፊ አለችው።‹‹....ቁጭ ብለህ በቀን በቀን ስትቀነጥሰው የነበረውን እጅና እግር ረስተህ



ማታለልህ ነው። ወይስ አይታወቅብኝም ብለህ ነው››ብሚል በንዴት ደጋግማ መታችው።ስራውን ቶሎ መጀመር ፈለገች። የጥላሁን ገሰሰ ዘፈን ያለበትን ቴፕ ከፈቱት። ድምጹንም ከፍ አደረገችት። ትልቁ ቴፕ ካሴቱን ጎርሶ መጫወት ጀመረ። የሰውየው ድምጽ ቢያመልጥ እንኳን የተከፈተው ቴፕ ውጡ እንዲያስቀረው የታሰበ ነበር። ስራውን ቶሎ ማከናወን በሳሰባቸው ሚማውን አወለቁት፡ ይሄ እንዳይደረግ ብዙ ታግሎ ነበር። ሊገርፉት እንደሆነ አውቆታል ‹‹ልትገርፉኝ አትችሉም››አለ

‹‹እንገርፍህም››
‹‹ማለት››
‹‹መግረፍ ቀላል ነው››
‹‹እና ምን ልታደርጉ ነው?››
‹‹እግርህን ቅቤ ልንቀባልህ ነው››
‹‹እየቀለዳችሁ ነው››
‹‹ቀልደን አናውቅም››
‹‹እና››
‹‹ባንተ መንገድ ነው የምንሄደው››
‹‹ምንድነው እሱ?››
‹‹ትደርስበታለህ››
‹‹አንቺን ግን አሁን አወቅሁሽ››
‹‹የት ነው የምታውቀኝ››
‹‹ከሆነ አመት በፊት.....››
‹‹ዛሬ የበሰጠ ታውቀኛለህ፤ለመሆኑ ትዳር ይዘሃል ?››
‹‹አዎ››
‹‹ስንት ልጆች አሉህ?››
‹‹አራት››
‹‹ለምን ትዳር ያዝክ?››
‹‹ምን ማለት ነው››
‹‹አንተ በሰራኸው ሀጢአት እነርሱን ለምን ትማግዳለህ››
‹‹ምንም የሰራሁት ሀጢያት የለም››
‹‹ለመሆኑ ለሚስትህና ለልጆችህ የሰራኸውን ነግረሃቸዋል?››
‹‹ምንም መጥፎ ነገር ስላልሰራሁ...››

‹‹አንተ ልጆች አሉህ››
‹‹እና››
‹‹እኔ ግን ልጆች የሉኝም››
‹‹ማለት››
‹‹እኔ መውለድ አልችልማ››
‹‹ለምን?››
‹‹አየሽው ጡቱን››(እያሳየችው)
‹‹ምንድነው እሱ››
‹‹ለልጅ ወተት ማጥቢያ የለኝም፣ ሌላም የጤና ችግር ስለሚያመጣ እንዳትወልጅ አሉኝ››
‹‹አዝናለሁ››
‹‹ግን እኮ እንዴት እንደሚያሳዝን የተሰማህ አልመሰለኝም››
‹‹የምትይው አልገባኝም››
‹‹በቅርብ ደቂቃ ይገባሃል››
‹‹ምን አልሽ?››
‹‹የእግር ጣቶችህ ያምራሉ››
‹‹ምን ልታደርጊ ነው?››
‹‹ምን የማደርግ ይመስልሃል››
‹‹ሚፌን እንዳትነኪኝ››
‹‹ምንም ትርፍ ነገር ካንተ አልወስድም››
‹‹ምን ማለት ነው?››
‹‹የወሰድክብኝን ብቻ እወስድብሃለሁ››
‹‹ምንድነው የምትወስጅው?››
‹‹መውሰድ ስልህ አልገባህም?››
‹‹አልገባኝም››
‹‹የሀሙራቢን ህግ ታውቃለህ?››
‹‹አውቃለሁ››
‹‹አይን ላጠፋ አይን ብሏል››
‹‹ለምን ግልጥልጥ አድርገሽ አትነግሪኝም››
‹‹ከእኔ የወሰድክብኝን ካንተም ወስዳለሁ››(ነገረችው)
‹‹ይሄን እንድታደርጊ አልፈቅድልሽም››





‹‹አንተ ነህ ይሄን ነገር ያመጣኸው››
‹‹እና››
‹‹ባንተ መንገድ እሄዳለሁ››
‹‹እረ ተይ!!››
‹‹ለማንኛውም ከረሳኸኝ ስሜ ፋንቱ ነው ››

ስለቱን ይዛ ወደ እግሩ በጣም ተጠጋች፡፡ ጣቱን አጥብቃ ያዘች፡፡ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው መቁረጫ የወሰደባትን አራት የእግር ጣት ለመውሰድ ተዘጋጀች፡፡ የጀመረችው ትንሿን ጣት በመቁረጥ ነው፡፡ስለቱ ጥሩ ቢሆንም የእግሩ አጥንት አስቸግሯት ነበር፡፡ስትቆርጥ ትልቅ እርካታ ተሰማት፡፡የቀረውን ጣት ጓደኞቿ ነበር የቆረጡት፡፡ ወንድሟ ነበር ትልቅ ተዋናይ፡፡ አንዱም ቁራጭ እሱ ነበር፡፡ከእግሩ ወደ እጁ ተሸጋገሩ፡፡ በወሰደባት ልክ ነው የሚቆራርጡት፡፡የቁራው ሰው ያኔ በግርፋቱ ወቅት የፋንቱን እጅ ከጨረሰ በኋላ ወደ ጡቷ ነበር የሄደው፡፡አሁን ወደ እርሱ ሲመጡ ጡት ስለሌለው ተመጣጣኝ ብለው ያሰቡትን ለመውሰድ እርስ በእርስ አወሩ፡፡ልዋጩን ተነጋገሩበት፡፡ ጡት በአይን እንዲቀየር ተስማሙ፡፡ እናም አይኑን ለማጥፋት ተዘጋጁ፡፡

## ከሆነ አመት በኋላ

በሚያዝያ ወር ሁለቱ እህትና ወንድም ባሉበት ጨዋታ ተጀመረ፡፡ ተጀምሮም ወደ ኋላ ሄደ፡፡ወደ ኋላ ሄዶ 1969ኙን ረገጠ፡፡ ይሄ አ.ም ለሁለቱም የስቃይ ግዜ የነበረበት ወቅት ነው፡፡እንዳሁኑ አካሏን ሳታጣና ዘናጭ የነበረችው ፋንቱ ከወንድሟና ከጓደኞቿ ጋር የተነሳችውን ፎቶ ለሶስተኛው ሰው አሳየች፡፡ ስለወቅቱ ማውጋቱን ተያያዙት፡፡ ድንገት ስለአደገኛው ጣት ቆረጣ ላይ ጨዋታው ደረሰ፡፡ ፋንቱ የደረሰባትን ስቃይ እያስታወሰች ወደ ወንድሟ ዞሯ‹‹ያኔ ስቃዩን ሳስታውሰው ይገርመኛል››አለች

‹‹እንዴት?››
‹‹የእግሬን ጣት ጨርሰው ወደ እጄ ዞሩ ከዚያ…››
‹‹ነገሩ እኮ ቀላል ነው››
‹‹ምኑ ነው ቀላሉ?››

‹‹ይሄን ያህል መጎዳት አልነበረብሽም››
‹‹አልገባኝም››
‹‹የፈለጉትን መስጠት ነበረብሽ››
‹‹ምንን?››
‹‹ዋናው ጥያቄ ያንቺ ከአብዮቱ ካምፕ መውጣትሽ አይደለም
‹‹ለእሱ ትንሽ እስንጋ ትበቃለች››
‹‹እኔ ያለሁበትን ቦታ እንድትነግሪያቸው አይደል የጠየቁሽ
‹‹አዎ››
‹‹ያንን ሁሉ ጣት እስኪቆርጡ ምን አስጠበቀሽ?››
‹‹ምን ማድረግ ነበረብኝ››
‹‹ያለሁበትን ለምን አትነግሪያቸውም››
‹‹ብውቅማ ይሄን ሁሉ ጣቴን አስጨርስ ነበር?››
‹‹እንዴት አታውቂም››
‹‹በትክክል አላውቅም››
‹‹አትዋሽ ታውቂያለሽ››
‹‹አቡቴ ጋር እንደምሄድ ነግሬሻለሁ››
‹‹አዎ››
‹‹እና››
‹‹ከተማ ይሁን ገጠር ያለው ቤት መቀመጥህን አላውቅም››
‹‹ከተማ ቤት የሰራው በኋላ ነው››
‹‹የገጠሩንም ቢሆን በትክክል እዚህ ቦታ ነው ብዬ አላውቀውም›››
‹‹አማዬ እኔ ጋር መጥታ ነበር››
‹‹እና››
‹‹ማን ነገራት?››
‹‹እኔ እንጃ››
‹‹ፋንቱ ነገረችኝ ብላ ነው የመጣችው››
‹‹ይሄን ነገር ብዙ ግዜ ታነሳለህ››

ሁለቱ ሲከራከሩ መተማመን አልቻሉም፡፡ሶስተኛው ሰው በመሀል ገብቶ ጨዋታው ውስጥ እየተሳተፈ ነው፡፡ ከወንድምዬው





ጋር ማውራት ጀመረ፡፡ግን በትክክል ፋንቱ ያለህበትን በምን አወቀች?››አለ
‹‹ከመሄዴ በፊት ነገርኳት››
‹‹እጎትህ ጋር እንድምትሄድ ነው የነገርካት››
‹‹እንደዛ አይደለም››
‹‹እና››
‹‹ልደበቅ ነው አልኳት››
‹‹የት?››
‹‹ጓደኞቼ ጋር››
‹‹እና››
‹‹እሷ ይቅርብህ የከፋ ነገር ሲመጣ አሳልፊው ይሰጡሃል አለችኝ››
‹‹ተውከው?››
‹‹አዎ እሷ አጎቴ ጋር ሂድ አለችኝ››
‹‹ተስማማህ››
‹‹አዎ››
‹‹በትክክል በወቅቱ አጎትህ ጋር መሄድህን ታውቃለች?››
‹‹ነግሬያታለሁ››
‹‹የእሷም ጥያቄ ይሄ መሰለኝ››
‹‹ምኑ?››
‹‹የነገርካት ለመሄድ መስማማትህን እንጂ በትክክል ሄደህ እዛ መቀመጥህን አላወቀችም››
‹‹ውሸቷን ነው››
‹‹እንዴት?››
‹‹እዛ መሆኔን ታውቃለች ግን አሳልፋ መስጥ አልፈለገችም››
‹‹ጣቷን ቆረጧት እኮ››
‹‹ከታትፊው ቢገሏትም አትናገርም››
‹‹ለምን?››
‹‹እኔ ተይገቼ እንድገደል አትፈልግም››
‹‹ይሄን ያህል እንዴት ተማመንክ››
‹‹ከእሷ በላይ በእዚህ ጉዳይ እርግጠኛ ነኝ››

‹‹ማን እኮ ልትወስን ነበር››
‹‹ቢሆን ኖሮ ግርፍያው ላይ ነገሮች ይቀየሩ ነበር››
‹‹እንዴት?››
‹‹ስትገረፍ ትናገር ነበር፤ወይም የመጀመርያው ጣት ሲቆረ
እኔ እያዘ ነበር››
‹‹ማረጋገጫህ ይሄ ነው?››
‹‹አዎ፤ ይሁን ሁሉ ጣት አታስከትፍም ነበር››
‹‹ስለእሷ ምንም አልሰማህም››
‹‹እናቴ በድጋሚ የመጣች ግዜ ነገረችኝ››
‹‹ድርጊቱን ስትሰማ ምን አልክ?››
‹‹አላመንኩም››
‹‹መቆረጡን ያየኸው መቼ ነው?››
‹‹ከአስር አመት በኋላ ተመልሼ መጣሁ››
‹‹አደጋ አልነበረውም››
‹‹ተደብቄ ነው››
‹‹ለምን መጣህ?››
‹‹እሷ ተፈትታ ነበር እኔን ካላየሁ ብላ አስቸገረች››
‹‹ለምን?››
‹‹መገደሌን ሰማች››
‹‹ማን ነገራት ››
‹‹ጓደኞቼ››
‹‹እና››
‹‹ለማረጋገጥ ያለሁበት ልትመጣ ፈለገች››
‹‹ምን ችግር አለ ብትመጣ››
‹‹ሊከተሏት ይችላሉ››
‹‹በምን አወቅክ?››
‹‹ቶሎ ነው የተፈታችው እኔ ወዳለሁበት ትመራናለች በሚል
ይጠብቁ ነበር››
‹‹እና››
‹‹ከእሷ ይልቅ እኔ ብመጣ ችግር የለውም በሚል ነው››
‹‹ብትያዝስ?››





‹‹ሊለዩኝ አይችሉም››
‹‹እንዴት?››
‹‹ፍጹም ተቀይሬያለሁ››
‹‹ሊለዩህ አይችሉም?››
‹‹አባቴን ከአስር አመት በኋላ ነበር ያገኘሁት››
‹‹የት?››
‹‹ገበር መጣ፤በደስታ ተውጬ ልስመው ስሄድ ማነህ አንተ
አለኝ››
‹‹ይሄን ያህል?››
‹‹አዎ እኔ ነኝ ብዬ ስነግረው አላመነም››
‹‹እንዴት ተሰማው››
‹‹አንቱ ከቤት ወጣና እኔ መሆኔን ነገረው››
‹‹ምን አሉ?››
‹‹እኔ እኮ የሰፈሩ ገበሬ መስሎኝ ነው አሉ››
‹‹ቃርስ ነበር››
‹‹ገበሬ ሆንኩና እዚያው ቀረሁ፤አባቴም...››
‹‹አባትህ ምን››
‹‹ብትመጣ ማንም አያውቅህም አለኝ››
‹‹ለዚህ ነው የመጣኸው?››
‹‹እሷን ማየት ፈልጌ ነው››
‹‹የት አገኘሃት?››
‹‹ቤተክርስትያን እናቴ ይዛት መጣች››
‹‹ምን አልካት?››
‹‹እሷ አልመሰለችኝም ታነክስ ነበር››
‹‹አየኸው››
‹‹ምኑን? ››
‹‹የቆራረጧትን››
‹‹አየሁና አለቀስኩ››
‹‹ሁሉንም አየህ››
‹‹አዎ በቁም ከታትፈዋታል››

አጠገቡ ሆና የምታዳምጠው እህቱ ወንድሟን ማናገር ጀመረ
‹‹የዛን ቀን እኮ እንዲህ አላልከም››አለች
‹‹ምኑን?››
‹‹ከታተፏት አላልከም››
‹‹ምን አልኩኝ››
‹‹እዚህ ውስጥ ለምን ገባሽ ነው ያልከው››
‹‹ምን ማለት ነው?››
‹‹እኔ ያለሁበትን ተናግረሽ ለምን አትገላገይም ነው ያልከኝ››
‹‹አሁንም አቋሜ እንደዚያ ነው››
‹‹የእኔም አቋም እንደዚያ ነው››
‹‹ምኑ››
‹‹የሆነ ሆኖ ያኔ የተደረገው ውሳኔ ሁለታችንን ዛሬ በህይወት አገናኝቶናል››

ፋንቱ አግብታ ልጅ ባትወልድም ሁለት የወንድሟን ልጆች ታሳዳጋለች። እንደ ልጆቿ ነው የያዘቻቸው። ወንድሟም ቢሆን ለእሷ ስለሰጣት ልጆቹ ብሎ አልመጣም።ሁሌም ጥንካሬዋ ይደንቀዋል።

## ፋንቱን ለማግኘት

## እንደገና ወደ ኋላ የሆነ ቀን

ከብዙ አመታት በፊት ፋንቱን ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረድ ነበር። እንዲህ አይነት ታሪክ እንዳላት የሚውቁት በቅርቧ የሚገኙ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው።ግን ብዙ ተፈለገች ፋንቱ ግን ልትገኝ አልቻለችም።እሷ ያለችበትን ታውቃለች የቅርብ ጓደኛዋ ናት የተባለች ሴት በፍለጋ ተገኘች ።አስማረች ትባላለች ።ፋንቱን የምታገናኝ እርሷ ናት።ተገናኘን‹‹ሰላም ነሽ››አልኳት
‹‹አለን››
‹‹የፋንቱ ጓደኛ ነሽ››
‹‹አዎ››
‹‹ስምሽን ማን ልበል››
‹‹አስማረች››
‹‹ስራ እንዴት ነው?››





‹‹ጥሩ ነው፤ምን ፈልገህ ነው?››
‹‹ፋንቱን ነው››
‹‹ለምንድነው የፈለግካት?››
‹‹ለግል ጉዳይ ነው››
‹‹ማነህ አንተ?››
‹‹እኔ››(ነገርኳት)
‹‹በትክክል ምን ፈልገህ ነው?››
‹‹የድሮ ጉዳይ ነው››
‹‹የድሮ ጉዳይ ምን?››
‹‹ከኢህአፓ ጋር የተያያዘ››
‹‹እ!!ስታወራ ሰምቻታለሁ››
‹‹አንቺም ታውቂያለሽ?››
‹‹በወሬ ነው ግን….››
‹‹ግን ምን…››
‹‹ላንተ ማን ነገረህ?››
‹‹ወንድሟን የሚያውቅ ሰው በስልክ አገናኘን››
‹‹ወንድሟም ኢህአፓ መሆኑን ሰምቻለሁ››
‹‹እና እሷን ታገናኘኛለሽ››
‹‹ስትመጣ ነዋ››
‹‹ስልክ የላትም››
‹‹የጎረቤት ነው ደግሞም ይርቃል››
‹‹እና እንዴት ላግኛት?››
‹‹ስትመጣ ነግራታለሁ››
‹‹አንቺ ግን ምኗ ነሽ››
‹‹አብሮ አደግ ጓደኛ››
‹‹ነግራሽ ነበር?››
‹‹ምኑን››
‹‹ብዙ አስቃይተዋት ነበር በግርፍያ…››
‹‹እሷን?››
‹‹አዎ››
‹‹እንዲህ አይነት ታሪክ አላውቅም››

‹‹ምንም አልነገረችሽም?››

‹‹አዎ››

‹‹ታድያ የሰማሁት ውሸት ነው?››

‹‹መሆን አለበት እንጅ እሰማ ነበር››

‹‹እንዲሁ ነዋ የለቀሁት››

‹‹ይሆናል››

‹‹እጅሽን ምን ሆነሽ ነው?››

‹‹ማሽን ቀረጠኝ››

‹‹የት?››

‹‹ፋብሪካ››

ብዙ ወራት ተመላለስ ግን አስማረች ፋንቱን ልታገናኘው አልቻለችም አሁን ቤቷ ስለሚመላለሰው ሰው በተደጋጋሚ እያጣራች ነው።ከባለ መመላለስ በኋላ ጉዳዩን ሊተወው ፈለገ። አንድ ቀን እንደልማዱ ወደ አስማረች ቤት ሄደ፡‹እንዴት ነሽ?››አለ

‹‹እግዚያብሄር ይመስገን ››

‹‹ዛሬም አላገኘሻትም?››

‹‹አዎ››

‹‹ግን አግኝተሻት ታውቂያለሽ?››

‹‹አንዳንዴ››

‹‹ነግረሻታል እንደምፈልጋት››

‹‹አዎ››

‹‹ምን አለችሽ?››

‹‹ተስማምታለች››

‹‹እርግጠኛ ነሽ?››

‹‹አዎ››

‹‹ለመቼ?››

‹‹አርብ››

‹‹የፊታችን?››

‹‹አዎ››

‹‹የት?››

‹‹እዚሁ››





‹‹ስንት ሰአት ልምጣ››

‹‹በዚህ ሰአት››

በተባለው ቀን መረጃ ፈላጊው ወደ አስማረች ቤት ሄደ።ፋንቱ ግን አልመጣችም ብዙ ጠበቀ። ቤቷ እንዳልፈለገችው ገባው‹‹ዛሬ መጣለሁ ብላ ነበር አይደል››አለ

‹‹አዎ››

‹‹ቀረች ማለት ነው››

‹‹መሆኑ ነዋ››

‹‹እንግዲያውስ አልፈለገችንም ማለት ነው››

‹‹በእርግጥ ፈልጋሃለች››

‹‹ታድያ ለምን ቀረች?››

‹‹ለምን ይመስልሃል››

‹‹አላውቅም፣ለማንኛውም....››

‹‹ለማንኛውም ምን?››

‹‹አመሰግናለሁ አስማረች››

‹‹አስማረች አይደለሁም እኮ››

‹‹ስሜ አስማረች ነው አላልሽም እንዴ››

‹‹አይደለሁም››

‹‹ማነው ስምሽ››

‹‹ስሜ ፋንቱ ነው››

‹‹አንቺ ፋንቱ ነሽ እንዴ!!››

‹‹አዎ››

‹‹ታድያ ለምን አስለፋሽኝ››

‹‹ማጣራት ነበረብኝ››

በዚህ መልክ ነበር ግንኙነት የተጀመረው። ቀይ ባንድራዎቹ ሁሌም ተጠራጣሪ ናቸው።

ምዕራፍ 5

## ዘበኛው ያላወቀው ግብ ጠባቂ

ሰሞኑን ወደ ደብረዘይት አይመለስም፡፡ አዲስ አበባ ጓደኛ ቤት ለሁለት ቀን ይቆያል፡፡ ጠዋት ከመለመለው ሰው ጋር ይወያያ ከሰዓት ከብሄራዊ ቡድን ጋር ልምምድ አድርጎ ምሽት ወደ ጓደኛ ቤት ይመለሳል፡፡ብሄራዊ ቡድኑ ሰሞኑን ወደ ሆቴል ተጠቃሎ በፈለገው ሰአት መንቀሳቀስ ስለማይችል ከጓደኞቹ ጋርያለውን ግ በዚህ ሳምንት መጨረስ አለበት፡፡በኪሱ የተጫዋችነት ቴሌራው ይዟል፡፡ምናልባት ይሄ ካልረዳው ደብዳቤ አለው፡፡ደብዳቤው ለሌ የተሰጠውአልነበረም፡፡ለብሄራዊ ቡድን ሲመረጥ ለክለቡ የተጻፈ ነው ይሄንን ፎቶ ኮፒ አድርጎ ይዟል፡፡ይሄም በቂ አልሆነንም ብሎ የሚጠይቀው ከመጣ ከቀበሌው ለብሄራዊ ቡድን ዝግጅት እንደሚመላለስ ያስጻፈው ደብዳቤ አለ፡፡

በርግጥ ይሄን ደብዳቤ አስጽፎ አዲስ አበባ የሚመላለሰው ግ ጥሪ ሳይደረግለት ነበር፡፡አዲስ አበባ ያለው ቁጥጥርከባድ በመሆኑ ችግር ቢከሰት እንኳን ከእነዚህ አንዱ ሊያተርፈው ይችላል፡፡ስለ በጣም የተማረ ሰው ነው ፡፡እንደ ተስፋዬ እምነት ይህ ሰው አገር ለመምራት የሚያስችል እውቀት እንዳለው ነው የተረዳው፡፡እድገት በህብረት ዘምተው በነበረ ግዜ ከሌላ ጣቢያ ወይም ከከተማው ቡድኖች ጋር በሚያደርጉት ውድድር ግብ የሚያስቆጠርላቸው እርሱ ነው፡፡ አሁን ተስፋዬ የሚገኝበትን ኢህአፓ ሴል የሚመራው እርሱ ነው፡፡ ዛሬም ለዚሁ ስብሰባ ሲል ነው ተስፋዬ በጠዋት አዲስ አበባ የደረሰው፡ ፡ሌሎች ሁለት ሰዎች እነርሱን ስብሰባ ይቀላቀላሉ፡፡

ባለፈው ሳምንት የጀመሩትን ጠንከር ያለ ውይይት ዛሬም ይቀጥላሉ፡፡ይሄ ብቻ አይደለም ፡፡ከላይ የመጣ አዲስ ትዕዛዝ ስላለ ያንን ለማስፈጸም ይወያያሉ፡፡ተስፋዬ በፖለቲካው በጣም እየተሳበ





ገብቷል፡፡መሳብ ብቻ ሳይሆን የሚያስበው የሚያብሰለስለውም ይሄንኑ ጉዳይ ነበር፡፡እዚህ ከሰዎቹ ጋር ያለውን ግንኙነት ቶሎ‑ጨርሶ ወደ አዲስ አበባ ስታዲየም በመሄድ ልምምዱን መቀላቀል ይኖርበታል፡፡ ከደብረዘይት በጠዋት ነው የተነሳው፡፡ እርፍዶ ነው አዲስ አበባ የደረሰው፡፡በየቦታው አሰልቺ ፍተሻ ስለነበር መድረስ ከነበረባቸው አንድ ሰአት ዘግይተዋል፡፡ለገሀር ከሎንችናው ከወረደ በኋላ በታክሲ ወደ ዳርማር ይሄዳል፡፡ሰኞ በመሆኑ ለስራ ሰአት የሚጣደፈው የአዲስ አበባ ነዋሪ እየተመለከተ ጉዞውን ጀመረ ፡፡ነገር ግንብዙም ሳይርቅ ሀይለኛ ተኩስ ተከፍቶ እዛው ባለበት‑ታገተ፡፡ከመንደር ውስጥ የኢህአፓ ሰኳዶችን በማባረር ላይ የነበሩት የአብዮት ጠባቂዎች አካባቢውን አተራምሰው መንገዱን ዘጉት፡፡

እየተባረሩ የነበሩት ልጆች መኪኖችን ከለላ አድርገው እየተኮሱ የገቡበት ባለመታወቁ‑ታጣቂዎቹአካባቢውን ከበው ታክሲና መኪኖችን አግተው ለተወሰነ ደቂቃ አቆዩ፡፡ አብዮት ጠባቂዎችና ወታደሮች ተሳፋሪዎቹን ከመኪኖች እያስወረዱ መፈተሽ ጀመሩ፡፡በተኩሱ መሀል ሹፌሩ የት እንደገባ ስላልታወቀ ተስፋዬ በእግሩ መሄድ ጀመረ፡፡እዚህ አካባቢ መገኘት እንደሌለበት ያውቃል፡፡የፈራው አልቀረም ፡፡አንድ ሰው ተከትሎት መጣ፤‹‹ወንድም ቁም››አለው

‹‹እኔን ነው?››

‹‹አዎ አንተ››

‹‹ምነው››

‹‹እዚህ ሰፈር ነህ››

‹‹አይደለሁም››

‹‹ምን ታደርጋለህ እዚህ?››

‹‹ለጉዳይ መጥቼ ነው››

‹‹መታወቂያ አምጣ››

አውጥቶ አሳየው፡፡ የህዝብ ደህንነቱ ሰው ከተመለከተው በኋላ ‹‹የደብረዘይት ልጅ ነህ?››አለው

‹‹አዎ››

‹‹አዲስ አበባ ለምን መጣህ?››

‹‹ለልምምድ››

‹‹የምን ልምምድ?››

‹‹ብሄራዊ ቡድን ተመራጭ ነኝ››

ወረቀቱንና ቀበሌው የጻፈለትን አሳየው፡፡ሰውየው አላመነው ኢህአፓ ብዙ ደብዳቤ አስመስላ ትጽፋለች ብሎ ስለሚገ ተጠራጠረው፡፡ ‹‹ብሄራዊ ቡድን የት ነው የሚለማመደው?››አለው

‹‹ስታዲየም››

‹‹አንተ ታድያ እዚህ ምን ትሰራለህ?››

‹‹ቁርስ ልበላ ነው››

‹‹ቁርስ እነርሱ ያበሏችሁ የለ››

‹‹ሆቴል ስንገባ ነው››

‹‹እርግጠኛ የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች ነህ?››

‹‹አዎ››

‹‹አልመሰለኝም››

‹‹ደውለህ ማረጋገጥ ትችላለህ››

‹‹ኢህአፓ በስልክ ብዙ ግዜ ትሸውዳለች››

‹‹እኔ ኢህአፓ አይደለሁም››

‹‹መቼ ነኝ ብለውን ያውቃሉ››

ሰውየው ምንም አላመነውም፡፡ከደብረዘይት በሉንችና ሲመ ለገሃር ይወርዳል፡ከለገሀር ቁርስ ቢፈልግ እንኳን እዛው ማግኘት ይችላል፡፡ከለገሀር ወደ ስታዲየም መሄድ ነው ያለበት፡፡ በምን መንገድ ወደ ሜክሲኮ መሄድ የለበትም በሚል ሰውየው ለተስፋዬ አስረዳውና ‹‹...እንዳውም አንተ ምንም የብሄራዊ ተጫዋች አትመስልም፡፡ ለሆነ ተልእኮ ነው የመጣኸው››፡በሚል ወደዚ ከመሄድ መለሰውና ‹‹እውነቱን ንገረኝ›› አለው፡፡ተስፋዬ ግን አስረግጦ ነገረው፡የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች ነው አይደለም የሚለውን ለማረጋገጥ ተያይዘው በእግር ወደ ፌዴሬሽኑ ሄዱ፡፡ በር ላይ ያለውን ጥበቃ የህዝብ ደህንነቱ ሰው እያነጋገረው ነው ፡፡ተስፋዬን ሁለት ሜትር ያህልራቅ አድርጎ በሌሎች ጓደኞቹ አስጠበቀው፡፡መሳርያ የታጠቀው ሰው ጥበቃውን‹‹ይሄ ሰው ታውቀዋለህ?››አለው

‹‹አላውቀውም››

‹‹እርግጠኛ አታውቀውም?››





‹‹አይቼው አላውቅም አልኩህ››

‹‹የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች ነኝ ይላል››

‹‹ይሄ?››

‹‹አዎ››

‹‹የብሄራዊ ቡድን ተጫዋቾች እነካሳሁን፤ዱላ፤አለማየሁ ፤አስፋው ሌሎችንም እናውቃለን ይሄን ግን....››

የህዝብ ደህንነቱ ሰው አጅበውት ከመጡት ጓደኞቹ ጋር ሽጉጡን አውጥቶ በመሄድ ‹‹ቅደም ወደ ፊት›› አለው

‹‹ምን አደረግሁ››

‹‹እኔ መጀመርያም አውቂያለሁ››

‹‹ምን››

‹‹የብሄራዊ ተጫዋች ያለመሆንህን››

‹‹እና››

‹‹አንተ ዋናው ኢህአፓ ነህ››

‹‹እንዴት?››

‹‹ቅድም አምልጠው ከተደበቁት ኢህአፓዎች አንዱ ነህ››

‹‹እረ እኔ ኢህአፓ አይደለሁም››

‹‹ዋሸህ እኮ››

‹‹ ምን አድርጌ››

‹‹እዚህ ነው የምጫወተው አላልክም?››

‹‹የተመረጥኩበትን ደብዳቤ አሳየሁክ እኮ››

‹‹ደብዳቤ አስመስሎ ማንም ይጽፋል››

‹‹ትክክለኛ ደብዳቤ ነው፤ገብተን ማረጋገጥ እንችላለን››

‹‹የት?››

‹‹ውስጥ››

‹‹ልታመልጥ...››

‹‹መሳርያ ይዛችሁ እንዴት አመልጣለሁ››

‹‹ቅድም ያመለጡን መሳርያ ይዘን ነው››

‹‹እኔ እንደነርሱ አይደለሁም››

‹‹የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች ስላልሆንክ የምናረጋግጠው
የለም››

‹‹እርግጠኛ ልንገራችሁ ነኝ››

‹‹ጥበቃው እኮ የብሄራዊ ቡድን ተመራጭ አይደለህም እ...

‹‹እሱ ላያውቀኝ ይችላል››

‹‹ሁሉንም አውቃለሁ አለ ››

‹‹ማለት››

‹‹የእያንዳንዱን ተጫዋች ስም ጠራ እኮ››

‹‹እኔ ላናግረው››

‹‹በቃ አረጋግጠናል ወደ እስር ቤት ትሄዳለህ››

‹‹ለምን ?››

‹‹ትሄዳለህ አለበለዚያ እዚሁ ደፋሃለሁ››

ሰዎቹ ሽጉጥና ክላሽ ደግነውበት መንዳት ጀመሩ:: ድን... ከሌላ አቅጣጫ ‹‹ተስፋዬ›› የሚል ድምጽ ሰማ:: ኮለኔል ተስፋ ነው::

‹‹አቤት››

‹‹ምን አድርገህ ነው››

‹‹ምንም››

‹‹ታድያ ለምን ተያዝክ?››

‹‹የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች አይደለህም ተብየ››

‹‹እሱማ ነህ››

ሰዎቹ ቆሙ:: አሁን የመጣውን ሰው ተመለከቱት:: የሲቪል ልብስ ለብሷል:: መሳርያ ግን ይዟል:: በርግጥ መሳርያው በኮ... የውስጥ ኪስ ውስጥ ነው ያደረገው:: ተስፋዬ ኮለኔሉን ሲመለከት ቆመ:: ሰዎቹ ደግሞ በመሳርያ ጀርባውን እየወጉት ወደ ፊት እንዲሄድ አደረጉት ::አሁን የመጣው ሰው ደግሞ እየተከተለ እያናገረው ነው:: ታጣቂዎቹ ሰውየውን በቁጣ‹‹ምንድነህ አንተ?›› አሉት

‹‹አውቀዋለሁ››

‹‹የት ነው የምታውቀው?››

‹‹ስፖርተኛ ነው››





‹‹አንተን ማን መስካሪ አደረገህ?››

‹‹እኔ የተያዘበትብን ጉዳይ አላውቅም፤ ግን የብሄራዊ ቡድን አባል ነው››

የህዝብ ደህንነቱ አባልና ጓደኞቹ ተናደዱ :: አሁን የመጣውን ሰው ሊመቱት ምንም አልቀራቸውም:: ተስፋዬ እንዳጭበረበራቸው ስለተረዱና ቅድም ሲያባርሯቸው የነበሩትን ሰዎች ስላጡዋቸው ከእነርሱ ጓደኛ አንዱ ይሄ ነው ብለው ስላመኑ ይዘውታል:: የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች ነኝ ብሎ ሊያታልል ሲል ተጠራጥረው እምጥተው ጥበቃው ተጫዋች እንዳልሆነ ነገራቸው:: አሁን የመጣው ሰው ሆን ብሎ ተከታትሎ በዘዴ ሊያስመልጠው የውሸት ምስክር እንደሆነ ነው የተረዱት:: ሰውዬውን ሰድበው ተስፋዬን እየነዱ ወሰዱት:: መንገድ ላይ አቆሙትና ‹‹የት ናቸው››አሉት

‹‹የትኞቹ?››

‹‹ጓደኞችህ››

‹‹እነማን?››

‹‹የቅድሞቹ››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ሰው ገድላችሁ እንዴት አይገባህም››

‹‹የምን ግድያ?››

‹‹ጓደኞችህ ጓዳችንን ገድለው ነው ያመለጡት››

‹‹እኔ ስለምትሉት ነገር ምንም አላውቅም››

‹‹እናንተ ኢህአፓዎች መቼ እናውቃለን ትላላችሁ!!››

‹‹እኔ ከመኪና ነው የወረድኩት››

‹‹በእግር ስትሄድ ነው ያገኘንህ››

‹‹ወርጄ ነው››

‹‹አሁን እንቅጩን እንንገርህ››

‹‹ምን››

‹‹ወደ እስር ቤት እንወስድሃለን››

‹‹ለምን?››

‹‹ላንተ አስበን ነው››

‹‹ካሰራችሁኝ ምኑን አዘናችሁልኝ››

ብትታሰር አይሻልም!!››
‹‹ከምንገድልህ ብትታሰር አይሻልም!!››
‹‹ጭራሽ ግድያ››
‹‹የእኛን ሰው ገድላችሁ የምንምርህ ይመስልሃል››
‹‹እኔ ምንም ውስጥ የለሁበትም››
‹‹አሁን አንድ ነገር እንንገርህ››
‹‹ምን››
‹‹አረንጓዴ ኮት ያደረገውን የት እንዳለ ንገረን››
‹‹የምን አረንጓዴ ኮት?››
‹‹ጓደኞቻችን ላይ የተኮሰው እሱ ነው››
‹‹ደጋግሞ ጓዳችን ላይ የተኮሰው እሱ ነው››
‹‹የምትሉት ምንም አልገባኝም››
‹‹እሱ ያለበት አሳየን››
‹‹አላውቀውም››
‹‹አንድ ነገር እንንገርህ››
‹‹ምን››
‹‹የሞተብን በጣም የምናከብረውና አስፈላጊ ጓዳችን ነው››
‹‹ስለሞተው ሰው አዝናለሁ››
‹‹እሱን ማጣታችን ስላንገበገበን አንተን ለመግደል የጉንዳን ያህል አያሳስበንም ››
‹‹ነገርኳችሁ እኔ....››

ይሄንን ቃላት አልጨረሰም፡፡ በያዘው ሰደፍ ከኋላ ያለ... ጀርባውን ሲመታው ተደፋ፡፡ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች አላየን... አልሰማንም ብለው ሸሹ፡፡ የተያዘው ሰው በስርቆት አይደለም፤ ወይ... ከሰው ጋር ተደባድቦ እንዳልሆነ ያውቃሉ፡፡ ኢህአፓ መሆን... ገብቷቸዋል፡፡ ኢህአፓ ከሆነ ደግሞ ስኳድ ነው፡፡ ስኳድ መሆ... የአብዮቱን ሰው ገድሏል፡፡ከገደለ ወይ በግድያ ተሳታፊ ከሆነ ሞት ነው... የሚጠብቀው፡፡ሞት ካለ ደግሞ ድርጊቱ በተኩስ ነው የሚጀመረው፡ ተኩስ ካለ ተባራሪ ጥይት ይበዛል፡፡ ይሄ ሰውዬ ጓደኞቹ እዚህ አካባ... አሉ፡፡ ስለዚህ ከሁለቱም ወገን አደገኛ ተኩስ ይኖራል፡፡ ይሄ በየቦታው ብዙ ግዜ ስለታየ እንደ ልማድ ሆኖ በቅድሚያ የአካባቢው ሰው ግጥሚያው ከመጀመሩ በፊት በሩጫም ይሁን በፈጣን ርም... ከአካባቢው ይሸሻል፡፡





ተስፋዬ ከወደቀበት ተነስቶ ግራ በተጋባ ሁኔታ እየተመለከታቸው ነው፡፡ እየነዱ ወደ እስር ቤት ወሰዱት፡፡እዚያ በግርፍያ ሊያውጣጡት ነው፡፡ እስጋልቱን መሻገር ሲጀምር ታጅቦ በመሄዱ ችግር እንዳለ የተረዱት ሻምበል ዘላለም ደስታ ብዙም ሳይርቁ ተከትለው ደረሱባቸው፡፡ ‹‹ተስፋዬ›› አሉት
‹‹አቤት››
‹‹ምንድነው?››
‹‹በማላውቀው ነገር ይዘውኛል››

የህዝብ ደህንነቱ ተስፋዬን በሽጉጡ እጀታ መታውና ‹‹እንዴት በማላውቀው ነገር ትላለህ›› ቢሎ ሊደግመው ሲል ተስፋዬ ሰውየውን አነቀው፡፡ አንቆም ሊደፋው ምንም አልቀረው፡፡ ሻምበሉ መሀል ገብተው ገላገሉ፡፡ የህዝብ ደህንነቱ ሰው ሻምበሉን ‹‹ሆር በል አንተ›› ብሎ አምባረቀበት
‹‹እኔ?››
‹‹እዎ››
‹‹ለምን?››
‹‹ዞር በል አለዚያ ደፋሃለሁ››
‹‹ወታደር ነን እኮ››
‹‹ብትሆንስ››
‹‹ችግር ካለ እንነጋገር››
‹‹ይሄን ሰው ወንጀለኛ ነው››
‹‹ምንድነው ችግሩ››
‹‹ከወንጀሉ ሌላ አታሉናል››
‹‹ምን ብሎ?››
‹‹ብሄራዊ ተጫዋች ነን ብሎ››
‹‹እንደሱ ከሆነ አላታለለም››
‹‹ታውቀዋለህ?››
‹‹እዎ በዚያ ላይ የአየር ሀይል ተጨዋች ነው››

ሻምበል ዘለላም መታወቂያ አውጥቶ አሳያቸው፡፡ ተስፋዬ የብሄራዊ ቡድን ተጫዋች እንደሆነ ነገራቸው፡፡ ለማጣራት ከፌስት ወደ ፌዴሬሽኑ ጽህፈት ቤት ሄደው ማረጋገጥ እንደሚችሉ

አስረዳቸው፡፡ ‹‹...እንዲሁ የምትወስዱት ከሆነ ድርጅቱ አየር ሀይል ቅር ይለዋል! አየር ሀይል ቅር ካለው ደግሞ ጥሩ አይደለም›› አላቸው፡፡ ሰዎቹ ትንሽ ተቀዛቀዙ፡፡ ተስፋዬን ለቀቁት፡፡ ሻምበል ተስፋዬን ወደ ስታዲየሙ ይዞት እየሄደ ነው ‹‹የት አገኘተውህ ነው›› አለው

‹‹ሜክሲኮ››

‹‹በምን ጠርጥረው ያዙህ?››

‹‹እንዲሁ››

‹‹እንዲሁማ አይዙህም››

‹‹ተኩስ ተከፍቶ ልጆቹ አመለጧቸው››

‹‹እና››

‹‹ፍተሻ ሲደረግ ጠርጠረው ያዙኝ››

‹‹መታወቂያ አላሳየህም››

‹‹እሱ ነው ችግር ያመጣው››

‹‹እንዴት?››

‹‹የደብረዘይት መሆኑን..››

‹‹ለምን?››

‹‹እዚህ ለምን ተገኘህ ብለው››

‹‹ሌላ ግዜ ከቀበሌው ወረቀት ማስጻፍ አለብህ››

‹‹እሺ››

‹‹እና››

‹‹ፎርጅድ ነው አሉ››

‹‹አስቸጋሪ ነው››

‹‹መጥተህ ስላስጣልከኝ አመሰግናለሁ››

‹‹ችግር የለም››

‹‹ግን ስለገላገልከኝ ቅር ብሎኛል››

‹‹የቱ?››

‹‹ቅድም››

‹‹እንዴት?››

‹‹ደፋው ነበር››

‹‹አንተ እኮ...››





ተስፋዬ ንዴቱ አለቅ ብሎታል፡፡ እልህም ተናንቆታል፡፡ ያላግባብ መያዛቸው ብቻ ሳይሆን በሽጉጡ እጀታ ስለመታው አብሽቆታል፡፡ ሻምበሉ ባይመጣ ኖሮ ይተላለቁ ነበር፡፡ አሁን የተፈጠረውን ነገር ተስፋዬ ከውስጡ ማውጣት ፈለገ፡፡ ወደ ቀጠሮው ቦታ መሄድ አለበት፡፡ ለልምምዱ ገና አንድ ሰአት ያህል ይቀረዋል፡፡ ከሻምበሉ ከተሰነባበተ በኋላ ወደ ቀጠሮው ሄደ፡፡ የተቀጣጠሩት ከዳርማር ወረድ ብሎ ከኢታሊ ሆቴል ፊት ለፊት ባለው ቦታ ነው፡፡ ዳርማር ጋር እንደደረሰ ገና ቁልቁለቱን ወደታች ወረድ ሲል አንድ ሬሳ ተመለከተ፡፡ ሬሳው መሬት ላይ ወድቆ አላፊ አግዳሚ እየተመለከተው ነው፡፡

የወደቀው ሰው ከወጣትነት ትንሽ የዘለለ መሆኑ ያስታውቃል፡ በለበሰው ጃኬት አወቀው፡፡ ‹‹እሱ ነው›› አለ፡፡ በጣም ደነገጠ፡፡ ነገሩ ተደርሶበታል ብሎ ስጋ፡፡ ከአካባቢው ቶሎ መሸሽ አለበት፡፡ ደግሞ እሱ ባይሆንስ? ብሎ አሰበ፡፡ እንዲህ አይነት ጃኬት ሌላም ሰው ሊኖረው ይችላል፡፡ አንድ ግዜ በደምብ ማየት አለብኝ ብሎ ወሰነ፡፡ ደግሞም አጠገቡ ሞት እየጎበኘው እንዳለ ተረድቷል፡፡ ቅድም ሜክሲኮ የያዙት ሰዎች ሊገድሉት ለትንሽ ነው የዳነው፡፡ ሞት እየጠራው መሆኑ ገብቶታል፡፡ እንዳውም እየሸተተው ነው፡፡ ግን ቁርጡን ማወቅ ይፈልጋል፡፡

ሰውነቱ እየፈራ መራመድ ጀመረ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሬሳው አጠገብ ሆነው ማንነቱን እየመረመሩ ነው፡፡ እከሌ ነው እየተባባሉ እያወሩ ይገኛሉ፡፡ ተስፋዬ አጠገቡ ጋር ደረሰ፡፡ ደረትና ግንባሩን በጥይት የበሳሉት እሬሳ ነው፡፡ አንድ አይኑን በጥይት ቦትርፈውታል፡፡ ግንባሩን ተመለከተው፡፡ ጸጉሩ ገባ ያለ ነው፡፡ በቃ እሱ መሆኑን አረጋገጠ ፡፡እንደገና ጫማውን አየው፡፡ ፍራቢ ነው፡፡ቅድም በርቀት ነበር ያየው፡፡ አሁን በደምብ ለየው፡፡ እንባው በውስጡ መውረድ ጀመረ፡፡ እንባው ሰው ፊት እንዳያመልጠው ስጋ፡፡ ኮስተር ማለት እንዳለበት አውቋል፡፡ እዚህ አካባቢ ብዙ ሰላዮች እንደሚኖሩ አይጠፋውም፡፡ ሬሳው ጋር በሚያሳዩት ሁኔታ የእሱ ወገን ናቸው ተብለው እንደሚያዙ ሰምቷል፡፡ አሁን ከዚህ መራቅ አለበት፡፡ ከቆየ በጥይት ከሬሳ አጠገብ እንደሚያጋድሙት አይጠፋውም፡፡ የቅድሞቹ

ሰዎች ተከትለውኝ ቢሆንስ? ብሎ አሰበ ይሄ ከሆነ ደግሞ አለተሰ...
የወደቀውን ሰው ሲያስብ ተናደደ።

ሀገር ሊያስተደድር የሚችል ትልቅ እውቀት እንዳለው የሚያምንበት ሰው እንዲህ መሆኑ አሳዘነው። እራሷ ሀገሪቷ ተገደለ የተጣለች መሰለው። የተማረ ሰው አለቀ ብሎ ለራሱ ተናገረ። ‹‹ወይ ተስፋዬ!!!!!!›› አለ በቁጭት። ብዙም ሳይርቅ ሌላ ሬሳ ወድቋል ሲትናት። ወዲያውኑ ነው ያወቃት። ከእነርሱ ቡድን አባል አንዷ ና በቃ ቡድኑ ተደርሶበት እርምጃ እየወሰዱ መሆኑን ነው የገባው። አሁን የቀረው እርሱና አንድ ጓደኛው ናቸው። እዚህ አካባቢ ዞር ዞር ቢል ሶስተኛውን ሬሳ እንደሚያገኝ አውቋል። ከዚያም አራተኛው ሬሳ የእሱ ይሆናል።ቡድኑ ተደርሶበታል ማለት ነው። አዲስ በመጣው መመርያ ለመወያየት ነበር ዛሬ የተቀጣጠሩት። አዲሱ መመርያ አደገኛ እንደሆነና ይሄ ጉዳይ ተደርሶበት እንዳስገደላቸው ነው የገመተው። አሁን ነገሩ ወደ እርሱ አፍጥጦ እንደመጣገባው። ጭንቅላቱ ላይ የሆነ ነገር መጣበት‹‹ተስፋዬ ጥፋ ከዚህ....››ብሎ አቃጨለበት።

ወደ ልምምድ ሲሄድ አእምሮው ታውኳል። ሰአቱ እስኪደርስ አንድ ካፌ ቁጭ ብሎ ወደ ኋላ ነገሮችን ማሰላሰል ጀመረ። ፍርሀቱ ግን ሊለቀው አልቻለም። ደጋግሞ እራሳው ፊቱ ላይ እየመጣ አስቸገረው።ከራሱ ጋር ማውራት ጀመረ። ትጥቁን ቀይሮ ልምምድ ላይ ቢሳተፍም ልክ አልነበረም። ግብ ጠባቂ ቢሆንም ችሎታው አሁን አብሮት የለም። ኳሶች ያመልጡታል። አሰልጣኙ ‹‹ተስፋዬ!!!››አለው

‹‹አቤት››

‹‹ምን ነካህ?››

‹‹ምን ሆኑ››

‹‹ኳሱን በደምብ ያዝ እንጂ››

‹‹እየሞከርኩ ነው››

ትንሽ ቆይቶ አሰልጣኙ በድጋሚ ተናገረው ።ተስፋዬ ምንም መልስ አልሰጠውም። ልምምዱ አልቆ ምሳ በልቶ ወደ ደብረዘይት መሄድ አለበት። ነገር ግን ምሳ ተሰ…የ እንጂ መብላት አልቻለም። አሰልጣኙ ‹‹ምን ሆነሃል ዛሬ›› አለው





‹‹ምንም››

‹‹ዛሬ ልክ አይደለህም››

‹‹ትንሽ ችግር ገጥሞኝ ነው››

‹‹ምንድነው?››

‹‹ጓደኛዬ በመኪና አደጋ ሞተ››

‹‹መቼ?››

‹‹ዛሬ ጠዋት››

‹‹ለምን አልነገርከኝም?››

‹‹እንደምንም ልሰራ ብዩ ነው››

ከልምምድ ሲወጡ ጥበቃውን አገኘው። ከስራ ተቀይሮ ለመውጣት እየተዘጋጀ ነበር ‹‹እንዴ ላናግርህ?››አለው

‹‹ምን ነበር?››

‹‹አታውቀኝም እንዴ››

‹‹አንተንማ አውቅሃለሁ››

‹‹ጠዋት ለምን አላውቅም አልከኝ››

‹‹በልብስ አይቼህ አላውቅም››

‹‹የምገደልም ቢሆን አስጨርሰኸኝ ነበር››

‹‹እኔ ምክንያቱን በምን አውቃለሁ››

ደብረዘይት ከገባ በኋላ በነገሩ ላይ ብዙ አሰበበት ፡የቤቱ በር በተንኳኳ ቁጥር ተጠቁሞበት ከአዲስ አበባ አብዮት ጠባቂዎች መጥተው የሚይዙት ነው የመሰለው። በሶስተኛው ቀን አንድ ሰው ደወለለት። በድምጹ አውቆታል‹‹ተስፋዩ ነህ››አለው

‹‹አዎ››

‹‹ጠፋህ››

‹‹መጥቼ ነበር ››

‹‹የሆነውን ሰማህ››

‹‹አዎ !ምንድነው?››

‹‹አሁን በስልክ አናወራም››

እነርሱ ሴል ውስጥ አራት ነበሩ። ሁለቱ ተገደሉ። ተስፋዬና ይሄ ሰው ናቸው የቀሩት።ሁለቱም የሚተዋወቁት ዘመቻ ጣቢያ ነው።

የእድገት በህብረት እውቀትና ስራ ዘመቻ በሲራሮ ወረዳ አጄ ከተማ ተመድቦ ነበር። ይሄ ጓደኛው አዲስ አበባ ሲመጣ መለመለው።በወቅቱ ተስፋዬ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረገው ለአስረኛው አፍሪካ ዋንጫ ለብሄራዊ ቡድኑ ተመርጦ ከዘመቻ ጣቢያ በአስቸኳይ እንዲመጣ ተደረገ።በመክፈቻ ጨዋታ ብሄራዊ ቡድኑ ከኡጋንዳ ጋር ሲጫወት የለበሰው ቀይ ማልያ ነበር።ቀይ አርማና ባንድራ ደግሞ የኢህአፓ ነበር።

የኢህአፓ ስሜት የነበራቸው ሰዎች ብሄራዊ ቡድኑን የኢህአፓን ማልያ አስለበሱት ተብሎ ተወራ። ያ ማልያ በድጋሚ እንዳይለበስ ተደረገ። ቀሪውን ጨዋታ ብሄራዊ ቡድኑ በሌላ ማልያ ተጫወተ።እዛው ብሄራዊ ቡድን ውስጥ የኢህአፓ አባላት መኖራቸው ቢታወቅም እርስ በእርስ ግን አይተዋወቁም። ተስፋዬ አንድ ሰሞን የሚያድረው ከተስፋዬ ስዩም(ወሎ) ጋር ነበር።ተስፋዬ ስዩም እንቅልፌ መጣ ብሎ ፊቱን አዙሮ ይተኛል። ዋናውመብራት ጠፍቶ ትንሿን የራስጌ መብራት አብርቶ እንቅልፍ እንደወሰደው ሰው ይሆናል ተስፋዬ ስዩም ስለተኛ ይሄኛው ተስፋዬ አጋጣሚውን በመጠቀም እሱም በራስጌ መብራት የኢህአፓን ፕሮግራም ያጠናል። ተስፋዬ ስዩም ተኛቻለሁ ብሏል ግን እንቅልፍ እንደወሰደው ሰው አይደለም። ምናልባት የደርግ ሰው ሆኖ ነቅቶብኝ ቢጠቁምብኝስ ብሎ ሰጋ። በሁለተኛው ቀን ተስፋዬ የደበቀው ወረቀት ተጣጥፎ ነበር የተሸጎጠው ግን አሁን ተዘርግቶ አገኘው።

በቃ ይሄን ነገር አይቶታል ብሎ ሰጋ። ካየው ደግሞ ይጠቁምበታል።ከጠቆመበት ከብሄራዊ ቡድኑ ይባረራል ፣መባረር ብቻ ሳይሆን ይታሰራል። መታሰር ብቻ በቂ አይደለም እንደጓደኞቹ ሊገደል ይችላል። ወረቀቱን ቀዳደደውና ሽንት ቤት ጨመረው።።ተስፋዬ ስዩም በተኛ ግዜ የሚንሾካሾክ ድምጽ ሰምቶ ነበር። በሌላ ቀን ተስፋዬ ስዩም መታጠቢያ ቤት ገብቶ ሻወር መውሰድ ጀመረ። የመጀመርያው ውሃ ማፍሰስ ሲጀምር ቶሎ ብሎ ከሻወር ሳይወጣ ትራሱን ገልጦ ተመለከተ። ደነገጠ። ግን በመደንገጥ ውስጥ ተደሰተ። ማንነቱን አውቆ ይጠቁምብኛል ብሎ የሰጋበት ሰው ለካ እንደርሱ የኢህአፓ ፕሮግራም እያጠና ነበር። እሱ ጋር ያለው ወረቀት ደግሞ ከፍ ያለ





ነው። ከእሱ ደረጃ ሻል ያለ ስፍራ እንደሚገኝ ተረዳ። እዚህ ብሄራዊ ቡድን ውስጥ እነማን ኢህአፓ እንደሆኑ ባይታወቅም ብዙዎቹ አባል እንደሆኑ ገመተ።

የተስፋዬ ስጋት አሁንም እንደቀጠለ ነው።ሁለቱ የሴል አባላት ከተገደሉ ከሶስት ወር በኋላ የተስፋዬ ጓደኛ ተያዘ። በቃ አሁን ተስፋዬ አለቀለት። ልጁ ተይዞ ተገረፈ ፣እስር ቤት እንዳለ ተስፋዬ ከብሄራዊ ቡድኑ ጋር ወደውጭ ሀገር ሄደ።እዛው ባለበት ከራሱ ጋር ብዙ ተሟገተ ።ልጥፋ አልጥፋ አለ።ከሁኔታው ያለመመቻቸት ይሁን ወይም በሌላ የመጣው ይምጣ ብሎ ወደ ሀገር ቤት ተመለሰ።አዲስ አበባ እንደመጣ ልጁ መገደሉን ሰማ።አሁን ነገሩ አስደነገጠው ፡ይሄ ልጅ ሲገረፍ ስሙን ከሰጣቸው የተስፋዬ እጣ ሞት እንደሆን አወቀ። እናም ሁል ግዜ ስጋት ብቻ ሆነ።

‹‹ውሸት ነው››
‹‹ምን አልከ››
‹‹ውሸት መሆኑ ብቻ አይደለም››
‹‹እና››
‹‹ሌላ ሰው እንዳይሰማ››
‹‹እኔ አላወራሁም ሰማሁ እንጂ››
‹‹ራሳ ሲሰጥ አይተሻል?››
‹‹አላየሁም››
‹‹እና››
‹‹ብርሀኔ ይረዳሻል ጠይቂው ስላሉኝ ነው››
‹‹ይረዳሻል ነው ወይስ እያስጠ ነው ያሉሽ››
‹‹ምን ማለት ነው?››
‹‹እውነቱን ንገሪኝ››
‹‹ይረዳሻል ጠይቂው ነው ያሉኝ››

ከሴትየዋ ጋር በጣም ይቀራረባሉ። ደግሞም የታወቁ ወሬኛ ናቸው። አንድ ግዜ ማውራት ከጀመሩ በየሰፈሩ ማዳረስ ይችላሉ። ሴትየዋን ቢቢሲ ነው የሚሏቸው፡ ፡ብርሀኔ ራሳ ሰማች ቤትለቤት ያስጣል ያሉት እራሳቸው የፈጠሩት ወሬ መሆኑ ገብቶታል ፡፡ለዚህም ነው ‹‹ብርሀኔ ይረዳል ነው ያስጣል?›› ብሎ የጠየቃቸው።አሁን ሴትየዋ የሚፈልጉትን ካልተባበራቸው ‹‹ይረዳል›› የሚለው ቀርቶ ‹‹ያስጣል›› የሚለውን ማውራት ይጀምራሉ ፡፡ይሄ ወሬ ደግሞ መድረሻው የት እንደሚሆን አውቋል። የት እንደሚሆን ብቻ ሳይሆን አብዮት ጠባቂ አለቃው ጋር ደርሶ ምን እንደሚያስከትል አልጠፋውም።

ሴትየዋ ቤት መጥተው ነው የጠየቁት። ደግሞም ተጣድፈዋል።ራሳ የሚቆየው ለጥቂት ሰአት ብቻ ነው።ሰዎች ከተመለከቱት በኋላ ከጠዋቱ 3 ወይም አራት ሰአት ላይ ይነሳል። ሰአቱን መሻማት ፈልገዋል። ሁለት ሰአት ከሆነ ወዲህ ሰዎች እየበዙ ነው የሚሄዱት። ብርሀኔ በጧት ወደ ልምምድ መሄድ ነበረበት። የዛሬውን ልምምድ መቅረት የለበትም ፡፡ደግሞ አንድ ሰው በጠዋት ልምምድ ከቀረ አንድ ቦታ ሄዷል ማለት ነው።ይሄ ደግሞ በልምምድ





ስበብ ጸረ አብዮት ተግባር ላይ ለመሳተፍ አስቧል። በወቅቱ የወጣው የአብዮቱ ቁጥጥር ደግሞ አንድ ሰው ከተሰማራበት ተግባር ከቀረ በአካባቢው ወረቀት እየተበነ ግድያ ላይ እየተሳተፈ እንደሆን ይጠረጠራል። ስለዚህ በቦታው መገኘት ተገቢ በመሆኑ በሁሉም በኩል ቁጥጥሩ የጠበቀ ነው።

ሴትየዋን እምቢ ብሎ ከሄደ ደግሞ ከልምምድ መልስ ወሬው ተባዝቶ ያገኘዋል።ሁለቱም ከባድ ቢሆንም አንደኛውን ከባድ መምረጥ አለበት። የሴትየዋን መርጧል።ነገሩ አስቸጋሪና እጅግ አስቸጋሪ ቢሆንም አንድ ግዜ ረድቷት ለማንን እንዳትናገር ማድረግ ነው።ርዳታ ማድረግ የሚችለው ከተሳካም ካልተሳካም ነው። ሴትየዋ መጥፎ እንዳልሆነና ጥሩነቱን ብቻ እንድታይለት ይፈልጋል። ሴትየዋ በነጠላዋ ተከልላ እያለቀሰች እየተንሰቀሰቀች ነው። ብርሀኔ መንታ መንገድ ላይ ነበር ያለው። በውስጡ ቢስማማም ውሳኔውን አላሳወቃትም። ሴትየዋ መፍጠንም ቁርጧንም ለማወቅ ብላ ‹‹ብርሀኔ እባክህ እርዳኝ››አለችው

‹‹ልረዳሽ እኮ ነው››
‹‹የወደቀውልጂ ብቻ አይደለም››
‹‹ሌላ ደግሞ ምንድነው?››
‹‹ሶስቱን ወስዱብኝ››
‹‹እና››
‹‹ሁሉቱን ምን ላድርጋቸው?››
‹‹ምን ማለት ነው?››
‹‹እምስቱንም አይኔ እያየ ይገድሉብኛል››
‹‹ግራ የሚያጋባ ነገር እኮ ነው››
‹‹ሞት አፋፍ ላይ ሆኜ እምጬ ነው የወለድኳቸው››
‹‹እና››
‹‹ያለ አባት እንዴት አድርጌ እንዳሳደግኳቸው ታውቃለህ?››
‹‹አውቃለሁ እኮ አልኩዎት!!!››
‹‹አሁን ያለ ልጅ ሊያስቀሩኝ ነው››
‹‹እርስዎ ታድያ ምን አሰቡ?››
‹‹ግራ ገባኝ››

‹‹ክፍለሀገር ዘመድ የለውትም››

‹‹እህቴ አለች››

‹‹ታድያ እዚያ ለምን አይልኳቸውም››

‹‹እንደዛ ይሻላል አይደል!!››

‹‹አዎ እዚህ ታውቀዋል››

‹‹ጥሩ ብለሃል››

‹‹አሁን የት ጋር ነው አለ ያልሽው››

‹‹ምኑ?››

‹‹የልጅሽ ሬሳ››

‹‹አውቶብስ ተራ አካባቢ ነው››

‹‹አስፓልቱ አጠገብ ነው?››

‹‹አይደለም ዳር ነው››

‹‹አረጋግጠሻል››

‹‹በደንብ››

‹‹ምልክት አለው?››

‹‹አዎ››

‹‹በምን መገደሉን አወቅሽ አንቺ››

‹‹ሌሊት ሲተኮስ ሰማሁ››

‹‹እና››

‹‹ጠርጥሬ ነበር፤እንደፈራሁት ሆኖ ተገኘ››

‹‹ስለጠረጠርሽነው የወጣሽው?››

‹‹ስምኑንም ሲተኮስ ሌሊት ገድለውብኝ ይሆን ብዬ ወደተገደሉበት ሰፍራ ሄጀ ነበር››

‹‹እና››

‹‹ሁለቴ ስሄድ ሌሎች ናቸው ፡፡አሁን ግን የእኔ ሆኖ ተገኘ››

‹‹እሱ መሆኑን በምን አወቅሽ?››

‹‹እየወጣሁ እያለ ሰዎች መጥተው እሱ መሆኑንና ቦታውን ነገሩኝ››

‹‹እነርሱ በምን አወቁ?››

‹‹ሌሊት ከተተኮሰ ጥዋት ሬሳ እናያለን፤የማን እንደሆነ አይተን ካልመጣች ለእናቱ እንነግራለን››





‹‹ለሟች እናት ምን ብለሽ ትነግሪያለሽ?››

‹‹ልጅሽን ገድለውታል እንላለን››

‹‹ከባድ ነው››

‹‹በፊት ነበር ከባድ››

‹‹አሁንስ?››

‹‹እያረርን ለመድነው››

ሴትየዋ ‹‹ለምደነዋል›› እያለች ተንሰቅስቃ እያለቀሰች ተንጨርጭራ እየነገረቻው ነው፡፡ ድምጿዋን ከፍ ባታደርገውም የእርግማን መአት እያወረደች ‹‹ሊያሳብዱን ነው›› በሚል እያጉተመተመች እየተራመዱ ነው፡፡ ብርሀኔ‹‹አሁን እኔ የምጠይቀውን ንገሪኝ››አለ

‹‹ምን››

‹‹በአይንሽ አይተሻል››

‹‹ምኑን?››

‹‹የልጅሽን ሬሳ››

‹‹በልብሱ ነው ያወቅሁት

ብርሀኔ ሴትየዋን ሌላ ቦታ አቁሞ ሁለት ብሎክ አቋርጦ ወደ ሬሳው ጋር ሄደ፡፡ ለስራ ወደ ጉዳዩ የሚሄድ መስሎ በልብሱ ምልክት ወደ ነገረችው ሬሳ አመራ፡፡ ተመለከተው ልቡ በጣም አዘነ፡፡ ስውነቱን በጥይት በሳስተውታል፡፡ እዛው ቆሞ መመልከት አልፈለገም፡፡፡ መንቀሳቀስ አለበት፡፡ ወደ ጎን ትንሽ ሄደ፡፡ እንደገናም ወደ ታች ወረደና ተመልሶ መጥቶ በደምብ ተመለከተው፡፡በቦታው የነበሩት ሬሳዎች አቀማመጣቸውን በደምብ አየ፡፡ ከሰባት ሬሳ መሀል ሁለቱ ተነጥለው ወደ መንደሩ መግቢያ አፋፍ ላይ ወድቀዋል ፡፡ቢያንስ 30 ሜትር ያህል ከሌሎቹ ይርቃሉ፡፡ እነዚህ ሁለቱ ፊታቸውን ወደ መንደሩ ነው ያዞሩት፡፡

ግድያው የተካሄደው ሌሊት በመሆኑ ሊያመልጡ ሲሉ እንደተረሸኑ ጠርጥሯል፡፡አለበለዚያ ይሄን ያህል ርቀው ደግሞም ፊታቸውን አዙረው ሊወድቁ አይችሉም ብሎ የራሱን ግምት አስቀመጠ፡፡ አሁን ስለነዚህ ሬሳዎች አወዳደቅ መመራመር ለእሱ

ምንም አይሰራለትም፡፡ የእሱ ጭንቀትና ስጋት ይሄን ሬሳ እን እንደሚገላገለው ነው የሚያስበው፡፡ ሬሳውን ለማየት መንገድ ሲጀ ‹‹ምነው እሱ ባልሆነ›› እያለ ሲጸልይ ነበር፡፡እሱ ካልሆነ ሴት ተገላግሉ ወደ ልምምዱ ይሄዳል፡፡ አሁን ግን የተባለው ሬሳ እሱ ተገኘ፡፡ ደግሞም እኮ ገበዝ ኳስ ተጨዋች መሆኑን ያው ለመጨረሻ ግዜ ያየው ከሁለት በወር በፊት ማዘጋጃ ሜዳ በተ የፍጻሜ ጨዋታ ነው፡፡በእዚያን ቀን እንቅስቃሴውና ባገባቸው ጎ በጣም ነበር ያደነቀው፡፡ ከዚያ ወዲህ የትም ሳያየው ዛሬ ሬሳ እየተመለከተው ነው፡፡ልጁ ኳሱን እርግፍ አድርጎ ከኢህአፓ ተጋብቶ ትምህርቱንም ትቶ ተጠቃሉ ገብቷል፡፡

ደግሞም በጣም አደገኛ ሆኖ ከቀበሌው አልፎ በየቡ እየተፈለገ መሆኑን ሰምቷል፡፡መገደሉ ቢያሳዝነውም አንድ ቀን ይ ወሬ እንደሚሰማ ይገምት ነበር፡፡ እናም ቀኑ ዛሬ ሆኖ አገ በችሎታው ስለሚደነቅ እሱ ክለብ እንዲገባ ደጋግሞ ጠይቆት ነበ ዛሬ ግን ሲመለከተው እንኳን እኔ ጋር አልመጣ ይሄኔ እ ጠቀምብኝ የእኔም ሬሳ እሱ ጎን ይገኝ ነበር ብሎ አሰበ፡፡ግን አወደ አይቶ በጣም አዘነለት፡፡ሳይታወቀው ‹‹እነዚህ ሰዎች ወጣቱን ጨረ ››አለ፡፡ ከቦታውላይ ራቅ ብሎ ሄደ፡፡አጠገቡ ያለውን ልጅ ተመለከተ እዚሁ ቀበሌ እሱ የሚያሰለጥነው ልጅ ነው‹‹ወይኔ እና ያብዳሉ››አለ፡፡እንደ አይን ብሌናቸው የሚንከባከቡት አንድ ልጃቸ ከተገደለ ሴትየዋ ሞታቸው ቅርብ ነው፡፡አሁን ጉዳዩ እ ስለመጣችው የቢቢሲዋ ሴትዮ ልጅ ሬሳ ነው፡፡

እንደገና ፊቱን ወደዚህ አዞረና ሬሳዎቹን የሚጠብቅ ሰ እንዳለ ዞር ዞር ብሎ ተመለከተ፡፡አንድ ሰው ብቻ ነው ያለው፡፡አብዮ ጥበቃ ነው፡፡ በርቀት በደምብ ልብሱና በመሳርያ አያያዙ ነው ያወቀው አንድ መሆኑ ደስ አለው፡፡ አሁን ለማከናውን ያሰበው ነገር ከቃው እዛው ከሬሳዎቹ ጋር እንደሚደፉት አልጠፋውም፡፡ እናም አንድ ዘ መጠቅም አለበት፡፡ እሱ ምንም ነገር ውስጥ እንዳሌለበት አድ መስራት አለበት፡፡ ማስረጃ በምንም አይነት ነገር መገኘት የለበትም ፈጠን ብሎ ወደ ሴትየዋ ሄደ፡፡ ጀርባውን ለሰውየው ሰጥቶ ‹‹ያ ሰው ይታይሻል››አለ





‹‹የቱ?››
‹‹በርቀት ከጀርባዬ መሳርያ የያዘው አብዮት ጥበቃ!!!››
‹‹አዎ››
‹‹እኔ አናግረዋለሁ››
‹‹ይሰጠናል?››
‹‹ትቀልጃለሽ እንዴ››
‹‹ምነው?››
‹‹እሱ እኮ ሬሳ ለመጠበቅ ነው የቆመው እንዴት ይሰጥሻል››
‹‹ታድያ ለምንድነው የምታናግረው?››
‹‹አናግረዋለሁ አልኩሽ››
‹‹ካናገርከው በኋላ መውሰድ እችላለሁ?››
‹‹አዳምጭኝ እንደርሱ አይደለም ››
‹‹እና››
‹‹ፊቱን ወደዚያ እንዲዞር አደርጋለሁ››
‹‹ከዚያስ?››
‹‹አንቺ ይዘሽ ትሮጫለሽ››
‹‹ብቻዬን››
‹‹ቶሎ ብለሽ ሰው ፈልጊ››
‹‹ከየት?››
‹‹እኔ ምን አውቃለሁ››
‹‹ጎረቤቱን ልጥራት››
‹‹ማንም ይሁን ግን››
‹‹ግን ምን››
‹‹ታማኝና ሚስጥረኛ ነው የሆነ ሰው ነው የምፈልገው››
‹‹እሱን ለኔ ተወው ትንፍሽ የማትል......››

ሴትየዋ በፍጥነት ወደ ቤት ሄዳ ጎረቤቷን ይዛ መጣች፡፡ ብርሀኔ ሻይ ቤት ውስጥ ሲጠብቃት ቀይቶ ተገናኙ፡፡ ስራው ሊጀመር ነው፡፡ ምን ያህል ደቂቃ ከሰውየው ጋር ሊቆይ እንደሚችል ነግሯቸው እነርሱ በእድሉ እንዲጠቀሙ አስረድቷት ተለያዩ፡፡አንድ ችግር ቢፈጠር እዚህ ነገር ውስጥ እንደሌለበት ነግሯታል፡፡ ደግሞም አበክሮ አስረድቷታል፡፡ በተቻለ ሁኔታ መፍጠን እንዳለበት አስጠንቅቋታል፡፡

ሰዎች ከመሰብሰባቸው በፊት ነገሩ መከናወን አለበት፡፡ አሁን ግ
ብዙም ሰው ብቅ አላለም፡፡ የነበሩትም ትኩረታቸው አስፓልት
ባሉት ላይ ያተኮረ ይመስላል፡፡ ብርሀኔ በሌላ አቅጣጫ አድርጎ
አብዮት ጥበቃው ሄደና ከኋላው ሆኖ ‹‹ጓድ እንደምንድነህ?››አለ

‹‹ሰላም ነኝ››

‹‹አወቅከኝ?››

‹‹አላወቅኩህም››

‹‹ብርሀኔ እባላለሁ››

‹‹ስፖርት ነው?››

‹‹የቀበሌው የስፖርት አሰልጣኝ ነኝ››

‹‹እና››

‹‹አሁን ደግሞ የከፍተኛው የማስ ስፖርት እንዳስለጥን ተመርጫለሁ››

‹‹የእኛን››

‹‹አዎ››

‹‹ጥሩ ነዋ››

‹‹ሴትየዋ ምንነካት ››በሚል ስጋት ውስጥ ገብቷል፡፡ በአብዮት ጥበቃው ትከሻ አሻግሮ እየተመለከተ ነው፡፡በቅርብ ርቀት ሆና ከሬሳው ጋር ተፋጣለች፡፡ ብርሀኔ ወሬው እያለቀበት ነው፡፡የራሷ ጉዳይ ብሎ ትቶ ለመሄድ ተዘጋጀ ፡፡ይሄ ደግሞ አደገኛ ነው ብሎ አሰበ፡፡ ትቶ እንደሄደ ሴትየዋ ሬሳ ስታነሳ ሰውየው ካየ እዚያው በትኩሱ ተጠቁሞበት ችግር ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡

ሬሳው እናቱን ያደነዘዛት ይመስላል፡፡ ምናልባት አተኩራ ስታየው የእሷ ልጅ መሆን ያለመሆኑን እያረጋገጠች ያለ ይመስላል፡ ቅድም እሱ በፍጥነት በሚራመድ ሁኔታ ነው የተመለከተው፡፡ እርሱ መሆኑን አይቷል፡፡ግን እርግጠኛ አይደለም፡፡በህይወት ያለ ሰውና ሬሳ አንዳንድ ግዜ ሊለያይ ይችላል፡፡እሱ ካልሆነ ቶሎ ትታ መሄድ አለባት፡ ያን ግዜ እሱም ወሬ ስለጨረሰ በፍጥነት በአንድ ነገር ወሬውን ቋጭቶ መሄድ አለበት፡፡ ሴትየዋ ወደ ሬሳው ተንቀሳቀሰች፡፡ ብርሃኔም ሰውየው እንዳይዞርበት በፍጥነት እዛው ገትሮ መያዝ አለበት፡፡ ብርሀኔ ለአብዮት ጠባቂው ‹‹አሁን ለምን መሰለህ ወዳንተ የመጣሁት››አለው





‹‹ንገረኛ››

‹‹የስፖርት ሜዳውን ታውቀዋለህ››

‹‹የትኛው?››

‹‹ትልቁ››

ሴትየዋ በፍጥነት ከጓደኛዋ ጋር ሬሳውን ብድግ አደረጉ፡፡ አብዮት ጥበቃው ፊቱን ለማዞር ተንቀሳቀሰ፡፡ ይሄን ግዜ በፍጥነት ወሳኝ ወሬ ላይ መድረስ አለበት፡፡ሬሳው የከበዳቸው ይመስል ተንገዳገዱ፡፡ አብዮት ጥበቃው አሁንም መሳርያውን እንደያዘ ዘወር ብሎ አካባቢውን ለመቃኘት ያሰበ ይመስላል፡፡ ትከሻው የነገረው ይመስል ድንገት ዞር አለ ፡፡ሴቶቹን ሬሳው እዛው ጠፍሮ የያዛቸው ይመስል ቆመዋል፡፡ቆመውም ፎቶ የሚነሱ መስለዋል፡፡ብርሀኔ በድንጋጤ ወሬው ሁሉ እየጠፋበት ነው፡፡ ሰውየው አሁንም ዞረ ፡፡ እየዞረ ብርሀኔ ‹‹አሁን ችግር ላይ ወድቀናል››አለው

‹‹ማለት››

‹‹ልትረዱን ይገባል››

‹‹ምኑን?››

‹‹ሜዳውን ያዙብን እኮ››

‹‹የቱን?››

‹‹ትልቁን››

‹‹እነማን?››

‹‹እነዚያ ዱርየዎች››

‹‹ማን አልከኝ?››

‹‹ኢህአፓ የምትባለዋ››

‹‹ምን አደረጉ?››

‹‹ማታ ጎሉን አፈረሱብን፤መረቡና ኳሱን ዘረፉን››

‹‹መቼ?››

አሻግሮ ተመለከተ፡፡ ሴትየዋን ማየት አልቻለም፡፡ምክንያቱ ደግሞ ከአውቶብስ ተራ ጩኸት ተሰማ፡፡ አብዮት ጥበቃው አቀባበሉ፡፡ ማቀባበል ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ድምጽ ወደሰማበት አማተረ፡፡አብዮት ጥበቃው በሰማው ነገር ደነበረ፡፡ከዚህ በኋላ እዚህ ቆሞ የሚጠብቅበት

ሁኔታ የለም።ጎሉ ምንም አልሆነም፤ ሌላም እቃም አልተዘረፈም። ነገሩ ከመወሳሰቡ በፊት ከዚህ መሄድ አለበት። ከመሄዱ በፊት ለሰውየው ‹‹የት ብለን እናመልክት?››አለው

‹‹ምኑን?››

‹‹ሌባውን እንዳይዘርፉን እንዲጠበቅልን››

‹‹ቀበሌው ነዋ!!!››

‹‹እኛ ተደራጅተን ብንጠብቅስ?››

‹‹እሱ ደግሞ በጣም ጥሩ ነው››

‹‹ጓድ ሊቀመንበራችንን የት አገኛቸዋለሁ?››

‹‹ምን ማለትህ ነው?››

‹‹የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበራችን ማለቴ ነው››

‹‹ቢሮ ታገኘዋለህ››

‹‹የት ነበር ቢሯችሁ?››

ይሄ ወሬ አላለቀም። ምክንያቱ ደግሞ ከአውቶብስ ተራ ጀርባ ሀይለኛ ተኩስ ተከፈተ ።አብዮት ጥበቃው አቀባበለ።ማቀባበል ብቻ ሳይሆን ወደረ።አሁን እሱ ወድሮ እዚህ ቆሞ ማናገር ህይወትን አሳልፎ መስጠት ነው። ከሰውየው አጠገብ በፍጥነት ሄደ። ሄደ ብቻ ሳይሆን በጥፍሩ በሚቆም በሚመስል ሁኔታ ተፈተለከ። እየተፈተለከ ሴትየዋን በአይኑ ይፈልጋታል።። በዚያ አካባቢ አንድ መኪና ቀስ እያለ ስለሄደ ሴትየዋን ለመመልከት አለቻለም። አንድ ቦታ ቆሞ መመልከት ፈለገ። ይሄ ደግሞ ትኩረት ሊስብ ይችላል። ደግሞም በዚህ ሁኔታ ወደ እርሷ መመልከት አደገኛ ነው።ሴትየዋ ትውሰድ በተኩሱ መሀል ትሸሽ ምንም ያወቀው ነገር የለም።

ሴትየዋ በነጋታው ወደ ቤቱ መጣች ።ሲያያት ደስ አላለውም ችግር ተፈጥሮ እሱ ላይ ለመጠቆም የፈለገች ነው የመሰለው።ብቻዋን መሆኗን ተመለከተና ቆጣ ባለ ድምጽ ‹‹ደግሞ ምን ፈለግሽ?››አለ

‹‹ላመሰግንህ ነው››

‹‹ምን ስለሆነ››

‹‹ስለትላንቱ ነገር››

‹‹እኔ ምንም አላደረግሁም፤ ደግሞም የለሁበትም››





‹‹ብቻ አመሰግናለሁ››

‹‹ለመሆኑ ሬሳውን ምን አደረግሽው?››

‹‹ቀበርነው››

‹‹እቤት ውስጥ?››

‹‹አይደለም››

‹‹ታድያ የት.....››

‹‹ቤተክርስትያን››

‹‹እንዴት ተቀበሉሽ››

‹‹አጎቴ ነው ብዬ››

ብርሀኑ ነገሩ በጣም ገረመው ።ደግሞም አስፈራው።ሁለተኛ እሱ ጋር እንዳትደርስ ማስጠንቀቅ አለበት።።

ከስአት በኋላ እቤት መጥተው ቀበሌዎች እንደፈለጉት ተነገረው። ቀበሌው ከፈለገው ቶሎ መሄድ እንዳለበት ያውቃል። ከቀረ ካለበት ቦታ እየተነዳ እንደሚሄድ ያውቃል።ከዚህ በፊት ጓደኛው በቀበሌ ተፈልጎ ስላልመጣ ምግብ ቤት ከብርሀኑ ጋር እየተመገቡ ቀበሌዎች መጡ። ከነምግቡ ሰሃን ይዘውት ሲሄዱ ብርሀኑ ‹‹ምን አይነት ዘመን መጣ›› ብሎ እስከመገረም የደረሰበት ግዜ ነበር።አሁንም ካለበት መጥተው ከመውሰዳቸው በፊት በፍጥነት ቀኑ ሳያልፍ ጸሀይ ሳታዘቀዝቅ መሄድ ይጠበቅበታል።እንደደረሰ ትፈለጋለህ ከተባለበት ክፍልገባ። ብዙ ግዜ ለስፖርት ጉዳይ ስለሚፈልጉት ዘና ብሎ ገባ ‹‹ፈልጋችሁኝ ነበር?››አለ

‹‹አዎ፤ቁጭ በል››

‹‹እሺ››

‹‹ጠዋት ነበር እንድትመጣ የተፈለገው››

‹‹‹ለስፖርት ነው የፈለጋችሁኝ?››

‹‹አይደለም››

‹‹እና››

‹‹ሬሳ ጠፍቷል››

‹‹ሬሳ?››(አለቀልኝ)

‹‹አዎ››

‹‹የምን ሬሳ?››

‹‹ከሰው ሌላ የምን ሬሳ አለ›
‹‹ማለቴ ስላልገባኝ ነው››(ሴትየዋ ጉድ አደረገችኝ)
‹‹አይጠፋህም ብለን ነው››
‹‹አሁን ገባኝ››

ሴትየዋ ከባድ ጣጣ ይዛበት እንደመጣች ተረዳ።ፍርሃት መጣበት።ሊወረው ነው።፡መፍራት የለበትም ዘና ማለት ይጠበቅበታል። ከፈራ ያውቁበታል።ዘና ብሎ መዋሸት አለበት‹‹ሬሳ ስለጠፋ ልናናግርህ ነው ››አለው

‹‹ሬሳ ምን?››
‹‹ጠፍቷል አልንህ ››
‹‹እኔ እኮ አስልጣኝ ነኝ››
‹‹እናውቃለን››
‹‹ታዲያ ከሬሳ ጋር ምን አገናኘኝ››
‹‹የጠፋው ሬሳ ጋር ነበርክ››
‹‹እኔ?››
‹‹አዎ››
‹‹ብሆንስ!!››
‹‹ምን እያልክ ነው?››
‹‹እናንተ እራሳችሁ ሰውን ሬሳ ጋር አቁማችሁ መፈክር ታሰሙ የለ››
‹‹ቢሆንስ!!››
‹‹እኔም እዛ እንድገኝ ተደረገ››
‹‹አንተ እኮ ለማሻገር ነው››
‹‹እኔ ››
‹‹አዎ››
‹‹የት ነው የማሻግረው››
‹‹ለጸረ አብዮተኞች››
‹‹እነማን››
‹‹ለሴትየዋ››
‹‹ተሳስታችኋል››





‹‹ጠባቂውን ሰው እንዳይጠብቅ ፊቱን እንዲያዞር ማድረግህን ደርሰንበታል››
‹‹እና››
‹‹ከዚያ ሴትየዋ ሬሳውን እንድትወስድ አደረግክ››
‹‹ውሸት ነው››
‹‹በዚህ ድርጊትህ ትገባታለህ እስር ቤት››
‹‹እኔ እንደዛ አላደረግሁም››
‹‹ሴትየዋ መስክራብሃለች››
‹‹ምን ብላ››
‹‹እኔ ሬሳውን እሰጥሻለሁ ብለህ እንደተባበርካት››

ቃለ ምልልሱ እንደዚህ ሊሆን እንደሚችል ብርሀኔ ስለገመተ በደምብ መዘጋጀት እንዳለበት አመነ።ራሱንም ረጋ አደረገ።ብዙ ግዜ ከአንድ ሰው ጋ ለመሟገት ከፈለገ ሰውየውን በውስጡ አድርጎ ጥያቄና መልስ አዘጋጅቶ ከራሱ ጋር ተሟግቶ ከጨረሰ በኋላ ወደ ጉዳዩ ይገባል። እንዲህ አይነቱ ነገር ለብዙ ግዜ ስለረዳው ደጋግሞ ይጠቀምበታል። እናም ተሟግቶ ጨረሰና ዝግጁ ሆነ። የቀበሌው ሰውየው ‹‹ለማንኛውም ሬሳ ጠፍቷል››አለው

‹‹የት ጠፋ?››
‹‹አውቶብስ ተራ ነው››
‹‹ማነው የሰረቀው?››
‹‹እኔ እንጃ››
‹‹ታድያ እኔ ለምን ተፈለግኩኝ››
‹‹አንተ ሬሳውጋር ነበርክ አሉ››
‹‹እኔ››
‹‹አዎ››
‹‹አሁን ገባኝ››
‹‹ምኑ››
‹‹ተሰብሰቡ ተብለን ነው››
‹‹ማን››
‹‹አብዮት ጥበቃዎቹ››
‹‹ለምን?››

‹‹መፈክር ለማሰማት ነው››
‹‹አንተ ነበርክ የተባለው እኮ ከዚያ በኋላ ነው››
‹‹እኔን ራሳ ወስደሃል እያሳችሁ ነው እንጂ…››
‹‹እንዳዛ አይደለም››
‹‹እና ››
‹‹ብርሀኔ አይቷል ነው የተባልነው››
‹‹እኔ የነዚያ የማይረቡ ኢህፓዎች ራሳ ምን ያደርግልኛል››
‹‹አላውቅም››
‹‹ገዛም ብሉ ወቀሳ ነው››

ደርግ ከገደለ በኋላ ሬሳ ለቤተሰብ አይሰጥም፡፡ ደፋሮቹ ሰርቀው ይወስዱት፡፡ከስድስት ወር በኋላ ግን በቀላል ጉዳይ የገደሉትን የጥይት እያስከፈሉ እስኪሰጡ ድረስ መስረቁ ትልቅ አማራጭ ነበር፡፡

## እንደገና በጥቂት ቀን

የሴትየዋን ጉዳይ ጨርሶ መገላገሉን አውቋል፡፡ ግን አውቀ እንጂ ጉዳዩ ያለቀ አልነበረም፡፡ምን አይነት ነገር ይዛበት እንደመጣች የገባው ቆይቶ ነበረ፡፡ ሌላ ሴት እቤቱን አንኳኩታ መጣች ‹‹ግን ልበላ?››አለ
‹‹እዚሁ የሰፈር ሰው ነኝ››
‹‹እና ቀበሌ?››
‹‹አዎ››
‹‹የት?››
‹‹ቤታችሁ መንደር››
‹‹አላውቅሁሽም››
‹‹ብርግጥ አንተ አታውቀኝም››
‹‹ምን ፈልገሽ ነው?››
‹‹ሰው ልኮኝ ነው››
‹‹እኔ ጋር››
‹‹አዎ››
‹‹ምን ነበር››





‹‹ልጄን ገድለውብኝ ነው››
‹‹የት?››
‹‹እዚሁ ቀበሌ››
‹‹ማነው የገደለብሽ?››
‹‹ታውቅ የለ››
‹‹እና አሁን እኔ ……››
‹‹የልጄን ሬሳ እንድታስጠኝ ነው››
‹‹እኔ ሬሳ አዳይ ነኝ እንጂ››
‹‹ጎረቤቴ ነግራኝ ነው››
‹‹ተሳስታለች››
‹‹አልተሳሳተችም››
‹‹በምን አወቅሽ እኔ……››
‹‹ያኔ እኔንኝ ያገዙኳት››
‹‹ምኑን?››
‹‹የእሷን ልጅ ሬሳ ስትወስድ››
‹‹እኔ እንደረዳኋት በምን አወቅሽ››
‹‹ሰውየውን ስታናግረው ስላየሁ ነው››
‹‹የቱ ሰውየ?››
‹‹ሬሳ የሚጠብቀውን አብዮት ጠባቂ››
‹‹የዛን ቀን?››
‹‹አዎ››
‹‹እኔ እኮ ሰውየውን በሌላ ጉዳይ ነው ያናገርኩት››
‹‹ተው ባክህ እሷ ነግራኛለች››
‹‹ምን ብላ?››
‹‹የእሱ እቅድ ነው ብላ››

ብርሀኔ ጸጥ አለ፡፡ ግን ደግሞ በውስጡ‹‹አለቀልኝ›› ብሎ ተናገረ፡፡ይህችን ሴት በሆነ ነገር ዋሽቶ ካልሸኘ አብዮት ጠባቂዎችም መግደሉን አያቆሙም፤ እናቶች ደግሞ ሬሳ ለመውሰድ እኔ ጋር መምጣታቸውን አይተውም፡፡ይሄን ነገር ቶሎ መዝጋት አለበት፡፡በዚሁ ከቀጠለ ለእርሱ አደጋ ነው፡፡የዚህችንም ሴት ጉዳይ ማስተናገድ

እንደሌለበት አምኗል። ቶሎ ብሎ ወደ ቢቢሲዋ ሴትዮ ቤት ሄደ ።
እንደደረሰ በቁጣ ‹‹ምን እያደረግሽ ነው?››አለ

‹‹ምን››

‹‹ለሰው መንገር ነበረብሽ?››

‹‹እኔ ለማንም አልነገርኩም››

‹‹አትዋሽ!!››

‹‹ምን አስዋሸኝ››

‹‹ጎረቤትሽ ነገረችኝ››

‹‹ምን ብላ?››

‹‹ሬሳ አሰጠኝ ብላ››

‹‹እና››

‹‹ለምን ነገርሻት››

‹‹አልነገርኳትም ያኔ ልትረዳኝ ተገኝታ ነበር››

‹‹አሁን እኔ ጋር መጥታ ነበር››

‹‹ለምን?››

‹‹ልጇ ተገድሎ ነው››

‹‹የእሷ ልጅ?››

‹‹አዎ››

‹‹አልመሰለኝም››

‹‹እንዴት?››

‹‹እኔ ማወቅ ነበረብኝ››

‹‹ምን ማለት ነው! እሷ ልጅ የላትም እንዴ?››

‹‹ጨርሳለች››

‹‹ጨርሳለች ማለት ምንድነው?››

‹‹ሁለት ነበራት››

‹‹እና››

‹‹ከሶስት ወር በፊት ሁለቱንም ገድለውባታል››

‹‹ታድያ ለምን መጣች››

‹‹ለእርሷ አይደለም››

‹‹ለእሷ አይደለም ስትይ ምን ማለት ነው››

‹‹በቃ!! ለእሷ አይደለም››





‹‹እንዴት እርግጠኛ ሆንሽ››

‹‹ለሌላ ሰው ነው››

‹‹ሌላ ሰው ስትይ››

‹‹የእናቶች ነገር ታውቅ የለ››

‹‹ማለት ››

‹‹የልጆቻችን ሬሳ ወድቆ ስናይ ያንገበግበናል››

‹‹እኔ እራሴን ሰውቼ እንደረዳሁሽ ታውቂያለሽ››

‹‹አዎ።አመስግንሃለሁ››

‹‹ታድያ ለምን አትረጂኝም››

‹‹ምኑን››

‹‹ይሄ ነገር እየሰፋ ሊሄድ ነው››

‹‹እና››

‹‹ይህችን ሴትዮ አስታግሽልኝ››

የቢቢሲዋ ሴትዮ ጎረቤቷን ይዛ መጣችና እውነቱን ለብርሀኔ እንድትነግረው አስደረገች። ነገር ግን ሌሎች እናቶች እየተቀባበሉ ስለነበር ድጋሚ ስላለመጠየቃቸው እርግጠኛ አልነበረም።በጥዋት እቤቱ በር ሲንኳኳ የማያውቀው ሰው ከሆነ የለም ያስብል ጀመር።

## ምዕራፍ 7 አርስቶው

እስረኛው እዚህ ክፍል ሲመጣ ለሁለተኛ ግዜ ነው። ባለፈው ግዜ በተደረገው ግጥሚያ እግሩን እንዳልነበረ አድርገውታል። በደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ ሰውነቱን ከታትፈውታል። እግሩን እንዳልነበረ ስላደረጉት ቆሞ መሄድ አቅቶታል። ውስጥ እግሩ ተተልትሎ ሰንፍ ገበሬ ያረሰው መሬት ይመስላል። እግሩ በየቦታው በስለት ስለተቆራረጠ ትንሽ ነገር ሲነካው ስለሚያመው ልብስ ፊርቶ በውስጥ ሱሪ ብቻ ይቀመጣል።መ ቀመጫው ላይ ሳይቀር ገልበው ስለገረፉት ቁስል በቁስል ሆኗል እናም መራመድም ሆነ መንፏቀቅ አይችልም። ወደ ሽንት ቤት መሄድ የሚችለው በሽክም ነው። መቀመጥ ስለማይችል ጎኑን ነው እንደመቀመጫ የሚጠቀመው። ቁስሉ በየቦታው እንደበር ተከፋፍቶ ለዝንብ አዲስ ምግብ ቤት የተከፈተላቸው ይመስላል። የታሰረበት ቦታ ዝንቦች ስለሚበዙ ስቃዩን አሳይተውታል።

ዛሬ በወጣው ፕሮግራም ምሽት ላይ የእሱ ተራ በመሆኑ ጓደኞቹ ወደ መገረፊያው ክፍል እንደታዘዙት በሽክም አምጥተውታል፡ በርላይ ካ.ጋደሙት በኋላ በጎኑ እየተንፏቀቀ እንዲገባ ተነገረው። ገራፊዎቹ በቁጣና በከፍተኛ ዝግጅት እየጠበቁት ነው።ዋናው ገራፊ ኮቱን እያወለቀ ነው ።ሌላኛው ደግሞ በስፖርት ቁምጣ ነው የመጣው።ሰዎቹንና የቤቱን ዝግጅት ተመልክቶ የዛሬው ግርፊያ የዋንጫ እንደሆነ ገምቷል። ማውጣጣት አልቻላችሁም ተብለው ስለተወቀሱ ማንነታቸውን ማሳየት እንደፈለጉ አውቋል። እስካሁን እዚህ ቤት ከተገረፉት ውስጥ ውሃ የሚያነሳ መረጃ አላመጣችሁም ተብለው ስለተወቀሱ የአገራረፍ ስልታቸውን መቀየርና ከፍ ማድረግ እንዳለባቸው ከንግግራቸው ሰምቷል።እናም በእርሱ ላይ እየዛቱበት ነው።





ከመሬት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በጎኑ በኩል በመሆኑ አሁንጎኑን በስለት ተልትለውና ገርፈው ምንም አይነት መርገጫ እንዳያገኝ እንደሚያደርጉት ነግረውታል። ይሄ ከመሆኑ በፊት ግን ስም ከሰጣቸው ምንም ዱላ ሳይነካው ህክምና ተደርጎለት እንደሚሄድ ነገሩት። እሱ ግን ዝምታ ነው የመረጠው። እናም ድብደባውን ከፍ እንደሚያደርጉ የተስማማ ይመስላል። ከእርሱ ጋር በመነጋገር ግዜ ማጥፋት እንደሌለባቸው ስላወቁ ወዲያውኑ እጅና እግሩን አስረው በታስረው መሀል ትልቅ አጠና ከትተው በሁለቱ ቋሚ እንጨቶች መሀል አስገብተው ከፍ አድርገው አንጠለጠሉት። ከአንደኛው ጠረጴዛ አጠገብ ትንሽ ጠረጴዛ አለች አጠገቧ ወንበር ይገኛል።ቁልቁል ተዘቅዝቆ እንደተንጠለጠለ ለጥቂት ደቂቃ አቆዩት። ከሰዎቹ እግር አጠገቡ ትንሿ ጠረጴዛ ላይ ከሚታየው ወረቀት በስተቀር ምንም አይመለከትም።ወረቀቱ ላይ የስም ዝርዝር ይታያል። ርእሱ እርምጃ የሚወሰድባቸው ሰዎችን ዝርዝር የያዘ ነው።ሰዎቹ ሳያናግሩትና ግርፊያውን ሳይጀምሩ ለጥቂት ደቂቃ ስላቆዩት ወረቀቱ ላይ ያለውን ስም ለማየት እየሞከረ ነው። ስለተገለበጠ ፊደሎቹን በደምብ መያዝ ባይችልም ከላይ ያሉትን ማወቅ ችሏል።

ሰለሞን ሀይሌ የሚለው ስም ግን አልገባውም። እርሱ ከሳምንት በፊት ከዚህ ተወስዶ ተገድሏል። አሁን እንዴት እዚህ ሊስት ውስጥ ሊገባ ቻለ?እንደገና ሌላ ስም አነበበ። ዳኜ የተባለውን ልጅ ስም አየው ።አሁን በሽክም አደርሶት የሄደው ልጅ ነው።እርሱም ሞት ዝርዝር ውስጥ መካተቱ ገርሞታል።እሱ ተገርፎ ተገራርፎ ጉዳዩን ጨርሰው ፋይሉ የተዘጋ ነው።ይፈታል ተብሎ እየተነገረለት ነው።የሌሎቹንም ስም ለመመልከት ሞከረ። ርቆበታል።ሰይድ ይሁን ሰይፉ መለየት አቃተው እንጂ እንዲህ አይነት ስም እየታየው ነው። ትንሽ ወደዚያ ፎቀቅ ቢል ስምንት ወይም አስር ስም ማየት ይችላል፡ ፡ግን ደግሞ የሆነ ነገር ጠረጠረ ።ሆን ተብሎ እነዚህን ስሞች እንዲመለከት ለማድረግ ታስቦ ይሆን? ምናልባትም ከግርፍያ በኋላ ወደ ክፍሉ ሲመለስ ያየውን ሌሎቹ መንገሩ ስለማይቀር በቀጣዮቹ ተገራፊዎች ላይ ፍርሃት እንዲለቅ ለማድረግ ታስቦ የተሰራ ሊሆን እንደሚችል ገመተ ።ደግሞም ተጠራጠረ።እንዲህ አይነት ረቀቅ ያለ

በስንልቦና የሚደረግ ጨዋታ ደርግ እንደማያስብ ይገምታል፡፡ ሩቅት ያለና ውስብስብ ነገር ኢህአፓ ጋር ብቻ ነው የሚኖረው ብሎ ያስባል፡፡

ያም ሆነ ይህ ይሄ የተመለከተው ወረቀት ስጋት ውስጥ ከተተው፡፡አሁን ሞት በትክክል ወደ እርሱ እንደመጣ አወቀ፡፡ በነጩ ወረቀት ላይ ሞት ተቀምጦ ተመለከተ፡፡ ደግሞም እንደ ቆርጦ የገባበት በመሆኑ ሞትን መፍራት እንደሌለበት ለራሱ አሳመነ፡፡ ራሱን እያሳመነ መፍራቱ ግን አልቀረም፡፡የፈራው ኢህአፓነቱ ሳይሆን ሰውኛ ነገሩ ነው፡፡ሰዎቹ ተመካክረው የጨረሱ ይመስል ተገልብጦ ወደተንጠለጠለው እስረኛ እየተጠጉ ቀረቡት፡፡ ጨዋታው ሲጀመር በመሆኑ በስንልቦና ዝግጅት ማድረግ አለበት፡፡ግን እንዳለፈው ግዜ ስለትና ዱላ አልያዙም ፡፡አላመጡም ሳይሆን በእጃቸው ላይ የለም፡፡ ምን ችግር አለ?፡፡

እዚህ ክፍል ካለው ሳጥን ውስጥ ጉጡት፣ስለትና ፒንሳ ሌሎችም መከተታፊያ ነገር ስላላቸው ለፈለጉት ስራ አስፈላጊውን መሳርያ ይጠቀማሉ፡፡ አንደኛው ሰው ጎንበስ ብሎ እየተመለከተው፡፡

‹‹ፈቃድህን ልጠይቅ ነው››አለ

‹‹የምን ፈቃድ?››

‹‹ዱላ እንጀምር ወይስ..››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ተባበርከን እንድንመታህ አልፈቀድክም ማለት ነው...››

‹‹ምንድነው የምተባበረው?››

‹‹የሁለቱን ጓዶች ስም ስጠን››

‹‹አላውቃቸውም››

‹‹ስለዚህ ዱላ እንድንጀምር ፈቅደሃል ማለት ነው››

‹‹እንደዛ አይደለም››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹ሰውነቴን ጨርሳችሁታል እኮ››

‹‹የተረፈውን እንዘጣጥስልሃለን››

የሁለቱን ሰዎችስም መስጠት እንዳለበት ያውቃል፡፡ ደግሞም ከውጭ ያሉት እለቶቹ የላኩበትን ነገር አስታወሰ፡፡አሁን ከመገረፉ





በፊት ስም ከሰጠጥርጣሬ ሊያድርባቸው ይችላል፡፡አንድ ሁለቴ ዱላ ካረፈበት የሁለቱን ስም ይሰጣል፡፡ስማቸውንም በደምብ አስታውሶታል፡ ፡ስማቸው እንዳይጠፋውከጠዋት ጀምሮ ሲያጠናው ቆይቷል፡፡ ጨዋታው እስኪጀመር ብቻ እየጠበቀ ነው፡፡በስንተኛው ደቂቃ ስሞቹን መስጠት እንዳለበት እያሰላ ነው፡፡ስማቸውን ስጠን እያሉ ብዙ ወተወቱት፡፡ እርሱ ግን አላውቃቸውም ከሚል በስተቀር ትንፍሽ አላለም፡፡ለጥቂት ግዜ ዝምታ ሆነ፡፡እዚህ ነገር ውስጥ እጁ እንደሌለበትና ሰዎቹን እንደማያውቃቸው ገራፊዎቹ የተማመኑ ይመስላል፡፡አንዳንድ ግዜ ለግርፊያገብተው ተስላችተው ወይም ሰውኛ ባህሪያቸው መጥቶ እስረኛውን ለኪኩፈው ወደ ክፍሉ የሚመልሱበት ግዜ እንዳለ ሰምቷል ፡፡ግን እንዲህ አይነቱን ወሬ ማመን ያቅተዋል፡፡

በየቀበሌው የግርፍያ ውድድር ያለ ይመስል እነ እከሌ እኮ በስራቸው የተዋጣላቸው ናቸውተብሎ እንደሚነገርላቸው ሰምቷል፡፡ እዚህ ቀበሌ ከሁለት ወር በፊትበአብዮታዊ ተሳትፎ ተብሎ ከተሸለሙት ውስጥ ገራፊዎች እንደሚገኙበትያውቃል ፡፡በግርፊያ ማውጣጣት አልቻሉም ተብለው ከሀላፊነታቸው የተነሱ እንዳሉ አይጠፋውም፡፡እናም የተዋጣለት ገራፊነት በአብዮቱ ውስጥ ትልቅ ሚና እንዳለው ያውቃል፡፡እነዚህ ሰዎች አዝነው እንደማይተውት አይጠፋውም፡፡ታድያ ለምን ዝም አሉት?፡፡ብዙ ግዜ እንደሰማውም እሱም እንደደረሰበት ከጥያቄው በኋላ ወዲያውኑ ነው ግርፍያ የሚጀመረው፡፡ታድያ አሁን ጥያቄው አልቋል ዝምታው ምንድነው ብሎ አሰበ፡፡ትንሽ ቆይቶ የተቀጣጠለ ከሰል ወደ ክፍል ውስጥ ሲገባ ተመለከተ፡፡ከሰሉን በምድጃ ይዞ የገባው ሌላው ገራፊ ነው፡፡ገራፊዎቹ ደረጃ አላቸው ፡፡አንደኛ ፣ሁለተኛ እያለ ይቀጥላል ፡፡

ይሄኛው ሶስተኛ ገራፊና ጫሂ ነው፡፡ሲገርፍ እየጮኽበህ ስለሆነ ያደናግርሃል፡፡አንደኛው ገራፊ ከሩስያ እንደመጣ ሰምቷል፡፡በፖለቲካ ትምህርት ስም የሄዱት ብዙ ገራፊዎች እንደነበሩ ያውቃል፡፡ሩስያዎች በግርፍያና በማውጣጣት የተካኑላቸው በመሆኑ ደርግ እዚያ ያስተማራቸው ሰዎች እንዳሉ ያውቃል፡፡ አንደኛው ገራፊ ከዚያ የመጣበመሆኑ ገራፊም አስተማሪም ነው፡፡ሶስተኛው ገራፊ ከሰሉን በካርቶን እያራገበ በደምብ እያከሳሰለ ነው፡፡ገራፊዎቹ የተሰቀለውን

ሰው መጎረፋቸውን ትተው እራት ሊበሉ እንዳሰቡ ገብቶታል።ሆቴል መሄድ ይፈራሉ መባሉን ሰምቷል። በጣም ተጠራጣሪ ናቸው።ምግብ እያስመጡ እንደሚበሉ ያውቃል።መጠጥም አስመጥው ሞቅ አድርገው ለግርፍያ እንደሚጠቀሙበት አይቷል።ማየቱ ብቻ ሰይሆን የመጠጡ ሽታ ቤቱን አውዶት ነበር።ምግብ ከማስመጣት ይልቅ እዚሁ መስራት መጀመራቸው ገርሞታል።እራት ሰርተውና በልተው እስኪጨርሱ እዚሁ ተዘቅዝቆ መቆየቱ ግራ አጋብቶታል፤ከሚገርፉት መንጠላጠሉ ይሻለዋል።ግን ስም መስጠት እንዳለበት አልጠፋውም። ይሄ ደግሞ ደግሞ ግዴታ ነው።እራት የመስራቱ ነገር ሊቀጥል ነው።

ከመሀላቸው አንዱ ንበዝ ሼፍ እንደሆነ አይጠፋውም።ከሰሉ በደምብ ፍም ሊሆን ድስቱን እሳቱ ላይ ጣደው።በትልቅ እቃ ውስጥየነበረውን ዘይትወደ ድስቱ ጨመረበት፤ ዘይቱ እንደሚያንስ እየተነጋገሩ ተመጥና ተጨመረ። ለእራት የሚያዘጋጁት ወጥ ያለ ሽንኩርት በዘይት ብቻ ሊሰሩ ነው ብሎ አሰበ። ሽንኩርት ለወጥ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃል።ሰዎቹን ወጥ በመስራት ቢረዳቸው ደስ ባለው ነበር። እሪፍ ወጥ ቢሰራላቸው ከተንጠለጠለበት ሊያወርዱትና ግርፍያውም ሊቀርለት ይችላል።እናትዬው የምግብ ስራ ሙያ በደምብ አስተምረውታል ።እድገት በህብረት ዘመቻ በመመደቡ ችግር እንዳይገጥመው ሁለት ወር ሙሉ ምግብ ስራ እናቱ ጎን ቁጭ ብሎ በተግባር ተምሯል። ሌሎች በሰሩት ምግብ እርካታ ስለሌላቸው በራሱ ሰርቶ እንዲበላ አስተምረውታል። ለሙከራም ደጋግሞ ሰርቶ እናቱንና እህቶቹን ጭምር እጅ የሚያስቆረጥም ባይሆንም የተመሰከረለት ወጥ እንደሚሰራ አሳይቷቸዋል። እነዚህ ገራፊዎች ወጥ ስራ ስላልተማሩ እንዴት መሰራት እንዳለበት አልገባቸውም።

ሽንኩርት ተቁላልቶ ዘይት ገብቶ ከዚያም ሽሮ ወይም ስጋ አለዚያ ድንች ገብቶበት የወጥ ስራው ይቀጥላል።ከሚገርፉት ወጥ ቢያሰሩት እሪፍ እራት ሊያበሉቸው ይችል ነበር።አሁን የእግሩ ሁኔታ እያሳሰበው ነው።የእግሩ መዳፍ ተተልትሎ ቆዳው እየተገፈፈ ነው። ከዚህ በኋላ በዚህ እግሩ ተመልሶ ኳስ እንደማይጫወት ቢያውቀውም የሼፍነት ሙያ አጠንክሮ መቀጠል እንዳለበት አምኗል።እናቱ ያስተማሩት እራሱን እንዲመግብ ቢሆንም ለስራ ይጠቀምበታል።ከዘመቻ ከተመለሰ





በኋላ በድርጅቱ ስራ ውስጥ ሲሳተፍ በደርግ ተፈላጊ በመሆኑ ቤት ውስጥ ከጓደኞቹ ጋር ነው ተደብቆ የሚያሳልፈው። እዛም ምግብ የሚሰራላቸውም እርሱ ነው። በሙያው ይገረሙበታል። እነሱም ሙያህን ተጠቀምበት እያሉ ይመክሩታል። ዛሬ ግን እዚህ በተንጠለጠለበት ቦታ እየተሰራ ያለው ምግብ ቀሽም እንደሆነ ገምቷል፡

ዘይቱ ይሄን ለብዙ ሰዓት መቆየቱ ምናልባት አሮስቶ ሊጠብሱበት ካልሆነ በስተቀር ይሄን ያህል ደቂቃ እያንተከተኩ መሆኑ ትክልል አይደለም ብሎ ለራሱ ተናገረ። እንዲህ ስቃይ ባለበት ቦታ ስለምግብ ስራ ማሰቡ ምን ማለት እንደሆነ ግራ ገብቶታል። ድስቱ ላይያለው ነገር መንተክተኩ በርከቶ ቤቱ በዘይት ሽታ ታውዷል። በወረቀት የተጠቀለለ ነገር አይቷል። ስጋ ነው ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም። ዘይቱ ላይ ስጋ ሊጨምሩበት መዘጋጀታቸው ገብቶታል። በእሱ ፊት እራታቸውን እየበሉ ሊያስጎመጁት ነው።እንዲህ አይነት ነገር ሰምቶም አያውቅም። ገራፊዎች እስረኛ አንጠልጥለው እራት መብላታቸው አዲስ ነገርነው።ስጋ ሊሰሩ ነው ብሎ አምኗል።። ምናልባት ሽሮ ሊሆን ይችላል። ይሄን ያህል ደቂቃ ዘይት ተንተክትኮ ሽሮ መጨመሩ አግባብ እንዳልሆነ አመነ። ሽሮ ከገባ ሲንተከተክ ሊመለከት ነው።60 ደናሽ አንድ አማሽ ሊሆን ነው። ሽሮ እየተንተከተከ ሲደንስ ማመስያው ውስጥ ገብቶ ያምሳል።

እስረኛው የሚሰሩት ወጥ ለማየት እየጠበቀ ነው።ከእራት በኋላ የእሱ እጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን አሰበ።ይለቁታል ወይስ ይገርፉታል?። ተንጠልጥሎ እረፍት ማድረጉን አልጠላውም። ወገቡ ሊሰበር ምንም አልቀረውም።በጣም ጠፍረውና ወጥረው ስላሰሩት እያመመው ነው። ግን መቻል አለበት።ገራፊው ሼፍ እስካሁን ዋናውን ነገር አልጨመረም። መቼም እንጀራ በዘይት አይበሉም። ሼፉ እየተንተከተከ የነበረውን ዘይት ክዳኑን ከፍቶ እያየ ‹‹ደርሷል››አለ

‹‹እርግጠኛ ነህ››

‹‹አዎ››

‹‹በደምብ ተንተክትኳል››

‹‹ይበቃዋል››

‹‹ለምን?››

‹‹ዘይቱ የተለየ ነው››

‹‹እንደዛ ነው››

‹‹አዎ ደግሞም ለእስረኛው ጥሩ እራት ነው››

እስረኛው ግራ ገባው፡፡ እሱንም እራት ሲጋብዙት ነው እንዴ፡፡ዘይቱ አሁንም በጣም እየተንተከተከ ነው፡፡ጎርጎድ ባለ ትልቅ ጭልፋ ቀዳ ወደ እስረኛው መጣ፡ስለተዘቀዘቀ ምን እየተደረገ እንደሆን አሳየውም ፡ለአለቃው ዘይቱ መንተክተኩን ለማሳየት እየመጣ እንደሆን ነው የገመተው፡፡ምናልባት ጣዕሙን እንዲያሽትለት ይሆናል፡፡ ድንገት ቤቱ ውስጥ ከፍተኛ የታፈነ ድምጽ ተሰማ፡፡ ዘይቱ ለምን ስራ እንደተፈለገ አሁን ገባው፡፡ እራት የሚያደርጉት እሱን ነበር፡፡ በተሰነጣጠቀውና በቆሰለው የተገለበጠ እግር ላይ የፈላውን ዘይት ሲጨምሩ ተስፈንጥሮ ለማምለጥ በሚመስል ሁኔታ ከእንጨቱ ላይ ምንጭት አለ፡፡ ግን የትም አልሄደም፡፡ ሁለተኛው ዘይት ሌላኛው ቁስሉ ላይ አፈሰሰበት፡ ያን ግዜ ህሊናውን ሳተ፡፡ ቆይቶ ግን ነቃ፡፡ቤቱ እሮስቶ የተጠበሰበት ይመስል ሸቷል፡፡ የምትናገረው ካለ ሌባ ጣትህን አውጣ ብለውታል፡ አሁን ግን የሁለቱንም እጆች ሌባ ጣት ነው ያወጣው፡፡‹‹ስማቸውን ትሰጠናለህ››አለው

‹‹ደበበ››

‹‹ሌላኛውስ››

‹‹ደጀኔ››

እንደ እሮስቶ ከጠበሱት በኋላ ስም ስላገኙ ደስ አላቸው፡ ዘይት በደምብ ያውጣጣል ብለው በስራቸው ተደሰቱ፡፡ ዛሬ ጠዋት ከኢህአፓ አለቆቹ የመጣለትን መልእክት አስታወሰ ፡፡እነዚህ ሁለት ልጆች ከጨዋታ መውጣታቸው ተነግሮታል፡፡ ሁለቱም በከፍተኛ አንድ ውስጥ ትላንትና ተገድለዋል፡፡ ስለዚህ ይሄን ስም ቢሰጥ ከግርፍያ ብዛት ሊተርፍ ይችላል፡፡ እናም ስሞችን ሰጠ ፡፡ግን በዱላ መስሎት ዘይቱ ብዙ ጉዳት አደረሰበት፡፡ ኢሳያስ(ስሙ የተቀየረ) እንደእሮስቶ ከተጠበሰ በኋላ የበሰለ ስጋ በልቶ አያውቅም፡፡የእሱንስጋ





ጠብሰው የሚያበሉት ነው የሚመስለው፡ በተለይ ቤቱም ሆነ ሌላ ቦታ የሚጠበስ ነገር ሲሸተው ግርያፊው ትዝ ይለዋል፡፡

## እንደገና ወደ ኋላ

ኢሳያስ እየተገረፈና እየተጠበሰ በነበረ በግድያው አልሳተፈም፡፡ እነማን እንደገደሉ አይጠፋውም፡፡ ገዳዮቹም አልተያዙም፡፡የት እንዳሉ ያውቃል፡፡እነዚህ ስኳዶች ድርጅቱ የሚተማመንባቸው ሰዎች ናቸው፡፡ እነማን እንደሆኑ ሊናገር ይችላል ፡፡ግን አያደርገውም፡፡እየተገረፈ ያለው በማያውቀው ጉዳይ ነው፡፡እሱ የገደለው ሌላ ሰው ነው፡፡ ተገዳዩ ብዙ የኢህአፓ አባላትን እየጠቆመ ያስያዘ ነው፡፡መንግስትን ተገን አድርጎ እየጎዳቸው ነው፡፡ከድርጊቱ እንዲቆጠብ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ሊታረም አልቻለም፡፡ ድርጊቱን አጠናክሮ ቀጠለ፡፡ተፈላጊውን ሰው ከሚስቱ ጋር አብረው ሲሄዱ መታጠፊያ ላያ ላይ ጠብቆ ነጥሎ መታው፡፡ ልጃቸው አብሯቸው ነበር፡፡ልጁ አይቶታል፡፡አይን ለአይን ተያይተዋል፡፡ሚስቱ የወደቀውን ባሏን ለማንሳት ስትሞክር ልጁ ግን እርቆ እስኪሄድ እሱን ነበር የሚመለከተው፡፡

ድርጊቱ ከተፈጸመ ከአምስት አመት በኋላ መንገድ ላይ ሰላምታ ተሰጣጡ፡፡ፊቱ ላይ ያለውን ስሜት ለማንበብ ሞክሮ ነበር፡፡ የልጅ አይን አንዴ ከከተበ አይረሳም የሚባል ነገር ሰምቷል፡፡ሌላ አስር አመት ጨምሮ እንደገና ተገናኙ፡፡ባገኘው ቁጥር እየተሳቀቀ ነው፡፡ልጁ በወጣትነቱ እየጠነከረ ሲሄድ ይሄኛው ደግሞ እድሜው እየጨመረ ነው፡፡ ብዙ አባቶች ልጆቻቸውን ጥለው ሞተዋል፡፡ልጆቻቸው ከጥቂቱ በስተቀር ብዙዎቹ የአባቶቻቸውን ገዳይ አያውቁም ፡፡አያንዳንዱ ገዳይ ልጆቻቸውን ያውቃሉ፡፡ግን ልጆቻቸው የአባቶቻቸውን ገዳይ ማወቅ ያለማወቃቸውን ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡በተለያየ መንገድ ያጣራሉ፡፡ አንዳንዶቹ ያውቃሉ ግን ሌላ ነገር ውስጥ ላለመግባት የእነርሱም ሰላም እንዳይደፈርስ ከአባቱ ገዳይ ጋር እየተያየ ይተላለፋል፡፡ኢሳያስ ግን ሁሌም ከሚበረግግ ልጁን ማናገር ፈለገ፡፡ልጁን ካደገ፣ከጎረመሰ፣ጺም ካወጣ፣ከጠነከረ በኋላ ማግኘት ፈለገ፡፡ አሁን ኢሳያስ ልጁን እያናገረው ነው‹‹እንተዋወቃለን አይደል?››አለው

‹‹የት?››

‹‹ስታዲየም››
‹‹ብእርግጥ እገባለሁ ግን..››
‹‹ግን ምን?››
‹‹አላስተዋልኩሁም ይሆናል››
‹‹የት ነው የምትገባው?››
‹‹ካታንጋ ነው››
‹‹የጊዮርጊስ ደጋፊ ነህ አይደል?››
‹‹አዎ››
‹‹እኔም እኮ ደጋፊ ነኝ››
‹‹የማን ክለብን››
‹‹የጊዮርጊስ››
‹‹አብረን ጨፍረን ይሆናላ!!!››
‹‹በደምብ እንጂ››
‹‹እኔ ብዙ ጓደኞች ያፈራሁት ስታዲየም ነው››
‹‹እኔም እኮ እዛ ስላየሁክ ነው ላናግርህ የፈለግሁት››
‹‹ሌላ ግዜ ካታንጋ ከተገናኘን እናወራለን››

ኢሳያስ የጊዮርጊስ ደጋፊ አይደለም። ሰፈር ውስጥ ባቋቋሙት የእግር ኳስ ቡድን ዋነኛ ተዋናይ ነው። የዚህንም ልጅ አባት የገደሉትና ያጀቡትየዚሁ ቡድን ተጨዋቾች ናቸው።።ልጁ የክለቡን ባንድራ ይዞ እየጨፈረ ሲሄድ ስላየው ነው ስታዲየም አውቅሃለው ብሎ ያናገረው።ግን እንደማያውቅ ሆነ እንጂ ሸውዶት ቢሆንስ? ኢሳያስ ልጅ ሆኖ ያየውን ነገር እስከትልቅ እድሜው ድረስ አልረሳም።ይሄ ልጅ ደግሞ በአይኑ የከተበው አባቱ የተገደለበት እለት በመሆኑ ላይዘነጋ ይችላል። ከግዜ ብዛት እየደበዘዘ ቢሄድም ሙልጭ ብሎ እንደማይጠፋ ከራሱ ተሞክሮ ያውቃል።ኢሳያስና ሚች አንድ ሰፈር ናቸው።ሚች የጊዮርጊስ ደጋፊ ነው። ልጁም ከአባቱ ወርሶ ክለቡን እየደገፈ መሆኑ ገብቶታል።አባቱ የጆንጆስ ጓደኛ ነው።ከጆንጆስ ጋር አብረው ነው የሚውሉት።ጆንጆስ የጊዮርጊስ ተጫዋች ነው። ጆንጆስ በሞተ አስራ አምስት ቀን ሳይሞላው ነው ይሄኛውም የተገደለው።ጆንጆስ ሲኒማ ራስ አካባቢ ነው ኢህአፓዎች የገደሉት ። አንዳንዱ ደግሞ ደርግ ገድሎ በኢህአፓ አሳበበ ይላሉ።ኢሳያስ





ስታድየም ገብቶ ጨዋታ ተመለከተ።ልጁን በቅርበት እየተከታተለ ነው።ከነበረበት ተነስቶ አጠገቡ ሄዶ ተቀመጠ።የጊዮርጊስ ጨዋታ ከመጀመሩ በፊት ቀዳሚውን ጨዋታ እየተመለከቱ ነበር።በመሀሉ ወሬ ተጀመረ ።ኢሳያስ በጥንቃቄ ነው ጨዋታ መስል ነገር የጀመረው‹‹ቤተሰቦችህ ይገፋሉ?››አለው
‹‹ማለት››
‹‹ወንድም እህቶች››
‹‹እህቴ ስፖርት አትወድም››
‹‹ወላጆችህስ?››
‹‹እናቴ በፊት ትገባ ነበር፤አባቴ ግን..
‹‹ግን ምን?››(ደነገጠ)
‹‹እሱ››
‹‹ማን?››
‹‹አባቴ በጣም ደጋፊ ነበር››
‹‹አሁንም ይደግፋሉ? ››
‹‹አይገባም››
‹‹ለምን››
‹‹የለም››
‹‹ሀገር ውስጥ የለም?››
‹‹አይደለም››
‹‹እና››
‹‹በህይወት የለም››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ሞቷል››
‹‹በበሽታ ነው?››
‹‹አይደለም››
‹‹በአደጋ?››
‹‹በሰው እጅ ተገድሎ ነው››
‹‹ያሳዝናል››
‹‹አዎ››
‹‹ጸብ ተነስቶ ነው?››

‹‹አይደለም››
‹‹ታድያ በምንድነው?››
‹‹ያኔ ኢህአፓ ምናምን ተብሎ.....››
‹‹ገባኝ››
‹‹እንደዚህ ነው››
‹‹ገዳዮች ተያዙ?››
‹‹አልተያዙም አመለጡ ግን...››
‹‹ግን ምን...››
‹‹ብቻ ነገሩን ተወው››
‹‹ይቅርታ መጥፎ ስሜት ቀሰቀስኩብህ››

አሁን ወሬው የቆመው አደገኛ ቦታ ነው። ‹‹ገዳዮቹ አመለጡ ...››ካለ በኋላ ምን ስሜት እንዳለው ማወቅ አልቻለም።አብረው ሰረጅ... ግዜ ከቆዩ አይን ለአይን ይላመዱና ከግዜ በኋላ ይሄን ፊት የት እንዳየው ሊመጣለት ይችላል ።እናም ፊት ለፊት ብዙ መተያየት ባይመርጥም ኳስ ላይ ስለሚያተኩሩ በቡድኑ ጨዋታ ብቻ ይገናኛሉ። አብረው በክለቡ ውጤት ሲጨፍሩ ሲደሰቱ፣ አብረው ሲበሉ ሲጠጡ ቤተሰብ ሆነው አሁን እሱ ከሀገር ወጥቶ ሄደ።





## ምእራፍ 8

### የተደበቁ ገዳዮች

ዛሬ በአዲስ አበባ ስታዲየም የሚደረገው ኢንተርናሽናል ጨዋታ ለመመልከት ብዙ ሰው ተገኝቷል። ብሄራዊ ቡድኑ አይደለም የሚጫወተው። ክለቦች ናቸውየሚጋጠሙት። የመድን ቡድን የመጀመሪያውን ኢንተርናሽናል ግጥሚያ በአሁን ሰዓት እያካሄደ ነው። ቡድኑ ጥሩ ፉትቦል ስለሚጫወት ደጋፊዎቹም ሆነ ሌላውም የስፖርት ቤተሰብ ኢንተርናሽናል ግጥሚያ ላይ እንዲሳተፍ ይፈልጉ ነበር።ምኞታቸውተሳክቶ እነሆ ዛሬ ለዚህ በቅቷል።የአጋጣሚ ሆኖ በዚህ የደርሶ መልስ ግጥሚያ የመጀመሪያው ጨዋታ አዲስ አበባ ላይ እየተደረገ መሆኑ ለመድን ጥሩ አጋጣሚ ነው።መድን የሚጋጠመው ከሩዋንዳው ራዮን ጋር ነው።ራዮን በዚህ የአፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ብዙ ልምድ ያለው በመሆኑ አዲስ ገቢውን መድን ነጥብ ቀምቶ ለመሄድ እንደመጣ ከከፈተው ተደጋጋሚ ጥቃት ያስታውቃል።

በአዲስ አበባ ስታዲየም የተገኘው ተመልካች መድን ለብዙ አመት ጥሩ ፉትቦል ሲያስኮመኩማቸው ስለነበር በግዜ ተሸንፎ ከውድድር እንዲወጣ አልፈለጉም።ለዚህም ነው ሙሉ ድጋፋቸውን እየሰጡ ያሉት።መድን የሚታወቅበትን የቅብብል ጨዋታ ቶሎ ሊመጣለት አልቻለም።ለውድድሩ አዲስ በመሆናቸው የከበዳቸው ይመስላል።የሚቀባበሉት ኳስ እየተቆራረጠ ለተጋጣሚ እየደረሰ በነዚህ ኳሶችም እየተጠቁበት ነው።አሁን ጫና እየተፈጠረባቸው ባለበት ግዜየሚያረጋጋቸው ሰው ያስፈልጋል።ቡድኑ ውስጥ እንጋፋና ልምድ ያለው ተጨዋች አምበሉ ብቻ ነው።ቡድኑ ከተመሰረ[illegible]ግዜ ጀምሮ ከመድን ጋር የዘለቀ ተጫዋች ነው።አሁን የሩዋንዳው ራዮን ቡድን ጫና እየፈጠረ ባለበት ሁኔታ ቡድኑን እያረጋጋና ወደታወቀበት መስመር ለማስገባት ጥረት እያደረገ ነው።ራዮን ደጋግሞ ወደ መድን ግብ ክልል የሚመጣበትሁኔታ በጣም ጨምሯል።መድን ላይ ተደጋግሞየመጣው ጭንት ለግብ የቀረበ መሆኑ ሁሉም ስጋት ላይ ወደቀ።በዚህ የጥቃት ቅጽበት የመድን አምበል ከራዮንተከላካዮችን

እምልጦ ወደ ግቡ ጋር ከመድረሱ በፊት አክርሮ ወደ ግብ የመታው ኳስ በመቆጠሩ ህዝቡ ደስታውን የገለጸበት ሁኔታ በማያቋርጥ ፉጨትና የደስታ ጩኸት ነበር።

ተጫዋቹ ያገኘውን ኳስ አክርሮ ባይመታ ኖሮ በረኛው ደርሶ በያዛት ነበር።እምበሉ ኳሱን ማክረር ብቻ ሳይሆን አጠንክሮና የበላ የጠጣውን ያህል ነው የመታው።እንዲህ ካልጠነከረ ፍጥነት አይጨምርም።ፍጥነት ከሌለው በረኛው ይደርስበታል።እናም እምበሉ ኳሱን ለመምታት ማክረርና ማጠንከር ነበረበት።እንዲህ አይነት ጠንካራ ኳስ የሚመታው የመጨረሻ ሰው ሲሆን ነው።አሰበለዚያ በታ አይቶ ወደ ግብ ይልካል ።አሰበለዚያ የመጨረሻ ሰው ካለ ያቀብላል ። ይሄን ኳስ ግን የመጨረሻ ሀይሉን ተጠቅሞ ወደ ግብ መላክ ነበረበት። ደግሞም ትክክል ነበር።ኳሱ ከመረቡ ላይ በማረፉ የራዮንን ሚና ከመቀነሱ ባሻገር የመድንን ቡድን ስነልቦና አስተካክሎ ወደሚታወቅበት ጨዋታ ለመመለስ የምታስችልና በመሪነት ላይ የምታቆም ግብ ነበረች።አሁን አንድ ግብ በመገኘቱም የጨዋታ አይናቸውን ይገልጻል።ይህች ግብ ቡድኑን መሪ የምታደርግ ብቻ አይደለችም።በአፍሪካ የክለብ ሻምፒዮና በመድን ስም የተቆጠረች የመጀመሪያ ግብ በመሆኗ ማነው የመጀመሪያውን ጎል የሚያስቆጥረው ለሚለው የደጋፊዎቹ ጥያቄ መልስ የምትሰጥ ነበረች።

ጎሉን ያገባው ተጫዋች ከዚህ በፊት ለወጣትና ለብሄራዊ ቡድን ስለተጫወተ ልምዱ በእጅጉ ጠቅሞታል።በግቡ መገኘት ጓደኞቹ በደስታ እንደጉብ እላዩ ላይ ወጥተው ሰፍረውበታል።በምቱ ጥንካሬ ተገርሟል።ደጋግሞ እንዲህ አይነት ምት መጠቀም አያዘወትርም። የዛሬውን ግን በረኛውን አቋቋም ስለየእንዲህ ማድረግ ነበረበት።ከዚህ በፊት እንዲህ አጠንክሮ በመታ ቁጥር እግሩን ስለሚጠዘጥዘው እንዲህ አይነቱን ነገርእንብዛም አይጠቀምም።ዛሬ ግን መድንን በመሪነት ላይ ለማቆም ማድረግ ነበረበት። አሁን ወደ ግብ አጠንክሮ የመታው እግር እዚህ ሜዳ ከመርገጡ በፊት አሳሩን አይቶና ዳግም ወደ እግር ኳስ ሜዳ ይመለሳል ተብሎ የሚታሰብ አልነበረም።በነጋ በጠባ እየተጠራ ክርክር ባለው ዱላ ሲቀጠቅጡትና በደም አበላ ሲነክር የነበረ እግር ነው።እሱም ቢሆን ገና በልጅነቱ የሚወደውን ኳስ ሌሊት ተነስቶ





መጫወት የጀመረ ምሽት ነበር የሚገላግለው።እንደኳስ የሚወደው ነገር የለም።በዚች ቀጫጭን እግሮቹ አብዶ እየሰራ በሚያስቆጥረው ግብ ሁሉም ይፈነድቅበታል።

እንዳንዱም ‹‹እስኪ ለአንድ ቀን እግርህን አውሰን››እስከማለት የሚደርሱት ችሎታውን ለማድነቅም ጭምር ነው።ጓደኞቹ ጥበበኛ እግር የሚሉት ለግርፊያ በመበቃቱ እንዳበቃለት አውቆ ነበር።ይሄን ለኳስ የተፈጠረ እግር በዱላ ሲተለትሉት....ዳግም ተመልሶ እግር ኳስ እጫወታለሁ ብሎ አስቦ አያውቅም።ነገር ግን ሁኔታዎች ተቀይረው ዛሬ በኢንተርናሽናል ግጥሚያ በዚያ በተቀጠቀጠበትና በተተለተለበት እግሩ ግብ ማስቆጠር ችሏል። ምናልባት ገራፊዎቹም ቢሆኑ ዛሬ እዚህ ስታዲየም ጨዋታ እየተከታተሉ ይሆናል። አንዳንድ ግዜ እዚሁ ሜዳ እየተጫወተ ገራፊዎቹ የሆነ ቦታ ቁጭ ብለው በእዚህ እግሩ ለሚያሳየው ችሎታ በአድናቆት ያጨበጭባሉ ብሎ ያስባል።ይሄን አሰቃቂና ዘግናኝ ግርፋትመቼም ስለማይረሳው እነርሱን የሚመስል ሰዎች ባየ ቁጥር ሁሌም ይዘገንነዋል። በግርፋቱ ብዛት ለሞት ትንሽ ሲቀረው ነበር በተአምር የተረፈው።አንዳንድ ግዜ እየተጫወተ እግሩ ሲደነዝዘው ገራፊዎቹን ያስባቸዋል።አሁን ለመድን ያስቆጠረው ወሳኝ ግብ ከግርፋቱ በተረፈ እግር መሆኑን ሲያስብ ያስገርመዋል።ስለእግሩ ሲያስብ ገራፊዎቹን ሁሌም ያስታውሳቸዋል።ምንም ርህራሄ የሌላቸውና በጭካኔ ዲግሪ ያላቸው ይመስሉታል።አንዳንዶ ከሰው የተፈጠሩ አይመስለውም።በተለይ በመጨረሻዎቹ ሁለት ቀናት ያየውን ስቃይ መቼም።አይረሳውም።በግርፋቱ ብዛት እራሱን ስቶ ምህዋሩ ዞሮ መሞቱን ብቻ ነበር የሚያስታውሰው።ነገሩ ሲጀመር እንዲህ ነበር።

በወርሃ መስከረም 1969 መርካቶና አካባቢው የፖለቲካ ሹኩቻው ከፍ ያለበት፤ወታደራዊ መንግስት በምሽት ብቻ ሳይሆን በቀንም ጭምር መቆጣጠር ያቃተው ይሄን አካባቢ ብቻ ነበር።የህዝብ ደህንነት ባለስልጣን ሰዎች ፤አብዮት ጠባቂዎች በወታደር ታጅበውና ታግዘው እንኳን በብዛት ሆነው ካልተንቀሳቀሱ ወደ ቤታቸው በሰላም የማይገቡበት ቦታ ነበረ።እንደዛም ሆኖ ለእሰላ ብቅ የሚሉት በቀን እንጅ በምሽትአልነበረም። በምሽት አካባቢውን በጣም ይፈሩታል።

እናም በግዜ ወደ ቤታቸው ይገባሉ፡፡በአካባቢው በፍጹም አይንቀሳቀሱም በዚህም ‹‹ደርግ የቀን ፤ኢህአፓ የማታ›› መንግስት መሆናቸው የታየበት ግዜ ነበር፡፡በምሽት ያለውን ሁኔታ ከሩቅም ቢሆን ለመቆጣጠር ደርግ እያንዳንዱ ሰው በቤቱ በር ላይ መብራት እንዲበራ ትእዛዝ አስተላልፏልፏዟን የሚያደርግ ጸረ አብዮተኛና የኢህአፓ ተባባሪ ተብሎ ስለሚፈረጅ በረንዳ በመብራት ቦግ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡የመንገድ መብራቶችም ቢሆኑ ፏ ብለው አካባቢው እንዲታይ በየግዜው መብራቶችን መቀየር ይጠበቅባቸዋል፡፡ነገር ግን እሳት የላሱ ወንጭፍ ያላቸው የኢህአፓ ታዳጊ ልጆች እያነጣጠሩ አምፖሎቹን ይሰባብሯቸዋል፡፡ በሰባተኛ እና አካባቢው ያሉ ታዳጊዎች ሰሞኑን ከባድ ስራ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ታዳጊዎቹ እንደዋናው ወጣቶች ግሩፕ አላቸው፡፡



ጌቱ መልካ

እያንዳንዱ ህዋስ አራት ሰው ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ ጌቱ መልካ የአንደኛው ሴል ሊቃ ነው፡፡ በስሩ አራት ታዳጊዎች አሉ፡፡ ከእሱ በላይ ሌሎች አራት ሰዎች አሉ፡፡ከእነርሱ ውስጥ አንዱን ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡፡እሱ ለጌቱ የበላይ ነው፡፡ማንኛውንም ትእዛዝ የሚቀበለው ከእርሱ ነው፡፡ ጌቱ በእርሱ ስር ያሉትን የታዳጊ አባላት የሚሰበስበው አመቺ በሆነ ቦታ ነው፡፡ ስብሰባውን የሚጠራው





ቀበሌዎች ወይም አብዮት ጥበቃ የማይደርስበት ቦታ ነው፡፡ቦታው እዛው ቀበሌጽፈት ቤት ውስጥ ነው፡፡ ለኢህአፓ የስራ እንቅስቃሴ ቀበሌ ውስጥ ተሰብስበው ይወያያሉ ብሎ የሚጠረጥር ስለሌለ ፍጹም አመቺ ቦታ ነው፡፡ቀበሌ ግቢ ውስጥቴኒስ መጫወቻና ሌላም ወጣቱና ታዳጊን የሚያስባብ ነገር ስላለ ለዚህ ጉዳይ የመጡ መስለው በቀበሌው ላይ ስለሚፈጸመው ኢህአፓዊ እንቅስቃሴ ተወያይተው ይሄዳሉ፡፡

ጌቱ በየቤቱ በር ላይ አምፖሎች እንዲሰበር ትእዛዝ የሚሰጡት እዛው ቀበሌ ውስጥ ተሰብስበው ነው፡፡እዛው ቀበሌ ውስጥ እነማን እንደሚፈለጉ ይሰማሉ፤ያውቃሉ፡፡የአብዮቱ ታዳጊዎች መስለው መረጃ ካገኙ ለተፈላጊዎቹ ቶሎ ያስተላልፋሉ፡፡እነዚህበየሴሉ የተደራጁ ታዳጊዎች ቀበሌውን መስለው ቀበሌውን ያጠቃሉ፡፡ቀበሌዎቹ ትላልቆቹን ሲያፈላልጉ ትናንሾች አፍንጫቸው ስር ይሸውዷቸዋል፡፡

በዚህ አካባቢ ያሉ የቀበሌ ሰዎች ባለፉት ወራት ውስጥ ከፍተኛስጋት ላይ ናቸው፡፡የቀበሌ ተመራጮቹና አብዮት ጥበቃ ሳይቀር ችግር ውስጥ ነው ያሉት፡፡ በዙርያቸው የተቀባበለ ጥይት ተነጣጥሮ እየጠበቃቸው መሆኑ አልጠፋቸውም፡፡ መቼና ከየት አቅጣጫ እንደሆነ እያውቁም እንጂ ኢላማ ውስጥ ናቸው፡፡ ኢህአፓ በስኳድነት አሰማርቷቸዋል ተብለው የሚታመንባቸው ሰዎች በቀበሌው ውስጥ የሆነ ቦታ ተደብቀዋል፡፡ የህዝብ ደህንነት ሰዎች፤የቀበሌ ተመራጮች፤ አብዮት ጥበቃዎች እነዚህን ስኳዶች ማንነታቸውን ደርሰውባቸዋል ግን ሊያገኟቸው አልቻሉም፡፡መንፈስ ነው የሆኑባቸው፡፡እዚህ ታዩ ሲባል በፍጥነት ለመያዝ ሲሄዱ አያገኟቸውም፡፡

በተለይ በከፍተኛ 6 ቀበሌ 10 ውስጥ በአደገኝነታቸው ተፈርጀው የሚፈለጉ ሰዎች ብዙ አሰሳ ተደርጎ ሊገኙ አልቻሉም፡፡ ሊገኙ ያለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን ገዳይነታቸውም እየጨመረ ሄዷል፡፡ አንድ የኢህአፓ አባል ሲገደል ከአብዮቱ ካምፕ ሁለት ሰው ዋጋይከፍላል፡፡ ድንገት ይደርሱና አንዱን የቀበሌ ሊቀመንበር ወይም አብዮት ጠባቂ አሰበለዚያ በእነርሱ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ትእዛዝ ሰጥቷል ወይም እጁ አለ የተባለውን ሰው ይገድሉታል፡፡በመርካቶና ሰባተኛ አካባቢለመንግስት ሰዎችና በተለይ ለቀበሌ ተመራጮች ቅዠት





የሆነባቸው አንዳርጌ ብዙነህ ነው እዚህ አካባቢ ብዙ ግዜ ታይቷል፡፡ እሱን ሊይዙት ቀርቶ ሊደርሱበት አልቻሉም፡፡ደፋርና ላመነበት አላማ ሟች መሆኑን ያውቃሉ፡፡እሱ አለበት ወይም ይውላል ተብሎ በሚገመትበት ቦታ ድርሽ የሚል ካድሬ እስከመጥፋት ደረሰ፡፡ አንዳርጌ ሳይታሰብ አንድ ቦታ ይከሰትና ሁለት ሶስቱን ረፍርፎ ይሄዳል፡ አንዳንድ ግዜከድፍረቱ ብዛት የተነሳ ድንገት ብቅ ብሎ ሪቮልቨር ሽጉጥ እጁ ላይ እንደ አክተር እያሽከረከረ ለጠላትም ለወዳጅም ታይቶ ይሰወራል፡፡አንዳርጌ በዋናዎቹ የደህንነት ሰዎች በእጁጉ የሚፈለግ ነው፡፡ግን ሊያገኙት አልቻሉም፡፡በምሽት ወደ መርካቶና ሰባተኛ ይመጣል ስለሚባል የቀበሌዎቹ ሰዎች ስጋት ላይ ይወድቃሉ፡፡ መብራት በየቀኑ በየቤቱ በረንዳ ላይ መኖሩን ያረጋግጣሉ፡፡ምሽት ሲሆን እንዳይሰበር ለመቆጣጠር ጥረት ቢያደርጉም አልተቻለም፡፡ እናም ኢህአፓ በምሽት ስለምትከሰት እስኪነጋ እንቅልፍ የላቸውም፡፡

ከአንዳርጌ ባሻገር ሌሎች ተጠርጣሪ ስኳዶች ከአካባቢው ስለጠፉ ቀበሌዎች ያሉበትን ለማወቅ ብዙ አሳሳ አድርገው አልተሳካም፡፡በቀበሌ 10 ውስጥ ተጠርጣሪ ወጣቶች እነማን እንደሆኑ ስለተደረሰባቸው ቤት ለቤት የድንገት አሰሳ ተደርጎ ሊገኙ አልቻሉም፡ ፡እነዚህ ወጣቶች ሳይታሰብ ድንገት መጥተው በቀበሌው ተመራጭና አብዮት ጠባቂዎች እንዲሁም ለመንግስት ይሰራሉ የተባሉትን ሰዎች እርምጃ ወስደው ስለሚሄዱ ከፍተኛ ስጋት ፈጥረዋል፡፡እነሆ ባለፉት ረጅም ወራቶች እነዚህን ሰዎች አድራሻቸውን ማወቅ አልተቻለም፡፡ የእነዚህ ልጆች እዚህ ቀበሌ ታይተዋል ተብሎ ጥቆማ የሚገኘው ርምጃ ወስደው ከሄዱ በኋላ ብቻ ነው፡፡እነዚህ ልጆች እስካልተያዙ ድረስ አብዮት ጥበቃዎቹ ምንም እረፍትና እንቅልፍ የላቸውም፡፡

እነዚህ ሰዎች የተደበቁት ሌላ ቀበሌ ነው፡፡ ቦታውን ካወቁት ሄደው መያዝ ይችላሉ ግን የት እንዳሉ አሳውቁም፡፡አንዳንድ ግዜ ትክክለኛ ጥቆማ ያገኙና አድፍጠው ሄደው ባሉበት ቦታ ሲደርሱ ለጥቂት ያመልጧቸዋል፡፡‹‹ከጥቂት ደቂቃ በፊት እዚህ ነበሩ እኮ..... ››የሚል መረጃ ያገኛሉ፡፡ግን ‹‹እንዴት ስንደርስባቸው ያመልጣሉ›› በሚል ብዙ ግዜ ይገረማሉ፤ከመገረም አልፎ ይናደዳሉ፡፡አንድ ሰው ከፊት በፍጥነትይቀድማል ብለው ይገምታሉ፡፡እንዳንዱም እራሳቸውን





ይጠረጥራሉ፡፡ ይሄን መረጃ የያዙ ሰዎች ከመሀከላቸው የኢህአፓ ሰው ይኖርና መረጃውን አስተላልፎ ተፈላጊዎቹ ያመልጣሉ፡፡ዋናዎቹ መረጃውን የሚያስተላልፉ ደግሞ ህጻናት መሆናቸውን የአብዮት ጥበቃዎቹ ፍጹም ያልደረሱበት ነገር ነበር፡፡

በየቀበሌ ውስጥ የተደበቁት ቁልፍ የኢህአፓ ሰዎች ህጻናቱ ምግብ ይወስዱላቸዋል፡፡መረጃ ያቀብሏቸዋል፡፡እናም ቀበሌዎቹ ተፈላጊዎቹን ሰዎች ማግኘት አልቻሉም፡፡ባለፉት ሳምንታት ተደብቀው ድንገት ከተፍ ብለው እርምጃ በሚወስዱ የኢህአፓ ስኳዶች በሚወሰደው እርምጃ የቀበሌ ተመራጮች ሳይቀር ወደ ቀበሌም ሆነ ስራ ቦታም ለመሄድ ፍራቻ ውስጥ ገብተዋል፡ ፍራቻ ሲባል ድርብ ፍራቻ ነው፡፡ቀበሌዎቹ በስጋት ተወጥረዋል፡፡፡

## ክረምቱ መዳረሻላይ

ዛሬ ከሰዓት እዚህ ቀበሌ በሚገኘው ሜዳ የሚደረገውን ጨዋታ ታዳጊዎቹ እየጠበቁ ነው፡፡እዚህ ቡድን ውስጥ ያሉ ልጆች አንዳንዶቹ እየተጫወቱ የመረጃ አገልግሎት የሚሰጡም አሉ፡፡የቡድኑ አውራ የተባለው ተጫዋች ከጨዋታው በፊት አባቱን ማገልገል እንዳለበት ያውቃል ፡፡

መርካቶ ባለው ሱቃቸው ስራ ያግዝና ለምሳ ከአባቱ ጋር አብረው መጥተው እንደገና ተመልሶ ወደ ሱቅ ይሄዳል፡፡ ትንሽ ቆይቶ ታዳጊው ወደሚጠበቅበት ግጥሚያ መሄድ አለበት፡፡የእሱ መምጣት ለቡድኑ አስፈላጊ ነው፡፡በዚህ አመት በተደረገው ውድድር በዙ አድናቆት አትርፏል፡፡ የውድድሩ ኮከብ በመሆን‹‹ሌኒንና አብዮቱ›› የተባለ መጽሀፍ ተሸልሟል፡፡ በዚህ ቀበሌ ውስጥ ለወደፊቱ ትልቅ ቦታ እንደሚደርስ ብዙዎቹ ይጠበቃሉ፡፡ ተስፋም ጥለውብታል፡፡ዛሬ በሚደረገው ጨዋታ ላይ ብዙ ተመልካች እንደሚመጣ ይጠበቃል፡፡ አሁን የጠዋት ስራውንቶሎ መጨረስ አለበት፡፡አባቱ ጋር እየሄደ ነው፡ ፡ድንገት ስሙ የተጠራ መሰለው፡፡ዞር ብሎ ሲያይ ምንም የለም፡፡ግን ድምጽ ሰምቶ ነበር በስህተት ይሆናል ማለት ነው ብሎ አሰበ፡፡ግን ጥሪው አሁንም መጣ፡፡ ከመንገድ አቋራጭ ብቅያለው አንድ ሰው

‹‹ጌቱ መልካ ››ብሎ ተጣራ፡፡የመጣውን ሰው ማንነቱንእንዲያውቀ ትንሽ ተደናገጠ፡፡ታከለ ነው(ስሙ የተቀየረ) ታከለ አጠገቡ እንደደረሰ

‹‹ጌቱ››አለ

‹‹አቤት››

‹‹ሰላም ነው››

‹‹ደህና ነኝ››

‹‹ወደየት እየሄድክ ነው?››

‹‹ወደ ሱቅ››

‹‹ሻይ እንጠጣ!››

‹‹ደስ ይለኛል››

ታከለ በቁመቱ ከፍ ያለ በመሆኑ የጌቱን ትከሻ አቅፎ ሻይ ወደሚገኝበት ቦታ እየተጓዙ ነው፡፡ጌቱ አባቱ ጋር ቶሎ መሄድ አለበት፡ ከዚህ ልጅ ጋር ከቆየ የከሰአቱ ግጥሚያሊያስረፍደው ይችላል፡፡ልጁ ግን ብቻውን መሆን የፈለገ አይመስልም‹‹ኳስ እንዴት ነው?››አለ

‹‹ጥሩ ነው››

‹‹ትምህርትስ!››

ልጁ ጌቱን አቅፎት ከቀልቡ ያለ አይመስልም ፡፡የሚፈልገው ነገር እንዳለ ያስታውቅበታል፡፡ ለአንድ ተልኮ ብቅ እንዳለ ገምቷል፡፡ ባያስታውቅበትም ማንም ሰው እንዳየው አደጋ ለማድረስ እንደመጣ አይጠረጠርም ፡፡ያዩት የአካባቢው ሰዎች አንድ ካድሬ በቅርብ ደቂቃ ውስጥ እዚህ ጋር እንደሚገደል አልጠፋቸውም፡፡ ድንገት ብቅ ያለውም ለዚህ ነው፡፡ታከለ ሌላ ቀበሌ ተደብቆ ቆይቶ አሁን እዚህ ብቅ ያለው እንድተፈላጊ የመንግስት ሰው ሊገድል እንደመጣ ነው የተገመተው፡፡ ባይገድልም ሽፋን ሊሰጥ ይሆናል፡፡በአካባቢው ግድያ የሚካሄድ ከሆነ ሽፋን ሰጭዎች ይኖራሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች ገዳዩን ችግር ከገጠመው ያሚያስመልጡት ናቸው፡ ፡የኢህአፓ ስኳዶች የመንግስት ሰው ሊገድሉ የሚመጡት በአብዛኛው ለበቀልነው፡፡የእነርሱ ሰው ከተገደለ ምላሽ በፍጥነት ይሰጣሉ፡፡ታከለም ድንገት የተከሰተው ቤተሰብ ሊጠይቅወይም ከጓደኞቹ ጋር ሊጫወት እንደማይሆን አሳዳጆቹ ያውቃሉ፡፡ከጌቱ ጋር ሻይወደሚጠጡበት





እየሄዱ ነው፡፡ታከለ ሻይ እንጠጣ ብሎ አብረው ይጓዙ እንጂ ሻይ ቤቶችን እያለፉ ነው፡፡ከዚህ በፊት ሰባተኛ አፋፉ ላይ የእህቱን ሻሽና ቀሚስ አድርጎ ድንገት የተከሰተው ወጣት የሚፈልገውን ሰው እመቺ ቦታ እስኪደርስ እየተከታተለ ሄደ፡፡ ዘንቢል በመያዙ መርካቶ እቃ ልትገዛ የምትጣደፍ የቤት ሰራተኛ ነበር የመሰላቸው፡፡ መታጠፊያ ቦታ ሲደርስ ዋናውን ሰው ከኋላ አናቱን በጥርቆት አጠገቡ ያለውንም ደግሞ በመምታት በአቋራጭ በማምለጡ ሁሉንም የአብዮት ጠባቂ አስደንግጦ ነበር፡፡

ገዳዩ ሲሮጥ ዘንቢልና ሻሹ በመውደቁ ቀበሌዎች ቤት ለቤት እየገቡ እናቶችን የማን ሻሽነው? እያሉ ካላወጣችሁ በሚል እየገረፉ እያስቃዩ ብዙ ሴቶች ታሰሩ፡፡ ቆይተው ግን ገዳዩ በመያዙ ሊለቀቁ ችለዋል፡፡ ቀሚስ ለባሹ ከቀበሌው ተሰውሮ ቆይቶ ድንገት ተከስቶ አደጋ በማደረሱ በመርካቶና አካባቢው የቀበሌ አመራርና ካድሬዎችን አስደንግጦ ነበር፡፡አሁን ደግሞ ታከለ ድንገት ብቅ አለ፡፡እናም ወደፊት እያማተረ ጌቱን እንደከለላ ተጠቅሞ ጉዞ ጀመሩ፡፡አሁንም እያወሩ ነው፡ ፡ታከለ ‹‹ኳስ እንዴት ነው?››አለ

‹‹ጥሩ ነው››

‹‹የት ነው የምትጫወቱት?››

‹‹እዚሁ ቀበሌ ነው››

‹‹መቼ አላችሁ?››

‹‹ዛሬ››

‹‹ስንት ሰዓት?››

‹‹ከሰአት በኋላ››

‹‹ታሸንፉላችሁ!!››

‹‹እዎ››

‹‹ዛሬስ መጥቼ አይሀለሁ››

ወሬውን ሳይጨርስ ድንገት ከኋላ የታጠቁ አብዮት ጥበቃዎችና ካድሬዎች ከተፍ አሉና

ቁም!!

እንዳትበላ!!!!

እጅህን ወደላይ!!!

እንዳትነቃነቅ!!!

ሳይሆን መሳርያ ወድረዋል፡፡ መወደር ሰዎቹ የታጠቁ ብቻ ሳይሆን በሁለቱም ላይ ደግነዋል፣መደገን ብቻ ሳይሆን አቀባብለዋል፡፡ እጃቸው ምላጭ ላይ ስለሆነትንሽ ውልፍጥ ካሉ እዛው ሊደፏቸው ተዘጋጅተዋል፡፡ ጌቱ ግራ ተጋባ፡፡ የኢህአፓ አባላት መሳርያ ተደግናባቸው ሲያዙ አይቷል፡፡ ርምጃ ሲወሰድም ሰምቷል፡፡ ይሄ ነገር እንዲህ አጠገቡ እንደሚመጣ አልገመተም፡፡ ግን ይሄው ተከሰተ፡፡ በጥቂት ደቂቃ ውስጥም ሊገደል ይችላል፡፡ሰዎቹ ለመተኮስ እንደተዘጋጁ ነው የተመለከተው፡፡ ሁኔታቸው አስፈርቶታል፡፡ ተኩስ ተከፍቶ ግድያ ከመምጣቱ በፊት ጌቱ ማምለጥ አለበት‹‹....እኔ እዚህ ውስጥ የለሁበትም!!!›› ብሎ ለመሄድ ሲዘጋጅ ልጁ እንዳቀፈው ነው፡፡፡ እላቂ ሲሄድ ሲል ‹‹እዚሁ ቁም!!!›› ተባለ፡፡መሳርያ ደግነው የከበቡት ሰዎች ታከለን እያዩ ‹‹አገኘንህ አይደል?››አሉት

‹‹ማንን››

‹‹አንተን ነዋ!!!››

‹‹ምን አድርጌ ነው››

‹‹ልትገድል ነው አይደል የመጣኸው››

‹‹የምን ግድያ››

‹‹ማንን ልትገድል እንደሆነ አንተው ንገረን እንጂ››

‹‹እረ!! እኔ ሰላማዊ ሰው ነኝ››

‹‹ግን የምታመልጥ መስሎህ ነው››

‹‹የተሳሳተ ሰው ነው የያዛችሁት››

‹‹እሱን አትነግረንም ስትገረፍ ሁንም ነገር ታወጣለህ››

ሰዎቹ ቶሎ ወደ እስር ቤት መወሰድ ነበረባቸው፡፡ እዚህ አካባቢ ረዳት ሊኖረው እንደሚችል ገምተዋል ፡፡መጥተው ተኩስ ከፍተው ሊያስጥሉት ይችላሉ፡፡ ግራና ቀኝ እየተገላመጡእያሰሱ ታከለና ጌቱን ከኋላ ደግነው እየነዱ ሄዱ፡፡እየተጓዙ ሳለ ታከለኢህአፓ መሆኑን አመነ፡፡ነገር ግን ወረቀት ከመበተን ያለፈ ነገር ውስጥ እንዳልገባ እየነገራቸው ነው፡፡ እየነገራቸው ብቻ ሳይሆን እያዘናጋቸው ነው፡፡ የሚፈላለጉት ታከለና መሳርያ ወዳሪዎቹ ናቸው ከስር በኩል ያለው ታዳጊው ጌቱ ግራ ተጋብቶ ተጨንቆ እንዲለቁት እየለመነነው፡፡ አባቱ





ለምሳ እንደሚጠብቁት እየነገረ ከቀለበቱ ውስጥ ለመውጣት እየታገለ ነው፡፡ ሰዎቹ ታከለን ‹‹ከነተባባሪህ ነው የያዝንህ››አሉ

‹‹ማነው ተባባሪ››

‹‹እሱ››

‹‹ህጻን እኮ ነው››

‹‹ላንተ ነዋ››

‹‹እኔ ወረቀት ከማንበብ የዘለለ ነገር የለኝም፣የፈለጋችሁት አድርጉኝ››

‹‹ማለት?››

‹‹እሱ የለበትም ልቀቁት››

‹‹እሱ አብሮህ ይሰራ የለ››

‹‹ምንም ውስጥ የለበትም አልኳችሁ››

‹‹የት ነው የምታውቀው?››

‹‹ትምህርት ቤት ነው››

‹‹እዛነው የመለመልከው?››

‹‹እንደዛ አይደለም››

‹‹እና››

‹‹ለህጻናት ቡድን ኳስ ሲጫወት ነው የማውቀው››

‹‹በኳስ ብቻ››

‹‹አዎ በችሎታው በጣም ነው የማደንቀው››

‹‹ሌላስ?››

‹‹ሌላ ማለት››

‹‹ለናንተ የሚላላከው እርሱ ነው አይደል?››

‹‹እዛውስጥ የለበትም አልኳችሁ ››

‹‹እሱን አንተ አትነግረንም››

እንዳውም ጌቱም ላይ አነጣጥረውና ወድረው ወደ እስር ቤት መሄድ ጀመሩ፡፡ወታደሮቹና አብዮት ጠባቂዎቹ ትልቁን አሳ አጥምደው ግራ ቀኝ አደጋ እንዳይጣልባቸው እያሰሱ በመንገዝ ላይ ናቸው፡፡ታከለ ከእዚህ በኋላ ምንም እንደማይጠቅማቸው ያውቃሉ፡፡ለብዙ ግዜ በማውጣጣት መረጃ ለማግኘት በመግረፍ ብዙ ሙከራ ተደርጎ አልተሳካም፡፡ገራፊዎቹ ስለቻቸው እንጂ እነርሱ ምንም አያጋልጡም፡፡

እናም በመግረፍ ከመድከም ወዲያውኑ ይገድሏቸዋል።ለመግደል ደግሞ ማንንም መጠየቅና ማስፈቀድ አያስፈልግም ።አንድ የአብዮት ጠባቂ ወይም የቀበሌ ተመራጭ ኢህአፓ ነው ብሎ የያዘውን ሳይመረምርና ሳያጣራ የመግደል ስልጣን አለው።ሲጀመር የኢህአፓ አባላት ፍርድ ቤት ያቀርቧቸው ነበር።በኋላ ግን ፍርድ ቤቱ ቀረና ‹‹ነጻ ርምጃ›› በሚል ለቀበሌዎች ስልጣን ተሰጠ።ነጻ ርምጃ እንደስሙ የሚያመለክተው እንደፈለጉ ለመግድል የተሰጠ ስልጣን ነው።

ታከለ ተይዞ ወደ እስር ቤት ቢገባ ምንም መረጃ ላይሰጣቸው ይችላል ።ጌቱን ግን ብዙ ነገር ያውቃል ብለው ገምተዋል ፣መገመት ብቻ ሳይሆን አምነዋል፣ ማመን ብቻ ሳይሆን በእሱ የተነሳ ሌሎችንም ከተደበቁበት ማጥመድ እንደሚችሉ ገብቷቸዋል።ታከለን ከተደበቀበት አውጥቶ የእነርሱን ሰው ለማስገደል እየመራ ባለበት ግዜ እንዳገኙት ነው ያመኑት።እናም ከጌቱ ብዙ ይጠብቃሉ።ጌቱ ነገሩን እንዲህ ያስታውሳል‹‹…ልጁን ሰፈር አየዋለሁ ።ድንገት ለብዙ ግዜ ጠፍቶ አላየሁትም ነበር።ለምን እንደመጣም አላውቅም።ድንገት አገኘኝና ብቻውን ላለመሆን ብሎ ነው መሰለኝ ጠርቶኝ ሻይ እንጠጣ አለኝ ። ወዲያውኑ አብዮት ጥበቃዎች ከበው ያዙት ።እኔም ምንም በማላውቀው አብረው ወሰዱን››ይላል።

ቀበሌዎቹ ግን ይሄንን በፍጹም አይቀበሉም ።ታከለና ጌቱን አብረው ስላገኙ ብዙ መረጃ እንደሚሰጣቸው ጠብቀዋል።እናም ታከለን አልፈለጉም። ማሰናበት ነበረባቸው። ከአንደኛው መንገድ ወጡ ። እንደገና ወደ ሁለተኛው አቋራጭ ተሻገሩ ።ድንገት አቀባበሉና ታከለን በጥይት ረፈረፉት።እዛው እንዳጋደሙት ወደ ትንሹ ልጅ መጡ ።ጌቱ ደነገጠ።መደንገጥ ብቻ ሳይሆን በረገገ።የሚይዘው የሚጨብጠው አጣ፡ ሞት እሱ ጋርእንደመጣ አወቀ። የሚፈልጉትን መረጃ ካልሰጣቸው እንደታከለ ይጠብሱታል።ለእነርሱ መግደል የተዘጋጀ ቁርስ እንደመብላት ቀላል ነው።ደህንነትናአብዮት ጠባቂዎች ታከለን ከገደሉት በኋላ ወደ ጌቱ መጡ‹‹ ማሙሽ ››አሉት

‹‹አቤት ››

‹‹ስምህ ማነህ?››

‹‹የእኔ!!!››





‹‹እዎ››

‹‹እኔ እንጃ››

‹‹አታውቀውም››

‹‹ረሳሁት››

‹‹ልክ ስናስገባህ ታስታውስዋለህ››

ጌቱ ካሁን አሁን ተኩሰው ገደሉኝ እያለ ፍርሃት ወረረው። ታከለን ሸኙተውታል።ሌሎችን ከተደበቁበት ለማግኘት ጌቱ ያሳዩናል በሚል ተስፋ አድርገዋል።እሱ ግን የሚያውቀውአልነበረም።እነርሱ ከታከለ ጋር እጅ ከፍንጅ ስለያዙት ሌሎችን እንደሚያውቅ አረጋግጠዋል።እስካሁን ድረስ ከተደበቁት እያወጣ ብዙ አባሎቻችንን አስገድሏል በሚል ደምድመዋል።ጌቱን መግደል አይጠቅማቸውም። በዱላ ብዙ ማውጣጣት እንዳለባቸው አምነዋል ።እናም በቀበሌው ውስጥ ጎበዝ ገራፊ አዘጋጁ።የኢህአፓ ስኳዶች የት እንደተደበቁ መምራት ብቻ ሳይሆን ከአብዮቱ ወገን እነማን ለመግደል እንዳሰቡ ሊጠቁመን ይችላል ብለው አምነዋል ደግሞም ደምድመዋል። ይሄ ብቻ አይደለም በቀበሌ ውስጥ ያለውን የኢህአፓ እንቅስቃሴ ያውቃል ብለው ወስነዋል።

እድሜው ገና 11 ቢሆንም ተገርመውበታል።ስኳዶችን የሚመራው እሱ ነው ብለው አምነዋል።ከታከለ ጋር ስላዩት ብቻ ብዙ ነገር ደፈደፉበት።ታዳጊ በመሆኑ የውስጥ እግሩ ለስላሳ ነው።ለስላሳ እግር በሁለትና በሶስት ግርፋት እንደሚበጣጠስ ያውቃሉ። ወፌ ላላ በሚለው የግርፋት ስልት እግርና እጁን አስረው በትልቅ ዱላ አንጠልጥለው አፉ ውስጥ ጨርቅ ወትፈው የተገለበጠው እግሩን መቀጥቀጥ ጀመሩ ።ብዙም ሳይቆይ ከእግሩ መዳፍ ደም እየረጨ መወረድ ጀመረ።የሚነግራቸው ነገር ካለ ሌባ ጣቱን ማውጣት እንዳለበት አስረድተውታል።ከብዙ ዱላ በኋላ ጣቱ ብቅአለች ። ገራፊዎቹ ደስ አላቸው።።የተደበቁት የት እንዳሉ ቦታውን ሊነግራቸው ነው።ጨርቁን ከአፉ አወጡለት።ጨርቁ እንደወጣ ጩኸቱን ለቀቀው‹‹ማሙሽ››አሉት

‹‹አቤት››

‹‹የት ነው የተደበቁት?››

-እኔ አላውቅም-

-እሱን እኮ ቤት ነገርኩን-

-የቱን-

-እንደሚታወቀው ከሬኪሰል ፡ጣትህን ያወጣኸው ግን ልትነግረን ነው-

-ምን አለክ-

እውቀው ተናደደ=ጣቱን ሚውጣት ያለበት ለመወሰኖት ሳይሆን የፈለጉትን እንዲነግራቸው ብቻ ነው። በሁኔታው ስለተናደደ ጨርቁን አንስቶት መቀጥቀጥ ጀመረ። ከብዙ ቆላ በኋላ ጣቱን ብቅ አደረገ። አሁን ልክ ገፀተኛል ብሎ ጨርቁን ከአፉ አወጣለት ነ-

-እኔምን!!!-አለ

-ንገሩ-

-እኔ አላውቅም-

-ጣትህን አውጥተሃል እኮ-

-ጨንቀኝ ነው-

-ልትነግረንም?-

-ምን ልንገራችሁ-

-የተደበቁትን-

-ባወቅ ነግሬቹሁ ነበር-

-ታስሬን ለማድ ያዘህ ወጥተሃል-

-መንገድ ላይ ነው ያገኘኹ-

-አናምንህም-

-ልማልላችሁ-

-ይኼን የመሰለ ቆላ ይዘን መሆኑ አንፈልግም።

እንደገና ጨርቁ ተወተፈና መቀጥቀጥ ጀመሩ። ብዙ ግዜ እስረኞች በመጀመሪያ ግርፊያአያምኑም የሚል ከልምድ የሚያውቁት ነገር አለ=እንዴ በቆላ ከተተለተለ በኋላ በነጋታው ቁስሉ ላይ ሲቀጥቀጡት ሁሉን ነገር ዝርግፍ ያደርጋል ይላሉ። በአንደኛው ቀን ብዙ ገረፉት ግን ምንም አላገኙም። በሁለተኛው ቀን እንደገና አመጡት ከትላንቱ በከፋ ሁኔታ እስኪበቃው ቀጠቀጡት። ግን እንዳችም ነገር አላገኙም።እንደታሰረ ሳይፈቱት ከ8 ሰዓት በላይ ሲሚንቶ ላይ ትተውት ሄዱ።ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ብዙዎችን





ያስፈታ በኋላ እንደታሰሩ ሳይፈቷቸውረስተው ሄደው በነጋታው ሲመጡ ሞተው ያገኟቸዋል።ጌቱም የሚጠብቀው ይሄው ነው።ገራፊው ሊገለው አለቀለት።

እንደገና ሌላ ግርፋት ተጀመረ። ስቃዩን መቋቋም አልቻለም። ገራፊዎቹም ስቃይ አብዝተው በመጨረሻ እንዲናገር ያደርጋሉ። ልሳኑት ቋንቋ ተተረተረ ይላሉ። ጌቱ እዚህ ደረጃ ደርሷል። ቁስሉን እየፈለጉ ይቀጠቅጡታል። ሌባ ጣቱን አወጣ። አሁን ልክ እንደገባ ምንተዋል።‹‹የት ነው ያሉት›› አሉ

‹‹እነማን››

‹‹እየቀለድክ ነው››

‹‹ምንም አላውቅም አልኳችሁ››

‹‹የሁሉንም ሳይሆን የአንድ ሰው እንኳን ንገረን››

‹‹የማን››

‹‹የስኳዶች››

‹‹የምን ስኳድ?››

‹‹የኢህአፓ››

‹‹ኢህአፓ ምንድነው››

‹‹አታውቀውም ኢህአፓን?››

‹‹እኔ ኢህአፓ የምትሉትን ነገር ሰው ይሁን ሌላ አላውቅም››

‹‹ማንን ነው የምታታልለው››

‹‹ምን አታለልኩ!!››

‹‹ኢህአፓ የሚባለውን አታውቅም?››

‹‹ስምቼ አላውቅም እኔ አባቴ ሱቅ ነው የምውለው››

‹‹እርግጠኛ ነህ ስለኢህአፓ አታውቅም?››

‹‹አላውቅም አልኳችሁ ወይም ምን እንደሆን ንገሩኝ››

በዚህ አድማው ይሄን ያህል ግዜ ተገርፎ ምንም ነገር ያለመናገሩ ግራ አጋብቷል። ከታከለ ጋር አግኝተውታል፣እጋጣሚ እንዳልሆነ ገምተዋል። አሁን ደግሞ ጭራሽ ኢህአፓ የሚባለውን ነገር አላውቅም ብሏል።ሊያምኑት ፈለጉ ግን ተቸገሩ።እሱ በራሱ በአካባቢው የታዳጊዎች የአንድ ሴል መሪ ነው።እሱ ከሚመራቸው

ታዳጊዎች አንዱ ባጋጣሚ ከተያዘ ጌቱ አስቀለት፡፡አለቃችን እሱ ነው ብሎ መጠቆሙ አይቀርም፡፡ ይሄ ስጋት አለ፡፡

እዚህ እስር ቤት ሀላፊዎች እየመጡ ተገርፈው የጨረሱትን ስማቸውን ይጠራሉ፡፡ መኖራቸውን ካረጋጡ በኋላ ይሄዳሉ ፡፡የእዚያን ቀን ማታ ይመጡና ቀን ስማቸውን የጠሯቸውን አውጥተው ይገድላሉ፡፡ ይሄን ሁሉም እስረኛ ያውቃል፡፡እንዲህ አይነቱ ሁኔታ የተለመደ ነው፡፡ ጌቱም ይሄን ታሪክ ያውቃል፡፡በግርፋቱ በሶስተኛ ቀን አንድ ሰው ድምጹን ከፍ አድርጎ‹‹ጌቱ መልካ!!!›› አለ

‹‹አቤት!!! ››

‹‹አለሁ››

‹‹አዎ አለሁ››

‹‹ጌቱ አንተ ነህ አይደል!!››

‹‹አዎ፤ ልምጣ እንዴ››

‹‹አትምጣ ››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹እዛው ቁጭ በል››

ጌቱ ደነገጠ፡፡ መደንገጥ ብቻ ሳይሆን በረገገ፡፡ ስሞኑን ስማቸው ተጠርቶ ‹‹አቤት›› ብለው ‹‹እዛው ቁጭ በሉ››የተባሉት የኢህአፓ አባላት ማታ አውጥተው ገድለዋቸዋል፡፡ ገራፊው ብዙ ቀጥቅጦት ምንም መረጃ ሳይሰጠው ስለቀረ ‹‹አንተ ከዚህ በኋላ ሞት ነው የሚጠብቅህ›› ብሎታል፡፡እናም ይሄው ዛሬ መጥተው ስሙን ጠርተው መኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ማታ ሊሸኙት ነው‹‹ወይኔ!! አለቀልኝ ብሎ››አለቀሰ፡፡ ማልቀስ ብቻ ሳይሆን ተንሰቀሰቀ፡፡ በቃ ሊገሉት ነው፡፡አጠገቡ ያሉት ሰዎች ቢደነግጡም አረጋጉት፡፡‹‹አይዞህ ችግር የለውም ህጻናት አይገድሉም›› ብለው ሊያረጋጉት ቢሞክሩም አልቻሉም፡፡ ነገር ግን የፈለጉት ገዳዮቹ ሳይሆኑ ቤተሰቦቹ ነበሩ፡፡ከብዙ ቀን በኋላ ነበር እዚህ እስር ቤት መሆኑን ያወቁት ፡፡ቤተሰቦቹ ድንገት ስለጠፋባቸው በአዲስ አበባ ከተማ ያልፈለጉት እስር ቤትና ፖሊስ ጣቢያ የለም፡፡ግን እዛው ቅርባቸው ባለው የቀበሌ እስር ቤት ነበር፡፡ እዚህ እስር ቤት ይኖራል ብለው አልገመቱም፡፡ሁሉም ቦታ ፈልገው





ሲያጡ ተስፋ በቆረጡበት ግዜ እስኪ እዚህ ሊኖር ይችላል ብለው በምልክት ሲጠይቁ አገኙት፡፡ስሙን የጠራው ሰው መኖሩን ለማረጋገጥ ነበር፡፡ጌቱ ግን ሊገሉት መስሎት ፈራ፡፡ለስምንት ወራት እዚህ እስር ቤት ቆየ፡፡

ከእስር ከመፈታቱ በፊት ‹‹ማሪኝ አብዮቱ›› ብሎ ወደ አብዮቱ ካምፕ ተመልሶ አብዮቱን ሊክስ ቃል ገብቷል ፡፡ስምንት ወር ሙሉ ነው ትምህርት የወሰደው፡፡በማንኛውም ግዜ አብዮቱ ጥሪ ሲያደርግለት በፍጥነት ምላሽ መስጠት አለበት፡፡ ከዘገየ፤ ካመነታ፤ካፈገፈገ ወይም የአምቢተኝነት ስሜት ካሳየ ወታደራዊ መንግስት ለሚመራው አብዮት ታማኝነቱን ባለማሳየቱ የገባውን ቃል አፍርሷልና ዋጋውን ሊያገኝ ይችላል፡፡ከእስር ከተፈታ ከአምስት አመት በኋላ የብሄራዊ ውትድርና አዋጅ ታወጀ፡፡እሱ ደግሞ ትክክለኛ የወጣትነት ግዜ ላይ ይገኛል፡፡ አሁን ጌቱ ለመድን ክለብ እየተጫወተ ነው፡፡

ለወጣት ቡድን ተመርጦም ወደ ሊቢያ ሄዷል፡፡እዚህ እየተጫወተ ቢሆንም ለብሄራዊ ውትድርና ጥሪ መልስ ካልሰጠ ለአብዮቱ የገባው ቃል ማፍረሱ ነውና የሚከተለው ችግር የከፋ ሊሆን ይችላል፡፡ እናም ጥሪውን ተከትሎ ኳሱን አርግፍ አድርጎ በውትድርናው ለመመዝገብ ፤ ብሎም ለመዝመትና ታግሎ ለማታገል ወደ ቀበሌ ሄደ፡፡ወጣቶች ከየቀቤሌው እየተነዱ መጥተዋል፡፡ ፍቃደኛ የሆኑትን በሰላም ፤እምቢ ያሉትን እያስገደዱና እያፈሱ አምጥተዋቸዋል፡ጌቱ ፍቃደኛ ነው፡፡ ደግሞም በፍቃደኛነት ቢሆን ይሻላል፡፡ አስገዳጅ ከሆነ የኋላ ታሪኩ ጥሩ ስላልሆነ አደጋ ውስጥ ይወድቃል፡፡በቃ ጌቱ መዝመቱ ነው፡፡ ወደ ቀበሌ አመራ፡፡ ጽፈት ቤት ገባ፡፡የምዝገባ ቦታውን ጠየቀና ተነገረው፡መዝጋቢው ጋር ተራው ደርሶ ተጠጋ፡፡ መዝጋቢው‹‹ስም?››አለው

‹‹ጌቱ››

‹‹ጌቱ ማን?››

‹‹ጌቱ መልካ››

ሰውየው ስሙን አገላብጦ ተመለከተ፡፡ እንደገናም ቀና ብሎ አየው፡፡ ማየት ብቻ ሳይሆን አፍጥጦ ተመለከተው ‹‹ስምንድነው የመጣኸው?›› አለው

‹‹ለመዝመት››

‹‹የት?››

‹‹ግዳጅ››

‹‹አንተ!! ››

‹‹አዎ››

‹‹ብቃ ተመዝግበሃል››

‹‹እና››

‹‹ወደ ቤትህ ሂድ››

‹‹መቼ ነው የምትጠሩኝ?››

‹‹አንተ አትጠራም››

‹‹ለምን?››

‹‹አትጠራም አልኩህ››

‹‹ምን አደረግኩ ››

‹‹ወድቀሃል››

‹‹ወድቀሃል ማለት ምንድነው?››

‹‹ወድቀሃል ማለት አትፈለግም ማለት ነው››

አሁን ጌቱ ነገሩ ገብቶታል።ኢህአፓ የሆነ ሰው በእንዲህ አይነት ቦታ አይታመኑም።ሲገርፈው የነበረው ወታደራዊ መንግስት እንዲህ ባለ የውትድርና ቦታ አምኖ ሊልከው እንዳልፈለገ ነው የተረዳው ።ይሄን ደግሞ ማጣራት አለበት። በራሱ ፍቃድ እምቢ ብሎ እንደሄደ ሊቆጠር ይችላል ።እዚህ መጥቶ ሊቀበሉት እንዳልቻሉ ማስተማመኛ ማግኘት አለበት።እናም አትፈለግም የሚል ወረቀት ሊሰጡት እንደሚገባ ያምናል።ጥፋቱ የመዝጋቢው እንጂ የእርሱ አይደለም። እንደገና መዝጋቢውን ማነጋገር ጀመረ‹‹እኔ ለመዝመት ነው የመጣሁት››አለ

‹‹ገብቶኛል››

‹‹እና ››

‹‹እኛ አንፈልግም አልንህ››

‹‹ለምን?››

‹‹ለእኛም አስብልን እንጂ››

‹‹አልገባኝም››





‹‹እኛ እኮ ኳስ ማየት እንፈልጋለን››

‹‹ምን አገናኘው ከእዚህ ጋር››

‹‹እናንተን ልከን ኳስ ሜዳ ሄደን ምን እናያለን››

‹‹እንዲህ ነው ነገሩ!!!››

‹‹አዎ በቀላል ቋንቋ አንተ ወድቀሃል››

‹‹ብቃ ይሄ ነው?››

‹‹አዎ ባንተ ቦታ ሌሎች ይዘምታሉ››

‹‹እና ወደ ቤቴ ልመለስ››

‹‹መመለስ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በኋላ ወደ ምዝገባ ቦታ እንዳትመጣ››

ጌቱ አሁን ነገሩ ገባው።ሰውየው ዘንድሮ እየተደረገ ባለው ውድድር ብዙ አይቷል። የመድን ቡድን ጥሩ አቋም ላይ እንደሚገኝና ለሻምፒዮናው የተሻለ እድል እንዳለው ተነጋገሩ።ግን ይሄ ሰውዬ በራሱ ፍቃድ ነው አትመዘገብም ያለው።ሌላ መዝጋቢ ጋር ቢሄድ ኖሮ ኤርትራ ውስጥ ናቅፋ ውጊያ ላይ ይታይ ነበር።ጌቱ አሁን ኑሮውን በአዲስ አበባ አድርጎ ይገኛል።

## ምዕራፍ 9 ሚቹ ገዳይ

ቀበሌው የስፖርት ውድድር በሚጀምርበት ቀን የሞቀና የደመቀ ለማድረግ የተቋቋመው ኮሚቴ ቀን ከሌት እየሰራ ነው። የሴቶች፣የወጣቶች፣የታዳጊዎችና ዋናውን ቡድን ያካተተ ውድድር ለማድረግ እያዘጋጀ ነው።ምክትል ሊቀመንበሩ ኮሚቴዎቹን ሰብስበው ያለችግር እንዲካሄድ መመርያስጥተዋል።ታደሰ(ስሙ የተቀየረ) የጸጥታው ሁኔታ በምን መንገድ መሆን እንዳለበት በዝርዝር ሀሳቡን እየሰጠ ነው።ምክትል ሊቀመንበሩ እዚህ ኮሚቴ ውስጥ እንደታደሰ የሚያቀርቡት ሰው የለም።ሁሌም ታታሪና ለአብዮቱ ታማኝነው። ደግሞም ለምክትሉ ጆሮ ጠቢ ነው ይሉታል።የኢህፓ ጠላት በመሆኑ ባገኘበት የሚጋፈጣቸው እሱ ነው ይሉታል።ምክትሉም የሚያቀርቡት አንድም በኢህአፓ ላይ ያለውን ጥላቻና አቋም ስለሚያውቁ ነው።

ቀበሌው ለመኖርያነት ቤት የሰጠውም በምክትሉ ትዛዝ ያለው ታማኝነት ከግምት ውስጥ በመግባቱ ነው።አሁን ያቋቋመው የስፖርት ማስተባበርያ ቡድን በእሱ እንዲመራ የተደረገውም ለዚህ ነው። ኢህአፓዎች ሁሌም አደጋ ሊያደርሱበት እየሞከሩ አልተሳካላቸውም እያሉ ምክትሉ ያወሩለታል ።እናም ከቀበሌው በጣም ምርጥ ሽጉጥ አስታጥቀውታል። ሽጉጡን የሰጡት ቀን‹‹አንተ እኮ የእኛ ታማኝ ሰው ነህ›› አለው

‹‹አውቃለሁ፣ለዚህ አይደል ኢህአፓ የምታሳድደኝ››
‹‹እሱን በደምብ እናውቃለን››
‹‹ብዙ ግዜ አምልጫቸዋለሁ››
‹‹ለዚህ እኮ ነው ዛሬ የጠራሁክ››
‹‹ምን አልከኝ?››
‹‹እንድትታጠቅ ወስነናል››
‹‹ቀበሌው ነው?››
‹‹ እኔ ከወሰንኩ በቂ ነው እነርሱም ያምኑኛል››





‹‹ለነገሩ አንተ ነህ ለቀበሌው ያለኸው…››
‹‹አሁን በጋራ እንሰራለን፣ ሽጉጡን ከ20 ጥይት ጋር እንሰጥሃለን››
‹‹20 ጥይት?››
‹‹አዎ፣ያንስሃል እንዴ? እንደዛ ከሆነ እንጨምራለን››
‹‹20 ጥይት ምን ያደርጋል?››
‹‹እንዴት››
‹‹አንድ ጥይት ትበቃለች››
‹‹ማለት?››
‹‹ለኢህአፓ ይሄ ሁሉ ጥይት ማባከን አያስፈልግም›››
‹‹አንተ እኮ ጎበዝ ወታደር ነህ››
‹‹ጦር ሜዳም አላስፈላጊ ጥይት እንዳይባክን አዛዦችን ይነግሩናል፣ይቆጣጠሩናል››
‹‹እግረ መንገዴን ልጠይቅህ…?››
‹‹እሺ ››
‹‹አንተ የት ነበር የተዋጋኸው?››
‹‹ጎዴ ነው››
‹‹እዚያ ነው የተመታኸው?››
‹‹እግሬን የተመታሁት ድሬዳዋን ስናስለቅቅ ነው››
‹‹አፍንጫህንስ?››
‹‹እሱን ጎዴ ነው፣አይኔንም እዛ ነው የተመታሁት››
‹‹አንድ ላይ ነው እንዴ?››
‹‹አዎ አዛዦችን በማነጣጠር ስለሚያውቁኝ አይኔ ሲጎዳ አዘኑ››
‹‹ለምን?››
‹‹በጦርነቱ መሳተፍ አልችልም››
‹‹ይገርማል ግን…››
‹‹ግን ምን…?››
‹‹አፍንጫህ ከጎን በመጣ ጥይት ነው››
‹‹አዎ››
‹‹አይንህ ደግሞ የተመታው ከፊት ለፊት በሚመጣ ጥይት ነው››
‹‹ልክ ነህ››

‹‹ታደሰ እንዴት ሁለቱ አንድ ላይ ሊመቱ ቻለ?››

‹‹ጦር ሜዳን ስለማታውቀው ነው፤ስትራቴጂ ቦታ ስትቀመጥ ከሁለቱም ቦታ ነው የሚያገኘህ››

‹‹እንደዛ ነው እንዴ?››

‹‹አዎ፤ስመሆኑ የጦር ሜዳ አሰላለፍ ታውቃለህ?››

‹‹አላውቅም››

‹‹አንድ ቀን በደምብ በስዕላዊ መግለጫ አሳይሃለሁ››

‹‹እጠብቃለሁ፤አንድ ነገር አለ..››

‹‹ምን?››

‹‹አብዮት ጠባቂዎችን ታስለጥንልሃለን››

‹‹የእግሬ እንካሳንትእያየህ.....››

‹‹አውቃለሁ››

‹‹እና››

‹‹ኢላማ ማስልጠንና በመኪና ሆነህ ስፖርት ማሰራት ነው››

‹‹ኢላማውን ብቻ ቢሆንስ››

‹‹ግዴለህም ሁለቱንም››

‹‹እሺ እስማማለሁ ለአብዮቱ.....››

‹‹አሁን ጉዳያችን ጨርሰናል፤ በስፖርቱ ላይ ችግር ካለ ትነግረኛለህ››

ሁለቱም ሰዎች ከተቀመጡበት ተነሱ፡፡ ታደሰ ፊቱን በሻርፕ ሸፈነ፡፡ ሻርፑ ያረፈው አፍጫውና አንድ አይኑ ላይ ነው፡፡ አፍንጫው አንደኛው ክፍሉ ተቦድሶ አንደኛው ብቻ ነው ያለው፡፡ መልኩን ሙሉ ለሙሉ ለውጦታል፡፡ ጺሙን ክፍ አድርጎ ስለሚያሳድግ ሽፍታ ነው የሚመስለው፡፡ ሲሄድ ያነክሳል፡፡ታፋው ላይ የገቡት ጥይቶች ስላልወጡ እግሩን አሳጥረውታል፡፡ ምክትል ሊቀመንበሩ አሁንም የቅድሙ ነገር ሊዋጥለት አልቻለም፡፡ ‹‹የአይንህና አፍንጫህ ነገር አሁንም አስደንቆኛል››አለው፡፡ ታደሰ ግን በድጋሚ ከወታደራዊ ጦርነት አንጻር ሊያስረዳው ሞከረ፡፡ ሊቀመንበሩ እዚህ ወታደር ላይ አንድ የሚያየው ገጽታ አለ፡፡ ምን እንደሆን ግን አልገባውም፡፡ በሱማልያ ወረራ ለሀገሩና ለአብዮቱ ታማኝ ሆኖ በጦር ሜዳ ስላሳለፈው ውሎ ስለሚነግረው በጀግንነቱ ይመካበታል፡፡





## እንደገና በዚያን ሰሞን

ከምሽቱ 3 ሰአት ላይ ቤቱ የተንኳኳበት አብዮት ጥበቃ መሳርያውን አቀባበሎ‹‹ማነህ?››አለው

‹‹እኔ ነኝ››

‹‹እኮ ማን?››

‹‹ታደሰ ነኝ››

‹‹ታደሰ?››

‹‹የእናንተ ኢላማና ስፖርት አስልጣኝ››

‹‹እርግጥኛ አንተ ነህ?››

‹‹አዎ››

አብዮት ጠባቂው የውጪውን መብራት አበራ፡፡ በጓሮ በር ዞሮ ቀስ ብሎ መጣና ተደብቆ ተመለከተው ፡፡በእርግጥም እሱ ነው፡፡ኢላማ የሚያስተምረውና ስፖርት በሌሊት የሚያሰራቸው ሰው ነው፡፡የእሱ ጽናትና ለአብዮቱ ያለው ታማኝነት ያስገርማቸዋል፡፡ሁሉም እንደርሱ መሆን ይመኛሉ፡፡፡‹‹እኔ ለአብዮቱና ለሀገሬ ሁሉንም ሰጥቻለሁ እናንተም ለአብዮቱ ታማኝ ሁኑ›› ይላል፡፡፡አብዮት ጠባቂው‹‹አንተ ነህ እንዴ?››አለው

‹‹አዎ ››

‹‹ምነው በማታ መጣህ››

‹‹ሰዎች ሊገድሉኝ ሲያባርሩኝ አምልጬ ነው››

‹‹እነማናቸው?››

‹‹ኢህአፓዎች››

‹‹የትናቸው አሁን?››

‹‹ወደ ታች ሄዱ››

‹‹ወደየት?››

‹‹ቤቴ ጋር ሊጠብቁኝ ነው መሰለኝ ወደዚያ ሄዱ››

‹‹እንዴት እናድርግ?››

‹‹ብንሄድ ሊመቱን ይችላሉ››

‹‹ዛሬ እኔ ቤት እደራ››

‹‹ቀበሌ ባድር አይሻልም››

‹‹ለምን››

‹‹እዚያ ጥበቃ ስላለ አይመጡም››

‹‹እንደዛ ከሆነ ላድርስሃ››

ሁለቱም ተያይዘው ወደ ቀበሌ ሄዱ። እዚያ የተሻለ ጥበቃ የሚደረግለት ቦታ ነው። ጠዋትአብዮት ጠባቂዎች ጋር ስፖርት ለመስራት ወደ ልምምድ ሜዳ ስለሚሄድ አሁን ያለበት ጥሩ ጥበቃ የሚደረግለት ቦታ ነው። በጠዋት ሲነሳ አካባቢው ቀውጢ ሆኗል። የቀበሌው ዋናው ሰው በኢህአፓ በመገደሉ ሰፈሩ ተተረማምሷል። ምክትል ሊቀመንበሩ ለአብዮቱ ታማኝ ሰው የነበረና በቀበሌው ብቻ ሳይሆን በጎረቤት ቦታዎች ሳይቀር የሚፈራና የሚርበተበቱለት ነበር። የቀበሌው አመራር ሰዎች የህዝብ ደህንነት አባላትና የአብዮት ጠባቂዎች የጠረጠሯቸውን ሁለት ሰዎች ገደሉ።ሌሎችንም አስሩ። የቀበሌው ነዋሪበፍራቻ በሩን ዘግቶ ቤቱ ተቀመጠ። ሌላው ደግሞ ሳይጣራ ሰለባ እንዳይሆን ወደ ሌላ ቀበሌ ሸሸ።

የአብዮት ጠባቂዎቹ ግድያውን እንደሰሙ ሌሎች ወደ ቀበሌውጽፈት ቤት መጥተው የበቀል ግድያ ስትራቴጂ ለመንደፍ ተሰብስበዋል። ሁሉም ቁጣ ላይ ናቸው።አንደኛው ሰው ታደሰ ተደብቆ ወዳደረበት ክፍል ሄደ። ሌሊቱን ሙሉ ሳይተኛ ነበር ያነጋው። የተቆጣውና በእልህ የነደደው አብዮት ጠባቂ በሩን ከፍቶ ገባና ‹‹ስማህ››አለው

‹‹ምኑን?››

‹‹ጓዳችን ገደሉብን እኮ››

‹‹ማንን?››

‹‹ምክትሉን››

‹‹ወይኔ ወንድሜ!!!!!!!አይሆንም!!!!››

‹‹ተዋቸው››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹አሁን እጁጃቸዋለን››

‹‹መቼ ገደሉት?››

‹‹አሁን››

‹‹መቼ አሁን?››

‹‹ሌሊት››



‹‹የት?››

‹‹እሳቻ ቦታ››

ታደስ እነርሱን ለማገዝ ተፍ ተፍ እያለ ነው ።የአብዮት ጥበቃው ሊቀመንበር ጠራውና‹‹ስምተሃል አይደል?››አለው

‹‹እዎ፤እነዚህ ምናምንቴዎች ልክ መግባት አለባቸው››

‹‹እንለቃቸውም››

‹‹እነዚህ ወሮበሎች መጠራረግ ነው››

‹‹አይቀርም ፤አንተን እንፈልግሃለን››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹አሁን የጠራሁክ ለጉዳይ ነው››

‹‹ምን››

‹‹ማታ አንተንም ሊገድሉህ እንደነበር ሰማሁ››

‹‹አዎ፤ ጓዴ ነው ደብቆ ያዳነኝ››

‹‹ነግሮኛል››

‹‹ለጥቂት ደርሰውብኝ ነበር እሱ ቤት ዘልዬ ገባሁ››

‹‹ሊገድሉህ የነበሩትን አይተሃቸዋል››

‹‹አዎ አንድ ሁለቱን አይቻቸዋለሁ››

‹‹ምን ይመስላሉ?››

‹‹ቀይ ሆኖ ሉጫ ጸጉር ነው››

‹‹ሌላኛውስ?››

‹‹ጥቁር ሆኖ ረጅም ነው››

‹‹ሌላ ግዜ አይተሃቸዋል››

‹‹አንዱን የማውቀው መሰለኝ››

‹‹አንተን ካሳደዱ በኋላ ነው ጓዳችንየተገደለው?››

‹‹እንደዛ አሉኝ››

‹‹ላንተ አሁን ትልቅ ጥበቃ ያስፈልግሃል››

‹‹ለምን?››

‹‹ለእኛ እንደምትሰራ አውቀዋል ማለት ነው››

‹‹እኔ ምንም አልፈራም››

‹‹ምን አልክ››

‹‹ጓዴን ገድለውብኛል፤ ፊት ለፊት እጋፈጣቸዋለሁ››

‹‹በስሜት ሳይሆን በዘዴ እናደርገዋለን››
‹‹እንዴት ይሄን ንጹህ ሰው ይገድላሉ(ማልቀስ ጀመረ)
‹‹እንዴት ይሄን ንጹህ ሰው እናስለቅሳለን››
‹‹ብቃ አታልቅ!እነርሱን እናስለቅሳለን››

ከአብዮቱ ወገን ያሉ ሰዎች ይሄን ወታደር ትልቅ ተባባሪያቸው በመሆኑ ያከብሩታል::ለእሱም ልዩ ጥበቃ ያደርጉለታል::እሱም በእኩል ብቃቱም ሆነ በኢላማ ስልጠና እንዲሁም እንዴት የኢህአፓ አባላትን አሳዶ መያዝ እንዳለበት በሚሰጠው አገዛ ደስተኛ ናቸው:: እናም እንደሌሎቹ የአብዮቱ ሰዎች ትልቅ እንክብካቤ እንደሚያሻው ያምናሉ::ሌሎች ከዳር ያሉ ደግሞ ታደሰ ወሬ አቀባይ በመሆኑ ጠልተውታል::ሁለት ግዜ ያህል የኢህአፓ ሰዎች የማስጠንቀቂያ ወረቀት ልከውለታል::ወረቀቱንም አምጥቶ ለቀበሌው ሰዎች አሳይቷቸዋል::የቀበሌውም ሰዎች በጣም ሲጋት በገጠመው ግዜ ወደ እዚህ ጽፈት ቤት መጥቶ ጥበቃ እየተደረገለት እንዲያድር ነግረውታል::የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበሩ ሁሉንም ሰብስቦ‹‹የጓዳችንን ሞት በሸህ ኢህአፓ ደም እንመልሳለን›› በሚል መፈክር አሰማ::‹‹ጓዶች አናቀላፋ!!!›› በሚል በፍጥነት እርምጃ እንዲወስዱ አነሳሳቸው::ከሁለት ሳምንት በኋላ የአብዮት ጥብቃው ሊቀመንበር በጥይት ተመታ ::ነገር ግን በህክምና ተረፈ::አሁንም የቀበሌው አመራርና ህዝብ ድርጅት ሰራተኞች ግራ ተጋቡ ::ነገሩ ሲጀመር እንዲህ ነበር::-

ወደ ኮተቤ መስመር እየሄደ የነበረው ትልቅ መኪና ለሽርሽር ከከተማ የሚወጣ አይደለም::ወይም እንደሌሎች መኪኖች መንገደኞችን ይዞ ወደ ክፍለሀገር የሚሄድአውቶብስ አልነበረም:: ሁሉም ወጣቶች ናቸው::መኪና ውስጥ ከፍ ባለድምጽ እየዘመሩ ነው::እንዲህ ባለድምጽወጣቶች የሚዘምሩት የእግር ኳስቡድን ተጫዋች ሲሆኑ ነው::ያውም ቡድናቸው አሸንፎ ሲመለስ መኪናው እስኪነቃነቅ ይጮሃሉ::ሹፌሩም ሳይቀር በደስታ ተሞልቶ ዘፈኑ ላይ ይሳተፋል:: ይሄ ግን እንደዚያ አይደለም::ሹፌሩም ከእነርሱ ጋር አይሳተፍም:: እንዲህ ተደስተው በመዝፈናቸው በራሱ በንዴት እየሰደባቸው ነው:: ወጣቶቹ አንዱ ለሌላው ሞራል እየሰጠ‹‹ማን ይፈራል ሞት!!!!ማን ይፈራል!!...››እያሉ ራሳቸውን በሞራል እየገነቡ ነው:: ብዙዎቹ ኳስ ተጫዋቾች ሲሆኑ አንዳንዶቹ ኳስ በደረሰበት ተገኝተው የማያውቁ





ናቸው::አንድ ሰው ከሁሉም ላቅ ብሎ ድምጹ ይሰማል::ታደሰ ነው:: ታደሰአጠገቡ ካለው ጓደኛው ጋር በብረት ሰንሰለት ተጣምረዋል:: ታደሰና ጓደኛው አንድ ክለብ ነበር የሚጫወቱት::

ሲያሸንፉ ሁሌም እነርሱ ናቸው መዝሙሩን የሚመሩት :: እየጮሁ ነው የሚዘፍኑት ዛሬ ግን ለእግር ኳስ ድላቸው አይደለም የሚዘምሩት::በጥንድ እያጣመሩ በሰንሰለት ተቆራኝተው የአንገታቸው ስር እስኪገተር ለዚህኛው ቡድናቸው ነው የሚዘምሩት:: ከእግር ኳስ ቡድናቸው በበለጠ የኢህአፓ ቡድን በፍቅር ይወዱታል::ለዚህም ነው እስኪሞቱ ለኢህአፓ የሚያዜሙት:: እናም ወደሞት ሲሄዱ ሳያዝኑ ሳያለቅሱና በስሩት ስራ ሳይቆጩ ነው የሚጓዙት::በጥቂት ደቂቃ ውስጥ እንደሚሞቱ ያውቃሉ:: ወታደራዊ መንግስት ምንም መረጃ ስለማያገኝባቸው ነው የሚገድላቸው:: ከተቆፈረው ጉድጓድ ኋላ ሁሉም የኢህአፓ አባላት ተደርድረዋል:: ምሽት ስለሆነ ይዘዋቸው የመጡት መብራቱንም እነርሱ ላይ አብርተዋል::

ብርሀኑ ሁሉንም ቦታ ስላዳረሰ ሟችም ገዳይም እየተያዩ ነው:: በዚህ መሀል ሁለት ልጆች ሰንሰለቱን እንዴት እንደፈቱት ሳይታወቅ መሮጥ ጀመሩ::ይሄን ግዜ ገዳዮቹ ግራ ተጋቡ::ሌሎችም ፈትተው እንደሚሮጡ ስለገመቱ እነዚያን እያባረሩ እነዚህ ላይ መተኮስ ጀመሩ::

## እንደገና ወደ ኋላ

ታደሰ ወደ ምክትል ሊቀመንበሩ ቢሮ ሄደ:: ብቻውን መሆኑን አረጋግጦ ነው የመጣው:: ምክትሉ ታደሰን እያየ‹‹በዚህ ሰአት እንዴት መጣህ?››አለው

‹‹ማለት?››

‹‹ዛሬ ሙሉ ቀን ፌስቲቫሉ ዝግጅት ላይ ትሆናለህብዬ ነው ››

‹‹በድብቅ አቋርጬ መጣሁ››

‹‹ምን ችግር ገጠመህ?››

‹‹ለትልቅ ጉዳይ ነው የመጣሁት››

‹‹ምንድነው ንገረኝ!!››

‹‹ተገኘ እኮ!!››

‹‹ማን?››

‹‹የምንፈልገው ሰው››

‹‹የቱ?››

‹‹የኢህአፓ ስኳድ ያልኩህ››

‹‹ጓዶቻችንን የገደለው?››

‹‹አዎ››

‹‹የት ተገኘ?››

‹‹መደበቂያውን አገኘሁት››

‹‹አሁን እዚህ ነው ያለው?››

‹‹አዎ፣ ማታ ተሸፋፍኜና እራሴን ቀይሬ ተከተልኩት፣ ዛሬም እዚያ መኖሩን አረጋገጥኩ››

‹‹ቶሎ መያዝ አለብና››

‹‹አዎ ግን መጠንቀቅ አለብን፣እንዴ ከተነቃብን አናገኘውም››

‹‹በስንት ሰአት እንሂድ››

‹‹አሁን ሰዎች ሊኖሩት ይችላሉ፣መሽት ሲል ይሻላል››

‹‹ለሌሎች ጓዶቻችን ልንገርና ላዘጋጃቸው››

‹‹እሱን ነገር አልወደውም››

‹‹ምኑን?››

‹‹ለሌሎች አባላት መንገሩን››

‹‹ለምን?››

‹‹ባለፈው ታስታውሳለህ?››

‹‹መቼ?››

‹‹ደርሰንበት ያመለጠው ልጅ?››

‹‹እና››

‹‹ለሌሎች አባሎቻችን ስለነገርን የሆነሰው ጠቆመው…››

‹‹የእኛ ቡድን ችግር ይሄ ነው፣ ማጥራት አለብን››

‹‹ሌላቀን የማጥራት ስራ ይቀጥላል፣ያሁኑ ግን እኔና አንተ እንበቃለን››

‹‹እንደዛ ይሻላል?››

‹‹አዎ፣ እኔ እኮ ወታደር ነኝ››





‹‹እሱ እንኳን ችግር የለም፣እኔምብቻዬን አሳድጄ የያዝኳቸው አሉ››

‹‹አሁን እቅድ እንንደፍ››

‹‹ያሰብከው ነገር አለ?››

‹‹አንዳችን ከፊት ሌላችን ከኋላ በር እንገባለን››

‹‹ከፊት ማን ይሁን››

‹‹እኔን ጠርጥሮ ካመለጠ አንተ ታገኘዋለህ››

‹‹ተስማምቻለሁ››

‹‹ሌላ ነገር ደግሞ አለ››

‹‹ምን?››

‹‹ስንሄድ ተበታትነን ነው››

‹‹ቤቱ ድረስ?››

‹‹አይደለም››

‹‹እና ››

‹‹እስከወፍጮ ቤቱ ድረስ አንገናኝም››

‹‹ከዚያስ?››

‹‹እዛ ተገናኝተን ትንሽ ወንዝ መሳዩን ጅረት ተሻግረን ቤቱ ጋር መድረስ ነው››

‹‹ስንት ሰአት እንገናኝ››

‹‹አንድ ሰአት፣ደግሞም….››

‹‹ደግሞ ምን››

‹‹እንዳትታወቅ፣ ራስህንም ሸፍን››

‹‹በደምብ የሚሸፍን ኮፍያ አደርጋለሁ››

‹‹ሌላም ነገር ጨምር››

ምሽት አንድ ሰአት ሲሆን ቀንደኛውን የኢህአፓ ስኳድ ለመያዝ ሁለቱ ሰዎች ለማንም ሳይነግሩ ተገናኙ። ምክትሉ ለታደሰ‹‹ምንም አንተን አትመስልም››አለው

‹‹በውትድርና አለም ራስን መቀየር ተምረናል››

‹‹ቆየህ ከመጣህ?››

‹‹አዎ አንድ 45 ደቂቃ ይሆነኛል››

‹‹ለምን ቀድመህ መጣህ?››
‹‹ከቤት ወጥቶ እንዳይሄድ ነው››
‹‹ወስጥ መኖሩን አጣራህ››
‹‹አዎ ከሱቅ እቃ ገዝቶ ሲገባ አየሁት››
‹‹ቆይቷል››
‹‹15 ደቂቃ ይሆነዋል፤ያልታወቀበት መስሎታል››
‹‹እሱ መሆኑን አረጋግጠሃል››
‹‹አዎ፤ሲገድልና ሌሎቹን ልኮ ሲያስገድል የነበረው እኮ እርሱ ነው››
‹‹አሁንማ ደርስንበታል››
‹‹አሁን እንሂድና ልክ እንግባው››
‹‹እንስፍርበትና እንበታትነዋለን››
‹‹እነዚህ ምናምንቴ......››
‹‹ለማንም አልነገርከም አይደል››
‹‹አዎ››
‹‹ለጥንቃቄጥሩ ነው››
‹‹እንዴት?››
‹‹ልፋታችን ከንቱ እንዳይሆን ነው››
‹‹ልክ ነህ››
‹‹እነዚህን አይጦች ከየጎሬው እየለቀምን እንጨርሳቸዋለን››
‹‹እንደአንተ አይነት ታማኝ ሰው ነው የሚያስፈልገን››
‹‹አብዮታችንን ጫፉን የሚነካ ካለ ወደ ኋላ አልልም››
‹‹ልክ ነህ››
‹‹ ወደ ጦር ሜዳ ስዘምትም ለአብዮቱና ለሀገሬ ታማኝ ሆኜ ነው ፤እነዚህን ቦርቧሪዎች አለቃቸውም››
‹‹በማንኛውም መንገድ ከጎንህ ነኝ››
‹‹አውቃለሁ››
‹‹ ግን ምንድ ነው የያዝከው?››
‹‹የቱ?››
‹‹ይሄኛው››
‹‹ገመድ ነው››





‹‹ምን ያደርጋል?››
‹‹ካመለጠ በጥይት ከያዝነው ደግሞ አስረንና ጠፍረን እናመጣለዋን››
‹‹በደምብ ነው የተዘጋጀኸው ማለት ነው?››
‹‹አዎ››
‹‹ታድያ ዱላ መያዝ ለምን አስፈለገ?››
‹‹እንዴት››
‹‹ሽጉጥ ይዘህ የለ እንዴ?››
‹‹ወደግቢ ስንዘልቅ ውሻ ካለ ሽጉጥ አትጠቀምም፤ በዱላ እንዳይጠጋ ታደርጋለህ››
‹‹ጎበዝ የስትራቴጂ ሰው ነህ››
‹‹ወታደር አይደለሁ እንዴ!!››
‹‹ወታደር ብቻ አትመስለኝም››
‹‹ምን ማለት ነው?››
‹‹ከዚያም በላይ››
‹‹አልገባኝም››
‹‹ወታደራዊ ደህንነት ወይም ስራቴጂስት ...››
‹‹ያው ከውጊያ ጋር አብረህ የምትማረው ነገር አለ እኮ..››
‹‹በዋናው መንገድ እንሄድ?››
‹‹ ይቅር
‹‹ለምን?››
‹‹ሰዎች ሊያዩን ይችላሉ››
‹‹እና ››
‹‹በእቋራጩ ሰው በሌለበት መንገድ እንሂድ››

ከምሽቱ አንድ ሰአት ራሳቸውን ቀይረውና ሽፍንፍን ብለው ወፍጮ ቤቱ ጋር የተገናኙቱ ሁለቱ ሰዎች በተነጋገሩት መሰረት ተፈላጊው የኢህአፓ አባል ወደተደበቀበት ቤት እያደቡ መሄድ ጀመሩ፡ ፡ወንዝ የመሰለችውን ውሃ መውረጃ ተሻግረው ጥቂት እንደሄዱ መደበቂያ ቤቱ ጋር ደርሰው በነደፉት እቅድ መሰረት ከፊትና ከኋላ ገብተው ድንገት ወደ ቤቱ ዘው ብለው ገብተው ይይዙታል። ጅረት መሳዩን ነገር ተሻግረው ወደ ቤቱ የሚወስደውን ኮረኮንች መንገድ

ከመድረሳቸው በፊት ወታደሩ ወደ ኋላ ቀረት አለና በዱላ ማጅራቱ ላይ ሲለው ተጠቀለለ። ቶሎ ብሎ ሸሚጡን ነጠቀው። ወደ ጢሻው ጎትተና አስገባው። በያዘው ገመድ እጁን ካሰረው በኋላ ሲሙህ ከሞካሪ አፉን በመሀረብ ሊሸጉጥበት ተዘጋጀ። አካባቢው በዚያ ሰአት ሰው የሚያልፍበት አይደለም፣ አንርሱም ሰው እንዳያያቸው ነው ዶሂን መንገድ የመረጡት። ቢሙህ እንኳን ወደ ቦታው የሚያደርስለት ሰው አያገኝም። ሰውየው በጭንቀት…ምን እያደረግክ ነው?‹‹አለው

‹‹ምንም››
‹‹መታሽን እኮ››
‹‹አንተ ብቻነው››
‹‹ለምን?››
‹‹እነግርሀለሁ››
‹‹ልጄን ልንይዝ አይደል እንዴ የምንሄደው?››
‹‹የምን ልጅ?››
‹‹የኢህአፓ ስኳድ ያልከኝ ልንገድል አይደል የመጣነው?››
‹‹እሱን እንገድልም››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ሟሬ የአንተ ተራ ነው››
‹‹አልገባኝም››
‹‹እዚህ የተደበቀ የኢህአፓ አባል የለም››
‹‹አንተ የአብዮቱ ልጅ አይደለህ እንዴ?››
‹‹አይደለሁም ሆኜም አላውቅም››
‹‹ለአብዮቱና ለሀገርህ ታማኝ ሆነህ……››
‹‹ምናልክ?››
‹‹ወታደር አይደለህ እንዴ››
‹‹ሆኜም አላውቅም››
‹‹ግን ማነህ አንተ?››
‹‹ታደለ ነኝ››
‹‹ታደለ!!!!!››
‹‹አዎ››
‹‹ጎርግጠኛ ታደለ ነህ››



‹‹አዎ አልኩህ››
‹‹አንተ ሞተህ የለም እንዴ?››
‹‹አዎ››
‹‹እና››
‹‹ከሰማይ ቤት መጥቼ ነው››
‹‹እንዴህ አይነት ነገር አለ እንዴ››
‹‹ምኑ?››
‹‹ሞቶ መመለስ››
‹‹ተጀምሯል እኮ››
‹‹አልገባኝም››
‹‹ያንተንና ያዜያን ሰውዬ ጉዳይ ለመጨረስ ነው የመጣሁት››
‹‹ማንን?››
‹‹የኢብዮት ጥበቃ ሊቀመንበሩ››
‹‹አገኙህ አይለቁህም››
‹‹ሊያውቁኝ አይችሉም››
‹‹እንዴት››
‹‹አንተ አፍንጫህ ስር ሆኜ መች አወቅኸኝ››
‹‹ግን ስትሞት እኮ አይቼሃለሁ››
‹‹ስትገድለኝ እንጂ ነፍሴ ስትወጣ አይተሃል?
‹‹ሁሉም ሰው እኮ መገደላችሁን አረጋግጦ ነው የሄደው››
‹‹እሱም ቀደቼ ነው ራሴን ያወቅሁት ግን…››
‹‹ግን ምን››
‹‹ሰው ያለቀት አይሞትም››
‹‹እንደዛ ነው››
‹‹አዎ ለምሳሌ ዛሬ ያንተ ቀን ነው››
‹‹ጉያቶችን ስር ተሸሽገህ….
‹‹ሽጉጥ የሰጠሸኝ ቀን ነው የሞትነው››
‹‹ያሆነ ነገርህ ግን አያመጣልኝ ነበር››
‹‹ጥይት የሰጠሸኝ ቀን ታስታውሳለህ››
‹‹ምን››
‹‹20 ስትሰጠኝ እንጅ ያለቃል አላልኩህም››

‹‹እና››

‹‹ላንተ ነበር የምፈልገው››

‹‹ግን ጨክነህ ልትገለኝ ነው››

‹‹ስንቱን ስትጨፈጭፍ ያላዘንክ ወዳንተ ሞት ሲመጣ ፈራህ?››

‹‹ግን አሁንም አንተ መሆንህን ማመን አቅቶኛል››

‹‹ይሄን እንዴት እንደተቆረጠ ታውቃለህ?››

‹‹የቱ? ››

‹‹አፍንጫዬ››

‹‹አውቃለሁ፤ጦር ሜዳ በጥይት ተመተህ አይደል?››

‹‹እሱ የውሸት ታሪክ ነው››

‹‹እና››

‹‹እስር ቤት እያለሁ ወታደሩ በሳንጃ አፍንጫዬን እንዲቆርጠኝ ያዘዝከው አንተ አይደለህ››

‹‹የት?››

‹‹ለመጨረሻ ግዜ የተገረፍኩ ቀን››(ቦታውን ነገረው)

ቀንደኛ ተብለው የተያዙትን የኢህአፓ አባላት ለማውጣጣት ብዙ አይነት የማስቃያግርፍያ ተካሂዶ ነበር። ታደሰ አስቸጋሪ ስለነበር ለግርፍያ ከሌላ ቦታ የመጣው ወታደር ሲታገለው አፍንጫውን በሳንጃ ቆርጦ የተቦጨቀውን እንዳጎረሰው አስታወሰው።ለግድያበወሰዷቸው ግዜ ከአብዮት ጥበቃ ፤ከህዝብ ደህንነትና ከቀበሌው አመራር የተውጣጣ ሰዎች ወደ ቦታው አብረው ሄደዋል። ግድያውን የሚፈጽሙት የተውጣጣው ቡድን አባላት ናቸው። ሁሉም ክላሽና ቺቺ ከነሙሉ ካርታው ታጥቀዋል።

ለግድያ የተደረደሩት የኢህአፓ አባላት ገዳዮቹ ከፊት ለፊታቸው መሆናቸውን አይተዋል።እንዳቸውም አይናቸው ስላልታሰረ ማን የት ጋር እንደቆመና ምን አይነት መሳርያ እንደያዙ ተመልክተዋል።ሟቾቹ ይዘምራሉ ፤ደርግን ያወግዛሉ፤ ይሳደባሉ።ተኩሱ ሲጀመር ሁሉም በእሩምታ እየመቱ ነው የጣሉዋቸው።ታደሰ ምክትል ሲቀመንበሩ የቆመበትን ቦታ፤ከግድያው በፊት ያደረገውን ንግግርና ያሰማውን





መፈክር ያስታውሰዋል። ማስታወስ የፈለገው ለማስረጃነት ይጠቀመኛል በሚል አልነበረም። ሲሞት ስለሆነ አይገናኙም። ነገር ግን በቦታው ስለነበር የግድ መስማት ስለነበረበት ነው።

ታደሰ ከግድያው በፊት ታናሽ ወንድሙ አጠገቡ መሆኑን ያስታወሳል፡ ከሌት ጓደኛው ጋር በሰንሰለት ተያይዘው እንደመጡ አይረሳም። ጥይት ከመተኮሱ በፊት ታደሰ ለወንድሙ‹‹ፈራህ እንዴ?››አለው

‹‹አልፈራሁም››

‹‹አትፍራ አይዞህ››

‹‹አንተ ወንድሜ እያለህልኝ እንዴት እፈራለሁ››

‹‹እናታችን ምን ትላለች››

‹‹ጠዋት ስታጣን ቁርጧን ታውቃለች››

‹‹ትንሹ ወንድማችንስ?››

‹‹እሱም ቆራጥ ስለሆነ ለድርጅቱ ታማኝ ነው››

‹‹በእነዚህ መገደል ያማል››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹በነዚህ ባልተማሩት ሰዎች መገደል››

‹‹እናገኛቸዋለን ተዋቸው››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ነገ በእኛ ሰዎች ተገድለው ያለንበት ድረስ ይመጣሉ››

‹‹እያለቀስክ ነው እንዴ?››

‹‹ማን››

‹‹አንተ››

‹‹እኔ ለእነዚህ አላለቅስም ማልቀስማ ለእነርሱ ሞራል መስጠት ነው››

መዝሙሩ ተጀምሯል ።አንድ ላይ እየጮሁ ነበር። ‹‹.....ሁላችሁም ፋሽስት ናችሁ ፤የህዝቡን ትግል አትቀለብሱም›› እያሉ በጩኸት እየተናገሩ ነው።

ተኩስ የተጀመረው በአንድ ላይ ነው።ከዚያ ሁሉም እየጮኹ ተረፈረፉ፡ ቀድሞ የወደቀው እሱ ነበር። ሌሎች በላዩ ላይ ተረባረቡበት። ‹‹በደምብ እንጨርሳቸው...›› የሚል ድምጽ ሰማ። የማጣርያ ተኩስ ሲደረግ እግሩን በጣም አመመው። አሁን የተተኮሰው

ጥይት እግሩ ውስጥ ሰርስሮ እየገባ ነው፡፡ ያመለጡትን ለመያዝ መሯሯጥ ጀመሩ፡ ፡ሌሎቹ ከመሄዳቸው በፊት አፈር ማልበስ ተጀመረ፡፡ አፈር ማልበሱ እንደነገሩ እንጂ በደምብ የተከናወነ አይደለም፡፡‹‹.... ብዙም አታልብሷቸው ጅብ በደምብ ይለቅማቸዋል›› የሚል ድምጽ ሰማ፡፡
ታደሰ ሁለት አይነት ነገር ላይ ነው ያለው፡፡ነገሮችን በደመነፍስ ነው የሚከታተለው፡፡እየሞተ መሆኑን ይሰማዋል፡፡እንደገና ነፍስ እንዳለውና ከዚህ ቦታ መውጣት እንደሚፈልግ ሆኖ ተንቀሳቀሰ ፡፡ግን አቅም አልነበረውም፡፡ሙሉ ለሙሉ ወደእሱ ማንነቱ እስኪመለስ ጠበቀ፡፡አሁን ራሱን በደምብ እያወቀ ነው፡፡ ጉልበቱንአሰባሰበ፡፡ከላይ የተከመሩትን ሬሳዎች አራግፎ ለመውጣት ብዙ ደቂቃዎች ፈጀበት፡፡ብዙ ከጣረ በኋላ ብቅ አለ፡፡ትንሽ ቢቆይ አዛው ያበቃለት ነበር፡፡፡ወደየት እንደሚሄድ ባያውቅም እግሩ ወደሚወስደውና ዋናው መንገድ ነው ብሎ ወዳሰበበት መሄድ ጀመረ፡፡የውሾች ጩኸት ሰማ፡፡በጨረቃ ብርሀን እየታገዘ ስለሚሄድ ውሾቹን ለማምለጥ ዛፍ ላይ ለመውጣት ሞከረ፡፡ግን እግሩ ዛፉን ሊቆነጥጥለት አልቻለም፡፡፡በቅርብ የወደቀ የቅርንጫፍ ዝንጣፊ ነገር አነሳና ውሾችን ለመከላከል ተዘጋጀ ፡፡

የቤቱ ባለቤት ድምጽ ስለሰማ ወደውጭ ወጣ፡፡ታደሰ ሰው ስላየ ደስ አለው፡፡ ግን ደግሞ ከከተማ ወደ ገጠር የሚሄዱትን ወጣቶች እየያዙ ለደርግ ያስረክባሉ የሚል ነገር ስለሰማ ፈራ ፡፡ግን ሰውየው ስላየው ወደእሱ ቀረበ‹‹ማነህ?››አለው

‹‹እኔ ነኝ››

‹‹እኮ ማን?››

‹‹ድብደባ ደርሶብኝ ነው››

‹‹ማነው የደበደበህ?››

‹‹ማጅራት መቺዎች››

ሰውየው አዘነለትና ወደ ቤት አስገባው፡፡ በባህላዊ ህክምና እየተረዳ ታከመ፡፡ ጠዋት ሀኪም ይገፎልህ መጣለሁ ብሎት ወጣ፡ ሚስቱ ፊት ላይ የሚመለከተው ነገር ጥሩ አልነበረም ፡፡ደግሞም ፈርታለች፡፡ ፊቷ ላይ ያለውን ነገር አነበበ፡፡ ጥሩ አልነበረም ወጥቶ መሄድ እንደሚፈልግ ነገራት ፡፡ፊቷ ላይ ያለው ነገር አምልጥ የሚል





እንደሆነ ገባው፡፡ደርግ ለገበሬዎች ሽልማትና ተጨማሪ መሬት ስሊሚሰጣቸው ጸረ አብዮት የተባሉትን ያስረክባሉ የሚል ነገር ሰምቷል፡፡ይሄ ወጣት ከደርግ ያመለጠና በመንግስት የሚፈለግ እንደሆነ አልጠፋውም፡፡

ሰውየው በየት በኩል እንደሄደ ቀድሞ አይቷል፡፡በተቃራኒ አቅጣጫ እግሩን እየጎተተ ሄደ፡፡ሄደና ራቀ፡፡ርቆም በደምብ ራቀ፡፡ አሁንም ራቀ፡፡የሰዎች ድምጽ ስለሰማ ተደበቀ፡፡ የገመተው ትክክል ነበር ፡፡አምስት የሚሆኑ የአካባቢ አብዮት ጠባቂዎች ጠመንጃ እንዳነገቱ ሰውየው እየመራቸው ወደቤቱ እየሄዱ ነው፡፡እቤት ደርሰው እስኪመለሱ ቢያንስ ግማሽ ሰአት ይፈጃል፡፡በዚህ ግዜ ብዙ እንደሚርቅ ገምቶ በሌላ አቅጣጫ ተንቀሳቀሰ፡፡ወደዋናው መንገድ ደረሰና አንድ የጭነት መኪና አገኘ፡፡ሰውየውን ቢጠይቅ ላይጭነው ይችላል፡፡ ሳይታይ ከውስጥ ገባና ተደበቀ፡፡ወደከተማ እንደገባ ቀስ ብሎ ወረደ፡፡ አጎቱ ቤት ተደብቆ ስድስት ወር ቆየ፡፡ወደ ሀረር ሄደና የተወሰነ ግዜ ሰነበተ፡፡ በጥይት የተመታ ቀን አይኑ መጥፋቱን አረጋግጧል፡፡እግሩ ስር የተሰገሰጉት ጥይቶች ቅዝቃዜ ሲኖር እንጅ ሰላሙን አላወኩትም፡፡ ቀጣዩ ስራ ከሞትነት ተነስቶ ገዳዮቹን ማሳደድ ነው፡፡እናም ጥይት የተኮሰበትና ያሰቃየውን ሰው አሁን በዱላ ብሎ ጥሎታል፡፡ታደሰ በምክትል ሊቀመንበሩ ላይ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት አንድ ነገር መጠየቅ ፈልጓል፡፡በእሱ ሴል ስር የነበረች ልጅ ትሙት ትኑር አያውቅም፡፡ልጅቷን በትግሉ ከጠንካራነቷ ባሻገር በፍቅር ይወዳታል፡፡ አብረው ነው የተያዙት፡፡ከእስር ቤት ይሄ ሰው ነው አውጥቶ የወሰዳት፡፡ ታደሰ‹‹አንድ ነገርልጠይቅህ?››

‹‹ምን?››

‹‹ትእግስትን ታውቃታለህ አይደል?››(ስሟ የተቀየረ)

‹‹የቷ››(በሽጉጡ እጀታ መታው)

‹‹አታውቃትም?››

‹‹አውቃታለሁ››

‹‹የት ነው ያደረግካት?››

‹‹ማለት?››

‹‹ገድለሃታል ወይስ በህይወት አለች?››

‹‹ተወስዳለች››
‹‹የት››
‹‹ወደ ሌላ እስር ቤት››
‹‹ምን አድርጋ››

ሁለቱም የነበሩበት ቦታ በምሽት ሰው አያልፍበትም:: ማጅራት መችዎች ብዙ ሰው ላይ ጥቃት ስለፈጸሙ 12 ሰአት ካለፈ በኋላ በዚህ መንገድ ዝር የሚል ሰው አይገኝም ::ለዚህም ነው ታደሰ ገዳዩን ለመግደል አመቺ ብሎ የመረጠው:: እናም ብዙም ሳይቆይ በያዘው ሽጉጥ መትቶ ከገደለው በኋላ በአቋራጭ መንገድ ገስግሶ አብዮት ጥበቃው ቤት ሄዶ ወደ ቀበሌ ጽፈት ቤት ተዘዋወረና ኢህአፓ ልትገድለኝ ነው ብሎ እዛው አደረ:: ሬሳው የሚገኘው ጠዋት በመሆኑ እሱን የሚጠረጥረው አይኖርም ::መገደሉን ሲነግሩት አለቀሰ::

ያሰበውን አሳካና በቀጣዩ የአብዮት ጥበቃውን ሊቀመንበር ተኩሶ ገደለው:: ግን የገደለው ይምሰል እንጂ ሰውየው ከሞት ጫፍ ደርሶ ተረፈ::እሱ አምልጦ በሱዳን አቋርጦ አሜሪካ ገባ::የኢህአዴግን መግባት ተከትሎ ተመለሰ::የአብዮት ጥበቃውን ሊቀመንበር አልፎ አልፎ ይመለከተዋል::በደምብ አድርጎ ዳጋግሞ ነበር የተኮሰበት ግን እንዴት እንዳልገደለው ይገርመዋል::ቀኑ አይደለም ብሎ ደመደመ:: ለወንድሙ ሲል ነበር እሱን መግድል የፈለገው::በግርፍያ ያሰቃየው እሱ ነበር::በርሸናው ግዜ ሰውየው መሳርያ አነጣጥሮ ፊት ለፊታቸው ነበር::የያኔውን ነገር ሲያስታውስ ይጨንቀዋል::ሁል ግዜም ሞት ጎረቤቱ ነበር::ዛሬ ሁሉን ነገር ረስቶ በሰላም መኖር ጀመረ::





ምእራፍ 10

## የሞቃዲሾው ሰው

ለከፍተኛ ሹመት ወደ አዲስ አበባ የመጣው ሰው ምን አይነት ሀላፊነት እንደሚሰጡት እያውጠነጠነ ነው::ደግሞም በእርግጠኝነት እየተጠባበቀ ነበር::ሹመት ላይሰጡት እዚህ ድረስ ጠርተው እንደማያመጡት አውቋል:: ግን ደግሞ ቀድሞውን የፖሊስነት ባህሪው ተጠራጣሪ ስላደረገው ሽጉጡን ካስቀመጠበት እነሳና በኪሱ ውስጥ ደበቅ አድርጎ ሸጎጠው::ደርግ በፖለቲካ ትኩሳት ውስጥ በነበረበት ግዜ ኢህአፓ ግራና ቀኝ ወጥሮ በያዘበት ሰዓት ይህን ሰው ሹመት መስጠቱ ለእነርሱ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለ አውቀዋል::ኢህአፓ አብዛኛውን ላብአደር በእጁ ባደረገበት ግዜ ለሰውየው ሹመት በመስጠት አብላጫውን የወዛደር ሀይል ወደ እነርሱ ያስገባሉ::ደርግ ‹‹ወዛደር›› ኢህአፓ ደግሞ ‹‹ላብአደር›› በሚል ሁለቱም ሰራተኛው ሀይል ላይ ተፋጠዋል::ወዛደሩን የሚያንቀሳቅሱት መሪዎቹ እንደሆኑ ደርግ ዘግይቶ ቢደርስበትም አሁን ግን በእጁ ለማስገባት ወይም ደግሞ….በቃ!!!!

ለሹመት ከክፍለ ሀገር የተጠራው ሰውዬ ምሽት ነው አዲስ አበባ የገባው:ያረፈው ራስ ሆቴል ነበር::ሹመቱን የሚቀበለው እዚህ ሆቴል አይደለም ወይም ዋናው መስሪያ ቤት አልነበረም::ሹመቱ አንድ ትልቅ ቦታ እንደሚሰጠው በጭምጭምታ ሰምቷል::የደርግ ሰዎች ያረፈበት ሆቴል ድረስ በጠዋቱ ብቅ አሉ::ከእነርሱ ጋር አንድ ትልቅ ባለስልጣን ይገኛል:: ወታደሮቹ መሳርያ ታጥቀው እዚህ የተገኙት ባለስልጣኑን ለመጠበቅ ይሁን አዲስ ተሿሚውን ለማጀብ አልታወቀም::ግን ይሄ ነገር አሁን በቅርብ ይታወቃል:: ወታደሮቹ እንግዳው ሰው ወዳለበት ተጠጉና‹‹ጤና ይስጥልኝ››አሉ

‹‹ጤና ይስጥልኝ››
‹‹አቶ ጌታቸው ነዎት?››

‹‹አዎ››
‹‹እርስዎ ጋር ነው የመጣነው››
‹‹ማን ልበል?››
‹‹የቤተመንግስት ልዩ ጥበቃ ሀይልና....››
‹‹ጉዳዩ ምንድነው?››
‹‹እርስዎን በክብር እንድናመጣ ታዘን ነው››
‹‹ማነው ያዘዘው?››
‹‹የደርጉ ሊቀመንበር ሻለቃ መንግስቱ እየጠበቁዎት ነው››
‹‹እንደዛ ነው ነገሩ!!››
‹‹አዎ››
‹‹እንሂዳ!››
‹‹እሽ፤እርስዎን ስላጀብን ትልቅ ኩራት ይሰማናል››
‹‹እኔም ለዚህ በመብቃቴ.....››
‹‹ከሆቴሉ ቶሎ እንውጣና መኪና ውስጥ እንግባ››
‹‹መኪና ይዛችኋል››
‹‹አዎ››
‹‹እናንተ በእርሱ ሂዱ››
‹‹ማለት››
‹‹እኔ መኪና ስላለኝ ተከታትለን ብንሄድስ?››
‹‹እንደዛ አይሆንም››
‹‹ለምን?››
‹‹ኢህአፓ አድፍጣ ብዙ ሰው ነጥቃናለች እርስዎንም ማጣት አንፈልግም››
‹‹ግን.....››
‹‹ግን ምን?››
‹‹ጉዳዩ ግራ አጋብቶኛል››
‹‹ማለት››
‹‹ለምን እንደተፈለግሁ አልገባኝም››
‹‹እርስዎ ተሿሚ እንደሆኑ ነው የተነገረን››
‹‹እንደዛ ነው››





‹‹አዎ ደግሞም በእንክብካቤ እንድናመጣዎት ነው የታዘዝነው። ይልቅ...››
‹‹ይልቅ ምን?››
‹‹እነዚህ ኢህአፓዎች እዚህ አካባቢ ስለሚኖሩ ቶሎ እንውጣ››
‹‹እነርሱን አትፍራ››
‹‹እንዴት?››
‹‹በቅርቡ ድባቅ ይገባሉ››
‹‹ድፍረትዎ ጥሩ ነው። አሁን ግን እንሂድ››

አዲሱ ተሿሚ ሰው እዚህ መኢሰማ ውስጥ ትልቅ ቦታ ሊሰጡት እንደሚችሉ ይገመታል።የታጠቁትና ከመታጠቅም በላይ የወደሩት ወታደሮች በላንደሮቨር መኪና ውስጥ ቶሎ ገቡ ሰውየውንም ከመሀል አደረጉት።ልዩ ጥበቃ እያደረጉለት ነው።መኪናዋ በፍልውሃ አድርጋ በውጭ ጉዳይ ቀና ብላ ወደ ቤተመንግስት ሄደች።ቀስ እያለች ዳገቱን መውጣት ጀመረች።ሂልተን ሆቴል አካባቢ ደረሰች። የወታደሮቹ አለቃ‹‹ አቶ ጌታቸው›አለ

‹‹አቤት››
‹‹ሽጉጥ ይዘሃል?››
‹‹ማለት!!!››
‹‹መሳርያ ከያዝክ ወደ ቤተመንግስት ይዞ መግባት አይቻልም››
‹‹ምን ችግር አለው?››
‹‹እንዴት?››
‹‹እኔ እኮ የናንተ ሰው ነኝ››
‹‹ለእኛ ታማኝ እንደሆንክ እናውቃለን››
‹‹እና››
‹‹ማንም ሰው መሳርያ ቤተመንግስት ይዞ አይገባም››
‹‹እናንተ ይዛችሁ የለ››
‹‹እኛ እኮ ወታደር ነን››
‹‹እኔም..የመንግስት.....››
‹‹ብትሰጠኝ ይሻላል››
‹‹ዛቻ ነው?››

‹‹አይደለም››

‹‹እና››

‹‹መሳርያህን ስጠን››

‹‹የእናንተ ሰው ነኝ አልኳችሁ እኮ››

‹‹እውነቱን እንንገርህ››

‹‹ምን››

‹‹አንተም የእኛ አይደለህም እኛም ያንተ አይደለንም››

ጌታቸው ወደ ኪሱ ከመግባቱ በፊት ወታደሩ በፍጥነት ከጎን ደገነበትና መሳርያውን ከኪሱ አውጥቶ ወሰደው።ቅድም የነበረው የመግባባትና የአንድ ነን ስሜት አሁን በቦታው የለም።እሱም ቢሆን ለስልጣን እንዳልጠሩት አውቋል።ቅድም በራሳችን መኪና እንሂድ ያለው ሁኔታቸውን ተመልክቶ ሊያመልጥ ነበር። ከዛ በፊት ደግሞ ሆቴል ውስጥ መሳርያ ተኩሶ ግርግር ፈጥሮ ለማምለጥ ፈልጎ ነበር። አሁን ግን ሁሉም ነገር ከእጁ አምልጧል።ሰሞኑን ከድሬዳዋ ከመምጣቱ በፊት በመኪናው ሲሄድ ተኩሰውበት ሊገድሉት ሰጥቶት ነው ያመለጣቸው።ተኳሾቹን ለማሳደድ ከመኪና ወርዶ ጎማውን ሲያይ ከለላ የያዙ መስሏቸው አመለጡት እንጂ እዛው ይዋደቁ ነበር። አሁንም ከዚያ የተረፈችውን ነፍሱን እዚህ ሊያስነጥቃት ነው።አሁን አጅበው ወደ ቤተመንግስት የሚወስዱት የልዩ ሀይል ወታደሮች ናቸው።ምን ማድረግ ይቻል እንደሆን ማውጠንጠን ጀመረ። እዚህ ቤተመንግስት ከገባ በህይወት እንደማይመለስ ተረድቷል።ብዙዎቹ የሚያውቃቸው ሰዎች እዚህ ገብተው ተመልሰው እንዳልወጡ ያውቃል።እናም አተርፋለሁ ብሎ ተስፋ ማድረግ የለበትም። ምናልባትም እድል ካለው እዚሁ መኪና ውስጥ መጨረስ ይኖርበታል፡

ሰዎቹን ቆጠራቸው ከሹፌሩ ጋ አራት ናቸው። አቀማመጣቸውና መሳርያ አያያዛቸውን ተመለከተ።ስፖርተኛ ነው። ለአሜድላና ለድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ በኢትዮጵያ ሻምፒዮና ተጫውቷል። በሶስተኛው አፍሪካ ዋንጫ ለብሄራዊ ቡድን የመመረጥ እድል አግኝቷል ።በእሱ ቦታ እነበርሄ ጎይቶምና ሌሎቹ የማይቀመጡ ስለሆን ለመሰለፍ እድሉን አላገኘም።የአሜድላ ቡድን በአካል ብቃት ጠንካራና የማይበገር አድርጎታል። አሁንም ጥንካሬው ከእርሱ ጋ





አብሮት አለ።እነዚህን ወታደሮች እዚህ መኪና ውስጥ ግብ ግብ ቢገጥም ሊተርፍ ይችላል፤ካልሆነም ይሞታል።አሁን የሚሄድበት ቦታ ወደ ሞት በመሆኑ እዚህ ቢጋጠም ልዩነት የለውም።ሰዎቹን ዞር ብሎ ተመለከተ፤ተዘጋጀ ፤ማንኛውን ቀድሞ መምታት እንዳለበት አሰበ። አራቱን አመቻቸ።ወደ ድርጊት ሊገባ ሲዘጋጅ መኪናው ወደ ቤተመንግስት ሰተት ብሎ ገባና አንድ ቤት ፊት ለፊት ቆመ።ቅድም በትህትና ሲያናግሩት የነበሩት ወታደሮች አሁን እያመናጩቁና እየወዘወዙ አስወረዱት።ከቤቱ አጠገብ በአንድ ጥግ አቆሙት። ወታደሮቹ ራቅ ብለው ስለቆሙ እዚህ ሊረሽኑት እንዳዘጋጁት ነው የገመተው።ምን ማድረግ እንዳለበትም ግራ ገባው።

ቤቱ ትንሽ ከፍ ብሎ በረንዳ ያለው ነው።በረንዳው ላይ አንድ ሰው ከርቀት አየ።ሰውየው በበረንዳው ኮሪደር ላይ እየተራመደ ነው። እየተራመደም ወደእርሱ መጣ ።በረንዳ ላይ የሚራመደው ሰው አሁን ገቢ ውስጥ የመጣውን ሰው አውቆታል።ሁለቱም አይተዋወቁም ግን ከሁኔታው እንደሚታየው በዚህ ሰአት ከግቢው ታዞ የወጣው መኪና ማንን ለማምጣት እንደሚሄድ አውቋል።እናም ተፈላጊው ሰው ወደ ግቢ መድረሱን ስላወቀ በደምብ ሊመለከተው በኮሪደሩ እየተራመደ ወደ እስረኛው ብቅ አለ።ጌታቸውና ተራማጁ ሰው ተያዩ።ሁለቱም በተቃራኒ የፖለቲካ መስመር ያሉ ናቸው።ተራማጁ ሰው ‹‹አንተ ነህ እንዲህ ያስቸገረከው?››አይነት አስተያየት ተመለከተው ‹‹..እናንተ ኢህአፓዎች አሁን ያልቅላችኋል››አይነት ገረመመው።እስረኛው ኮሪደሩ ላይ እየተራመደ አፍጥጦ የሚያየውን ሰው እሱም ተመለከተው።ሰውየው ሀይሌ ፊዳ ነው።ሀይሌ የመኢሶን ሊቀመንበር ነው።ደግሞም የህዝብ ደህንነት ድርጅት የበላይ ሀላፊ ነው።በወቅቱ መኢሶን ከደርግ ጋር በመሆን ኢህአፓን በመመንጠር ስራ ላይ ተሳትፈው ነበር።ኢህአፓም በተለይ የመኢሶንን ሰዎች እያሳደደ በመግደል ላይ ስለተጠመደ ሀይሌን ጨምሮ ዋናዎቹ ሀላፊዎች ቤተመንግስት የመሸጉበት ግዜ ነበር።ብዙዎቹ ጸጉር ለመስተካከል እንኳን ከተማ የማይወጡበት ግዜ እንደነበር ይወራባቸዋል።ያን ግዜ ነው እንግዲህ ጌታቸውን ሹመት ሊሰጥህ ነው በሚል አባብለውና አጥምደው ወደ ቤተመንግስት የወሰዱት።





አሁን ታጅቦ የመጣውን ሰው ሻለቃ መንግስቱ ወዳለበት ሊወስዱት ተዘጋጁ።ግን ትእዛዙ ይሄ አልነበረም።ወደ ሻለቃ መንግስቱ ጋር ከመሄዱ በፊት ወደ እንግዳ መቀበያ ክፍል አስገቡት።እንግዳ መቀበያው ለሚመጣው ሰው ተስማሚ እንደሚሆን ይጠበቃል።፡መሬቱ ደም በደም ሆኗል።ቤቱ የከብት እርድ የተካሄደበት ይመስላል። ግድግዳው የእጅ መዳፍ ታትሞበታል።የሆነ ሰው እጁ ደም በደም ሆኖ እዚህ ላይ አድርግ ብለው ያተመበት ነው። እንግዳውን ወደ ውስጥ አስገብተው አስቀመጡት። አስቀምጠውም ማውራት ጀመሩ።

‹‹ጌታቸው›› አሉት

‹‹አቤት››

‹‹ይሄ ማህተም ይታይሃል?››

‹‹የቱ?››

‹‹ግድግዳ ላይ ያለው››

‹‹ምንድነው?››

‹‹ማንበብ አትችልም?››

‹‹ምኑ ነው የሚነበበው?››

‹‹የእጅ ምልክቱ ይታይሃል››

‹‹እዎ››

‹‹የደም ማህተም ነው››

‹‹ምን ማለት ነው››

‹‹የዶክተር ተስፋዬ ገብረእዝጊ……››

‹‹የሞተው?››

‹‹እዎ የእሱ አሻራ ነው››

‹‹እና እኔ ለምን…››

‹‹እሱ እኮ ተሰቃይቶ ነው የሞተው››

‹‹ምን እያላችሁ ነው››

‹‹እስካሁን የነገርንህ አልገባህም?››

‹‹የተስፋዬ አሻራ ነው አላችሁኝ››

‹‹አሁን ለእኛ ሁሉንም ነገር ካልነገርከን …››

‹‹ምን ለማድረግ››

‹‹እዚህ ላይ የደም አሻራ ትተህ ትሞታለህ››

‹‹ምኑን ነው የምነግራችሁ››





አሁን የነገሩት ገብቶታል። ገርፈውትና ሸረካከተውት በደም የጨቀየውን የእጁን መዳፍ ግድግዳው ላይ ካተሙ በኋላ ነፍሱን እንደሚነጥቁት አውቋል።ጌታቸው የሚሰራው በድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ ነው። በመስርያ ቤቱ የሰራተኛ ማህበር ሊቀመንበር ነው። የፋብሪካው ሰራተኛ 7500 ነው።ይሄ ሁሉ ወዛደር በእርሱ ስር ነው ያለው።ስልጣኑ ይሄ ብቻ አይደለም ።የክፍለሀገሩ ሰራተኛ ሊቀመንበር ነው።ከመስርያ ቤቱ ጋር ጨምሮ 15 ሺህ ሰራተኞች አለቃ ነው። ወዛደሩን ከደርግ አስክዶ ወደ ኢህአፓ መስመር እያስገባ ነው በሚል ክስ ቀርቦበታል። ደርግ በድሬዳዋ የሚገኘውን የኢህአፓ መዋቅር በእርሱ ስር ነው ያለው በሚል ያምናል።ማመን ብቻ ሳይሆን ደምድመዋል።የእህቱ ልጅ ከኢህአፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አንዱ በመሆኑ ከእርሱም ጋር ተያይዞ በብዙ መንገድ እጁ ደርግን ሊጥሉ ከሚንቀሳቀሱ መካከል አንዱ እንደሆን ታምኖበታል።እናም ዛሬ ዋጋውን ያገኛል።ድሬዳዋ ውስጥ እሱን ማሰርና አስሮም ወደ አዲስ አበባ ማምጣት አስቸጋሪ ነው።ወዛደሩ አያስነካም።እዛም የመግደል ሙከራ ተደርጎ አምልጧቸዋል።ግዜው ደርሶ አድብተው በሹመት ሰበብ አዲስ አበባ አምጥተው ቤተመንግስት አስገብተውታል። አሁን ደርግ የሚተማመንበት የመግረፊያ ክፍል ውስጥ ይገኛል።ሁሉንም ነገር ካላወጣ ፍዳውን ያሳዩታል።በሰራተኛው አመራር ውስጥና እስከታችኛው የስልጣን እርከን እነማን የኢህአፓ አባል እንደሆኑና የት እደሚሰሩ ፤ምን ለማረግ እንዳሰቡ ማወቅ ይፈልጋሉ።በሌሎች መስርያ ቤት የሚገኙትን የኢህአፓ ሰዎች ከነመዋቅሩ ማወቅ ይፈልጋሉ።እሱ የበላይ ስለሆነ ብዙ ነገር ያውቃል። ሁሉ ገር ካልነገራቸው አለቀለት።ደግሞም እኮ ሁሉንም ነገር ከነገራቸው በኋላ እንደሚገሉት ያውቃል።አንዱን ግን መምረጥ ነበረበት።ገራፊዎቹ ለመከታተፍ ተዘጋጁ።ይሄ ከመሆኑ በፊት አንድ ነገር አሰበ።ዛሬ ለመግረፍና ከዚያም አልፎ ለመግደል ነው እዚህ ያመጡት። ነገር ግን ከዚህ በፊት እዚህ ቤተመንግስት በእንክብካቤ ነበር የተቀበሉት።ነገሩ ሲጀመር እንደዚህ ነው።

## እንደገና ወደጊላ

ሻለቃ መንግስቱ ሀይለማርያም ወደ ሱማሌ የሚሄደውን ሰው ከፍተኛ ጥበቃ እንዲደረግለት አዘዋል ፡፡ደግሞም መመርያ ለመስጠትና በሞራል ለማስታጠቅ ወደ እሳቸው ቢሮ እንዲመጣ ልከውበታል፡ የኢትዮጵያና ሶማልያ ጦርነት ተባብሷል፡፡ጦርነቱ ከፍ ብሎ ከእግረኛ አልፎ በታንክና በአየር እየተቀጣቀጡ ነው፡፡የጦርነቱ ሚዛን ወደ ሶማሌ እያመዘነና ድል እየተገኘ ቢሆንም ብዙ ሰው መስእዋት እየሆነ ነው፡፡የአለም አቀፍ ሚዲያ የሁለቱ የጦርነት ጉዳይ የእለት አጀንዳ እየሆነ ነው ፡፡በዚህ የጦርነት ሂደት ውስጥ ወደ ሱማልያ የሚሄደውን ሰው ሻለቃው ሰግተውለታል፡፡ሰውየው ለግዳጅ የሚሄድ አልነበረም፣ ለአምባሳደርነት ወደ ሱማሌ የሚጓዝም አይደለም፡፡የሁለቱ ሀገሮች ሁሉም ነገር ተቋርጦ በጦርነት ሂደት ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ሰውየው ኢንተርናሽናል አልቢትር ጌታቸው ገብረማርያም ነው፡፡ይሄን ሰው የአለም እግር ኳስ ፌዴሬሽን ወደ ሱማሌ እንዲሄድ አዞታል፡ መንግስት ጉዞውን ማስቆም አይችልም፡፡ ግን ደግሞ ዜጋው ወደ ሱማሌ ተልኮ እንዲሞትባቸው አይፈልጉም፡፡ደግሞም ሱማሌዎች በሰውየው ላይ እየዛቱ ነው፡፡ ሻለቃ መንግስቱ አልቢትሩን ቤተመንግስት አስጠሩት፡፡አቶ ይድነቃቸውና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ይዘውት ሄዱ፡፡ሻለቃው በአስቸጋሪ ስራ ላይ ቢሆኑም አልቢትሩን ‹‹ለመሄድ ወስነሃል?››አሉት

‹‹ታዝዤ ነው››

‹‹እምቢ ማለት አትችልም?››

‹‹ፍራቻ ያስመስላል››

‹‹እንግዲያውስ እኛም እንድትሄድ እንፈልጋለን››

‹‹እሺ››

‹‹ግን ታጥቀሃል?››

‹‹ምን?››

‹‹ሽጉጥ››

‹‹አልታጠቅኩም››

‹‹ከግምጃ ቤት መሳርያ ይሰጥሃል››

‹‹መታጠቅ አስፈላጊ አይደለም››





‹‹ታዲያ በባዶ እጅህ ልትዋጋ ነው››

‹‹መታጠቅ ስለማይቻል ነው››

‹‹ለምን?››

‹‹ሽጉጥ ይዞ መሄድ አይቻልም››

‹‹አንድ ነገር ቢያደርጉህስ?››

‹‹ለሀገሬ እንደተሰዋሁ እቆጥራለሁ››

‹‹የሚጠብቁህ ወታደሮች አብረውህ መሄድ አለባቸው ፤ ይሄ ትእዛዜ ነው››

‹‹እሺ››

‹‹ለመሆኑ መቼ ነው የምትሄደው?››

‹‹ከእነርሱ መልስ ሲመጣ ነው››

‹‹ከማን? ››

‹‹ከሱማሌዎቹ››

ኢትዮጵያና ሱማልያ የተጧጧፈ ጦርነት ላይ ባሉበት ግዜ የአለም ዋንጫ ማጣርያ ሱማልያና ኒጀር ሞቃዲሾ ውስጥ ወሳኝ የተባለ ጨዋታ ያደርጋሉ፡፡በወቅቱ የሱማልያ ቡድን ጠንካራ የነበረበትና በታሪኩ ለመጀመርያ ግዜ ለምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ ፍጻሜ ላይ የደረሰበት ግዜ ነበር፡፡ይሄን ጨዋታ ሱማሌ ማሸነፍና ማሸነፍ ብቻ ነው የሚጠበቅበት፡፡አልቢትሩ ከኢትዮጵያ መመደቡን ሲሰሙ ህዝቡ ቅሬታውን አቀረበ፤ ተንጫጫ ፡፡ፌዴሬሽኑ ተቃውሞውን ከፍ አድርጎ አሰማ፡፡ጉዳዩን ለፊፋ አሳወቀ፡፡የተመደበው አልቢትር እንዲቀየርላቸው አሳሰቡ፡፡ ፊፋ ግን ጨዋታውን መምራት ያለበት ይሄ አልቢትር መሆኑ አሳወቀ፡፡ነገሩ ወደ ሌላ ጉዳይ ሄደ፡፡ ኢትዮጵያ ሰው ስላላት በሱማሌ ጨዋታ የኢትዮጵያን አልቢትር መድባ ችግር ልትፈጥርብን ነው በሚል ቅስቀሳ ጀመሩ፡፡በግልጽ ልትበቀለን ነው አሉ፡፡ይድነቃቸው የካፍ ፕሬዝዳንት ነው፡፡የፊፋም አባል ነው፡፡ የአልቢትር ምደባ በእሱ በኩል እንደተካሄደ ነው ያመኑት፡፡ ይሄን ለቅስቀሳ ለመጠቀም በቂ ነው፡፡በዚህ ህዝቡን አነሳሱ፡ ፡ጉዳዩ ከፌዴሬሽኑ አልፎ ወደ መንግስት ተሸጋገረ፡፡ሶማሌዎቹ ይሄን አልቢትር ካላስቀየሩ በፖለቲካው በኩል በኢትዮጵያ እንደተበለጡ ነው የገመቱት፡፡

ሁለቱ ሀገሮች ጦርነት ላይ ናቸው፡፡ጦርነት ላይ ነው ሲባል ከቃላት አልፎ በመድፍ በታንክና በአየር እየተከታከቱ ነው፡፡ እየተከታከቱ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ብዙ ህዝብ እያለቀ ነው፡፡የሱማሊ መንግስት የተወሰደብንን መሬት እስካላስመለስን ድረስ ወደኋላ አንመለስም በሚል ዘልቀው ገብተዋል፡፡ እንዳውም ተወሰደብን ካሉት መሬት አልፈው ምስራቁን ክፍል ወስደዋል፡፡የሀገሪቱ መሪ ሲያድባሬ የሱማሌ ህዝብ በራሱ ፍላጎት እንደሚዋጋና የሚፈልገውን እስከሚያገኝ እንዳማይመለስ አያሳወቀ ነው፡፡በዚህ መሀል ኢትዮጵያዊ አልቢትር ወደ ሱማሌ ምድር ከገባ ህዝቡ በቁጣ ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶ በአልቢትሩ ላይ አደጋ ካደረሰ መንግስት ተጠያቂ እንደማይሆን አሳወቀ፡፡ይሄ ሁሉ ከመሆኑ በፊት አልቢትሩን እንዲቀይር የሱማሊ መንግስት በድጋሚ ለፊፋ አሳወቀ፡፡ከዚህም ሌላ ጠላቱ የሆነ ሀገር በጦርነት ላይ እያለን አንዴት ልናምነው እንችላለን አሉ፡፡ይሄ ብቻ ሳይሆን በትክክል አጫውቶን ብንሸነፍ እንኳን ህዝቡ አይቀበለውም፤ በዚህ የተነሳ አልቢትሩ ካልተቀየረልን ሞተን እንገኛለን አሉ፡፡ በመንግስት ደረጃ ሙግት እየተደረገበት ያለው ነገር ብዙዎቹን አሳምኗል፡፡በጦርነት ላይ እያሉ ጠላቱ ነው ከሚለው ሀገር አልቢትር መመደብ ተገቢ አይደለም በሚል የውጭ ሚዲያ ተቀበለው፡፡ ተቀባበለው ብቻ ሳይሆን ተቀባበለውና ጣራ ላይ አውጥቶ ሱማሊ ትልቅ አቅም አገኘ፡፡ሱማሌም በአለም አቀፍ ሚዲያና በተባባሪዎቹ እየታገዘ የፊፋን እጅ ጠምዝዞ አልቢትሩን ለማስቀየር ዳር አደረሰው፡፡ ፊፋ አጣብቂኝ ውስጥ ገባ ፡፡የሱማሌን ጥያቄ ተቀብሎ አልቢትሩን ከቀየረ ፊፋ ፖለቲካ ውስጥ ገባ ማለት ነው፡፡ፖለቲካ ውስጥ ገባ ማለት ደግሞ መርሁን ሊጥስ ነው፡፡ መርሁ ከተጣሰ ነገም የደበረው አገር እየተነሳ ምክንያት እየፈጠረ አልቢትር በማስቀየር ችግር ሊፈጥር ነው፡፡

ብዙዎቹ አለም አቀፍ አካላት ሁለቱ ሀገሮች በጦርነት ላይ ሆነው ለሶማልያ የኢትዮጵያ አልቢትር መመደቡ ይቃወማሉ፡፡ምሳሌም ያቀርባሉ፡፡በ1966 የአለም ዋንጫ ጀርመንና እንግሊዝ ለፍጻሜ ቀረቡ፡፡ እንግሊዝን ለማሸነፍ ያስቻለችው ግብ እስካሁን መግባትና ያለመግባቷን የሚያረጋግጥ አልተገኘም፡፡ የእንግሊዙ ጀኦፍ ሀርስት





በቴስታ የመታው ኳስ አግዳሚውን ብረት መትቶ ወደ መሬት ነጠረ፡፡ የነጠረው መስመሩ ላይ ነው፡፡እንግሊዞች ጎል ብለው ጨፈሩ ፡፡ ጀርመኖች ጎል አልገባም አሉ፡፡ የነጠረውንም ኳስ ወደ ውጭ አወጡ፡፡ አልቢትሩ በቅርብ አለ፡፡ግን እሱም ቢሆን መግባቱን አላረጋገጠም ፡፡ አልቢትሩ በርቀት የነበረውን መስመር ዳኛ ሊጠይቅ ሄደ፡፡መስመር ዳኛው መስመሩ ላይ ቆሞ መጠበቅ ሲገባው ዋናው ዳኛ ሲመጣ ተቻኩሎ ወደ ሜዳ ውስጥ ገባ፡፡ እንደደረሰም ጎል ነው አለ፡፡ አልቢትሩም መስመር ዳኛው ስለነገረው አጸደቀ፡፡ ስሕቱ አልቆ ስለነበረ በዚህች ግብ እንግሊዝ የአለም ዋንጫን ወሰደ፡፡ይህች ግብ በርቀት ያለው መስመር ዳኛ ቀርቶ በካሜራ እንኳን ደጋግሞ ሲታይ መግባቱን አላረጋገጠም፡፡ብዙዎቹ ይህችን ግብ የፖለቲካ ውሳኔ ይሏታል፡፡ ጀርመኖችም ቢሆን ‹‹በቀል ነው›› ብለው አምነዋል፡፡

ረዳት ዳኛው ዶቪድ ቫክራሞን ይባላል፡፡ መስኮቫዊ ነው፡፡ በሁለተኛው አለም ጦርነት ቤተሰቦቹና ዘመዶቹ በጀርመን ጦር ተገድለዋል፡፡እሱ በሰጠው ውሳኔ የመስኮብ ህዝብ ጀርመን በመሸነፉ አልቢትሩ ወደሀገሩ ሲገባ ትልቅ አቀባበል ነው የተደረገለት፡፡ ከዚያም አልፎ በስሙ ስታዲየም ተሰየመለት፡፡በጦርነት የጎዳቸውን ሀገር መበቀሉን መስኮቦች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ተጎጂ ሀገሮች ለቫክራሞን አጨብጭበውለታል፡፡በጦርነት ውስጥ ያሉ ሀገሮች አልቢትሮቻቸው እንዲህ አይነት ነገር መስራታቸው ለብዙ ግዜ ተነግሯል፡፡በአለም ላይ ይሄ አይነቱ ስሜት እያለ ሱማሌ አልቢትሩን አልቀበልም ማለቷ ብዙዎቹ ደገፉ፡፡ ሱማሌም ‹‹ከኢትዮጵያ ጋር በጦርነት ላይ ሆኜ እንዴት አልቢትሩን ልመን›› ብላ ሰውየው የሀገሬን መሬት እንዳይረግጥ በሚል በአቋሟ ገፍታለች፡፡

## እንደገና በሌላ አመት

የሁለተኛውን አለም ጦርነት ጠንሳሾች በጀርመን የሚገኙ የናዚ አባላት ናቸው፡፡አለቃቸው ደግሞ አዶልፍ ሂትለር ነው፡፡ሂትለር በከተማ ውስጥ ቅስቀሳ ሲያደርግ ለድህነታቸውና ለወድቀታቸው መነሻ ያደርገው በጀርመን የሚኖሩ አይሁድ ማህበረሰብን ነበር፡፡‹‹.....እነርሱ ሀብታምና ባለጸጋ ሆነው እኛን እያስራቡን፣እያስፈዙን ነው›› አለ፡፡

እንደገናም «....እነርሱ እየበለጸጉ እኛ እየቆረቆዘን ነው ››ብሎ ተናገረ፡፡የህገሪቱ ዜጎች የኑሮ ሁኔታ ከብዷቸው ድህነት በራቸውን እያንኳኳ ስለነበር ሂትለር ስለአይሁዶች የተናገረው ትክክል ነው በሚል ህዝቡ ተቀበለ፡፡ሂትለር ስልጣኑን ካደላደለ በኋላ አይሁዶችን ወደ እስር ቤት እንዲገቡ አደረገ፡፡ማስር ብቻ ሳይሆን መግደልም እንዳለባቸው ሊፓርቲው ውስኝ ሰዎች አሳወቀ፡፡ጀርመን አውሮፓን መውረር ጀመረ ፡፡የናዚ ጀርመን ጦር በሄደበት ሀገር አይሁዶችን እየለዩ ማሰርና ለብቻቸው በካምፖች ማቆየት ጀመሩ፡፡

ሂትለር የአይሁዶች ጉዳይ ለብቻው መያዝ ስላለበት ሁነኛና ታማኝ የሆነ ሰው ፈለገ፡፡ኤድዋርድ ሮችማንን መረጠ፡፡ሮችማን ጨካኝና ርህራሄ የሌለው በመሆኑ የሂትለርና የናዚውን ፍላጎት ከግብ ያደርሳል ተብሎ ብዙዎቹ ተስማሙበት፡፡ነገር ግን ሮችማን ስሜታዊና ስልት የለውም በሚል ተቃውሞ ተነሳበት፡፡ከእርሱ ይልቅ ነገሮች በብልሃትና በረቀቀ ሁኔታ አይሁዶችን መፍጀት የሚችል ሰው አለ ተባለ፡፡ይህ ሰው አዶልፍ ኢክማን ነው፡፡በማርቲን ቦርማን የሚመራው መራጭ ኮሚቴ ድምጽ እንዲሰጥበት አደረገ፡፡ በስብሰባው ላይ የነበረው አዶልፍ ኢክማን ለራሱ ድምጽ መስጠቱ ምን ያህል አይሁዶችን በመደምሰስ ስራ ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት እንዳለው ያሳየበት በመሆኑ የእሱን ስም አሳለፈ፡፡ሁኔታውንም ለሂትለር አሳወቀ፡፡አይሁዶችን በመጨፍጨፉ ስራ ኢክማን ፈልጎና ፈቅዶ፣አምኖበትና ተስማምቶ ለመስራት የፈለገው ጉዳይ ነበር፡፡

ኢክማን የመግደል ስራውን ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይል ለመስራት ሙሉ ፈቃደኛ በመሆኑ የአይሁድ ማህበረሰብ ሰዎችን ጊዜ ሳይፈጅ እንዲጨርሳቸው ተመደበ፡፡11 ሚሊዮን አይሁድ በተወሰነ አመት ለመጨረስ እቅድ ያዘ፡፡ለስራው የመደባቸው ሰዎች እንደርሱ አይሁዶችን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሱትን ነበር ፡፡አይሁዶችን ብቻ ሳይሆን አይሁዶችን የሚደብቁትን፣አይሁዶችን ያገቡትን ፣ከዚያም አልፎ አይሁዶችን ለመግደል ዳተኛ የሆኑትንና ለማሰር የተሰላቹትን ጀርመናውያን ጭምር መፍጀት ጀመረ፡፡አይሁድ የተባለ ከተደበቀት ጉርጓድ ጨምሮ በየቦታው እያሳደነ መግደሉን አጧጧፈው፡፡የጀርመን





ጦር ኢላማ እንዲለማመድ አይሁዶችን አቀረበላቸው፡፡ ይሄም ትልቅ እድገት ነው ተባለ፡፡ኢላማን በሰው መለማመድ የሚሞከር አልነበረም፡፡ አፎቹን ከግንድ ጋር ያስሩና ለኢላማ ተለማማጆች.. አይኑ ላይ ፣ ግንባሩ ላይ፣ሆዱ ላይ.... እያሉ ተኩስ ይለማመዱባቸዋል፡፡ይሄን ሁሉ ሀሳብ አምጥቶ የሚያስፈጽመው ኢክማን ነው፡፡አዶልፍ ኢክማን ተደናቂና በሂትለር ተከታታይ የምስጋና ደብዳቤ ደረሰው፡፡የማእረግ እድገትም አገኘ፡፡ከተጠበቀው በላይ እድገት እያሳየ በመምጣቱ መነጋገርያ ሆነ፡፡

ኢክማን የሚለው ስም በአይሁድ ማህበረሰ የቅዠት ስያሜ ሆነ፡፡ገዳዮችና አሳዳጆች እንዳይሰንፉ ማበረታቻ ገንዘብ እስከመሸለም ደረሰ፡፡ወደ ሪጋ በሄደበት ግዜ በአካባቢው አዛዥ ለነበረው ለኤድዋርድ ሮችማን‹‹...የኔ ወታደሮች ትንሽ ስለተሰላቹ አንተ ጋር ጎበዝ ገዳይ ካለ በእድገት ልውሰዳቸው ››በሚል ጥያቄ አቀረበ ፡፡እንዳለውም ተሳካለት፡፡በአውሮፓ ለስድስት ወር አሰሳና ግድያ ጋብ አለ፡፡አይሁዶች ኢክማን ተቆናል በሚል ትንሽ ተንፈስ አሉ፡፡ሀሳባቸው ግን ትክክል አልነበረም፡፡አሳዳጅና ገዳዮቹ ከፍተኛ የመግደልና የማሳደድ ትምህትርት እየወሰዱ ነበር፡፡ከስልጠናው ሲመለሱ ግድያና ማሳደዱ በሶስት እጥፍ የጨመረ ነበር፡፡

በአራት አመት ተኩል ግዜ ስድስት ሚሊዮን አይሁዶችን ገደለ፡፡በመጨረሻ ጦርነቱ አልቆ የናዚ አባላት ከየቦታው እየታደኑ በኑረንበርግ ፍርድ ቤት ቀረቡ፡፡ሞት እየተፈረደባቸው ፋይላቸው ተዘጋ፡፡ያ ሁሉ የናዚ አባላት ለፍርድ ሲቀርብ ለእስራሎች ግን ብዙም ያስደሰተ ነገር አልነበረም፡፡ከህጻን እስካዋቂ አይሁዶች የሚፈልጉት አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡እሱም አዶልፍ ኢክማንን ነው፡፡ግን ኢክማን ሊገኝ አልቻለም፡፡በብዙ ቦታ መፈለጋቸውና ማፈላለጋቸውን አልተውትም፡፡ከሀምሳ ሽህ በላይ ጥቆማዎች ለተቋቋመው ቡድን ተልከዋል፡፡የተጣሩትና እምነት የተጠላባቸው ቦታ አሰሳ ቢደረግባቸውም ሰውየው ሊገኝ አልቻለም ፡፡አስራ አምስት አመት ሙሉ ሲፈልጉ ቢሰላቹም ተስፋ አልቆረጡም ፡፡በመጨረሻ ግን ተስፋ መቁረጡ ብቅ አለ፡፡አንድ ቀን በፖላንድ የሚኖር አይሁድ ኢክማን የት እንዳለ ስሙም ማን እንደሚሰኝ ጻፈላቸው፡፡ይሄ ጥቆማ እንደሌሎች

ጊዜ በመሆኑ ትኩረት አልሰጡም ::ግን የኤክማንን ነገር መተው የሚችሉት ባለመሆኑ ‹‹ለመጨረሻ ጊዜ እንሞክር...›› አይነት ስዚህ ሰውዬ ጥቆማ ቦታ ለመስጠት ወሰኑ::

## እንደገና የሆነ ቀን በቡነስ አይረስ

ለረጅም ጊዜ ቤት ተከራይተው ሲከታተሉት የነበረው ሰው አስልችቷቸው ወደ ሀገራቸው ለመመለስ በዝግጅት ላይ የነበሩት ሰላዮች ሰውየውን ትተው እቃቸውን እየሸከፉ ነው::እዚህ ቤት እስካሉና እስኪለቁ ድረስ በመስኮት ወደ ውጭ ማየታቸውን አልተውም:: ከመጡበት ቀን ጀምሮ ሁሉም ነገር ተመሳሳይና አንድ አይነት በመሆኑ መመልከትም አልፈለጉም:: ነገር ግን የክፍሉ አቀማመጥ በግዴታ ወደ ውጭ በመስኮት እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል፡ ፡እቃቸውን እየሸከፉ ሳለ አንድ ሰው ድንገት ውልብ ሲል አዩት:: የሚከታተሉት ሰው ነው ::ዛሬ በተለየ መልኩ ያልተለመደ ነገር እየታየበት ነው::ሌላ ጊዜ ከሰርቪስ ወርዶ ወደሚያዘወትረው ምግብ ቤት ገብቶ እራቱን በልቶ ወደ ቤቱ ያመራል:: የዘወትር ተግባሩ ይሄ ነበር ::ዛሬም እንደዚህ እንደሚያደርግ ገምተው ነው ለመመልከት ያልፈለጉት:: ነገር ግን ሰውየው ከሰርቪስ ወርዶ ወደ ወደ ምግብ ቤት አልሄደም:: ወደ አበባ መሸጫ ሱቅ አመራ ::አበባ ገዝቶ ወደ ቤቱ ሄደ::ያንን ቀን አገላብጠው ሲመለከቱ የሚፈልጉት ሰው ሆኖ አገኙ:: ልክ ቀኑን እንዳወቁ ‹‹ቢንጎ!!›› አሉ::ዛሬ የልደት ቀኑ መሆኑን አወቁ፡ ፡ ሰውየው ተገኘ::ይህ ሰው የናዚ አዛዥ ከነበሩት ሰዎች አንዱ ሲሆን ስሙም አዶልፍ ኤክማን ነው::አዶልፍ ኤክማን ለ15 አመታት ተሰውሮ ከነበረበት በብዙ ፍለጋ ተገኘ::ለጠላፊዎቹ መገኘቱ ቢያስደስታቸውም እንዴት አድርገው አፍነው ከአርጀንቲና ይዘው መውጣት እንዳለባቸው ትልቅ ፈተና ሆነባቸው::ኤክማንን እዚህ መግደል የለባቸውም::ወደ እስራኤል ወስደው ለፍርድ እንዲቀርብ ማድረግ አለባቸው ከሀገራቸው ሲነሱ እሱንቱ ከተረጋገጠ የተሰጣቸው ትእዛዝ በህይወት ማምጣት እንዳለባቸው ነው::





ሰውየው ከተገኘ በኋላ ለረጅም ሰዓት ጠለቅ ያለ ስብሰባ አደረጉ::ኤክማንን እነማን ያፍኑት፤ካፈንን በኋላ የት እንደብቀው፤ እንዴትስ ወደ እስራኤል እንውሰደው በሚለው ጉዳይ መከሩበት :: ከኋላ ያሉት ሁለቱ ጉዳዮች ሲሳኩ የሚችሉት አፈናው የተሳካ ሲሆን ብቻ ነው::ስለዚህ የማፈኑን ነገር ኮሽታ ሳይሰማ መጠናቀቅ አለበት:: ለአፈና የሚያስፈልጉ ሰዎች ተዘጋጁ:: ጥናት ተደረገ:: ሰውየው የሚንቀሳቀስባቸውን ቦታዎችን ለብቻው የሚሆነው በየትኛው ሰዓት እንደሆነ አጠኑ::የአፈናውን ቀን ወሰኑ፡

አፈናው በጥንቃቄ መሆን አለበት::ትንሽ ነገር ከታየ ሰውየው ተሰውሮ እስከመጨረሻ ሊጠፋባቸው ይችላል::15 አመት ሙሉ በመላው አለም ተበትነው ቢፈልጉት አላገኙትም ነበር:: ኤክማን በተለያየ ቦታ ራሱን ደብቆ ሲንቀሳቀስ አፍሪካ ደርሶ ማንነቱን የሚቀይር አድራሻ ይዞ ወደ አውሮፓ ተመልሶ በዚያ አቋርጦ ብራዚል አንድ አመት ቆይቶ ማረፊያውን አርጀንቲና ወስጥ አደረገ::ሚስቱ ቀድማ ወደእዚያ እንድትሄድ አስደርጓል:: መሞቱን ለቤተሰቦቹና ለጓደኞቹ እንዲደርስ አድርጓል::በተለያየ ጋዜጣ ላይ በእስራኤል አፋኞች እንደተገደለ አስነግሯል::የሚከተሉት ሰዎች ካሉ እንኳን አድራሻውን እንዳያገኙ ዱካውን እያጠፋ ለብዙ ጊዜ ተደብቋል:: እስራኤሎች ሌሎቹን የናዚ ባለስልጣንና አባል የመከታተል ዝንባሌ የላቸውም:: እነዚህን በትርፍ ግዜና ባገኙት አጋጣሚ ነበር የሚፈልጉትና የሚከታተሉት:: እነርሱ ዋናው ጉዳያቸው እሳራቸውን ያሳያቸውን በመላው አውሮፓ ከተደበቁት እየፈለገ ሲገላቸውና ሲያስቃያቸው የነበረውን አዶልፍ ኤክማንን ነው የሚፈልጉት::እርሱ የእነሱን ጉዳይ የሚከታተል ቡድን እንዳቋቋመ ሁሉ እነርሱም የእርሱን ጉዳይ የሚከታተል አንድ ተቋም ነበራቸው ::

ስለእርሱ የሚሆን መረጃ ከጥቃቅኑ ጀምሮ የሚሰበስብና የሚተነትን፤ትንትኖም ለክትትል የሚሆን መረጃ የሚያቀርብ ቡድን አላቸው:: በመደርደሪያዎቹ ላይ ተጠርዘው የሚገኙ ወረቀቶች ከመላው አለም የተሰባሰቡና ክትትልና ፍለጋ ተደርጎባቸው የከሸፉ ናቸው::ከየቦታው ኤክማን እዚህ ታይቷል በሚል ፍለጋ የተደረገባቸው ናቸው::ለ15 አመትታት ያህል ጥቆማዎችን እየተቀበሉ

በየሀገሩ እየሄዱ ሲፈልጉና ሲያስሱ እሱን ቀርቶ እርሱን የሚመስል ሰው አላገኙም። ሳያገኙት ወይም መሞቱን ሳያረጋግጡ በጥቅሉ ቁርጡን ሳያውቁ ፕሮጀክታቸውን መዝጋት አልፈለጉም ግን ተስላችተዋል። አሁን የሚከታተሉት ሰው ኤድዋርድ ክሌመንት ነው የሚባለው። ኤክማን መሆኑን በልደቱ ቀን አበባ ሲገዛ አወቁት እንጂ እሱነቱን የሚያሳይ ሙሉ መረጃ አላገኙም። ግን እሱ ነው ብለው ስላመኑ ማፈን አለባቸው።

አሁን እንዴት እናፍነው የሚለውን ነገር በስፋት ያዙት። ቀንም ቆረጡ ። ግን ለማፈን የሚሆን የተመቻቸ ሁኔታ አላገኙም ። እርሱ ከአውቶብስ ወርዶ ወደ ምግብ ቤትና ወደ ቤቱ በሚሄድበት ሰዓት የጸሀይ ብርሀን ስላለ ሰዎች ከርቀትም ቢሆን ስለሚመለከቱ ሊከሽፍ ይችላል ። አንድ ሰው እንደጓደኛው በመሆን ቀርቦ ጨለም እስኪል እንዲያቆየው ለማድረግ ሞከሩ። ይሄም አልተሳካም። ቀኑ ደግሞ እየረፈዳባቸው ነው። አፈናው ቶሎ እንዲካሄድ አለቆቻቸው እየጨቀጨቋቸው ስለሆነ ግራ ተጋብተዋል። ተፈላጊው ሰውየው በሌሊት ነው የሚነሳው ። ለዶሮዎቹ ቀለብ ይሰጥና አትክልቱን ይኮተኩታል። ከዚያም 12 ሰዓት ሲሆን ከአቋራጩ ይወጣና ወደ ዋናው መንገድ ያቀናል። በአውቶብስ ይሳፈርና ወደ ፋብሪካ ያመራል ። እርሱ የሚሰራው በማርቸዲስ ፋብሪካ ነው። ከስራው ውጭ ከሰዎች ጋር አይቀራረብም ። እንኳን እዚያ ይቅርና ከጎረቤቶቹ ጋር አያወራም፡ ፡ሀገሬው የሚጠቀምበትን የስፓኒሽ ቋንቋ ቅላጼ ወደ ጀርመንኛ ስለሚሄድበት ከአጭር ሰላምታ ውጭ ከሰዎች ጋር ለመነጋገር አይዳፈርም። በጥቅሉ ከሁሉም የሸሸና የራቀ ነው። ከስራ ሲመለስ በአውቶብስ ወስጥ በስፓኒሽ ቋንቋ የተጻፈ መጽሀፍ ስለሚይዝ ከማንም ጋር አያወራም፡፣ 12 ሰዓት አውቶብሷ ሰፈሩ ታደርሰዋለች። 10 ደቂቃ በምግብ ቤት ያሳልፍና እስከ ተኩል ወደ ቤቱ ይገባል። ዛሬ ግንቦት 11 ቀን ነው። በፋብሪካው የተለየ ነገር ነበር።

ከስራ በኋላ ስብሰባ ስላደረጉ ክሌመንት አርፍዶ ነበር ወደ ሰፈሩ የመጣው። ይሄ ደግሞ ለአፋኞቹ አመቺ ሆነላቸው። እነርሱ ደግሞ አውቶብሱ ስላልመጣ ብዙ ስለቆየባቸው በሌላ አቅጣጫ ሄዷል በሚል ሊበታተኑ ነበር። ግበንቦት 11 ቀን ተሳፍሮ ከመጣበት





አውቶብስ ወረደና ጎዳናውን ማቋረጥ ጀመረ። የመሸ ቢሆንም ያን ያህል የጨለመ አይደለም ። ሰው መለየት ይቻላል። እዚያ ጋር ከአውቶብስ የሚወርደው አንድ ሰው ብቻ መሆኑ ለአፋኞቹ የጠቀማቸው ይመስላል። ክሌመንት ከአውቶቡስ ወርዶ ሲሄድ እርሱ መሆኑን ማረጋገጥ ነበረባቸው። በእርግጥም ክሌመንት ነው። ልክ ከአውቶብስ ወርዶ ወደሚፈልግበት ለመሄድ ሲንቀሳቀስ አንድ ሸንጠ ረጅም ጥቁር የቤት መኪና አጠገቡ መጥታ ቆመች። እርሱ ያሰበው ከውስጡ ሰው እንደሚወርድና መኪናው ተነስቶ ሲሄድ መንገዱን ለማቋረጥ ነው። በእርግጥ ሰው ወረደ ነገር ግን በሩ አልተዘጋም። የወረደውም ሰው ወደ እርሱ መጣ። መንገድ ወይም ሰው ሊጠይቀው እንደሆነ ነበር የገመተው ። ነገር ግን ይሄ ሁሉ አልሆነም ። ወዲያውኑ ሌሎች ሰዎች ተጨምረው አፍን አደረጉና ወደ ውስጥ አስገቡት። ከኋላ ወንበር መሀል አስቀመጡት። ስለደነገጠ ራሱን መከላከል እንኳን አልቻለም። ግራና ቀኝ የተቀመጡ ሰዎች ተጠግተውት እንዳይነቃነቅ አድርገውታል።

መኪናው ወዲያውኑ ተነስቶ ከከተማው ወጥቶ ወደ ገጠራማው ቀበሌ መብረር ጀመረ። ሹፌሩ ሰሞኑን ሲለማመድ ስለነበረ አቅጣጫና ቦታ ሳይሳሳት መንዳት ጀመረ። አያፈጥንም ደግሞም ዝቅ አያደርግም። ይሄ ከሆነ በትራፊክ ጥርጣሬ ውስጥ ሊገባ ይችላል። ሁለትና ሶስት መስቀለኛ መንገድ አለፈ ። አንድ ቦታ የትራፊክ መብራት ያዛቸው። ረጅም ሰልፍ በመሆኑ ሁለት ግዜ ያህል ያቆማቸዋል። ከመንገዱ 10 ሜትር ርቀት ላይ ፖሊስ ቆሟል። አፋኞቹና ኤክማን ተያዩ። በመጮህ ርዳታ ሊጠይቅ እንደፈለገ አውቀዋል። ወዲያውኑ ሽጉጥ አውጥተው በጎን በኩል ሸንጡ ላይ ደገኑበት። ሽሚዙን ገልጠው አፈሙዙን ሆዱ ላይ አደረጉት። ቀዘቀዘው። ትንሽ ከጮኸ እንደሚተኩሱ ስለነገሩት ከፖሊሱ ጋር በቅርብ እየተያዩ እርዳታ መጥራት አቃተው። ማን እንደሆኑ፣ ለምን እንዳፈኑትና ወደየት እንደሚወስዱት ቢጠይቃቸውም ምንም መልስ አላገኘም። እነርሱም አያወሩም። ወደተዘጋጀው ቤት እንደወሰዱት በአስቸኳይ ልብሱን እንዲያወልቅ አደረጉት። ይሄ ሁሉ ሲሆን የተሳሳተ ሰው እንዳፈኑ እየነገራቸው ነው። እነርሱ ግን ቶሎ ብሎ

ልብሱን እንዲያወልቅ እየነገሩት ነው።ኮቱን አወለቀ። ቀጥሎ ከረባቱን፣ እንደገና ሸሚዙን አስወለቁት። ሱሪውን ለማውለቅ ቀበቶውን መፍታት ሲጀምር እርሱን እንዲተው ነገሩት።ቀበቶውን መልሶ እንዲያጠብቅና ይልቅስ ካናቴራውን እንዲያወልቅ ነገሩት። እንደታዘዘ አደረገው።ይሄን ካደረገ በኋላ እጁን ወደ ላይ እንዲሰቅል ነገሩት። አደረገው። ወደ ላይ በተዘረጋው እጁ ብብቱን ተመለከቱት። ወዲያውኑ ሶስቱም ሰዎች ተያዩና ተደሰቱ ።ተደስተው ተቃቀፉ። የሚፈልጉት ሰው እርሱ መሆኑን አረጋገጡ ።

በናዚ ስርአት መሰረት እያንዳንዱ የኤስ.ኤስ አዛዥ በብብቱ ስር የደም አይነቱ እንዲነቀስ ይገደዳል።በአደጋ ግዜ ችግር ቢፈጠር ለእርሱ የሚሆን ደም ቶሎ እንዲያገኝና እንዲደርሰው ለማስቻል ነው። የታፈነው ሰው ይሄንን ንቅሳት ከጦርነቱ በኋላ ለማጥፋት ብዙ መሞከሩን በጠባሳው ያስታውቃል ።ብዙ ተጫጭሯል፤ ተፋፍቋል ግን ምልክቱ ጨርሶ ስላልጠፋ ቁጥሩ ይታያል።

አንድ ሰው ኮፍያ ይዞ መጣ።ይሄ ኮፍያ የናዚ አባል አርማ ያለበት ባለጌጥ መለዮ ነው።ኮፍያውን አናቱ ላይ አድርገው ፎቶ አነሱት።እናም አሁን የተነሳውን ከበፊቱ ፎቶው ጋር አስተያዩት ። የእድሜ ልዩነት እንጂ በጣም የተቀራረበ ነው።እንደገናም ወረቀት አምጥተው ስሙን እንዲጽፍ አደረጉት።ሪካርዶ ክሌመንት ብሎ አድራሻውን ጭምር ጻፈ።እርሱ የጠበቀው በእዚህ አድራሻ ለቤተሰቡ እንዲደውሉለት ነው።ምናልባት ገንዘብ ጠያቂ አፋኞች ከሆኑ ለመደራ[illegible]ደር እንዲያስችለው ነው።ወዲያውኑ አዛዥ በነበረ ግዜ በእጅ ጽሁፉ ትእዛዝ የሰጠበት ደብዳቤ ጋር ጽሁፎቹን አመሳሰሉት ትክክል ናቸው።።ብዙ ነገር መከሩና አብልጫው ተመሳሳይ በመሆኑ እርሱነቱን በደምብ ለዩት።እስካሁን ምንም ነገር አላዋሩትም። በመጨረሻ አንድ ሰው እንዲህ አለው።ስምህ ክሌመንት ነው አይደል? አለው። ክሌመንትም ‹‹አዎ ስሜ ሪካርዶ ክሌመንት ነው አድራሻዬ.....›ብሎ ሳይጨርስ አቋረጠውና ‹‹አንተ ካርል አዶልፍ ኢክማን ነህ አይደል?›› ብሎ ጠየቀው ።ለጥቂት ግዜ በዝምታ ተዋጠና ሁሌም ሲሰጋ የነበረው ነገር እንደደረሰ አውቆ ማንነቱን





ለይክድ ሁሉንም ነገር ዘርዝሮ ነገራቸው።ይህን ሰው ወደ እስራኤል መውሰድ አለባቸው።አፋኞቹ እንዴት አድርገው ከሀገር እንደሚያወጡት ዘዴ ቀየሱ።የአርጀንቲናና ብራዚል መንግስት ለናዚ ሰዎች ትልቅ እገዛና ጥበቃ እንደሚያደርግ ስለሚያውቁ ማፍጠን አለባቸው።እነዚህ የናዚ ሰዎች ብዙ ገንዘብ ከአውሮፓ ዘርፈው ወደ ላቲን ስለገቡ ገንዘቡ እነዚህን ሀገሮች በደምብ እየጠቀመ ነው። ናዚዎቹን የሚንከባቸውና እነርሱ ላይ የሚያተኩር ማንኛውም ወገን ጠላታቸው ነው።በዚህ የተነሳ ለጠላፊዎቹ ይሄን ሰው አፍኖ መውሰድ አስቸጋሪ ሆነባቸው።ጉዳዩን ወደ እስራኤል ሰደዱ።ከቴላቪቭ አንድ መልእክት ደረሳቸው።ይሄ ሁሉ ነገር ከአፈናው በፊት የተቀነባበረ ነው።

ግንቦት 17 ቀን በእስራኤል ጋዜጦች ከነገ ወዲያ ስለሚጀመረው አዲስ በረራ እየተዘገበ ነው።አዲሱ በረራ ከእስራኤል ወደ አርጀንቲና የሚያመራ ነው።። 27 ሰዓት የሚፈጀው በረራ ለምን ባሁን ሰዓት እንደተመረጠ ለብዙ ሰው ግራ አጋብቷል። የኤል ኤል አየር መንገድ ብዙ አውሮፕላኖች የሉትም። በአውሮፓ ያለውን በረራ እንኳን በአግባቡ ሳይሸፍን እየተጣበበት እንዴት ወደ ላቲን አሜሪካ ረጅም በረራ እንደመረጠ ግራ አጋብቷል። በዚያ ላይ የተሟላ መንገደኛ ወደዚያ የሚሄድ አያገኙም። ይሄ መስመር ከፍተኛ ኪሳራ እንደሚያመጣ እየተተነበየ ነው።የአርጀንቲና መንግስት በረራው በመጀመሩ ደስተኛ ሆነዋል። ብዙ ታላላቅ አየርመንገዶች ተጠይቀው መልሳቸው እምቢታ በሆነበት ግዜ በራስ ተነሳሽነት ኤል ኤል ያውም በፍጥነት መስመሩን ለመጀመር በመስማማቱ አስደስቷቸዋል።በቡነስ አይረስ ትልቅ አቀባበል ይጠብቃቸዋል። በእስራኤል የአርጀንቲና አምባሳደር እንግዳ በሆኑበት ዝግጅት ተደርጎ አምባሳደሩን ብቻ ጨምሮ የተመረጡ ባለስልጣናት ብቻ ተሳፈሩ ።በረራው በመክፈቱ ለመስተናገድ የመጡ ተሳፋሪዎች የዛሬው በረራ ለእንግዶች ብቻ የተዘጋጀ በመሆኑ በቀጣይ ቀን እንደሚሳፈሩ ተነገራቸው።አውሮፕላኑ በፍጥነት በርሮ ቡነስ አይረስ ደረሰ። የአቀባበል ስነስርአት ተደርጎ ግብዣው ከተካሄደ በኋላ ለአብራሪዎቹ ሞተሩን ሳያጠፉ ጥገና እያደረጉ እንዲጠብቁና ፈጣን የመልስ በረራ እንደሚኖር ተነገራቸው።

ወዲያውኑ ሁለት መኪኖች መጥተው ሰዎች ወረዱ። የሆነ ሰው ከመሀል ሆኖ እየተንገዳገደ ግራና ቀኝ ያሉት ሰዎች እየደጋገፉት ወደ አውሮፕላን አመጡት።ሰውየው የእስራኤል ነጋዴ እንደሆነና በግብግቡ ብዙ መጠጥ ወስዶ የሰከረ እንደሆነ ስለታመነበት በአካባቢው የነበሩት አርጀንቲናውያን ጠባቂዎች እነዚህ ነጋዴዎች ሲባሉ መጥነው መጠጣት አይሆንላቸውም በሚል እየተገረሙ ሰውየው እንደታዘለ ወደ አውሮፕላን ወስጥ ሲገባ ተመለከቱት። ሰውየው ሰክሮ ሳይሆን እራስን የሚያስት መርፌ ወግተውት እግሩ መሬቱም መርገጥና መናገር እንዳይችል ነው ያደረጉት ።ሰውየው ወደ ውስጥ እንደገባ አውሮፕላኑ ሌሎችን ሳይጠብቅ በፍጥነት ተነስቶ በረረ። አንድ ግዜ ብቻ ሴኔጋል ነዳጅ ለመቅዳት ከማረፉ በስተቀር የትም ቦታ አላረፈም።

## ኤክማን በአየር ላይ

ወደ ሀገሩ የአየር ክልል የገባው አውሮፕላን መንገደኞቹ ደስታቸው አጥፍ ድርብ የለውም።አውሮፕላኑ የትኛው ከተማ ማረፍ እንዳለበት በመወሰኑ በቴላቪቭ አየር ላይ ከፍ ብሎ ማንዣበብ ጀመረ፡ ፡እዚህ ቦታ ለማረፍ እንደማይቻል መረጃ ቢኖራቸውም በድፍረት ነበር እዚህ ሰማይ ላይ የተገኙት። በአየር ትራፊክ መቆጣጣርያ ክፍል የሚገኘው ሰው በሰማይ ላይ የሚገኘውን አሞራ ተመለከተው።አሞራ ነው ብሎ የወሰነው አውሮፕላን ወደዚህ አየር ማረፍያ እንደማይመጣ እርግጠኛ ስለሆነ ነው።በአሁን ሰአት የእስራኤልን አየር ክልል አልፎ የገባ ማንኛውም አውሮፕላን ቴላቪቭ ውስጥ ማረፍ እንደማይችል መረጃ ስለሚኖረው ነው። ለዚህም ነው መሬት ላይ ነበረው ሰውዬ በአየር ላይ የነበረውን አውሮፕላን አሞራ ነው ብሎ ገመተው። እንዳሰበው ግን አሞራ አልነበረም።

አሞራ መሳዩ ነገር ከነበረበት ራቅ ካለ የአየር ከፍታ ዝቅ እያለ ሲመጣ እውነትም አውሮፕላን ነው።አየር መቆጣጠርያ ክፍል የነበረው ሰውዬ እዚህ ለማረፍ እንደማይችል እያወቀ እንዴት መጣ? እያለ በማሰብ ‹‹ሊሆን አይችልም ››ብሎ መነጋገሪያውን ቶሎ ብሎ ማነጋገር ጀመረ።ይሄ አውሮፕላን ችግር ገጥሞት እንደሆነ ገምቷል።





ችግር ቢገጥመው እንኳን እዚህ መምጣት የለበትም። አየር ትራፊክ መስመር ላይ የነበረው ሰው መነጋጋሪያውን እንደገና እያናገረ ነው ። ከአውሮፕላኑ አብራሪ ጋር በሬድዮ ግንኙነት ፈጥሮ ‹‹አየር ላይ ያለኸው ሰው ትሰማኛለህ?››አለው

‹‹እኔን ነው?››

‹‹አዎ አንተን ነው››

‹‹እየሰማሁ ነው››

‹‹ምን እያደረግክ ነው?››

‹‹ላርፍ ነው››

‹‹እዚህ ማረፍ አትችልም››

‹‹ለምን?››

‹‹አትችልም አልኩህ››

‹‹እባክህ ፍቀድልኝ››

‹‹ችግር ገጥሞህ ነው?››

‹‹‹ችግር እንኳን አልገጠመኝም››

‹‹ለማንኛውም ወደ ቀጣዩ ከተማ ሂድ››

‹‹ለምን?››

‹‹እዚህ ዛሬ አይቻልም››

‹‹እባክህ ፍቀድልን ልረፍ››

‹‹አይቻልም አልኩህ፤ እምቢ ካልክ ትመታለህ››

‹‹ሌላ ቦታ ሂድ እያልከኝ ነው››

‹‹አዎ ቅርብ ከተማ አለ ››

‹‹እኔማ የፈለግሁት እዚህ ማረፍ ነበር››

‹‹ ወዳንተ ያነጣጠረው መሳርያ ሊተኮስብህ ስለሆነ ብትሄድ ይሻላል ››

‹‹እዚህ ደረጃ ላይ እንኳን ባንደርስ ጥሩ ነው››

‹‹አሁን ከዚህ መስመር ውጣና ሌላ ቦታ ሂድ ብየሃለሁ፤አንድ ደቂቃ ካለፈ ወዮልህ...››

‹‹የያዝኩትን እቃ ብታይ ኖሮ እንዲህ አትለኝም ነበር››

‹‹የፈለግከውን ነገር ብትይዝ አያገባኝም››

‹‹አሁንም ልድገመው?››

‹‹ምን››
‹‹እቃውን ብታዩው እንዲህ አትልም ነበር››
‹‹የአለም መሪዎችን ብታሳፍር እንኳን እዚህ ማረፍ አትችልም››
‹‹ምንም ብይዝ አይደንቅህም ማለት ነው?››
‹‹ነገርኩህ እኮ ይልቅ አንድ ደቂቃህ እያለፈ ነው፤ውርድ ከራሴ በል››
‹‹እና ምንም አይደንቅህም››
‹‹አይደንቀኝም አልኩህ፤የሞቱት እናትና አባቴን ይዣለሁ ብትለኝ እንኳን እዚህ አላሳርፍክህም፤ ይልቅስ...››
‹‹እሽ ማረፍ ከከለከልከኝ እንዳልከው ሌላ ከተማ ሄዳለሁ››
‹‹እንደዛ ይሻላል፤ፍጠን››
‹‹በቃ ወደዛ ልሄድ ነው››
‹‹ሂድ በቃ››
‹‹ምን እንደያዝኩ እንኳን አልጠየቅከኝም እኮ››
‹‹ምንም ብትይዝ አያገባኝም ማወቅም አለፈልግም አልኩህ››
‹‹እኔ አንተን ብሆን ኖሮ እቃው ምን እንደሆን እጠይቅ ነበር››
‹‹ምን ብትይዝ ነው እንደዚህ....››
‹‹አዶልፍ ኤክማንን ይዤ ነው ለማረፍ የከለከልከኝ››
‹‹ማን አልክ!!!!››
‹‹ኤክማን!!››
‹‹ቆይ!!ቆይ!!!ቆይይይይይይይይይይይይይይይ!!!!!!››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ና!!!ና!!!!!! ቶሎ ውረድና እረፍ ሌላ ከተማ እንዳትሄድ ብዬሃለሁ...››

አየር ትራፊክ መቆጣጠርያ የነበረው ሰው ይሄንን ስም እንደሰማ መነጋገሪውን በአግባቡ ቦታው ላይ ሳያስቀምጥ ጥሎት እየበረረ ወደማረፍያ ሜዳው በሩጫ ገሰገሰ፡፡አውሮፕላኑን የያዙት ሰዎች እዚህ ቦታ ለማረፍ እንደማይከለከሉ አውቀው ወደሌላ ቦታ ፊታቸውን እንኳን ማዞር አላሰቡም፡፡በአሁን ሰአት ጥብቅ ቁጥጥር እዚህ ስለሚደረግ ነው የመጡት፡፡ ሰውየው እየሮጠ ነው፡፡እየሮጠ ብቻ





ሳይሆን እየገሰገሰ ነው፡፡ደግሞም መገስገስ ብቻ ሳይሆን አንገቱን ሰብሮ ወደ ሰማይ እየተመለከተ ነው፡፡አንድ ግዜ አደናቅፎት ወድቆ እንደምንም ተነስቶ ነው የሮጠው ፡፡ጉልበቱ እንደተጎዳ አውቋል ፡፡ግን ምንም አይደለም፡፡ አሁን የሰማው ስም ለእርሱ መድሃኒቱ ነው፡፡ እዚህ ግቢ ካሉት ሰዎች አውሮፕላኑ ውስጥ ያለውን ሰው የሚያውቀው እሱ ብቻ ነው፡፡ ወሬውን ለማንም መንገር የለበትም፡፡ ማንም ሰው ሊቀድመውም አይገባም፡፡ ተጋሪም አይፈልግም፡፡ አውሮፕላኑ እንዳረፈ ቀድሞ ወደ ውስጥ የገባው እርሱ ነበር፡፡ወደ ውስጥ እንደገባ ኤክማንን አነቀው፡፡ማነቅ ብቻ ሳይሆን እጁን ነከሰው፡፡ ይሄ ሰውየ ከአስር ቤተሰቡ አባላት ውስጥ የተረፈው እርሱ ብቻ ነበር፡ ኤክማን ያዘበት በነበረበት ቦታ ነው እናቱና ሁለት እህቶቹ የተገደሉት፡፡ እርሱም ቢሆን በየቱቦውና ጉራንጉር ውስጥ እየተደበቀ ነበር ያመለጠው፡፡አምስቱን አመት በሰቆቃ ነበር ያሳለፈው፡፡እዚህ ሀገር ያሉ እስራኤላውያን ከሞት የተረፉ በኤክማን ስቃያቸውን ያዩ በመሆናቸው እያንዳንዱ ሰው እየነከሰ ትንንሽ ስጋ እንደሚፈልግ የታወቀው ከዚህ ሰው ነበር፡፡

ወዲውኑ ፓርላማ ስብሰባ እየተደረገ ስለነበረው መረጃው ተላለፈ፡፡ወሬው በሬድዮ ተነገረ ፡፡በቡነስ አይረስ ደግሞ ሚስቱ ግራ ተጋብታለች፡፡ ባሏ ሪካርዶ ክሌመንት በመጥፋቱ ለፖሊስ አመልክታ ፍለጋ ላይ ናቸው፡፡አንድ ሰው ከሁለት ቀን በኋላ ባሏ በጥቁር መኪና ተሳፍሮ ወደ ሰሜን እንደሄደ ስለነገራት ወደ ተባለበት ስፍራ ፖሊስ እያሰሰ ነው፡፡ ሚስቱና አሳሾቹ በኋላ የተደበቀበትን ቤት አገኙት፡፡ ነገር ግን ረፍዶ ነበር፡፡ እነርሱ የደረሱት ግንቦት 20 ነበር፡፡ግንቦት 20 ደግሞ ክሌመንት አውሮፕላን ውስጥ ገብቶ በረራ ላይ ነው፡፡

በመጨረሻም የአርጀንቲና መንግስት እስራኤሎች ጠልፈው እንደወሰዱ ደረሰበት፡፡ ይሄ የአንድን ሀገር ሉአላዊነት የደፈረ በመሆኑ መንግስትና ህዝቡን እጅግ አስቆጣ፡፡ወደያውኑ አምባሳደሩ ተጠርቶ የወሰዱት አዶልፍ ኤክማን ሳይሆን ሪካርዶ ክሌመንት የተባለ ሰው መሆኑን ይሄንም በአስቸኳይ እንዲመልሱ አሳወቁ፡፡ምንም ምላሽ አልተገኘም፤አንድም እስራኤላዊ በአርጀንቲና እንዳይኖር ተጠራርገው እንዲወጡ ታዘዙ፡፡ ድርጅቶቻቸው ሁሉ ተዘጉ፡፡ በየትም መንገድ

እስራኤል የሚባለውን ሀገር በገባበት ገብተው የሚችሉትን ነገር እንደሚያደርጉ እንዲሁም በሁሉም ቦታ እስራኤልን እንደሚያሳጡና እንደሚቃወሙ አሳወቁ።በሀገራቸው የሚገኙ የእስራኤል ዜጎች ቶሎ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ አደረጉ፤አርጀንቲና ለ●ተባበሩት መንግስታት አመለከተች። እስራኤል ክሌመንት የተባለውን ዜጋየን ኢክማን ነው ብላ ወስዳብኛለችና ካልመለሰች ወደጦርነት የሚያስገባ እርምጃ እንወስዳለን ሲሉ አሳወቁ።ይሄ ዛቻ ከተሰማ ከጥቂት ግዜ በኋላ በኖርዌይ የእስራኤል ኤምባሲ ውስጥ ቦምብ ፈነዳ።። በሀንጋሪ አውሮፕላን እንደቆመ ተቃጠለ። ይሄ ሁሉ የአርጀንቲና እርምጃ ነው ተብሎ ተነገረ።ሁሉ ነገር ፍጥጫ ሆነ።ሁለቱ ሀገሮች አይጥና ድመት ሆነው እንደተነካከሱ ዘለቁ።የኢክማን መዘዝ የሚጀምረው እንግዲህ እዚህ ላይ ነው።የአርጀንቲና ወታደራዊ መንግስት የ1978ቱን የአለም ዋንጫ ለማስቀረትና የህዝቡን ደስታ ከፍ ለማድረግ የተዘጋጀበት ግዜ ነበር።

የፍጻሜውን ጨዋታ የሚመራው አልቢትር ታወቀ። እስራኤላዊ አብርሃም ኬለን ነው። ፊፋ በዛ ውድድር ጥሩ ብቃት ያለው አልቢትር እርሱ እንደሆነ ስላመነ መደበው። ደግሞ በወቅቱ ምርጡ ዳኛ ተብሎ በብዙዎቹ የተደነቀው እርሱ ነው። ኬለን በሌላ ወድድር ባሳየው ብቃት በአለም ጋዜጦች ሳይቀር የተወደሰ ነበር። ሆኖም የፍጻሜውን ጨዋታ ለመምራት በተመደቡት አልቢትር ላይ የተጻፈው ዘገባ አርጀንቲና ውስጥ ትልቅ ትርምስ ፈጠረ ።ፊፋንም ስጋት ውስጥ ጣለው።አርጀንቲና በውድድሩ አንድ ጨዋታ ብቻ ነው የተሸነፈችው።በምድብ ጨዋታ ጣሊያን ረታቻት።ይሄን ጨዋታ የመራው ኬለን ነው።አሁን ለፍጻሜ ሲመደብ የአርጀንቲና መንግስት በግልጽ ለፊፋ ደብዳቤ ጻፈ‹‹ከእስራኤል ጋር ባለን ጥሩ ያልሆነ ግንኙነት ይሄ አልቢትር ሊጎዳን ይችላል።ጨዋታውን በጥሩ ሁኔታ መርቶ ብንሸነፍ እንኳን ግጥሚያው ሳያልቅ በረብሻ ሊቋረጥ ይችላል። ስለዚህ እስራኤላዊ አልቢትር ተነስቶ የማንኛውም ሀገር ዜጋ ይመደብልን›› አሉ።ፊፋም አብርሀምን ከፋይናል ዳኝነቱ አነሳው። የእስራኤል ፌዴሬሽን ተቃወመ።ፊፋ ግን ውድድሩ ከሚበላሽ እናንተ ብትቃወሙ ይሻላል አለ።አንድ የፖርቱጋል ጋዜጠኛ እንዲህ አለ።





‹‹ጀርመን በ1966ቱ አለም ዋንጫ የተሸነፈችው ባክራሞቭ በጦርነቱ ጀርመኖች ቤተሰቡን ስለገደሉበት ተበቀላቸው።አሁንም አብርሀም አርጀንቲና በእስራኤል ዜጎች ላይ እየፈጸመባቸው ስላለው ጥቃት ሊበቀል ይችላል ››አለ።የፊፋን አሰራርና አልቢትሩን በአርጀንቲና መንግስት ጥያቄ በመቀየሩ ተቹት፤ነቀፉት፤ብዙ ቦታ ነከሱት፤ በጫጩቁት ...ብቻ ያላሉት ነገር የለም።

ያም ሆነ ይህ ፊፋ እስራኤላዊ አልቢትር በኢክማን ጦስ ተሰናብቶ ኢጣሊያዊ አልቢትር ቦታውን ተካ። እናም አርጀንቲና ዋንጫውን ወሰደች።የፊፋው ፕሬዝዳንት የጻፍኩት ደብዳቤ ልክ ነው አሉ።አርጀንቲናና እስራኤል በነበረባቸው ቁርሾ የእስራኤሉ አልቢትር ቢያጫውትና ሆላንድ ብታሸንፍ ኖሮ ከፍተኛ ረብሻ ተነስቶ የአጫዋቹም ህወይት ሊያልፍ እንደሚችል ብዙዎቹ ይገምቱ ነበር።

የሶማልያን ጥያቄ የደገፉ የምእራባውያን ሚዲያ የሱማልያና የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ በተጧጧፈ ጦርነት የታጀበና ከአርጀንቲናና ከእስራኤል የባሰ ሁኔታ ውስጥ ስላሉ አልቢትሩ ሞቃዲሾ ገብቶ ማጫወት የለበትም ባይ ነበሩ።ፊፋ አሰበ፤አሰላሰለ፤ መረመረ፤አመዛዘነ ዙርያ ጥምጥሙን አየ።የእስራኤል አልቢትር በአርጀንቲና ጥያቄ መቀየሩ ፖለቲካ ውስጥ ገብቷል በሚል ትልቅ ማብጠልጠል ደረሰበት።በተመሳሳይ በሁለት ሀገሮች ላይ በ1960ዎቹ አጋማሽ በፖለቲካ እጁ እየረዘመ ክርክር አስነስቶበታል። የሞቃዲሾውም ጨዋታ ይሄ አደጋ ተጋርጦበታል።እነዚህን ነገሮች መዝኖ መዛዝኖ ሚዛኑ ላይ አስቀምጦ የማይቀለበስ አንድ ውሳኔ አሳለፈ።

## እንደገና በሌላ ቀን

የፋብሪካው የእግር ኳስ ቡድን በቅርብ ለሚጠብቀው የዋንጫ ውድድር እየተዘጋጀ ነው። የድሬዳዋ ጨርቃ ጨርቅ ቡድን በ1952-54-55-57 የኢትዮጵያ ሻምፒዮና በመሆኑ የሀገሪቱን እግር ኳስ መቆጣጠር የቻለ ነው። ከዚያ በኋላ ወደዚያ ስፍራ መጥቶ አያውቅም፡ ፡ የዘንድሮ ቡድኑ ጠንካራና የበፊቱን ዝና ለመመለስ የተዘጋጀ ነው። ወጣትና ነባር ተጫዋቾችን አቀላቅሎ የያዘ በመሆኑ ብዙዎቹ ተስፋ

ጥለውበታል፡፡እነ ቡኔና ሌሎችም ቡድኑን ያንቀሳቅሳሉ፡፡እናም የዘንድሮ ኮተኒ ክለብ ከሌላው ግዜ በተለየ ምርጥ ነው፡፡ተጫዋቾቹ ልምምድ የሚያደርጉት እዛው መስርያ ቤቱ አካባቢ ነው፡፡ከፋብሪካው ጀርባ ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀ ስፍራ አለ፡፡ስፖርተኞቹ የፋብሪካው ቋሚ ሰራተኛ ናቸው፡፡ ሰአቱ ሲደርስ ተጫዋቾቹ ልብሳቸውን እዛው ቀይረው በጓሮው በኩል ወደ ሜዳው ይሄዳሉ፡፡የሚመጡት ተንጠባጥበው በመሆኑ ቀድሞ የደረሰ በኳስ እያሟሟቀ ይጠብቃል፡፡

ወጣቱ ተጫዋች መሀመድ ኡስማን (ሚግ) አንድም ቀን ሞልቶለት አያውቅም፡፡ ሁሌም ዘግይቶ ነው የሚደርሰው ፡፡የሚሰራው ማሽን ላይ ስለሆነ ልብሱን ቀይሮ ወደ ሜዳ ለመሄድ ሲዘጋጅ እዚህም እዚያም ቢሮ እየገባ ጓደኞቹን ሲያናግር ጉዳዩን ሲፈጽም እንዲሁ ሲባዝንይረፍድበታል፡፡አንዳንዴም እላፊ ስለሚያረፍድ አሰልጣኙ የስፖርት ቅጣት ይጥልበታል፡፡ዛሬ ግን ቢያረፍድም በአርፋጅነት አይቀጣም፡፡ ገና በማሟሟቅ ላይ ናቸው፡፡ሚግ እዚህም እዚያም ሲዋከብ ሽንቱን አላስተናገደም ነበር፡፡ልምምዱ ብዙ ሰአት ስለሚያቆየው ቶሎ ማራገፍ አለበት፡፡ከሜዳው በአንደኛው ጥግ እየሮጠ ሄደ፡፡ፊት ለፊቱ ቁጥቋጦና ትልቁ ተራራ ነው የሚታየው፡፡ ተራራው ፋብሪካውን ተንተርሶ የተተከለ ይመስላል፡፡ሚግ እየሸና፤ እየተነፈሰና እያስተነፈሰ ነው፡፡የሚያስበው ስለልምምዱ ነው፡፡ዛሬ አርብ ነው፡፡ እሁድ የደርቢ ጨዋታ አለ፡፡ይሄ ደርቢ ድሬዳዋን በአንድ እግሯ የሚያቆም ነው፡፡ጨዋታው የሚደረገው ከባቡር ጋር ነው፡፡ከተማዋ በጦርነት ድባብ ላይ ሆና እንኳን ይሄ ደርቢ መነጋገርያ መሆኑን አላቋረጠም፡፡ኢብራሂም ጃሚ የተጨበጨበለት የባቡር በረኛ ነው ፡፡ በዘንድሮው አቋሙ ለብሄራዊ ቡድን ተመርጧል፡፡ኢብራሂም አንድጠባይ አለው፡፡ብዙ ግዜ ኳስ ከክልሉ በራቀ ቁጥር ከግቡ ወጣ የማለት ባህሪ አለው፡፡እሁድ በሚደረገው ጨዋታ ኢብራሂም እንደወጣ ሚግ ጠብቆ ከርቀት መትቶ ለማግባት ፈልጓል፤መፈለግ ብቻ ሳይሆን ተዘጋጅቷል፡፡ መዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ሰሞኑን እየተለማመደ ነው፡፡

ዛሬ የመጨረሻ ከርቀት የማነጣጠርና የመምታት ልምምድ እያደረገ ነው፡፡አሁን ትንሽ ችግር የሆነበት የመመጠኑ ነገር ነው፡፡ ካለበት ቦታ ሆኖ የጎሉን ርቀት ለክቶ አስተካክሎ መምታት አለበት፡፡





ሽንቱ ቶሎ የሚያልቅ አልሆነም፡፡ዛሬ ምንም ስፖርት መስራት የለም፡፡ የሳምንቱ መጨረሻ በመሆኑ የእርስ በእርስ ግጥሚያ ነው ያለው፡፡ አሁንም እያስተነፈሰ ነው፡፡ሽንቱን እንደጨረሰ ይቀላቀልና ያገኘውን ኳስ ካለበት ቦታ ከርቀት እየመታ ይሞክራል፡፡እዛው እየሸና በእሱና በኢብራሂም መካከል የሚኖረውን ርቀት መገመት ፈለገ ፡፡‹‹.....እኔ እዚህ ብሆን.....ኢብራሂም ደግሞ እንደዛ ቢርቅ.....››ብሎ ለመገመት ራቅ አድርጎ ተመለከተ፡፡ኢብራሂም ይርቅበታል ብሎ ወደገመተው ቦታ አሻግሮ ተመለከተ፡፡ተመልክቶም አይኑን እዛው ላይ አደረገ፡፡ነገርግን ኢብራሂም ይገኝበታል ብሎ ወደገመተው ቦታ ሲመለከት የሆነ ነገር ሲንቀሳቀስ አየ፡፡ተራራው ላይ ምንም ነገር እንደሌለ ነው የሚያውቀው፡፡ምንድነው ታድያ የሚንቀሳቀሰው?ብሎ አተኩሮ ተመለከተ፡፡የኢብራሂምን ነገር ተወና አሁን ወደተንቀሳቀሰው ነገር አማተረ፡፡አይኔ ነው እንጂ የተንቀሳቀሰ ነገር የለም ብሎ ሀሳቡን ተወና ወደ ኢብራሂም ጉዳይ ተመለሰ፡፡

አሁንም ኢብራሂምን ከርቅት አቀመና እሱ ካለበት ቦታ እንዴትና በምን ሁኔታ መምታት እንዳለበት እያሰበ ሳለ የቅድሙ ነገር እንደገና ተንቀሳቀሰ፡፡አሁን በትክክል የሆነ ሰው አይቷል፡፡ ኢብራሂንም እርግፍ አድርጎ ተወው፡፡ተንቀሳቃሹ ነገር ላይ አተኩሮ ተመለከተ፡፡እንደገና ሌላ ቦታ ተንቀሳቃሽ ነገር አየ፡፡እየበዙበት ሄዱ፡፡ ወታደሮች ናቸው፡፡የሱማሌ ወታደሮች ፡፡ በልብሳቸው ነው ያወቀው፡፡ ‹‹ወይኔ ሱማሌ ገብታለች››ብሎ የጀመረውን ሽንት እስከመጨረሻው ሳይጠናቅቅ እየሮጠ ሄደ፡፡ልምምዱም ቆመ፡፡ወሬው ቶሎ ተዛመተና የፋብሪካውም ሰራተኛ ስራውን አቆመ፡፡የፋብሪካው የሰራተኛ ማህበር ሊቀመንበር ጌታቸው ገብረማርያም ከአባላቱ ጋር በመሆን ሰራተኛው ይስራ ወይስ ስራ አቁሞ ቤቱ ይቀመጥ? በሚል ለመነጋገር ቀጠሮ ይዘው ሳለ ከሰአት በኋላ ሌላ ጉዳይ ገጠማቸው፡፡ፊፋ ሱማሊያና ኒጀርን በአልቢትርነት እንዲመራ በእስቸኳይ በሮም አድርጎ ወደሞቃዲሾ እንዲሄድ ጥሪ አደረገላቸው፡፡ፊፋ ለሱማሌ የጻፈው ደብዳቤ ኢትዮጵያዊ አልቢትር እንደሚያጫውትና የማይስማሙ ከሆነ በፎርፌ እንደሚሸነፉ አስታወቀ፡፡የሱማልያ መንግስት ለፖለቲካው ሲል በመርህ ደረጃ እምቢ ቢልም ፌዴሬሽኑ ደግሞ ለመቀበል

ተስማማ፡፡ሁለቱ ረዳት ዳኞች ከኬንያና ኡጋንዳ በቀጥታ በረራ ሞቃዲሾ ሲደርሱ ኢትዮጵያና ሱማልያ የአየር በረራ ስላቋረጡ አልቢትር ጌታቸው በሮም አድርጎ ወደ ሞቃዲሾ ገባ፡፡

## ከጨዋታው በፊትና......

ደህንነቶች በገባበት እየተከታተሉት ነው፡፡በአምስት ቀን ቆይታው ከተማ ውስጥ ሲዘዋወር የሚያየውን ነገር በአእምሮው ይመዘግባል፡፡የመዘገበውን ወደ መኝታ ክፍሉ ገብቶ በማስታወሻው ያስፍራል፡፡ከተማ ውስጥ ያሉትን ወታደራዊ ተቋማት ሌሎችም የሚሊተሪ እንቅስቃሴ የት እንደሚገኙ እያጣራ ነው፡፡ጨዋታው እስኪካሄድና ከዚህ ሀገር ለቆ እስኪወጣ ድረስ ያሉትን እንቅስቃሴዎችና የሰዎችን ከጦርነቱ ጋር ያላቸውን ተሳትፎ እየመዘነ ይጽፋል፡፡ከውጭ ሀገር ሰዎች ጋር ስለጦርነቱ መነሻ ካገኘ ያወራል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከከተማ ውጭ ስለሚንቀሳቀሱ ያዩትን በአስተያየት ደረጃ ሲያወሩ ይመዘግባል፡፡፡እስረኞች የት እንዳሉ ይጠይቃል፡፡ የመጠየቁ ምክንያት ደግሞ ዘመዱ እንደተያዘበትና ለመጠየቅ በሚመስል አይነት ነው፡፡የኡጋንዳና የኬንያ ረዳት ዳኞቹ ሳይቀር ያዩትና የሰሙት ይነግሩታል፡፡ባይጠይቃቸውም ያወሩለታል፡፡ ማንኛውም መረጃ ለእሱ አስፈላጊ ነው፡፡ትንሿም ነገር ለኢትዮጵያ መረጃ ናት፡፡ እነዚህ ተጠረቃቅመው ትልቅ ነገር ይወጣቸዋል፡፡፡የእሱን ተመልሶ ወደ ሀገር መምጣት ቁጭ ብለው የሚጠብቁት የወታደራዊ መረጃ ክፍል ሳይቀር ያየውና የሰማውን በደምብ እንዲነግራቸው ይፈልጋሉ፡፡በተለይ የሶማልያ ህዝቡ በጦርነቱ ላይ ያለው ሞራልና ገፍቶ የመዝለቅ ብቃቱን ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ እናም ከዳኝነቱ ጎን ትልቁ ስራው ለሀገሩ መሰለል ነው፡፡

በጦርነቱ የተነሳ ሀበሾች ከከተማው ተባረዋል፡፡ሌሎችም ደግሞ ታስረዋል፡፡ የታሰሩት እዚህ ከተማ ያሉት ብቻ አልነበሩም፡፡ የሶማልያ ወታሮች ድንበር ጥሰው በምስራቅ ያሉትን ከተሞች በወረሩ ግዜ ከጅጅጋ ሳይቀር ብዙ ምርኮዎችን አምጥተው እዚሁ አጉረዋቸዋል፡፡ በዋናው ከተማ ሞቃዲሾ ሀበሻ ዝር በማይልበት ቦታ ይሄኛው ሰው ፊፋን ተገን አድርጎ እንደፈለገ እየተንቀሳቀሰ ነው ፡፡ከከተማው





ሊያባርሩት ቀርቶ በግዴታ የተቀበሉት ሰው ነው፡፡ከተማው ውስጥ በፈለገው ሁኔታ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ሲሰልል ያዝነው ቢሉ እንኳን የሚጣሉት ከፊፋ ጋር በመሆኑ ፎርፌ ከመበላታቸውም ሌላ ብዙ ዋጋ ያስከፍላቸዋል፡፡ይሄን ስለሚያውቁ ከተማውን ለቀውለታል፡፡ አልቢትሩም ይሄን ስለተገነዘበ የሚፈልገውን እየወሰደ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ሲነሳ በመንግስት ሰዎች እንዴት መረጃ እንደሚያሰባስብ በሚስጥር በደምብ ተነግሮታል፡፡ ደግሞም እኮ እሱ በራሱ ፖሊስ ስለነበረ መረጃ እንዴት እንደሚኀለኀል ያውቀዋል፡፡አንዳንድ ግዜ ደፈርና ጠንከር ብሎ ተገቢ ያልሆነ ቦታ በመሄድ መንገድ እንደተሳሳተ ሆኖ የሚፈልገውን አከናውኖ ሆቴል ውስጥ ይከሰታል፡፡ መጀመርያ ሻለቃ መንግስቱን ጨምሮ ሌሎች ባለስልጣኖች ወደሱማልያ እንዲሄድ አልፈለጉም ነበር ፡፡በኋላ ግን ስለሱማልያ የጦር እንቅስቃሴ ምንም መረጃ ስሌላቸውና ሰላይ ማስገባት ስላልቻሉ በአጋጣሚ ፊፋ በሰጣቸው እድል ተጠቅመው አልቢትሩን መረጃ እንዲያመጣላቸው እንዲሄድ ተስማሙ፡፡ሁሉንም ነገር በሚስጥር ነገሩት፡፡መረጃ እንዴት እንደሚያሰባስብ አስረዱት፡፡

ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ ‹‹ለሀገርህ ምን ይዘህ መጣህ?›› ለሚለው ምላሽ እንዲሆነው በቆየበት ግዜ ሁሉን ነገር ለማድረግ እየሰራ ነው፡፡ግን ደግሞ‹‹አንተን ለመርዳት ዝግጁ ነኝ›› ብሎ አንድ የሱማሌ ጄኔራል አጠገቡ ተገኝቷል፡፡ደግሞም ስለላውን እንዳያከናውን አላፈናፍን ብሎታል፡፡ይህ ሰው ጄኔራል ሙሳ ነው፡፡አንዳንዴ ሙሳ ወደ ቤቱ እስኪሄድ ድረስ ጌታቸውን በሆቴል እንደሚያስተናግድ መስሎ ይጠብቃል፡፡ወደ ቤት ከሄደ በኋላ ጌታቸው ወደ ስለላው ይመለሳል፡፡በኋላ ግን እየተግባቡ ሲሄዱ ጌታቸውም ሆነ ሙሳም መጠቃቀም ጀምረዋል፡፡ጄኔራል ሙሳ በሱማልያ ውስጥ አሉ ከሚባሉ ዳኞች አንዱ ነው፡፡ስራው ሚሊተሪ ቢሆንም በአጭር ግዜ ከታች ተነስቶ የጄኔራልነት ማእረግ አግኝቷል ፡፡ተስፈንጥሮ ትልቅ ማእረግ ማግኘት በራሱ አንድ መረጃ ነው፡፡ለጦርነቱ ሲባል በሱማልያ ሚሊተሪ ውስጥ ማእረግ እየታደለ እንደሆን የሚሳይ ነው፡፡ሰውዬው ወደ ሆቴል መጥቶ ወሬ ከጀመሩ በኋላ ‹‹ጌታቹ!!››አለ

‹‹አቤት››

‹‹የምረዳህ ነገር አለ?››

‹‹እኔን?››

‹‹እዎ››

‹‹ምንም››

‹‹ችግር የለም እኮ....››

‹‹ማለት››

‹‹እኔና አንተ እኮ.....››



አልቢትር ጌታቸው ገብረማርያም

ጌታቸው ነገሩ ገብቶታል፡፡ የእኔና አንተ ሀገር ጦርነት ላይ ቢሆንም ሁለታችን ግን ወዳጆች ነን አትፍራኝ ቅረበኝ በሚል አይነት የፈለገውን ሊረዳው እንዳሰበ ከስሜቱና ከአይኑ ውሃው ተረድቷል፡፡ ጌታቸው ዘመዱ የታሰረበት በማስመሰል የእስረኞችንና የምርኮኞች ቦታ የት እንዳለ ለመጠየቅ ግዜው አሁን ነው ብሎ ተዘጋጀ፡፡ጄኔራሉ በጣም እየቀረበው ነው፡፡ በድጋሚ‹‹ጌታቾ››አለ ፡፡

‹‹አቤት!!!››

‹‹ቤቴ ልውሰድህ››

‹‹አንተ?››

‹‹እዎ››

‹‹ቅርብ ነው?››

‹‹አይርቅም››





‹‹ሌላ ቀን እንሄዳለን››

‹‹መሄድ ስትፈልግ ንገረኝ ››

‹‹እሺ››

ይሄን ወሬ እዚህ ላይ መዝጋት አልነበረበትም፡፡ይሄ ሰውዬ ከፍተኛ ወታደራዊ ሰው በመሆኑ ቤቱ ሄዶ ወጣ ገባ ሲል መበርበር ይችላል፡፡አንድ ወሳኝ መረጃ ቢኖረውስ?በድጋሚ ይሄን ጥያቄ ሲያነሳ ለመሄድ ተዘጋጅቷል፡፡ እንደገና ወሬው ቀጠለ፡፡ጄኔራል ሙሳ‹‹..እኔ ኢትዮጵያን በጣም ነው የምወደው››አለ

‹‹አንተ!!!!!››

‹‹አዎ››

‹‹በምን ምክንያት››

‹‹ኢትዮጵያ ለእኔ ብዙ ነገር ናት››

‹‹እውነትህ ነው(በሆዱ እየወጋችሁን ይላል)

‹‹ሰውዬውን በጣም ነው የምወዳቸው››

‹‹ሻለቃ መንግስቱን?››

‹‹አይደለም››

‹‹ታድያ ማንን ማለትህ ነው››

‹‹ይድነቃቸውን ››

ነገሩ ለጌታቸው ግልጽ እየሆነለት ነው፡፡ይሄ ጄኔራል በአለም አቀፍ መድረክ ትልቅ ቦታ መድረስ ይፈልጋል፡፡ሱማሌን በአለም አቀፍ መድረክ በኮሚቴነት የሚወክል ሰው ስለሌለ እይታ እንዳጣና በኢንተርናሽናል ውድድር ትልቅ ቦታ ለመድረስ የወጠነው ህልሙ እንዳልተሳካለት አውቋል፡፡ኢትዮጵያ እንዲህ አይነት ሰው ስላላት ብዙ አልቢትሮቿ ትኩረት አግኝተው ለትልቅ ደረጃ እንደበቁ ያምናል፡፡ ደግሞም ነግሮታል፡፡ይሄን መንገድ የሚጠርግለት ሰው ሲፈልግ ጌታቸውን አግኝቶታል፡፡ኢትዮጵያንና ይድነቃቸውን ከልቡ እንደሚወድ እየነገረው ነው፡፡ ጄኔራል ሙሳ ስሙን ለይድነቃቸው እንዲስጥለት ለጌታቸው ነገረው፡፡ ጌታቸውም ምንም ችግር እንደሌለውና ይድነቃቸውም በተለይ ለምስራቅ አፍሪካ አልቢትሮች ድጋፍ እንደሚሰጡ አስረዳው፡፡ አሁን ነገሩ መስመር ላይ ገብቷል፡፡፡ ጉዳዩ

እንካ እምጣ ነው፡፡ግን ልብ ለልብ ለመግባባት እንዳይችሉ ጦርነቱ ሊጋርዳቸው እንደሚችል ስጋት አለ፡፡

እዚህ በሞቃዲሾ ከተማ ውስጥ ሰዎች ስለኢትዮጵያ ያላቸው ጥላቻ ከልክ በላይ እያለፈ ነው፡፡ ቴሌቪዥኑ ፤ሬድዮና ጋዜጣው በጦርነቱ የሶማልያ ወታደሮች ብዙ ሰው እንደገደሉና የምስራቁን ክፍል እንደያዙ ብዙ አደጋም እንዳደረሱ እየተናገሩ ፤ እየፎከሩ፤ እየዛቱ፤እያቅራሩ ነው፡፡በዚህ መሀል ነው ሁለቱ አልቢትሮች፤ሁለቱ የባላንጣ ሀገር ሰዎች እንደሚዋደዱና መረዳዳት እንዳለባቸው የሚነጋገሩት፡፡እናም ይሄ ጦርነት ትልቅ መጋረጃ እንዳይሆንባቸው ሰግተዋል፡፡ ሁለቱም ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ነው የሚፈልጉት፡፡ ጌታቸው መረጃ ይፈልጋል ፡፡ጄኔራሉ ደግሞ ወደ ኢንተርናሽናል ማማ መውጣት አስቧል፡፡ጌታቸው ይሄን ሰውዬ ወሬውን እያሰበ ለላኩት የመረጃ ሰዎች ጥሩ ነገር ይዞላቸው መሄድ ፈልጓል፡፡መረጃዎችን በዘዴ ማግኘት እንዳለበት አውቋል፡፡ጄኔራሉ እዚህ ጦርነት ውስጥ ስሜቱ እንደሌለው ማሳየት የፈለገ ይመስላል፡፡ ወሬውን እንደገና ጀመረው፡፡ሙሳ‹‹ይሄ ጦርነት ሊያቃቅረን ነው አይደል?››አለ

‹‹ምን ታደርገዋለህ››

‹‹ከጦርነት ይልቅ በመነጋገር መፍታት ይቻል ነበር እኮ››

‹‹እንደዛ ቢሆን ጥሩ ነው››

‹‹የእኔ ፍላጎቴ ይሄው ነው አሁንም ቢሆን…››

ጄኔራሉ ከጦርነት ውስጥ ወጣ፡፡መውጣትም ነበረበት፡፡እሱ እዚህ የሚፎክር ከሆነ የሚፈልገውን ነገር አያገኝም፡፡ነገሩ እንካ እምጣ ነው፡፡ አሁን የማኝከውን ነገር ስጠኝና አንተ የምትፈልገውን ነገር ታገኛለህ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡ ጌታቸው ‹‹..በአልቢትርነት ትልቅ ደረጃ መድረስ ትፈልጋለህ?››አለው

‹‹በጣም እንጂ››

‹‹ተስፋ አትቁረጥ››

‹‹እሺ››

‹‹እኔ ሁሉንም ነገር አመቻችልሃለሁ››





‹‹ትነግርልኛለህ?››

‹‹ለማን››

‹‹‹ለአቶ ይድነቃቸው››

‹‹ችግር የለም››

‹‹እና››

‹‹ፎቶህና ሌሎች ዶክመንትህን ትሰጠኛለህ››

‹‹በጣም አመሰግንሃለሁ››

ጌታቸው ምስጋና ምንም አያደርግለትም፡፡የሚፈልገው መረጃ ነው፡፡መረጃውን እንዲሰጠው ማግባባት ጀመረ፡፡

## ፕሪማች ሚቲንግ

ከጨዋታው በፊት የተደረገው ፕሪማች ሚቲንግ በጣም አጨቃጫቂና ረጅም ደቂቃ የፈጀ ነበር፡፡የቶጎው ኮሚሽነር አካዬ እንዲህ በዋዛ ስብሰባውን ለመጨረስ አልቻለም ነበር፡፡በማልያና በሌላ ጉዳይ ያደረጉት ውይይት አጭር ነበር፡፡ሶማሌዎች የፈለጉት ሌላ ነገር ነበር፡፡የሱማሌው የቡድን መሪ ለቶጎው ኮሚሽነር ‹‹ይሄን ዳኛ አንፈልግም››አለ

‹‹ለምን?››

‹‹እኛ እኮ ከእነርሱ ጋር ጦርነት ላይ ነን››

‹‹ቢሆንስ!!!››

‹‹ይጎዳናል››

‹‹ችግር የለውም››

‹‹በጣም ችግር አለው ይጎዳናል ብቻ ሳይሆን በጣም ይጎዳናል››

‹‹እናንተ ከፊፋ ጋር ጸብ ናችሁ እንዴ?››

‹‹አይደለንም››

‹‹እሱ እኮ የኢትዮጵያ ዳኛ አይደለም››

‹‹እና››

‹‹የፊፋ ነው››

‹‹እኛ የምናውቀው ኢትዮጵያዊ መሆኑን ነው››

‹‹ካጠፋ እኛ ነን የምንቀጣው››

‹‹በዘዴ ነው የሚጎዳን››
‹‹እሱን በደም'ብ እንከታተላለን››
‹‹እውነቱን እንንገርህ››
‹‹ምንድነው?››
‹‹እዚህ ሜዳ የሀበሻ ዳኛ አንፈልግም››
‹‹ያዳላል ብላችሁ ነው?››
‹‹ስለማዳላቱ ብቻ አይደለም ››
‹‹እና››
‹‹ህዝቡ አይኑን ማየት አይፈልግም››
‹‹ብቃ ችግር የለውም››
‹‹ስለዚህ ትቀይሩልናላችሁ››
‹‹አንቀይርም››
‹‹እና››
‹‹ጨዋታው እንዳውም አይኖርም››
‹‹ለምን?››
‹‹ዳኛ ከሌለ በምን ትጫወታላችሁ››
‹‹እኛ ያለብንን ችግር አልተረዳችሁም››
‹‹ተረድተናል፤ግን ፊፋ ፖለቲካ ውስጥ አይገባም››
‹‹እሽ አንድ አማራጭ እናቅርብ››
‹‹ምን››
‹‹ረዳት አልቢትሩ መሀል ሆኖ ያጫውት››
‹‹ዋናውስ?››
‹‹ዳር ይሁን››
‹‹አይሆንም››
‹‹እኛም መሀል እንዲሆን አንፈልግም››

ክርክሩ ረጅም ሰአት የወሰደና ሶማሌዎቹ አልቢትሩን ከቦታው ለማንሳት ብዙ ተሟገቱ፡፡ኮሚሽነሩ ግን አማራጭ ሰጣቸው ፡፡ አልቢትሩን መቀበል ወይም ፎርፌ መስጠት፡፡በአልቢትሩ የተነሳ ፎርፌ መስጠት እንደገና ከባድ ሽንፈት ሆነባቸው፡፡እያመማቸው እየቆሰሉም አልቢትሩን ለመቀበል ተገደዱ፡፡





## ሜዳ

ወደ ሜዳ የመጣው ተመልካች ስታዲየሙን ጢም አድርጎ ሞልቶታል፡፡ተመልካቹ ኒጀርና የኢትዮጵያን ዳኛ ለመግጠም እንደመጡ ነው የሚናገሩት፡፡ይሄ አልቢትር ለብቻው ከዚህ ውድድር ሊያስወጣቸው እንደሚችል አውቀዋል፡፡አብዛኛውሰው የሰሙት ዛሬ ወይም ትላንት ነው፡፡ የኢትዮጵያ አልቢትር በተመደበ ግዜ በከፍተኛ ሁኔታ ተቃውሞ አሰምተዋል፡፡ አልቢትሩ እንደተቀየረ ነው የተነገራቸው፡፡ ሚዲያው ይሄን ነው የዘገበው፡፡ ግን እነሆ ዛሬ አልቢትሩን ሜዳ ላይ አገኙት፡፡ እናም በተቃውሞ መጮህ ጀመሩ፡፡ ግን መጮህ ምንም አያደርግም፡፡ ኢትዮጵያ የሚለውን ቱታ አድርጓል፡ ይሄ ለእነርሱ ጥሩ ስሜት አይሰጥም፡፡ሲያፈጡና ሲፋጠጡት ደግሞ የፊፋን ያደርጋል፡፡

ሁለቱ ቡድኖች ወደ ሜዳ ገቡ፡፡ገብተውም ተደረደሩ፡፡የክብር እንግዳው ይመጣና ተዋውቆ ቀጣዩ ስነስርት ተካሄዶ ጨዋታው ይጀመራል፡፡የክብር እንግዳው ወደ ሜዳ ወረዱ፡፡በድምጽ ማጉያ የሆነ ነገር እያቅራራ እንግዳውን አጅቦ ወደ ሜዳው ጠርዝ አደረሰ፡፡ አልቢትሩ የክብር እንግዳውን ተመለከተ፡፡ እንደጠረጠረው እራሱ ነው፡ ፡ አልቢትሩ ሰውየውን አፍጥጦና ትኩር ብሎ አየው፡፡ ሰውነቱ ተወጣጠረ፡፡ ይሄን ሰውየው በኢትዮጵያ ጉዳይ ሲፎክር ብዙ ግዜ ሰምቶታል፡፡እራሱን ለማረጋጋት ሞከረ፡፡አሁን ያለው በፊፋ ካፖርት ውስጥ ነው፡፡እንግዳው ከደረጃው ወርደው መጡ፡፡ሰውየው የሀገሪቱ መሪ ዚያድ ባሬ ናቸው፡፡ይመጣሉ ብሎ አልገመተም፡፡እንደማይመጡ ነው የተነገረው፡፡ሰውየው ኳስ ሜዳ መምጣቱ ላይ እምብዛም ናቸው፡፡ በተለይ አሁን በጦርነት በተጠመዱበት ሰአት ብዙ ህዝባዊ ቦታ ላይ አይሄዱም፡፡ዛሬ ግን እዚህ መጥተዋል፡፡ምናልባትም ይሄን ጨዋታ የጦርነቱ አንድ አካል አድርገው የወሰዱት ይመስላል፡፡እዚህ ሜዳ የኢትዮጵያ አልቢትር እንዳይመጣ በመንግስት ደረጃ ሲከራከሩ የነበረው ነገር ተጥሷል፡፡የኢትዮጵያ አልቢትር የእኛን መሬት አይረግጥም ሲሉ ቢፎክሩም አልተሳካም፡፡ አልቢትሩ ካልተቀየረ ከውድድሩ እንወጣለን ብለው ቢዝቱም አላደረጉትም፡፡እናም ለምን እንደመጡ ባይታወቅም ሰውየው ተገኝተዋል፡፡ዚያድባሬ ወደ

አልቢትሮቹ ተጠጉ። የኢትዮጵያን ዳኛ ተመለከቱት። ፊታቸው ላይ የጦርነት ስሜት ይነበባል።ክብር እንግዳ የተባሉ ሰዎች ወደሚተዋወቁት ሰው ሲሄዱ ፈገግታ ሊነበብባቸው ይገባል ።ፈገግታ ባይኖራቸው እንኳን ሰላማዊ ፊት ይኖራቸዋል።ኮስታራ ቢሆኑ እንኳን ግርማ ሞገስ ያለው ነው። እኘህ ሰው አሁን እያሳዩት ያለው ፊት ኮስራታነት ሳይሆን ቁጣ ነው በፊታቸው ላይ ይዘው የመጡት።ቁጣ ብቻ ሳይሆን ንቀትም ተከተለ ።ከፊት ለፊት ያለው ተመልካች ድንበር ላይ ከፍተኛ ውጊያ የሚያደርጉ ሀገር ሰዎች እዚህ በሰላም የሚያደርጉትን የሰላምታ ልውውጥ ለማየት የጓጉ ይመስላል።

ዚያድባሬ በየቀኑ በሬድዮ ስለኢትዮጵያ የሚያሰሙት የጥላቻ ንግግር እዚህ አልቢትር ላይ እየተገለጸ ይመስላል።የቶጎው ኮሚሽነር ክብር እንግዳውን አልቢትሮቹ ጋር አድርሷል። ዚያድባሬ ለመተዋወቅ ሲመጣ ጌታቸው ትግስት እንዲኖረው ኮሚሽነሩ በሚገባ አስረድቶታል ።ዚያድ ባሬ ነገር ፈልጎ እዚህ መበጣበጥ እንዳይነሳ ስለሰጋ ነው።ኮሚሽነር አካዬ በፕሪማች ሚቲንግ ግዜ የሱማሌ ተወካዮች ጸብ አጫሪ መሆናቸውን ስላወቀ እዚያ የተደረገው ግብ ግብ እዚህ ሜዳ እንዳይቀጥል ሰግቷል።እንደርሱ እምነት ይሄ መተዋወቅ ባይኖር ደስ ይለው ነበር። ግን ግዴታ ሆኖበታል።አካዬ ዚያድ ባሬን ወደ ሜዳው ጠርዝ ካደረሰ በኋላ አልቢትሮቹን ተዋውቆ ወደ ተጫዋቾቹ መሄድ እንዳለበት ስለሚያውቅ ትውወቁን ቶሎ አስጀመረ። ዋናውን ዳኛ ዚያድባሬ እንዲተዋወቅ አምጥቶ ፊት ለፊት አገናኛቸው፡ ፡ሁለቱንም ለተመለከተ በሪንግ ውስጥ ያሉ ቦክሰኞች ይመስላሉ። የጦርነቱ ስሜት ሁለቱም ፊት ላይ አለ ።ጦርነቱን ማን እያጠቃ እንደሆን ለማሳየት የፈለጉ ይመስላሉ።

ትውውቁ ቶሎ አልተጀመረም ።ተፋጠዋል።ሁለቱም ፖሊስ ናቸው።ጌታቸው የቀድሞ ፖሊስ ባልደረባ ነው ።በተፈጥሮው እንደፖሊስ ተጠራጣሪ ከመሆኑም ሌላ ፖሊስ ቤት ገብቶ ትምህርት አግኝቶ እንደፖሊስ የኖረ ሰው ነው።ዚያድባሬ በጣሊያን አስተዳደር ግዜ የፖሊስ አስር አለቃ ነበር። በጣም ተናጋሪ በመሆኑ ህዝቡ እሱ የሚለውን ያምን ነበር። የጄኔራልነት ማእረግ ከደረሰ በኋላ ጓደኞቹን





አስተባብሮ መፈንቅለ መንግስት ካደረገ በኋላ ሶሻሊዝምን አውጆ ታላቋን ሶማልያን ለመፍጠር ህዝቡን ያንቀሳቀሰ ሰው ነበር።እነዚህ ሁለቱ ሰዎች የፖሊስነት ባህሪያቸውን ይዘው ኮሚሽነር አካየን አስጨንቀውታል።ዚያድ ባሬ ወደ ቦታው ከደረሰ በኋላ አልቢትሩን ከፍ ዝቅ እያደረገ በመመርመር መልክ ቆመ።ባሬ ለመተዋወቅ ዘገየ። የመሀል ዳኛውን ሳይጨብጥ ለመሄድ ፈልጓል።ፊቱን ወደ ሌሎቹ ዳኞች አዞረ።እንደገና የመሀል ዳኛውን ተመለከተው ።ሁለቱ ቢተናነቁና ሁሉም ነገር እዚህ እንዲፍረጠረጥ የፈለጉ ይመስላሉ። አካዬ አሁን ሰግቷል።ባሬ የመጣው የሆነ ነገር ለመፍጠር እንደሆን አውቆታል።ጌታቸው መስእዋትነት ከፍሎ ይሄን ጨዋታ በደምብ እንዲያስተናግድ ነግሮታል። እነሆ እስካሁን መጨባበጡ የለም። ባሬ የሚሰነዝረው እጅ አልነበረም።የጦርነቱ ወላፈን እዚህ ሜዳ ሰይ የደረሰ ይመስላል።

ኢትዮጵያ ጦርነቱ እንዳይካሄድና ችግሩ በድርድር እንዲፈታ ፈልጋ ነበር። ባሬ ግን ፈቃደኛ አልሆነም። እዚህ ሜዳው ጠርዝ ላይ ደግሞ ባሬ እጁን አልሰነዘረም። የክብር እንግዳ ናቸው እጃቸውን ቀድመው መሰንዘር ያለባቸው።ግን እጃቸው አየር ላይ የለም። የእሳቸው እጅ ከሌለ ደግሞ የተቀባይ እጅ አይኖርም።ምናልባት አሁን ጥሩ ሊሆን የሚችለው ሰውዬው ቶሎ እንዳላዩ ሆነው ቢያልፉና አልቢትሮቹን ትተው ወደ ተጫዋቾቹ መሄድ እንዳለባቸው ነው።ክብር እንግዳው ባይዘረጋም ምናልባት ነገሩን ሰላም ለማድረግ ይመስላል ጌታቸው እጁን ዘረጋ።ባሬ ግን ይሄን እጅ መጨበጥ አልፈልግም አይነት ዝም አለ።አሁንም የአልቢትሩ እጅ አየር ላይ ነው ያለው፡ ጨዋታው ሶማልያ ከኒጀር ነው። ነገር ግን የሁለቱ ቡድኖች ግጥሚያ እዚህ ካለው መፋጠጥ አይበልጥም።ዋናው ነገር ያለው እዚህ ነው። የጌታቸውና የባሬ ነገር ደርቢ ሆኗል።አሁንም ባሬ አልሰነዘረም። ከስድስት ወር በፊት በየመን ኤደን ወስጥ ጦርነቱን ለማስቀረት ብዙ ጥረት ተደርጓል።ዚያድባሬ ሶሻሊዝም አውጆ ከሶሻሊስት ሀገሮች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ፈጥሯል።



የሶማልያው መሪ ዚያድ ባሬ

በመጋቢት 1969 የኩባው መሪ ፊደል ካስትሮ በአንድ ሻምበል ጦር ታጅቦ አዲስ አበባ ገባ፡፡ደርግ ከኢህአፓ ጋር መዋጋቱን አይተው ካስትሮ ትክክለኛ አብዮት እየተካሄደ ነው አሉ፡፡ፊደል የመጡት ከሞቃዲሾ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ሞቃዲሾ መንግስት የሶሻሊዝምን መንገድ መከተሏ ጥሩ በመሆኑ ከሱማሊያ ጋር መደራደር አለባችሁ አሉ፡፡ካስትሮ መጋቢት 8/69 ኤደን ላይ ከደቡብ የመን መሪ ጋ በመሆን አደራደሩ፡፡ዚያድ ባሬ ኦጋዴን ይሰጠኝ አሉ፡፡‹‹....ካልደገፋችሁን ከሳውዲና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር መሳሪያ ወስዳለሁ ከእነርሱ ጋር እደራደራለሁ እናንተ ከሶሻሊዝም ጋር ገደል ግቡ›› አሉ፡፡ካስትሮ‹‹ኩባ ከሶማልያ መነጠል አትፈልግም ግን በኢትዮጵያ አብዮት እየተካሄደ ስለሆነ እንደግፋለን››አሉ፡፡ ዚያድ ባሬ የኦጋዴን ጉዳይ ያለቀለት በመሆኑ በጦርነት አገኘዋለሁ በሚል ዛቱ፡፡ሶሻሊዝም አባትና አስተማሪው ሶቭየት ህብረት ከጅምሩ ሱማሊያን፤ኢትዮጵያ፤ኩባ፤የመንን በአንድ አይነት ኮንፈረንስ ለማያያዝ እንዲሁም ተራማጅ የነበሩትን ታንዛንያ፤ሞዛምቢክ፤አንጎላ ፤አልጀርያ፤ቤኒን፤ሊቢያን





በአንድ አይነት መንገድ ለማሰባሰብ ያቀዱትን ጉዳይ በሱማሌ ማፈንገጥ ምክንያት ተደናቀፈ፡፡ስብሰባው እንደገና በካስትሮ አደራዳሪነት ሻለቃ መንግስቱ ሀይለማርያምና በዚድባሬ አማካይነት ረጃጅም ደቂቃዎች የፈጀ ድርድርና ውይይት አድርገው ሊሳካ አልቻለም፡፡ እንዳውም ባሬ በሀይለቃል ካስትሮን አውግዘውና ከፍ ዝቅ አድርገው ሳይጨባበጡና ቻው ሳይባባሉ ‹‹ጦርነት ይለየን ›› ብለው ወጡ፡፡

እናም በዚሁ ግዜ ዚያድባሬ መንግስቱንም ሳይጨብጡ እየተሳደቡ ወጥተው እንደዛቱት በፍጥነት ጦርነቱ ተጀምሯል፡፡ ተጀምሮም ተጧጡፏል፡፡ እነሆ ባሬ እዚህ ሜዳ ጠርዝ ያለውን ግብግብ ለመጀመር የመጡ ይመስላሉ፡፡ሰውየው እንዲህ ናቸው፡፡ ባሬ አልቢትር ጌታቸው ፊት እንደቆመ እየተመለከቱት ነው፡፡ መሳደብ የፈለጉ ይመስላል፡፡ ፊታቸው ላይ ከባድ የጥላቻ ጭነት አለ ፡፡ይሄን ጭነት እዚህ አልቢትር አካባቢ ለማራገፍ የመጡ ይመስላሉ፡፡ አልቢትሩ አሁንም እጁ በአየር ላይ ነው፡፡ አካዬ እንዲጨብጡ ለባሬ እየነገራቸው ነው፡፡፡ባሬ እጁን ሰደደ ፡፡ግን ሁሉንም አይደለም፡፡አራት ጣቱን ሰጠው፡፡ጌታቸው አራቱን በእጁ እንዳስገባ የእንደምንህ አይነት ለመወዝወዝ ፈለገ፡፡ ነገር ግን ባሬ አራቱን እንደሰጠ በዛው ሰከንድ ሁለቱን አስለቅቆ መለሰ፡፡ጌታቸው ማንነቱን ማሳየት የፈለገ ይመስላል፡፡ አራቱንም የባሬ ጣት ይዞ አምስተኛውን ለማስገባት ሲታገል ሁለቱ አመለጠው ፡፡ሁለቱን ለመያዝ ሲታገል ባሬ ቶሎ አላቀቀና ወዲያውኑ ወደ ረዳት አልቢትሮቹ ሄዶ በደምብ ጨበጣቸው ፡፡መጨበጥ ብቻ ሳይሆን ትከሻቸውን እያቀፈ እየወዘወዘ ‹‹እንደምናችሁ!!›› አይነት ነገር በደምብ ሰላምታ ሰጣቸው፡፡ሁለቱ ረዳት ዳኞች ከኬንያና ከኡጋንዳ የመጡ ናቸው፡፡ዋናውን ዳኛ ለማበሳጨትና በኢትዮጵያ ላይ ያለውን ጥላቻ አሳየ፡፡ባሬ ወደ ሜዳ የመጣው ይሄን ለማድረግ እንደሆን ሁኔታው መስክሯል፡፡

የትውውቁ ፕሮግራሙ አለቀ፡፡ጨዋታው ሊጀመር ነው፡፡ የማስጀመሪያው ፊሽካ ያለው የመሀል ዳኛው እጅ ነው፡፡ህዝቡ ቡድኑን እያበረታታ ነው፡፡ ቶሎ ቶሎ ለማጥቃት እንዲያስችላቸው ጨዋታው

እስኪጀመር ተቻኩለዋል።ጨዋታውን የሚጀምረው ሱማሌ ነው።ቶሎ ለማጥቃት የአልቢትሩን ፊሽካ እየጠበቁ ነው ።ግን ፊሽካው ዘገየ። መዘግየት ብቻ ሳይሆን ተጎተተ።መጎተት ብቻ ሳይሆን ወደ ኪስ ተከተተ።አልቢትሩ ኳሱን ለመጀመር የተጣደፉትን የሶማልያ ተጫዋቾች ትቷቸው ሄደ።መሄድ ብቻ ይሆን ሜዳውን አቋርጦ ወጣ። ኮሚሽነሩ ወደ እርሱ ሲመጣ እያየ ነው።ባሬ ባሳየው ንቀት ያለው ሁኔታ ለአካየ አላስደሰተውም ።አልቢትሩ ጥሎ ለመውጣት እንደፈለገ ነው የተረዳው ።አካዬ ወደ ጌታቸው እየሄደ‹‹ምንድነው››አለ

‹‹ይሄ ሰውዬ ከስታድየም ካልወጣ አላጫውትም››

‹‹ማን?››

‹‹ዚድባሬ››

‹‹ለምን?››

‹‹ጨዋታውን ሊያስረብሽ ነው የመጣው››

‹‹ችግር የለም››

‹‹እኔ አልወደድኩትም ቀይ ልሰጠው ነው››

‹‹ተው እንጂ አይደረግም››

‹‹ ታያለህ አደርገዋለሁ››

አልቢትሩ በውስጡ ያሰበው ይሄን ነገር ነበር።የክብር እንግዳው በሙሉ እጁ ስላልጨበጠው እንደናቀው ነው የቆጠረው።እንዲህ አይነቱ ነገር ለሀበሻ የማይቀበሉት ነገር ነው ።የሱማሌ ቡድን ኳሱን ለመጀመር ተጣድፎና ጓጉቶ በነበረበት ሰአት አልቢትሩ ትቶ ሲሄድ ህዝቡ መጮህ ጀመረ።የቡድን መሪዎቹ መጀመርያም የኢትዮጵያ ዳኛ እንዳይመደብብን ብለው ሲጨቃጨቁ ስለነበር ‹‹የፈራነው ደረሰ›› አይነት ከኮሚሽነሩ ጋር መከራከር ጀምረዋል።አልቢትሩ ወደ መስመር ተጠግቶ ቆመ።ቆሞም ለማጫወት ፍቃደኛ እንዳልሆነ እያሳየ ነው። ህዝቡ ግራ ተጋባ።ኮሚሽነሩም ደነገጠ።ይሄ አልቢትር ምንካው ብሎ ከትሪቡን ወርዶ ወደ መስመሩ እያመራ ነው።የባለሜዳው ቡድን ሰዎች ወደ መስመር ተጠግተው ጌታቸውን‹‹ምንድነው?››አሉ

‹‹ያ ባንድራ ይታይሃል››

‹‹የቱ?››

‹‹እዛ የተሰቀለው ባንድራ የኢትዮጵያ ነው››





‹‹እና››

‹‹አስተካክለው››

‹‹ምንድነው የሚስተካከለው?››

‹‹አስተካክል ብየሃለሁ››

‹‹ምን ሆነ?››

‹‹ምን እንደሆነ አንተ ታውቀዋለህ››

‹‹አልገባኝም››

‹‹አውቃችሁ ነው ያደረጋችሁት አይደል?››

‹‹ባንድራውን?››

‹‹አዎ ገልብጣችሁ ነው የሰቀላችሁት እኮ››

‹‹እኛ እንዲህ ነው የምናውቀው››

‹‹የተነገረህ እንደዚህ ነው?››

‹‹አዎ››

‹‹አሁን አስተካክሉ››

‹‹አይስተካከልም እንደዚህ ነው››

‹‹አትቀይርም?››

‹‹አንቀይርም››

‹‹እኔም አላጫውትም››

አሁን ትልቅ ችግር ተፈጠረ።ህዝቡ ባለበት የኢትዮጵያን ባንድራ ክብር ሰጥቶ እንዲሰቀል መድረጉ ለሰዎቹ ሽንፈት መሰላቸው፡ ፡በእርግጥም ከሽንፈትም በላይ የማይቀበሉት ነገር ነው። በከተማው ውስጥ ያቃጠሉት ባንድራ ክብር ሊሰጠው ነው።በጦርነት ላይ ያለን ሀገር ባንድራ በፊሽካ የተነሳ ከተሰቀለበት ወርዶ እንደገና ተስተካክሎ ሊሰቀል ነው።ይህ ጨዋታ ይለቅ እንጂ ቀጥቅጠው እዚህ ጎል ላይ ለመስቀል እንደማይመለሱ አልቢትሩ በደምብ ያውቃል።ባንድራው ወርዶ እንደገና ሲሰቀል ህዝቡ ቁጣውን ገለጸ።። ዚያድ ባሬ ባለበት ባንድራው መከበሩ ለእሱም ለእነርሱም የሚዋጥ ነገር አልሆነም። አማራጭ አልነበራቸውም ወይ ባንድራውን ማስተካከል አለበለዚያም ፎርፌ መስጠት ነው።ሁሉም እዛው ስታዲየም መፋጠጥ ሆነ። አልቢትሩ ጨዋታውን አልጀምርም ያለው በባንድራው ምክንያት መሆኑ ስለገባቸው ተናደዱ።በጦር መሳርያ ሳይሆን በፊሽካ ብቻ

ባንድራውን ማክበር እንደሚችል ገብቷቸዋል፡፡እየተናደዱ፣እየነደዱ፣እየመረራቸው፣እየኮስኮሳቸው፣እየቀፈፋቸው፣እየተንጨረጨሩ፣እያረሩና እየጎመዘዛቸው ባንድራውን አውርደው ፣አስተካክለውና አሳምረው በስነስርት ሰቀሉ፡፡አሁን ባንድራው በመከበሩ ወደመሀል ሜዳ ለመመለስ ተዘጋጀ ፡፡ነገር ግን ባንደራው ጫፍ ላይ አልደረሰም፡፡ ጌታቸው ለሰውየው‹‹በደምብ አስተካክል››አለ

‹‹ምን ሆነ››

‹‹አይታይህም እንዴ››

‹‹የተገለበጠውን አስተካክልን እኮ››

‹‹ወደላይ አውጣው››

‹‹ምን ማለት ነው››

‹‹ግማሽ ድረስ የሀዘን ነው››

‹‹እና››

‹‹ጫፍ አድርስ ካለበለዝያ...››

ሁሉም ተስተካከለ፡፡ በስነስርአት በመስቀላቸው አልቢትሩ አመስግኖ ጨዋታውን አስጀመረ፡፡አልቢትሩ ባንድራው ሲወጣ አወጣጡንና እንደገናም ዚያድባሬን እየተመለከተው ነበር፡፡ሰውየው እጁን ቢያወራጭም ምንም ማድረግ አልቻለም፡፡ጸጥ ለጥ ብሎ ከተማው ውስጥ በጥላቻ እንዲቃጠል የሚያደርገውን ባንድራ በፊሽካ ብቻ እንዲከብር ሲደረግ ለእሱ ትልቅ ውድቀት ነበር፡፡ባንድራውን በዚያን ግዜ ቀብሪድሃርና ጅጅጋ አቃጠሉ፣የሱማሌን ባንድራ ተክሉ ይሄን ያህል ወደ ኢትዮጵያ ዘልቀው ብዙ ከተሞችን ተቆጣጥረው የኢትዮጵያን ባንድራ አውርደው የሱማሌን እየሰቀሉ የሚቃወማቸውን እስር ቤት አጎሩ፡፡ግን በስታዲየም ውስጥ በፊሽካ ተገዶው አስተካከሉ፡፡ ኢትዮጵያ ማለት ይሄ ባንድራው ነው፡፡አልቢትሩ በፊሽካ ኢትዮጵያን አስከበረ፡፡ጨዋታው ተጀመረ፡፡ተጀምሮም ሱማሌ አግብቶ 1ለ0 መርቶ እረፍቱን ጨረሰ፡፡ከእረፍት ተመልሶም ማጥቃቱን ቀጠለ ነገር ግን ተጋጣሚው እያየለበት መጣ፡፡

ጨዋታው ሊጠናቀቅ ነው፡፡ኒጀር 1ለ0 እየተመራ ነው፡፡ ኒጀሮች ይሄ ውጤት ይጎዳቸዋል፡፡አቻ ለመሆን እየተሯሯጡ ነው፡፡መሯሯጥ ብቻ ሳይሆን አጣድፈው እያጠቁ ነው፡፡ሱማሌ ይሄን ውጤት ይዞ





ለመውጣት እየተቸገረ ነው፡፡ በዚያ ላይ በአልቢትሩ ላይ እምነት የላቸውም፡፡ስአቱ አላለቀም፡፡ የተወሰነ ደቂቃ ይቀራል፡፡አንድ ኳስ ኒጀሮች አገኙ፡፡ሄዱ፡፡ዘመቱ ፡፡ወደ ግብ እየተጠጉ ነው፡፡ አደገኛ ኳስ ነው፡፡ሱማሌ ሊያበቃለት ነው፡፡፡ተከላካዮቹ ማስጣል አልቻሉም፡፡ ወደ ግብ እየቀረበ ነው፡፡ ህዝቡ ተጨንቋል ግን የሆነ ነገር ሆነ፡፡ፊሽካ ተነፋ ፡፡ፋወል አይደለም፡፡ ከጨዋታ ውጭም አልነበረም፡፡አልቢትሩ ጨዋታው ያቆመው አልቋል ብሎ ነው፡፡ ይሄ ግብ ቢቆጠር ሱማሌ ‹‹ቻው›› ይባል ነበር፡፡ይሄ ግብ ቢቆጠር ሁሉም ነገር መበላሸቱ አይቀሬ ነው፡፡ፊሽካው ለአልቢትሩም ለባለሜዳውም ቡድን በጥቅሉ ለሁለቱም ወሳኝ ነው፡፡ሱማሌም አሸናፊነቱን ያረጋግጣል፡፡ አልቢትሩም በሰላ ያገኘውን መረጃው ይዞ በሰላም ወደ ሀገሩ ይመለሳል፡፡እንደኳሱ አደገኛነት ቢቆጠር ኖሮ አልቢትሩ በህይወት ላይመለስ ይችላል፡፡

ገና ቀሪ ደቂቃ እያለ ሱማሌ ኒጀርን መቋቋም ስላቃተው ውጤቱን ይዞ ለመውጣት‹‹ስአት !!!ስአት!!!››እያሉ አልቋል ብለው እየጮሁ ነው፡፡ኳሱ ቢገባ እላፊ ስአት አጫውቶን ነጥብ ጣልን ተብሎ በቋፍ ላይ ያለውን ተቃውሞ ወደለየለት አደጋ ሊገባ ይችላል፡፡አንድ ግዜ ሜዳውን ገብተው ከወረሩት አልቢትሩ በህይወት ላይመለስ ይችላል ፡፡የኢትዮጵያ መንግስትም እየጠበቀ ያለው መረጃ ከአልቢትሩ ጋር እዛው ሊቀበር ይችላል፡፡ሱማልያ በሜዳ ላይ አሸነፈች አልቢትሩም በመረጃ አሸንፎ እገባደደ፡፡አልቢትሩ ያየውን፣ የሰማውን ፣የሰበሰበውን መረጃ ደብቆ ወደሀገሩ ተመለሰ፡፡የእሱ መረጃ በደህንት ክፍሉ በጉጉት እተጠበቀ ነበር፡፡ለሀገሩ በሰራው ውለታ ተመስገን ነገር ግን እመት ሳይሞላው የፋብሪካውን ሰራተኞች ኢህአፓን እንዲደግፉ አመቻችቷል ደርግ ላይ ተቃውሞ አስነስቷል በሚል ጠልፈው ወሰዱት ፡፡ብዙ ካንገላቱት በኋላ ወደ ከርቸሌ ወረወሩት፡፡አሁን በእግር ካስ ፌዴሬሽን በውድድሮች ላይ በኮሚሽነርነት ያገለግላል፡፡

## ምእራፍ 11

### ፈላጊና ተፈላጊ

### ሻሸመኔ 1969

ሻሸመኔ ከተማ በስተሰሜን ባለው ዳርቻ ላይ የሚገኘው አካባቢ ጃማይካውያን የከተሙበት ሰፈር ነው። ቦታው ከከተማው ወጣ ያለ በመሆኑ ጭር ያለ ነው። አልፎ አልፎ መኪኖች የሚመላለስበት ቢሆንም እግረኛ እምብዛም አይታይም።አንድ ሰው በመንገዱ ላይ ጣደፍ ጣደፍ እያለ ይሄዳል።የሚመጣው ከአውራ ጎዳና መስሪያ ቤት ነው።መስሪያ ቤቱ ከጃማይካ መኖሪያ ቤት ፊት ለፊት 50 ሜትር ርቀት ላይ ነው።ጥላሁን በላይ የቀበሌ 10 ሊቀመንበር ነው። ዛሬ በዚህ ቦታ ለብቻው እንዴት እንደተገኘ የሚያውቅ ባይኖርም መገኘት እንዳልነበረበት ራሱ ያውቃል። ቀበሌ 10 የሚገኘው እሱ ከሚጓዝበት በስተምዕራብ አቅጣጫ ነው።እየተጓዘ ያለው እሱ በሊቀመንበርነት በሚመራው ቀበሌ ክልል ቢሆንም ከዋናው ሰፍራ ራቅ ያለና ሰው የማይበዛበት አካባቢ ነው።ነገር ግን ጭር ባለው መንገድ እየተጓዘ ቅርብ ቦታ ባለው የእንጨት ስራ ድርጅት መግባት ፈልጓል።

የሀይሉና ስራው የእንጨት ስራ ድርጅት ከመንገዱ ባሻገር ትንሽ ገባ ብሎ ይገኛል።ወደዚያ ለመድረስ አሁን ካለበት ስፍራ ጥቂት መሄድ ይጠበቅበታል።ሁለት ወጣቶች ከየት መጡ ሳይባል መንገዱ ላይ ተገኙ ።አስበውበትና ተዘጋጅተውበት ይሁን ባይታወቅም ከጀርባው እየተከተሉት ይገኛሉ። ጥላሁን ዞር ሲል ልጆቹን ያያቸዋል፡ ፡እንዴት ሊሆን ቻለ? እነርሱም መከተላቸውን አላቆሙም።ጥላሁን ልጆቹ ወደ ጉዳያቸው የሚሄዱ ሳይሆኑ እሱን እየተከታተሉት እንደሆነ ጠርጥሯል። በእንዲህ አይነት ገላጣና ሰውእምብዛም በማይመላለስበት መንገድ ለብቻው መሄዱ ያልተለመደ ነው። በሻሸመኔ ያሉ ወጣቶች ከከተማ ወጣ ያለ ስፍራመሽገው የኢህአፓን እንቅስቃሴ ያከናውናሉ። ከአዲስ አበባ ጠፍተው ሻሸመኔ የመሸጉ





ከፍተኛ የኢህአፓ አመራሮች እዚያ ቦታ ተጠልለዋል ።ነገር ግን የቀበሌው አብዮት ጥበቃዎች እያሳደዷቸው ነው።በዚህ ሁኔታ የተናደዱት ወጣቶች በቀል ፈልገዋል።ኢህአፓ የቀበሌውን ሊቀመንበር ታርጌት እንዳደረገች ቢነገርም ከወሬ ያለፈ ነገር እንደሌለ እየታየ ነው፡

ዛሬ ግን የተባለው ነገር ውሸት እንዳልሆነ ሊረጋገጥ የተቃረበ ይመስላል። ጥላሁን በዚህ ስፍራ በእንዲህ ባለ ሁኔታ መገኘቱ እንደቀፈፈው ያስታውቃል። በድጋሚ ዞር ብሎ ሁለቱን ወጣቶች ሲያያቸው ሽንታቸውን ለመሽናት ከመንገዱ ዳር ወዳለው ጢሻ ሄድ አሉና ተሰየሙ።እሱም ተመልሶ ሄደ።ፈጠን ብሎ ተራመደ።ሁለቱ ልጆች በእጃቸው ቦርሳ ይዘዋል። አንደኛው በእጁ ኳስ ታቅፏል። የአውራ ጎዳና ቡድን በሳምንት ሁለቴ ልምምድ ይሰራል።ቡድኑ በከተማው ውስጥ በሚደረገው የተጧጧፈ ግጥሚያ ተሳታፊ ከሆኑት ቡድኖች ዋነኛው ነው።ዛሬ ትሬኒንግ ከሚሰራባቸው ቀናት አንዱ ነው።የሚለማመዱት ከድርጅቱ ጀርባ በሚገኘው ሜዳ ነው።

ተጫዋቾቹ አብዛኛው የድርጅቱ ሰራተኛ ሲሆን የተወሰኑት ተማሪና የተለያየ መስሪያ ቤት የሚገኙ ናቸው።ሌላ ቦታ የሚሰሩት ተጫዋቾች ከሰዓት ከከተማ በድርጅቱ መኪና ፣በፈረስ ጋሪ ወይም በእግር እያዘገመ ወደ ሜዳ ይመጣሉ።አሁን በመንገዱ ዳር የሚታዩት ተጫዋቾች ከከተማ ለልምምድ ወደ ሜዳ የመጡ ልጆች እንደሆኑ ነው ጥላሁን ያሰበው።ግን ልጆቹ ወደ ሜዳ መሄድ ሲገባቸው ለምን ወደ ተቃራኒው መስመር ይጓዛሉ?

ጥላሁንም ጥርጣሬ የፈጠረበት ሁኔታ የልጆቹ አካሄድ ነበር። አንድ ቦታ ከለላ መያዝ ፈለገ።ከመለማመጃው ሜዳ በስተደቡብ 70 ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ፋርማሲ አለ። ከፋርማሲው አጠገብ ያሉት ቤቶች በራቸው ዝግና ጭር ያሉ ናቸው።

ፋርማሲው የባቾሬ ሲሆን አገልግሎት የሚሰጠው ቀጥራቸው አነስተኛ ለሆኑት የአካባቢው ቤቶች ነው።ብዙ ጊዜ ሰው አይገባበትም ።በሳምንቱ ቅዳሜ ቀን ለገበያ ወደ ከተማ የሚመጡ ገበሬዎች መድሀኒት ስለሚገዙ በወረፋ ነው የሚሸጠው። ከዚያ ቀን ውጭ ደንበኞች ጎራ ስለማይሉ አንዳንዴ ውስጥ ያለው ሰው ከፋርማሲው ጀርባ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ተጠርቶ ነው አገልግሎት የሚሰጠው ።

እለዚያም እዚሁ ጋዜጣና መጽሀፍ በማንበብ ጊዜውን ያሳልፋሉ፡፡ አሁን በዚያ አካባቢ የሚታዩት ጥላሁንና ሁለቱ ወጣቶች ናቸው፡፡ ወጣቶቹ እየተጠጉት ነው፡፡50 ሜትር ያህል ርቀት ደርሰዋል፡፡ጥላሁን ግራ ተጋባ፡፡ ልጆቹ ደረሱበት፡፡ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ‹‹ሰውዬ››አሉ

‹‹እኔን ነው?››

‹‹አዎ››

‹‹ምንድነው?››

‹‹ልናናግርህ ነው››

‹‹ለምን?››

‹‹ለጉዳይ››

ለመቆም አልፈለገም፡፡ ወጣቶቹ 30 ሜትር ያህል ርቀት ላይ ደርሰዋል፡፡ ከተማው በፖለቲካ በተወጣጠረበት ጊዜ ጥላሁን እዚህ መገኘቱ ስህተት እንደሆነ አውቋል፡፡ወጥመድ ውስጥ መግባቱን ገምቷል፡፡በጥቂት ደቂቃ ውስጥ በሁለቱ ተጫዋቾች ግድያ እንደሚፈጸምበት ጠርጥሯል፡፡ ብዙ ጊዜ ሽጉጥ ይታጠቃል፡፡ዛሬ ወደ መስሪያ ቤት ሲመጣ ሽጉጡ በእጁ አልነበረም፡፡ቢያንስ መሳሪያውን ቢይዝ መከላከል ይችል ነበር፡፡ ወጣቶቹ እየተጠጉት ነው፡፡ ዞር ብሎ ሲያይ አንድ ቤት ክፍት ነው፡፡ ቤቱም ፋርማሲው ነው፡፡ጊዜ ሳይጠፋ ለልጆቹም መልስ ሳይሰጥ ዘው ብሎ ገባ፡፡‹‹እዚህ ቤት?››አለ

‹‹አቤት››(ከሌላው ክፍል የመጣው ሰው)

‹‹ደህና ዋልክ››

‹‹ደህና..... ምን ልስጥህ?››

‹‹መድሀኒት››

‹‹ምን አይነት?››

‹‹የጉንፋን››

ከባንኮኒው ጀርባ ያለው ሰው ከመደርደሪያው ላይ ለጉንፋን የሚሆን መድሀኒት ለማምጣት ተንቀሳቀሰ፡፡ ጥላሁን መናገር ጀመረ‹‹እኔ የምልህ!!››አለ

‹‹አቤት››

‹‹መድሀኒቱን ተወው››





‹‹ለምን?››

‹‹ታውቀኛለህ እኔን?››

‹‹የማውቅህ መሰለኝ››

‹‹ ካላወቅከኝ እዚህ ቀበሌ ሀላፊ ነኝ››

‹‹እና››

‹‹አንድ ነገር ልጠይቅህ?››

‹‹ምን?››

‹‹እነዚህን ልጆች ታውቃቸዋለህ?››

‹‹የትኞቹ?››

‹‹ወደ ውጭ ውጣና እያቸው››

ውስጥ ያለው ሰው ወጣና ተመለከተ ፡፡ ልጆቹ መንገዱ ዳር ደርሰው ወደ በሩ ተጠግተው ነበር፡፡ ሲገቡ በተዘጋጁበት ሰዓት ውስጥ ያለው ሰው ሲወጣ ተመልሰው የእጥሩን ጥግ ይዘው ኳሱን እያነጠሩና በእጅ እየተቀባበሉ ወደ ላይ ወጡ፡፡ሰውየው ወደ ውስጥ ገባና ‹‹አየኋቸው››አለው

‹‹ታውቃቸዋለህ?››

‹‹አላውቃቸውም.....ችግር አለ እንዴ?››

‹‹መሰለኝ››

‹‹እንዴት?››

‹‹ሊተናኮሉኝ ፈልገው ነበር››

‹‹በምን ምክንያት ?››

‹‹አላውቅም››

‹‹አይመስለኝም››

‹‹ግን ታውቃቸዋለህ?››

‹‹አላውቃቸውም››

‹‹እዚህ ሰፈር ናቸው?››

‹‹አይመስለኝም››

‹‹ከየት የመጡ ናቸው?››

‹‹ኳስ ተጫዋቾች በዚህ ማለፋቸው የተለመደ ነው››

‹‹ሁሌ?››

‹‹ አዎ...እዚህ ገብተው መድሀኒትም ይገዛሉ››

‹‹ኳስ ተጫዋቾቹን ታውቃቸዋለህ?››

‹‹አንዳንዶቹ አዲስ ናቸው››

‹‹እነዚህስ?››

‹‹አዲስ ይሆናሉ››

‹‹እርግጠኛ ኳስ ተጫዋቾች ናቸው?

‹‹አዎ ኳስ ይዘዋል። ትጥቅም በቦርሳ አንግተዋል››

‹‹ታዲያ ለምን ወደ ኳስ ሜዳ አይሄዱም? ››

‹‹ማለት ››

››ለምን ወደ ታች ይመጣሉ?››

‹‹ፋርማሲ አንዳንዴ መድሀኒት ፍለጋ ብቅ ይላሉ››

‹‹አሁን ታዲያ ለምን አልገቡም?››

‹‹የት ?››

‹‹እዚሀ››

‹‹እነርሱ እኮ ወደላይ ሲሄዱ ነው ያየኋቸው››

ጥላሁን ከፋርማሲው በር ብዙም ሳይወጣ አንገቱን ብቅ አድርጎ ወደ ውጭ ተመለከተ። ወጣቶቹ ከባሻገር ባለው መንገድ ቆመዋል። አይሄዱም። አይመጡም። እስኪወጣ እየጠበቁ እንደሆነ ገመተ። አንደኛውን በመልክ ያውቀዋል ግን የት እንዳየው ግራ ገባው። ወጣቱ የሹራብ ኮፍያ አድርጓል።ጥላሁን ስልክ እንዳለ ጠይቆ ወደ ቀበሌ አስር (0 -10) ደውሎ በአስቸኳይ ታጣቂዎች እንዲላኩለት ነገራቸው።አለቃቸው ችግር ውስጥ መግባቱን የተረዱት አብዮት ጠባቂዎች ከንፋስ ባልተናነሰ ፍጥነት ቦታው ላይ ደረሱ። እነርሱ እስኪመጡ ጥላሁን ለሰውየው ፋርማሲውን ‹‹ዝጋ››አለው

‹‹ለምን ?››

‹‹አደጋ አለ››

‹‹ምን እያልክ ነው?››

‹‹ማንነቴን ታውቃለህ?››

‹‹ነገርከኝ እኮ››

‹‹ሰዎቹ እኔን ለመግደል ነው የመጡት››

‹‹እስከዚህ ድረስ››(ደነገጠ)

‹‹ቤቱን ዝጋ ብዬሀለሁ››

‹‹እሺ ››





በሩ ተዘጋ ።ምናልባት መጥተው ጥሰው ከገቡ በሚል ለመሸሸጊያ ወደ ሌላኛው ቤት ተዛወሩ።አብዮት ጠባቂዎቹ ወደ ቤቱ እንደደረሱ በርግደው ገቡና ውስጥ ያለውን ሰው ጠመንጃ አቀባብለው ሊደፉት ተዘጋጁ ።አለቃቸውን አግቶ የያዘው እሱ መሰላቸው። ሁኔታውን ዘርዝሮ ከነገራቸው በኋላ ወጣቶቹን ለመያዝ ወደ አውራ ጎዳና ሜዳ ሄዱ።አብዮት ጠባቂዎቹ ተቅበዘበዙ። አለቃቸውን ለመግደል ወይም ለመተናኮል አስበዋል ያሉትን ወጣቶች እዚሁ ነው የሚደፏቸው።ጥላሁን ልምምድ የሚያደርጉትን ተመለከተ ። ከመሀላቸው አምበሉ ወደ እነሱ መጣ ‹‹ችግር አለ እንዴ?››አለ

‹‹ሰው ፈልገን ነው››

‹‹ማንን?››

‹‹ሁለት ልጆች ቅድም ወደ እዚህ መጥተው ነበር››

‹‹እነማን?››

‹‹እዚህ የሚጫወቱ››

‹‹ታወቋቸዋላችሁ?››

‹‹ በስም አናውቃቸውም››

‹‹የኛ ተጨዋቾች እነዚህ ናቸው››

‹‹ሌሎች የሉም››

‹‹አንድ ሁለት አሉ ።ግን መስሪያ ቤት ለስራ ወደ መስክ ልኳቸዋል››

‹‹ስለዚህ ሌላ የለም?››

‹‹የለም››

ጥላሁን ቅድም ኳስ ይዘው ያያቸው በእርግጠኝነት ስፖርተኞች ሳይሆኑ ገዳይ እንደሆኑ አውቋል። አሁን ደግሞ የበለጠ አረጋግጧል። ፋርማሲ ወስጥ ሆኖ በርቀት አጮልቆ ሲያይ ወደ ጃማይካውያኑ መኖሪያ ቤት በር ላይ ደርሰው አይቷቸዋል ።ስለዚህ ወደ እዚያ ነው የሄዱት፡ በፍጥነት ወደዚያ ሄዱ። ዳንኤል ሪችን አገኙት‹‹ሰው ፈልገን ነበር››አሉት

‹‹ማን? ››

‹‹ሁለት ልጆች አሁን ወደዚህ ገብተው ነበር››

‹‹አላየኋቸውም››

እዚያ አካባቢ እሰሳ ተደረገ፡ አንዳንዶቹ ቤቶች ዝግ ስለነበሩ ለፍተሻ አልተመቸም፡፡ጥላሁን በእግርጠኝት ልጆቹ ወደዚህ ቤቶች እንደመጡ አውቋል፡፡ስለተፈጠረው ሁኔታ ከአብዮት ጥበቃዎቹ ጋር እያወራ በአካባቢው መጠበቅ ጀመሩ፡፡ምናልባት ከተደበቁበት ጎሬ ብቅ ሲሉ ሊይዟቸው ነው፡፡ብዙ ጠበቁ፡፡ ምንም የለም፡፡ እስዚያም የተዘጉት ቤቶች ባለቤቶቹ እስኪመጡ ለመጠበቅ ተነጋገሩ፡፡ እንደገናም ማሰላሰል ጀመሩ፡፡አሁን የሚገኙት አዋሽ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው፡፡ይሄ ደግሞ የእነሱ ክልል አይደለም ፡፡ቀበሌዎች‹‹በኔ ክልል ሳታስፈቅደኝ ገባህ››በሚል ይካሰሱና ይወቃቀሱ ስለነበር ከዚህ አካባቢ ቶሎ መልቀቅ ፈለጉ፡፡

ከእነርሱ ክልል ወጥተው በፍጥነት ወደ ቀበሌያቸውተመለሱ፡፡ ጥላሁን ወደ ከተማ በመሄድ ለህዝብ ደህንነት ሰዎች የተፈጠረውን ሁኔታ ነገራቸው፡፡የገዳዮቹን መልክና የለበሱት ሳይቀር አስረዳ ፡፡ወደ ስራ እንዳይሄድና ሰዎቹን ተከታትለው እንደሚይዙ ነገሩት፡፡ከሁለት ቀን በኋላ መጥቶ ሪፖርት እንዲያደርግ አሳወቁት፡፡በነጋታው ከሰዓት ስልክ ደውሎ የጠራጠራቸውን ወጣቶች እነማን እንደሆኑ እንዳወቃቸው በነርሱም ላይ መረጃ እንዳገኘለገበየሁ ይነግረዋል፡፡ በተለይ የሹራብ ኮፍያ ያደረገው ልጅ የት እንደሚያውቀው ዘግይቶ ነው የደረሰበት፡፡ ገበየሁ ከህዝብ ደህንነት ሰዎች አንዱ ሲሆን የከተማው አብዮት ጠባቂዎች አሊቃ ነው፡፡ጥላሁን ለገበየሁ የልጆቹን ማንነት፣ የት እንደሚገኙ በስልክ አስረዳው፡፡ እንዴት እንደሚይዟቸው ለመነጋገር ምሽት ላይ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ሆቴል እንዲገናኙ ቀጠረው፡፡ቦታውን ለምለም ሆቴል ነው፡፡

ለምለም ሆቴል የሚገኘው ከተማውን አቋርጦ ከሚሄደው ከኤሳ ወንዝ ድልድይ በስተደቡብ በኩል 100 ሜትር ርቀት ላይ ነበር፡፡ ገበየሁ ለጥንቃቄ ሲል በሁለት አብዮት ጠባቂዎች ታጅቦ ቦታው ላይ ደርሶ እየጠበቀው ነው፡፡ ገበየሁ ለጥላሁን ስለገድያው ሙከራና ስለሰዎቹ ማንነት ለማንም እንዳይነግር አስጠነቀቀው፡፡እቅዱ ጥላሁን እንደመጣ ልጆቹ የት እንዳሉ እንደሚነግረውና ምሽቱን አፍሰው እስር ቤት በማስገባት ሊመረምሯቸው ነው፡፡ጉዳዩ በከተማው ባሉ በትልልቅ አመራሮች ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ነው፡፡ጥላሁን እንዳስታወቀው





በእርግጥ ሊገሉት የተከታተሉት ሰዎች እንዳሉ ከታወቀ ኢህአፓ የስኳድ ቡድን ሻሸመኔ አስገብታለች ማለት ነው፡፡

እስከዛሬ ከተማ ውስጥ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንኳን ጎልቶ የማይታይ ነው፡፡ቢኖርም ወረቀት ከማንበብ፣ ከመበተን የዘለለ ነገር የለውም፡፡በስኳድ ደረጃ ግን የማይታሰብ ነው፡፡አሁን ግን ጥላሁን ደረሰብኝ ካለው ነገር ስኳዶች ከተማ ውስጥ ካሉ ነገሩ ወደ ሌሎች ከፍተኛ ባስልጣናት ጦሱ ስለሚተርፍ መጠንቀቅ ይፈልጋሉ፡፡ዋናው ነገር እነዚህን ሁለት ወጣቶች በመያዝ በግርፋት እናግዘው ሌሎችንም መልቀም ነው፡፡የቀበሌው አብዮት ጥበቃዎች የወጣቶቹን ማንነት በስም እንዲነግራቸው ወተወቱት፡፡ምናልባት ማንነታቸውን ካወቁ መንገድ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩበት ለመያዝ ነው፡፡ጥላሁን ግን ገበየሁ ለማንም ስም እንዳትሰጥ በሚል እንዳስጠነቀቀው ነገራቸው፡፡

## በተኩስ መሀል

ከባሌ ጎባ መስመር ወደ ሻሸመኔ ከተማ እየገቡ ያሉ መኪኖች ብዛታቸውን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡አንዱ ሲያልፍ ሌላው ይከተላል፡፡ አንዱ ሲሄድ አንደኛው ይመጣል፡፡መኪኖቹ እንደጉድ ይግተለተላሉ፡፡ አውቶብሶች ናቸው፡፡መንገደኛ የጫኑ አልነበሩም፡፡ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ አውቶብሶቹ በሰልፍ ቀስ እያሉ ይጓዛሉ፡፡ ከመኪኖቹ ፊት ላንድሮቨር መኪና ውስጥ አንድ ሰው ቁጭ ብሏል ፡፡የደርጉ አባል ሻለቃ አሊ ሙሳ ነው፡፡ሻሸመኔ ውስጥ ብዙዎቹ የእሱን ስም ሲጠራ የሚደነግጡለት ሰው ነው፡፡አወቶብሶቹ ገና ከተማው ዳርቻ እንደተጠጉ በክላክስ ቀውጢ አደረጉት፡፡የጡሩምባው ጩኸት ሳያልቅ ከሁሉም መኪኖች ውስጥ ጥይት እየተተኮሰ አካባቢውን ጦር ሜዳ አስመሰሉት፡ ፡ የሚተኮሰው ወደ ሰማይ ቢሆንም የከተማው ሰው በድንጋጤ መግቢያ ጠፋው፡፡ ሁኔታውን እስኪያውቅ በየስርቻው ይደበቅ ጀመር፡፡ ምን ጉድ መጣ!!

መኪና ወስጥ ያሉት ወደ ዘማች ወታደሮች ናቸው፡፡እነዚህ የገበሬ ሚሊሺያዎች የሲያድ ባሬን ወረራ ለመመከት በተደረገው የመንግስት ጥሪ የተመለመሉ ናቸው፡፡የሚሄዱት ወደ ማሰልጠኛ ጣቢያ ነው፡፡ማደሪያቸውን ሻሸመኔ አድርገው በነጋታው ወደ ታጠቅ

ጦር ሰፈር ይሄዳሉ።የአውቶብሶቹ ቁጥር ከመቶ ይበልጣል ።በዚያ ላይ የጭነት መኪኖችም ተጨምረዋል።ገና ከከተማው ዳርቻ በተኩስ እያደበላለቁ ሲገቡ አንድ ባለማዕረግ ወታደር አስቆማቸው።ሰውየው ኮሎኔል ሲሆን በወታደር ካምፕ የፓራኮማንዶ ወታደሮች አሰልጣኝና ሀላፊ ነው።‹‹ህዝቡን እያረበሻችሁ ስለሆነ ተኩስ አቁሙ ወደ ከተማውም አትግቡ›› አለ።ነገር ግን ሰውየው‹‹ምን አገባህ?››በሚል ተይዞ ታሰረ።መኪኖቹ የሻሸመኔን ዋና ዋናው መንገዶች በጥይት ተኩስ አጃቢነት በማቋረጥ የከተማው ሌላኛው ጫፍ ደረሱ። ቡልቻና ቀበሌ ሲደርሱ ታጥፈው ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ተመለሱ።

ሻለቃ አሊ ሙሳ ወደ ሻሸመኔ ከተማ ሲመጣ ከፊት አብሳሪ ላንድሮቨር ከተማ ውስጥ እየበረረች ትገባለች።በድምጽ ማጉያ ‹‹የፍየል ወጠጤ ›› የሚለውን ሙዚቃ አይለያትም።የከተማው ህዝብ ይሄን ሙዚቃ ሲሰማ ምን ማድረግ እንዳለበት ያውቃል።ዛሬ መኪናዋ ከፍየል ወጠጤ ሙዚቃ በኋላ በድምጽ ማጉያ መልዕክት እየተላለፈ ነበር ‹‹....ለሻሸመኔ ከተማ ነዋሪዎች በሙሉ!!!የእናት ሀገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበር የሚሄዱት ሚሊሺያዎች ዛሬ የእናንተ እንግዳ ስለሆኑ ለሰራዊቱ የምሽት ቀለብ ያላችሁን ምግብ እንድታቀርቡ ሻለቃ አሊ ሙሳ ያሳስባሉ››አለ።የተጠየቀውን ቶሎ ለማግኘት አሁን የተጠራው ስም በቂ ነበር።ተናጋሪው ቀጠለ።‹‹መኪኖች በየበራቹሁ ስለሚመጡ እንጀራም ሆነ ዳቦውን እንድታስረክቡ ይሁን ።ያልሰጠ የቤት ቁጥሩ ይመዘገባል››ብሎ ቀጠለ።ነገሩ ቀላል ነው ።እንጀራና ወጥ ያልሰጠ ስሙ ለሻለቃ አሊ ሙሳ ይተላለፋል።የከተማው ነዋሪ በቀረበው መኪና ላይ ምግብ ጫነ። ሌላው ሰው መኪናው ሲያመልጠው ሆነ ለመታየት ሚሊሺያዎቹ ወዳለበት ድረስ እየሄደ አስረከበ።መኪናው የተጫነውን ይዞ ለእራት ደረሰ። መኪናው ገልባጭ ስለሆነ መሬቱ ላይ ሸራ ተነጥፎ ተገለበጠና እየተሰፈረ ለሚሊሽያዎቹ ታደለ።ወደ ከተማ እንዳይገቡ የተከላከለው ኮሎኔል ሻለቃ አሊ ሙሳ ፊት ቀረበ።‹‹ለምንድነው መኪኖቹ ወደ ከተማ እንዳይገቡ ያገድከው?›› አለው

‹‹ህዝቡ እንዳይረበሽ ነው››

‹‹ስለህዝቡ ምን ታውቃለህ?››





‹‹ጸረ አብዮተኞች እንዳይተናኮሉ ነው››

‹‹እንዴት?››

‹‹ከተማው ውስጥ የመሸጉ የኢህአፓ አባላት አሉ››

‹‹ታዲያ ለምን አልያዛችኋቸውም?››

‹‹እያፈላለግናቸው ነው››

ሰውየው መልስ ቢሰጥም ከኩርኩምና ከዱላ አላመለጠም ። እንደውም ከፍተኛ ነገር ይደርስበት ነበር።የወታደሩ ፍላጎት

-- ይሄ ሁሉ ጥይት ለምን ይባክናል

--ህዝቡን ለምን ይረብሻሉ

-ማደሪያቸው እዚህ ከሆነ ለምን ወደ ከተማ ይገባሉ...የሚል ነበር ።ግን ሰሚ አላገኘም።......ኮሎኔሉን ርምጃ ሊወስዱበት አዘጋጁት። አሊን የተቃወመ የሚወስድበት ርምጃ ሞት ነበር።።ነገር ግን ከካምፕ የመጡ ፓራኮማንዶ ወታደሮች ኮሎኔሉ ትንሽ ጭረት ከተገኘበት ምላሹ የከፋ እንደሆን አስጠነቀቁ።የሻለቃ አሊ ጠባቂና ወታደሮች ነገሩ ስላሰጋቸው ኮሎኔሉን ለቀቁት።ይሄ ብቻ አይደለም ባስቸኳይ አሊና ወታደሮቹ ከተማውን ለቀው እንዲወጡ ፓራኮማንዶዎቹ ቀጭን ትዕዛዝ ሰጡ።ምሽቱን ወደ ነጌሌ አካባቢ የነበረ የሚሊተሪ ማቆያ ስፍራ ሄዱ።

ሚሊሺያዎቹ የሻሸመኔ ዋና ዋና መንገዶች አጨናንቀው ሲዞሩ ረጅም ሰዓት ነበር የፈጀባቸው።ከተማ ውስጥ ገብተው እስኪወጡ የመሳሪያው ተኩስ ያልተቋረጠ ነበር።የተኩሱ ያለማቋረጥ ከሌላ አቅጣጫ የተደረገውን ጥቃት የተመለከተ አልነበረም።ሁሉም ነገር በሚሊሺያዎቹ ተኩስ ተሸፍኖ ነበር።

ገበየሁ አስፈላጊ መረጃ የያዘውን ሰው እየጠበቀ ነው።ነገር ግን ጥላሁን ቡቶሎ አልደረሰም።ገበየሁ ከነበረበት ለምለም ሆቴል በ100 ሜትር ርቀት ላይ ጥላሁን በጥይት ተመትቶ ወድቆ ነበር።በአካባቢው የነበሩ ነዋሪዎች የሆኑ ሰዎች ተኩሰው እንደሮጡ ቢያዩም ስለጉዳዩ መናገር አልፈለጉም።(ይሄ የታወቀው ቆይቶ ነው) በጥላሁን ላይ ጥይት ሲተኮስ ድምጹ በሚሊሺያዎቹ የመሳሪያ ጩኸት ተውጧል። ጥላሁን እንደተመታ አብዮት ጥበቃዎቹ በፍጥነት ደረሱ።አንድ ሰው ጥላሁንን ሲታገለው አገኙት።ሲጨርሰው የተመደበ ሰው እንደሆነ

ደረሱበት፡ ገዳዩም እሱ እንደሆነ ስለታወቀ እየጠፈጠፉ ወደ ጣቢያ ይዘውት መጡ፡፡በከተማው ታዋቂ የሆነውን የፖለቲካ ሰው ገድሉ እንዲሁ በዋዛ ሊተውት አልፈለጉም፡፡ እስኪበቃቸው ቀጠቀጡት ፡፡ ከዱላው በኋላ ጥያቄ ተጀመረ፡፡‹‹ማነው የላከህ?››አሉት

(ዝም)

‹‹ሌሎቹ ጓደኞችህ የት አሉ?›››

(ዝም)

በገበየሁ የሚመራው የገራፊ ቡድን በደምብ ቶርች አድርገው እንዲያውጣጡት ሀላፊነት ተሰጣቸው፡፡ጥላሁን እነማን ሲገድሉት እንደፈለጉ እንዲነግረው ነበር ለምለም ሆቴል ገበየሁ የቀጠረው ፡፡ ነገር ግን እሱ ባይነግረውም አንዱን ገዳይ አግኝተውታል፡፡እሱን በመግረፍ ሌሎቹን ያገኟቸዋል፡፡ሌሊቱን ሁሉ ሲገርፉት አደሩ ፡፡ በነጋታው ሁለት ሰው አጋለጠ፡፡ እነዚህም ተያዙ ፡፡ነገር ግን አንድ የተምታታ ነገር ነበር፡፡አሁን የተያዙት የእዚህ ሰው ግብረ አበሮች ናቸው፡፡አንደኛው ሽማግሌ ነው ፡፡እነዚህ ሰዎች በፖሊስ ያላቸው ሪከርድ ሲታይ በሌብነት የሚታወቁ ናቸው፡፡ አሁን በናዝሬት መምህር የሆነው ብርሀኑ ግዛው በኢህአፓነት ተጠርጥሮ ተይዟል፡፡ የጥላሁን ገዳይ ተብዬ ተይዞ ሲመጣ ብርሀኑ እስር ቤት ነበር፡፡ ሰውየውን አይቶታል፡፡

ብርሀኑ ስለጥላሁን ግድያ እንዲህ ያስታውሳል ‹‹.....የጥላሁን ገዳይ ተብሎ አንድ ሰው ማታ ተይዞ መጣ ፡፡ሌሊቱን ሁሉ ደበደቡት፡፡ሌሎች የኢህአፓ ስኳዶችን እንዲያጋልጥ አሰቃዩት፡፡ ሰውዬው የኢህአፓ አባል አልነበረም፡፡ሌባ ነው፡፡ ጥላሁን ተመትቶ እንደወደቀ ሰው እንዳልደረሰለት ነው የሰማሁት፡፡ የሚሊሺያዎቹ ተኩስ ገዳዮቹ እንዳይታወቁ አድርጓል፡፡ጥላሁን እንደወደቀ ሰውየው የእጅ ሰዓቱን እየፈታና ኪሱን እየበረበረ ሳለ ነው የደረሱበት፡፡ጥላሁን ሰክሮ የወደቀ ስለመሰለው እቃ ለመስረቅ ትግል ያዘ፡፡ ሲይዙት ሌባ ነው ብለው አልገመቱም፡፡ ገዳይ እንደሆነ ነው ያወቁት፡፡ ለብዙ ግዜ ሲገርፉት ቆይተው በመጨረሻ ሌባ መሆኑ ስለተረጋገጠ ለቀቁት››ይላል፡፡





የጥላሁን ገዳዮቹ አልታወቁም፡፡ እዚህ ከተማ ስኳዶች እንዳሉ በመታወቁ የአጸፋ እርምጃ ለመውሰድ መነቃነቅ ጀመሩ፡፡የቀበሌ 10 አብዮት ጠባቂዎች ጓዳቸውና አለቃቸው በመገደሉ በጣም ነው ያንገበገባቸው፡፡ የገደሉት እነዚያ ሁለት ወጣቶች መሆናቸውን ጠርጥረዋል፡፡የዚያን ቀን በደምብ አሰሳ አላደረጉም እንጂ እዚያ ጀማይካ ሰፈር ሁለቱ ልጆች መሽገው እንደነበረ ያምናሉ፡፡አንድ ነገር ማድረግ አለባቸው፡፡ በቀል ሸተታቸው፡፡ወትሮም ቢሆን እነዚህን ጀማይካውያን አይወዷቸውም‹‹ንጉስ ናፋቂ››ስለሚሏቸው አብዮቱን ለመጣል እንደሚተባበሩ ያምናሉ፡፡ አብዮት ጠባቂዎቹ ጓዳቸው እዚህ በመሸጉ ገዳዮች እንደተመታ አምነዋል፡፡እናም እነርሱ እዚህ ሰፈር ጥቃት ሰንዝረው መበቀል ፈለጉ፡፡ቀን ቆረጡ፡፡ጥናት አደረጉ፡፡መሳሪያና ታጣቂ አዘጋጁ፡፡

## ምዕራፍ 12

# የፍየል ወጠጤ

ግቢ ውስጥ በሚገኘው ጠርዝ ላይ በተተከለው ድንጋይ አንድ ሰው ቁጭ ብሏል፡፡ሰውየው ብቻውን ነው የተቀመጠው፡፡በባህሪው ብቸኝነት የሚወድ አልነበረም፡ሁሌም ከሰው ጋር ተቀላቅሎ መጫወት የሚወድ ነው፡፡ ቁምነገርናቀልድ የሚያውቅ ሰው በመሆኑ ሁሉም ይቀርቡታል፡፡ዛሬ ግን ከሰዎችተገንጥሎ ጥግ ላይ ተቀምጧል፡፡ሰዎችን ጠልቶ አይደለም ከእነርሱ የራቀው፡፡ ለምን እንደተገነጠለ ምክንያቱን ቢጠየቅ መልስ የለውም፡፡ለምን እንደተከዘ ባያውቅም በቀጣዮቹ ጥቂት ደቂቃ ውስጥ ከዚህ ድንጋይ ላይ ተነስቶ ጓደኞቹን ይቀላቀላል፡፡ እዚህለብቻው ከሚሆን ከእነርሱ ጋር ሆኖ ተቀላቅሎ ቢጫወት እንደሚሻለው አምኗል፡፡

በአጭር ደቂቃ ውስጥ ከተቀመጠበት ይነሳል፡፡ለመነሳት እራሱን እያዘጋጀ ነው፡፡እዚህ ያመጣውን ጉዳይ ደግሞ ደጋግሞ ገምግሞ ጨርሷል፡፡ ጉዳዩ የማያልቅ ቢሆንም ላሁኑ ግን የገመገመው በቂ ነው፡፡እዚህ ከቆየ እንደ፞ገና ሌላ ግምገማ ውስጥ ገብቶ ከመጨናነቅ በግዜ ከዚህ መነሳት አለበት፡፡መነሳቱ ምንም ጥያቄ የለውም ፡፡እሱም ወስኖ የስከንዶች ግዜ ቀርተውታል፡፡የሰውነቱን ክብደት ተቆጣጥሮ ለመነሳት ተዘጋጀ፡፡ለመነሳት ብቻ ሳይሆን እነማን ጋር ሄዶ ማውራት እንዳለበት ወስኗል፡1…2….3 ቆጠረና ለመነሳት አኮበኮበ፡፡ ነገር ግን በዋናው የግቢው በር የገባውን ነገር ስለተመለከተ የዚህን መጨረሻ ካወቀ በኋላ ለመነሳት ወሰነ፡፡

እናም ሊነሳ ያኮበኮበው ሰውዬ እዛው ድንጋዩላይ ቁጭ ብሎ ቀረ፡፡ግን አልቆይም ብሎ ለራሱ ተናገረ፡፡በግቢው በር የገባውን ነገር እንደተመለከተው ስሜቱ ድፍርስ ሲል ተሰምቶታል ፡፡ግን እንዲህ አይነት ስሜት ያመጣበት ምን እንደሆን በውል አልገባውም ነበር፡፡ ስሜቱን ለማወቅ ሌላ ምርምራ ውስጥ መግባት አልፈለገም፡፡ይሄን





በዋናው በር የገባውን ነገር ማንነቱን ካረጋገጠ በኋላ ቶሎ ተነስቶ ይሄዳል፡፡ለማረጋገጥ ደግሞ ትንሽ ስከንድ ብቻ ነው የሚፈልገው፡፡ ማረጋገጥ የፈለገው ለሌላ ጉዳይ ሳይሆን እንዲሁ ለማወቅ ብቻ ነው፡፡ ምንም ይሁን ምን ተነስቶ ወደ ጓደኞቹ ጋር ሄዶ ከመቀላቀል አያግደውም፡፡በዋናው ግቢ በር ብቅ ያለው ነገር ገና ሙሉ ለሙሉ ተጠቃሎ አልገባም፡፡ግማሽ አካሉ ብቻ ነው የሚታየው፡፡ግማሽ አካሉን አይቶ ማንነቱን ለመገመት እንኳ ለማወቅ አልቻለም፡፡ግማሽ ጎኑ ነው የታየው፡፡የጠረጠረው ነገር ስለነበር ‹‹እሱ ነው አይደለም?››ብሎ ማወቅ ፈለገ፡፡

እንዴት አድርጎ ማረጋገጥ እንዳለበት ግራ ገባው፡፡ ተነስቶ ሄዶ ማጣራት ይችላል፡፡ነገር ግን አልፈለገም፡፡እንዲያውም ወደዛ ላለመመልከትና ነገሩንም ችላ ብሎ ማለፍ እንዳለበት ለራሱ ተናገረ፡፡ ግን ይሄንን አልቻለም፡፡ከትላንትና ጀምሮ ውስጡ የፍራቻ ስሜት አድሮበታል፡፡ዛሬ ደግሞ ከጠዋት ጀምሮ የሚሰማቸው ወሬዎች ደስ የሚል ባለመሆኑ ሁሉም ነገር ተምታቶበታል፡፡ጥፋተኛ እንዳልሆኑ የሚመስክርላቸው ሰዎች ወደ ባለስልጣኞቹ ልከዋል፡፡ነገር ግን እስካሁን ምንም ያገኙት መልስ የለም፡፡በተፈጠረው ድርጊት ባለስልጣኞችንና የደርግ ዋና ዋና ሰዎች ስለተናደዱ የሚከተለውን ነገር ህይወታቸውንእንደሚቀጥፍ አልጠፋውም፡፡ባለስልጣኞቹ ጋር የተላኩት ሰዎች‹‹እጃቸው እዚህነገር ውስጥ የለበትም››ብለው ማሳመን ካልቻሉ አለቀላቸው፡፡

የተላኩት ሰዎች ቸር ወሬ ይዘው እንዲመጡ እየጸለዩ ነው፡፡ ችግር ባለመምጣታቸው ሰዎቹ እስካሁን መልሱን ይዘው እንደገጠማቸው ጥርጣሬ አላቸው፡፡ሁሉም በየራሱ ከዚህ የሞት አጥር ውስጥ የሚያወጣቸው ነገር እየፈለጉ ነው፡፡የተላኩት ሰዎች በመቆየታቸው ነገሩ እንዳልተሳካ ገምተዋል፡፡እዚህ ባይመጡ በቀብራቸው ላይ እንደሚገኙ ያምናሉ፡፡ ምናልባት የቀብራቸው ቦታ ስለማይታወቅ እዛው ባሉበት አርማቸውን እንደሚያወጡ ያገምታሉ፡፡ እንዲህ ድንጋዩ ላይ ተቀምጦ ለመነሳት እየተንደረደረ የነበረው ሰው እያሰበ እንዴት ከዚህ ማምለጥ እንዳለበት ጭምር እየቀመረ ነው፡፡ ሁሉ●ንም አውጥቶና አውርዶ ደምሮ ቀንሶ ሁሉም ዜሮ ሲሆንበት

እንዴት እዚህ ነገር ውስጥ እንደገባና ችግሩ የት ጋር እንደተፈጠረ እያሰላሰለ ነው፡፡ ሁሉንም ከፍ አድርጎም ዘቅዝቆም ቢገመግመው ምንም ጠብ የሚል ነገር አላገኘበትም፡፡እናም ለመሞት መዘጋጀት እንዳለበት አመነ፡፡ግን እንዲሁ መሞት የለብኝም አለ፡፡

የተላኩት ሰዎችእነርሱ ባይመጡ እንኳን መልእክት መስደድ እንዳለባቸው ተነጋግረው በዚያው የውሃ ሽታ ሆኑ፡፡የተላኩት ሰዎች ስላልተሳካላቸው ቀጣዩ እርምጃ ምን እንደሚሆን እያሰላሰለ ባለበት ግዜ ነበርበዋናው የግቢ በር ግማሽ አካላቱታይቶ የነበረው ነገር ሙሉ ለሙሉ ወደ ውስጥ ሰተት ብሎ የገባው፡፡እያሰበና እየተጨናነቀ ባለው ጉዳይ ላይ እያወጣ እያወረደ ባለበት ግዜ ሰተት ብሎ የገባውን ነገር ሲያይ ደነገጠ፡፡፡መደንገጥ ብቻ ሳይሆን ደነበረ፡፡መደንበር ብቻ ሳይሆን በረገገ፡፡ከጠዋት ጀምሮ ምንይወሰንብን ይሆን ብሎሲሰጋና ሲጨነቅ ምላሽ ያገኝስለመሰለው ከነገሮች ጋር ስለተጋጠመ ‹‹አለቀልን››ብሎ ድንገት ፈንጠር ብሎ ተነሳና ወደ ጓደኞቹ ጋር ሄደ፡፡እየሄደም‹‹ይሄ ነገር ሆን ተብሎ ነው ወይስ ድንገት የተፈጠረ››ብሎ ለራሱ ተናገረ፡፡ ከቅድሙ ጀምሮ በበሩ ግማሽ ሰውነቱን ያስገባው ነገር ከኋላ ብቻ እየታየው ስለነበር ይሄ ነገር በግ ነው ወይስ..... እያለ ባለበት ግዜ ነበር ፍየሏሙሉ ለሙሉ ሰውነቷን አስገብታ ወደ ግቢው ሰተተ ብላ የገባችው፡፡፡

ፍየሏ በራሷ ተነሳሽነት ከመጣች ችግር የለውም፡፡ መልእክት ለማስተላለፍ ከተላከች ግን አለቀላቸው፡፡ሰውዬው ልክ እንደተመለከታት ከግቢ ለማስወጣት ፈልጎ ነበር፡፡ ግን ሰውነቱ ብቻ ሳይሆን አንደበቱም ነው የተያያዘበት፡፡ከጠዋት ጀምሮ ሲፈራ ሲቸር የነበረው ጉዳይ አሁንም አብሮት ነው ያለው ፡፡ ሁሉም ነገር ተመሰቃቅሏል፡፡ ፍየሏን ካዬ ግዜ ጀምሮ ደግሞ በአእምሮው ውስጥ ያለውን ነገር ብቻመተርጎም ጀመረ፡፡ሰሞኑን በሬድዮ ከሞት በኋላ የሚሰጠውን መግለጫ አስታወሰ፡፡

የፍየል ወጠጤ
ትክሻው ያበጠ
ልቡ ያበጠበት
እንዋጋ ብሎ ከነብር ላከበት





የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች
ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች

ደርግ ርምጃ የወሰደባቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር በአስገምጋሚ ድምጹ የሚያነበው አሰፋ ይርጉ ነው፡፡የእሱን ድምጽ ሁሉም ይፈሩታል፡፡ ደርግ ደግሞ ይመካበታል፡፡አሰፋ መግለጫውን ካነበበ በኋላ የፍቐል ወጠጤ የሚለው ዘፈን ይከተላል፡፡አሁን ፍየሏ በራሷ ፍቃድ ወደ ግቢው አልገባችም፡፡የደርግ ሰዎች እዚህ ግቢ ባሉት ሰዎች ላይ የወሰኑትን ነገር መልእክት እንድታስተላልፍ የተላከች ናት ብሎ አመነ፡፡ከዚህ ውጭ ምንም ነገር የለም፡፡ለመንግስት ባለስልጣናት እኛ እዚህ ነገር ውስጥ የለንበትም ብለው የላኩት ነገር እንዳልተሳካ እዚህ ግቢ በመጣችውመልእክተኛ ተ●ረጋግጧል፡፡ከተቀመጠበት ቢነሳም ሰማይ ምድሩ ዞሮበታል፡፡እዛው ባለበት አሰፋ ይርጉን አስታወሰ፡፡አሰፋን ከዚህ በፊት ሴንስ ላይ ተገናኝተው ብዙ ነገር ተጫውተዋል፡፡በጣም ስለተቀራረቡ ጥሩ ሰው እንደሆነገብቶታል፡፡ደርግ ስልጣን ላይ ከወጣ ወዲህ አሰፋም ሆነ ይሄ ሰው ላለመገናኘት መንገድ እስከማሳበር የደረሱበት ግዜ እንዳለ አስታወሰ፡አንድ ቀን ሁለቱም አሳቻ ቦታ ተገናኙ፡፡ ሰውየው አሰፋን አይቶ ምን መናገር እንዳለበት እንኳን ጠፋው፡፡ ቀልደኛ ቢሆንም አሁን ከእሱ ጋር መቀለድ እንደሌለበት ተሰማው፡፡ ግን እንዳው ፊት ለፊት ስለተገናኙ

‹‹ሰላም ነህ››አለው
‹‹ሰላም ነው››
‹‹ስራ እንዴት ነው››(በውስጡ ሰው እያስጨረስክ አለው)
‹‹ጥሩ ነው››
‹‹ጠፋህ እኮ››(በል አሁን ጥፋልኝ ከፊቴ)
‹‹አለሁ የት እጠፋለሁ››
‹‹እዛ ሬድዮ ነህ አይደል?››(በየቀኑ በዚህ ድምጽህ ሰው እያስደነገጥክ)
‹‹አዎ እዛው ነኝ››

የሚያወሩት ነገር ቶሎ ለመለያየት መንገድ እስኪከፍት እየጠበቁ ነበር፡፡አሰፋ ይርጉ ድምጹ ለየት ያለና ሞት የሚጠራ

ይመስላል፡፡ደርግ ርምጃ የወሰደባቸውን ሰዎችና ቀጣይ ለአብዮቱ ስጋት የሆኑትን የሚያስፈራራው በእርሱ ድምጽ ነው፡፡ምሽት ላይ መግለጫ ካለ አሰፋ ነው የሚያቀርበው ፡፡ድምጹ አስገማጋሚ ነው ፡፡ሰዎች አደጋ እንዳያደርሱበት በሚል በቴሺም መግለጫ ሲያነብ ምስሉ እንዳይታይ ይደረጋል፡፡ብዙዎቹ ደርግ ለሚፈልገው መግለጫ ተስማሚ ሰው እንዳገኙ ይመሰክራሉ፡፡ህዳር 14 ቀን 1967 ለመጀመርያ ግዜ ደርግ በንጉሱ ሚኒስትሮች ላይ የሞት እርምጃ ወሰደ፡፡ መግለጫውን አዘጋጅተው ወደ ሬድዮ ጣቢያ ሲሄዱ ዋናዎቹ መግለጫና ዜና አንባቢዎች ለግዜው አልነበሩም፡፡ እዛው በቅርብ ቢሆኑም እነርሱንከመጥራት ይልቅ የቅርብ ሰራተኞች‹‹ አሰፋም ቢሆን ጥሩ ድምጽ አለው››በሚል ስለተነገራቸው መግለጫውን አነበበ፡፡ ሰዎቹ ለራሳቸው አዳመጡና ተስማሙበት፡፡

የተገደሉትን ሚኒስትሮች በአሰፋ ድምጽ ሲሰማ ህዝቡ ተገረመ፡፡ደግሞም ደነገጠ፡፡ ከዚያ ወዲህ አብዮታዊ እርምጃ የተወሰደባቸውን ሰዎች መግለጫ የሚያነበው እርሱ ሆነ፡፡ከአሰፋ መግለጫ ምንም የሚተርፍ ነገር የለም፡፡በዚህ አስገምጋሚ ድምጹ ሞትን ብቻ ነው የሚጠራው፡፡አንዳንድ እናቶች የተበሳጩበትን ሰው ‹‹እንዳው ምንም አልልህም አሰፋ ይርጉ ስምህን ይጥራው›› በሚል እስከመራገም ይደርሱ ነበር፡፡ አሁን እዚህ ግቢ ያለው ሰው አሰፋ ይርጉን አስታወሰ፡፡ እንደገናም ፍየሏን አተኩሮ ተመለከተና ዛሬ ምሽት ‹‹አብዮታችን መቼም ቢሆን አይቀለበስም ፡፡እኛን ሲበጠብጡን ከአድሃርያን ጋር ተሰልፈው የነበሩት….›› ከእርሱ በኋላ ጥፋተኞቹ መንግስት ለመገለበጥ ሙከራ በማድረጋቸው ርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡

1ኛ አውላቸው ደጀኔ

2ኛ ደበበ እሸቱ

3ኛ ወጋየሁ ንጋቱ

4ኛቀለመወርቅ ደበበ……..

አብዮታዊ ርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡ቀብራቸው የተፈጸመ በመሆኑ ማንን ቤተሰብ ወይም ዘመድ ነኝ ባይ መጠየቅ አይችልም፡፡ በቃ ይሄው ነው፡፡ከአሰፋ መግለጫ በኋላ የፍየል ወጠጤ ዘፈን ይቀጥላል፡፡እንዲህ እንደሚሆን ስላወቀ ሰውየው ደነገጠ፡፡በቃ አለቀልን





አለ፡፡በግቢ ውስጥ የተሰበሰቡት ሰዎች ረጋ ያለና ቁም ነገር ያለው ጨዋታ እያወሩ ነው፡፡ይሄ ሰው ግን ወደ ግቢው ሰተት ብላ በገባችው ፍየል የተነሳ ይሄ ነገር ሊፈጠር ይችላል ብሎ በውስጡ ያለውን ነገር እያሰላሰለ ተደናብሯል፡፡ፍየሏ አስደንግጣዋለች ፡ከአሰፋ ይርጉ መግለጫ በኋላ ነበር የምትመጣው ፡፡አሁን ለእነርሱ ቀድማ መጥታለች፡፡ከአሰፋ መግለጫ በኋላ መደምደሚያው ዘፈን ማንም ሰው በአእምሮ የታተመ በመሆኑ የትም ቦታ ይሄ ዘፈን አይከፈትም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ዘፈኑ ሲሰማ ሰው ሁሉ ይብረግጋልና፡፡ ዘፈኑ የይርጋ ዱባለ ነው፡፡ ከወር በፊት ሰርግ ቤት አግኝቶት ነበር፡፡ ሰውየውን ሲመለከተው ደነገጠና ወደ እሱ ጋር ጠጋ ብሎ በቀስታ

‹‹ይርጋ!››አለው

‹‹አቤት ››

‹‹ሰው አለቀ እኮ››

‹‹ምን አልክ!!!››

‹‹ፍየሏ››

‹‹የምን ፍየል?››

‹‹የፍየል ወጠጤ››

‹‹ሰው እኮ እየገላመጠ አስቸገረኝ››

‹‹ለምን?››

‹‹ለግድያው ማጀብያብዬ የዘፈንኩ እየመሰለው››

‹‹እና››

‹‹ለሰርግ ስራ እንኳን አይጠራኝም››

‹‹እንዴት››

‹‹ሰው አንተ መሆንህን ካወቀ ይሸሻል እያሉ…..››

‹‹ታዲያ ምን ተሻለ?››

‹‹እኔ እንጃ››

‹‹ሁሉንም ቤት በር እያንኳኳነው››

‹‹ምን ይደረግ››

‹‹ነገ ወደ እኛ ሊመጣ እኮ ይችላል››

‹‹ምን አልከኝ?››

‹‹ዘፈኑ እየከበደ ሄዷል››

‹‹እንግዲህ ምን ይደረግ››

‹‹እኔና አንተም ነገ በዚህች ዘፈን ልንሸኝ እንችላለን›› ማለቱ ነበር። አሁን ግን እርሱ ቀድሞ ለዚህች ዘፈን አጃቢ ሊሆን ነው። ዛሬ ማታ ያልቅልናል አለ።በርግጥ ይርጋ ዱባለ ለዚህ የአሰፋ ይርጉ መግለጫ ማጀቢያ ተብሎ አይደለም የዘፈነው።ግን ዘፈን ሲፈለግ ይሄ ተስማሚ ሆኖ በመገኘቱ ነው።ስተት ብላ የገባችው ፍየል ለምን እንደመጣች ሰውየው ገባው።ዛሬ ማታ ወስደው እንደሚገድሏቸው ገብቶታል።ሰውየው አውላቸው ደጀኔ ነው።አውላቸው ከተቀመጠበት ተነስቶ ስለፍየሏ ከመናገሩ በፊት እዚያ የተሰበሰቡት ጓደኞቹ አይተዋት ምንም በባይመስላቸውም ጆንበሬ በላይ ‹‹እረ ሰዎች ጉድ ሆንን›› አለ

‹‹ምንድነው?››

‹‹ፍየሏ››

‹‹እና ምን ይሁን››

‹‹አለቀልን እኮ››

‹‹ምን እያልክ ነው?››

‹‹ብቃ ጨረሱን››

‹‹ማን የሚጨርሰን?››

‹‹ምን መናገር ያስፈልገዋል የፍየል ወጠጤ ሊባልብን ነው››

ሁሉም ግራ ተጋቡ። አውላቸው ጓደኞቹን እየተቀላቀለ ባለበት ግዜ ወደ ጆንበሬ እየሄደ‹‹እኔ አሁን ከደቂቃ በፊት አንተ የተናገርከውን እያሰብኩ ነበር››አለው።ግን በቃሬዛማታ በእነዚህ ሁሉ አርቲስቶች ላይ ወታደራዊ መንግስት ግድያ እንደሚፈጽም አውቀው ተደናገጡ።ከጥቂት ቀናትበኋላ አንድ የደርግ አባል ወደ እስረኞቹ መጡና ሁሉንም አነጋገሩ።በመጨረሻም ‹‹ብቅርቡ ከዘመዶቻችሁ ጋር ትቀላቀላላችሁ››አለ። ሁሉም ደስ አላቸው።ጆምበሬ በላይና ከተማ መኮንን እየተነጋገሩ ነው‹‹ጥሩ ነው አይደል››አለ

‹‹ምኑ?››

‹‹ልንፈታ ነው እኮ››

‹‹ነው እንዴ››

‹‹አዎ አትሰማም እንዴ ያለውን››





‹‹ለመሆኑ የተናገረው ገብቶሃል?››

‹‹ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ልትቀላቀሉ ነው አለ››

‹‹ከየትኛው ቤተሰብ?››

‹‹ቤተሰብ ነዋ››

‹‹የት ካሉት ማለቴ ነው››

‹‹እቤት ካሉት ነዋ››

‹‹ሰውየው እንደርሱ አይደለም ያለው››

‹‹ምን እያልክ ነው?››

‹‹ደርግ ከመጣ ጀምሮ እየገደለ ነው››

‹‹እና››

‹‹ብቅርቡ ከቤተሰብ ትቀላቀላላችሁ ያለው ከሞቱት ዘመዶቻችን ጋር እንደሆነ ነው የገባኝ››

‹‹ተው እንጅ!!!››

‹‹ታያለህ››

‹‹ሊገሉን ነው ማለት ነው››

‹‹ፍየል ከላኩብን አይገባህም››

ነገሩ ወደ ሌሎች ሰዎች ተዛመተና አሁን ንግግሩ አስደስቷቸው እንደገና ሌላ ፍርሀት ለቀቀ። ለመሆኑ እነዚህን ሁሉ አርቲስቶች ሰብስቦ እስር ቤት ያስስገባቸው ነገር ምን ነበር? ነገሩ ሲመጀር እንዲህ ነበር-፡

ብሄራዊ ቲያትር ውስጥ በአንደኛ ክፍል የተደወለው ስልክ የሚያነሳው ሰው አልነበረም።ስልኩ ደጋግሞ ይጮሃል።ስልኩ አጠገብ የነበረው ሰውዬ አላነሳውም። በሶስተኛው እጀታውን ብድግ አደረገው። ትክለኛው ነገር ይሄ ነው።በሁተኛው ግዜ ቢነሳ ትክክለኛው ሰው ስላልሆነ ደዋዩ ዘግቶ ሳያናግረው ይሄዳል።አሁን ግን ትክክለኛው አነሳስ ነው።ደዋዩ በተዋከበ ሁኔታ ነው የሚያዋራው‹‹ማነህ አንተ?››አለ

‹‹ምን ፈለግህ?››

‹‹ማነህ አንተ ነው ያልኩት››

‹‹አንተ ራስህ ማነህ?››

ስልኩ ተዘጋ። የዘጋው ደዋዩ ሳይሆን ተቀባዩ ነው።ጥቂት ቆይቶ ደዋዩ እንደንደገና ስልኩን መታ ።ቢሮ ያለው ሰው መልሰ አነሳው‹‹ማነህ አንተ?››አለ

‹‹አንተ ስምህን ንገረን››

‹‹አብርሀም ነህ?››

‹‹አይደለሁም››

‹‹ታድያ ማነህ?››

‹‹የአብርሀም ወንድም ነኝ››

‹‹የእሱ ወንድም ሆነህ ነው የምታስለፋኝ››

‹‹ስላላወቅሁ ነው››

‹‹እቃውን አላክልኝም››

‹‹የቱን እቃ››

‹‹የተነጋገርነውን››

‹‹አ!!አስታወስኩት››

‹‹መቼ ነው የምታመጣልኝ››

‹‹አሁን ይላክልሃል››

‹‹ይቆያል?››

‹‹አይቆይም››

‹‹ስንት ሰአት››

‹‹በ30 ደቂቃ ይደርሳል››

አብርሀም የሚባል ሰው እዛ ክፍል አልነበረም።ወንድምም የለውም።የሚላክ እቃም የለም።ስልክ ደዋዩ ሰው በቅርብ ወደሚገኘው ማዘጋጃ ሜዳ ሄደ። በሜዳው ላይ ግጥሚያ እየተደረገ ነው።ጨዋታው በገንዘብ የሚደረግ ውርርድ ነው።ስልክ ደዋዩ ሰውየ ከሜዳው ጠርዝ ወደቆመው አሰልጣኝ ተጠግቶ‹‹ያንተ ቡድን ዛሬ ጥሩ ይመስላል››አለው

‹‹አዎ ደህና ናቸው››

‹‹እስካሁን ግብ አላገቡም››

‹‹ሙከራ እንጅ ግብ አልተገኘም››

‹‹አይዞህ ያገባሉ››

‹‹እንደዛ ነው ግን..››





‹‹ግን ምን?››

‹‹እቃው ደረሰ እንዴ››

‹‹አልመጣም››

‹‹እንዴት››

‹‹በርግጥ ይመጣል››

‹‹ይቆያል?››

‹‹ትንሽ››

‹‹ትንሽ ሲባል ስንት ነው››

‹‹30 ደቂቃ››

‹‹ርግጠኛ ነህ››

‹‹አዎ የአብርሀም ወንድም እንደዛ ነው ያለኝ››

‹‹እቃው በመኪና ነው የሚመጣው››

‹‹አይደለም››

‹‹እና››

‹‹በእግር ነው››

‹‹እቃውን ለመቀበል የት እንጠብቃቸው››

‹‹እዚሁ ይመጣሉ››

‹‹የት?››

‹‹ማዘጋጃ››

አሰልጣኙ በረጅሙ አፏጨ። የቡድኑ አምበል ወደመስመሩ ተጠጋና ‹‹ኮች ፈልግከኝ እንዴ?››አለው

‹‹ግብ አግቡ እንጂ››

‹‹እየታገልን ነው››

‹‹እነዚህ ላይ ማግባት ያቅታችሁ እንዴ!!!››

‹‹እናገባለን››

‹‹በ30 ደቂቃ ውስጥ ግብ ማስቆጠር አለባችሁ››

‹‹እስከዛ እንቆይም እናገባለን››

አሰልጣኙ የነገረውን አምበሉ እየተዘዋወረ ለተጨዋቾቹ አስረዳቸው።በ30 ደቂቃ ውስጥ ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ተደረገ።ብሄራዊ ቲያትር የነበሩት ተዋናዮች ስልፍ

ለመውጣት እየተዘጋጁ ነበር።ስልፉ መብታችን ይከበር የሚልና አቶ ጸጋዬ ከሀሳፊነትም እንዲነሳ ጭምር የሚጠይቅ ነው።እውላቸው ያጁ ትከሻው ላይ ቀንበር ተደርጎ ስልፉ ተጀመረ። ደበበ እሸቱ ከብሄራዊ ቲያትር ለቆ መጽሄት እዘጋጅ ቢሆንም ሙያው ስለሆነ በስልፉ ላይ ተሳተፈ።ቲያትር ቤት ውስጥ የነበሩት የኢህአፓ አባላትም መረጃ አስተላላፊ ሆኑ።ጥያቄው የሙያ መብት በመሆኑ ማዘጋጃና ሀገር ፍቅር ቲያትር ቤቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ ስልፈኛውመጀርያ ወደማዘጋጃ ቀጥሎ ወደሀገር ፍቅር ሄደ።ሀገር ፍቅር ብዙዎቹ ባይሳተፉም ቀለመወርወቅ ደበበ እነርሱ ጋር ገባ።

ወደ ብሄራዊ ቲያትር ስልክ የደወለውና የአብርሀም ወንድም ነኝ ብሎ ስልኩን የተቀበለው የኢህአፓ አባላት ናቸው።እቃው የተባለው ስልፈኞቹን ነው።በ30 ደቂቃ ይደርሳል ያሉት ከብሄራዊ ቲያትር የተነሱት አርቲስቶች ወደ ማዘጋጃ ቲያትር ቤት የሚደርሱበትን ጊዜ ለመንገር ነው።ማዘጋጃ ሜዳ የሚጫወቱት ወጣቶችና አሰልጣኙ የኢህአፓ አባላት ናቸው።በ30 ደቂቃ ግብ አግቡ ያላቸው ሰዎቹ እዚህ የሚደርሱበትን ለመጠቆምና እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው።ስልፈኞቹ እንደደረሱ ጨዋታው እንዲበጠበጥ አድርገው አቋረጡ።ማቋረጥ ብቻ ሳይሆን ቶሎ ብለው ሌሎችን አሳትፈው ከሰልፈኞቹ ኋላ ተሰብሰው እየሄዱ ነው።ሰልፈኞቹ የሀገር ፍቅር ሰዎችን እናግረው ወደታች ወረድ ብለው በራስ መኮንን ድልድይ አጥፍ ብለው ወደ አራት ኪሎ መሄድ ጀመሩ።አራት ኪሎ ብዙ ሰው የሚሰበሰብበትና የመንግስት መቀመጫ ስፍራ በመሆኑ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ወደፊት መራመድ ጀመሩ፡ታዋቂ ሰዎች በመሆናቸው ወጣቶች እየተከሏቸው ነበር። ማዘጋጃ ሜዳ የነበሩት ወጣቶች በአሰልጣኙ መሪነት ከአርቲስቶቹ ጀርባ ተሰልፈው ጥያቄያቸውን እያስተጋቡ ነበር።አርቲስቶቹ የሚመለከቱት ወደፊት እንጅ ወደ ኋላ አልነበረም።ከኋላ የእግር ኳስ ቡድኑ ኢህአፓዎች የሚያስደነግጥና ከአርቲስቶቹ እውቅና ውጭ የሆነ መፈክር ይዘው እየተሳተፉ ነበር።ይሄ መፈክር ወዲያውኑ ለደርግ ሰዎች ደረሰ። በፍጥነት ወታደሮች ጅፕ በተጠመደበት መኪኖች እየተንጋጉ መጡ። አርቲስቶቹ ደነገጡ።ልክ ቱሪስት ሆቴል ጋር እየደረሱ ሳለ መጥተው





የሩምታ ተኩስ አርከፈከፉባቸው ።ወዲያውኑ ቀይታና ለቅሶ ሆነ። አርቲስቶቹ ደንግጠው እየሮጡ ግማሹ በቅርብ በሚገኝ ምግብ ቤት ገብቶ አስተናጋጅ ሆኑ።ሌሎቹ አካው ባለ መስርያ ቤቶች እየሮጡ ገብተው ታይፒ ጸሀፊ፣የጠቅላላ አገልግሎት ሰራተኛ...ብቻ ሁሉም ለመደበቅ ተፍጨረጨረ ነገር ግን ደርግ ካሉበት ለቀመና ወደ እስር ቤት ከተታቸው።ማሰር ብቻ ሳይሆን በከባዱ ዛተባቸው።ፍየሏ ወደታሰሩበት የገባችው በዚህ ጊዜ ነበር።በእርግጥ እነርሱ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ነው ሰልፍ የወጡት። ግን ኢህአፓ ሰልፉ ላይ ስለተደባለቀች የያዙት መፈክር አርቲስቶች ከፍተኛ የደርግ ተቃዋሚና ከስልጣን እንዲለቅ አስመሰለባቸው።




ደበበ የብሄራዊ ቲያትር ባልደረባ ነበር። አሁን ግን አይደለም። ቲያትር ቤቱን ለቆ በሌላ ስራ ተሰማርቷል።የሀገሪቱ ፖለቲካ ከፍ ብሎ ሄዷል።ሁሉም ሰው የሀገሪቱን መጻኢ እድል ለመወሰን በየፊናው

ይሮጣል፡፡ሚዲያ ሁሉም ነገር ነበር፡፡ደበበ ቁም ነገር የተባለ መጽሄት አሳታሚና አዘጋጅ ነው፡፡መጽሄቱ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅ በመሆኑ እዚህ ስራ ላይ ተፍ ተፍ እያለ ነው፡፡ከቲያትር ስራው ርቋል፡፡ዛሬ ግን በቲያትር ቤቱ ተገኝቷል፡፡የቲያትር ቤቱ ቁልፍ ተዋንያን ሳይቀሩ ሰልፍ ወጥተዋል ፡፡ደበበም እዚህ ሰልፍ ላይ ተገኝቷል፡፡ግዜው ደርግ እግሩ መሬት ቆንጥጦ ያልረገጠበትና መያገ መጨበጫ የጠፋበት ወቅት ነበር፡፡ኪነጥበብ ደርግን እየሸነቆጠና ከህዝብ እያራቀው ባለበት ግዜ ሰልፍ ሲወጡ የበለጠ ግራ ተጋባ፡፡የብሄራዊ ቲያትር ሙያተኞች መብታቸውን ለማስከበር ቢወጡም ደርግ እንዲህ አላሰበም፡፡ከጀርባቸው የሆነ ነገር ይዘዋል የሚል ግምት ነበረው ፡፡በ■ርጥም ከጀርባቸው ያለው ነገር ሲፈነዳ ደርግ የባሰ አስደነበረው እና ተኮሱ፡፡

ደበበ አሁን ጋዜጠኛ ነው፡፡ መጽሄት ያዘጋጃል ከብሄራዊ ትያትርና ከሙያው ርቋል፡፡ ይሄ የቲያትር ቤት ሙያተኞች ሰልፍ ነው፡፡ የደበበ እዚህ መገኘት ደርግን ጥርጣሬ ላይ መጣሉ አልቀረም፡፡ ለእኛ ጥሩ አመለካከት የለውም የሚል አቋም ያላቸው ይመስላል፡፡

## እንደገና ወደ ኋላ

ከየካቲት 66 ጀምሮ የተቀጣጠለውና ተቀጣጥሎም የፈነዳው፤ ፈንድቶም አገሩን ያተራመሰው አብዮት ከጎዳና ላይ ግርግር አልፎ የዘውዱን ስልጣን እየወዘወዘው ነው፡፡አሁን ስርአቱን ለመጣል ወደ እርምጃ መገባት እንዳለበት ሁሉም አምኗል፡፡አራተኛ ክፍለጦር የተቋቋመው ደርግ ማዘዣውን አራተኛ ክፍለጦር ግቢ አድርጎ የንጉሱን ባለስልጣኞች ቀስ በቀስ እያሰሩ ነው፡፡ማሰር ብቻ ሳይሆን ንጉሱ ዙርያ ያለውን አጥር እያፈረሱ ነው፡፡በመጨረሻ ወደ ንጉሱ እንደሚመጡ ብዙዎቹ ገምተዋል፡፡

ወታደሮቹ አንድ ሁለት ባለስልጣን ካሰሩ በኋላ ንጉሱ ጋር ተገኝተው ለእሳቸውና ለዘውዱ ታማኝ መሆናቸውን በመግለጽ እጅ ነስተው ይወጣሉ፡፡እንዲህ እያሉ በዙርያቸው ያሉትን ቁልፍ ባለስልጣን ወደ እስር ቤት ከተቱ፡፡ንጉሱን ከስልጣን ለማውረድ ግን እንዲህ የሚሞክር ሆኖ አልተገኘም፡፡እንደሚኒስትሮቹ ወስደው





ለማሰር የሚቻል አይደለም፡፡ንጉሱን ከስልጣን ለማውረድ ወይም ለማሰር የህዝቡን ድጋፍ ማግኘት አለባቸው፡፡የወሎ ድርቅ በህዝቡ ዘንድ ትልቅ ቁጭት የፈጠረ ነበር፡፡በውጭ ጋዜጠኞች የተቀረጸው የወሎ ድርቅ ፊልም ህዝቡን እንዴት ሊቆሰቁስ እንደሚችል የደርግ አባላት ፊልሙን እንዲመለከት ተደረገ፡፡ ሁሉም በሁኔታው አለቀሱ፡፡ ወታደር አያለቅስም፡፡ይሄ ፊልም ወታደር ካስለቀሰ ህዝቡ ቢመለከት ደግሞ እንዴት እንደሚንጫጫ ቁልጭ ብሎ ታያቸው፡፡በቃ ንጉሱን ለማወረድ ትልቅ መሳርያ ተገኘ፡፡

መስከረም 1 ቀን ዘመን መለወጫ ነው፡፡በዚሁ ቀን ደስታው፤ ፌሽታውና ፌንጠዝያው የተለመደ ነው፡፡ደርግ ይሄን የድርቁን ፊልም በቴሌቪዥን ለህዝቡ አሳየ፡፡ ጥላሁን ገሰሰ «ዋይ ዋይ» የሚለው ዘፈን ሲጨምርበት ህዝቡ እያነባና እየተንሰቀሰቀ ተመለከተው፡፡ንጉሱና ባለስልጣኖቻቸው ለፍርድ መቅረብ አለባቸው አለ፡፡በነጋታው በትኩሱ ደርግ ንጉሱን ለማውረድ ወደ ቤተመንግስት ሄዱ፡፡ሄዱ ብቻ ሳይሆን ነጎዱ፡፡የክብር ዘበኛ፤የፖሊስ፤የጦር ሰራዊት የብሄራዊ ጦርና የአየር ሀይል አባላት ከሁሉም ተውጣጥተው ቁጥራቸው 11 የሚሆኑ ሰዎች ወደ ቤተመንግስት ገቡ፡፡ንጉሱን ከስልጣን ለማውረድ የታጠቁ ወታደሮች በብዛት ይዞ መምጣት በቂ አይደለም፡፡ እንዳውም አስፈላጊም አልነበረም፡፡

እዚህ ግቢ ከጦር መሳርያ በበለጠ አስፈላጊው ነገር ሚዲያ ነው፡፡ የቴሌቪዥን ጋዜጠኞች መጥተዋል፡፡ቴሌቪዥን ብዙ ሰው ቤት የለም፡፡ ደግሞም ቴሌቪዥን ሀብታም ቤት ነው ያለው ፡፡ሀብታሞቹ ከደርግ በተቃራኒ የቆሙ ናቸው፡፡ሁሉም ቦታ የሚደርሰውና አብዮቱን ለማቀጣጠል የሚጠቀሙት ሬድዮ በመሆኑ የሬድዮ ጋዜጠኞች እየተጠበቁ ነው፡፡ እነርሱ ሲመጡ ነው ለንጉሱ ውሳኔያቸውን የሚያሳውቁት፡፡ግን የሬድዮ ጋዜጠኞቹ አሁንም አልመጡም ፡፡ወታደሮቹ አልደረሱም፡፡ እንደገናም አሁንም አልመጡም፡፡ ይሄን ዜና ለህዝቡ ተቻኩለዋል፡፡ ገና ትልቅ ስራ ይጠብቃቸዋል፡፡ግን ይሄን ወሬ አድርሰው የሚመጣውን ምላሽ ይጠብቃሉ፡፡ህዝቡ መረጃ ስለሌለው የሚያደርስላቸው ሬድዮ ግን በግቢው የለም፡፡

አንድ ነገር ቤተመንግስት አካባቢ ይፈጠራል ብሎ ዙርያውን ከቧል። መከበብ ብቻ ሳይሆን ተኩልኩሎ እያወራ ነው።ግን ምንም መረጃ የለውም ።ወታደሮች ወደ ውስጥ መግባታቸውን አውቀዋል ግን ንጉሱን ከስልጣን ለማወረድ ይወስኑ አይወስኑ ህዝቡ አላወቀም። ከዚህ በፊት ንጉሱ ጋር ገብተው ለዘውዱ ታማኝ ነን ብለው እንደሚወጡት አይነት ነው የመሰላቸው።ወታደሮቹ ግን ቆርጠዋል ። ያሰቡትን ነገር ለህዝቡ ለማሳወቅ ወሬውን ለህዝብ የሚያደርስ ሬድዮ ይፈልጋሉ። ከአጥር ውጭ ከህዝቡ ጋር ተቀላቅሎ እየተዘዋወረ የነበረውን አንድ ሰው ወታደሩ አየው። ወደ እርሱ መጣና ‹‹አንተ!!!›› አለው

‹‹አቤት››

‹‹ምን ታደርጋለህ እዚህ››

‹‹ዝም ብየ ነው››

‹‹አንተን አይደል እንዴ የምንጠብቀው››

‹‹እኔ ?››

‹‹አዎ››

‹‹ማን ፈለገኝ››

‹‹ስንት ቦታ…››

‹‹አልገባኝም››

‹‹በል ና ግባ››

‹‹ወዴት? ››

‹‹ወደቤተመንግስት››

ደበበ እሸቱ የሬድዮ ጋዜጠኛ ነው።የማታውን ፊልም ካየ በኋላ አንድ ነገር ይከሰታል ብሎ ስለጠበቀ ወሬ ፍለጋ ወደ ቤተመንግስት ሄደ። ህዝቡ ግምቱን እያስቀመጠ ያወራል።እሱም የሚሉትን ያዳምጣል። እንደገና እየተዘዋወረ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላ ይሄዳል ። ምናልባት አንድ ወሳኝ መረጃ ከተገኘ ብሎ ከቢሮ ሬድዮ መቅረጫ ይዞ ነው የወጣው ።አንድ ነገር ከተከሰተ ለክስተቱ ዜና ይዞ ለመመለስ ነው።ድንገት አንድ ወታደር አይቶት‹‹አንተን አይደል እንዴ የምንጠብቀው›› በሚል ወደ ግቢው ይዞት ገባ።ወደ ግቢው ብቻ ሳይሆን ንጉሱ ወደተቀመጡበት ሳሎን ይዞት አመራ።አሁን እየያ





ያለው ነገር ያላሰበው ነበር። ወታደሮቹና ንጉሱ ተፋጠዋል። አንድ ነገር እንዳለ ጠርጥሯል። በጋዜጠኝነቱ ለዚህ ጉዳይ ተጠርቶ አይደለም የመጣው። እናም አሁን ለተጠራበትና እያየው ላለው ነገር አልተዘጋጀም። ደግሞም እዚህ ለምን እንደመጣ አያውቅም።ምን ማድረግ እንዳለበት አልተዘጋጀም። እነዚህ በደርግ የተወከሉ ሰዎች ንጉሱ ፊት ቀርበዋል። እነዚህን 11 ሰዎች በቡድን መሪነት የሚመራው ከፖሊስ የተወከለው ሻለቃ ደበላ ዲንሳ ነው።በደርግ ሰዎች ተጽፎ የተሰጠውን ወሳኝ ወረቀት ለንጉሱ ድምጹን ከፍ አድርጎ ማንበብ ይጠበቅበታል።

ይህች እለት ለወታደሮቹ ወሳኝ ናት።ነገሩ የዋንጫ እንደሆነ ደበበ ተረድቷል።እዚህ ጋር አንድ ነገር ከተበላሸ ጉዳዩ ወዷልታሰበ አቅጣጫ መሄዱ አይቀሬ ነው።ይሄ ከሆነ ደግሞ ለወታደሮቹ ጥሩ አይደለም። ያሰቡትና ያቀዱት ነገር ገደል ሊገባ ይችላል።ህዝቡን በእጃቸው ማስገባታቸውን ገና አላረጋገጡም።የደርግ ዋናዎቹ ሰዎች አራተኛ ክፍለጦር ሆነው የእዚህን መጨረሻ ለማወቅ በጉጉት ላይ ናቸው።

አሁን እዚህ ቤተመንግስት የሚፈጠረውን ነገር ጋዜጠኞቹ ማየት አለባቸው። ወይም የለባቸውም።ዝግጅቱ ቢደረግም ንጉሱንና ወደተጠሩበት ቤት አልመጡም። ሌላ ክፍል ነበሩ።ወታደሮቹ ለብርቱ ጉዳይ ይፈልጓችኋል ስለተባለ ነው ወደ ጽፈት ቤታቸው የመጡት፡ ወንበራቸው ላይ እንደተቀመጡ ወታደሮቹን ተመለከቱ።አጠገባቸው ራስ እምሩ አሉ።ራስ እምሩ አብሮ አደግ ናቸው። ከ7 አመታቸው ጀምሮ ይተዋወቃሉ።እንዳውም የስጋ ዘመድ ናቸው።ልጅ እያሱን ከስልጣን በማውረዱ ላይ ዋነኛ ተዋናይ ናቸው።ራስ ተፈሪ እቴጌ መነንን ሲያገቡ አንደኛ ሚዜ ናቸው። በስልጣን ዘመናቸው ንጉሱ እንዲህ አይነት ነገር ገጥሟቸው ባያውቅም አሁንም አብረዋቸው ናቸው።ከዚያኛው ክፍል ራስ እምሩ ናቸው ጠርተዋቸው የመጡት።

አሁን የዋንጫው ጨዋታ ሊጀመር ነው።ምን ይፈጠራል በሚል ደበበና ሌሎች ጋዜጠኞች በጉጉት እየጠበቁ ነው።ደበላ ዲንሳ ወረቀት አወጣ።ወደ ጋዜጠኞቹ ተመለከተ።ከእዚህ ቤት የሚወጣው

ወሬ ወሳኝና አስፈላጊ ነው፡፡ይሄ ወሬ ከእነርሱ መስመር ውጪ እንዲስራጭ አልፈለጉም፡፡ በተዛባ መንገድ ወይም ከእነርሱ መስመር ውጪ ሄዶ ከተሰራጨ ህዝቡን ሊያወናብድባቸውና ድጋፉም ከእጃቸው ሊወጣ ይችላል፡፡በተለይ ወደ ህዝብ የገቡ ጋዜጠኞች ከሆኑ መስመር ሊያስቷቸው ይችላል፡፡ደበላ ዲንሳ ወረቀቱን ከማንበቡ በፊት ወደ ደበበ ተመለከተ፡፡ደበበ ከጋዜጠኝነትም በላይ እንደሆነ ያውቃል፡፡ የኪነጥበብ ባለሙያ በመሆኑ ተደራሽነቱ ብዙ ነው፡፡እናም እዚህ ያለውን ወሬ ሲያሰራጭ ወታደሮቹን የሚነካ ከሆነ አስቸጋሪ ነው፡፡

እነዚህ ሰዎች ምን አስበው እንደመጡ ደበበ አያውቅም፡፡ እነርሱም በግልጽ አልተናገሩም ፡፡ግን ለሚሆነው ነገር ስጋት አላቸው፡ ፡ወታደሮቹ ደበበ አይነውሃውን አዩት፡፡የወደዱት አይመስልም፡፡ ደግሞም ጠርጥረውታል፡፡ እናም ይሄን ነገር መስመር ማስያዝ አለባቸው፡፡ንግግር ከመጀመሩ በፊት አደጋ ያመጣል ያሉትን ጋዜጠኛ ማነጋገር እንዳለባቸው አመኑ፡፡ወረቀት አንባቢውና ቡድን መሪው ደበላ ዲንሳ‹‹ደበበ!!››አለ

‹‹አቤት››

‹‹ና አንድ ግዜ››

‹‹እኔ››

‹‹አዎ ››

ከክፍሉ ተያይዘው ወጡ፡፡ደበላ መሳርያቸውን እያስተካከሉ ነው፡ ፡አንድ ነገር ትንፍሽ ብትል ያልቅልሃል አይነት ነው፡፡ከጋዜጠኞቹ መሀል ተመርጦ ሲወጣ ስጋት እንዳደረባቸባው ያሳያል፡፡ደበላ ፖሊስ ናቸው፡፡ፖሊስነታቸው ደግሞ ተጠራጣሪነታቸውን ከፍ አድርጎታል፡፡ ይሄን ጋዜጠኛና ተዋናይ የሆነውን ሰው ደበላ ጠርጥረውታል፡፡ የተነሳንበትን አላማ ሊያስተን ይችላል በሚል ፈርተውታል፡፡ ከባድ ማስጠንቀቂያ መስጠት እንዳለባቸው አመኑ፡፡ ደበላ ደበበን ወደ ጥግ ወስዱትና አስረግጠው በድጋሚ‹‹ደበበ ››አሉ

‹‹አቤት››

‹‹አሁን ለንጉሱ ንግግር ላደርግ ነው››

‹‹እርስዎ››

‹‹አዎ››





‹‹እሺ››

‹‹ንግግሩ በጽሁፍ ይቀርባል››

‹‹ለንጉሱ››

‹‹አዎ››

‹‹ለእኛ ይሰጠናል?››

‹‹ምኑ?››

‹‹ጽሁፉ››

‹‹መጀመርያ አድምጠኝ››

‹‹እሺ››

‹‹ይዘን የመጣነውን ጉዳይ በወረቀት አነባለሁ››

‹‹ገባኝ››

‹‹እሽ ካሉ››

‹‹ማን? ››

‹‹ንጉሱ››

‹‹ምኑን ››

‹‹ስልጣን መልቀቁን››

‹‹ስልጣን እንዲለቁ ነው የምትጠይቁት?››

‹‹አዎ ፡፡ግን.....››

‹‹ግን ምን?››

‹‹እሳቸው እሽ ካሉ እዚህ ትሆናላችሁ››

‹‹በቃ ይሄ ነው››

‹‹አይደለም››

‹‹እና››

‹‹እምቢ ካሉ......››

‹‹ስልጣን አለቅም ካሉ ማለት ነው››

‹‹አዎ››

‹‹ምን ይደረጋል?››

‹‹ከክፍል ቶሎ ውጣ››

‹‹እሺ››

‹‹ገብቶሃል ያልኩህ››

‹‹በደምብ ገብቶኛል››

ደበላ ደበበን በደምብ አስጠንቅቀውታል፡፡ ንጉሱ እምቢ ካሉ አንድ ነገር ይደረጋል ማለት ነው፡፡ ይሄንን መመልከት የለበትም፡፡ ካየ በሆነ መንገድ ለህዝብ ካቀረበ አስቸጋሪ ነው፡፡ደበላ ዋናውን ሰው ካስጠነቀቁ በኋላ በወረቀት ተጽፎ የመጣውን የደርጉን ውሳኔና ትእዛዝ ለንጉሱ አነበቡ፡፡ ከንባቡ በኋላ ንጉሱና ወታደሮቹ ተፋጠጡ፡፡ ውጥረት ነገሰ፡፡ ደበላ ንግግር ጨርሰው ‹‹ግርማዊነትዎ ለእርሶ የተዘጋጀ ቦታ ስላለ ወደዚያ እንዲሄዱልን እንጠይቃለን…››አሉ፡፡ንጉሱ ‹‹…..ያላችሁትን ሰምተናል ፤ለኢትዮጵያ የሚበጅ ከሆነ ጥሩ ነው…›› አሉ፡፡ብለውም ዝም አሉ፡፡ቤቱ ውጥረት ነገሰ፡፡ ንጉሱ‹‹..ያላችሁትን ሰምተናል አሁን ከዚህ ግቢ ውጡልኝ ››አይነት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

ወታደሮቹ ደነገጡ፡፡መደንገጥ ብቻ ሳይሆን ግራ ተጋቡ፡፡ይሄን ግዜ ደበበ ከክፍሉ ለቆ ወጣ፡፡ አሁን አደገኛው ነገር ሊመጣ ነው፡፡ የተባለውን ሰምቶ ሊያመልጥ ነው፡፡ እዚህ ያለው ጉዳይ እልባት ሳያገኝ ትቶ መሄዱ ለወታደሮቹ አደገኛ ነው፡፡ደበላ ዲንሳ ከንጉሱ ጋር ያላቸው የመጨረሻ ነገር ሳይደመድሙ ደበበ አመለጣቸው፡፡ ግን ርቆ አልሄደም፡፡ በፍጥነት ተከትለው ወጡና ያዙት‹‹አንተ!!››አሉ

‹‹አቤት››

‹‹የት ነው የምትሄደው?››

‹‹ስልጣን አለቅም ካሉ ቶሎ ውጣ ብለኸኝ የለ››

‹‹ታድያ መቼ አለቅም አሉ››

‹‹ዝም አሉ እኮ››

‹‹ዝም ቢሉስ…››

‹‹አለቅም ማለታቸው ነዋ››

‹‹እና››

‹‹እንዳዘዘከኝ ቶሎ ወጣሁ››

‹‹እኔ ያልኩህን ለምን በደምብ አታዳምጥም,,

‹‹በደምብ ነው ያዳመጥኩት፤ ንጉሱ ለመውረድ ፍቃደኛ አይደሉም እኮ››

ሻለቃ ደበላ ተናደዱ፡፡ በእርግጥ ሰውዬው ደበበ እንዳለው መውረድ እንደማይፈልጉ አሳውቀዋል፡፡ ስልጣን ለቅቂያለሁ ብለው ከወንበራቸውም አልተነሱም ‹‹ያላችሁትን ሰምተናል›› እንጂ





‹‹ለቀናል›› አላሉም ፡፡ደበበ ይሄን ወሬ ይዞ ከወጣ ህዝቡ ወታደሩ ሰውየውን ለማውረድ አቅም እንዳጣ ስለሚገምት በእነርሱ ላይ ትልቅ ጫና ነው የሚፈጠረው፡፡ሻለቃው ደበበን ከእዚህ በኋላ ከእኛ መስመር ብትወጣ ላንተ ጥሩ አይደለም በሚል ወደ ውስጥ መልሰውታል ፡፡ ንጉሱን እንደሌሎች ባለስልጣኖች አንጠልጥለው መውጣት የሚቻላቸው ሆኖ አልተገኙም፡፡ወታደሮቹና ንጉሱ ተፋጠጡ፡፡ይሄ ጋዜጠኛ ንጉሱ እምቢ በማለታቸው የተደሰተ መስሏቸዋል፡፡ደርግን እንደማይወድ ጠርጥረውታል፡፡ወታደሮቹ ንጉሱን ከስልጣን ካወረዱ በኋላ ህዳር 14 ሚኒስትሮቹን ገደሉ፡፡ከውጭና ከውስጥ ተቃውሞ ገጠማቸው፡፡አርቲስቶቹን የህዝብ ስለነበሩ ደርግን በቲያትሩም በዘፈኑም መጎንተል ጀመሩ፡፡

እንደገና ሚዝያ 14 የብሄራዊ ቲያትር ሰራተኞች በጠሩት ሰልፍ ደበበን ጨምሮ አርቲስቶቹ ተጠራርገው ታስረዋል፡፡ ከታሳሪዎቹ ሰዎች አንዱ ተስፋዬ ለማ ነበር፡፡ከተማ ውስጥ አሁን ጎልቶ የወጣውና የሰው መነጋገርያ የሆነው የጥላሁን ዘፈን ነው፡፡ግጥሙ ምንም ፍቺ አያስፈልገውም፡፡

> አልማዝን አይቼ አልማዝን ባያት
> ሶስተኛዋ አልማዝ ብትመጣ ድንገት
> ሁለቱን አልማዞች ስላስረሳችኝ
> ምርጫዬ በድንገት ተበላሸብኝ

አሁን ደርግ በስልጣን ላይ ሲቀመጥ ሊቀመንበሮቹ ሶስት ናቸው፡፡ በአጠራርም ‹‹ሶስቱ ሊቃነመናብርቶች›› በሚል ነው የሚታወቁት፡፡ ተስፋዬ ለማ ለጥላሁን በሰጠው ዘፈን አንዱን ለመምረጥ እንደተቸገረና ሶስቱም ለስልጣን ብቁ እንዳልሆኑ የሚገልጽ ነው በሚል ህዝቡ ውስጥ ደርግ ላይ ጥርጣሬ ለመፍጠርና ሀገር ለመምራት ብቃት እንደሌላቸው ለማሳየት ነው በሚል ተስፋዬ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል፡፡ ተስፋዬን ጠርተው አነጋገሩት‹‹ምንድነው ይሄ ዘፈን››አሉ

‹‹የቱ?››

‹‹ አልማዝን አይቼ…››

‹‹የፍቅር ነው››

‹‹ነው እንዴ? ››
‹‹እዎ››
‹‹ስልጣን ላይ ሶስት ሰዎች አሉ››
‹‹እንደዛ አይደለም››
‹‹እንዴት ነው ታድያ?››
‹‹ፒያሳ ቡና ቤት››
‹‹እና››
‹‹አንዷ ስሟ አልማዝ ነው››
‹‹እሺ››
‹‹ተጣራሁ››
‹‹ቀጥል››
‹‹ሌላኛዋም አቤት አለች››
‹‹እሺ››
‹‹ሌላኛውም እንደዚሁ››
‹‹ምን ማለት ነው?››
‹‹ሶስቱ ስማቸው አልማዝ ነበር››
‹‹ብቃ ይሄ ነው!!!››
‹‹እዎ››
‹‹ማንም አያምንህም››



**ተስፋዬ ለማ**





በእርግም ተስፋዬን ማንም አያምነውም፡፡እነዚህ የኪነጥበብ ሰዎች ወታደር ድንበር መጠበቅ እንጂ ሀገር መምራት አይችልም ብለው ነቀራ እንደያዙ ገብቷቸዋል፡፡ኢህአፓ ገና ከጅምሩ ‹‹ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም›› የሚል ጥያቄ ነበረው፡፡ ደርግ በሶስቱ አልማዞች ተመስሏ፡፡ ከደርግ ይልቅ ኢህአፓን እንፈልጋለን የሚል ጥያቄ እንዳለው በብዙዎቹ ዘንድ ተተረጎመ በግጥሙ ውስጥ እንዲህ የሚል ሀረግ አለው

ከአልማዝ መሀል ገብቶ በአልማዝ መቸገር
ለሰሚው ግራ ነው የሚያደናግር
የሶስቱ አልማዝ ምርጫ ስላስጨነቀኝ
ጥሩወርቅተሽላ ስለታየችኝ...

ሄድኩኝ ከጥሩ ወርቅ አልማዞቹን ትቼ
አላዋጣም ሲለኝ ነገሩን ገምቼ

እንግዲህ አነጋጋሪ የነበረውና ጥሩወርቅ የተባለችው በኢህአፓ የምትወከል ናት በሚል ተተረጎመ፡፡ ተስፋዬ በዘፈኑ ዛቻ ተከተለው፡፡ ከዛቻው በኋላ ወደ እስር ቤት እንዲገባ ተደረገ፡፡ ከሶስቱ ሊቃመናብርቶች ወሳኙ ሰው መንግስቱ እንደሆነ ብዙ ሰው ማወቅ ጀምሯል፡፡ ተስፋዬ ለማ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ውስጥ ወጣት የሙዚቃ አባላትን ግጥምና ዜማ አስጠንቶ ሙዚቃውን ወደ መድረክና ወደ ህዝብ እያወጣ ነው፡፡በሙዚቃ ውስጥ ያለው ግጥም እንዲህ የሚል ነው(ተስፋዬ ባሳተመው መጽሀፍ ላይ ጠቅሶታል)

የበሰለ ፍሬ መብላት ካማራችሁ
ልጆች አትንጫጩ በአፍ አምላክ ብላችሁ
በጣም አትቸኩሉ በጣም አትክነፉ
ዝንጀሮም ቅርብ ነው ይወርዳል ከዛፉ

ይሄ ዘፈን ግልጽ ነው፡ስልጣኑን የያዙት ሻለቃ መንግስቱ የቆዳቸው ቀለም ጥቁር በመሆኑ ‹‹ዝንጀሮም ቅርብ ነው ይወርዳል ከዛፉ››የሚለው ሰውየው ከስልጣን እንደሚወርዱ የሚያሳይ ነው፡፡ እናም ተስፋዬ ብዙ ተዳፈረ ተብሎ ለዚህኛውም ጉዳይ ተደምሮበት እስር ቤት ገብቷል፡፡እርግጥም ደርግ እነዚህን የኪነጥበብ ሰዎች ከጅምሩ ፈርቷል፡፡ደግሞም ነክሰው የያዙት ሻለቃ መንግስቱን ነበር፡፡

ገና ወደ ስልጣን እንደመጡ ብሄራዊ ቲያትር ‹‹ሎሚ ተራ ተራ›› የሚለውን ለህዝብ አቅርቧል። ግጥሙ የጌታቸው ደባልቄ ነው። ሙዚቃውን የምትጫወተው ደግሞ ጠለላ ከበደ ናት።

ሎሚ ተራ ተራ፤ሎሚ ተራ ተራ
የእማምየን ነገር ጎረቤት አደራ.......የሚል ነው።በግጥሙ ውስጥ

እናቴ ከአንድ አባት 14 ወልዳለች
ሞግዚትም እናትም ሆና አሳድጋለች
ሞግዚት በማጣቷ አሁን ታለቅሳለች
አባባም ተግዞ ወህኒ ገብቷል አሉ
ጋሽዬም ጤና አጥቶ ከሀገር ወጥቷል አሉ
ወራሽ ነኝ ይል ጀመር እንዳንድ ዲቃላ
ከአማካሪው ጋራ ተሻርኮ ሊበላ......እያለ ይቀጥላል ።

ይሄ በወቅቱ ግልጽ ነበር። ንጉሱ ታስረዋል ፤አልጋ ወራሽ በጤና ችግር ምንክንያት ከሀገር ወጥተዋል። ስልጣን በሻለቃ መንግስቱ እጅ ስለገባ‹‹ወራሽ ነኝ እያለ እንዳንድ .....››የሚለው ሀረግ ማንን ለመንካት እንደሆነ ህዝቡ ገባው ።ሁለቱም ታስሩ ።የግጥሙ ባለቤት ጌታቸው ሞት እንደሚጠብቀው ብዙዎቹ እውቀዋል። ይገደላል ተብሎ እየተጠበቀ በመጨረሻም እስም ቢታኝ ገብቷል። ሉሉችም እስር ቤት ሆነው መጨረሻቸውን እየጠበቁ ነው።እነደበበ እስር ቤት ቆይተው ነገሩ ተጣራ። ከጀርባው ሌላ ቡድን ገብቶ የአላማው ማስፈጸሚያ እንዳደረጋቸው መረጃ ተገኘ። ነገር ግን ቶሎ አለቀቃቸውም።በዚህ መሀል በናይጀርያ ሌጎስ ትልቅ የኪነጥበብ ፌስቲቫል ተደረገ።እነደበበ በዚህ ላይ መሳተፍ ስለነበረባቸው ምን ይደረግ ተባለ።ፖሊስ ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ ተደረገ ።የፖሊሱ ስራ እነደበበ እንዳይጠፉ በአይነ ቁራኛ መጠበቅ ነበር።በመጨረሻ ልኡካን ቡድኑ ወደ ሀገር ቤት ተመለሰ።ይጠፋሉ ተብሎ በከባድ ጥበቃ ስር የነበሩት እነደበበ ሲመለሱ እንዳይጠፉ ጠባቂ የነበረው ፖሊስ ግን ሳይመለስ በዛው ጠፍቶ ቀረ።





# ምእራፍ 13

## ሽልንጌን

በስታዲየም ለተገኘው ተመልካች ብቻ ሳይሆን በመላ ሀገሪቱ በሬድዮ ጨዋታውን ለሚከታተሉት ሁሉ አስጨናቂ ሰዓት ነበር።በዚህ የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ውድድር ቡድናችን ለሻምፒዮናነት ተጠብቆ በአስቸጋሪ ሁኔታ ነበር ለዋንጫ የደረሰው።በፍጻሜው ጨዋታ የዙምባብዌ ቡድን የሚቀመስ አልሆነም። ተጋጣሚያችን ለረጅም ደቂቃ በመረብት ላይ በመቆየቱ ተመልካቹን ድንጋጤ ውስጥ ገብቶ በጭንቀት ጥፍራቸውንና የኮታቸውን ጫፍ እስከማኘክ ደርሰው ነበር። የሀገሪቱ መሪ ኮለኔል መንግስቱ ሀይለማርያም ሳይቀሩ ሰዓቱ እተገባደደ ሲሄድ ሲቁነጠነጡና ሲጨነቁ ላያቸው እስከመደነቅ ያደረሰ ሁኔታ ነበር ። ታህሳስ 17 የተደረገው ይሄ ጨዋታ ዋንጫ እንዲገኝ ከሁለት ቀን በኋላ ለሚከበረው የአመቱ የቁልቢ ገብርኤል ንግስ በዓል ስለት የተሳሉ ብዙ ተመልካች ነበር።ቡድናችን ግብ ባለማግኘቱ ሰዓቱ በመጠናቀቁ ተስፋ የቆረጠው ተመልካች ስታዲየሙን ለቆ በመውጣት ላይ እያለ ገብረመድን ያስቆጠረው ኳስ ጨኸቱ ስታዲየሙን በአንድ እግሩ ነበር ያቆመው።

በጭማሪው ሰዓት ድካምና ጉዳት ከእቋማቸው ያወረዳቸው ተጫዋቾች በተገቢው መንገድ ባለመንቀሳቀሳቸው ግብ ለማግኘት ባለመቻሉ ቡድናችን ወደ መለያ ምት ሄደ።በጭማሪው ሰዓት ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ እግሩ የታጠፈው ግብ ጠባቂው ተካበ ተቀይሮ ለመውጣት ቢፈልግም 3 ተጫዋች ስለተለወጠ ከእነህመሙ መቀጠል ግድ ሆነበት።ቡድናችን ወደ መለያ ምት ሲገባ ከፍል ሁለት ጭንቀት ተጀመረ ። ገብረመድን፤ አማኑኤልና ነጋሽ አከታትለው በማስቆጠራቸው ቡድናችን ዋንጫ የማግኘት ተስፋው ከፍ አለ። ህዝቡን ያስደተው የእኛ ግብ ማስቆጠር ብቻ ሳይሆን የመጀሪያውን ሁለት ሪጎሬ ተካበ በማዳኑ ነበር።የተመቱትን ኳሶች እየተወረወረ

ሲያድን የህዝቡ ጭብጨባና ሙገሳ የተለየ ነበር፡፡እየተወረወረ ኳሶችን የሚመልስባቸው እጆቹ ብዙ ዱላ ተቀብለውና ተቀጥቅጠው እዚህ የደረሱ ናቸው፡፡በልጅነቱ ገና ባለጠነከረ ሰውነቱ ለሳምንት ያህል ገራፊዎች እየተፈራረቁ በመቀጥቀጥ ብዙ ቢጎዱትም ዛሬ ግን ለሀገር ድንቅ ነገር እየሰራበት ነው፡፡ መለያ ምቱ ቀጥሎ በቀለና መንግስቱ በመሳታቸው ከዙምባብዌ ጋር እኩል በመምጣታችን አንድ - አንድ ምት ተሰጠና የመጀመርያውን ዙምባብዌዎች ሳቱ፡፡የመጨረሻውን ምት ለመምታት ተካበ ኳሱን ይዞ ሲሄድ ‹‹ማንን …ማንን››የሚል ድምጽ ሰማ፡፡ ይሄን ስም ያወጣለትና በዚህ ስያሜ የሚጠራው አስራት አዱኛ ስለነበር ወደ እርሱ ዞር ብሎ ሲመለከት ‹‹..አንተ እንዳትመታ ለዳኛቸው ስጠው ››አለው፡፡

ዳኛቸው ኳሱን ተቀብሎ መምቻው ላይ በማስቀመጥ እግሩን ተረረም…ተረረም አድርጎ በማስቆጠሩ ተሟጦ የነበረው ተስፋችን በዋንጫ በመካሱ የህዝቡ ደስታ ከፍተኛ ነበር፡፡ህዝቡ ይሄንን ደስታውን ጥግ እንዳያደርስ ስእት አላፊው ስለሚያግደው በሀገሪቱ ለረጅም ግዜ ተጥሎ የነበረው ሰአት እላፊ ተነሳ፡፡ ቤተመንግስት በተደረገ ግብዣ የሀገሪቱ መሪ ኮለኔል መንግስቱ‹‹ ይሄ ዋንጫ የተገኘው በአንዳች ሀይል ነው በሚል እየተወራ ያለው ትክክል አይደለም፡፡ ቡድናችን ያሸነፈው በአብዮታዊ ልጆቻችን ቆራጥ ተጋድሎ ነው››በሚል የተናገሩት ህዝቡ ለቁልቢ ገብርኤል ተስሎ ነው ዋንጫው የተገኘው የሚለውን ወሬ መልስ የሰጡበት ነበር፡፡በግብዣው እለት ለተጫዋቾችና አሰልጣኞች የገንዘብ ሽልማት ተሰጠ፡፡ብሄራዊ ሎተሪ ቴሌቪዥንን ሲሸልም መንግስት ለእያንዳንዱ አምስት ሽህ ብር ሰጠ፡፡የሽልማቱ ስነስርአት ተጠናቀቀና ወደ እራት ግብዣው ለመግባት ሲሰናዱ ከመድረኩ በድምጽ ማጉያ የአንድ ሰው ስም ተጠራ ‹‹ተካበ ዘውዴ››የሚል ነው፡፡ ተካበ ግራ ተጋባ፡፡ ሽልማት ለሁሉም ተሰጥቶ ተጠናቋል፡፡ይሄ ስም እንዲመጣ የተጠራው የሀገሪቱ መሪ ወዳሉበት ስፍራ ነው፡፡ለምን እንደተጠራ ግራ ገባው፡፡ ለግዜው ደነገጠ፡፡የቡድኑ አምበል አልነበረም፡፡ ወይም የተጨዋቾቹ ተወካይ አይደለም፡፡ታዲያ ለምን ጠሩት?፡፡በዚያች ሰከንድ ግራ ስለተጋባ ወደተጠራበት ቦታ ቶሎ





ለመሄድ አልሞከረም፡፡እርግጥ የተጠራው የእሱ ስም ነው ወይስ የሌላ?፡፡ይሄን ለማወቅ ድጋሚ ጥሪ እስከመጠበቀ ደረሰ፡፡

አሁንም ‹‹ተካበ ዘውዴ›› የሚል ስም በድጋሚ ተጠራ፡፡ የባሰ ተደናገጠ ‹‹ሽልማቱን መልስ ሊሉኝ ነው›› ብሎ አሰበ፡፡በምንም መንገድ ልጠራ አልችም ብሎ ባሰበበት ሰዓት በድጋሚ ወደ ጓድ መንግስቱ ጋር እንዲቀርብ በመጠራቱ ግራ አጋባው፡፡እነዚህ ሰዎች የጀርባ መደቤን ደርሰውብኝ ይሆን እንዴ? ብሎ አሰበ፡፡አንድ ቀን ያለፈ ታሪኩን ከደረሱበት አለቀለት፡፡ ድሬዳዋ ጥጥ ማህበር የነበሩ ተጫዋቾች ወታደራዊ መንግስትን በመቃወም የሚታወቁ ናቸው፡፡ የዚህ ክለብ ተጨዋቾች ደግሞ ለፖለቲካ የተጋለጡ ናቸው፡፡ለዚህ የሴካፋ ዝግጅት አብሮት ተመርጦ የነበረው መሀመድ ኡስማን (ሚግ) ለትሬኒንግ ሲሄድ የደህንነት ሰዎች ታፍኖ እስር ቤት ገብቶ ብዙ ግርፋት ደርሶበት አሳሩን አሳይተውት ነበር፡፡ሚግ የታሰረው ከአስር አመት በፊት ለኢህአፓ መረጃ በማቀበል ለብዙ ሰዎች ሞት ተጠያቂ በመሆኑ ነበር፡፡፡ሚግ ለታሰረበት ጉዳይ ተሳታፊ ከነበሩትና ከተገደሉት መካከል አንዱ አበራ የተባለው ወጣት ነበር ፡፡ አበራ በትግሉ ውስጥ ሀይለኛና ለድርጅቱ ታማኝ የነበረ ወጣት ነው፡፡ እሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ወንድሞቹ በትግሉ ውስጥ የኢህአፓን አርማ አንስተው የሚታገሉ ነበሩ፡፡ የዚህ ወጣት ታናሽ ወንድም አሁን ቤተመንግስት የሀገሪቱ መሪ ጋር እንዲቀርብ ስሙ እየተጠራ ነው፡፡ሁሉም ነገር ተጠናቆ ስሙ መጠራቱ ‹‹በአብዮታችን ውስጥ ኢህአፓ እንዴት እንሸልማለን ››የሚል ጉዳይ ሽልማቱን አስመልሰው እንደ ሚግ ወደ እስር ቤት ቢወረውሩትስ?፡፡በዚያች አጭር ሰከንድ ውስጥ ተካበ ጉዳዩን እስኪያውቀው ድረስ በጣም አስጨነቀው፡፡ የኢህአፓነት ጥላው ቤተመንግስት ድረስ ተከትሎት እንደመጣ በመጠርጠሩ ስጋት ሊያድርበት ይችላል፡፡ነገሩ ሲጀመር እንዲህ ነበር፡፡

በአብዮቱ ወቅት ኢህአፓ የጀመረው ትግል በተፋፋመት ግዜ የውስጥ ስሜቱ እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡የኢትዮ-ሱማሊያ የውስጥ ስሜቱ እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡የጠላት ጦር ጦርነት በተነሳበት ግዜ ድሬዳዋን እጅግ አስጨንቆ ነበር፡፡የጠላት ጦር እየገፋ በሄደበት ግዜ ከተማ ውስጥ የሚተኮሰው ከባድ መሳርያ በየቦታው ይወድቅ በነበረ ግዜ ብዙ ሰው ለአደጋ ተጋልጦ ነበር፡፡

የመጣውን ጦር ለመመከት ድሬዳዋን ለቀን እንሄድም ያሉ ሰዎች በአካፋም ሆነ በቆንጨራ ጠላትን እንፋለማለን ብለው ከተማውን ለመጠበቅ ተዘጋጁ፡፡ የዚያኑ ያህል ቤተሰባቸውን ጠቅልለው ወደ መሀል ሀገር የሸሹም አልጠፉም ነበር፡፡ጠላትን ለመፋለም የተዘጋጁ ወጣቶች ደግሞ መሳሪያ ታጥቀው በመከላከል ሳይሆን በማጥቃት ስራ ላይ ለመሳተፍ ወደ መሳርያ ግምጃ ቤት ነጎዱ፡፡ ብዙዎቹ ኳስ ተጫዋች እንጂ የጦር ሰዎች አይደሉም፡፡ ውትድርናም አልሰለጠኑም፡፡ መሳሪያ መፍታትና መግጠም አያውቁም፡፡ ለመተኮስ በእጃቸውም አልነኩም፡፡ ግን ‹‹የሱማሌ ወረራ አሳስቦናል›› በሚል በቁጣ እየተራመዱ ግምጃ ቤት በራፉ ላይ ደርሰዋል፡፡ የወጣቶቹ መሪ ጥያቄውን ለማቅረብ ወደ ሀላፊዎቹ ተጠጋ ‹‹ማነህ አንተ?›› አሉት

‹‹እኔ?››

‹‹አዎ››

‹‹ተካበ ዘውዴ እባላለሁ››

‹‹ምን ፈልጋችሁ ነው?››

‹‹መሳሪያ››

‹‹ምን ለማድረግ?››

‹‹ሱማሌን ለመውጋት››

‹‹እናንተ?››

‹‹አዎ››

‹‹እንዴት?››

‹‹ዳር ድንበሩን አስከብረን ለመሞት ቆርጠናል››

‹‹እና››

‹‹አስታጠቁን››

‹‹ጭራሽ በድፍረት እዚህ ድረስ መጣችሁ?››

‹‹ለሀገራችን ለመዋጋት ነው እኮ››

‹‹እኛ ለኢህአፓ መሳሪያ አናስታጥቅም››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹ማንነታችሁን አውቀናል››

‹‹እረ እኛ ኢህአፓ አይደለንም››

‹‹ሳናስራችሁ በአስቸኳይ ከዚህ ጥፉ››





ታዳጊ ወጣቶቹ ከሀላፊው የተሰጠው መልስ አላስደሰታቸውም፡፡ ችግር ከመፈጠሩ በፊት በፍጥነት አካባቢውም ለቀው ሄዱ፡፡በወቅቱ በፍቃደኝነት ታጥቀው ወደ ጦርነቱ ለመግባት የተመዘገበ እንዳሉ አውቀው ነበር፡፡እነርሱም ለመታጠቅ ነበር የሄዱት፡፡ ሀላፊው ግን ግንባራቸው ላይ የኢህአፓ ደም እንዳለባቸው ያወቀ ስለመሰላቸው የመጡበትን ጉዳይ ሳያሳኩ ተመለሱ፡፡ሰውየው ግን ምን ሰምቶ ነው እንዲህ ያላቸው?፡፡ግን ተካበ ኢህአፓ ነበር እንዴ? ነገሩ ሲጀመር እንዲህ ነበር ፡-

በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ላይ የነበረው ርእስ መምህሩ ዛሬ ለምን ማንሳት እንደፈለገ ባይታወቅም ተማሪዎቹ ሞቅ ባለ ስሜት እየተሳተፉና እየተከራከሩበት ነው፡፡መምህር ሽመልስ ክፍሉ ውስጥ እየተንጎራደደ ደግሞም ወደ ብላክ ቦርዱ የሆነ ነገር እየጻፈ እንደገና ወደ መምህሩ ማስተማርያ መጽሀፍ እያተኮረ ማስረዳቱን ቀጠለ፡፡‹‹....እያችሁ ተማሪዎች!!!!! ይህች ወጣት ሴት ስርቃ የምታድር ነች፡፡ ገንዘብ ለማግኘት መንገድ አለባት ፡፡ የምትተዳደረው በዚህ ስራ ነው...›› ብሎ ስለልጅቷ ማውራት ጀመረ፡፡ የዚህችን ልጅ ታሪክ ተማሪዎቹ በደምብ ያውቁታል፡፡እንኳን እነርሱ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ተማሪዎች አትጠፋቸውም፡፡ እርሷ ደግሞ የዚህ አካባቢ ሴት ነች፡፡ አሚና ትባላለች፡፡ሽልንጌን በተባለው ታሪክ ውስጥ ትልቋ ተዋናይ ናት፡፡በባቡሩ መቆሚያ ቦታ ተሳፋሪው የሚበላ የሚጠጣ ነገር ስለሚፈልግ የአካባቢው ነዋሪ ፍራፍሬ በመሸጥ ይተዳደራል፡፡አሚናም ለአንዱ ተሳፋሪ ብርቱካን ሸጠችለት፡፡ ገንዘቡን ሳትቀበል ባቡሩ ተነሳ፡፡ተነሳና ተንደረደረ ፡፡ተንደርድሮም ፍጥነቱን ጨመረ ፡፡ይሄ ሁሉ ሲሆን ፍራፍሬውን የገዛው ሰው ለአሚና ገንዘቡን አልሰጣትም፡፡የገዛው የሃምሳ ሳንቲም(ሽልንግ) ብርቱካን ስለነበር ባቡሩን እየተከተለች ‹‹ሽልንጌን... ሽልንጌን.... ሽልንጌን.... ሽልንጌን›› እያለች ትከተል ነበር፡፡ ነገር ግን ሽልንጓን ሳታገኝ ባቡሩን እየተከተለች ትሮጥ ጀመር፡፡

መምህሩ ታሪኩን ሲያወሩ መጨረሻውን ለማወቅ ተማሪው በጉጉትና በንቃት እያዳመጠ ነው፡፡መምህር ሽመልስ ግን ታሪኩን አልጨረሱም፡፡መጨረስም አልፈለጉም፡፡ተማሪው ጆሮውን እንደቀሰረ

አንድ ጥያቄ ጣል አደረጉ፡፡‹‹…ለመሆኑ አሚና ወዝአደር ነች ወይስ ላባደር?›› አሉ፡፡ተማሪው ጸጥ አለ፡፡እነርሱ የሚፈልጉት በጥሩ አገላለጽ የጀመሩትን ታሪክ እንዲጨርሱላቸው ነበር፡፡መምህሩም ጥያቄያቸው እንዲመለስላቸው ስለፈለጉ‹‹ይሄን ጥያቄ የሚመልስ የለም?››አሉ

‹‹እለሁ››
‹‹ማነው ስምህ?››
‹‹ተካበ››
‹‹ተካበ ማን››
‹‹ተካበ ዘውዴ››
‹‹እሺ!!ታሪኩን በደምብ ስምተሃል››
‹‹እዎ››
‹‹አሚና ወዛደር ነች ወይስ….››.
‹‹ወዛዳር አይደለችም››
‹‹እና››
‹‹ላባደር ነች››
‹‹እስኪ. አብራራው››

ተካበ ወዛደር የሚለውን አጠራር ስለማይመቸውና ላብ አደርነቷን በሚገልጽ ሁኔታ አብራርቶ መለሰ፡፡መምህሩም ‹‹ሌላ አስተያየት ያለው ተማሪ አለ?›› አሉ፡፡ሌሎቹም ተካበ በሰጠው ምላሽ ላይ የተስማሙ በሚመስል ሁኔታ አሚና ላብ አደር እንጂ ወዛደር እንዳልሆነች በመስማማት ጨረሱ፡፡መምህሩም የወዛደርና ላብአደርን ጉዳይ ለምን መከራከርያ እንዳደረጉት ባይታወቅም ላብ አደር ነች በሚል ስምምነት በመጠናቀቁ እነተካበን ያስደሰተ ጉዳይ ነበር፡፡ነገሩ ግን ጥሩ አልነበረም፡፡ ተካበ በዚህ ንግግሩ ኢህአፓነቱ ተረጋግጦ ከሰአት ወታደሮች እንቀው እስር ቤት ወሰዱት፡፡

ምሽት ላይ የመጣው ገራፊ እስረኛውን እያየ ከንፈሩን በመምጠጥ ‹‹አሳይሃለሁ!!!!›› አይነት ይንጎራደድ ጀመር፡፡ደግሞም ለመግረፍ ሞራል እንዲሆነው መጠጥ ቀማምሶ ነው የመጣው፡፡ ቀማምሶ ብቻ ሳይሆን በደምብ እንደገለበጠ ያስታውቃል፡፡‹‹ሳልገርፍህ ታወጣለህ አታወጣም?››አለ





‹‹ምኑን?››
‹‹ወረቀቱ››
‹‹ወረቀቱ ምን ሆነ?››
‹‹በእኔ ላይ ነው የምታሾፈው?››
‹‹አልገባኝም››
‹‹ማነው ወረቀቱን የበተነው?››
‹‹የት?››
‹‹ትምህርር ቤት››
‹‹ እኔ አላውቅም››
‹‹የማናውቅ መስሎሃል ››
‹‹ምኑን ?››
‹‹ዋናው ኢህአፓ መሆንህን››
‹‹እረ እኔ እህአፓ አይደለሁም››
‹‹ስትገረፍ ሁሉን ነገር ትዘከዝካለህ››

ግርፊያው ተጀመረ፡፡ ሁለቱም ይጯጯሃሉ፡፡ ማን ገራፊ ማን ተደብዳቢ እንደሆነ እንኳን መለየት አልተቻለም፡፡ ገራፊው ሰክሮ ስለነበር እየጮሀ ይቀጠቅጠዋል፡፡ እስኪበቃው ከቀጠቀጠው በኋላ እረፍት አደረጉ፡፡ አሁንም ማውጣጣቱ ቀጠለ፡፡ ‹‹ማነው ስምህ››አለው

‹‹ተካበ ዘውዴ››
‹‹አንተ ነህ አይደል ወረቀቱን የበተንከው››
‹‹አይደለሁም››
‹‹ካንተ ጋር እነማን እንደተባበረ ንገረንና ግርፋቱ ይቁም››
‹‹አላውቅም አልኩህ››
‹‹አልከኝ እንዴ?››

እንደገና ግርፍያው ተጀመረ፡፡ድብደባው ሲበዛበት ያምናል ሌሎችንም ይጠቁማል ተብሎ ቢጠበቅም ታዳጊው ወጣት ትንፍሽ ሳይል ቀረ፡፡ተገራፊዎች በመጀመሪያ ቀን ብዙ እንደማያምኑ ከልምድ ስለሚታወቅ ሲደጋገምበት እንደሚያወጣ ጠብቀዋል፡፡ኢህአፓነቱን እንደደረሰብት አውቀዋል፡፡አሚና ላብ አደር ነች ብሎ ስላብራራ ከየትኛው ወገን እንደሆነ ተማሪውም መመህሩም አውቀዋል፡፡የተካበ መታሰር ቤተሰቡን አስጨንቋል፡፡ አንደኛው ወንድሙ የኢህፓ አባል

በመሆኑ በካድሬዎች ተገድሏል፡፡ሌላኛው ደግሞ ወደ አሲምባ ገብቷል፡ ፡ ገራፊው በነጋታው መጥቶ ያገኘበት ቦታ ይመታዋል፡፡ ወገቡን፣ እፉን፣ እግሩን፣ደረቱን ብቻ ያገኘበት ቦታ በስካር መንፈስ ይቀጠቅጠዋል፡፡ ነገር ግን ምንም ትንፍሽ አላለም፡፡ ተካበ ብዙ ቀን ታስሮ ከተገረፈ በኋላ የተደራጀ ነገር ስላላገኙበት ቢለቀቅም መልሰው ያስሩኛል ብሎ ስጋት ነበረው፡፡ለቀበሌው ክለብ በእግር ኳስ ንቁ ተሳትፎ በማድረጉ ክትትሉ እየላላለት ሄደ፡፡

ከቀበሌው ከፍ ብሎ ወደ ከነማ ፣ከዚያም አልፎ ከነማዎችን ወደሚጠቀልለው የካቲት 66 ቡድን ተሸጋግሮ አለፍ ሲልም ወደ ኮተን ክለብ ተዛውሮ ቡድኑን በ1975 ለኢትዮጵያ ሻምፒዮና በማብቃቱ ለመጀመሪያ ግዜ ለብሄራዊ ቡድን ተመርጦ ሀገሩን ወክሎ መሰለፍ ቻለ፡፡በምስራቅ አፍሪካ ዋንጫ ውድድር ቡድኑን ለዋንጫ በማብቃቱ ከሀገሪቱ መሪ ሽልማት ተቀበለ፡፡ስነስርአቱ እንዳለቀ ተካበ ዘውዴ ተብሎ እንደገና ሲጠራ ደነገጠ፡፡ነገር ግን ወደተጠራበት ቦታ እንደደነገጠ ሄደ፡፡ሰውየው ፈገግ ብለው ‹‹አንተ ነህ ጀግናችን!!!›› በሚል ልዩ ሽልማት ተሰጠው፡፡ለዚህ ነው እንዴ የደነገጥኩት?፡፡ ሽልማቱ የቪዲዮ ማጫወቻ ዴክ ነበር፡፡ ያኔ ቪዲዮ ማሳያ ቤት እንጂ እንደ ተካበ ያለ ወጣት እንዲህ አይነት እቃ አልነበረውም፡፡በፖለቲካ ልዩነት ሲገርፈው የነበረው ፓርቲ ልዩ ተሸላሚ ነህ አለው፡፡

የአሚና ታሪክ ክፍል ውስጥ ካከራከረ ከ30 አመት በኋላ ሁለት ሰዎች አዲስ አበባ ላይ ተገናኙ፡፡ወጣቱ ሰው በርቀት ወዳየው እንግዳ ተጠጋና ‹‹ጤና ይስጥልኝ››አለ፤

‹‹ጤና ይስጥልኝ››

‹‹አቶ ሽመልስ››

‹‹አዎ››

‹‹ድሬዳዋ እንተዋወቃለን››

‹‹የት ሰፈር?››

‹‹መምህሬ ነበሩ››››

‹‹እኔ?››

‹‹አዎ››





‹‹ድሬዳዋን አላውቀውም››

‹‹እረ እኔ አውቅዎታለሁ››

‹‹ተሳስተሃል››

‹‹አልተሳሳትኩም››

‹‹ከሌላ ሰው ጋር ተመሳስየብህ ይሆናል››

‹‹በፍጹም››

‹‹እረ ያውቁኛል!!››

‹‹ማን ትባላለህ?››

‹‹ተካበ ዘውዴ››

‹‹እንዲህ አይነት ሰው አላውቅም፡፡››



**ተካበ ዘውዴ**

ተካበ ተናደደ፡፡ ከሰውየው ጋር ማውራት ፈልጎ ነበር፡፡ያን ግዜ ስለአሚና ያነሳው ጉዳይ ለምን እንደሆነ ለመጠየቅ ብዙ ግዜ ይፈልግ ነበር፡፡ስለ እሷ ታሪክ ማውራቱ ምንም ማለት አልነበረም ፡፡በመምህሩ ማስተማሪያ መጽሀፍ ላይ የአሚና ታሪክ ስላለ ችግር የለውም፡፡ ግን ላብ አደር ነች ወዛደር ?ብሎ ለምን ጠየቀ? የሚለው ጉዳይ ተካበን ሁል ግዜ የሚከነክነው ጉዳይ ነበር ፡፡ምክኒያቱ ደግሞ ተካበ ተጠርጥሮ የታሰረው አሚና ላብ አደር ነች በማለቱ ነበር፡፡ላብአደር የሚለው ደግሞ ደርግ ሳይሆን ኢህአፓ ነበር፡፡እናም እስር ቤት ማንነታቸውን ክደው ተወረወረበት፡፡መምህሩ ግን ጉዳዩን ሳይነግሩትም ‹‹አላውቅህም›› በሚል ዘግተውት ሄዱ፡፡እሳቸው የአሚናን ታሪክ

ለፖለቲካ ይጠቀሙበት ወይም ለማስተማርማንም የሚያውቅ አልነበረም፡፡ብቻ ወጣቱን ልጅ ለቶርች አሳልፎ ሰጠው እንጂ፡፡ተካበ ከኢህአፓ ጋር በተያያዘ አንድ ወንድሙን በሞት አጥቷል፡፡ሌላኛው ወንድሙ ደግሞ በካድሬዎች በጥብቅ ሲፈለግ የት እንደገባ አልታወቀም፡፡እሱም እራሱ ኢህአፓንነቱ ታውቆ ብዙ ተገርፏል፡፡አሁን የግብጠባቂ ችሎታውን እየተጠቀመ ነው፡፡እንዳኛቸውና መስፍን የመሳሳሉት ተጫዋቾች ከክለቡ ለቀው አዲስ አበባ ክለብ ሲገቡ ተካበ አልተፈቀደለትም፡፡እንዳውም መድን ክለብ ሲሰራ እንቀው ወደ ድሬዳዋ መለሱት፡፡አንድ ቀን በጉዳት ወይም በብቃት መቀነስ ከክለቡ ሲገለል እንደገና የዚህ የኢህፓንነቱ ታሪክ እየተንተተ ችግር ውስጥ ሊከተው ይችላል፡፡እናም አንድ ነገር ማድረግ አለበት፡፡

## እንደገና በሌላ ቀን

የደህንነት ባልደረቦችና የፖሊስ አባላት እስረኞቹ ወዳሉበት ክፍል ገቡ፡፡ሶስቱ እስረኞች ተክዘውና ቆዝመው ቁጭ ብለዋል፡፡ መቆመጥ ብቻ ሳይሆን ደንግጠዋል፡፡ መደንገጥ ብቻ ሳይሆን በርግገዋል፡፡በዚህ ግቢ ይሆናል ብለው ያላሰቡት ነገር ተፈጥሯል፡፡ ድንጋጤያቸውም ከች ያለው ለዚህ ነበር፡፡እነዚህ ሀበሾች እዚህ ካይሮ በሚገኘው ትልቁ እስር ቤት ተከርችሞባቸው ቆይተዋል፡፡እዚህ እስር ቤት እስከቆዩ ድረስ ሊገደሉ ይችላሉ፡፡ይሄ ከመሆኑ በፊት ግን ከዚህ ወይን ቤት ማምለጥ አለባቸው፡፡ማምለጥ ካልቻሉ ህይወታቸው ሊያመልጥ ይችላል፡፡ በፈቃዳቸው ከዚህ እስር ቤት መውጣት ይችላሉ ግን ወደ ሌላ እስር ቤት እንደሚሄዱ ነው የሚገምቱት፡፡ሁሉም ቦታ አደጋ፤ሁለቱም ቦታ ሞት እንዳለ አውቀዋል፡፡ አሁን ያሉበት ሁኔታ ለመወሰን አስቸጋሪ ነው፡፡ወደውና ፈቅደው የገቡበት ነገር ህይወትን የሚቀጥፍ ወጥመድ ውስጥ እንደጣላቸው አውቀዋል፡፡እነዚህ እስረኞች ወደ ሀገራቸው መመለስ ከፈለጉ እዚህ እስር ቤት አይቆዩም፡፡ ካለበለዚያ እዚህ መበስበሳቸው ነው፡፡

እነዚህ ሰዎች እስረኞች አይደሉም ነገር ግን እዚህ ወህኒ ቤት ከእስረኞች በላይ ነው በአይነ ቁራኛ የሚጠበቁት፡፡ወደ ክፍላቸው





የገቡት ደህንነትና ፖሊሶች አተኩረው ተመለከቷቸው፡፡ሰዎቹ ቶሎ ወደ ጉዳዩ መግባት ፈለጉ ፡፡ አንደኛው ፖሊስ ወደ እስረኞቹ እየተመለከተ‹‹ሰላም ናችሁ››አለ

‹‹ሰላም ነን››

‹‹እንተካበ መሄዳቸውን ሰምታችኋል አይደል?››

‹‹ወደየት››

‹‹ወደሀገር ቤት››

‹‹ኢትዮጵያ!!!››

‹‹አዎ››

‹‹መቼ?››

‹‹ትናንት ማታ››

‹‹እንዴት?››

‹‹አማራጭ የላቸውማ››

‹‹ማለት››

‹‹እዚህ እስር ቤት ከመማቀቅ …››

‹‹እርግጠኛ ናችሁ››

‹‹አዎ ለእናንተም መልእክት ልከዋል››

‹‹ምን ብለው?››

‹‹መሄዳቸውንና እናተም ቶሎ መምጣት አላባችሁ ብለው››

‹‹ወደ ሀገር ቤት መመለሱ እኮ ችግር አለ››

‹‹ነበረ አሁን ግን ዋስትና ተገኝቷል››

‹‹ከማን?››

‹‹ከኢትዮጵያ መንግስት››

‹‹ምን ብሎ?››

‹‹ምንም እንደማያደርጋችሁና ችግራችሁም ይቀረፋል ተብሏል››

‹‹ ምን ዋስትና አለው?››

‹‹መንግስት ሀላፊነት ወስዷል››

‹‹የማን መንግስት››

‹‹የግብጽ መንግስት››

‹‹በምን ጉዳይ››

‹‹አንድ ችግር ቢደርስ በአለም አቀፍ ደረጃ ይፋ.ረዳል››
‹‹እውነት!!!››
‹‹አዎ፤ዛሬ እኮ ግብጽና ኢትዮጵያ አዲስ ግንኙነት ጀምረዋል››
‹‹እና››
‹‹ይሄ ከእኛ ይልቅ ለኢትዮጵያ ይጠቅማል››
‹‹ምን ማለት ነው?››
‹‹ይሄን ጥሩ ግንኙነት በእናንተ የተነሳ እንዲፈርስ አይፈልግም››
‹‹ስለዚህ....››
‹‹ እንደነተካበ ወደሀገራችሁ ብትመለሱ ጥሩ ነው››
‹‹እናስብበት››
‹‹ቶሎ ብትወስኑ ይሻላል ከዚህ በኋላ ሌላ እድል አታገኙም››
‹‹ቶሎ ሲባል?
‹‹15 ወይም 20 ደቂቃ››

ሶስቱ እስረኞች የሰሙትን ነገር መቀበል አልቻሉም። የመጨረሻውን ውሳኔ ሲሰሙ ማልቀስ ፈለጉ። ግን ለቅሶ የትም አያሻግራቸውም። አንዱ ሌላውን መገምገም ጀመረ። ሀሳባቸው እንዳይለያይ እንደ ብረት የጠነከረ እምነት ገንብተው ነበር። ሲጀመር ስድስት ነበሩ። ምለው ተማምለው እንዳቸው እንዳያፈገፍጉ ተስማምተው ነበር።አንድ ሰው አፈገፈገና ችግር ውስጥ ገቡ። ይሄ ነገር ከተከሰተ በኋላ የገቡበትን ችግር ተቋቁመው ለመውጣት እንደገና የማይታጠፍ ቃል ገቡ።አሁን ደግሞ ሁለቱ ሀሳባቸውን ቀይረው ወደ ሀገር ቤት ተመለሱ።እነሆ በመጨረሻ ሶስት ቀርተዋል ፡፡ከመሃላቸው አንድ ወይም ሁለቱ ሀሳባቸውን ቀይረው ወደ ሀገር ቤት ሊመለሱ ይችላሉ።ሶስቱም አሁን ጥሩ አቋም ላይ ቢሆኑም ነገር ግን እራሳቸውን ማመን ግን አቃታቸው።ሁሉም በውስጡ ማፈግፈግ ጀመረ። ግን ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ አስቸጋሪ መሆኑ አልጠፋቸውም ።

በተካበ ጉዳይ ሁሉም ተገርመዋል። የኩብለላው ካፒቴን እርሱ ነበር።ለመሄድ የሚፈልግ ተጫዋች በአቋሙ እንዲጸና ቃል እያስገባ





መርበትበትና ማፈግፈግ እንደሌለበት አሳሰበ። ግሩፑን የገነባው እርሱ ነው። ለመጥፋት ፈልገው ፈራ ተባ የሚሉትን እያስቀረ ቡድኑን የሰራ ሰው ነው። እዚህ እስር ቤት ከገቡ በኋላም በአቋማቸው እንዲጸኑና ፍንክች እንዳይሉ ሲያሳስብ የነበረው ሰው ሀሳቡን ቀይሮ ወደ ሀገሩ መመለሱ ግራ አጋባቸው።በቀለም ቢሆን እዚህ እስር ቤት ከብዙዎቹ እስረኞች ጋር ጠንካራ ግንኙነት የነበረው እርሱ ነው። እነዚህ እስረኞች ያሉበት ሁኔታ አለም አቀፍ ሚዲያው እንዲያውቅ እዚህ ያሉት እስረኞች በተለየ የሙስሊም ወንድማማች አባሎች በጋዜጣና በመጽሄት እንዲጻፍ በማድረግ ጫና ይፈጥሩላቸው ነበር። ይሄን የሚያመቻቸውና ግንኙነት የሚፈጥርው በቀለ ነው።እዚህ ወህኒ ቤት የሚገኙት የፖለቲካ እስረኞችም በአቋማችው እንዲጸኑ ያበረታታሉ፤ ያሳስባሉ። በተለይ በቀለና ተካበ ያላቸውን አቋም ያደንቁላቸው ነበር።አሁን ግን እነርሱ አቋማቸው ተሸርሽሮ ሶስቱን እስረኞች ሸውደው በመሄዳቸው ተናደዋል።ሶስቱ እስረኞች በነተካበ እንዳዘኑ ቁጭ ብለዋል። አንደኛው‹‹ተካበ ግን...››አለ

‹‹ግን ምን?››
‹‹ተካበ እንዴት ለመመለስ ወሰነ?››
‹‹አላውቅም››
‹‹ከሁላችንም ጠንካራው እርሱ ነበር እኮ››
‹‹በጣም እንጂ››
‹‹ግን በምን ተስማምቶ ነው የተመለሰው?››
‹‹አይታወቅም››
‹‹እኛን እንዲህ ሲያስፈራራን››
‹‹ማለት?››
‹‹ሀሳባችንን ከቀየርን እንተላለቃለን እያለ...››
‹‹የሰው ነገር ይሄ እኮ ነው››
‹‹አሁን እሽ ምን እናድርግ?››
‹‹አላውቅም››
‹‹አላውቅም?››
‹‹ ወደ ሀገር ቤት ካልተመለስን እዚህ እስር ቤት መበስበሳችን ነው››

‹‹ምን አማራጭ አለን››

‹‹እኔ ከምመለስ እዚህ እስር ቤት ብሞት ይሻለኛል››

‹‹እኔም እንደዚሁ››

ሶስቱም የቆረጡ ይመስላል፡፡ግን እርግጠኛ አይደሉም፡፡ሁሉም ተካበ ላይ ነበር እምነታቸው፡፡ እዚህ እስር ቤት ብዙ ችግርና መከራ ደርሶባቸው እየመከረ፣ሞራል እየሰጠ፣አቋም እያስዘ ከዚያም አለፍ ሲል እንተላለቃለን እያለ እንደገናም ፖሊስ ሲያስቸግር እየደበደበ ለቡድኑ ጥላ ከለላ ሆኖ የቆየ እርሱ ነበር፡፡ አሁን ግን እነርሱ ምን አቋም እንዳላቸው ውስጣቸው ነው የሚያውቀው፡፡ለአፋቸው እንመለስም ይበሉ እንጂ ውስጣቸው ገና አልተረጋገጠም፡፡ፖሊሶቹና የደህንነት ሰዎች ከውጭ ራቅ ብለው እየጠበቋቸው ነው፡፡ተመካከረው አስበውበት ቶሎ መልሱን እንዲያሳውቋቸው ይሻሉ፡፡ሶስቱም የሆነ መልስ መስጠት አለባቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ሌላ እድል እንደማይኖራቸው ተነግሯቸዋል፡፡ከዚህ በኋላ እንደፍርደኛ እስረኛ እዚህ እንደሚበሰብሱ አሳውቀዋቸዋል፡፡ከዚህ በኋላ ለምንውም እንኳን እንመለስ ቢሉ እድል እንደማያገኙ ነግረዋቸዋል፡፡ከዚህ በኋላ አሁን የሚያገኙትን ምግብና ሌላም ነገር እንደማያገኙ አስረድተዋቸዋል፡፡ከዚህ በኋላ ምንም ነገር የለም፡፡ፖሊሶቹና ሶስቱ እስረኞች በርቀት እየተያዩ ነው፡፡ስአቱ አልቋል፡፡ ፖሊሶቹ ወደ እስረኞቹ ተንቀሳቀሱ፡፡የሆነ ሰው ውሃ ቀድቶ እየተመለሰ ነው፡፡

ፖሊሶቹ ሶስቱ እስረኞች ምን እንደወሰኑ ለማወቅ ወደ ክፍላቸው ለመሄድ ተንቀሳቀሱ ፡፡እዚህ ወህኒ ቤት የተለያዩ እስረኞች አሉ፡፡ሀገራቸውን ለእስራኤል ሲሰልሉ የተያዙ፣እንዋር ሳዳትን በመግደል ስራ ተሳትፈዋል በሚል የተፈረደባቸው ፡፡የሙስሊም ወንድማማች አባል ሆነው ለብዙ አመት ተፈርዶባቸው የታሰሩና ሌሎችም ይገኛሉ፡፡እዚህ እስር ቤት ውስጥ ሼኮች በብዛት አሉ፡፡ አብለጫው ሼኮች የሙስሊም ወንድማማች አባል ሆነው የታሰሩ ናቸው፡፡ብዙዎቹ እስረኞች ሼኮቹን ይፈራሉ፡፡እዛ ግቢ ሼኮች ያሉት ነገር የመጨረሻ ነው፡፡ፖሊሶችና የወህኒ አዛገሮች ሳይቀር እነዚህን ሼኮች በጣም ያከብራሉ፡፡ ሼኮቹ ለእነዚህ ተጫዋቾች ብዙ ድጋፍና ምክር





የሚለግሱ እንዲሁም ከፖሊስ ጥቃት የሚከላከሉላቸው ነበሩ፡፡ የከፋ ነገር ሲኖር ውጭ ላሉ ሚዲያዎች ልከው እያስጻፉ በግብጽ መንግስት ላይ ጫና እስከመፍጠር የደረሱ ናቸው፡፡በጥቅሉ ለእነዚህ ልጆች ጋሻና መከታ ናቸው፡፡ አሁንም ፖሊሶች ለምን እንደመጡ ስላወቁ ይሄን ማክሸፍ ነበረባቸው፡፡አንደኛው ሼክ ውሃ ለመቅዳት ወደ ቧንቧው ሄዱ፡ ቧንቧው የሚገኘው እስረኞች ካሉበት ክፍል መስኮቱ ስር ነው፡፡ሼኩ ውሃውን እየቀዱ መናገር ጀመሩ፡፡‹‹ሰማችሁ ልጆች›› አሉ

‹‹አቤት››

‹‹ወደ እኔ እንዳትመለከቱ››

‹‹እሺ››

‹‹እንተካበ እዚህ ናቸው››

‹‹የት? ››

‹‹እዛኛው ብሎክ ናቸው››

‹‹ምን እያደረጉ ነው?››

‹‹ፖሊሶች አፍነው ወስደዋቸዋል››

‹‹አልሄዱም ማለት ነው››

‹‹ወደ የት››

‹‹ወደ ሀገር ቤት››

‹‹አልሄዱም››

‹‹ እርግጠኛ እዚህ ናቸዋ!!!››

‹‹አዎ፡፡ እናንተም እንዳትስማሙ››

ልጆቹ ተደሰቱ፡፡ለካ ፖሊሶች ሸውደውናል ብለው አሰቡ፡፡ቅድም እንተካበን ሲኮንኑ የነበረውን ነገር አነሱ፡፡በኋላ ከርቀት እዛኛው ብሎክ አዩዋቸው፡፡እነዚህ ልጆች እንዴት ነው እዚህ ወህኒ ቤት የታሰሩት ?፡፡ ነገሩ ሲጀመር እንዲህ ነው

በግንቦት 1981 ወደ ካይሮ የግብጽን ብሄራዊ ቡድን ሊገጥም የሄደው ቡድን ከጨዋታው በኋላ 6 ተጨዋቾች ከቡድኑ ተለይተው ኮበለሉ፡፡የነኚህ ተጫዋቾች መጥፋት በህዝቡ ዘንድ ትልቅ መነጋገርያ ሆነ፡፡ከሁለት አመት በፊት ካይሮ ላይ ተጫዋቾች በመኮብለላቸው ሆነ፡፡ከሁለት አመት በፊት ካይሮ ላይ ተጫዋቾች በመኮብለላቸው ... ኢትዮጵያ ኢንተርናሽናል ውድድር ሙሉ ለሙሉ ዘጋች፡፡ከሀገር

መውጣት ተከለከለ፡፡ተጫዋቾች እንዳይኮበከልሉ ትልቅ ትምህርትና ምክር ተሰጥቶ ችግሩ መቀረፉ ተረጋግጦ መጥፋት ሳይሆን መጥፋትን ማሰብ እንዳይችሉ ተደርጎ ነው የተሰራው ተባለ፡፡ከአመት በፊት አዲስ አበባ ላይ በተደረገው የምስራቅና መካከለኛው የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ኢትዮጵያ ሻምፒዮና በመሆኗ ለስርአቱ ጀርባውን ሰጥቶ የነበረው ህዝቡ ከዳር እስከዳር ተደሰተ፡፡በፖለቲካው ሲጨቀጭቁት የነበረው ህዝብ አልሰማ ብሏቸው ዛሬ በኳስ አገኙት፡፡

በሜዳ ተገኝተው የነበሩት ኮለኔል መንግስቱ ተደስተው ለህዝቡ ‹‹በቅርቡ 100 ሺህ ተመልካች የሚይዝ ስታዲየም እናሰራለን››አሉ፡፡ተጫዋቾቹም በቤተመንግስት ተገኝተው ከሊቀመንበሩ እጅ ተሸለሙ፡፡ ሀገራቸውን ለማገልገል ቃል ገቡ፡፡ተጫዋቾቹ የገቡትን ቃልና አይነውሃቸውን አይተው ከእንግዲህ ስለማይጠፉ ከሀገር ወጥተው እንዲጫወቱ የታገደው የውጭ ሀገር ጉዞ እገዳ ተነሳ፡፡ቡድኑ ወደማላዊ ሄዶ ሲመለስ አንድም ተጨዋች አልኮበለለም፡፡የተሰጠው ምክርና ትምህርት ትልቅ ስራ መስራቱ ተረጋገጠ፡፡ግን ካይሮ ሄደው ቀልጠው ቀሩ፡፡ህዝቡ መነጋገርያ በማድረጉ መንግስት ነገሩ አስደነገጠው፡፡ተጫዋቾቹ የጠፉት ስርቱን ተቃውመው መሆኑ ስለተነገረ እነዚህን ልጆች እንደምንም አድርጎ ከካይሮ በማስመጣት የኮበለሉት በጸረ አብዮተኞች ተታለው መሆኑን እንዲናገሩ ማድረግ ነው፡፡ (ሻምበል ፍቅረ ስላሴ ወግደረስ እኛና አብዮቱ በተባለው መጽሀፍ ‹የእነ ተካበ መጥፋት ትልቅ ጫና ፈጥሮብን ነበር ማለታቸው ልብ ይሏል) መንግስት ከግብጽ ጋር አዲስ ግንኙነት ፈጥሮ ልጆቹን ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ እየተረባረበ ነው፡፡ የተጫዋቾቹ መጥፋት በአለም አቀፍ ሚዲያ በመነገሩና የተነገረበት መንገድ ስርአቱ ላይ ላይ ትልቅ ጫና ፈጠረ፡፡የግብጽ መንግስት ተጨዋቾቹን ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ ለኢትዮጵያ መንግስት ቃል ቢገባም አንጠልጥሎ ለማስረከብ ከውጭ ሚዲያ ጫና ደረሰበት፡፡ያለው እድል በራሳቸው ፈቃድ አስፈራርቶ አስደንብሮ አጨናንቆ መመለስ ነው፡፡





## እንደገና ወደ ኋላ

ከፌዴሬሽን የተወከሉት ፕሬዝዳንቱ ኮለኔል ጌታሁን ደሌሳና ጸሀፊው አቶ ካሳን ጨምሮ የመንግስት ሰዎች ቻርተር አውሮፕላን ይዘው ካይሮ ተገኝተዋል፡፡ አላማው አግባብተውና ለምነው ልጆቹ እንዲመለሱ ማድረግ ነው፡፡ ተጨዋቾቹን ለየብቻው ነው የሚያነጋግሯቸው፡፡ መጀመርያ የተጠራው ተካበ ነው፡፡ ተጣልቶ ተመለሰ፡፡ ቀጥሎ የሄደው ጌቱ ከበደ ነው፡፡የፌዴሬሽኑ አመራርና የተወከሉት ሰዎች እያነጋገሩት ነው፡፡ ‹‹እናትህን ትወዳለህ?››አሉት

‹‹እዎ››

‹‹ሀገርህን ትወዳለህ?››

‹‹እዎ››

‹‹ለምን ትጠፋለህ?››

‹‹እናንተን ስለማልወድ››

ከጌቱ ጋር የተደረገው ክርክር ጥሩ አልነበረም፡፡ ተጫዋቾቹ እንደብረት የጠነከረ አንድነት እንደገነቡ እየተነጋገሩ ነው፡፡ስለሞን ዮሀንስ(ቸርኬ) ተራው ደርሶ ሄደ፡፡ሰዎቹ አግባብተው ነገሩት፡፡ በክርክሩም አሳመኑት፡፡ ወደ ሀገር ቤት ለመሄድ ቃል ገባና ወደ ክፍሉ ተመለሰ፡፡ተመላሾች ምን እንደተነጋገሩ ከሰዎቹ ጋር ሲመለስ ቀሪዎቹ በጥያቄ ያጣድፉታል ፡፡ስለሞን እንደተመለሰ ከጌቱ ጋር እየተነጋገረ ነው፡፡ጌቱ‹‹እንዴት ነው?››አለ

‹‹ምኑ››

‹‹ምን ተባባላችሁ››

‹‹ጥሩ ነው››

‹‹ጥሩ ነው ማለት ምንድነው?››

‹‹ጥሩ ነዋ››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ተስማማሁ››

‹‹ምን ለማድረግ?››

‹‹ለመመለስ››

‹‹ወደየት?››

‹‹ወደ ሀገር ቤት››

‹‹አንተ!!!!››

‹‹አዎ››

‹‹ይሄ እኮ የእኛን ህይወት የሚበላሽ ነው››

‹‹ምን ላድርግ ታድያ››

‹‹ምን አልክ!!!!!››

‹‹ብቃ ለመመለስ ወስኛለሁ››

‹‹የት እንደምትሄድ ታውቃለህ?››

‹‹ማለት››

‹‹የወንዶች ሰፈር እኮ ነው የምትገባው››

‹‹የት?››

‹‹ስትመለስ››

‹‹እና››

‹‹በገጀራ እግርህ ነው የሚቆራረጡት››

‹‹ተው እንጂ!!!››

‹‹አንተ ከመመለስህ በፊት ወደ ሀገር ቤት ደብዳቤ እልካለሁ››

‹‹ምን ብለህ?››

‹‹ህይወታችንን አበላሽተህ እንደተመለስክ››

ሰለሞን ነገሩ አስደነገጠው፡፡ ሰፈር ውስጥ ድብድቦች ሁሌም አይጠፉም፡ ድብድቡ በጩቤ የታጀበና ማጠቃለያው ገጀራ የሚታከልበት ነው፡፡ እዚህ ሰፈር የሚደረገውን ድብድብ ስለሚያውቅ ሁሌም ያሰጋዋል፡፡የጌቱ ወንድም በራሱ ጩቤ ከኪሱ አይጠፋም፡፡ ሰለሞን እንደተመለሰ ጩቤ በሰውነቱ እንደሚሰካ ነው የተነገረው፡፡ ሰለሞን ማስላሰልም አልፈለገም ለመመለስ የነበረው ወሳኔ ቶሎ ሰረዘ፡

## እንደገና በድጋሚ ወደ ኋላ

ወደ አሜሪካ ኢምባሲ ስተት ብለው የገቡት ኮብላዮቹ ተጫዋቾች ሀላፊውን እየፈለጉ ነው፡፡ የስደተኞችን ጉዳይ ተጠሪ የሆነችው ሴት እያናገረቻቸው ነው፡፡ስለ ኮበለሉ ተጫዋቾች በሚዲያ ሰምታለች፡፡እነርሱ ጋር እንደሚመጡ ጠብቃለች፡፡ ማንነታቸውን እየተናገሩ ባለበት ግዜ‹‹ማንነታችሁን አውቀናል››አለች



‹‹ነው እንዴ!!!››

‹‹አዎ፡፡ ምን ፈለጋችሁ?››

‹‹ጥገኝነት ጥያቄ ነው››

‹‹ማለት ››

‹‹ወደ አሜሪካ ለመሄድ››

‹‹እኛ ሀገር››

‹‹አዎ››

‹‹ለምን አሜሪካንን መረጣችሁ››

‹‹ዲሞክራሲ ስላለ.....››

‹‹ነው እንዴ››

‹‹አዎ››

‹‹መጀመርያ የተባበሩት መንግስታት ቢሮ ትሄዳላችሁ››

‹‹እኛ እነርሱን አንፈልግም አሜሪካን መሄድ ነው››

‹‹እሱን ተስማምተናል››

‹‹እና››

‹‹እዚያ ሄዳችሁ ተመዝገቡ››

‹‹ከዚያስ!!››

‹‹ከተመዘገባችሁ በኋላ እኛ ጋር ትመጣላችሁ››

‹‹እንደዛ ነው አሰራሩ?››

‹‹አዎ››

‹‹እሽ ተመዝግበን እንመጣለን››

‹‹ግን››

‹‹ግን ምን?.....››

‹‹እነርሱ ጋር ስለተመዘገባችሁ ብቻ ወደ አሜሪካ አትሄዱም››

‹‹ሌላ ደግሞ ምን አለ?››

‹‹ዋናውን ነገር ማወቅ አላባችሁ››

‹‹ምን?››

‹‹ቃላችሁ አንድ መሆን አለበት››

‹‹ቃላችንማ አንድ ስለሆን ነው እዚህ የመጣነው››

‹‹እንደርሱ አይደለም››

‹‹እና››

‹‹ከመሀላችሁ አንድ ሰው ሀሳቡን ከቀየረ ጉዳዩ ያከትማል››

‹‹ማንም ሀሳቡን አይቀይርም››

‹‹እርግጠኛ ናችሁ?››

‹‹እንደብረት የጠነከረ አንድነትና መተሳሰብ ያለን ነን››

‹‹አንድ ከሆናችሁ በቃ አሜሪካ ገባችሁ››

‹‹ሌላ ችግር ግን የለም አይደል?››

‹‹ብቃ አንድ ሀሳብ ብቻ ይኑራችሁ››

‹‹እሱን ለእኛ ተይው››

‹‹አሁን እዛ ሂዱ ፤ሀሳቡን የቀየረ ሰው ካለ እኛ ጋር እንዳትመጡ ፋይላችሁ ይዘጋል››

‹‹ችግር የለም››

ሁሉም ተያይዘው ወደተባበሩት መንግስታት ቢሮ ሄደው ተመዘገቡ፡፡መመዝገብ ብቻ ሳይሆን ማረፊያ ሆቴልም ያዙላቸው፡፡ የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ሀላፊዎቹ ወደ አዲስ አበባ አልተመለሱም፡፡ፖሊስና የደህነት ሰዎች አግባብቶና አባብለው፤ ካልሆነም አስገድደው ተጫዋቾቹን ሊሰጧቸው ቃል ስለገቡላቸው እየጠበቁ ነው፡፡ከአዲስ አበባ የሀገሪቱ መሪ ሳይቀር ትልልቅ ባለስልጣኖች ተጨዋቾቹ ተስማምተውም ሆነ ተይዘውም እንዲመጡላቸው እየጠበቁ ነው፡፡ የአሜሪካ ኤምባሲ ሀላፊዋ ወስዳ ለተባበሩት መንግስታት ተጠሪዎች አስረክባለች፡፡ ግን የሀገር ውስጥ ደህንነት አልመዘግባቸውም አለ፡፡የሀገር ውስጥ ደህነት ካለመዘገበ ደግሞ ችግር ነው፡፡ምክንያቱ ደግሞ ያልመዘገበው ወደ ሀገር ቤት አፍስው ሊወስዷቸው ይፈልጋሉ ማለት ነው፡፡ በዚህ የተነሳ ተጫዋቾቹ ደነገጡ፡፡ የተባበሩት መንግስታት ሰዎች ተጨዋቾቹን ወደ ሆቴል ወስደው አሳረፉዋቸው፡፡ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ አልወሰዳቸውም፡፡ልጆቹ ጠዋት ከመኝታ ሲነሱ ሆቴሉ በፖሊስ ተከቧል፡፡ሰለሞን ሀይሌ ከፎቅ ላይ በመስኮት ሊዘል ሲል እንተካበ ያዙት፡፡ፖሊሶቹ የመጡት እንደጠረጠሩት አስረዋቸው ወደ ሀገር ቤት ሊመልሱ እንደሆነ አውቀዋል፡፡





ፖሊሶቹ ወደ ውስጥ ገቡ ፡፡ከተጨዋቾቹ ጋር ተያዩ፡፡ ወታደሮቹ ብዛት አላቸው፡፡ በዚያ ላይ ግብዳ ናቸው፡፡ ወደ እነርሱ ተጠጉ፡፡ በቃ እንጠልጥለው ሊወስዷቸው ነው፡፡ሰለሞን ገና እንዳያቸው ለምን እንደመጡ አውቋል ፡፡ከፎቅ ዘሎ ቢወድቅ ምን እንደሚሆን ያውቃል፡፡ ወደ ሀገር ቤት ከተመለሰ እንደሚገደል ስላወቀ ይሄ ከመሆኑ በፊት እዚሁ ሊሰናበት ነው የመረጠው፡፡፡ሆኖም ጓደኞቹ አትርፈውታል፡፡ግን ተረፈ ለማለት ያስቸግራል፡፡አዲስ አበባ ያለው አመራር ሲመለሱ ሊቦጫጭቃቸው እንደተዘጋጀ አልጠፋውም፡፡ ፖሊሶቹ በከበባ መልክ ሲጠጓቸው ነገሩ እንዳበቃለት አውቀዋል፡፡ፊት ለፊት ተገናኙ፡፡ ተጫዋቾቹ‹‹ምን ልታደርጉን ነው?››አሉ

‹‹ማን››

‹‹እናንተ››

‹‹ምን አደረግን››

‹‹እኛን ለመያዝ ነው?››

‹‹እረ አይደለም››

‹‹ታድያ ለምን ብዙ ሆናችሁ እዚህ መጣችሁ?››

‹‹ተረጋጉ እንጂ››

‹‹ እንዴት እንረጋጋ ከባችሁን››

‹‹ለምን እንደመጣን ታውቃላችሁ?››

‹‹ልትይዙን ነዋ››

‹‹እነደርሱ አይደለም››

‹‹እና››

‹‹እናንተን ልንጠብቅ ነው››

‹‹ለምንድነው የትምጠብቁን?››

‹‹አንድ ነገር ብትሆኑብን እኛ ነን የምንጠየቀው››

‹‹እየሸወዳችሁን ነው››

‹‹እንደዛ አታስቡ፤ግን...››

‹‹ግን ምን?››

‹‹ቁርስ በልታችኋል››

‹‹ሰቀቀን ውስጥ አስገብታችሁን እንዴት ቁርስ እንበላለን››

ፖሊሶቹ ‹‹ተረጋጉ እኛ የመጣነው የእናተን ደህንነት ለመጠበቅ ነው›› በሚል በድጋሚ አስረድተዋቸው ወደ ቁርስ መመገቢያ ቦታ ወሰዷቸው፡፡ቁርስ አብልተው በደምብ ተንከባክበው ካስተናገዱ በኋላ ሀላፊው›› እንዴት ነው ምግቡ?››አላቸው

‹‹ጥሩ ነው››

‹‹የግብጽ ፖሊስ እንዲህ ነን››

‹‹ማለት?››

‹‹እንግዶቻችንን በደምብ እንንከባከባለን››

‹‹ነው እንዴ!!››

‹‹አዎ ፤ቅድም ግን ፈርታችሁን ነበር አይደል››

‹‹አዎ አመጣጣችሁ….››

‹‹እኛ ሰላማዊ ነን››

‹‹እኛም እንደርሱ ብትሆኑ ነው የምንመርጠው››

‹‹አሁን አንድ ነገር ልንነግራችሁ እንወዳለን››

‹‹ምን››

‹‹እናንተ በሀገር ውስጥ ደህንነት አልተመዘገባችሁም››

‹‹አልመዘግብም ስላሉን ነው››

‹‹ስለዚህ ከተማ ውስጥ መዘዋወር አትችሉም››

‹‹እና››

‹‹እኛ ለእናንተ በማዘን ከከተማ ወጣ ያለ ጥሩ ሆቴል እንስቀምጣችኋለን››

‹‹እንደዛ ይሻላል ማለት ነው?››

‹‹አዎ እኛ ደግሞ ከእናንተ ጎን ነን››

‹‹እርግጠኛ ናችሁ?››

‹‹አዎ እመኑን ››

‹‹እንዴት እንመን››

‹‹ብዙ ግዜ ከኢትዮጵያ ተጫዋች እዚህ በኮበለለ ግዜ ወደ አሜሪካ ያሻገርነው እኛ ነን››

‹‹እንደዛ ነው››

‹‹አዎ፤አሁን ደግሞ ቁርስ ጋብዘናችኋል››

‹‹እና››

‹‹በኋላ ደግሞ አሪፍ ምሳ እንዲዘጋጅ አዘናል››





ኮብላዮቹ ፖሊሶቹን ባያምኑም አሁን ግን ስለተንከባከቡዋቸው የሚሉትን ለመፈጸም ተዘጋጁ ፡፡ደግሞም በእርግጥ እንደተናገሩት ብዙ የኢትዮጵያ ስፖርተኞች ካይሮ ጠፍተው ወደ አሜሪካ ተልከዋል፡፡ የፖሊሱ ሀላፊ እነዚህንም ተንከባክቦ ወደ አሜሪካ እንደሚልክ ስላወቁ የሚሉትን ለማድረግ ተስማሙ፡፡ ፖሊስ ሁሉንም ኮብላይ በፖሊስ መኪና ጭነው መሄድ ጀመሩ፡፡ይሄን መንገድ ያውቁታል፡፡ወደ ኤርፖርት የሚወስደው መንገድ ይመስላል፡፡እንደዚህ ከሆነ አግተው በግድ እንጠልጥለው ሊወስዷቸው ነው፡፡ተጫዋቾቹ መንጫጫት ጀመሩ ፡፡እዛው ግብ ግብ ያዙ፡፡

ነገር ግን ፖሊሶቹ መንገዱን በደምብ አሳዩዋቸው፡፡ቦታውን አጣርተው ከተማመኑ በኋላ ከከተማው ወጣ ወዳለው አሪፍ ወደተባለው ሆቴል መሄድ ጀመሩ፡፡ ሆቴሉ ጥሩ መሆኑን እነርሱም እንደሚወዱት ማንም መጥቶ እንደማያናግራቸው አስረዱዋቸው፡፡ ተጫዋቾቹ የቡድኑ ሰዎች እዚህ ከተማ እየፈለጉና እያሰሱ በመሆኑ ከእነሱም መራቅ በመፈለጋቸው ከከተማ ወጣ ያለውን ሆቴል ወደውታል፡፡መኪናው አንድ ትልቅ ግቢ በር ላይ ቆመ፡፡ ምን አይነት ሆቴል ይሆን እያሉ በመደመም ላይ ናቸው፡፡ከመኪና ወረዱ ፡፡ወደ ውስጥ እንዲገቡ ተጠየቁ፡፡ሌሎች ፖሊሶች በብዛት ሆነው እየጠበቁ ነው፡፡ተጫዋቾቹ ወደ ታዋቂው ሆቴል እንዲገቡ ተነገራቸው፡፡የዋናው በር እንዳለፉ ግራ ተጋቡ‹‹ምንድነው ይሄ?››አሉ

‹‹ምኑ!!!››

‹‹ቦታው››

‹‹ለእናንተ ጥሩ ማረፍያ ነው››

‹‹ምን እያደረጋችሁ ነው?››

‹‹ዝም ብላችሁ ግቡ››

አሁን የዋናው ግቢ በር አቋርጠው የገቡት ሆቴል አይደለም፡፡ በግብጽ ትልቁ ወህኒ ቤት ነው፡፡ግቢው በር ላይ ሆነው አንገባም አሉ፡፡ ግብ ግብ ተፈጠረ፡፡ ሀይለኛ ድብድብ ተከተለ፡፡ እነርሱ ላለመግባት ግን ፖሊሶች ለማስገባት የዋንጫ በሚመስል ሁኔታ ሲደባደቡ ተጫዋቾቹን ወደ ሀገሩ ተጫዋቾቹ አልቻሉም፡፡የአሜሪካ ኤምባሲ

ሲወስዳቸው ተስማምቷል።የእነርሱን ጉዳይ እንደራሱ ዜጎች ነው የያዘው።ነገር ግን ሴትየዋ እንደጠረጠረችው በተፈጠረው ስህተት ተጨዋቾቹ እስር ቤት ገቡ።ገና ከጅምሩ ሴትየዋ‹‹..እኛ እናትን ለመቀበል ችግር የለብንም ነገር ግን ከመሀላችሁ አንድ ሰው ሀሳቡን ከቀየረ ኤምባሲው የእናንተን ስም ከዚህ ሊስት ላይ ይሰርዛል›› ብላ ነግራቻቸው ነበር።ነገር ግን የፌዴሬሽኑ ሰዎች እያንዳንዱን ተጫዋቾች ጠርተው ሲያናግሩ አንድ ተጫዋች ለመመለስ ተስማምቶ በመጨረሱና ልጁም ወደ ሀገር ቤት በመሄዱ የአሜሪካ የኤምባሲ እጁን በማንሳቱ ተጨዋቾቹ የሚወስዳቸው ማጣት ብቻ ሳይሆን የሚከራከርላቸው ባለማግኘታቸው ወደ እስር ቤት ተወረወሩ። ‹ፖሊሶችም እዛው አጨናንቀው ወደ ሀገር ቤት በፍቃዳችን እንመለሳለን ብለው አስፈርመው ሊልኳቸው አዘጋጁ።

## እንደገና በመጨረሻ

ከዚህ እስር ቤት ወጥተው ወደሚፈልጉበት ሀገር ካልላኩዋቸው እራሳቸውን በምግብ ጎድተው ለመሞት እንደተዘጋጁ አሳወቁ።ይሄን ውሳኔ ለወህኒ ቤቱ አለቃ ካሳወቁ በኋላ የረሀብ አድማ ጀመሩ።ምግብ ሲመጣላቸው እየመለሱ የረሀብ አድማውም አጠናከሩት።በአራተኛው ቀን ቤቱ ውስጥ ጩኸት ተሰማ‹‹ወይኔ ወንድሜ……ወይኔ ወንድሜ!!!!!››የሚል ዋይታና እሪታ በክፍሉ ውስጥ በረከተ። ፖሊሶችና እስረኞች ድምጽ ወደሰሙበት ክፍል እየሮጡ ገቡ።አንድ ሰው ወድቆ ይንፈራፈራል።ሰለሞን ሀይሌ ነው። መንፈራፈር ብቻ ሳይሆን አረፋ ደፍቆና በአፉ ሞልቶ ነፍሱ ልትወጣ ጥግ እንደደረሰ ያሳያል። ፖሊሶቹ አንከብክበው ወደ ህክምና ቦታ ወሰዱት።ሼኮቹ ወሬውን ለሚዲያ አሳልፈው ሰጡ ።እነዚህ ልጆች እዚህ ከሞቱ የግብጽ መንግስት የሚደርስበት አለም አቀፍ ተቃውሞ ስላሰጋው በቶሎ ለተባበሩት መንግስታት ሰዎች አሳወቁ ።እነርሱም በፍጥነት መጥተው እነዚህ ሰበበኞች ጉድ ሊያደርጉን ነው ብለው ከእስር ወጥተው ወደሌላ ሀገር እንዲዛወሩ ወሰኑ።ሰዎቹ አስፈራርተው ችግር ውስጥ ሲገቡ ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ በሚል ነው በወህኒ እንዲቆዩ የተደረገው ።ነገር ግን ሀገራችን ከምንመለስ





እዚሁ ብንሞት ይሻላል ብለው እንደወሰኑ ስለገባቸው ወዲውኑ ወደ ሜክሲኮ ላኳቸው።ከሜክሲኮ ቤሊዝ ወደተባለው ሀገር ገቡ።ቤሊዝ በጓቲማላና በሜክሲኪ መካከል የምትገኝ ናት።እዚህ ከተማ እንደገቡ የተባበሩት መንግስታት ይሰጥ የነበረውን አበል አቆመ።አሁን ችግር ውስጥ እየገቡ ነው። ጉሮሮን ለመሸፈን በፋብሪካ ተቀጥረው መስራት ጀመሩ።አላማቸው እዚህ ለመኖር ሳይሆን ወደ አሜሪካ ተጉዘው ለመማርና ለመስራት ነበር።ነገር ግን አጉል ቦታ ተገኙ።በጣም ተጨነቁ።

ዶክተር ሳለ የሱፍ በአሜሪካ አላባማ ዩንቨርስቲ በሀላፊነት ቦታ ይሰራል። ።ብዙ ኢትዮጵያውያን ተጫዋቾች ካሉበት አፈላልጎ በዩንቨርስቲው ወረቀት ወደ አሜሪካ እያስመጣ ያስተምራል ። እነርሱም በምላሹ ለዩንቨርስቲው እንዲጫወቱ ያደርጋል።አንዳንዶቹ ወደ ኮሌጁ ገብተው ትምህርቱንም ሳያጋምሱ እየወጡ ቡድኑን እንጉዱት ነው ። በእነርሱ ተስፋ ይቆርጥና ምንም ቢሆን ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ይልቅ ለሀበሾቹ ቅድሚያ ይሰጣል።ዶክተር የሱፍ የተወለደው ሀረር ነው። አልፎ አልፎ ወደ ሀገር ቤት ይመጣል።ጥሩ ተጫዋቾች ማን እንደሆነ የሚጠቁምለትና የሚመለምለት የመብራት ደጋፊ የሆነው አሚር ነው። ጎበዝ ተጫዋቾች ቢገኝም ትልቁ ችግር የሚሆነው ተጫዋቾቹን ከአዲስ አበባ ማውጣቱ ላይ ነው።ዶክተር ሳላ ተካበን ብዙ ግዜ ለመውሰድ ይፈልግና በምንም መንገድ አልተሳካለትም።ዘንድሮ ለኮሌጁ ቡድን አጥቂና ግብ ጠባቂ ስለፈለገ ወደ አሚር ጋር ደወለ‹‹አሚር››አለ

‹‹አቤት››

‹‹ ጥሩ ተጫዋች አለ?››

‹‹ምን አይነት…››

‹‹አጥቂ፤በረኛ…››

‹‹ጣጣውን የጨረሰ አለልህ አይደል!!››

‹‹ምን አይነት››

‹‹ከሀገር የወጡ››

‹‹እነማን?››

‹‹እነተካ››

‹‹ተካበ!!!!››

‹‹አዎ››

‹‹እርግጠኛ ነህ ተካበ.....››

‹‹መቶ ፐርሰንት››

‹‹የት ነው ያሉት››

‹‹ግብጽ››

‹‹መቼ››

‹‹ቆየ እኮ››

ጣጣውን የጨረሰ ማለት ከኢትዮጵያ ወጥቶ በሆነ አፍሪካ ሀገር የተቀመጠ ማለት ነው፡፡አዲስ አበባ ካለ ግን ከሀገር ለማውጣት ጣጣ አለው ፡፡ዶክተር ሳለ በፍጥነት ወደ ካይሮ ሄደ ግን አልተሳካለትም ፡፡እንተካበን ያልፈለገበት ቦታ የለም፡፡ስደተኞች ይገኙበታል በተባለ ቦታ ፈለገ ፡፡ሊያገኛቸው ስላልቻለ ተመለሰ፡፡ ተጫዋቾቹ ስደተኞች በሚገኙባቸው ቦታ አልነበሩም፡፡በወህኒ ቤት ስምንት ወር ስለተዘጋባቸው ሊገናኙ አልቻሉም፡፡ጌቱ ከበደ ብዙ እቃ ጠፍቶበታል ፡፡ግን አንድ ወረቀት ከእሱ አልለይም አይነት ከልብስ ወደሌላ ልብስ ትመላለሳለች፡፡ ወረቀቱ ለረጅም ግዜ በኪሱ ከመቆየቱ ተነሳ መጨማደድ ጀምሯል፡፡ አንድ ቀን ይሄ ወረቀት ምንድነው ብሎ ሲከፍተው የዶክተር ሳላ ስልክ ነው ፡፡አዲስ አበባ የነበረው ጓደኛው ከመሄዱ በፊት ድንገት መኩብለሉ ከቀናህ የዶክተር ሳላ ስልክ ይሄውልህ ብሎ ሰጠው፡፡ ብዙ ግዜ ይሄን ስልክ ፈልጎ ስላጣው ተስፋ ቆርጦ ነበር፡፡አሁን ግን ከኪሱ እንዳገኘ ደስ ብሎት ‹‹ተካበ!!!!››ብሎ ተጠራ

‹‹አቤት››

‹‹የዶክተር ሳለን ስልክ አገኘሁ እኮ››

‹‹እስከ ዛሬ የት ነበር?››

‹‹ኪሴ ውስጥ ተደብቆ ነው››

‹‹እና››

‹‹ልደውልለት እንዴ?››

‹‹ትግባባዋለህ?››

‹‹እረ እንተዋወቅም››





‹‹ምን ልትለው ነው››

‹‹እንዲወስድን እንጠይቀዋለሁ››

‹‹እሽ ይለናል?››

‹‹እንሞክራ!!››

አሜሪካ ወደሚገኘው ዶክተር ሳለ ቤት ደወለ፡፡ባለቤቱ ነው ያነሳችው፡፡ ሳለ እዚህ እንደሌለና ሰሞኑን እንደሚመጣ ነገረችው፡፡ አቀባበሏ ቀዝቀዝ ያለበት መሰለው፡፡ብዙ ሰው ውስደን እያለ ስለሚያስቸግረው አሁን የደወለው ከእነዚህ አስቸጋሪዎች አንዱ ሊመስላት ይችላል፡፡ ጌቱ ማንነታቸውን ነግሮ ተሰናበተ፡፡ዶክተር ሳለ ወደ ቤት ሲመጣ ተነገረው፡፡ ስልክ ባለማስቀመጣቸው ተናደደ፡፡የት ሀገር እንደሚገኙ እንኳን አልተናገሩም፡፡እንተካበ ነገሩን ተውት፡፡ እንዳውም ሳላ እዛው ቤት ውስጥ ሆኖ ለማናገር እንዳልፈለገ ነው የገባቸው፡፡እናም ነገሩን ትተው እዛው ቤሊዝ ስራ እየሰሩ ቆዩ፡፡ አራት ወር፤ ስድስት ወር፤ ስምንት ወር.... አመት እንዲህ እያሉ ነቀሪነታቸውን እየቀጠሉ ነበር፡፡እዚህ መሆኑ ስለቻቸው፡፡የመጨረሻ ሙከራ በሚል ጌቱ ወደ ሳላ ቤት ደወለ፡፡ዶክተር ሳላ ገና ድምጹን እንደሰማ የስድብ አይነት አወረደበት፡፡ጌቱ ደነገጠ፡፡ ዶክተሩ በንዴት ‹‹ምን ነካችሁ?››አለ

‹‹ምን አደረግን››

‹‹እንዴት ያላችሁበትን አትናገሩም››

‹‹የታወቀ መስሎን ነው››

‹‹ባለፈው ደውለህ ለምን ስልካችሁን አላስቀመጣችሁም››

‹‹ረስተን ነው››

‹‹አሁን የት ነው ያላችሁት?››

‹‹ቤሊዝ ነው››

‹‹በሁለት ቀን ጠበቁኝ መጣለሁ››

‹‹በሁለት ቀን!!!!!››

‹‹አዎ ዶክመንታችሁን ይዛችሁ ተዘጋጁና ጠብቁ››

ጌቱ ግራ ተጋባ፡፡ ለአመት ያህል እዚህ ተቀምጠው ብዙ ሙከራ አድርገው ያልተሳካለቸው ይሄ ሰው እንዴት እንዲህ

ይዋሽናል ብሎ ደመደመ፡፡ ደምድሞ አላስቀረውም፡፡ ተካበን አገኘው ‹‹ሰውየውን እኮ አገኘሁት››አለ

‹‹ማንን››

‹‹ዶክተር ሳላን››

‹‹ምን አለህ?››

‹‹ባክህ አታላይ ነገር ነው››

‹‹እንዴት››

‹‹በሁለት ቀን መጥቼ እወስዳችኋለሁ አለ››

‹‹እንዴት አድርጎ››

‹‹ምናውቅለታለሁ››

‹‹ያውም እሱ እዚህ ሊመጣ!!!››

‹‹ባክህ ውሸቱን የማይሆን ተስፋ ሊሰጠን ነው››

ብዙ ጓደኞቻቸው ወረቀት ከአሜሪካ ልከውላቸው መውጣት ስላልቻሉ ተስፋ ቆርጠው ሰውየው በሁለት ቀን መጥቼ ይዣችሁ ሄዳለሁ ሲል እንደአታላይ ነው የቆጠሩት ግን ባለው ግዜ መጣ፡፡ በፍጥነት ይዟቸው ወደ አሜሪካ ሲወስዳቸው ማመን ነው ያቃታቸው፤ግን ሆነ፡፡እናም ሰለሞን ዮሀንስ ብቻ እዛው ሲቀር አራቱ ግን አሜሪካ ገብተው ኑሯቸውን እዛው አድርገዋል፡፡





ምዕራፍ 14

# አደፍርስ ተሾመ

በአዲስ አበባ ስታዲየም የተገኘው ተመልካች ይሄን የዋንጫ ጨዋታ ለማየት ከሌሊት ጀምሮ ሰልፍ በመያዝ ቀኑን ሙሉ እዚህ ጨዋታ ለማየት ከሌሊት ጀምሮ... ታጭቆ ነው የዋለው፡፡ዘመኑ 1978 ነው፡ለፍጻሜ የቀረቡት ቡናና ጊዮርጊስ ናቸው፡፡ቡና በኢትዮጵያ ደረጃ በፍጻሜ ጨዋታ ላይ ሲገኝ የመጀመርያው ነው፡፡በፌዴሬሽኑ ውድድር ከተመዘገበ ገና 3 አመት ቢሆንም በአስደናቂ ፍጥነት ከነባሮቹ ተሽሎ በፍጻሜ ውድድር ላይ ለመገኘት በቅቷል፡፡በስታዲየሙ የነበረው በርካታው ደጋፊ የጊዮርጊስ ነው፡፡በሜዳ ላይ ግን ሁለቱም እኩል የብቃት ደረጃ ነው የያዙት፡፡ በማጥቃቱ በኩል ከጊዮርጊስ ሙሉጌታ ከበደና ገብረመድን ሀይሌ ሲመሩት ከቡና ደግሞ ሙሉጌታ ወልደየስና ሚሊዮን በጋሻው ፊታውራሪ ናቸው፡፡ በሁለቱም ወገን ያሉት እነዚህ አራቱም ተጫዋቾች ለብሄራዊ ወጣት ቡድን ወሳኝ ናቸው፡፡

በዛሬው ጨዋታ ሁለት ተጫዋቾች ከባድ ፍልሚያ ውስጥ እንደሚገቡ ይጠበቃል፡፡ የጊዮርጊስ ደጋፊ ከሙሉጌታ ከበደ ጎል ይጠብቃል፤ በቡና በኩል ደግሞ ተሾመ ተፈራ ሙሉጌታን ሳያነቃንቅ ማቆም እንዳለበት ያውቃሉ፡፡ የቡና ተጫዋቾች ለማሟሟቅ ወደ መልበሻ ክፍል እንደገቡ አሰልጣኙ ተሾመን ጠርተው ‹‹ተዘጋጅተሃል?›› አሉት

‹‹እም››

‹‹ሙሉጌታ ለሰከንድም ቢሆን ከአይንህ እንዳይጠፋ››

‹‹እጠብቀዋለሁ››

‹‹ደጋፊው ቢጮህም ከምንም አትቁጠር››

‹‹ችግር የለም››

‹‹ኳስ ይዞ ከመዞሩ በፊት ነው የምትገባበት››

‹‹እድል አልሰጠውም››

‹‹ሊተናኮልህ ይፈልጋል››

‹‹እንዴት ማለት?››

‹‹በዳኛ ለማስቀጣት››

‹‹ጠብቂው ኳስ ብቻ ነው የምጫወተው››

‹‹ሙሉጌታ ኳስ ማግባት ቀርቶ ከሞከረ አንተ ነህ ተጠያቂ››

‹‹እሱን ለኔ ተወው››

ሙሉጌታ ከሚቸገርበት ተከላካዮች አንዱ ተሾመ ተፈራ (ውቃው) ነው። ወደ ቡና ከመግባቱ በፊት በነበረበት ክለብ አጥቂ በመሆኑ የአጥቂን ባህሪ በደምብ ያውቃል። ለዚህም ነው ብዙ አጥቂዎች አልፈውት ለመሄድ የሚቸገሩት። በቴክኒክም በዱላም በሁለቱም መንገድ ማቆም አይቸግረውም።ዛሬ ተመልካቹ የተሾመና የሙሉጌታን ፍልሚያ ለማየት ቀዳሚ ነገር አድርጓል። አይኖች ሁሉ እዛ ቦታ በብዛት ያፈጣሉ።ተሾመ ለፍልሚው ለመዘጋጀት ትጥቁን ማድረግ ጀመረ።ጫማውን ከማድረጉ በፊት ካልሲው ይቀድማል። ከካልሲው በፊት ደግሞ ባንዴጅ በእግሮቹ ዙርያ ይጠመጥማል። በተለይ ውስጥ እግሩን በደምብ እንዲይዝለት ደርቦና አጥብቆ ያስረዋል።ባንዴጁን ከመጠምጠሙ በፊት የውስጥ እግሩን ተመለከተው።

የጠቆረውን ቦታ አየው።የታሪክ አሻራ እዚህ ቦታ እንደማህተም ታትሞ እንደቀረ ተመለከተ።ሁሌም ጫማውን ሲያወልቅና ሲያደርግ ይመለከተዋል።የሚመለከተው መመልከት ፈልጎ አይደለም ።የውስጥ እግሩ ስሜቱን ይጠራዋል።ዛሬ ይሄ እግር እዚህ ፍጻሜ ጨዋታ ላይ የተገኘው በተአምር ነው።ይሄ ጉድ በጫማ ተሸፍኖ እንጂ ሰዎች ሊመለከቱት የሚችሉት እግር አልነበረም።በግርፋት እሳሩን የበላ እግር ነበር።ገራፊዎቹ እስኪቆረጥ ወይም እስኪበጠስ ነበር የሚገርፉት።ዛሬ ከግርፍያው የተረፈው እግር ነው ሙሉጌታ ከበደን ለማቆም ወደ ሜዳ የሚገባው።ማን ያውቃል ይሄኔ ከገራፊዎቹ አንዱ እዚህ ሜዳ ለመመልከት መጥቶ ሊሆን ይችላል።በተለይ አንድ ምሽት የደረሰበትን ግርፍያ መፈጠሩን እስኪጠላ ነበር የጠበጠበቡት።ገራፊዎቹ በገመድ አየር ላይ አንጠልጥለውት የመጨረሻውን ነገር የጠየቁትን አይረሳውም።ነገሩ ሲጀመር እንዲህ ነበር ።





ተፈላጊው ሰው እየታደነ ቢሆንም ከሰፈር ሰፈር እየተሹለከለከ መደበቁን ቀጥሏል። እስከመቼ እንደሚደበቅ ባያውቅም እስኪይዙት አድራሻውን ማጥፋት እንዳለበት አምኗል።መደበቂያ ቦታዎቹ እየተባነነባቸው እንደሆን ያውቃል።ከአንዱ ቤት አንዱ ቤት እየተደበቀ ውሎ ምሽት ላይ ወደ ማደርያው ተደብቆ ገብቶ ያሳልፍና ሌሊት ወጥቶ መደበቅያ ፍለጋ ይሄዳል።አንድ ቀን ግን እንደሚይዙት አልጠፋውም። ጓደኞቹ ተይዘው በግርፋት አሳራቸውን እያዩ እንደሆን ሰምቷል።ሌሎቹ ለግድያ እንደተወሰዱ አውቋል።አንድ ቀን በጠቋሚዎች ካለበት እንዳይያዝ ነው የሰጋው።ግን በህይወት እስካለ ድረስ መሹለክለኩን ይቀጥላል።

ድንገት አንድ ቀን ከአብዮት ጥበቃዎች ጋር ፊት ለፊት ተገናኘ፣ ተጠቁመው እንደመጡ አውቋል። እዚህ ቦታ መገኘት እንደሌለበት የተረዳው አሁን ነው። ግን እንዴት አገኙኝ ብሎ ለራሱ እየጠየቀ ነው።ጥያቄው መልስ የለውም። ደግሞም ምንም ጥያቄም መልስም አያስፈልገውም። ዛሬ እጃቸው መግባቱን አውቋል። ማምለጥ ቢፈልግም ቢሮጥ ተኩሰው ይገሉታል ።ደግሞም ሮጦ ቢሄድ አባረው ሊደርሱበት ይችላሉ። አማራጮቹ ሁሉ እንደተሟጠጡበት አውቋል። አሁን ያለው እድል ጓደኞቹን ተቀላቅሎ የሚመጣውን ሁሉ መቀበል ነው።አብዮት ጥበቃዎቹ ወደ እርሱ እየተጠጉ መጡ።እንዳላየ በመሆን ፊቱን አዙሮ ለመደበቅ እየሞከረ ነው። አንደኛው አብዮት ጥበቃ ‹‹ተሾመ›› ብሎ ጠራው።

‹‹አቤት››

‹‹ሰላም ነህ?››

‹‹ሰላም ነኝ››

‹‹ስንፈልግህ ነበር እኮ››

‹‹እኔን?››

‹‹እዎ››

‹‹አለሁ የት እሄዳለሁ››

‹‹ብዙ ቦታ ፈልገንህ እዚህ መኖርህን ነገሩን››

‹‹እነማን?››

‹‹ጓደኞችህ››

‹‹እኔማ እዚህ አልጠፋም እኮ››

‹‹እንዲህ ጥፍት ትልብናለህ?››

ሰዎቹ መሳርያ አለመያዛቸውን አረጋገጠ፡፡ለዚህም ነው በእርጋታና በዘዴ የሚያነጋግሩት ፡፡ቢይዙ ኖሮ በቁጣ እየጮሁበት እያጣደፉና እየከተከቱ ነበር የሚወስዱኝም ብሎ አሰበ፡፡እናም መሳርያ ስላልያዙ ሮጦ ለማምለጥ አሰበ፡፡ማሰብ ብቻ ሳይሆን ተዘጋጀ፡፡ መዘጋጀቱ የምር ሆነ፡፡ከሮጠ እንደማይደርሱበት ያውቃል፡፡በቀበሌው ቡድን ውስጥ ወሳኝ አጥቂ ነው፡፡ አምልጦ ከሮጠ ተከላካዮች አይደርሱበትም፡፡መሮጡና ማምለጡ ብቻ ሳይሆን በየትና በምን ቦታ አሰባብሮ የት መድረስ እንዳለበት በአእምሮው ሁሉን ነገር አዘጋጅቷል፡፡

አሁን የሚቀረው በተጀመረው ወሬ መሀል ፈትለክ ብሎ መሄድ ነው፡፡ይሄን እድል ካመለጠው እንደሚቆጨው አውቋል፡፡እናም እንዳይቆጨው አሁኑኑ በውሳኔው ጸንቶ ወደ ተግባር መግባት አለበት፡፡ለመሮጥ ተዘጋጀ በውስጡ መቁጠር ጀመረ ‹‹ተሼ!!!! ተዘጋጅ!!!›› አለ፡፡ ከ1 እስከ 3 ይቆጥርና መሮጥ ይጀምራል‹‹ ተዘጋጅ!!!1......2....››ድንገት 3 ሲል ሲል ወሬ ተጀመረ ‹‹ለዋንጫ ማለፋችንን ታውቃለህ?››አለው

‹‹ማን?››

‹‹የእኛ ቡድን››

‹‹የቀበሌው?››

‹‹አይደለም››

‹‹እና››

‹‹የአብዮት ጥበቃ ቡድን››

‹‹እውነታችሁን ነው››

‹‹ምኑ?››

‹‹ዋንጫ መድረሳችሁ››

‹‹እየቀለድክ ነው››

‹‹እኔ እኮ ትምህርት ቤት ጥናት ስለበዛብኝ አልተከታተልኩም››

‹‹ብቻ !! ለዋንጫ ደርሰናል››

‹‹በጣም ደስ ይላል››





ተሾመ አዘናግተው ሲይዙት እንደፈለጉ ገምቷል፡፡ በምንም መንገድ ለሰላማዊ ጉዳይ እንዳልመጡ ገብቶታል፡፡ቅድም ያቋረጠውን ሩጫ ዝግጅት መቀጠል አለበት፡፡ አሁንም በምንም መንገድ ማቋረጥ የለበትም፡፡ ኋላ እንዳይቆጨው አሁን መወሰን ነው፡፡የቆሙት ተራርቀው ነው፡፡ ለመሮጫ የሚሆን ክፍት ቦታ አለ፡፡ለመሮጥ ዝግጅቱን ጨረሰ ‹‹ተዘጋጅ!!! 1......2 ሶስተኛውን ቁጥር ከመጥራቱ በፊት‹‹አሁን ምን እንደቸገረን ስምተሃል?››አሉት

‹‹ምን አልክ!!››

‹‹አጥቂ እንደሌለን ታውቃለህ››

‹‹ማን?››

‹‹የእኛ ቡድን››

‹‹አላውቅም››

‹‹ተከላካይና አማካይ አሉን››

‹‹እና››

‹‹ግብ የሚያገባልን አጣን››

‹‹ምንም አጥቂ የላችሁም››

‹‹አጥቂማ አለን ግብ የሚያገባ ወሳኝ ሰው የለንም ደግሞ....››

‹‹ደግሞ ምን....››

‹‹ይሄን ዋንጫ እንፈልገዋለን››

ተሾመ እዚህ በወሬ ተጠምዶ እድሉን እያበላሸ ነው፡፡ አሁን የገባው ነገር ቢኖር እነዚህ ሰዎች መሳርያ አልያዙም፡፡ መሳርያ የያዘ ሰው እስኪመጣ እየጠበቁ ነው፡፡ ያን ግዜ ደግሞ የመሮጥም እድል ሰው አያገኝም ጠብሰው ነው የሚጥሉት፡፡እናም መሳርያ የያዘ ሰው ከመምጣቱ በፊት መመረሽ አለበት፡፡ይሄን ወርቃማ እድል መጠቀም አለበት፡፡ሰዎቹ እየተጠጉት ነው፡፡ ከበባው ከመጀመሩ በፊት ባለችው ክፍት ቀዳዳ ማምለጥ ይኖርበታል፡፡ማምለጥ ብቻ ሳይሆን ከስፈሩም መጥፋት አለበት፡፡አሁን ወሳኙ ነገር ወስኖ ከዚህ ቀዳዳ ውስጥ ሾልኮ መሄድ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች በኳስ ወሬ ጀምረው አታለው ሊወስዱት እንደተዘጋጁ ገብቶታል፡፡

እዚህ ቀበሌ ውስጥ የታወቀ አጥቂ ነው፡፡ ብዙ ግብ የሚያስቆጥረውም እርሱ ነው፡፡ ተከላካዮችን አምልጦ በማግባትም ይታወቃል፡፡ስለአጥቂ እያወሩ ሊያግቱት ተቃርበዋል፡፡ ስለዚህ መሮጥ አለበት፡፡ያሁኑ ቆጠራ የመጨረሻ ነው ‹‹ተዘጋጅ!!!! 1....2›› ሶስትን ለመጥራት ተዘጋጅቶ መሹለኪያ ቀዳዳውን እያማተረ ሳለ‹‹...ግን አንተ እንዴት ነህ?›› አሉ

‹‹አለሁ››
‹‹እሱን አይደለም››
‹‹ማለት››
‹‹በአጥቂ ቦታ እንዴት ነህ?››
‹‹ጎል ጋር ስደርስ መተኮስ ነው››
‹‹ለምን እኛ ጋር አትተኩስም››
‹‹ማለት››
‹‹ለእኛ ለምን አትሰለፍም››
‹‹ለምኑ?››
‹‹ለዋንጫ ጨዋታው››
‹‹እኔ?››
‹‹አዎ››
‹‹እኔ እኮ አብዮት ጥበቃ አይደለሁም››
‹‹ለአንድ ቀን ብትሆንስ?››
‹‹ማለት››
‹‹የእኛ አባል››
‹‹የአብዮት ጥበቃ ልብስ አድርጌ››
‹‹እንደዛ አይደለም››
‹‹እና››
‹‹ማልያውን ብቻ ትለብሳለህ››
‹‹ለመቼ?››
‹‹ለዋንጫው እለት››
‹‹ፎርፌ አያሰጥባችሁም››
‹‹ለምን?››
‹‹አባል ሳልሆን መጫወቱ››





‹‹ችግር ከመጣ ትሆናለህ››
‹‹አልገባኝም››
‹‹ገፍተው ከመጡብን ትታጠቃለህ››
‹‹እኔ?››
‹‹አዎ››
‹‹መቼ ነው ጨዋታው››
‹‹እሁድ››
‹‹እደርሳለሁ እንዴ?››
‹‹ማለት ››
‹‹እግሬን እኮ አሞኛል››
‹‹አሁን ስናይህ ደህና ነህ››
‹‹ለመሄድ ችግር የለም ለመሮጥ እቸገራለሁ››
‹‹እስከዛ ትድናለህ››
‹‹እናንተ ካላችሁ ይሁን››

ሰዎቹ አሁን አዘናግተው ለመያዝ አመቺ ሁኔታ በማግኘታቸው የተታለለ መሰለው፡፡ ለመሮጥ በተዘጋጀበት ግዜ ሰዎቹ ትተውት ሄዱ፡፡ግራ ገባው፡፡ እውነት ለጨዋታ ፈልገውኝ ነው እንዴ? ብሎ አሰበ፡፡ዝም ብሎ እየተሹለከለ ግዜውን እንዳጠፋ ተሰማው፡፡ ተፈላጊ ኢህአፓነቱን አላወቁበትም ማለት ነው?፡፡ ድርጅቱ እንዲደበቅ ያዘዘው በስህተት ነው ብሎ አመነ፡፡፡ አሁን በነጻነት ቀበሌ ውስጥ መዘዋወር እንደሚችል ገባው፡፡እናም ለመሮጥ የተዘጋጀበትን ስሜት አውርዶ ነጻነቱን አወጀ ፡፡አብዮት ጥበቃዎቹን ባገኙት ቁጥር ቢጠራጠርም የምር ለጨዋታ እንደፈለጉት ስላወቀ ዘና ማለት ጀምሯል፡፡ መንገድ ላይ ሲያገኙት ለመሮጥ እያሰበ ለካ ነጻ ነኝ ይላል ፡፡ያናገሩት ሰዎች ሲያገኙት‹‹እንዴት ነው?››አሉት

‹‹አለሁ››
‹‹እረፍት አድርግ እንጂ››
‹‹ምን አልክ››
‹‹ለእሁዱ ዋንጫ ባንተ ነው እምነታችን››
‹‹አውቃለሁ››

በፍጻሜው ጨዋታ የቀበሌ 10 አብዮት ጥበቃ ቡድን ከተጋጣሚው ከፍተኛ ጫና ደርሶበታል፡፡ጎል ተቆጥሮበት እየተመራ ነው፡፡ዋንጫው ከእጃቸው ሊያመልጥ ነው፡፡ ይሄ ቡድን ካሸነፋቸው የማይቀበሉት ነገር ነው፡፡እስር ቤት ብዙ ወጣት ገልብጠው ቶርች በመግረፍና አሳዶ በመግደል የተቀጣላቸውም ቢሆንም ይሄን ጨዋታ ግን ለማሸነፍ ዳገት ሆነባቸው፡፡ተጋጣሚያቸው በጣም የሚንቃቸውና ዝቅ የሚያደርጋቸው በመሆኑ ተሸንፎ መሄዱን አልፈለጉም፡፡ የሚችሉትን ነገር ቢያደርጉም ተጋጣሚያቸው የሚቀመስ አልሆነም ፡፡ ዋንጫው ከእጃቸው ወጥቶ ሄደ በተባለበት የተሚጠጠ ደቂቃ ላይ ተሾመ አከታትሎ ባስቆጠረው ግቦች ዋንጫው በእጃቸው በማስገባታቸው ደስታቸው ወሰን አልነበረውም፡፡መሳርያ አልተኩሱም እንጂ ቡረቃው በዚያ መልኩ የሚያልፍ ነበር፡፡ለእዚህ ያቢቃቸውን ተሼን ተሸክመው ጨፈሩ፡፡ ምሽቱም ለእነርሱ ጥሩ ነበር፡፡በዋንጫው እየተደሰቱ ቀሪውን ሰአት ኢህአፓን በማሳደድ ነበር ያነጉት፡፡በነጋታው ጎል አግቢያቸውን አገኙት‹‹ትላንት አስደስትከን እኮ››አሉት

‹‹ቀበሌያችን መሸነፍ ስለሌለበት ነዋ››

‹‹ተጨንቀን ነበር እኮ››

‹‹ለምን?››

‹‹በነዚህ መሸነፍ ለእኛ ሞት ነው››

‹‹ይሄን ያህል››

‹‹በጣም ያበሽቁናል››

‹‹አሁን ማብሸቁ የናንተ ተራ ነው››

‹‹አዎ፤ለማንኛውም ከጉድ አወጣኸን››

‹‹ምንም አይደለም››

‹‹አሁን ሌላ ከባድ ጨዋታ አለን››

‹‹መቼ?››

‹‹ሳምንት››

‹‹እና››

››ትሰለፋለህ››

‹‹እኔ?››

‹‹አዎ››





‹‹ለአንድ ቀን ነው የምንፈልግህ አላላችሁኝም እንዴ››

‹‹ነበረ››

‹‹እና››

‹‹እጥቂ መስመር ላይ አንተ በግድ መኖር አለብህ››

‹‹አይበቃም እንዴ››

‹‹ምን ይበቃል ተጀመረ እንጂ››

‹‹ተጋጣሚ ሊያውቅ ይችላል››

‹‹እሱን ለእኛ ተው ችግር የለም››

በፍጻሜው እለት የሰራው ስህተት ችግር እያመጣበት ነው፡፡ የዛን ቀን ዋንጫ የሚያስገኘውን ግቦች ባያስቆጥር ኖሮ ዛሬ ድጋሚ እንዲጫወትላቸው ባልፈለጉት ነበር፡፡እርግጥ ነው ዋንጫ ማስገኘቱ እየተሹለከለከ ከመሮጥ ተርፏል፡፡በምሽት በጓሮ በር ወደ ቤቱ ተደብቆ የሚገባውና እንደቆቅ በስጋት መተኛት አሁን የለም፡፡የትም ውሎ በነጻነት በዋናው በር ወደ ቤቱ ይገባል፡፡በር ሲንኳኳ አይሰጋም ፤ አይደበቅም፤አይሳቀቅም ቤተሰቡንም አያሳቅቅም፡፡የቡድኑ ወሳኝ አጥቂ በመሆኑ አብዮት ጠባቂዎቹ እንደ እንቁላል ተንከባክበው ነው የያዙት፡ ቁፊታቸው የሚገኘውን ከባድ ጨዋታ ከተወጡ ለተሼ ልዩ ሽልማት አላቸው፡፡ያኛው ዋንጫ የእሱ አሻራ ያለበት ነው ፡፡እሱ ባይኖር ባዶ እጃቸውን እንደሚገቡ እነርሱም አልጠፉቸውም፡፡ መጀመርያም እርሱን የመረጡት ጎል አግቢና ሻምፒዮና እንደሚያደርጋቸው ስላወቁት ነው፡፡በቀጣዩም ጨዋታ ተስፋቸው በተሼ ነው፡፡

## ከ3 ቀን በኋላ

የታጠቁትና ጠመንጃ የወደሩት አብዮት ጠባቂዎች ምሽቱን ተገን አደርገው በድቅድቅ ጨለማ ቤቱን ከበውታል፡፡ እዚህ የመጡት ከባድና በዋናነት ተፈላጊ የሆነውን ሰው ለመያዝ ነው፡፡ አደገኛነቱ ተነግሯቸዋል፡፡ ተነግሯቸዋል ብቻ ሳይሆን እንዳያመልጣቸው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ መያዝ ካልቻሉና የሚያመልጥ ከሆነ ህይወቱን በጥይት መንጠቅ እንዳለባቸው መመርያ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ተፈላጊው ሰው ድምጽ ሰምቶና ነቅቶ እንዳያመልጣቸው ቀስ ብለው ኮሽታ ሳያሰሙ እንደሌባ አድፍጠውና እንደ ድመት አድብተው ወደ

ቤቱ ተጠጉ፡፡ተፈላጊው ሰው ቤት ውስጥ እንዳለ ያውቃሉ፡፡ መረጃውም የሚለው እንደዚሁ ነው፡፡መጀመርያ ተፈላጊውን ሰው ከመያዛቸው በፊት አባቱን በቁጥጥር ስር ማድረግ እንዳለባቸው አውቀዋል፡፡አባቱ ለውጡን የማይደግፉ አድሃሪ የሚል ስም የተሰጣቸውና ብዙ መሳርያ ያላቸው በመሆኑ የደበቁትን መሳርያ አውጥተው እንዳይተኩሱባቸው በማሰብ ነው፡፡አባቱን ቀድመው በማጥቃት ልጅየውን በቁጥጥር ስር ማዋል ነው፡፡

ተፈላጊው ወጣት ካመለጠ ተኩሰው መግደል እንዳለባቸው ቢነገራቸውም ከመግደላቸው በፊት ግን ማቁሰል እንዳለባቸው ተነጋግረዋል፡፡ለማቁሰል የት ቦታ መምታት እንዳለባቸው የወሰኑት ነገር የለም፡፡ብዙ ግዜ ለሚያመልጥ ሰው ለማቁሰል እግሩን እንደሚመታ ያውቃሉ፡፡ አሁን ግን እነዚህንእግሮች ለመምታታቸው እርግጠኛ የሆኑ አይመስሉም፡፡ትእዛዝ ግን መከበር እንዳለበት አልጠፋቸውም፡፡የአብዮቱ ተቃዋሚ የሆነ ሁሉ የእነርሱ ወዳጅ እንዳልሆነ ያወቃሉ፡፡አብዮት ጠባቂዎቹ እንደወደሩ ቤቱን በርግደው ገቡ፡፡በተነጋገሩት መሰረት በቅድሚያ አባትየውን በማገት ተፈላጊውን ሰው በቁጥጥር ለማዋል ተንቀሳሱ፡፡ወዲያውኑ ወደመኝታ ክፍል ገቡና በመብራት ብርሀን በፍጥነት ‹‹እጅ ወደ ላይ!!!!›› ብለው ወደሩበት ‹‹ብትነቃነቅ አሰቀልሀ››አሉት

‹‹እኔ?››

‹‹አዎ››

‹‹እጅ ወደ ላይ››

‹‹ምን አደረግሁ››

‹‹ምን ያላደረግከው ነገር አለ››

‹‹እረ እኔ ንጹህ ሰው ነኝ››

‹‹ቀበሌውን በማመስና በማስቸገር.....››

‹‹እረ የተሳሳተ ሰው ነው የያዛሁት››

‹‹እስከዛሬ ስናፈላልግኽ....››

‹‹እኔ?››

‹‹አዎ››

‹‹ተሾመ እኮ ነኝ››





‹‹ቀንደኛው ኢህአፓ››

‹‹ለእናንተ ተጫውቼ››

‹‹ምን ትጫወታለህ ጉያችን ስር ሆነህ ተጫወትክብን እንጂ››

‹‹ዋንጫ አምጥቼላችሁ››

‹‹ያንተ ዋንጫ ጥንቅር ብሎ ይቅርብን››

‹‹ሰሞኑን እኮ ለእናንተ ለመጫወት ተዘጋጅ ብላችሁን....››

‹‹ከፈለግክ ለእነርሱ ተጫወት››

‹‹የተሳሳተ ሰው ነው የያዛችሁት››

‹‹አልተሳሳትንም እንዳውም እዚህ ልንረሽንህ እንችላለን››

‹‹እንደርሱማ ጥሩ አይደለም››

‹‹ተነስና ቅደም››

አንድ ግዜ በስደፍ ማጅራቱን ሲሉ እየተንገዳገደ ወደፊት መሄድ ጀመረ፡፡ ነገሩ ግራ ገባው፡፡ እዘናግተው እንደያዙት ነው የተረዳው፡፡ ሰሞኑን ፍቅር በፍቅር ሆነው ተወዳጅው እየጋበዙት፣ አጅበው ወደ ቤት እየወሰዱት እንደ እንቁላል እየተንከባከቡ ሲጠብቁት ቆይተው ዛሬ በዚህ ሁኔታ መያዛቸው አስገረመው፡፡እሱ ያጠፋውያን ግዜ ተደብቆ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ባልተዘናጋ ነበር፡፡በሰደፍ እወቀጡ የሚወስዱትን ወጣት‹‹ትንሽ አታፍርም?››አሉት

‹‹ምኑ?››

‹‹ልትሰልለን መሀላችን ገብተህ....››

‹‹እናንተ አይደል እንዴ የጠራችሁኝ››

‹‹ማለት››

‹‹እኔ እምቢ ስል ተጫወት ብላችሁ....››

‹‹ተጫወት አልንህ እንጂ ሰልለን ተባልክ››

‹‹እረ እኔ አልሰለልኩም››

‹‹አሁን የተፈለግከው በከባድ ጉዳይ ነው››

‹‹ምን አጠፋሁ?››

‹‹ስትገረፍ ታወጣታለህ››

‹‹እኔ ለእናንተ መጥፎ ነኝ?››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹ዋንጫ አምጥቼላችሁ.....››

‹‹ዋንጫውን ከፈለግከው እንስጥሃለን ግን መገረፉ አይቀርልህም››

‹‹ዋንጫው ለእኔ ምን ያደርግልኛል የእናንተ ነው››

‹‹እንዳውም የኢህአፓ አጥቂ ባገባው ግብ የተገኘ ዋንጫ አንፈልገውም››

ተሾመ ተደናገጠ፡፡ እነዚህ ሰዎች ጨካኝና ለምንም እንደማይመለሱ ያውቃል፡፡እብሯቸው ሲጫወት ወሬያቸው ሁሉ ስለግድያና ማስታየት እንደሆን ሰምቷል፡፡የሚያወሩትን ወሬ እሱ ላይ አሁን እንደሚተገብሩት ተረድቶታል፡፡ያን ግዜ ጠፍቼ ቢሆን ኖሮ ዛሬ አያገኙኝም ብሎ ተጸጸተ፡፡ለእብዮት ጥበቃ ቡድን ባደረገው አስተዋጻኦ ምህረት እንዲደረግለት ቢጠይቅም ምንም ማስተዛዘኛ ነገር እንደማይደረግ አሳሰቡ፤ ይልቅ ለቶርች እንዲዘጋጅ አሳሰቡት እስር ቤት ካስገቡት በኋላ ዋነኛ ተፈላጊ በመሆኑ ወደ ግርፍ ክፍል ተወሰደ፡

ገራፊዎቹ በደምብ ተዘጋጅተው ነው የመጡት፡፡ውጤት ያለው ነገር ከእነርሱ ይጠበቃል፡፡አለቆቻቸው መግረፍ ብቻ ሳይሆን የተገረፈው ሰው እውነታውን ነግሯቸው የተጨበጠ ነገር እንዲያመጡ አሳስበዋቸዋል፡፡ ሰሞኑ በየቦታው የሚደረገው ግርፍያ ስልቱና ጭካኔው እጅግ የበረታ ሆኗል፡፡አሁን በገራፊዎቹ እጅ ገብቶ ተራውን የሚጠብቀው እስረኛ የበለጠ ውጤት ይጠበቅበታል፡፡ሰሞኑን የቀበሌውን አመራሮች ያስቸገረው ጉዳይ ቢኖር የኢህአፓ አባላት የሚያደርጉት የመረጃ ልውውጥ ነው፡፡በራሪ ወረቀቶችና የድርጅቱ ጋዜጣ በቀበሌው ውስጥ እንድልብ እየተዘዋወረ ሁሉምን አስጨንቋል፡

ጋዜጣው የሚታተምበት ማሽን እዚሁ አፍንጫቸው ስር ሆኖ እያተመ ሲያስራጭ መያዝና መቆጣጠር አቅቷቸው ነበር፡፡አሁን ግን ደርሰንበታል በሚል ይዘውታል ፡፡ቀጣይ ስራው ማሽኑ የት እንዳለ አግኝተው በእጅ ማስገባት ነው፡፡ግርፍያው ውጤታማ ነው የሚባለው ሰውየውን አውጣጥቶ ማሽኑን በእጅ ማስገባት ሲቻል ነው፡፡ማሽኑን በእጅ ማስገባት ለሁሉም መፍትሄ ነው፡ እስረኛው ወደ ወስጥ ከገባ በኋላ ግርፍያው ከመጀመሩ በፊት እውነቱን እንዲነገራቸው ተጠይቆ ዝምታ በመምረጡ ግርፍያው እንዲጀመር የተስማማ ይመስላል፡፡





የእሉቱን ግጥሚያ ለመጀመር ስምምነት ላይ በመድረሳቸው ጨዋታው ሊከፈት ነው፡፡ገራፊዎቹ እስረኛውን እንደበግ መሬት ከጣሉት በኋላ ለእርድ እንደሚዘጋጅ ነገር እጅና እግሩን በገመድ ጥፍር አድርገው አስረው ትልቅ አጠና እንጨት በገመዶቹ ስር አስገብተው ለመግረፍ በሚመች መንገድ አዘጋጅተው አንጠለጠሉት.፡፡ አፉ ውስጥ ጨርቅ አስገብተው ግርፍያው ተጀመረ፡፡እስረኛው ከውስጥ በታመቀ ድምጽ ይጮሃል፡፡ጩኸቱ የድረሱልኝ ጥሪ አይደለም ፡፡ማንም እንደማይደርስለት ያውቃል፡፡

የሚጮኸው ስለጨነቀው ብቻ ነው፡፡ ጩኸቱ የሚቀረው ግርፍያው ሲቆም ብቻ ነው፡፡ ግርፍያው የሚቆመው ደግሞ እሱ እውነቱን ሲያወጣ ነው፡፡ሁሉም ነገር ያለው በእስረኛው እጅ ነው፡፡ ሰዎቹ እስኪበቃቸው ከገረፉ በኋላ ቃሉን ለመቀበል ጨርቁን ከአፉ አውጥተው ጥያቄ ተጀመረ‹‹ተሾመ..››

‹‹አቤት››

‹‹እውነቱን ብቻ ነው ካንተ የምንፈልገው››

‹‹እሺ››

‹‹አትዋሸንም አይደል››

‹‹የማውቀውን ነግራችኋለሁ››

‹‹አድፍርስ የት ነው?››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹አደፍርስ የት እንዳለ ንገረን››

‹‹እኔ አደፍስር የሚባል ሰው አላውቅም››

‹‹እያሾፍክ ነው››

‹‹አላወቀውም አልኳችሁ››

‹‹የት እንዳለ አትነግረንም?››

‹‹ባውቅማ እነግራችሁ ነበር ››

‹‹የት ነው የሚታተመው?››

‹‹ምኑ››

‹‹ጋዜጣው››

‹‹የምን ጋዜጣ?››

‹‹ማሽኑ አንተ ጋር አይደል ያለው››

‹‹የምን ማሽን? ››

‹‹አደፍርስ››

‹‹አደፍርስ የሚባለውን ሰው አላውቅም አልኳችሁ እኮ››

‹‹አደፍርስ ሰው ነው እንዴ?››

‹‹ታድያስ?››

‹‹እያታለልከን ነው?››

‹‹ምኑን ነው የማታልላችሁ››

‹‹እንደማያውቅ ለመሆን አትሞክር››

‹‹ከዚህ በኋላ ባለው ግርፍያ መፈጠርህን ትጠላለህ››

‹‹እኔ እኮ እውነቱን እየነገርኳችሁ ነው››

ቀበሌ ውስጥ የሚሰራጨው ጋዜጣ የሚታተመው አደፍርስ በሚባለው ማሽን ነው።ማሽኑ በድብቅ ቦታ ተቀምጦ በእጅ መዘውር እየታገዘ ህትመት ይካሄድበታል።ማሽኑ ከተያዘ በአካባቢው ላሉት ኢህአፓ ውድቀት፤ ለቀበሌው አብዮተኞች ደግሞ ትልቅ ድል ነው። እስረኛው አደፍስ የሚባል ማሽን አላውቅም በሚል ስግርፊያው ዝግጁ ሆኗል።አደፍርስ የኢህአፓ እስትንፋስ መሆኑን ሁሉም ያውቃሉ። ማሽኑ በእጁ ቢኖርም አሳልፎ ከሚሰጥ ቢሞት እንደሚመርጥ ገራፊዎቹ ያውቃሉ። ምናልባት እድል ከቀናን ብለው መግረፋቸውን ይቀጥላሉ። እስረኛው እስኪበቃው ሳይሆን እስኪሞት ድረስ መግረፍ እንደሚችሉ ያውቃሉ።ከዚህ ቀጥሎ ያለው ግርፍያ የዋንጫ እንደሚሆን እስረኛውም ያውቀዋል።አደፍስ ሰው ሳይሆን ማሽን እንደሆነ ማብራሪያ ተሰጠው።ገራፊው‹‹ስማኸኝ ጓዴ››አለ

‹‹አቤት››

‹‹መጨረሻ ላይ ማመንህ እኮ አይቀርም››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹አንተም አትጎዳ እኛንም አታስለፋን››

‹‹እኔ አደፍርስ የሚባል ነገር አላውቅም››

‹‹አንተ ጋር የለም?››

‹‹አዎ››

‹‹አንተ ጋር የለም ብለን እንመን››

‹‹እሽ››





‹‹ሌላ ሰው ጋር አለ››

‹‹ሊኖር ይችላል››

‹‹ማን ጋር እንዳለ ታውቃለህ?››

‹‹አላውቅም››

‹‹ምርጫ እንስጥህ››

‹‹ምን?››

‹‹ማን ጋር እንዳለ ስም ስጠንና እንፍታህ ወይም በግርፍያው እንቀጥል››

‹‹እኔ በድርጅቱ ውስጥ ወረቀት ከማንበብ ውጭ ምንም ተሳትፎ የለኝም››

ከ30 ደቂቃ በኋላ እስረኛው እራሱን ስቶ በሸክም መምጣቱን ብቻ ጓደኞቹ ያውቃሉ።።እግሩን ስንበር በሚመስል ሁኔታ ተልትለውና አጥንቱ ድረስ በሚሰብር ዱላ ቀጥቅጠው አሽመድምደው ነው የላኩት፡

ከጥቂት ግዜ በኋላ በሆነ ቀን ሌሊት በሩ ሲንገጫገጭ እስረኛው ሁሉ ከእንቅልፉ ነቃ።እዚህ ክፍል እንቅልፍ አለ ይባል እንጂ የሰቆቃ መኙታ ነው ያለው።በሩ ተከፍቶ መብራት ከበራ በኋላ የህዝብ ደህንነት ሰዎችና የአብዮት ጥበቃ አባላት መሳርያቸውን እንደወደሩ በሀይል ቃል እየተናገሩ በሩ ላይ ቆመዋል።ለሆነ ጉዳይ እንደመጡ ከሁኔታቸው ያስታውቃል። በከተማው ውስጥ አንድ አብዮታዊ ጓድ ሲሞት በቀል ለመስራት በየቀበሌው እስረኛው አውጥተው መግደል የተለመደ ሆኗል።ሌላም ነገር ደግሞ አለ ።ወሳኝ መረጃ የሚፈለግባቸው እስረኞች በተደጋጋሚ ተገርፈው መረጃ ካልሰጡ ቀጣይ ርምጃው ጥይት እንደሆነ ተደጋግሞ ታይቷል ። አንዳንዴም እስረኛው አውጥተው ወደ ሌላ እስር ቤት ይወስዳሉ። ደግሞም ሽነጥ ሲያደርጋቸው አውጥተው በነጻ ይለቃሉ።እናም ዛሬ ሌሊት በቁጣ የእስረኞችን በር በርግደው የገቡት ሰዎች ሞትን በእጃቸው ይዘው እንደመጡ እስረኛው ጠርጥሯል።ይሄ ካልሆነ ደግሞ ለአንድ ጉዳይ እንደመጡ ይገመታል።

ደርግ ጽህፈት ቤት ባሉት የማጎርያ ቦታ በተሰጠ ጥቆማ የሚፈለገው እስረኛ በአስቸኳይ ይምጣ ከተባለ እንደዚሁ በሌሊት

ተጣድፈው መጥተው ይወስዷሉ ።ዛሬ በሌሊት በከፍተኛ 23 ቀበሌ 10 እስር ቤት የተገኙት ከሁለት በአንዱ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። መሪያቸው ኢህአፓን እንቋሾ እስረኞችን ተሳድቦ ብዙ ከፎከረ በኋላ‹‹ሁሌን!!››አለ

‹‹አቤት››
‹‹ና ወደዚህ››
‹‹ እሺ››
‹‹አባተ››
(ዝምታ)
‹‹አባተ ይርዳ››
(ዝምታ)
‹‹አባተ የለም..››
‹‹አለሁ››
‹‹ለምን ዝም አልክ?››
‹‹እኔን አልመሰለኝም››
‹‹ተነስ››
‹‹ምን አልክ››
‹‹ተነስና ወደ ውጭ ውጣ››
‹‹እቃዬን ይገፎ ነው››
‹‹ስለምትመለስ አትያዝ››
‹‹ተሾመ››
(ዝምታ)
‹‹ተሾመ ተፈራ››
(ዝምታ)
‹‹ተሾመ የለም?››

ተሾመ አለ ግን ለምን እንደሆን ሳይታወቅ ዝም አለ።አቤት ማለት ፈልጎ ነበር።እንደበቱ እምቢ አለው።እስረኛው እንዳይታይ በጋቢውና በብርድልብሱ ፊቱን እየከለለ በቆረጣ እየተመለከተ ነው። አንዳንዱ ተጋድሞ በጎንዮሽ ይመለከታል ሰወዬው ግን ‹‹ተነሱና ቁሙ›› አለ።ተነስተው ተገተሩ ግማሹ አቀርቅሯል፤ማንነቱ እንዳይለይ ጥረት እያደረገ ነው።እነዚህ ሰዎች ለሆነ መጥፎ ነገር እንደመጡ





የተረዱት እስረኞች ተረባርበው ቢይዟቸው ለማሸነፍ እንደሚችሉ ያውቃሉ ግን እነርሱም አውቀው መሳርያ ደግነው ነው የሚጠበቁት። ሀላፊው እስረኞቹን እየተመለከተ ነው‹‹ተሾመ››አለ

‹‹አቤት››
‹‹ና ውጣ››
‹‹ምን አደረግኩ?››
‹‹ተወስኖብሃል››
‹‹ምን?››
‹‹ሞት››
‹‹እኔ››
‹‹አዎ››
‹‹ምን አደረግኩ››
‹‹አደፍርስን ስላላመጣህ እንድትገደል ተብሏል››

ተሾመ ደነገጠ ሰውየው አተኩሮ ሲመለከተው የእሱን ስም በድጋሚ የጠራ መስሎት በሀሳቡ እነርሱ ለሚጠይቁት ነገር መልስ እየሰጠ ነው።በቃ አሁን ከጠሩት ሊገድሉት የሚችሉት በአደፍርስ ነገር ብቻ ነው።ሰውየው እስረኞቹን እየተመለከተ ነው። ተሾመ አቀረቀረ።አሁን ተጠርቶ የወጣው አባተ ከእርሱ ጋር አንድ ሴል ናቸው።ከዚህ ሴል ውስጥ ባለፈው አንድ ሰው ተገድሏል ። ሁለተኛው አሁን ተጠርቶ ወጥቷል። በቀጣይ ተረኛው ተሾመ ነው።ስሙ እንደተጠራ ሰምቷል ።አቤት ማለት ግንአቅቶታል።ሁለቱ ጓደኞቹ በተጠሩ ግዜ በመደንገጡ ምን እየተካሄደ መሆኑን ግራ ገብቶታል። አሁን ድጋሚ ከተጠራ አቤት ማለቱ አይቀርም።ደግሞም ማመለጥ አይችልም።በመልክ ያውቁታል።

አሁን እያንዳንዱን እስረኛ ወደፊት እያመጡ ማንነቱን በብርሃን ያለያሉ።አንድ በአንድ ወደፊት እንዲመጣ ትእዛዝ ተላለፈ። በብርሃን ያለያሉ።አንድ በአንድ ወደፊት እንዲመጣ ትእዛዝ ተላለፈ። የትም ማመለጥ አሁን ሁሉም ሰው ማንነቱ ይታወቃል ማለት ነው። የትም ማመለጥ እንደማይችል የተረዳው ተሾመ ‹‹አለሁ›› ብሎ ለመናገር በተዘጋጀበት ግዜ ድንገት ከግቢው ውስጥ ግርግርና የሀይለቃል ንግግር ሲሰማ ሰዎቹ የእስረኞቹን በር ዘግተው ተጨማሪ ሰው ሳይወስዱ ወደ ውጭ

ወጡ።እስረኞቹ ቁጭ እንዳሉ እንቅልፍ በአይናቸው ሳይዞር ነጋ። በሌሊት ከቅርብ ጀምሮ እስከሩቅ የሚንጣጣውን የጠመንጃ ተኩስ እየቆጠሩ አነጉ።በጠዋት በሩ ላይ እንደተለመደው እናቶችና እህቶች ቁርስ ለማቀበል በር ላይ ተኮልኩለዋል።እናች ልጆቻቸውን እስኪያዩ ድረስ ምንም እምነት የላቸውም።ተሾመ እናቱ ቁርስ እያቀበሉት አይን አይኑን ይመለከቱታል።እናቱ ‹‹እንዴት ነህ ልጄ››አሉት

‹‹ደህና ነኝ››

‹‹ሁላችሁም ሰላም ናችሁ?››

‹‹አዎ ግን....››

‹‹ግን ምን?››

‹‹ማታ ሁለት ልጆች ለጥያቄ ነው መሰለኝ ተወስደዋል››

‹‹እነማን?››

‹‹እነ አባተ››

‹‹እነርሱማ.....››

‹‹ምን?››

‹‹ሌሊት ተገደሉ እኮ››

‹‹አባተ!!!!!!!››

‹‹አዎ››

እናትዬው ይሄን ብለው አለቀሱ።ነገ የእሳቸውም ልጅ ይሄ እጣ እንደሚገጥመው አልጠፋቸውም።አላወቁም እንጂ ስሙ ሲጠራ ደንግጦ ‹‹አቤት›› ያለማለቱ ነው የተረፈው። ነገ ሰዎቹ ተመልሰው መጥተው እንደሚወስዱት አልጠፋውም። ለመሞት ከመዘጋጀት በስተቀር ምንም አማራጭ አልነበረውም።ማታ ነው የሚመጡት። በር ላይ ቆመው ነው ለግድያ የሚፈልጓቸውን እስረኛ የሚያስወጡት። ከወሰዱት ይገድሉታል። ብቻውን መሞት አልፈለገም አንዱን ባለመሳርያ ታግሎ ለመንጠቅና እዛው ለመጫረስ ተዘጋጀ።ቀኑን ሙሉ ስልት ሲነድፍ ቆየ።ይሄን ሁሉ ለማድረግ የፈለገው የመንጠቅ ችሎታ ስላለው ሳይሆን በድፍረቱ ነው ።ድፍረት ዋና መለያው ነው። ሰውየው ግብዳም ይሁን ከእሱ ይብለጥ ምንም ሳይፈራ ያደርገዋል።





## እንደገና በሌላ ቀን

በ1979 መጨረሻ የዲናሞ ሚኒስክ ቡድን ከመስኮብ ወደ አዲስ አበባ መጣ ።የወዳጅነት ጨዋታ ለማድረግ ነው።ቡና ጥሩ አቋም ላይ ስለነበር ሁለቱ ግጥሚያ እንዲያረጉ ተመቻቸ።ይሄ ጨዋታ ለቡና የመጀመርያው ኢንተርናሽናል ግጥሚያ ነው።7 ቁጥር የለበሰው ተጨዋች በጣም አስቸገራቸው።በክንፍ ያለው ተጫዋች እየደረመሰ ወደ ግብ እየመጣ ነው።ተጫዋቹ ግዙፍና ሚኒባስ ነው የሚያክለው። አንድ ሳይሆን 3 ሰው ነው የሆነባቸው።7 ቁጥር ለባሹ ተጨዋቾቹን ማለፍ ብቻ ሳይሆን እየገረሰሰ፣እየገነደሰ፣እየናደ፣እየጨፈለቀ ነው የሚሄደው።በሆነ መንገድ ይሄን ሰውዬ መትተው ማስወጣት አለባቸው።

ተሾመ ይሄን ለማድረግ ተዘጋጀ ።ግን የሚያግዘው ሰው ያስፈልጋል።መስመር ላይ ተከስተ ደምሴ ይገኛል።ኳስ ወደውጭ ሲወጣ ተሾመ ወደ እርሱ ሄደና‹‹ተከስተ››አለው

‹‹አቤት››

‹‹ይሄ ሰውዬ››

‹‹የቱ?››

‹‹7 ቁጥሩ››

‹‹ምን?››

‹‹ጨረሰን እኮ››

‹‹ምን እናድርግ?››

‹‹ልመታው ነው››

‹‹ተው አትችለውም!!!!››

‹‹እሱን ለኔ ተወው››

‹‹ምን እናድርግ?››

‹‹ለሁለት እንምታው››

‹‹እረ እኔ አልችለውም››

‹‹አንድ ዘዴ አለኝ››

‹‹ምን?››

‹‹አንተ ጀምረው››

‹‹እና››
‹‹እኔ ጨርሰውና አስናብተዋለሁ››
‹‹ትችለዋለህ?››
‹‹ከሜዳ ማስወጣት ብቻ ሳይሆን ሳምንት ሙሉ እንዳይነሳ አደርዋለሁ››
‹‹ግን ተሼ...››
‹‹አትፍራ አድርገው እኔ ጨርሰዋለሁ››

የተሾመን ድፍረት ስለሚያውቅ ተከስተ ለመተባበር ተዘጋጀ። ተከስተ ትንሽ ነኩቶ ሲያንገዳግደው ተሾመ የተንገዳገደውን ተጫዋች ባላንሱን ሳያስተካክል ስትራቴጂ ቦታ መትቶ ያስወጣዋል።ብዙ ግዜ አጥቂዎች የሚፈሩትም እንዳይነሱ የሚያደርግ ቦታ ይመታና ቁጭ ያደርጋቸዋል።ተጫዋቹ በፍጥነት እየነዳ መጣ።ተከስተ ለማንገዳገድ ቶሎ ብሎ ሄደበት።ሰውየው የተንገዳደገ ስለመሰው ተሾመ ቶሎ ገባና ስነዘረ ግን እንዳሰበው፤ እንደተዘጋጀበት፤እንደፈለገውና እንደተመኘው አልሆነም። ሰውየው በዛ ግዙፍ ሰውነቱ በፍጥነት መጥቶ ተሾመ ታከል እንደወረደ አናቱን፤ ሆዱንና እግሩን ደርምሶት ሄደ።ተሾመ ተንደፋድፎ ጸጥ አለ።

እዚህ ሜዳ ተሾመ ሁሉንም አጥቂ ያንደፋድፋል እንጂ ሲንዳፋደፍና ሲዘዘር ተመልካቹ አይቶ ስማያውቅ ተገረመ።7 ቁጥሩ ገንጥሎት ሳይሆን ገጭቶት ነው የሄደው።ተሾመ ሰማይ ምድሩ ዞረበት። ቀይ ፤ሰማያዊ፤ቢጫ፤ውሃ ሰማያዊው ...የማያየው የቀለም አይነት የለም። ታዋቂው ወጌሻ ይስሃቅ ሽፈራው ተሾመ ጠንካራና አቻዮ መሆኑን ያውቃል። ቅጽል ስሙን ‹‹ተሼ ብረቱ›› ብለው ነው የሚጠሩት።ይስሃቅ እየበረረ ወደ ሜዳ ገባ። ተሾመ ይስሃቅን እየው ግን ተሽከርክሮ ጠፋበት።ይስሀቅ ቀና አደረገውና ‹‹ተሼ››አለው
‹‹ማነህ አንተ?››
‹‹ይስሃቅ ነኝ››
‹‹ማን አልከኝ››
‹‹ይስሃቅ››
‹‹ይስሃቅ የቱ››





ተሾመ ክፉኛ መጎዳቱን ይስሃቅ አወቀ።ቀስ ብሎ ወደ ውጭ አወጡት።ህክምና ብቻ ሳይሆን መጀመርያ እሱነቱን መመለስ አለበት። ተሾመ ጠንካራ መሆኑን ይስሃቅ ያውቃል።እናም የተጎዳበትን እያከመ የማረጋጋት ስራ እየሰራ ነው።ትንሽ እንደቆየ ይስሃቅ‹‹እንዴት ነህ ተሼ?››አለው
‹‹ሊያስመልሰኝ ነው››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹የበላሁት ሊወጣ ነው››
‹‹አይዞክ››
‹‹ምን አይዞክ ትለኛለህ››
‹‹ምን ሆንክ››
‹‹መኪና ነው እኮ የገጨኝ››
‹‹አሁን ተነስ ቁም››
‹‹አልችልም››
‹‹ትችላለህ››
‹‹ልውጣ በቃኝ››
‹‹የት ነው የምትወጣው››
‹‹ወደ ቤት ልሄድ››
‹‹እዚህ ቆይ››

ይስሃቅ እንደምን አረጋጋውና ወደ እሱነቱ ተመለሰ።ትንሽ ዘግይቶ እንዲገባ አደረገው። እንደገባ ሰውየውን የት ጋር መትቶ መጣል እንዳለበት አሰላሰለ።

## እንደገና በሌላ ቀን

የቡና ተከላካይ መስመር ጥንካሬው የሚጀምረው ተሾመ ላይ ተንጠልጥሎ ነው። ተሾመ ከሌለ በመከላከል ወረዳ ላይ አጥቂዎች እንደፈለጉ ይፈነጫሉ።አንድ አጥቂ ካስቸገረ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ወድቆ ይገኛል። ማን እንዴትና በምንሁኔታ እንደመታው አይታወቅም።አልቢትሮች ግን ባያዩም ተሾመን ይጠሩታል፤ጠርተውም በቀይ ያሰናብቱታል።በቀይ ሰለባ የመሆኑ ጉዳይ ተደጋገመ ። በችሎታው ክለቡ ይመካበታል ግን በቀይ እየወጣ አስቸገራቸው።ከሜዳ

ውጭም ነውጠኛ ሆነባቸው። ብዙ ተመከረ ግን የሚመለስ አልሆነም። ሁሉም ሰው ተናደደበት። ደግሞም ሲቆጡት የሚሰጠው ምላሽ አናዳጅ ሆነባቸው።የክለቡ ሀላፊዎች እየወደዱ ከክለቡ አራቁት። ከስፖርት ክለቡም አስወጡ።

የክለቡ ቋሚ ሰራተኛ ስለሆነ ወደ ስራው ገቢታው መለሱት። ኮሚቴው በደምብ መቀጣት አለበት ብሎ ስላመነ እዚህ ቢሮ ከሚቀመጥ ከከተማ ሊያስወጡት ፈለጉ።ከከተማ ማስወጣት ብቻ ሳይሆን ማራቅ አለባቸው።ከከተማው ማራቅ ብቻ ሳይሆን እንጨቀረር መስደድ አለባቸው።ሰው የሌለበት ቦታ ሄዶ በደምብ መቀጣት አለበት አሉ።ሱዳን ጠረፍ ላይ የሚገኝ ከተማ ላኩት። ከሰው ይልቅ አውሬ የሚበዛበት ነው።ቴሌቪዥን ቀርቶ ሬድዮ የለም፣ጋዜጣ እንኳን አይገኝም።ከሁሉም ነገር የተቆራረጠ ከተማ ነው።በጥቅሉ ምንም አይነት ነገር የለም። የቡና ምርት ወደ ገበያ ሲወጣ ይገዛሉ። በከተማው ስልክ የሚባል ነገር የለም። አንድ ቀን ገበያ ቁጭ ብሎ ቡና እየሸመተ ‹‹ተሾመ ተፈራ›› የሚል ድምጽ ሰማ። የመገናኛ ሬድዮ የያዘው ሰውዬ ወደ እርሱ መጣ‹‹ተሾመ›› አለ

‹‹አቤት››

‹‹በሬድዮ ትፈለጋለህ››

‹‹ማነው? ››

‹‹ዋናው መስርያ ቤት ነው››

‹‹ምንድነው ?››

‹‹በአስቸኳይ ይፈልጉሃል››

‹‹ለምንድነው?››

‹‹እንድትመለስ ተብሏል››

‹‹እኔ እዚህ ስራ ተስማምቶኛል››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹ተመችቶኛል››

‹‹እንኳን አንተ እኛ አልተመቸንም››







**የቡና ገበያ ቡድን በ1978 ተሾመ ከተቀመጡት ከግራ ወደ ቀኝ ሁለተኛው ነው**

ተሾመ መመለሱ ደስ ብሎታል ግን አካባቢው እንደተመቸው መናገር አለበት። የቡና ቡድን ተሾመ ከተባረረ በኋላ የኋላው መስመር ተናወጠ። እሁድ ከመብራት ሀይል ጋር ወሳኝ ጨዋታ አላቸው። ቢያስቡ ቢያሰላስሉት ያ ቦታ ያለ ተሾመ አስቸጋሪ እንደሚሆን ስላወቁ ስልክ ስለሌለ የሬድዮ ግንኙነት ፈጥረው ቶሎ እንዲመጣ መልእክት አስተላለፉ። ቶሎ ብቻ ሳይሆን አመጣጡን አስቸኳይ አደረጉት። አዲስ አበባ በፍጥነት ደረሰ። ኮሚቴው አነጋገረው‹‹ለምን እንደተፈለግክ ታውቃለህ›አሉት

‹‹ወደ ክለቡ እንድመለስ...››

‹‹ ወደ ቡድኑ አልተመለስክም እኮ››

‹‹በሬድዮ በአስቸኳይ ወደ ክለቡ እንድትመለስ ተብሎ...››

‹‹ማን መለሰህ?››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ገና መመለስህ አልተረጋገጠም››

‹‹እና››

‹‹መጀመርያ ጸባይህ ታይቶና ተረጋግጦ ነው በቋሚነት የምትመለሰው››

‹‹እረ አስተካክላለሁ››

‹‹ታይቶ ነዋ!!!››

‹‹ችግር የለም››

‹‹ከእንግዲህ ቀይ ቀርቶ ቢጫ ካየህ ካሁኑ የባሰ ቅጣት ነው የሚጠብቅህ››

‹‹እሽ ችግር የለም፤እንኳን ካርድ ላይ ባለበትም አልደርስም››

ከበረሃ በተመለሰ በሶስተኛ ቀን ወሳኙ ጨዋታ ከመብራት ሀይል ጋ ተደረገ:: ሰለሞን ጋሜ አስቸገራቸው:: ላስቸገረ ተጫዋች ደግሞ ተሾመ መልስ ነበረው:: የተባለውን ማስጠንቀቂያ ረሳ:: ተንደርድሮ ታክል ገብቶ ወደቁ እንደተነሱ ተሾመ በክርን ሰለሞንን መታው ብቻ ሳይሆን ዘረረው:: አልቢትሩ ጌታቸው ገብረማርያም ነው (የጌታቸው ታሪክ በዚህ መጽሀፍ በምእራፍ አስር ይገኛል) እየሮጠ መጣ ወደ ኋላ ኪሱ እጁን እያስገባ ነው ::ቀይ እንደሆነ አውቋል:: ተሾመ አሰቀሰት:: ቀይ ከሆነ ቅጣቱን ያውቀዋል ‹‹ጋሽ ጌታቸው!!››አለ

‹‹ምንድነው?››

‹‹እባክህ››

‹‹መትተኸው የለ››

‹‹በትክክል መትቼዋለሁ››

‹‹እኔም ይሄን አይቼ ነው የመጣሁት››

‹‹ቀይ ልትሰጠኝ እንደመጣህ አውቂያለሁ››

‹‹ልክ ነህ››

‹‹ይሄ ቀይ እንደሌላው ግዜ አይደለም››

‹‹ምን ማለት ነው››

‹‹ተቀጥቼ ሱዳን ድንበር ጥግ ተልኬ ነበር››

‹‹ሰምቻለሁ››

‹‹አሁን ቀይ ከሰጠኸኝ ከድንበሩ አሻግረው ከሀገር ነው የሚያባርሩኝ››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹ከስራም ያባርሩኛል››

‹‹ታድያ ለምን ቀስ ብለህ አትጫወትም››

‹‹ሁለተኛ አይለመደኝም››

‹‹አስኩናኝ››

‹‹እንደርሱ ብትለኝ ይሻለኛል››





ጌታቸው ተሾመን ምን እንደቀጡት ሰምቷል:: ይሄ ቀይ ህይወቱን እንደሚያመሰቃቅል አውቋል::: ካርድ ለእሱ ከባድ በመሆኑ በግሳጼ አለፈው::

## እንደገና ወደኋላ

ቡና ለኢትዮጵያ ሻምፒዮና ለማለፍ እርሻ ሰብልን ማሸነፍ ይጠበቅበታል::እለቱ ማክሰኞ ነው:: ቀኑ ደግሞ ግንቦት 8 ሆኗል:: አመተ ምህረቱ 1981 ላይ ተተክሏል::9 ሰአት ላይ ምድርጦር መብራት ሀይልን ይገጥማል::መብራት 1ለ0 እየመራ ነው::ቀጣዩ ጨዋታ ቡና በመሆኑ ወደ መልበሻ ክፍል ገብተዋል::ትጥቃቸውን ቀይረው አሟሙቀው ይጠብቃሉ:: ይሄኛው ጨዋታ እንዳለቀ ወደ ሜዳ ይገባሉ::ተጨዋቾቹ ከሚያሟሙቁበት አናት ላይ ጄቶች ይበራሉ: : ጄቶቹ ከተመለደው በተለየ ሁኔታ ዝቅ ብለው እየሄዱ ህዝቡን እያስደነገጡት ነው::በከተማው ውስጥ ከፍተኛ ችግር እንደተፈጠረና አካባቢው ተኩስ በተኩስ በመሆኑ ፌዴሬሽኑ በአስቸኳይ ተመልካቹ ከስታየም ለቆ እንዲወጡ አሳሰበ::

በዚህ የተነሳ ሲጠበቅ የነበረው የእርሻና የቡና ጨዋታ ተቋረጠ:: ተጫዋቾቹ አሟሙቀው ወደ ሜዳ ለመግባት እንደተዘጋጁ በአስቸኳይ ወደ ሰርቪሱ እንዲገቡ ተነገራቸው::በሀገሪቱ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት እየተካሄደ በመሆኑ ሁሉም አካባቢው በተኩስ እየተንጣጣ ነው: ::የቡና ተጨዋቾች ሳይጫወቱ ከነትጥቃቸው ወደ ካምፕ ተመለሱ::ብዙ ግዜ ተጨዋቾች ወደ ካምፕ በመጡ ግዜ ምሽቱን ከግቢ ወጥተው በአካባቢው ባሉት መዝናኛ ቤቶች ያመሻሉ አሰልጣኙ ተጨዋቾቹን በሳሎን ሰብስቦ ‹‹..... በሀገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ችግር ተከስቷል ::የመፈንቅለ መንግስት ድርጊት እየተከናወነ በመሆኑ አሸናፊው እስኪታወቅ በከተማው ትልቅ ጦርነት ሊከሰት ይችላል:: ነገሮች እስኪረጋጉ ማንም ሰው ከካምፑ መውጣት የለበትም:: ምክትል አሰልጣኜ ወታደር ቀመስ ስለሆነ በጦርነት ግዜ ችግር ቢፈጠር እንዴት አድርጋችሁ እራሳችሁን ማትረፍ እንድምችሉ ይነግራችኋል:: እኔ የቤተሰብ ሀላፊ ስለሆንኩ ወደ ቤት መሄድ አለብኝ:: ጥያቄ ያለው ካለ››አለ

‹‹እኔ አለሁ››
‹‹ምንድነው ተሾመ?››
‹‹ልጆች ስላሉህ ወደ ቤት ልትሄድ ነው?››
‹‹አዎ››
‹‹እኔም የቤተሰብ ሀላፊ ነኝ››
‹‹እና ››
‹‹እኔም ወደ ቤት መሄድ አለብኝ››
‹‹ከዚህ ንቅንቅ ማለት አትችልም››
‹‹መብቴ ነው ፤አንተም ከሄድክ እኔም እሄዳለሁ››
‹‹አንተ ሰው ጤና የለህም ፤ከእኔ ጋር እልህ  የምትይዘው……››

አስልጣኙ ከተቀመጠበት ወንበር ተነስቶ በሀይለቃል እየተሳደበ ወደ እሱ መጣ፡፡ተሾመም ሊመታኝ ነው ብሎ ለመዘጋጀት ቶሎ ከተቀመጠበት ሶፋ ተነሳ፡፡ ያደረገው ብሎን ጫማ ነው፡፡መሬቱ ደግሞ ሴራሚክ ነው፡፡ በፍጥነት ተነስቶ ሲቆም ሴራሚኩ እያንሸራተተው ፤ እያንሸራተተው፤ እንደገናም እያንሸራተተው ባላንሱን መጠበቅ አቅቶት ወደ ፊት እየተምዘገዘገ ሄደ፡፡ ብሎን ጫማ ሳይሆን እግሩ ላይ ኩሽኔት ያለ ይመስል ተንሸራትቶ አሰልጣኙ ጋር ደረሰ፡፡ፍጥነቱ ከፍተኛ በመሆኑ  መቆም ስላልቻለ የአሰልጣኙን አንገት አንቆ ለመቆም ሞከረ፡፡ግን የመጣበት ፍጥነት ሀይል ስለነበረው አሰልጣኙን እያንገዳገደ ወደ ኋላ ወሰደው፡፡ አሰልጣኙም ሊመታው የመጣ መስሎት እሱም ተሼን አነቀውና ተያይዘው ሁለቱም ሶፋ ስር ወደቁ፡፡

አወዳደቃቸው ተሾመ ከላይ አሰልጣኙ ከታች ናቸው፡፡ተሾመ አሁን ሰንዝሮ አሰልጣኙን እንደሚመታ ሁሉም ገመቱ ፡፡ሰውዬው ተሾመ ስለሆነ ለዚህ ነገር እንደማይመለስ የገባቸው ትላልቆቹ ተጫዋቾች እነሚሊዮንና ሙሉጌታ ከወደቁበት ገላግለው አስነሷቸው፡፡ በሌላ ቀን  ተሾመ አሰልጣኝ ለመደብደብ በሚል 100 ብር ተቀጣ ፡፡ 100 ብር ያን ግዜ 2 ኩንታል  ጤፍ ይገዛ ነበር፡፡





## እንደገና ወደ ኋላ

ምሽት ላይ ጓደኞቹ ወደ ሌላ እስር ቤት ትዛወራላችሁ በሚል ስማቸው ሲጠራ ‹‹አቤት››አሉ፡፡ የተሾመ ስም ሲጠራ ግን አቤት ማለት አቃተውና ጓደኞቹ ተገደሉ፡፡ ምሽት ላይ ሊመጡ ስለሚችሉ እንዱን ገድሎ ሊሞት ተዘጋጀ ፡፡ግን አንድ ነገር ተከሰተ፡፡  የደርግ አባል የሆኑት ደበላ ዲንሳ ወደቦታው  በመምጣት ‹‹ከእንግዲህ ግድያ ቆሟል›› ብለው ንግግር አደረጉ፡፡ ገዳዮቹ ተመልሰው ወደ እስረኞቹ አልመጡም ፡፡ ተሼ አቤት ቢል ኖሮ ዛሬ በህይወት አይገኝም ነበር፡፡ ተሾመ አሁን ኑሮውን በአዲስ አበባ ከትሞ ይገኛል፡፡ለቡና የመጀርያዎቹን ትላልቅ ዋንጫዎች አምጥቶ ቡድኑን በህዝብ እንዲታወቅ አድርጓል፡፡

## ምእራፍ 15

# የአጥሩ ገዳይ

አጥር ላይ የተንጠለጠለውን ልጅ ማንም አላየውም፡፡ ጊዜው ከምሽቱ አንድ ሰዓት ገደማ ነው፡፡ ከእሱ ጋር አብሮት የመጣው ጓደኛው በሩን ያንኳኳል፡፡ድምጽ ስለሰሙ የሆኑ ሴትዮ መጡ፡፡ በሩ ላይ ያለው ልጅ ‹‹ ሲሳይ አለ?›› አላቸው፡፡

‹‹ ማን ነህ?››

‹‹ ጓደኛው ነኝ ሲሳይን ፈልጌው ነው››

‹‹ ግባ››

‹‹ ውጭ ላናግረው ነው የፈለግኩት››

‹‹ እንግዲያውስ ልጥራልህ››

የሲሳይ እናት ልጃቸውን ሊጠሩት ወደቤት ገቡ፡፡ ሲሳይ የመኢሶን አባል ነው፡፡ ኳስ መጫወቱን ትቶታል፡፡ እዚያ ቡድን ውስጥ አሰልጣኙን ጨምሮ የኢህአፓ አባላት ይበዛሉ፡፡ ማንነቱን ስላወቁ ኳስም አይሰጡትም፡፡ የትሬኒንግ ሰዓትም አይነግሩትም፡፡በዚህ የተነሳ ለጊዜው ራሱን አገለለ፡፡

ኢህአፓ በስፖርት ውስጥ ለውጥ ለማምጣት እየሰራ ይገኛል ስለተባለ እሱ የኢህአፓ አባል ባለመሆኑ የስፖርት እድገት ፀር ነው ብለው ያወሩበታል፡፡ ጓደኞቹም ተበታትነዋል፡፡በአዲስ አበባ የባንክ ዘረፋ በተደረገበት ግዜ የተሳተፉት አንዳንዶቹ እዚህ ክለብ የተመረጡ ናቸው፡፡አንዳንዶቹ በሽፋን ሰጭነት ነበሩበት፡፡የዚያ ቡድን ተጫዋቾች ኦፕሬሽኑ ውስጥ እንዳሉበት አውቋል፡፡ ከባንክ ዝርፊያ በኋላ ያልተያዙ ልጆች ነበሩ፡፡ኦፕሬሽኑ ከተደረገ ከአንድ ቀን በኋላ በጥቆማ የተወሰኑት ተይዘዋል፡፡ በዚህን ጊዜ የሆነ ሰው እየጠቆመ መሆኑን በተለይ ኳስ የሚጫወቱ የኢህአፓ አባላት ጠርጥረዋል፡፡

አንድ ሰው በጣም ተጠርጥሯል፡፡ ግን እስከ ጥቆማ ያደርሳል ብለው አልገመቱም፡፡ ይህን ጠቋሚ ማስወገድ አለባቸው ፡፡ መጠቆም





ብቻ ሳይሆን በየቦታው እየሄደ እንደሚያስለቅማቸው መረጃ አገኙ፡፡ ስለዚህ በእሱ ላይ ቶሎ እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡ ሲሳይ የልጆቹን ማንነት ለአንድ ካድሬ ነግሯል፡፡ካድሬው የመኢሶን አባል ቢሆንም በሽፋን ለኢህአፓ የሚሰራ ነበር፡፡ካድሬው ሁኔታውን ነገራቸው፡፡ቶሎ መወገድ እንዳለበት ላከባቸው፡፡ ካድሬው የሲሳይን ጥቆማ ተግባራዊ ካላደረገ ለሌላ ካድሬ ነግሮ ችግር ይፈጠራል፡፡

የነሲሳይ ቤት ከመንደሩ ወጣ ያለ ስለሆነ እሱን ለመምታት አመቺ ነው፡፡ ይህንን ሥራ የሚፈፅሙት ሁለት ልጆች ተመረጡ፡፡ አንደኛው ከሌላ ቦታ የመጣ ነው፡፡ ሌላኛው ደግሞ የጎረቤት ሰፈር ልጅ ነው፡፡ ሲሳይ ከሌላ ቦታ ከመጣ ገና አንድ ዓመቱ ነው፡፡ ግን ችግር ከመፍጠሩ በፊት መልቀም አለባቸው ፡፡ ደግሞም ሁለቱም ወደ እሱ ቤት የሄዱት ሲሳይ ከጠቆመባቸው ተፈላጊዎች መካከል ናቸው፡፡

ከጎረቤት ሰፈር የመጣው ልጅ አጥር ላይ ወጣ፡፡ ሌላኛው ልጅ በር ማንኳኳት ጀመረ፡፡ እናቱ ጠርተውት ሲሳይ መጣ፡፡ በሩን ሳይከፍት ከውስጥ ሆኖ ‹‹ ማን ነህ?›› አለ፡፡

‹‹ እኔ ነኝ››

‹‹ አንተ ማን ነህ?››

‹‹ጓደኛህ ነኝ፡፡ አላውቅከኝም?››

‹‹ስምህ ማን ነው?››

‹‹ አንተ ሲሳይ ነህ አይደል?››

‹‹ አዎን››

‹‹ላናግርህ ፈልጌ ነው››

‹‹ማን ነህ ግን አንተ?››

‹‹ልኮኝ ነው (የካድሬውን ስም ጠቅሶ )

‹‹ እርግጠኛ ነህ?››

‹‹ አዎን››

‹‹ ምነው?››

‹‹የጠቆምካቸውን ልንይዝ ነው

‹‹እና››

‹‹አንተ ታስፈልገናለህ››

‹‹መቼ?››

‹‹ዛሬ ማታ›

ሲሳይ ጠርጥሯል። ለመክፈት አልሞከረም። በሩን ሳይከፍት ወደ ቤት ሲመለስ ፈለገ። ምናልባትም መሣሪያ ሊያመጣ ይሆናል። ከውጭ የአጥሩን አምፖል ቀድመው ስላጠፉት በቀዳዳ አይታዩም። ሲሳይ ወደ ቤቱ ለመሄድ ሲዘጋጅ አጥር ላይ የተንጠለጠለው ልጅ ግማሽ አካሉን ወደ ውስጥ አስገባና ቁልቁል እያየው ‹‹ ሲሳይ ደህና ነህ?›› አለው።

‹‹ ደህና!!.........ማን ነህ አንተ?››

‹‹አታውቀኝም››

‹‹ አጥር ላይ ምን ትሰራለህ?

‹‹አንተን ልሰርቅ ነው››

‹‹ ምን?››

አጥር ላይ ያለው ሰውዬ ወዲያውኑ በጥይት አናቱ ላይ ሁለት ጊዜ ተኩሶ ጣለውና ከአጥሩ ወርዶ አመለጠ።ካድሬው የልጁን መገደሉን ሰማ ።ነገሩ ተሸፋፈነ ።ሲሳይም የኢህአፓ አባል ነው ተብሎ እንዲወራበት ተደረገ።ሁኔታውም እንዲድበሰበስ ተደረገ።

ሁለቱ ገዳዮች በማግስቱ ሌላ ሥራ አላቸው። ከተማው ውስጥ ያስቸገራቸው ሌላ ሰው ነበር። የመንግስት ባለስልጣን ነው። ስለእነሱ የሚውቀው ሚስጥር ስላለ ሪፖርት ሊያደርግባቸው ነው። ስልክ ደወሉለት። ያነሳው እሱ ነበር ። ‹‹ሃሎ›› አለ።

‹‹ አቶ እከሌ ነዎት?››

‹‹አዎን ነኝ››

‹‹ ደህና ነዎት?››

‹‹ ማን ነህ አንተ?››

‹‹አያውቁኝም››

‹‹ ታዲያ ለምን ደወልክ?

‹‹ ለጥብቅ ጉዳይ ፈልጌዎት ነው››

‹‹ ለምን?››

‹‹ሁለት ልጆችዎ.....››

‹‹ ታዲያ ምን ይሁን››

‹‹ ቆንጆና እንቦቃቅላ ናቸው››

‹‹ ምን እያልክ ነው?››





‹‹እነሱን ማጣት ይፈልጋሉ?››

‹‹እንዴት?››

‹‹ ጠብቀን እንገላቸዋለን››

‹‹ምን አልክ?››

ሰውየው ደነገጡ ምንም አብዮትና ትግል ላይ ቢሆኑም ማንኛውም ነገር ከልጆቻቸው አይበልጥም። የመስማማት በሚመስል መልኩ ‹‹ልጆቼን እንዳትነኩ›› አሉ

## ምዕራፍ 16

### ተኳሹ ቆርቆሮ

ለቀስተኛው ወጣ ገባ እያለ ነው የሚያለቅሰው፡፡ድንገት የሆነ ሰው ቢመጣ ችግር ላይ እንዳይወድቁ እየተጠነቀቁ ነው፡፡ለቅሶው ደግሞ የተመጠነና በሹክሹክታ ውስጥ ያለ ንግግር ነው የሚመስለው፡፡ ‹‹…እህህህ…..እህህ ….››በሚል አይነት ድምጽእየተካሄደ ነው፡፡ ሲቃ የታከለበት፤ እልህና ቁጭት የተቀላቀለበት ድምጽ ሲከተል ደግሞ የለቅሶውን ስሜት ከፍ ያደርገዋል፡፡ከውጭ በቃፊርነት የቆመው ሰው ወደ ውስጥ በፍጥነት ገብቶ‹‹….. እናንተ ድምጽ ቀንሱ እንጂ!!!!!›› በሚል ማስጠንቀቅ ሲጀምር ለቅሶውከነበረበት ከፍታ ዝቅ ብሎ እንደገና ውስጥ ለውስጥ በእንጉርጉሮ መልክ ይቀጥላል፡፡

እዚህ ግቢ ውስጥ እንኳን በለቅሶ መልክ በሌላው ጉዳይ ይሄን ያህል ሰው መገኘት የለበትም፡፡አንድ እንግዳ እዚህ ቤት ሲመጣ ከነበረበት ክፍለ ሀገር ወይም ከቀበሌው ሰላማዊሰውመሆኑን የሚገልጽ ሸኚ ደብዳቤ ይዞሊገኝ ይገባዋል፡፡እዚህ ግቢ ውስጥ ሰርግ ወይም ማህበር ቢኖር እንኳን ለቀበሌው አመልክቶ ፈቃድ ሲገኝ ብቻ ነው ማከናወን የሚቻለው፡፡ካለበለዚያ ሰዎች በአንድ ቤት እንዲሰበሰቡ ይሄ ቀበሌ አይፈቅድም፡፡አሁን ግን እዚህ ግቢ ሰዎች ተሰብሰበው ለቅሶ መካሄዱ በፍጹም አደገኛ ነው ፡፡ሟች የአብዮቱ ጠላት ተብሎ ነው የተገደለው፡፡ግድያውን በጸጋ መቀበል እንጂ መቃወምና ማልቀስ አብዮቱን ማፍረስ በመሆኑ ከተደረሰበት እጅግ ከባድ ዋጋ ያስከፍላል ፡ ፡ዋጋውም ሞትን ያመጣል፡፡እናም እነዚህ ሰዎች ለሞተ ሰው እያለቀሱ ሞትን ቶሎ ና በሚል እየጋበዙት ነው፡፡

ብርሀኔፑሳ እዚህ ቤት የተገኘው የራቀም ቢሆን ዝምድና ስላለው ነው፡፡ወደግቢው የዘለቀው ለሰላምታ ነበር፡፡በዚህ አካባቢ ባለፈ ቁጥር የዚህን ቤት ሰዎችሰላም ብሎ መሄዱ የተለመደ ነው፡፡ዛሬ ግን





በሩው ላይ ሲደርስለሰላምታ የሚዘረጋ እጅ አልነበረም፡፡ ሰዎች ተሰብስበው እያለቀሱ ነው የደረሰው፡፡የለቅሶውን ሁኔታ አይቶና ተመልክቶ ማንንም ሳይጠይቅ ማን እንደሞተ ገብቶታል፡፡በምን እንደተገደለ በእለቃቀሳቸው አውቋል፡፡የተሰበሰቡትን እንግዶች ሊመለከታቸውየቅርብ ሰው ስለሆኑ ለቅሶውን መቀላቀልና መሳተፍ የግድ ነው፡፡ድምጽ አልባ ለቅሶ በየአካባቢው የተለመደ ነው፡፡እንባ ይወርዳል ድምጹ ግን የታፈነ ነው፡፡

በኢህአፓ ለተገደለ ሰው ለቅሶ መድረስ ምን እንደሚያስከትልት ብርሀኔ አልጠፋውም፡፡በዚህ ሁኔታ ግቢው ውስጥ ገብቶ ዝም ብሎትቶ መሄዱም ከሰዎቹ ጋር እንደሚያቆራርጠውያውቃል፡፡ነገር ግን በፍጥነት ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ይኖርበታል፡፡የሟች እናት እሜታቸው በተጎዳ ሁኔታ አንጀታቸውን ይዘው ያለቅሳሉ፡፡ ሲብስባቸው መሬት ወድቀው ይንከባለላሉ፡፡አሁን የተገደለው ሁለተኛ ልጃቸው ነው፡፡ታላቅየው ባለፈው ሳምንት ተገደሎ ሀዘናቸው ሳይበርድነው ይሄኛው ዛሬ የተደገመው፡፡

ነገሩ አሳዛኝ ቢሆንም ከቤተሰብ ውስጥ ሁለትና ሶስት ሰው ለአብዮቱ መገበር ብዙ ቦታ የተለመደ ነው፡፡ ወደ ግቢው እንደገባ ሁኔታውን ተመልክቶ የሆነ ድምጽ‹‹ብርሀኔ››አለ

‹‹አቤት››

‹‹ይሄ ነገር ጥሩ ነው?››

‹‹የቱ?››

‹‹እዚህ መገኘቱ››

‹‹ሰዎቹ እኮ ዘመድ ናቸው››

‹‹እና››

‹‹እንዲህ ሆኖ ጥዬ መሄድ አለብኝ?››

‹‹ሰዎቹ ከመጡ ምን እንደሚከተል ታውቃለህ?››

‹‹እነማን?››

‹‹አብዮት ጥበቃዎቹ››

‹‹እሱማ ከባድ ዋጋ ያስከፍላል››

‹‹እና ብትሄድ አይሻልም››

‹‹እንደዛ ላድርግ››

‹‹እዎ ቶሎ ሽሹ››

‹‹እሺ››

‹‹ፍጠን... ፍጠን››

ብርሀኔ ከራሱ ጋር ተነጋግሮ ለመሄድ ወሰነ፡፡ ከዚህ ግቢመውጣት ብቻ ሳይሆን አወጣጡንም ማስተካከል አለበት፡፡በዋናው በር ከወጣ ሰዎች ሊመለከቱት ይችላሉ፡፡እዚህ ቤት ውስጥ ለቅሶ ነበር ተብሎ ከተጠቆመ እነማን ነበሩ የሚለው ነገር ሲጣራ ስሙ መገኘት እንደሌለበት አውቋል፡፡እዚህ ነበረ ከተባለ ነበረ ብቻ ሳይሆን ለቅሶውን በአስለቃሽነት የመራው እሱ ነው በሚል ታርጋ ተለጥፎበት ፍዳውን ማየቱ አይቀሬ ነው፡፡ እናም እዚህ ግቢ አልነበርኩም ለማለት ሰዎች አይተነዋል ብለው እንዳይመሰክሩበት በጓሮ በር ለመውጣት ወሰነ፡፡ እናም ከራሱ ጋር ተነጋግሮ በወሰነው መሰረት ፊጥኖ ግቢውን መልቀቅ አለበት፡፡እህህህ እያለ ከሚያለቅሰው ሰው መሀል ወደ ሽንት ቤት የሚሄድመስሎ ወደ ጓሮው በር እያማተረ ሳለ ከኋላው የመጣ አንድ ሰው እጁን ሲይዘው ለመራመድ የሰነዘረውን እግሩን እዛው ባለበት አቆመው፡፡የያዘውን እጅ ዞር ብሎ ሲመለከት እሳቸው ናቸው‹‹እቴቴ››አለ

‹‹አቤት››

‹‹ሰላም ነዎት››

‹‹ምን ሰላም አለ ጨረሱን እኮ››

ሴትየዋ ጎረቤቱ ናቸው፡፡ ለብርሃኔ ጎረቤት ሲባል ከጎን በአጥር የተለየ ሳይሆን ከርቀት ያለውም ግቢ ጎረቤቱ ነው፡፡ ከሁሉም ስለሚግባባና ለችግራቸው ደራሽ ቤተሰብ ነው፡፡ ሴትየዋ ሰውነታቸው ወፍራምና ግዙፍ ነው፡፡ ፈጥኖ ለመሄድ ሳይሆን ለመራመድ እንኳን ሰውነታቸው እንደልብ የሰጠ አይደለም፡፡ አንድ ቦታ ከቆሙ ወይም መራመድ እንደጀመሩ ሰው መደገፍ ወይም የሰው እጅ መያዝ አላባቸው፡፡እጃቸው ግን እንደብረት የጠነከረ ነው፡፡የብርሀኔን እጅ አንጓ ጨብጠው ሲይዙ የፖሊስ ካቴና ውስጥ የገባ ነው የመሰለው፡፡





ሴትየዋ የብርሃኔን እጅ በአንድ እጃቸው ይዘው በሌላኛው እጃቸው ደረታቸውን ቀስ አድርገው እየመቱ ለቅሶውንመሳተፍ ጀምረዋል፡፡ሚቿን እንደልጃቸው ስለሚያዩትነው እዚህ የተገኙት፡፡ ሴትየዋ እያለቀሱ እንደገናም ከብርሀኔ ጋር እያወሩ ነው፡፡ብርሀኔ ሴትየዋንያከብራቸዋል ብቻ ሳይሆን በጣም ያከብራቸዋል፡፡ከንጉሱ ዘመን ጀምሮ ቤተመንግስት ጠጅ ጣይ ስለነበሩ የተከበሩ ናቸው፡፡ ሁሉም ሲገናኙ ‹‹እንቴ›› ብሎ ነው የሚጠራቸው፡፡እጁን ይዘው ለቅሶ ስለጀመሩ ነገሩ ስጋት ውስጥ ከተተው፡፡ድንገት ሰዎች ከተገኙ ለእርሱ ጥሩ አይደለም፡፡

ሰዎቹ መምጣታቸው ብቻ ሳይሆን ሰላይም ሆነ ጠቋሚ ሊኖር ይችላልየሚል ስጋት ነበረው፡፡ቶሎ ፈጥኖ ባለመሄዱ ራሱን ወቀሰ፡፡ ሴትየዋ እጅ ውስጥ መግባቱ ጥሩ ግዜ እንዳመለጠው ተረድቷል፡፡ አሁንም ግዜ አለው፡፡ምክንያት ፈጥሮ ቶሎ ግቢውንመልቀቅአለበት ጭራሽ ሴትየዋ በለቅሶው እንዲያጅባቸው እየገፋፉት ነው፡፡ እሱ ደግሞ ለቅሷቸውን እንዲያቆሙ ዘዴ እየፈለገ ነው፡፡ሴትየዋ ድምጻቸው ከፍ እያለ፤እንደናም ከፍ እያለ ሄደ፡፡እንደገናም በበለጠ ሙክ እያለ ሄደ፡፡ብርሀኔ ድንገት አቋርጧቸው‹‹እቴቴ››አለ

‹‹አቤት››

‹‹እረጋ በሉ እንጂ››

‹‹ምን አልክ!!››

‹‹ተረጋጉ እያልኩ ነው››

‹‹ምነው ብርሀኔ ሚቿ ልጁ እኮ ነው››

‹‹እንደርሱ ማለቴ አይደለም››

‹‹መግደላችሁ አንሶ እታልቅሱ ትለናለህ››

‹‹እኔ ምን አደረግሁ››

‹‹አታልቅሽ አልከኝ››

‹‹አብዮት ጠባቂዎቹ ከመጡ ለእርሶ ጥሩ አይደለም ማለቴ ነው››

‹‹ይምጡ ማን ይፈራል!!!!››

‹‹ለእርሶ ብቻ ሳይሆን ለሁላችንም ጥሩ አይደለም››

‹‹አትፍራ ባክህ››

‹‹ለእኔ እንኳን ችግር የለም፤ለእርስዎ ግን......››

‹‹ምን አልክ!!!!!››

‹‹ቤተመንግስት ስለነበሩ››

‹‹እና ››

‹‹የንጉሱ ደጋፊ ነዎት በሚል....››

‹‹ብሆንስ ደግሞ ይምጡ ልክ ልካቸውን ነገራቸዋል››

በዚህ ግዜ አንድ ሰው ወደ ግቢው ገባ፡፡የሚፈልገው ሰው ያለ ይመስል ማማተር ጀመረ፡፡ሁሉምማልቀሱን አቁሞ መሬት መሬት እየተመለከተ ምንም እንዳልተፈጠረ ለማስመሰል ሞከረ፡፡ሴትየዋ ድንገት ዝም አሉ፡፡ ብርሀኔ ‹‹እነርሱ ናቸው››አለ

‹‹ማን?››

‹‹ደህንነቶች!!!!››

‹‹ይሄ?››

‹‹አዎ››

‹‹እኔ ምንን አላልኩም››

‹‹አውቃለሁ››

‹‹ሰውየውን ታውቀዋለህ እንዴ››

‹‹አዎ››

‹‹ንገረዋ!!!››

‹‹ምኑን?››

‹‹አብዮቱን እንደምደግፍ››

‹‹አውቃለሁ››

‹‹ንገረው ነው ያልኩህ››

‹‹ያውቃል እሱም››

‹‹ምኑን?››

‹‹አብዮቱን እንደማይደግፉ››

‹‹በምን አወቀ?››

‹‹ቤተመንግስት ስለነበሩ››

‹‹ቢሆንስ አብዮቱን መደገፍ አልችልም እንዴ!!!!››

‹‹አሁን እጀን ልቀቁኝ››

‹‹ንገረዋ››

‹‹ምኑን››





‹‹አሁን ያልኩህን››

‹‹እሱም እኮ አብዮቱን አይደግፍም››

‹‹ደህንነት ነው አላልከም››

‹‹አይደለም እኔን ፈልጎ ነው የመጣው››

‹‹እንደዛ ነው እንዴ››

‹‹አዎ››

ሰውየው የብርሀኔ ጓደኛ ነው፡፡ወደ ልምምድ እንዲሄዱ ለመጥራት ነው የመጣው፡፡ እዚህ ግቢ ሰላም ብሏቸው እንደሚመጣ ነግሮት ውጭ ጠብቀኝ ብሎት ስለቆየ ነው የመጣው ፡፡ሴትየዋ የተነገራቸውን ከሰሙ በኋላ እጁን ቀንጥጠውት ማንም እንደማይፈሩ ነገሩት‹‹አንተ ግን ትፈራቸዋለህ?››አሉት

‹‹ለምን ፈራቸዋለሁ››

‹‹ታድያ አታለቅስም››

‹‹እያለቀስኩ እኮ ነው››

‹‹ምን ታለቅሳለህ ጭራሽ አታልቅሱ እያልከን.....››

‹‹እኔ ለእናንተ ብዬ ነው››

‹‹ቤታችን እኮ ነው ማልቀስ መብታችን ነው››

‹‹ልክ ነው ሰው ከበዛ ተጠቁመውከመጡ ጥሩ አይደለም››

‹‹አንተ ግን ከእኛ ነህ ወይስከእነርሱ ጋር....››

‹‹ከእናንተ ነኝ››

‹‹አይመስለኝም››

‹‹እኔም እኮ ተሳዳጅ ነኝ››

‹‹ምን አልክ?››

‹‹እያሳደዱኝ ነው››

‹‹የእኛ ከሆንክ እናልቅስ ሟቹ ደግሞ ወዳጅህ ነው››

ብርሀኔ ነገሩ አስፈራው፡፡ ሴትየዋንጉስ ናፋቂ ናቸው፡፡ ከእሳቸው ጋር እዚህ ያልተገባ ለቅሶ ቤት መታየቱ አደገኛ ሆኖበታል፡፡ለመሄድ ቢወስንም ሴትየዋ እጁን እስካለቀቁት ድረስ ንቅንቅ ማለት አልቻለም፡፡ የቀበሌው ሰዎች፣ ደህንነቶች ወይም አብዮት ጠባቂዎች ተጠቁመው ከመጡ አለቀለት፡፡ከውጭ እንዲጠብቅ የተመደበው ሰውመዘናጋቱ አይቀሬ ነው ፡፡ቅድም እንኳን ጓደኛው ሲገባ ያቀመው ሰው የለም፡፡

ታጣቂዎቹ ከመጡ ሀጢአቱን ከፍ ያደርገዋል።አብዮቱን እየተፈታተነ ነው በሚል እየተከታተሉት መሆኑን ያውቃል።እናም ቶሎ ብሎ ዘዴ ፈጥሮ ማምለጥ አለበት። በርግጥ አሁን ያለበት የለቅሶ ሂደት ድምጹ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው። ሴትየዋ ግን ስሜታቸውን መቆጣጠር ስላቃታቸው መንስቅስቃቸው በርትቶ ድምጻቸው ከፍ እያለ ነው። የእለቃቀሳቸው ሁኔታ ቤተሰቡን ለከፍተኛ ጩኸታማ ለቅሶ እየገፋፋ ነው።ሴትየዋን መቆጣጠር እንዳለበት አውቋል ።

አንድ ግዜ አምልጧቸው ከተደበላለቀና ሁሉም ጩኸቱ ላይ ከተሳተፉበትመንገደኛው በራሱ ሰምቶ ስለሚጠቁም ታጣቂዎቹ ከተፍ ማለታቸው አይቀርም። ይሄኔ ብርሀኔ አለቀለት።እሱ ደግሞ የሚያስለጥንበት ቡድን ተጫዋቾች ኢህአፓ ናቸው በሚል ውንጀላ ደርሶበታል። እነርሱን እንዲያጋልጥና የጠፉትንም እንዲያመጣጫና እየፈጠሩበት ነው። የቡድኑ ተጫዋቾች ደርግን የሚቃወም ወረቀት እርሱ ባለበት ክበተኑ በኋላ ጭንቅ ውስጥ ገብቷል።በተለይ እሱ ክለብ ለመጫወት ከሌላ ቀበሌ የመጣው ልጅ በስሙ ቤት ተከራይቶለታል። ዋስ ሆኖ ፌዴሬሽን ፈርሞለታል። ልጁ ግን የታወቀ የኢህአፓ ስኳድ ሆኖ በመታሰሩ ጣጣ ውስጥ ገብቷል።አሁን ደግሞ እዚህ ለቅሶ ቤት ከተያዘ ወረቀት አስበታኝ ብቻ ሳይሆን ለኢህአፓ ሚኞች አስለቃሽ በሚል እስር ቤት ይወረውሩታል።ማሰር ብቻ ሳይሆን እንደሚሰቅሉት ያውቃል። አብዮት ጠባቂዎቹ በተለይ አንዳንዶቹ ባገኙት ቁጥር ሲዝቱበት አንድ ቀን እንዲህ አይነት ቦታ እጃቸው እንደሚገባ የገመተ አይመስልም።በዚህ ሁኔታ ከመያዙ በፊት ማምለጥ አለበት። ሴትየዋ አሁንም እጁን ይዘው ለቅሶውን እያሞቁትና እያጋሉት እያጋጋሉት ነው።

## እንደገና ወደ ኋላ

በአጎራባች ቀበሌ ተኩስ እየተሰማ ቢሆንም ወደዚህ እስካልመጣ ‹‹እህህ ….›› የሚለው ለቅሶ እንደቀጠለ ነው። የሰውየው ሁኔታ ግን ከእህህ አልፎ ድምጹ ከፍ እያለ ነው። ይሄ ነገር ለብርሀኔ አላስደሰተውም እናም ከግቢው ለመውጣት እየተዘጋጀ ነው።ሴትየዋን መሰናበት አለበት።አሁን ይዘውት እያወሩ ባለበት ግዜ ድንገት ግቢ





ውስጥ ተረረረረረረረረም በሚል ከፍተኛ ተኩስ ተንጣጣ። እንዲህ ባለ ከፍተኛ ድምጽ ሊንጣጣ የሚችለው ቺቺ ወይም መትረየስ ነው ።ይሄ የተኩስ ድምጽ ግቢ ውስጥ እንደተሰማ ብርሀኔ ሴትየዋን ከእጁ ላይ ለማስለቀቅ ቢሞክርም አጥብቀው ስለያዙት አልቻለም። በዚሁ ሰከንድ እትቱ የሚላቸው ሴትዮ እንቺ አስኝቶ ‹‹ልቀቂኝ›› ብሎ እጃቸውን ነክሶ ከግቢው ፈትለክ ብሎ ወጣና እግሬ አውጭኝ ብሎ ቁልቁል ወደታች መሮጥ ጀመረ። ዝናብ ዘንቦ ሰፈሩ በጎርፍና በጭቃ ርሶ ስለነበር ውሃውን እያንቦራጨቀ ቁልቁለቱን ተያያዘው። እጁን ከሴትዮዋ እስኪያስለቅቅ ድረስ ያ እንደመብረቅ የተስገመገመው የተኩስ ድምጽ ግቢው ውስጥ እንደተንጣጣ በድንጋጤ እሱን ቀድመውት የሮጡት ሶስትና አራት ሰዎች ሊደርስባቸው ባይችልም በሌላ አቅጣጫ እየሮጠ ነው። ከእነርሱ ጋር አብሮ መያዝ የለበትም። እነርሱም እይታ ውስጥ ስለገቡ በነርሱ አቅጣጫ መሄድ ጥሩ አይደለም። ከኋላ አንድ ሴትና ሁለት ወንድ እየተከተሉት መሆኑን አውቋል። ‹‹አለቀልን…..›› እያሉ ስለሚሮጡ ከዚያው ግቢ አምልጠው እንደወጡ ገምቷል። አሁን የእሱን ማምለጫ ማመቻቸት አለበት። ማን ጠቁሞባቸው እንደሆን ግራ ገባው። እዚህ ግቢ ውስጥ የተሰበሰቡትን ሰዎች አይቷቸዋል። አንዳቸውም ከአብዮት ጥበቃዎች ጋር ግንኙነት አላቸው ብሎ አይገምትም። ለቅሶው ደግሞ እህህህ ቢሆንም ድምጹ ከግቢው ውስጥ አልፎ ውጭ እንደማይሰማ አረጋግጧል። ምናልባትም ጋቢ አድርጎ የሚያለቅሰው ሰውዬ ስሜቱን መቆጣጠር አቅቶት ከፍ እያለ መሄዱ ደስ አላለውም ነበር። ምናልባትም እዚህ ግቢ የኢህአፓ ወጣት እንደሞተ ስለሚታወቅ የሰውየውን ከፍ ያለ ድምጽ ሰምተው ወደግቢው እንደተኮሱ ጠርጥሯል። ለማናቸውም ያ ሁሉ ተኩስ ሲንጣጣ አንድም ጥይት እንዳልነካው አረጋግጦ ከአካባቢው ርቋል።ከዚህ በፊት ለሞተ ኢህአፖ በትኩሱ ሲለቀስ ግቢ ውስጥ ገብተው ቤተሰቡን በጥይት መትተው መሄዳቸውን ያውቃል።



*የመጋቢቱ ስሰሳ*

ብርሀኔ ጭቃውን እያተራመሰ ሲሮጥ ተኳሾቹ ሳያዩኝ አይቀርም ብሎ ስጋት ውስጥ ገብቷል። ሌላ ተኩስ ከሚሮጥበትበግራ በኩል ትንሽ ራቅ ብሎይሰማዋል። በሌላ አቅጣጫ የሮጡትን ደርሰውባቸው እየረፈረፏቸው እንደሆን ገምቷል።አሁን እሱ የያዘበት መስመር ጥሩ እንደሆነ አውቋል። ከአካባቢው በሰላም እስካልራቀ ድረስ ይሄ ተኩስ እሱ ጋር እንደሚመጣ አልጠፋውም።አሁን እየሰማ ያለው ተኩስ ምናልባት ከቦ ለመያዝ የታሰበ ይሆን እንዴ? ብሎ መገመቱ አልቀረም።ተኩሱ ከግራ ስለተሰማ በቀኝአቅጣጫ ታጠፈና ሰዎች ወደበዙበት አካባቢ ተቀላቀለ። የአዲስ አበባ ህዝብ መጋቢትን በተለየ ሁኔታ ‹‹የሞት ወር›› ብሎታል። ደርግ የኢህአፓን መዋቅር አፈራርሶ ለማጥፋት የመጋቢቱ አሰሳ ተብሎ በተሰየመው ዘመቻ ከመጋቢት 15 እስከ 18 ቀን ማንም ሰው ከቤቱ እንዳይንቀሳቀስ አድርጎ ትራንስፖርት አስቁሞ ትምህርት ቤት አዘግቶ አሰሳ በማድረግ ብዙ ሰው ተገድሏል። ከመጋቢት 19 በኋላ የቤት ለቤት አሰሳ ባይኖርም የተረፉትን እያሳደደ የሚገድልበት ግዜ ነበር። ብርሀኔ የተሳተፈበትም ለቅሶ በመጋቢት መጨረሻ አካባቢ የተደረገ በመሆኑ ግድያው





ያልበረደበት ግዜ በመሆኑ በማንኛውም ሰአት ሞት አጠገባቸው አለ። ተኩስ በተሰማ ቁጥር ሁሉም በርግጎ እግሬ አውጭኝ ማለት ነው።

## እንደገና የሆነ ቦታ

ብርሀኔ በዛ በተንጣጣው ተኩስ በግቢው ውስጥስንት ሰው እንደሞተ ማወቅ ፈልጓል።ተኳሾቹ ውስጥ ገብተው እነማን በለቅሶው እንደሳተፉ መጠየቃቸው አይቀርም።በቦታው መኖሩ ከታወቀ ዋናው አስለቃሽ እሱ ነው በሚል ጣጣ ውስጥ ሊገባይችላል።በኢህአፓ ለቅሶ ላይ የተገኘ፣ያለቀሰ ፣ያስለቀሰ ምን እንደሚጠብቀው ያውቃል። በቤተሰብ በኩል ‹‹ለቅሶዬን በላህ››በሚለውመወቃቀስ ባይኖርም እንዲህ አይነቱ ማስተዛዘን ወቅቱ የሚጠይቀው ነገር ነበር። ከሩጫው በኋላ በግማሽ ተረግጋቶ አንድ ሻይ ቤት ገብቶ ነገሩን ማረጋጋት ፈልጓል። አሁን ከሩጫ ወጥቶ ሰላማዊ ቦታ ነው ያለው። ቦታው አስተማማኝ አይደለም ብሎ ስለገመተ ድጋሚ ሩጫ ሊያስፈልግ ስለሚችል መዘጋጀት አለበት።እዛው ባለበት ሁኔታውን መገምገም ጀመረ።እጁን ከሴትየዋ ላይ አስለቅቆ የሄደበት መንገድ ትክክል እንደሆነ አምኗል ። እሳቸው እንደያዙት ቢቀር ኖሮ አልቆለት ነበር።ሴትየዋ ማምለጥ ስለማይችሉ እንደሚገደሉ ይገምታል። መሮጥ ቀርቶ መንቀሳቀስ አይችሉም።እጃቸውን ሲያስለቅቅ ሳይወድቁ አይቀርም።ምናልባት ከመገደላቸው በፊት ከተያዙ አስለቃሹ ብርሀኔ ነው በሚል ከመሰከሩበት አለቀለት ብቻ ሳይሆን ፋይሉን እንደሚዘጉት አይጠፋውም። አጠገቡና በዙርያው ያሉት ሰዎች ብዙዎቹ ታስረዋል ፣ተገድለዋል። እሱም ቢሆን ከአንዳንድ ቦታ በተአምር እንደተረፈ ያምናል።

ከጉዳዩ መራቅ ብዙ ግዜ ሞክሯል።ነገርየው እራሱ ወደ እርሱ ስለሚመጣ ማምለጥ ተቸግሯል ።ግን አንዳንድ ቦታዎች መሸሽ እየቻለ ሄዶ ጥልቅ ይላል።አሁን እዚህ ለቅሶ ቤት መሄድ አያስፈልገውም ነበር።ግን ተገኘ። ምን ሲያቀብጠው እዛ ግቢ እንደገባ ገራ ገብቶታል።በየቀኑ እዛ ሰፈርና አካባቢ የሚሰማውና የሚታየው ነገር ሞትና እስር ነው።ዛሬን ይሄው ጉዳይ ተከትሎት መጥቷል። ዋናው ነገር ሰውየው ድምጹን ከፍ ባያደርግ ኖሮ ያ ሁሉ ተኩስ ባልተንጣጣናይሄ ሁሉ ጣጣ ባልመጣ ነበር።ሰወዬው በተኩሱ መሀል

የመጀመርያው ሟች እንደሆን ገምቷል።ዛሬ ባይሞት እንኳን ቀበሌ ወስደው በጥይት ይሸኙታል። ምክንያቱ ደግሞ ከሌላ ቦታ ነው የመጣው። በዚህ መጋቢት ወር አሰሳና ግድያ በበዛበት ግዜ ከሰፈሩ ርቆ እዚህ መገኘቱ ሌላ ተልእኮ ይዞ ነው የመጣው በሚል በእጅጉ ያስጠይቀዋል። በዛ ግቢ የተነሳው ግርግር እስኪበርድ እዚህ ሆኖ መጠበቅ አለበት። ወደ ሌላ ቦታ መሄድ የለበትም።ቅድም ግቢ ውስጥ ተኩስ ሲንጣጣ ቀድሞ ሮጦ ያመለጠውን ልጅ አየው።ከተለያዩ ቢያንስ ከሰላሳ ደቂቃ በላይ ያልፈዋል። እሱ መረጃ እንዳለው ገምቷል። ልጁን ያውቀዋል። ጠራውና‹‹እንዴት ነህ?››አለው

‹‹እለሁ››

‹‹ወደየት እየሄድክ ነው?››

‹‹የትም አልሄድም››

‹‹ተርፋሃል አይደል!!››

‹‹አዎ››

‹‹ምንም ጥይት አልመታህም?››

‹‹እረ!! አላገኘኝም›››

‹‹ወደዚያ ተመልሰህ ሄደህ ነበር?››

‹‹አልሄድኩም››

‹‹ምንም አልሰማህም!!››

‹‹ማለት››

‹‹የሞተ ሰው››

‹‹እኔ እራሴ ተደናግጬ ወደሰፈሩ አልተመለስኩም››

‹‹አሁን ትመለሳለህ?››

‹‹ዛሬ ወንድሜ ጋር ነው የማድረው››

‹‹ለምን?››

‹‹ነገሩ ጥሩ አይደለም››

‹‹ካንተ ጋር የነበረው ጓደኛህስ?››

‹‹የቱ?››

‹‹አብሮህ ሲሮጥ የነበረው››

‹‹ተለያየን እኮ››

‹‹የት ?››

‹‹መታጠፊያው ላይ እሱ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ››





ልጁ በእጅጉ ተደናግጧል። እጁ ኢህአፓ ውስጥ እንዳለበት ሁኔታው ይመሰክራል። እዛ ግቢ ለሰቅሶ ብቻ ሳይሆን ለአንድ ተልእኮ እንደመጡ ጠረጠረ።ከዚህ ልጅ ምንም መረጃ እንደማያገኝ አውቋል። ስለዚህ እዚሁ ሻይ ቤት አካባቢ ባለበትሆኖ መጠበቅና መረጃ ሲያገኝ ወደ ሰፈሩ መመለስ እንዳለበት አምኗል። እናም ባለበት ቦታ ሆኖ የሚመጣውን ነገር መጠበቅ ነበረበት። ነገሮችን ደጋግሞ መገምገም ጀመረ። ድንገት አንድ ሰው መንገዱን ሲሻገር ተመለከተ። ሰውየውን ይመስላል ብሎ አሰበ። እሱ ወዳለበትአቅጣጫ ነበር የተሻገረው። ሰውየው እየቀረበ ሲመጣ ቁርጥ እሱን ይመስላል፡ ፡ደግሞም ተመሳሳይ ጋቢና ልብስ ነው ያደረገው። አይኑን በደምብ ከፍቶ ሲመለከት እራሱ ሰውየው ነው። እንዴት ከሞት ተረፈ ብሎ ተገርሟል። መገረም ብቻ ሳይሆን ተደንቋል። ከመራቁ በፊት ሰውዬውን ሄዶ ሊያናግረው ፈለገ። ግን ደግሞ ሰላይ ሆኖ እኔን ቢያስይዘኝስ ብሎ ተጠራጠረ። ሰውየው እየሄደ ነው። እየሄደ ብቻ ሳይሆን ከአካባቢው እየራቀ ነው። ሰውዬው የሴትየዋ ወንድም ነው። የልጁ መሞት እንገብግቦት እንዴት እንዳለቀሰ ስላወቀ ለገዳዮቹ ትልቅ ጥላቻ እንዳለው መገመት አያዳግትም። እናም ሰላይ አይሆንም ማለት ነው። ስለዚህ ሰውየውን ማናገሩ አይከፋም ብሎ ወሰነ። ወስኖም እዛው አልተቀመጠም። ሮጦ መሄድ ጀመረ። ብርሀኔ ወደሰፈሩ ከመመለሱ በፊት እዛ ግቢ ምን እንደተፈጠረ ስለእሱም ታውቆ እንደሆን ማረጋገጥ የሚችለው ከዚህ ሰውዬ ነው። ከሻይ ቤቱ እንደወጣ ሄዶ አገኘው‹‹……ሰላም ነው››አለው። ሰላም እንዳልሆነ እኮ ያውቃል። ይህን ወሬ ለመጀመር ብሎ ነው። ሰውየውም ‹‹እንዴት ነህ?›› አለ

ብርሀኔን በፍጥነት‹‹አውቅከኝ››አለው

‹‹አዎ ግን….››

‹‹ግን ምን….››

‹‹ሴትየዋን ጎዳሃት እኮ››

‹‹ማንን››

‹‹እቴቴን››

‹‹ምን ሆኑ?››

‹‹ምን አልክ?››
‹‹ተገደለች እንዴ?››
‹‹ምን እያልክ ነው››
‹‹ተጎዳች ወይ››
‹‹አዎ ስትገፈትራት እግሯ ተሰበረ››
‹‹እግሯ!!!››
‹‹አዎ ፤ግን ለምን ገፈተርካት?››
‹‹ምን ላድርግ››
‹‹እንዴት ምን ላድርግ?››
‹‹እኔ ልሙት እንዴ››
‹‹ማነው የሚገድልህ?››
‹‹ትቀልዳለህ ልበል ››
‹‹አንተ ነህ እየቀለድክ ያለኸው››
‹‹እንዴት››
‹‹እንደዛ እየተኮሱብን››
‹‹አልገባኝም››
‹‹እንዴት አልገባኝም ትላለህ››
‹‹ምን እያልክ ነው?››
‹‹ከዚህ በላይ ያ ሁሉ ቺቺና መትረየስ እየተተኮሰ....››
‹‹ማን ላይ?››
‹‹አንተ ላይ ነዋ››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹እኛ ላይ››
‹‹የት?››
‹‹እዚያ ግቢ››
‹‹በህልምህ ነው?››
‹‹ህልም አልከው››
‹‹አዎ››
‹‹ለመሆኑ አንተ እንዴት ተረፍክ?››
‹‹ከምኑ?››
‹‹ያ ሁሉ ጥይት ሲርከፈከፍብክ››





‹‹የምን ጥይት ነው?››
‹‹ያ ሁሉ ጩኸት››
‹‹አሁን ገባኝ››
‹‹ምኑ››
‹‹ቆርቆሮውን ማለትህ ነው››
‹‹ቆርቆሮ?››
‹‹አዎ››
‹‹አልገባኝም››
‹‹ለቆርቆሮው ነው እንደዚያ የሮጣችሁት››
‹‹የምን ቆርቆሮ?››
‹‹ቆርቆሮ ሲጮህ ጥይት መስሏችሁ.......››
‹‹ምን ማለትህ ነው?››
‹‹ማለት››
‹‹እኔ ብርሀኔ ነኝ ለቆርቆሮ የምሮጠው?››
‹‹ነው እንጂ››
‹‹አንተ እንደውም ሌላ ተልእኮ ይዘህ ነው የመጣኸው››
‹‹ምን እያልክ ነው?››
‹‹እዛ ግቢ መልእክት ልታደርስ ነው››
‹‹ለማን?››
‹‹ለማን እንደሆነ ሰዎቹ ሲመጡ ትናዘዛለህ››
‹‹እነማን?››
‹‹አብዮት ጥበቃዎቹ››
‹‹እረ እኔ ምን ነገር.....››
‹‹እንዳውም እዚህ ሁን››
‹‹ምን?››
‹‹ከዚህ እንዳትነቃነቅ››
‹‹ምን አደረግሁ››
‹‹ንቅንቅ ብትል አስይዝሃለሁ›››
‹‹ምነካህ ሰውዬ››
‹‹ሰውየ አትበል››
‹‹እንዴት››

‹‹ስውየ ማለት የእነርሱ ነው››
‹‹የማን?››
‹‹የኢህአፓ››
‹‹ኢህአፓ?››
‹‹አዎ አንተ ኢህአፓ ባትሆን ኖሮ እኔን ሰውዬ አትልም››
‹‹እረ እኔ አላውቅም››
‹‹የአብዮቱ ሰው ጓድ ነው የሚባለው ኢህአፓ ግን ሰውዬ ነው የሚለው››
‹‹ምን እያልክ ነው?››
‹‹አንተ ነህ ሰውዬ ያልከው››
‹‹ስህተት ከሆነ ይቅርታ አድርግልኝ››
‹‹እሱን የአብዮቱ ሰዎች ሲያናግሩህ መልስ ትሰጣለህ››
‹‹እኔ እኮ ሰውዬ ያልኩህ ስምህ ስለጠፋብኝ ነው››
‹‹የእኔ ስም በአካባቢው ብቻ ሳሆን በሀገሩም የታወቀ ነው ። አንተ ግን ሰውዬ የሚለውን ቃል መጠቀም ስለፈለግክ ነው›
‹‹ቢቃ ትልቅ ይቅርታ አድርግልኝ››
‹‹ምንም ይቅርታ አያስፈልግም፣ ደግሞም ያለምክንያት እንደዛ አልሆንክም››
‹‹ምኑ?››
‹‹እንዳዛ ተንገብግበክ ያለቀስከው››
‹‹ምነው እንደዛ ትላለህ››
‹‹እንዴት››
‹‹ስጋዬ እኮ ነው››
‹ላንተ?››
‹‹አዎ እሷ ትውለደው እንጂ እኔ ነኝ ያሳደግኩት››
‹‹ስለዚህ ልክ ነዋ››
‹‹ምኑ?››
‹‹ያንተን ተልእኮ ለመፈጸም ሲል ነው የሞተው››
‹‹የምን ተልእኮ?››
‹‹ምን ሆኖ የተገደለ ይመስልሃል››
‹‹እረ ተው››





‹‹አንተ ዋናው ኢህአፓ ነህ››
‹‹እረ አይደለሁም››
‹‹መሞቱ እንገብግቦኛል አላልክም እንዴ?››
‹‹ስጋየ ስለሆነ ነው››
‹‹አንተ ነህ ማለት ነው ተልእኮ እያስያዝክ ያስጨረስከው››
‹‹እረ ተው እንጂ››
‹‹ቀበሌው እንደውም እንዳንተ አይነቱን ሰው ነው ይዞ ማነጋገር ያለበት››
‹‹እረ ሰውየ ተው››
‹‹አሁንም ሰውየአልክ፤ አይለቅህም ማለት ነው››
‹‹እሽ ትልቅ ይቅርታ››
‹‹ምንም ይቅርታ አያስፈልግም እዚሁ ጠብቀኝ...››

ብርሀኔ እየተጣደፈ ሄደ። እየዞረ ሰውየውን ይመለከተዋል። ለመሮጥ የተዘጋጀ ቢመስልም እስኪ.ርቅ የጠበቀ ይመስላል። ብርሀኔ በአንደኛው አቋራጭ ታጠፈ።እርግጠኛ ሰውየው እንደሚሮጥአውቋል ፡ ደግሞም እንዲሮጥ ነው የታጠፈለት።ለቆርቆሮ ጩኸት ነው የሮጥከው ስላለው ነገሩ አሳፍሮት ነው ሰውየውን ሌላ ተልእኮ አለህ ብሎ ያጨናነቀው።መቸም በእርግጥ የሮጠው ለቆርቆሮ ጩኸት ከሆነ ይሄንን ጉዳይ ለምእተ አመታት ይስቅበታል።ግን ይሄን ነገር ሰው መስማት የለበትም።እሱ እንኳን ለቆርቆሮ ለሌላም ነገርአይበገርም ‹‹ዘራፍ ብርሀኔ!!!!!!›› ብሎ እራሱን አነቃቃና ወደ ድፍረት ተመለሰ። ግን ይሄን ጉዳይ ማረጋገጥ አለበት።ሰውየው ዋሽቶት ቢሆንስ። ምናልባት ሰውየው እውነቱን ላለመንገር ብሎ በቆርቆሮ አሳቦ ከእዚህ አካባቢ ለመራቅ ፈልጎ ቢሆንስ።

ቅድም ያገኘው ወጣት የጥይት እሩምታ ተኩስ መሆኑን ነግሮታል። ድንጋጤው ለብዙ ሰአት እንዳልጠፋ ከፊቱ ላይ አንብቦታል።በምንም መንገድ ቆርቆሮ ሊሆን አይችልም።ደግሞም ጥይ[illegible]ት ቆርቆሮ መሆን የለበትም።ቆርቆሮ መሆኑ ለእሱ ያሳፍረዋል።ጥይት ጋቢ መሆን የለበትም ብዙ ሰው ይጨርሳል።ብቻ የሆነውን ነገር ያን ካለበሰው ሰው ብቻ አምኖ መቀበል የለበትም።ደግሞ እርሱ ነበር

ሁሉ ጣጣ ያመጣው።እሱ ድምጹን ከፍ አድርጎ ባያለቅስ ኖሮ እንደዛ አይነት የተኩስ እሩምታ ባልተተኮሰ ነበር ብሎ ለራሱ ተናገረ። ሰውየው አሁን እንደተናገረው ሳይሆን ይሄ ነገር ተደርጓል።ግን ማጣራት አለበት።ሰውየው ያለውን ካመነ ወደ ሰፈሩ ይሄዳል። ሰውዬው የነገረው ውሸት መሆኑን ሲሰማው እንደገና መራመዱን እያዘገመ ወደ አካባቢው ደረሰ።

## እንደገና ወደ ኋላ

እቴቴ እጁን እንደያዙት ማነጋገር ጀመሩ። ሞራል እንዲሰጣቸውና እንዲያበረታታቸው ነበር የፈለጉት። ከመጣ ጀምሮ ግን ስለስጋትና ወዮላችሁ አይነት ነበር ወሬው። እቴቴ‹‹አንተ ትፈራቸዋለህ እንዴ››አሉት

‹‹ለምን ፈራቸዋለሁ››

‹‹ታድያ ለምን ሰውን ታዋክባለህ››

‹‹ሰዎች እየበዙ ከሄዱ ጫጫታ ይጀመራል››

‹‹ቢንጫጩስ ለቅሶ አይደለም እንዴ››

‹‹ጫጫታውን ሰምተው ታጣቂዎች ሊመጡ ይችላሉ››

‹‹ቢመጡስ ቤታችን አይደለም እንዴ››

‹‹ነው››

‹‹አንተም ከእነርሱ አንዱ ልትሆን ነው?››

‹‹እንደዛ አይደለም››

‹‹ሆነሃል መሰለኝ››

‹‹እንዴት እሆናለሁ፤እኔም ተሳዳጅ ነኝ››

‹‹ምን አልክ!!!››

‹‹እኔም ተሳዳጅ ነኝ››

‹‹ነኝ ነው››

‹‹አይደለም ሆኛለሁ››

‹‹እርግጠኛ ነህ››

‹‹አዎ እንዳውም ሙክ ብላችሁ አልቅሱ››





ሰዎቹ ድምጻቸውን ከፍ ማድረግ ጀመሩ።ብርሀኔ ነገሩ አስፈራው።ሴትዬዋ የቤተመንግስት ጠጅ ጣይ ናቸው።በዚህ ላይ ማንስ ስርአት ናፋቂ ናቸው። የቀበሌው ሰዎች ሳይቀር ሴትየዋ አብዮቱን እንደሚቃወሙ ያውቃሉ። ከአንድ ሁለት ግዜ አስጠንቅቀዋቸዋል። ከዚህ በኋላ አብዮቱን መቃወም ሳይሆን የሚቃወሙ ሰዎች ጋር ቢሆኑ ውርድ ከራሴ የተባሉ ሰው ናቸው። ... ግን የመጣ ይምጣ ብለው እዚህ ተገኝተዋል።መገኘት ብቻ አይሆን ለሞተው ኢህአፓ ለቅሶውን ማስተባበር ይዘዋል።እዚህ ያሉት ሌሎች ሰዎች እንደሴትየዋ ቤታችን ማልቀስና ማስለቀስ እንችላለን የሚል የለቅሶውን ደረጃ ከፍ ለማድረግና ስርአቱንም ለመቃወም ... የተነሱ ይመስላል። በዚህ መሀል ወታደሮች ፤የቀበሌው ሰዎች ወይም አብዮት ጥበቃዎች ብቅ ካሉ ብርሃኔ አለቀለት። የሚያስለጥንበት ቡድን ተጫዋቾች በኢህአፓነት ታስረውበት ነገሩ ሁሉ ወደ እርሱ ዞሮ ክትትል እየተደረገበት ነው።በከፍተኛ አንድ በስኳድ ደረጃ የሚፈለግ የኢህአፓ አባል እሱ ያለበት ቡድን ገብቶ ቤት ተከራይቶለታል። በሸዋ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በዋስትና ፈርሞ አስገብቶት ልጁ ሲያዝ መግቢያ ጠፍቶታል ።በእርሱ የተነሳ ጣጣ ውስጥ ገብቷል። ይሄ ጉዳይ አንድ እልባት ሳያገኝ ቀንደኛ ነው ተብሎ በተገደለ ኢህአፓ ለቅሶ ላይ መገኘቱ አደገኛ እንደሆነ ያውቀዋል። እንኳን እዚህ መገኘቱና በበሩ ማለፍ ለእርሱ ጥሩ እንዳልሆነ አይጠፋውም። በዚያ ላይ በቀበሌው ሰዎች የአብዮቱ አደናቃፊ ተብለው ጥርስ ከተነከሰባቸው ሴትዮ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ መገኘቱ ምን ማለት እንደሆነ እርሱ ያውቀዋል።ሴትየዋ አሁንም እጁን ይዘው ለቅሶ ጀመሩ። አሁን ነገሩ እየከፋ እንደሚሄድ አውቋል ።ስለዚህ በግዜ ሹልክ ማለት እንዳለበት አውቋል‹‹እቴቴ›› አለ

‹‹አቤት››

‹‹ሱቅ ደርሼ ልምጣ››

‹‹ምን ታደርጋለህ››

‹‹እቃ ልገዛ››

‹‹ሰው ላክ አንተ ከእኔ ጋር ሁን››

‹‹እዚህ እኔ ምን አደርጋለሁ››

‹‹አብሮኝ የሚሆን ሰው ያስፈልገኛል››

ማምለጫ እንደሌለው ስላወቀ የታገተ ይመስልእጁ በእጃቸው ተጠፍሮ በካቴና እንደታሰረ እዛው ባለበት ቆየ፡፡ሴትየዋ ወዲህና ወዲያ ሲሉ አብሮ መንጎራደድ ጀመረ፡፡ጋቢ የለበሰው ሰውዬ እህህ.....እህህ እያለ ወዲህ ወዲያ ይላል፡፡መንጎራደዱ ብቻ ሳይሆን ድምጽ ጨምሯል፡፡በእቴቴ ቁጥጥር ስር የነበረው ብርሀኔ ከአንድም ሁለት ግዜ ተቀመጥ ብሉታል፡፡ግን አልተቀመጠም፡፡ለምን እንደሆን እንኳ ሰውየው አልተመቸውም፡፡ ብርሀኔ በትህትና‹‹ጋሼ››አለው

‹‹አቤት››

‹‹እዚህ ጋር ተቀመጥ››

‹‹ተቀመጥ አልከኝ››

‹‹አዎ ስለደከመህ እኮ ነው››

‹‹ምኑን አረፍኩኝ ልጄን ገድለውብኝ››

‹‹እኛም እኮ ሀዘን ላይ ነን››

ሰውየው የሚሰማው አይነት ነገርአይደለም፡፡ እህህ እያለ ይመላለሳል፡፡ የዚህ ሰው እህህታ ድምጹ አሁንም ከፍ እያለ ነው፡፡ ብርሀኔ ሰውየውን እንደገና ማናገር ፈለገ‹‹ጋሼ››አለ

‹‹አቤት››

‹‹ድምጽህ እኮ ከፍ እያለ ነው››

‹‹ምኑን ከፍ አለ ታፍኜ እህህህ ብቻ ሆኛለሁ››

‹‹ከፍ ብሏል ድምጽ ቀንስ ››

‹‹ከዚህች እህህታ ምኑን ልቀንስ››

‹‹ከፍ ብሏል ሰዎች ይሰማሉ››

‹‹ግን ጮህኩ እንዴ?››

‹‹ትንሽ ከጨመረ ሰዎች ይመጣሉ››

‹‹ማነው የሚመጣው?››

‹‹ዋናዎቹ››

‹‹ገዳዮቹ ማለትህ ነው››

‹‹እንደዛ ነው እንዴ?››

‹‹ገዳይ ናቸው››

‹‹እኔ አላልኩም››

‹‹ትፈራቸዋለህ እንዴ?››





‹‹እኔ ፈርቼ አላውቅም››

‹‹እና››

‹‹ሌሎች ልጆቻችንን እንዳይገድሉ ነው››

ብርሀኔ በእቴቴ እጅ ላይ እንዳለ ነው፡፡ ሰውዬው ጭራሽ እየባሰበት ነው፡፡እጁን ወደ ኋላ አጣምሮ እህህ እያለ እንደገናም ድምጹን ከፍ እያደረገ ወዲህና ወዲያ ይላል፡፡ የግቢው ጓሮ ሰፋ ያለና በአጥሩ ጥጋ ጥግ ዛፎች ዘርዘር ብለው ተተክለው ግቢውን እንደጥላ አልብሰውታል፡፡ የዛፎቹ ቅርንጫፍ ወደታች ዝቅ ብለው ቅጠሎቹ ሰውን እንደመከለል ደርሰዋል፡፡ሰውየው ለመንጎራድና ጥግ ድረስ ሄደው ለመመለስ ቅርንጫፎቹን እየጣሰ መጨረሻው አጥር ጋር እየደረሰ ይመለሳል፡፡

ብርሀኔ የነበረው በሩ አጠገብ ነው፡፡ሰውየው እነብርሃኔ ጋር ሲደርስ ድምጹን ዝቅ ያደርጋል፡፡ወደ አጥሩ ጥግ መሄድ ሲጀምር ድምጹ ይጨምራል፡፡ሰውየው ወደ አጥሩ ጥግ ሲሄድ የዛፎቹ ቅርንጫፍ ስለሚከልለው ደርሶ እስኪመለስ ድረስ ብዙ አይታይም፡፡ አንድ ሁለት ግዜ ከተመላለሰ በኋላ ፈጠን እያለ ደርሶ መመለስ ጀመረ፡፡ይሄ ሁሉ ሲሆን ድምጹን ከፍ እያደረገ በመሆኑ ብርሀኔ ስጋት ላይ ነው ያለው፡፡ ይሄ ድምጽ ወደ ውጭ ከወጣ አብዮት ጥበቃዎች ርምጃ ሊወስዱባቸው ይችላሉ፡፡ ከዚህ በፊት ከእነርሱ ቀበሌ ቀጥሎ ባለው ቦታ ለትኩስ ሬሳ ሲለቅስ ታጣቂዎቹ ደርሰው ግርግር ተፈጥሮ እዛው ሁለት ሰው ረሽነው መሄዳቸውን ያውቃል፡፡ብርሀኔ ሰውየው ድምጹን ከፍ ባደረገ ቁጥር እዚህ ርሸና ሊመጣ ስለሚችል እጁን ከሴትየዋ አስለቅቆ ለመሄድ እየተዘጋጀ ነው፡፡መዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ወስኗል፡፡

በዚህ ሰአት ነበር ነገሩ የተከሰተው፡፡ሰውየው ፈጠን እያለ ዳር ደርሶ ተመለሰ፡፡ጥግ በደረሰ ግዜ በልጁ ሞት ውስጡ ስለተነካ የአጥሩን ቆርቆሮ ተደግፎና ተሻሽቶ ነው የሚመለሰው፡፡ በዛን ግዜ የነበረው ቆርቆሮ በምስማር ሳይሆን አንዱ ከሌላው ጋር በሽቦ የሚያያዝ ነው፡፡ ሽቦው ተጣጥፎ ትንሽ ቦታ የሚይዝ ሲሆን ሲወጠር ግን ረጅም ቦታ መዘርጋት የሚችል ነው፡፡ሰውየው ደርሶ በመመለስ ላይ እያለ መሀል ላይ ያለው የሽቦው ጫፍ የለበሰውን ጋቢ ቆንጥጣ ያዘችው፡፡ሰውየው

ዳር ደርሶ ወደፊት ሲሄድ ሽቦው እየተወጠረ፣እየተመዘዘ፣እየተለጠጠ፣ እየተሳበ ረጅም ቦታ ሄደ፡፡ሽቦው የመጨረሻ ደረጃ ደረሰና ጫፉ ከጋቢው ላይ ሲላቀቅ በፍጥነት ተወርውሮ ቆርቆሮውን ተረረረረረረረረም ሲያደርግ ድምጹ ከፍተኛ በመሆኑ መትረየስ የተተኮሰ ስለመሰላቸው ሁሉም በግቢው በር እግሬ አውጭኝ ብለው አመለጡ፡፡ በሁሉም ጭንቅላት የአብዮት ጥበቃዎቹ ከደረሱብን ይተኩሱብናል የሚል ሀሳብ ላይ ስለነበሩ ተረረረረረረረረም የሚለው ከፍተኛ ጩኸት የቆርቆሮ ነው ብለው አልገመቱም፡፡ ሰውየው በራሱ በድንጋጤ ወድቆ ከተነሳ በኋላ ነው ያረጋገጠው፡፡ ብርሀኔ በራሱ ከመጡ ይተኩሱብናል የሚል ጥርጣሬ ላይ ባለበት ግዜ ነው ነገሩ የተከሰተው፡፡ ይሄ ጉዳይ ለብዙ ግዜ ይገርመው ነበር፡፡ግዜው ተኩሶ የመግደል ወቅት በመሆኑ የመኪና ጎማ ሲፈነዳ እንኳን ማንም ሳያጣራ ተባራሪ ጥይት እንዳይበላው ሮጦ የማምለጥ ግዜ ነበር፡፡እናም ብርሀኔ ቆርቆሮ ባየ ቁጥር በውስጡ ያስቀዋል፡፡





## ምዕራፍ 17

## በቀዳዳ የታየው ልጅ

እድሩ ቀብር ትቷል፡፡ ሞትን የሚያስተናግደው በህመም በአደጋና ተያያዥነት ስሆኑ ነገሮች ብቻ ነው፡፡ ለሩቅ ዘመድ የሚያስተናግደውም ሟቹ ባረፈበት ቀበሌ በጤና ችግር መሞቱን የሚያረጋግጥ ወረቀት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡ በኢህአፓነታቸው ለተገደሉት እድሩ ምንም አይነት ነገር አያስተናግድም ፡፡በዚሁ መጋደል ውስጥ በኢህአፓ ተገድለዋል ለተባሉት ጓዶች ግን እድሩ በደምብ ነው የሚያስተናግደው፡፡ አንድ ቤት ውስጥ በኢህፓ ለሞተው ዝምታ መርጦ የመኢሶን ወይም ከደርግ ወገን ከሆነ ድንኳን ይጣላል፡ ሌላም ከእድሩ የሚገኘው ጥቅም አይቀርበትም፡፡እዚህ እድር ላይ የተገኙት እናቶች እያወሩ ነው፡፡ ሁለቱም በጣም ይቀራረባሉ፡፡ አንደኛዋ ሴትዮ በቅርብ የምታውቃትን የእድሯን አባል፡፡እንዴት ነሽ?፡፡አለቻት

‹‹እኔ ሰላም ነኝ››

‹‹ፈልገሽን እንደነበር ነገሩኝ››

‹‹አዎ››

‹‹በሰላም ነው››

‹‹ልጅሽን አኮ ላገኘው ፈልጌ አጣሁት››

‹‹የእኔን?››

‹‹አዎ››

‹‹የቱ?››

‹‹ትልቁ››

‹‹ምነው በሰላም ነው››

‹‹አረ በሰላም ነው እንዳው ሳላመሰግነው….››

‹‹ለምን ነው ምስጋናው››

‹‹የእኔን ድህነት ታውቂዋለሽ››

‹‹ማለት››

‹‹ቤቱን ማደስ እንኳን አልቻልኩም››

‹‹እና የእኔ ልጅ ምን አደረገልሽ››

‹‹በችግሬ ደረሰልኝ››
‹‹ለማስጠገን?››
‹‹እንደዛ በይው ››
‹‹በምን አቅሙ?››
‹‹ማለት?››
‹‹ስራ የለው ተማሪ እኮ ነው››
‹‹እኔም እኮ ተማሪ እንደሆን አውቃለሁ››
‹‹ኖሮት ከረዳሽ መርቂው››
‹‹እንዴ!! ብዙ ቀን መረቀሁት››

ሁለቱ ሴቶች የእድሩ ስብሰባ እንዳለቀ ይሄን ወሬ ጨርሰው ሌላ ርእስ ውስጥ ገብተው ተጨዋወቱ:: በመለያየት ላይ እያሉ የልጁ እናት የከነከናቸው ይመስላል:: ቤታቸውን ለመጠገን በገንዘብ አቅሙ እንደማይፈቅድ ያውቃሉ:: በጉልበት እንዳገዛቸው ገምታለች:: ግን እንዲህም አይነት ነገር ሲያደርግ ሁሌም እንደሚያወራላቸው ያውቃሉ::ይሄ ነገር የሚደበቅ ነገር አይደለም::ሴትየዋ አሁን የገባት ሌላ ሰው እንጅ የእሷ ልጅ እንዳልሆነ ነው::ጉዳያቸውን ጨርሰው በመለያየት ላይ እንዳሉ ‹‹እርግጠኛ የእኔ ልጅ ነው የረዳሽ?››አለች

‹‹አዎ፤ደግሞም እኔ ሳላይ.....››
‹‹እኔ ሳላይ ማለት አንቺ በሌለሽበት ማለት ነው?››
‹‹አዎ፤ቤቴን ታውቂያለሽ አይደል››
‹‹አዎ››
‹‹አሮጌ ነበር ቀለም ቀባልኝ››
‹‹ያንችን ቤት?››
‹‹አዎ››
‹‹መቼ?››
‹‹ሰሞኑን በሌሊት መጥቶ››
‹‹የእኔ ልጅ?››
‹‹አዎ››
‹‹በሌሊት ማለት?››
‹‹ሌሊት ነዋ››
‹‹አልገባኝም››
‹‹ሌሊት መጥቶ በቀዳዳ ሳየው ቀይ ቀለም ቀባልኝ››
‹‹ምን አልሽ!!!!!!!!!››
‹‹ቀለም ቀባልኝ››





‹‹ይሄን ለሰው ነግረሻል?››
‹‹ምኑን››
‹‹የእኔ ልጅ ቀለም መቀባቱን››
‹‹እረ ለማንም አልነገርኩ ለማመስገን እየፈለግሁት ነው››
‹‹እንዳታመሰግኝ››
‹‹ምን ማለት ነው››
‹‹የእኔ ልጅ ያንችን ቤት ቀለም አልቀባም››
‹‹አየሁት አልኩሽ እኮ››
‹‹ስሚ!!!!››
‹‹ምን››
‹‹ለሰው ነግረሽ ልጄ አንድ ነገር ቢሆን አለቅሽም››
‹‹ምን እያልሽ ነው?››
‹‹ጉሮሮሽን አንቄ ነው ሲጥ የማደርግሽ››
‹‹እንዴ ምን ነካሽ››
‹‹አንቺ ልጄን ለማስገደል ነው የፈለግሽው››
‹‹ለምንድነው የማስገድለው››
‹‹እንዳውም አንቺ ዋና ጠላቴ ነሽ››
‹‹የምትይው አልገባኝም››
‹‹አፍሽን ዝጊ ወይም ያልቅልሻል!!››

የልጁ እናት ብትደነግጥም ሴትየዋን ማስፈራራት ነበረባት:: ከመሄዷ በፊት ወደ አንድ ጥግ ወሰደቻት፤ ወስዳም ጉሮሮዋን አንቃ ያዘቻትና እንደፋደፈቻት::‹‹..ትንሽ ነገር ብሰማ አንገትሽን በስለት ነው የምቆርጠው አሁን ያነቅሁሽ ለሙከራ ብቻ ነው›› አለቻት::ሴትየዋ ደነገጠች አናቲዋ የዛተችውን እንደምታደርግ ታውቃለች:: ያንግዜ ኢህአፓ በየግድግዳው መንግስት ለመቃወም ቀይ ቀለም እየቀባ ያሸበርቃል:: በአጥሮችና ፖል ላይ የጨርቅ ባነሮች ይሰቅላሉ:: በመንገድ ላይ ወረቀት ይበትናሉ:: በዚያ ሰሞን ሌሊት ጨለማን ተገን አድርገው ግድግዳ ላይ ቀለም ሲቀቡ ሴትየዋ የወሬ ሹክሹክታ ሰምተው በቀዳዳ ሲመለከቱ ወጣቶች የሆነ ነገር ያደርጋሉ፤ በቀዳዳ ያዩት አንደኛውን ልጅ ተመለከቱት:: ልጆቹ ከሄዱ በኋላ በጠዋት ሲመለከቱ ግድግዳው ቀለም ተቀብቷል:: ግን ሌላ ሰው ስለመጣባቸው ወይም ተቻኩለው ቀቡ እንጂ ሳይጽፉበት ሄደዋል:: ለችግራቸው የደረሱላቸው ማመስገን ፈለጉ:: አሁን ግን እናትየው ይሄ ወሬ ልጇን እንደሚያስገድል ስላወቀች ማስፈራራት ነበረባት::

## ምእራፍ 18

### ለቅሶ ቤት

የመሞቻው ጥይት በጀርባው ሊሰርግበት የመጨረሻ ደረጃ ላይ የሚገኘው አስፋው እንደምንም በአጥሩ አጠገብ እጥፍ ሲል በጆሮ ግንዱ ስር ጥይቱ እያፏጨ ሲሄድ አይቶታል ወይም ተሰምቶታል። አባራሪዎቹ ደርሰውበት በጥይት ሊያንጥፉት ሲሉ ድንገት ባልታሰበ ቦታ ሲጠመዘዝ ለጥቂት አመለጣቸው።ሩጫው ፈጣን በመሆኑ ለማነጣጠርም ቢቸገሩም እየተቃረቡት በመሆናቸው በአጭር ደቂቃ ውስጥ እንደሚደፉት እርግጠኛ ናቸው። እየደረሱበት ሁለት ግዜ ከኢላማው ውጭ እየሆነ አምልጧቸዋል።አጥሩን ታጥፎ ሲሄድ ምንም መደበቂያ ስለሌለው እንደሚጨርሱት አልጠፋውም።እነርሱ ከመድረሳቸው በፊት በቅርብ ያገኘው አንድግቢ በአጥር ዘሎ ገባ። ሁለተኛውን ግቢ ዘሎ መደበቂያ ፈለገ።ውሻ ሲያባርረው ከግቢው ወጥቶ መሮጥ ጀመረ። አባራሪዎቹ አዩት። ለሶስተኛ ግዜ ተኮሱበት። አንድም ጥይት እንዳላገኘው አውቋል።ወዲያው ታጠፈና ሄደ። አቋራጩ ጋር ደርሰው ሲመለከቱ ተሰወረባቸው ።መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆመው የሚሮጥ ሰው መፈለግ ጀመሩ።ከዚህ አካባቢ እንዳልራቀ አውቀው አሰሳ ጀመሩ።

### እንደገና አሁን

ጥግ ላይ የተቀመጠው ለቀስተኛ በሰሃን የያዘውን እንጀራ እየቀመሰ አማትሮ ወደ ውጭ ያያል የለበሰውን ቀይ ጃኬት አውልቆ ተቀምጦበታል። መሳሪያ የያዙ ሰዎች በሰፊው ግቢ ወደተጣለው ድንኳን እየገቡ ነው።አስፋው አጠገቡ ካለው ሰው ጋርማውራት ጀመረ‹‹መቼ ነው የሞቱት?››አለው

‹‹ከትላንት ወዲያ››

‹‹ምን ሆነው ነው››

‹‹ህመም ነበር....ብዙ ችግር ነበረው››

‹‹እኔን...እኔን››





መሳሪያ የያዙት ሰዎች ዋናው በር ወደ ውስጥ ገባ ብለው እየተመለከቱ ነው።አስፋው አንገቱን ሰበር አድርጎ እየተመለከታቸው ነው።በር ብሎ ወደ ጓሮ አየ።ለማምለጥ የሚያስችል ቀዳዳ በመፈለግ ላይ ነው።መሳሪያ የያዙት ሌሎች ሰዎች በጓሮ እያያቸው ነው። ቦታውን እንደከበቡት ተረድቷል።ዝም ብሎ መሞት እንደሌለበት አሰበ።አጠገቡ ያለውን ሰው እንደገና እያዋራው ነው‹መቼ ነበር ቀብሩ‹››አለ

‹‹ትላንት››

‹‹ለምን አልነገሩኝም››

‹‹እነማን››

‹‹እነርሱ››

‹‹ብዙዎቹ ሰምተዋል››

አስፋው ጎንበስ ብሎ ድምጹን ዝቅ አርጎ ማልቀስ ጀመረ። አጠገቡ ያለው ሰው በቃ አታልቅስ እያለው እያጽናናው ነው።አጉንብሶ የሚያለቅስ መስሎ ሰዎቹን ፊቱን በያዘበት ጣቶች መሀል እየተመለከተ ነው።ገዳዮቹ ግን አልተነቃነቁም ።በአይናቸው እየመነጠሩ ነው።ምናልባት ያሳሳታቸው የለበሰውን ጃኬት ስለሚፈልጉ ይሆናል።አስፋው ሰሀኑን መሬት አስቀመጠ።መሀረብ ሊያወጣ እጁን ወደ ሱሪ ኪስ ሰደደ።ጣቶቹ ውሃ ሆኑ።ቀስ ብሎ እንዳጎነበሰ ሲመለከት እጁ በከፊል ደም ሆኗል።እግሩን እየቀዘቀዘው ሄደ ።ታፋው ላይ በጥይት እንደመቱት አወቀ።የተመታው እግሩ አሁን እያወራው ካለው ሰው አጠገብ በመሆኑ ተጨናነቀ።ወደ እግሩ እንዳያተኩር ማውራት ጀመረ።‹‹..የአባቴ የቅርብ ቤተሰብ ሲሞት ለቀብር ያለመድረሴ....››አለ

‹‹ይቀራረቡ ነበር?››

‹‹በእድሜም እኩያ ናቸው››

‹‹ምን አልከኝ››

‹‹እኩያናቸው››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ነገርኩህ››

‹‹መሰረትን ማለትህ ነው››

‹‹ምን አልክ››
‹‹የሞተችው ሴት ናት መሰረት ትባላለች የአምስት ልጆች እናት ናት››
‹‹እንደዛ ነው እንዴ››
‹‹አዎ››
‹‹ሰዎች የአባቴን ጓደኛ ቤት ስጠይቅ ይሄ ግቢ ነው ብለው ጠቆሙኝ››
‹‹ከየት ነው የመጣኸው››
‹‹ከጅማ››
‹‹ለቅሶ ቤት የተሳሳትክ መሰለኝ››
‹‹ምን አልክ››
‹‹በቃ እሳቸው ቤት ሂድ›
‹‹እንደዚያ ነው፤ከመጣሁ አይቀር የመሰረትንም ነፍስ ይማር››
‹‹አሜን››

ሰዎቹ ከግቢው ብዙም አልራቁም። ትልቅ ስህተት እንደሰራ አውቋል።አሁን አጠገቡ ከተቀመጠው ሰውዬ ቶሎ መራቅ አለበት። ‹‹ሽንት ቤት በዚህ ነው አይደል?›› ብሎ ቀስ ብሎ ወደ ጓሮ ሄደ። እስፋው እዚህ ሁሉ ነገር ውስጥ የገባው በጥንቃቄ ጉድለት ነው። ወደዚህ ሰፈር መመለስ አልነበረበትም።የሚጫወትበት ክለብ ልምምድ የሚሰራው እዚህ ሰፈር በቅርብ ርቀት ከሚገኘው ሜዳ ላይ ነበር። ከእርሱ ጋር አብረው የተመደቡትን የኢህአፓ አባላት የሚያገኘው እዚህ ክለብ ውስጥ በመሆኑ ከእነርሱ ጋር ስለተሰጣቸው ሚሽን ለመወያየት ነው።ነገር ግን ለመምጣት በተዘጋጀበት ግዜ ሀይለኛ የፊሽካ ድምጽ ሰማ ።ፊሽካው ሰዎች እንደመጡበት የሚጠቁም መልእክት ነበር። ቶሎ ብሎ በአጥር ቀዳዳ ሲመለከት እዛው ሰፈር ውስጥ ያወቀው የመኢሶን አባል መደበቂያውን ደርሶበት ኖሮ አብዮት ጠባቂዎችን እየነዳቸው ወደ ግቢው መጣ። ቶሎ ብሎ በኋላኛው አጥር ዘሎ አመለጠ። ግን የውሻ ድምጽ ስለሰሙ ከጓሮ በኩል ባለው መንገድ በፍጥነት ሄዱ።እስፋውን ሲሮጥ አዩት። ጠቋሚው እሱ መሆኑን እየተናገረ እንዳያመልጣችሁ ብሎ ሲናገር ይሰማዋል ።





የመጀመርያው ጥይት ሲተኮስ እየጮኸበት ሊዘነጥለው ይከተለው ግበረው ውሻ የት እንደገባ አላወቀም።ከለቅሶ ቤቱ ወጥቶ ከእጥሩ ጋር በተያያዘው ሽንት ቤት ዘሎ አቆራርጦ ለጓደኞቹ መልእክት ከሰደደ በኋላ ሌላ መደበቂያ ተሰጠው።እስፋው ለቅሶ ቤት መግባቱን ያዩ ሰዎች ለአብዮት ጥበቃዎቹ ተናገሩ። የሚቿ ባል ከትኩሱ ለቅሶ ላይ ተይዞ ተወሰደ። ከሳምንት በኋላ ደግሞ ሰፈር ውስጥ እየጠቆመባቸው ሲያስይዛቸው የነበረው የመኢሶን ወጣት ቤቱ ውስጥ ተገደለ። የሚኖረው ከጓደኛው ጋር ነበር።ጓደኛው ነገሩ ባልታወቀ ምክንያት ቤት አላደረም።ሰዎች እንዲመለከቱ ሬሳውን አውጥተው መንገድ ላይ አጋድመውት ሄዱ።

## ምእራፍ 19

### መኩርያ

በቆርቾ እግሩ የተተለተለው ወጣት እራሱን ለመከላከል የሚችልበት አንዳችም ነገር አልነበረውም፡፡ግርፋቱ በጣም ስለበዛበት ከአቅሙ በላይ ሆኗል፡፡ ከሰላሳ ደቂቃ በላይ እየተፈራረቁ ገርፈውታል፡ ዱላ ቻይ መሆኑ እንጅ እንደድብደባቸው መሞት ነበረበት፡፡ ስፖርተኛ መሆኑ ጠቀመው እንጂ በዱላው ብዛት ይሞት ነበር፡፡ ገራፊዎቹ እንደኢህአፓ አባላት የሚያስለቻቸው የለም፡፡ ተደብዳቢዎቹ ቶሎ ስለማያምኑላቸው ድክም ነው የሚላቸው፡፡ ይሄኛው ተደብዳቢ እነሆ ሶስተኛ ቀኑ ነው፡፡ እስካሁን ትንፍሽ አላለም፡፡ አሁን ግን አቃተው መሰል ሌባ ጣቱን እየቀሰረ ነው፡፡ ሌባ ጣት በተገራፊና በገራፊ መሀል አገናኝ ድልድይ ነች፡ ‹‹ለመናገር ፈቃደኛ ነኝ›› የሚለውን ምልክት የምትጠቁም ነች፡፡ ተባባሪዎቹ እነማን እንደሆኑ፤መሳርያ የት እንደደበቁና ለሌሎችም ጥያቄ ጠይቀውት ‹‹አላውቅም›› ብሎ ከተናገረ ወደ ግርፊያ ይገባል፡፡ ጣቱን ሲያወጣ ሌላ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ሳይሆን በጠየቁት ነገር አምኖ የሚያጋልጥ ወይም የሚጠቁም ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ይሄም ወጣት በግርፋት ከእግሩ የሚወርደውን ደም ተዘቀዝቆ እየተመለከተ ጣቱን ብቅ አደረጋት፡፡ ጩኸት እንዳይኖርና እንዳይረብሽ አፉ ውስጥ የተወተፈለትን በጣም የቆሸሸ ጨርቅ አወጡለት፡፡‹‹አውርዱኝ››አለ

‹‹ለምን››

‹‹ግዴላችሁም አውርዱኝ››

‹‹ንገረና››

‹‹እንዲህ ሆኜ!!!››

‹‹አዎ››

ወጣቱ ዝም አለ፡፡ ስቃዩ ስለበዛበት እረፍት ለማግኘት የፈለገ ይመስላል፡፡ እጁ ከኋላ ታስሯል፡፡ እግሩንም እንደዚሁ፡፡ እንደገናም እጅና እግሩ ከኋላ በገመድ በደንብ ተወጥሮ ተሸብቧል፡፡ እንዲህ





ካደረጉ በኋላ በእጁና በእግሩ መሀል ትልቅ አጠና ነገር ይገባና ከፍ አድርገው የሆነ ነገር ላይ ያንጠለጥሉታል፡፡ጭንቅላቱ ቁልቁል ይዘቀዝቅና እግሩ ወደላይ ይገለባጣል፡፡ ይሄን ግዜ የእግሩ መዳፍ ተገልብጦ ለዱላ ተመቻችቶ ዝግጁ ይሆናል፡፡ ይሄን አይነት የመግረፍ ስልት ስምንት ቁጥር ይሉታል፡፡አሁንም በዚህ ሁኔታ ነበር እየተጠበጠበ ያለው፡፡ ከገራፊዎቹ አንዱ ድምጹን ከፍ አድርጎ‹‹ መሳርያውን የት ነው የደበቃችሁት?››አለ

‹‹መኩርያ ጋር››

‹‹መኩርያ የቱ››

‹‹አንበሳው››

‹‹ይሄ የክብር ዘበኛው?››

‹‹አዎ››

‹‹እኮ ይሄ የሚያስፈራው አንበሳ››

‹‹አዎ››

‹‹ይሄ ማነው!!! ጉብሬ የሚሉት ሰው ነው አሳዳጊው አይደል?››

‹‹ልክ ነህ››

‹‹እዛ ነው መሳያው የተደበቀው››

‹‹አዎ››

‹‹እሃ!! አንበሳውም ኢህአፓ ወገን ነው ማለት ነዋ!!››

አሁን እየተገረፈ ያለው ወጣት መሳርያውን እንዴት እንደደበቀ ቢናገርም ካድሬ ገድሎ ያመለጠው የእሱን ጓደኛ የት እንዳለ ግን መናገር አልቻለም፡፡መሳርያውን ካገኙ በኋላ ጓደኛውን ለማውጣጣት ሌላ ግርፍያ እንደሚያካሂዱ ነግረውታል፡፡ ደግሞም ዝተውበታል፡፡ገዳዩ ከቀበሌው ወደ ከፍተኛው ተላለፈ ፡፡የካድሬዎቹ ሀላፊ የአንበሳውን አሳዳጊ ጉብሬ እንዲመጣ አስደረገ፡፡እስረኛውን አምጥተው አንድ ክፍል አስቀመጡ፡፡ ጉብሬ ክፍል ውስጥ ተጠርቶ ገባ፡፡ ካድሬው ወደ እስረኛው እያመለከተ‹‹ታውቀዋለህ?››አለው

‹‹አላውቀውም››

‹‹እርግጠኛ ነህ?››

‹‹እዎ››

‹‹እይተኸውም አታውቅም››

‹‹በፍጹም››

ሰዎቹ ከገብሬ ጋር ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ እስረኛውን ወደ ውጭ አወጡት፡እስረኛው ወደ ውጭ ይውጣ እንጂ ርቆ አልሄደም፡፡ ክፍል ውስጥ ገብሬ፣ የአብዮት ጥበቃው ሰውና ካድሬው ሲነጋገሩ ያዳምጣል፡ ፡ ካድሬው ገብሬን ‹‹ልጆቹ መሳርያአንተጋ ደብቀዋል››አለው

‹‹የት?››

‹‹እቤትህ››

‹‹እኔ ቤት?››

‹‹እዎ››

‹‹መፈተሽ ትችላላችሁ››

‹‹አሁንማ ልታሸሽ ትችላለህ››

‹‹የወታደር ግቢ እኮ ነው የምኖረው››

‹‹ምን ማለት ነው››

‹‹ጥብቅ ቁጥጥር ስለሚደረግ ለማስገባት አስቸጋሪ ነው››

‹‹እነርሱ የሚሉትን ሰምተሃል?››

‹‹እነማን?››

‹‹የጠቆሙት ልጆች››

‹‹ምን አሉ!!››

‹‹አንበሳው አጠገብ መደበቃቸውን ተናግረዋል ››

‹‹መሳርያውን?››

‹‹እዎ››

‹‹እንዴት ሆኖ››

‹‹እሱ ክፍል ደብቀዋል››

‹‹የማን ክፍል?››

‹‹የአንበሳው ማደርያ ክፍል››

‹‹እንግድያውስ ስለተጨነቁ ነው እንዲህ ያሉት››

‹‹ምን እያልክ ነው››

‹‹አንበሳው የራሱ ክፍል የለውም››

‹‹የት ነው የሚያድረው?››





‹‹ከእኔ ጋር››

‹‹አንድ ክፍል!!?››

‹‹እዎ››

‹‹አትፈራም››

‹‹ለምን››

‹‹አንድ ነገር ቢያደርግህስ?››

‹‹እስካሁን አለሁ››

‹‹ስንት አመት አብራችሁ ኖራችሁ?››

‹‹20 አመት ያህል ሆነን››

‹‹እንዴት አምነህ…››

‹‹ችግር የለም››

‹‹እንቅልፍ ሲወስድህ ቢዘነጥልህስ››

‹‹አላደረገውም አያደርገውም››

‹‹እንዴት አመንከው?››

‹‹እሱ እንደ ልጄ ነው የማየው››

‹‹የሚገርም ነገር ነው››

‹‹ለእኔ የእሱ ጉዳይ ምንም አይገርመኝም››

‹‹ሌላ ሰው እንዳንተ ይቀርበዋል?››

‹‹ማለት››

‹‹እቤት ለማደር የመጣ…..››

‹‹ከእኔና ልጆቼ ጋር አንድ ክፍል ነው የምናድረው››

‹‹ልጆችህም እዛው አንበሳው ጋር ነው የሚያድሩት?››

‹‹እዎ››

‹‹ቤተሰብህንም አይተናኮልም››

‹‹በፍጹም››

‹‹አሁን የምትለውን እንዴት እንመን››

‹‹ምኑን?››

‹‹አንበሳው ለብቻው አንድ ክፍል ያለመኖሩን››

‹‹መጥታችሁ ማረጋገጥ ትችላላሁ››

‹‹በእርግጥም ማየት ይኖርብናል››

‹‹እንደርሱ ጥሩ ነው ፤እንዳውም አሁን እንሂድ››

‹‹የት?››
‹‹እኔ ቤት››
‹‹ይቻላል ግን…››
‹‹ግን ምን?››
‹‹አንበሳው ይታሰራል አይደል››
‹‹አዎ ግን አንዳንዴ ይፈታዋል››
‹‹ማለት››
‹‹የታሰረበትን ይፈታዋል››
‹‹እና ልታስጨርሰን ነው››
‹‹ሰው አይነካም››

ሰዎቹ ነገሩ አሰጋቸው፡፡ የአንበሳውን አሳዳጊ እንዴት ይመኑት? የኢህአፓ ተባባሪ ሆኖ መሳርያውን እዛ ከተደበቀ እንደገቡ አንበሳውን ፈትቶ ቢለቅባቸውስ?፡፡ ደግሞም የክብር ዘበኛ ወታደሮች የዘውድ ጠባቂ ናቸው፡፡ ለንጉሱ ትልቅ አክብሮትና ውዴታ አላቸው፡፡ ይሄ ሰው የንጉሱ ደጋፊ ከሆነ ለአብዮቱ ጥላቻ አለው፡፡ አብዮቱን ከጠላ ደግሞ ከኢህአፓ ወገን ነው ያለው፡፡ እናም ወደ ግቢ ከሄዱ በአንበሳው ላለማስበላቱ ምን ማረጋገጫ አላቸው፡፡ ደግሞም ዋሽቷቸዋል፡፡ እንኳን አንበሳን የመሰለ አደገኛ አውሬ ቀርቶ ውሻ እንኳን ግቢ ውስጥ አንድ ጥግ የራሱ ማደርያ ተሰርቶለት ነው የሚያድረው፡፡ እንዴት አንበሳ አንድ ክፍል ከሰው ጋር ይተኛል? ይሄ የሚታመን አይደለም፡፡

ሰዎቹ ወደ ሶስተኛ ሻለቃ ግቢ ቢሄዱም ስላላመኑት የግቢውን ዘቦች ጠየቁ፡፡ገብሬ የነገራቸውን ደገሙት፡፡አንበሳው የራሱ ክፍል እንደሌለው አስረግጠው ነገሯቸው፡፡ ወደ ውስጥ ገብተው ግን አላረጋገጡም፡፡እስካላዩ ድረስ ማረጋገጥ አቃታቸው፡፡አንበሳው የሚያድርበትን አይተው ማረጋገጥ አለባቸው ፡፡ግን አንበሳው ያለበት ቦታ መግባት ፈሩ ፡፡ፈሩ ብቻ ሳይሆን ነገሩ ቀፈፋቸው፡፡ይሄ ግቢ ብዙ ወታደሮች ከነቤተሰባቸው የሚኖሩበት ነው፡፡እዚህ ግቢ ባለች አንድ ክፍል ቤት ነው ገብሬ የሚኖረው፡፡ከአንበሳው ጋር ብቻውን አይደለም የሚኖረው፡፡ቤተሰቡንም ይጨምራል፡፡





ገብሬ አበበ ከክፍለሀገር እንደመጣ ስራ ሲያፈላልግ ደጃዝማች አበበ ቤት በከብት ጥበቃ ተቀጠረ፡፡ሰውየው በአካባቢው የታወቁ ስለነበሩ የአባቱን መጠርያ ስም በእሳቸው በማድረጉ ገብሬ አበበ ተብሎ ተሰየመ፡፡ቁመቱና ሰውነቱ የተደላደለ በመሆኑ በክብር ዘበኛ ወታደርነት ተቀጠረ፡፡መኖርያውንም እዛው ሶስተኛ ሻለቃ ግቢ አደረገ፡፡ አንድ ቀን ወታደሮቹ ሰልፍ ላይ ሆነው የእለቱን የስራ መመርያ በሚቀበሉበት ሰአት ሀላፊው አንድ ጥያቄ መሰል ነገር አቀረቡ፡፡ እንዲህም አሉ ‹‹….ክብር ዘበኛ አንድ አንበሳአላምዶ ማሳደግ ይፈልጋል ››ብለው ተናገሩ፡፡ ወታደሩ ግራ ተጋባ፡፡ሰውየው በዚህ ብቻ አላቆሙም‹‹ከእናንተ መሀል ይሄን አንበሳ አላምዶ የሚያሳድግ አለ?››አሉ፡፡ የጉድ ቀን መጣ በሚል አይነት በውስጥ ለውስጥ አጉረመረሙ፡፡ እንዴት ነው አንበሳ የሚላመደው አይነት ሁሉም ዝም አለ፡፡አሁንም ደገሙ‹‹….ክብር ዘበኛ ይሄን አንበሳ የግድ ማሳደግ አለበት›› ብለው ፈቃደኛ የሚሆነው ሰው ቢፈልጉ ሁሉም ዝም አለ፡፡ ግን ሰውየው ድጋሚ ንግግር ከማድረጋቸው በፊት አንድ እጅ ብቅ አለ፡ እጁን ከማውጣቱ በማስከተል ‹‹እኔ አሳድጋለሁ››አለ፡፡ ሁሉም ተገረሙ፡፡

ወታደሮቹ በግቢው ውስጥ በተደራራቢ አልጋ ላይ ነው የሚያድሩት፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ብዙ ወታደሮች ናቸው የሚኖሩት ሀላፊው‹‹…ገብሬ እውነተኛ ወታደር ነህ፡፡ ከዚህ በኋላ ቤት ይሰጥህና ከአንበሳው ጋር አንድ ክፍል ቤት ውስጥ አብራችሁ ትኖራላችሁ›› አሉ፡፡ ወታደሮቹ ለገብሬ አዘኑ፡፡ አንበሳ ቀልድ አያውቅም፡፡ አንድ ቀን ይሰለቅጥሃል አሉት፡፡ ሁልግዜም ጠዋት ወታደሮቹ ከመኝታቸው ሲነሱ ቶሎ ብለው ወደ ገብሬ ማደርያ ሄደው እንኳኩተው በህይወት መኖሩን ሳያረጋግጡ ወደ መደበኛ ስራቸው አይሄዱም፡፡ ሁሌም ‹‹…አንበሳው እኮ ገብሬን ገድሎት በላው›› የሚለውን ወሬ ነበር የሚጠብቁት ግን በአስደናቂ ሁኔታ ገርቶ ከኢትዮጵያ አልፎ ከአለም የሚመጡትን ቱሪስቶች በሚያስደንቅ ሁኔታ ከሰው ጋር ተግባብቶ የሚኖር አንበሳ አደገረው፡፡ አንድን ቀን ተተናኩሎ አያውቅም፡ ገብሬ እዛች አንዷት ክፍል ውስጥ ብቻውን አልነበረም፡፡ ወይዘሮ አለሚቱን አግብቶ ስምንት ልጅ ሲወልድ ስምንቱን አንበሳው ባለበት ክፍል

ውስጥ ነው ያደጉት። ሀብታሙ ከገብሬ ልጆች ውስጥ ቀልጣፋውና መኩርያንም በረዳት አሳዳጊነት ያገለገለ ነው‹‹እኛ ሳንወለድ ነው ከአባቴ ጋር እዛ ክፍል ያድር የነበረው። ህጻን ሆነን ድመት መስሎን ነበር። ከዚያም ትንሽ ከፍ ስንል ውሻ ነው ብለን ገመትን። ትልቅ ስንሆን አንበሳ መሆኑን ስናረጋግጥ ተገረምን። እንዴት ይሄን ያህል ግዜ ያለምንም ችግር አብረን ኖርን? አልን ።ከውጭ ለሚያየን ሰው ስጋት አለው። እንዴት እምናችሁ ከአንበሳ ጋር አንድ ክፍል ታድራላችሁ? ይሉናል። እኛ ግን ያለምንም ስጋት እንደቤተሰብ ነው ከመኩርያ ጋር የኖርነው››ይላል።



መኩርያና አሳዳጊው ሀምሳ አለቃ ገብሬ አበበ

ወደ ሶስተኛ ሻለቃ ለማጣራት የሄዱት ካድሬውና የደህንነት ሰዎች አንበሳው ያለበትን ክፍል ገብተው ባያዩም ከሚያምኗቸው ሰዎች ጠይቀው ገብሬ ያላቸው ትክክል እንደሆነ ባያምኑም ተቀብለዋል። እስረኞቹ ዋሽተዋል ማለት ነው።እነዚህ የኢህአፓ ወጣቶች ሁሉ ነገራቸው ድብቅ ነው።አንደኛ ደረጃ ገራፊዎች ልክ





እንዲያስገቧቸው ተነጋገሩ።አሁን የዋሸውና ተፈላጊውን ወጣት ቀድመው መግረፍ አለባቸው።

## እንደገና በሌላ ቀን

የእስር ቤቱ ሀላፊዎች ምሽት ላይ እስረኞች ቆጥረው ነው የሚያስገቡት። ተወስዶ የተገደለ ካለ ከየትኛው ክፍል እንደሆነ ይመዘግቡና ቁጥጥርና ክትትል ይደረግባቸዋል። በተለይ ተፈላጊ እስረኛ ላይ በአይነ ቁራኛ ቁጥጥር ይደረጋል። ጠዋትና ከሰአት የትና ከነማን ጋር እንደሚውልም ክትትል ይደረግበታል።አንዳንድ ግዜ ከክፍል በሁለት ምክንያት የማይወጡ እስረኞች አሉ።አንዱ በግርፍያ ብዛት መንቀሳቀስ የማይችሉ፣ሁለተኛው ከሰው ላለመገናኘት ወስነው የሚቀሩ አሉ።እነዚህ እስረኞች ከቤት ውጭ የማይታዩ ክፍል ውስጥ እንዳሉ ይቆጠራሉ።

ዛሬ ግን አንድ ወሳኝ እስረኛ ጠፍቶባቸዋል። ጠዋት ቆጠራ ሲደረግ ዋናው እስረኛ የለም። በየክፍሉ ሲፈለግ በፍጹም ሊገኝ አልቻለም። ምናልባት ድንገት በሌሊት የደህንነት ሰዎች ወስደው ገድለውት ሊሆን ይችላል ተብሎ ስለተገመተ ትናንትና እስር ቤት የነበሩ የጥበቃ ሀላፊዎች ተጠይቀው ምንም ምላሽ አልተገኘም። ነገሩ ግራ የሚያጋባ ሆነ። ምናልባት አሳቻ ቦታ ተደብቆ ይሆናል በሚል ግቢው በሁሉም ቦታ ታሰሰ። አሁንም አልተገኘም። ምናልባትም ደግሞ ሌላ ትልቅ እስር ቤት ለምርመራ ሄዶ ሊሆን ይችላል በሚል ወደ ከፍተኛቸው ደወሉ። እዛም አልተገኘም። ነገሩ አሁን ገባቸው። እስረኛው አምልጧል ማለት ነው።

ከዚህ በፊት ሶስት ግዜ እስረኛ አምልጦ ከፍተኛ ግምገማ ተደርጎ ጥበቃዎች ውስጥ የኢህአፓ አባላት ተሰግስገው በመገኘታቸው እርምጃ ተወስዶ ከፍተኛ መሻሻል ተደርጓል። አሁን ታድያ እንዴት ይሄ ስህተት ተፈጠረ?። ጉዳዩ ሁሉንም አነጋገረ። በዚያ ላይ ይሄ እስረኛ በግርፍያ ብዛት ብዙ የተጎዳ በመሆኑ እንደልቡ መንቀሳቀስ የማይችል ስለሆነ እገዛ ካልተደረገለት በስተቀር ማምለጥ አይችልም ብለው ወሰኑ። ይሄ እስር ቤት ትልቅ ቁጥጥር የሚደረግበትና ተፈላጊ

እስረኞች የሚገኙበት ነው፡፡ አሁን ያመለጠው እስረኛ ገና ያላወጣው መረጃ የያዘ በመሆኑ አስፈላጊያቸው ነው፡፡ ደግሞም ውጭ ከወጣ መረጃ ለሌሎች ስለሚሰጥ ብዙዎቹ ተፈላጊዎች እንዲሸሹ ያደርጋል፡፡ እናም በብዙ መልኩ ጉዳት አለው፡፡ ርቆ ሳይሄድና አድራሻውን ሳያጠፋ መፈለግ አላባቸው፡፡

የሚያመልጥ እስረኛ ምንግዜም ሽፋን የሚያገኝ ነው፡፡ሽፋኑን የሚሰጡት አብረው በአንድ ጉዳይ የታሰሩ እስረኞች ናቸው፡፡ሌላው ቢቀር የሚመልጥም ከሆነ የት መደበቅ እንዳለበት የሚነግረው ለሚያምናቸው ጓደኞቹ ነው፡፡ ከእሱ ጋር በአንድ ጉዳይ የታሰሩ ሁለቱ ጓደኞቹን ሀላፊው ቢሮ ጠራቸው፡፡ በቁጣና በስሜት ተሞልቶ እያነጋገራቸው ነው ‹‹የት እንደሄደ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ?››አለ

‹‹አናውቅም››

‹‹ጓደኛችሁ አይደል››

‹‹አዎ››

‹‹እቅዱን ይነግራችኋል እኮ››

‹‹ማለት?››

‹‹ለመጥፋት ሲያስብ ሀሳቡን ይነግራችኋል››

‹‹በእርግጥ አውርተናል››

‹‹ስለመጥፋቱ!!!!››

‹‹አይደለም››

‹‹እና››

‹‹ህመም እየገጠመው መሆኑን ነው የነገረን››

‹‹ታድያ እንዲሁ ከመሬት ተነስቶ አመለጠ?››

‹‹እኛም ግራ ገብቶናል››

‹‹እንዳውም እውነቱን እንንገራችሁ››

‹‹ምንድነው?››

‹‹እቅዱን ያወጣችሁት እናንተ ናችሁ››

‹‹እረ እኛ እንዳውም ልንጠይቅ ነበር››

‹‹ምንድነው የምትጠይቁት?››

‹‹የት እንደሄደ የሚነግረን እንፈልግ ነበር››

‹‹እያሾፋችሁ ነው››





‹‹ማሾፍ አይደለም››

‹‹ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል የተባለውን ታውቃላችሁ?››

‹‹ሲባል ሰምተናል››

‹‹እንደዛ አይነት ነገር ነው ያነሳችሁት››

‹‹እንደዛ ለማለት አይደለም››

‹‹እውነቱን አትነግሩንም?››

‹‹እኛ ምንም አናውቅም››

‹‹ስትገረፉ እውነቱን ትነግሩናላችሁ››

ብዙ ጥያቄ ተንከባለለ ግን ምንም ፍንጭ አጡ፡፡ ጭራሽ ልጆቹ ጓደኞችን ያለበትን እናንተ ንገሩን እያሉ መጠየቃቸውን በመደጋገማቸው እያሾፉባቸው መሆኑን ተገንዝበው ልክ ማግባት እንዳለባቸው ተረዱ፡፡እነዚህ ሁለት እስረኞች መገረፍ ያለባቸው በአንደኛ ደረጃ መሆኑን ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ሁለት መግረፊያ ቤቶች በግቢው ይገኛሉ፡፡ ቁጥር ሁለት የተባለው ሁሉም የሚገረፍበት ‹‹ለብለብ ቤት›› ይሉታል፡፡ ቁጥር 1 የሚባለው ግን ተፈላጊና ትልቅ መረጃ አላቸው የሚባሉ እስረኞች የሚገረፉበት ብቻ ሳይሆን እንደ በሬ ስጋ የሚተለተሉበት ነው፡፡እዚህ ክፍል ውስጥ ከጥፍር መንቀያ አንስቶ ስጋ መበላለቻ ስለት ነገሮች እንዲሁም ለዘይት ማፍያ የሚሆኑ ከሰል ማንደጃ ሳይቀር የሚገኝበት ነው ፡፡ገራፊዎቹ ሁለት ሲሆኑ እየተፈራረቁ ነው ስራቸውን የሚያከናውኑት፡፡ ዋናው ገራፊ የትራኮማ አይን መነጽር የሚያደርግና በጣም ጩኸኝ ዱላው ስስ ብልትን ቀርድዶ የሚገባና በማውጣጣቱም የሚታወቅ ነው፡፡

ሰውየው ፊቱ የማይፈታና በራሱ የስነልቦና ችግር ያለበትና በውስጡ ትልቅ ምቀኝነት የተፈጠረበት ነው፡፡ተረኛ ገራፊው እሱ መሆኑ ከታወቀ ለቶርች የሚገባው ሰው በደም ተጨማልቆና ሰውነቱ ተተልትሎ እንደሚመጣ ሁሉም ያውቃሉ፡፡እስረኛው ወደ ግፍርያ ክፍል ሲገባ ለረጅም ሰአት ቢለዋ ሲስል ከሰል ሲያቀጣጥል ስለሚታይ እስረኛው ሳይገረፍ ሱሬው ሲረጥብ ይታያል፡፡አሁንም ለእነዚህ ሁለት እስረኞች ቁጥር 1 ክፍል ገብተው ምርመራ እንደሚደረግባቸው ሲነገራቸው ፍርሀት ወረራቸው፡፡ እስረኞቹ ለብቻቸው አንድ ክፍል

እንዲሆኑ ተደረገ።ዋናው ገራፊ ከመምጣቱ በፊት ክፍሉን ማስተካከል አለባቸው።በዚህ ሁለት ቀን ምንም ለግርፍያ የገባ እስረኛ አልነበረም። ዋናው ገራፊ ሲመጣ ተገራፊውን ውስጥ አስገብተው ለግርፍረያ ለማዘጋጀት አንጠልጥለው ነው የሚጠብቁት።

ቀዳሚ የሚሆነው ተገራፊ ከመሄዱ በፊት እውነቱን እንዲነግራቸው ጠየቁት ምንም ምላሽ የለም። እየተነዳ ወደ ቁጥር አንድ ክፍል ተወሰደ። ክፍሉ ተከፈተ። አስገራፊና ተገራፊ ወደ ውስጥ ገቡ። ክፍሉ ይሸታል። በርግጥም መሽተት ነበረበት። እስረኛ በደም የሚጨማለቅበት በመሆኑ ጠረኑ ጥሩ አይደለም። አንዳንዴ ጠረኑን ለመቀየር ያጨሱብታል። ያሁኑ ጠረን ግን የተለየ ነው። የክፍሉ መብራት ቦግ ሲል አንድ እስረኛ ለግርፍያ በተዘጋጀ መልኩ ተንጠልጥሏል። አሁን የገባው እስረኛ የተንጠለጠለውን ሰው ሳይመለከተው በልብሱ ነው ያወቀው። ጓደኛቸው አላመለጠም። አልተሰወረም። ከአንድ ቀን በፊት ለግርፍያ እንደገባ ገራፊው ረስቶት ወደ ቤቱ ሄደ። ግን ሰውየው ከቤቱ አልተመለሰም ነበር።።

እንዳንድ ግዜ ገራፊዎች ጠዋት ቀጥቅጠው ከሰአት በኋላ ዱላውን ስለሚቀጥሉ ለምሳ እዛው እንዳንጠለጠሉ ይሄዳሉ። ከዚህ በፊት አንዱ ተረስቶ ምሽት ላይ በመታወቁ ከሞት ተርፏል። ይሄኛው ግን መጀመርያም በዱላና በስለት ከመቀደድ ብዛት ነፍሱ ተንጠልጥላ ስለነበር ከአንድ ቀን በላይ በመቆየቱ በዛው አሸልቧል። የገባው እስረኛ ከመገረፍ በመትረፉ ቢደሰትም ጓደኛው በዚህ ሁኔታ በመሞቱ በጣም አዘነ። ከሶስት ቀን በፊት ጸሀይ ሲሞቁ እንዲጠነክሩና ሚስጥር ማውጣት እንደሌለባቸው ሲነግራቸው ነበር። በዋነኛነት ግን በተለያየ ግዜ ለግርፍያ በተወሰደ ግዜ ከገራፊዎቹ ጋር ያደረገውን የቃላት ምልልስ በደምብ ነግሯቸው ነበር። ለሶስተኛ ግዜ ተጠርቶ በተገረፈ ግዜ ሁለቱ ጓደኞቹ እሱ ክፍል ገብተው ህክምና እያደረጉለት ‹‹ምን አሉህ?››አሉት

‹‹ነገርኳቸው››

‹‹ምን››

‹‹የተሳሳተ ነገር››





‹‹ፍንጭ አልሰጠሁም››

‹‹እዎ ግን....››

‹‹ግን ምን?››

‹‹ቃላችን አንድ ይሁን››

‹‹ችግር የለም››

ከገራፊዎቹ ጋር የተለዋወጣቸውን ቃላት ሁሉ ነገራቸው። ለአራተኛ ግዜ በተወሰደ ግዜ ጠንክር እንዲል ነግረውታል። ነገር ግን እንደሄደ አልተመለሰም። ከዚህ በፊት ለመጀመርያ ግዜ ሲገረፍ ለብቻው አንድ ክፍል ካስቀመጡት በኋላ ሌላ እስር ቤት ተወስዶ ሁለት ቀን ካቆዩት በኋላ በሌሎች ላይ ማስረጃ እንዲሰጥ ተወስዶ ነበር የተመለሰው። ፡ሌላው ጓደኛቸው ከግርፋት በኋላ ወደ ክፍሉ ሳይመለስ በዚያው ተወስዶ መገደሉን ሰምተዋል። አሁንም ይሄ ጓደኛቸው በተመሳሳይ ሌላ እስር ቤት እንደተወሰደ ነበር የተረዱት ።ግን ተረስቶ በዛው አሸለበ። ባለመነጽሩ ገራፊ ሲመጣ ነገሩ ተነገረው። ምንም አልተሰማውም ትንኝ የሞተ ያህል ነበር ስሜቱ። ከጓደኞቹ በቀር ማንም አላዘነም። መሳርያውን መኩርያ ጋር ነው የደበቅሁት ብሎ ለስተኛ ሻለቃ ሄደው ካረጋገጡ በኋላ እንደዋሻቸው በማወቃቸው ነበር ለአንደኛ ገራፊው አሳልፈው የሰጡት። ገራፊው ግን ረስቶት ይሂድ፣ ገድሎት ይሂድ አልታወቀም ግን ሞቶ ተገኝ።

## ምእራፍ 20

### ሆያ ሆዬ

ምሽት አንድ ሰዓት ሆኗል። ሲነጋ መስከረም ይጠባል።ለዘመን መለወጫ ዋዜማ ሁሉም በየቤቱ አዲሱን አመት ‹‹እንኳን ደህና መጣህ›› ለማለት ሽር ጉድ እያለ ነው።ታዳጊ ወጣቶች ቡሄን እየጨፈሩ ነው።ቀበሌ 9 አራዳ የደረሱት ወጣቶች ግቢው ደጃፍ ላይ ሞቅ አድርገው እየጨፈሩ ነው።‹‹ሆያ ሆዬ››

‹‹ሆ!!››

‹‹ሆይሽዬ››

‹‹ሆ !!››

‹‹የኔ አብዬ››

‹‹ሆ !!!››

የባለቤቱን ስም እየጠሩ አሞጋገሱ ።የበሩን ቆርቆሮ እየመቱ ወጥተው የደንቡን እንዲያደርሱዋቸው መወትወት ጀመሩ ። በተለምዶ አንድ ቤት እየጨፈሩ ካልተከፈተ ትተው ወደ ሌላ ቦታ ይሄዳሉ ። እነዚህ ግን ከዚህ በር ላይ ንቅንቅ አላሉም።ሙጭጭ ! ድርቅ ግግም ብለው ይጨፍራሉ።ይሄን በር ማስከፈት ከቻሉ ብዙ ፍራንክ ያገኛሉ።ስለዚህ የዋዛ ሊለቁ አልፈለጉም።አሁንም መጨፈር ጀመሩ። ነገር ግን የግቢውን በር ከፍቶ የሚሰጣቸው ሰው አላገኙም።እንደገና ስልታቸውን ቀይረው መጨፈር ተያያዙ

‹‹ክፈት በለው በሩን››

‹‹የጌታዬን››

‹‹ሆያ ሆዬ››

‹‹ሆ››

‹‹ሆያ ሆዬ››

‹‹ሆ››

‹‹ያች ድንክ አልጋ››

‹‹ሆ››





‹‹አመለኛ››

‹‹ሆ››

‹‹ያለ አንድ ሰው››

‹‹ሆ ››

‹‹አታስተኛ ››

‹‹ሆ››

‹‹የዚህ ቤት ጌታ››

‹‹ሆ››

የዚህ ግጥም ስንኝ ሳያልቅ በሩ ተከፍቶ ባለቤቱ ለመናገር ሲዘጋጁ ከጨፋሪዎቹ ጀርባ ተሸሽገው የነበሩት አብዮት ጥበቃዎች ዘለው ገቡ።እራቱን በልቶ ወደ መደበቂያ ስፍራው ሊያቀና ያለውን ተፈላጊ አድብተው ያዙት። በፍጹም በዚህ ሁኔታ ይደርሱብኛል ብሎ አላሰበም። አባይነህ ከይርጋለም ነበር የመጣው። የባንክ ዘረፋ ኦፕሬሽን ላይ ከተሳተፈ በኋላ ሲፈለግ አልተገኘም። መኪና ተራና መውጫ መግቢያ ላይ ፈለጉት። እዚያም የለም። አብዛኞዎቹ የመጡት ከይርጋለም በመሆኑ በመልክ የሚያውቁት ተመርጠው እዚያ ድረስ ሄደው ፈልገውታል። አረሳስቶ ከዚህ ከተማ ለመውጣት እዚሁ ተደበቀ። ነገር ግን አንድ ጥቆማ ደረሳቸው።

ዘመዱ ቤት እንደተደበቀ አወቁ። መረጃውን ያገኙት ከቤቱ ጀርባ ካለው ጎረቤታቸው ነበር።ሁለቱ ሰዎች ጥለኛ ነበሩ።በአጥር ቀዳዳ ካልሆነ በቀር ልጅ አይወጣም አይገባም።ድምጹንም ዝቅ አድርጎ ነው የሚያወራው።አንድ ጥፋት ሰርቶ እንደሆን አወቁ።ጉዳዩን ለቀበሌ አሳወቁ። አብዮት ጠባቂው በአጥር ቀዳዳ አሾልኮ አየው።ማንነቱን ወዲያው አወቀው። የሚፈልጉት ሰው እዚህ ግቢ እንዳለ አረጋገጡ። የባንክ ኦፕሬሽን ሲካሄድ አንድ ሰው ገድሏል።ከባንክ ገንዘብ ይዞ እንደሄደ መረጃ ደርሷቸዋል።ገንዘቡም እዚህ ቤት እንደሚገኝ ገምተዋል።እዚህ መደበቁን መረጃ ያገኙት ከሰዓት ነው።ነገር ግን አንኳኩቶ መግባቱ ልጁ ሊያመልጥ እድል ሊሰጠው እንደሚችል አምነዋል። ቤቱን ከበው ለመያዝ ያቀዱትም አስተማማኝ አልሆነላቸውም።ምክኒያቱ ደግሞ ከጀርባው ያሉት ቤቶች በአጥር

የሚገናኙና መሹለኪያ የሚበዛባቸው በመሆኑ ሊያመልጥ ይችላል ብለው በመስጋታቸው ነበር፡፡

አንድ ዘዴ መጣላቸው ፡፡አካባቢውን በሰላይ በማስጠበቅ እስኪመሽ ጠበቁ፡፡ ሆያ ሆዬ የሚጨፍሩ ወጣቶችን ተከራዩ፡፡ ምሽት አንድ ሰዓት በሩ ላይ እንዲጨፍሩ አደረጉ፡፡በሩ የሚከፈተው ለጨፋሪዎቹ ሳንቲም ለመስጠት በመሆኑ ማንም ሰው ሳይዘጋጅ ዘለው ለመግባት እንዲመቻቸው ነበር፡፡እለቱ ቅዳሜ ጳጉሜ 5 ሲሆን ኦፕሬሽኑ በተካሄደ በሳምንቱ ተፈላጊውን ሰው አንቀው ያዙት፡፡

በጠመንጃ ከበው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱት፡፡ከነገነት ገብረስላሴ ቤት ጆርባ ከነብርሀኑ ቤኛ ቤትፊት ለፊት ባለው መንገድ እየሄዱ ነው፡፡ቦታው ወደ ወንዝ የሚወስደውን መንገድ የያዘች ናት፡፡እዚያ ስፍራ ትልቅ የውሃ መውረጃ ቦይ ይገኛል ፡፡ክረምት ሲሆን ቦዩ ጥልቀቱ ይጨምራል፡፡እስረኛው ከፊት ሆኖ እየተነዳ ነው፡፡ድንገት እንቅፋት እንደመታው ሆኖ ወደቀ፡፡መሬቱን ሳይነካ ተንደርድሮ ወደ ጭለማው ሮጦ ገባ፡፡ጠመንጃቸውን አቀባበሉ፡፡ወደ እርሱ ደገኑ፡፡ ባፈጠጠው ጭለማ ላይ ጆርባውንና እናቱን ለመፈረካከስ የተኩስ እሩምታ ለቀቁ፡፡ ይሄ ሁሉ ተኩስ በጣጥሶ ስለሚጥለው የመትረፍ እድል የለወም፡፡አማራጭ ስላጡ እንጂ በህይወት ነበር የሚፈልጉት ፡፡ ምናልባት ከዚህ ሁሉ ጥይት ከተረፈ እሳከመው ያናዝዙታል፡፡ የሚፈለገውን መረጃ ከሰጠ በኋላ ባይሞትም ይገሉታል፡፡

በቅርብ ካለው ቤት ባትሪ ፈልገው በጥይት የበሳሱትን ሬሳ ለማየት ድቅድቅ ወዳለው ጭለማ በየቦታው አበሩ፡፡ግን የባትሪው ብርሀን ሟቹን አላሳያቸውም፡፡ እነርሱ ሲተኩሱ በነበረው ቦታ ላይ የውሃ መውረጃ ቦይ እንዳለ አዩ፡፡ሲተኩሱ የነበረው ባዶ አየር ላይ እንደሆነ ተረዱ፡፡እዛ አካባቢ ፍለጋቸውን ጀመሩ፡፡እንዴት እንዳመለጣቸው ሲያስታውሱ ተናደዱ፡፡ ያበሳጫቸው ደግሞ መታለላቸው ብቻ ሳይሆን ኦፕሬሽኑ ላይ ጓደኛቸው የሆነውን አብዮት ጥበቃ ጭምር መግደሉ ነበር፡፡በፍለጋው ስላልተሳካላቸው ሌሊቱን እዚያ አካባቢና በየአልቤርጎው ሲያስሱ አነጉ፡፡ ነገር ግን ሊገኝ አልቻለም፡፡ ከቡሄ ጆርባ ገብተው በብልጠት ስለያዙት እንጂ ዘዴኛ መሆኑ አልጠፋቸውም፡፡ወደ ቤት ተመልሰው ዘመዱን ሄደው እሰሩ፡፡





ይርጋለም ቤተሰቦቹ የት ቀበሌ እንደሚገኙ አጣሩ፡፡ ከዘመዱ ቤት ለማስታወሻ የሰጣቸውን ፎቶግራፍ ተቀበሉ፡፡ሁለት ሰው ለስለላ ወደ ይርጋለም ላኩ፡፡ ሳምንት ያህል እዚያ አካባቢ እንዲቆዩ ተደረገ፡፡ በስስተኛው ቀን ውጤታማ ነገር ታየ፡፡

ሻሸመኔ ለሚገኘው የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበርና ለህዝብ ደህንነት ሰዎች የደረሰው መረጃ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡ፎቶውን ይዘው ሲፈልጉት የነበሩት የመረጃው ሰዎች ድንገት ከሰርግ ቤት ሲወጣ የነበረውን ሰው አዩት፡፡ ፎቶውን ተመለከቱ፡፡ምንም ጥርጥር የለውም እራሱ ነው፡፡ወደየት እንደሚሄድ ተከተሉት፡፡ቡና ቤት ገባ

-ሻይ አዘዘ
-ከጓደኛው ጋር አወራ
-ወጥቶ ሄደ
-ከአንዲት ሴት ጋር ሰላምታ ተለዋውጦ ትንሽ ተጫወቱ
-ቤተክርስቲያን ሄዶ ተሳለመ
-ግድግዳ ላይ የተለጠፈ ማስታወቂያ አነበበ
-ከኪሱ ወረቀት አውጥቶ ማስታወሻ ጻፈ
-መንገድ ላይ ሲደባደቡ የነበሩ ህጻናቶችን ገላገለ
-መንገድ ዳር ሽንቱን ሸና

የሚከተሉት ሰዎች እያንዳንዱ እንቅስቃሴውን እየተከታተሉ በጭንቅላታቸው እስፈሩ፡፡አሁን የሚፈልጉት ማረፊያውን ነው፡፡ እየተከታተሉት ቆዩ፡፡ ከምሽቱ 12 ሰዓት ሲሆን ወደ አንድ ቦታ ደረሰ፡ ፡አንድ ቤት እንዲገባላቸው ተመኙ፡፡ልክ እንዳሰቡት ግቢውን ሲያንኳኳ ተደሰቱ፡፡ሰውየው እሱ ራሱ ነው፡፡ፎቶው ብቻ ሳይሆን የተሰጣቸው የቤት ቁጥር የእነአባይነህ መኖሪያ ቤት ነው፡፡አይደረስብኝም ብሎ በአደባባይ አገኙት፡፡እዚህ እንደሚኖር መረጃ ያገኙ ብሎ ስለማይገምት ሳይታሰብ ደረሱበት፡፡ ወዲያውኑ ወደ ሻሸመኔ ደወሉ፡፡ ሌሊቱን ፖሊስና አብዮት ጥበቃ ሲገስግስ መጣ፡፡

አመቺ ቦታ ያዙ፡፡ አባይነህ አደገኛ በመሆኑ ቤት ውስጥ ሊይዙት እንደማይችሉ አውቀዋል፡፡በቡሄ ሰበብ መያዛቸው ለእነርሱ ድል ቢሆንም ዛሬ ሌላ ዘዴ መፈለግ አላባቸው፡፡ከቤቱ ሲወጣ እሳቻ

ቦታ ከበው ለመያዝ ተዘጋጁ፤ከበባውም ጥንቃቄ ይሻል፡፡‹‹ይሄ ሰላቢ መሹለኪያው ስለማይታወቅ ሁሉንም ቦታ በዘዴ ክበቡ ››ተባለ፡፡ ግቢው ሁለት በር ያለው መሆኑን የተረዱት ዘግይተው ነበር፡፡በጓሮ በር ወጥቶ በርቀት ሲሄድ የተመለከቱት ሰላዮቹ ‹‹ያውና…ያውና›› በሚል አሳዩዋቸው፡፡ታጣቂዎቹ ጥግ ጥጉን ይዘው በፈጣን እርምጃ ወደ ታየበት አቅጣጫ አመሩ፡፡ ማንነቱን የሚያውቁት አብዮት ጥበቃዎች ቶሎ ለዩት፡፡ ባለ ሽምቀቅ ቦርሳ ይዟል፡፡ የመጀመሪያውን አቋራጭ ተሻገረ፡፡ እንደተመለከታቸው ጠርጥረዋል፡፡ ሊያመልጣቸው እንደተዘጋጀ አወቁ፡፡

አሁን እሱን ማሳደዱ እንደማያዋጣ ስለተረዱ በመሳሪያ እግሩን ብለው ሊጥሉት ወሰኑ፡፡ አነጣጥረው በመተኮስ የተሻለ ችሎታ አላቸው ተብለው የተገመቱ ከፊት እንዲሆኑ ተደረገ፡፡በቦርሳው መሳሪያ እንደያዘ አውቀዋል፡፡ የመጀመሪያ ቀን ሲያባርሩት ቦምብ ወርውሮ ሰው ጎድቶ ማምለጡን ያውቃሉ፡፡ እዚህ ቦርሳው ውስጥ ከሽጉጥ ሌላ ቦምብ ሊይዝ ስለሚችል ሳይጠጉ ሊወረወርና ሊያመልጥ ይችላል ብለው ስላሰቡ በዘዴ ሊይዙት ተነጋገሩ፡፡ ወደ ቀኝ ባለው መንገድ እንደተጠመዘዘ እንዳይሰወርባቸው በሽምጥ ሩጫ ወደ መታጠፊያው ደረሱ፡፡

መንገዱን እንደዞረ አስር ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ ሱቅ ሲጋራ እየገዛ ነበር፡፡የወሰደውን ኪሱ እየጨመረ ሳለ ቶሎ ደርሰው ሰፈሩበት፡ ፡መሳሪያውን አውጥቶ ቦምብ እንዳይወረውርባቸው ቦርሳውን ከትከሻው ላይ ቶሎ ነጠቁት፡፡ በተኛበት ማጅራቱን በሰደፍ መትተው አደነዘዙት፡ ከኋላ ስትከታተላቸው የነበረችው ላንድሮቨር ውስጥ ወረወሩት፡፡በካቴና አሰሩት ‹‹አገኘንህ!!!››አሉት

‹‹ምን !!››

‹‹የማትገኝ መስሎህ ነው››

‹‹ከኔ ምንም አታገኙም››

‹‹እሱን እናያለን››

‹‹ነገርኳችሁ ልቀቁኝ››

‹‹ገና እንዘለዝልሃለን››





እየዛቱበት እንደገናም በሰደፍ ወደ ታች እየወቀሩት ወደ ሻሸመኔ ይዘውት መጡ፡፡ቦርሳ ወስጥ ያለውም መሳሪያ ለማየት አወጡ፡፡ባዩት ነገር ተገረሙ፡፡

- ካልሲ
- አሮጌ ማሊያ
- ቁምጣ
- የኳስ ጫማ

ሌላ ነገር የለም፡፡ ሰላማዊ ነኝ ለማለት አስቦ እንደሆነ ተነጋገሩ፡፡ አባይነህ ኳስ ተጫዋች መሆን የመረጠው ለሽፋን እንደሆነ ተረድተዋል፡፡ መኪናውን እያከነፉ ዋናውን ተፈላጊ ይዘው ሄዱ፡፡ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አልወሰዱትም፡፡ ወታደሮች ካምፕ አመቺ ቦታ ስላለ እዚያ አስገቡት፡፡ በጣም ተፈላጊ ሁለት እስረኞች አንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ሁለቱም በግርፊያ ብዛት መንቀሳቀስ ቀርቶ መናገር አይችሉም፡፡ አንደኛውን ልጅ ያውቀዋል፡፡ ይርጋለም የአቦስቶ ልጅ ነው፡፡ ሌላኛው የሀዋሳ ሀይቅ ቡድን ተጫዋች ነው፡፡ 11 ሰዓት ላይ በግርፍ የታወቀውን ሰው ይዘው መጡ እስረኛውን ቁልቁል እየተመለከተ ‹‹ካንተ ጋር እነማን ነበሩ?››አለው

‹‹ማንም››

‹‹ገንዘቡ የት ነው ያለው?››

‹‹የምን ገንዘብ?››

‹‹እየቀለድክ ነው?››

‹‹ምንም አልገባኝም››

ገራፊው በንግግር የሚያምን የኢህአፓ አባል እንደሌለ ስለሚያውቅ በሰለጠነው የግርፋት ትምህርት መቀጥቀጥ ጀመረ፡፡ በጠረጴዛዎቹ መሀል አግድም የተቀመጠው ትልቅ አጠና ላይ እግርና እጁን አጠላልፎ አንጠለጠለው፡፡ ካልሲ በአፉ አስገባበት፡፡የውስጥ እግሩን በተዘጋጀው መግረፊያ ይቀጠቅጠው ጀመር፡፡እስረኛው እየተናጠ ተንገበገበ፡፡ግርፋቱ ቆመና ከአፉ ካልሲ ወጥቶ‹‹የምትናገረው ነገር አለ?››አለው

‹‹ምንድነው የምናገረው››

‹‹የጠየቅንህን››

‹‹ኢህአፓ ከእኔ ምንም አያገኝም››
‹‹ምን አልክ?››
(ያሁኑን ቃል ደገመው)
‹‹ማን ነው ኢህአፓ?
‹‹እናንተ ናችሁ››
‹‹የተገላቢጦሽ ሆነ?››
‹‹ምን አልክ?››
‹‹ገንዘቡ የት ነው ያለው?››
‹‹የቱ ?››
‹‹ከባንክ የወሰድከው!!››
‹‹የምን ባንክ?››
‹‹ጊዜ ባትገል ጥሩ ነው››

መርማሪው በጣም ተናደደ። ዛሬ ሳይበስል ነው የሚጠይቀው። በግርፋት ቋንቋ ‹‹ማብሰል›› ማለት ልቡ እስኪጠፋ ገርፎ ደም እስኪወጣ አቁስለው፤ ለሃጩ አፉ ውስጥ ከተከተተው ካልሲ አልፎ በጉንጩ ሲሄድ ልክ መግባቱን ተረድተው ለጥያቄ ከተሰቀለበት ያወርዱታል።

ይሄ እስረኛ እዚህ ደረጃ ባለመድረሱ መርማሪ ሊያበስለው ተዘጋጀ። ‹‹ማለት የምትፈልገው ነገር ሲኖር ሌባ ጣትህን ቀስርና አመልክተኝ›› ብሎ መመሪያ ሰጠውና ለማብሰል አንጠለጠለው። ደሙ እስኪወርድ ድረስ ተለተለው። ነገር ግን አውርደው ቢጠይቁት ምንም ነገር ሊያገኙ አልቻሉም። ሶስት ቀን በተከታታይ ደበደቡት። ሰውነቱ ቁስል በቁስል ሆነ።
ጥርሱን በፒንሳ አወለቁ
ውሀ የተሞላ ኮዳ ብልቱ ላይ አንጠለጠሉ
በፈላ ዘይት ጠበሱት
ፊቱን በምላጭ ቆራረጡት

ይሄ ሁሉ ነገር ተራ በተራ ቢደረግም ከእስረኛው የረባ ነገር አላገኙም፡አብዮት ጥበቃ መግደሉንም ካደ። በምሽት ይዘውት ያመለጠ ቀን እንዴት እንደጠፋባቸው ሲጠይቁት ይሄንን ነገር እንደማያውቅ





ነገራቸው።ጭንቅላቱ እንደተነካ ወይም ማንኛውም ነገር ሊያምን እንደማይችል ተረዱ።

እንዴት አድርገው ማውጣጣት እንዳለባቸው መምከር ጀመሩ።ቀን በሄደ ቁጥር እስረኛው እየተዳከመ ሄደ።በጣም የገረማቸው ነገር እሱ ኢህአፓ እንዳልሆነና ይልቁንስ እየመረመሩ ያሉት ሰዎች ለኢህአፓ እንደሚሰሩ እየነገራቸው ነው።ደግሞም ንጹህ አብዮተኛ እንደሆነ አስረዳቸው። እንዴት እያታለላቸው እንደሆነ ሲረዱ ዘዴው አስገረማቸው። አብዮት ጥበቃዎቹና ወታደሮቹ ወደ ታሰረበት ቦታ ሲያመሩ ሁሌም የሚጠብቁት አንድ ነገር አለ ‹‹አመለጠ›› የሚል ቃል ነው። እሱ ግን እዚያው ነው። እንዲያውም በዱላ ብዛት ሊሞት እያጣጣረ ነው። ምግብ ለመብላት አፉ አይፈቅድለትም። ዳቦ በውሀ እርጥበው እየሰጡት ሳያላምጥ ይውጠዋል። አብረውት ያሉት ሁለት እስረኞች ክፉኛ ቢደበደቡም የእሱ ግን የተለየ እንደሆነ ስላወቁ ሟች እንደሆን ተረድተዋል።

እንደዛም ሆኖ በጥብቅ የሚፈለግ እስረኛ በመሆኑ ወደ መጸዳጃ ቤት በሽክም ሲሄድ በከፍተኛ ጥበቃ ስር አድርገውት ነው። ከአምስት ቀን በኋላ ወደ አዲስ አበባ እንዲሄድ አዘጋጁት። በአስቸኳይ እንዲልኩት ስለታዘዘ ነው የሚሄደው። የእሱ ጉዳይ ለከፍተኛ ሀላፊዎች ስለተነገረ ቶሎ እንዲደርስላቸው ይፈልጋሉ። ደርግ ጽህፈት ቤት ምርመራ ክፍል ሲገባ እውነቱን ይና ገራል።አንዳንዶቹ ‹‹ቶሎ ይሂድ እዚህ ሊሞት ነው››ይሉ ጀ መር።መስከረም 13 ቀን እስረኛውን ወደ አዲስ አበባ የምትወስደው መኪና ወደ ግቢው ዘለቀች። መኪናዋ መጠነኛ ጥገና ሊደገረግላት ወደ ጋራዥ አመራች። ከአንድ ሰዓት በኋላ እስረኛው ያለበት ክፍል በር ላይ ቆመች። አጃቢዎቹ አበላቸውን ወሰዱ። መሳሪያቸውን አዘጋጁ። ተጨማሪ የጥይት ካርታ ከመሳሪያ ግምጃ ቤት ወሰዱ። ይሄ እስረኛ መወሰድ ያለበት በፖሊስ ሆኖ እንዴት ወታደር ያጅበዋል በሚል ቅሬታ የነበረ ቢሆንም ፖሊስ ሌላ አሰሳ ስላለበትና እጥረት ስለተፈጠረ ወታደር በአስቸኳይ እንዲወስደው ነበር የተደረገው። ጸሀይ ከማዘቅዘቁ በፊት እስረኛው አዲስ አበባ መድረስ አለበት። ከመሸ መንገድ እንዲሄዱ አይመከርም። ኢህአፓ

ጨለማን ተገን አድርገው ብዙ ግዜ በመኪና የሚሄድ እስረኛ ያስጥላሉ። ከአንድ ወር በፊት ከቦረና ተይዞ የተወሰደ እስረኛ መንገድ ላይ በምሽት ጠብቀው ተታኩሰው አስመልጠውታል። አሁን እዚህ ካምፕ የሚገኘው አባይነህ በቶሎ ለመውሰድ ተፍ ተፍ እያሉ ነው። መኪናዋ በር ላይ እንደቆመች እስረኛው ከክፍል እንዲወጣ ትእዛዝ ደረሳቸው። በሸክም መኪናው ወለል ላይ አስተኙት። መንቀሳቀስ ባይችልም እጁ በካቴና ታስሯል።

ከ30 ደቂቃ በፊት የገቡት ሶስት ሰዎች ወደ ሲዳሞ የህዝብ ደህንነት ጽህፈት ቤት ስልክ እየተደዋወሉ ነበር።እነዚህ ካድሬዎች ከይርጋለም የህዝብ ደህንነት ጽህፈት ቤት የመጡ ናቸው። የሻሸመኔ አብዮት ጥበቃ ሀላፊ በአስቸኳይ ወደ ግቢው እንዲመጣ ተደረገ። ከይርጋለም የመጡት ካድሬዎች አንድ ሴት ለአስረጂነት ይዘው መጥተዋል። ሴትየዋ ፎቶግራፍ በጋዜጣ ጠቅልላ ይዛለች። እስረኛው እንዲመጣ ተደረገ ።ሹፌሩ‹‹አረ ቶሎ እንሂድ ይመሽብናል!!!››እያለ ቅሬታውን እየገለጸ ነው። እስረኛውን ወዲህና ወዲያ ማመላለሳቸው ግዜ እየገደሉ እንደሆነ ገብቶታል። አባይነህ ወደ ሀላፊው ክፍል በሸክም ገባ። መቀመጥ ስለማይችል መሬት ላይ አጋደሙት። ሴትየዋ ስታየው እሪታዋን ለቀቀች።ልጇን እንደዚህ ተልተለው ይጨርሱታል ብላ አልጠበቀችም።

የአብዮት ጥበቃ አስተባባሪው ከከተማ በፍጥነት መጣ። እስረኛው ወደ አዲስ አበባ ዛሬ ጠዋት እንደሄደ ነው የሚያውቀው። ከእንግዲህ አባይነህ ላይ ምንም ምርመራ ሳያደርጉ እንዲልኩ ስለተነገራቸው የእሱ ጉዳይ ከእጃቸው ወጥቷል። ታዲያ አሁን ለምን ጠሩት? የካምፑ ሀላፊ የአብዮት ጥበቃ አስተባባሪውን እየጠየቀው ነው ‹‹ወንጀለኛው እሱ ነው እንዴ?››አለ

‹‹አዎ››(ባለመገረም)

‹‹እርግጠኛ ናችሁ?››

‹‹በጣም እርግጠኛ ነን››

‹‹እሱ ለመሆኑ ምንድነው ማስረጃው?››

‹‹ጓዳችንን ገሎብናል ገንዘብም ዘርፏል››





‹‹ከዚህ በፊት ይዛችሁት እንደነበር ነግረኸኛል››

‹‹አዎ አምልጦን ነው››

ሃላፊው ለአብዮት ጥበቃ አስተባባሪው አንድ ፎቶ ሰጠው። ፎቶው ትልቅና ሁለት ወንድማማቾች የተነሱ ነው።የካምፑ ሃላፊ ጠየቀው‹‹አባይነህ የቱ ነው?››አለ

‹‹ምን አልክ? ››

‹‹ለይተህ ንገረኝ››

‹‹ግራ ያጋባል››

‹‹እንዴት?››

የአብዮት ጥበቃው አስተባባሪው ፎቶውን ደጋግሞ አየው። የሚፈልጉት ወንጀለኛ በትክክል ይሄ ነው ብሎ ለመናገር አቃተው። ሀላፊው ‹‹እስረኛውን ከይርጋለም ስታመጡ አረጋግጣችኋል?››አለ

‹‹እንዴት?››

‹‹እሱ መሆኑን››

‹‹እዚህ ከተማ ካለው ዘመዱ ፎቶ አገኘን ከዚያም ለፍለጋ ሰው አስማራን››

‹‹እና ››

‹‹መንገድ ላይ አገኙት››

‹‹እሺ ››

‹‹ለእኛ ነገሩን››

‹‹ቀጥል››

‹‹ስንሄድ እሱ መሆኑን አረጋገጥን››

‹‹እሱ ልክ ነህ ግን እዚያ ላሉት ካድሬዎች ለምን አላሳያችሁም?››

‹‹እሱ መሆኑን አልተሳሳትንም››

‹‹አሁንስ?››

‹‹ግራ ያጋባል››

እስረኛው መሬት እንደተኛ የሚነጋገሩትን ሰምቷል። ደግሞም እያለቀሰ ነው። ሀሳብ ለመስጠት ተንቀሳቀሰ ግን መናገር አልቻለም። ተፈላጊው አባይነህና ወንድምየው መንታ ናቸው። ምንም አይለዩም። አባይነህ ከራንቻ ጥርሱ በቁመት በመልክ በሁሉም ይመሳሰላሉ።

ስለተሸረፈ ሁለቱም በዚህ ይለያሉ። ጓደኞቻቸው ሲጠራጠሩ ማንነታቸውን ለማወቅ ከንፈራቸውን እያስገለጡ ጥርሱን አይተው ያጣራሉ። የአብዮት ጥበቃ አስተባባሪው ፎቶውን ይዞ ተገተረ። ይሄኛው እስረኛ የመኢሶን ጓድ ነው። አባይነህ ወንድምየው ኢህአፓ መሆኑን አያውቅም። በእሱ የተነሳ እንደያዙት አልረተዳም።

የይርጋለም ህዝብ ደህንነት ሰዎች ጓዳቸው በመጥፋቱ ባለሱቁ ጠቆሚቻቸው። በማፈላለግ ባዘኑ በመጨረሻ ሻሸመኔ እንደታሰረ መረጃ ስለደረሳቸው መጡ። ኢህአፓ ለግድያ እንደምትፈልገው ስለሚያውቁ እነርሱ ጠልፈው እንደወሰዱ ነበር የገመቱት። እሱም ቢሆን ገራፊዎቹን ኢህአፓ ናችሁ እያለ ይናገር ነበር። እግሩ ስለተተለተለ እንኳን ኳስ ሲጫወት ለመራመድም ችግር ሆነበት። የዚያን ቀን ለልምምድ ትጥቅ ይዞ ሲሄድ ነው የያዙት። ካድሬዎቹ በደረሰበት ድብደባ በጣም አዘኑ። በአብዮቱ ስም ይቅርታ ጠየቁት።





## ምእራፍ 21

## የበረቱ ግብግብ

በስተሰሜን ሻሸመኔ በከተማው ጥግ ላይ የሚገኘው ቀበሌ 10 በተለምዶ ሀሴሉ ቀበሌ ይባላል። ሀሴሉ የገበያው ስም ነው።በደቡብ ትልቁ ገበያ እንደሆነ ይነገርለታል። ሻሸመኔ የአራት ክፍለ ሀገር መገናኛ በመሆኑ ገበያው ሰፊና ሁሉን ያጨቀ ነው።ሀሴሉ ቀበሌ የሚገኙ አብዮት ጥበቃዎች ተርብ ናቸው።አንዳንዴ ከስርአቱ ወጥተው በገበያው አመለካከት ይመራሉ።እዚያ ያሉ አብዮት ጠባቂዎች በጣም የሚታወቁት በመግረፍ ነው።

ዛሬ አንድ የሚፈልጉት፣ፈልገው የሚይዙት፣ይዘው የሚገርፉት ፣ገርፈው የሚያሰቃዩት ሰው አለ። ያሰቡት እሱን ብቻ ነው።በኋላ ግን መረጃ አግኝተናል በሚል የተፈላጊዎቹን ቁጥር ከፍ አድርገውታል። የአብዮት ጠባቂዎቹ ወደ ተፈላጊዎቹ ጃማይካውያን ሰፈር በስልት ቀስ ብለው መጡ። የቀበሌያቸው ሊቀመንበር ጥላሁን በላይን የገደሉት ወጣቶች የመሸጉት እዚህ ጃማይካ ሰፈር ነው።ደግሞም ‹‹እኛ ጋር አልመጡም›› ብለው ክደዋቸዋል።አንዱ ቤት ውስጥ ተሸሽገዋቸው ነው ብለው አምነዋል።የነዚህ የኢህአፓ ስኳዶች መነሻቸውና መሸሸጊያቸው እዚህ ሰፈር ነው።የዚያን ቀን ሁለቱን ወጣቶች አሳልፈው ቢሰጧቸው ሊቀመንበራቸውና የትግል ጓዳቸው አይሞትም ነበር።ለብዙ ቀን ስብሰባ አደረጉ።ብዙ ነገር አጣሩ ።

የአብዮቱ ጠላቶች የተሰገሰጉት እዚህ ጃማይካ ሰፈር ነው።እዚህ ሰፈር ምንጠራ መደረግ አለበት ።ጃማይካውያን በሁለት ቀበሌ ተከፋፍለው ይኖራሉ።አንደኛው ወገን በስተምስራቅ በኩል ሰፍሯል። ይሄ ክልል አዋሾ ገበሬ ማህበር ይባላል።ሌሎቹ ደግሞ በስተምዕራብ በኩል ቀበሌ 10 ይኖራሉ።አንደኛው በከተማ ሌላኛው በገበሬ ማህበር ቢጠቃለሉም የሚራራቁት በ50 ሜትር አካባቢ ሲሆን የሚለያቸው

ዋናው እስፓልት ነው። የሁለቱ ቀበሌ አብዮት ጠባቂዎች ድንበር ቢለያቸውም የሀሌሉ ቀበሌ ሰዎች ድንበር አቋርጠው እነዚህን ተፈላጊ ጃማይካውያን ለመያዝ ተዘጋጅተዋል።ኢህአፓ ጃማያካውያን ሰፈር መሳሪያ ደብቋል።ለገዳዮችም መሸሸጊያ ሰጥቷል።እነዚህ የተሸሸጉት ስኳዶች እዚህ ተደራጅተው በከተማው ዋና ዋና ቦታ ጥቃት ሊፈጽሙ ነው በሚል መረጃ አግኝተዋል።እንዳለፈው ጊዜ የተልፈሰፈሰ አሰሳ ብቻ አድርገው አይመለሱም።ለዚህ እቅድ ሲዘጋጁ ሌላ መረጃ አገኙ። በተገኘው መረጃ ላይ በዝርዝር ተነጋገሩ።የተገኘው ነገር ሰፋ ተብሎ ተተነተነ።

መረጃው መንግስቱ ሀይለማርያም ወደ ሀዋሳ ስለሚመጣ እዚህ አካባቢ መንገድ ዘግተው ለመግደል አቅደዋል የሚል ነው።መረጃውን ሀሰት ነው ብሎ ለመጣል ምክኒያት የላቸውም።ባለፈው ጥላሁን ስኳዶች እዚህ ተደብቀዋል በሚል ሁሉን ዘርዝሮ ሲነግራቸው ቢያምኑትም ጥርጣሬ ነበራቸው።ምክኒያቱ ደግሞ ባለፋርማሲውን ጠይቀውት ስፖርተኞች ናቸው ብለው ስለነገሯቸው ነው።ለዚህም ነው ለዘብ ያሉት።‹‹የጥላሁንን ስጋት ተጋርተን ድብን አድርገን ብንፈትሽ ገዳዮቹን እናገኝ ነበር›› በሚል ተቆጭተዋል። በአሁን ግዜ ለጥቃቅኗ መረጃ ጥርጣሬ ሳይሰማቸው አምነው በመቀበል ወደ እርምጃ መሄድ ነው።አሁን እንደተባለው ሻለቃ መንግስቱ እዚህ አካባቢ ርምጃ ቢወሰድባቸው........እረረረረ!! አይደረግም። ለማንኛውም አካባቢውን ለማጥራት የመንጥር ዘመቻ ማካሄድ አለባቸው።

ዋናው ነገር ለጥላሁን ገዳዮች የበቀል ርምጃ መውሰድ ፈልገዋል።ጃማይካውያን በቀበሌ 10 ቢኖሩም የኢህአፓ ምሽግ ነው ያሉት ስፍራ ከፊት ለፊት ባለው ገበሬ ማህበር ነው የሚገኘው።ይሄ ደግሞ አዋሽ ቀበሌ ይባላል።የሀሌሉ ቀበሌ ሰዎች ይሄን ያቀዱትን ነገር ለመፈጸም የአዋሽ ቀበሌ አብዮት ጠባቂዎች እንዲተባበሯቸው ይፈልጋሉ። የጥላሁን ገዳዮች እዚህ መሽገው እንደነበር አስረዷቸው ።በሻለቃ መንግስቱ ላይ የታቀደውን ሴራ ነገሯቸው። ይሄንን ሲሰሙ የአዋሽ ሰዎች‹‹ይሄማ ታላቅ ሴራ ነው›› በሚል ለትብብር ተዘጋጁ። የሀሌሉ ቀበሌ ሰዎች ትብብር የፈለጉት ዘጠና በመቶ ጃማይካውያን የሚገኙት በአዋሽ ቀበሌ በመሆኑ ነበር።





አንድ እለት ጢሻ ውስጥ ተደበቁና ሳይታዩ ድንገት በከበባ ለመያዝ በነደፉት ስትራቴጂ ለጥቃት ተዘጋጁ። ጃማይካውያን ብዙ ጊዜ ቤታቸው ዝግ ነው። የአጥር በራቸውም ቅርቅር ነው። በብዛት ወደ ውጭ አይታዩም።አብዮት ጥበቃዎቹ በግላጭ ከሄዱ ተሸሽገዋል ተብለው የሚጠረጠሩት የኢህአፓ ስኳዶች ሊያመልጧቸው ይችላሉ። ሙክታር ስራጅና ታዬ ጸጋዬ በር ላይ ከዳካ ጋር ቆመው ያወራሉ። ብስክሌት ይዘዋል።ሁለቱም በከተማው የታወቁ ኳስ ተጫዋቾች ናቸው።ዳካም ከእነርሱ ጋር ገሞራው ለተባለ ቡድን ይጫወታል። ሁለቱ ወጣቶች የመጡት ከመልካ ኦዳ ነው።ከአብዮት ጥበቃዎቹ አንዱ ሙክታርን በጣም ያደንቃዋል፤ ይወደዋል።ሁለቱም ጥቂት ካወሩ በኋላ ብስክሌታቸው ላይ ወጥተው ወደ ከተማ ሄዱ።አብዮት ጥበቃዎች አስቁመው ሊያናግሯቸውና ለምን እዚህ እንዳመጡ ሊጠይቋቸው ነበር። የሌሎችን ትኩረት ላለመሳብ ሲሉ ተዋቸው (በነገራችን ላይ ሁለቱም ተጫዋቾች ከሻሸመኔ ባንክ ኦፐሬሽን በኋላ የገቡበት አልታወቀም) ጥቂት ቆዩና የሁኔታውን መመቻቸት አይተው ለመንቀሳቀስ ተዘጋጁ። አንድ ሰው ወደ እርሻ ውስጥ ሲገባ አዩ። ጃማይካዊ ነው ።መጀመሪያ እሱን በቁጥጥር ስር ለማድረግ ፈለጉ።

ማንነቱን ሲያዩት ሁሉም ለመድፈር አልፈለጉም። ሰውየው አማዞን ይባላል።አጭር፤ ፈርጠም ያለ፤ ጥቁር ሆኖ ጺሙ ጥቅጥቅ ያለ ነው።የከተማው ሰው በጨካኝነቱ ነው የሚያወቀው።ሰው ላይ አይደርስም። ከነኩት አይመለስም። ‹‹እኔ በር ላይ ሽንትህን ለምን ትሸናለህ?›› ብሎ ከአንዱ ጋር ተጨቃጭቆ ስለሰደበው ሰውየውን ጣቱን በቆንጨራ ከትፎ በመጣሉ ታስሮ ነበር። በሌላ ግዜ ከሶስት ወታደሮች ጋር ተጣልቶ ተሸክመው ድልድይ ውስጥ ጨምረውት ከዚያ ወጥቶ እያሳደዳቸው አደጋ አድርሶባቸዋል። ተፈንክቶ አይደማም፤ በጥይት ተመቶ አይበገርም እያሉ በጨካኝነቱ ያወሩለታል። አሁን እርሻ ውስጥ አማዞንን ያዩት አብዮት ጥበቃዎች ያወሩለታል። አሁን እርሻ ውስጥ አማዞንን ያዩት አብዮት ጥበቃዎች

ጥበቃ) ነገሩን እንዲህ ያስታውሳል‹‹የአዋሽ ገበሬ ማህበር ታጣቂዎች መንደሩን ዙሪያውን ከበቡት፡፡እኛእዚህ መሸገዋል የተባሉትን ለመያዝ ተንቀሳቀስን››ይላል፡፡

ወዲያውኑ የግቢውን በር እየደረመሱ ገቡ፡፡ ቤታቸውን መፈተሸና የተደበቁትን ስኪዶች ፈልፍለው ለመያዝ መበርበር ጀመሩ፡፡ ከአንዱ ግቢ ወደ ሌላው ቤት በፍጥነት ተንቀሳቀሱ፡፡ግን ጸጉረ ልውጥ ሰው አላገኙም፡፡ የተደበቀ መሳሪያ አለ ስለተባሉ ያንንም መበርበር ያዙ፡፡ ምንም ስላልተገኘ ሌላ ነገር ፈለጉ፡፡ ጃማይካዎቹ የቢቢሲ ሬድዮ የሚያደምጡት በአንቴና ነው፡፡ሰዎቹ አንቴናው ከኢህአፓ ጋር መልዕክት የሚለዋወጡበትና ለሲአይኤ መረጃ ማስተላለፊያ ነው አሉ፡፡የአናጺ እቃ...መጥረቢያና ሌላ የስለት መሳሪያ ሰበሰቡ፡፡ ቤቱ ውስጥ የጃንሆይ ፎቶ ተሰቅሏል‹‹ይህችን ይወዳል !!! የወረደው ንጉስ እንናንተ ሰቀላችሁት?››እያሉ ማዋከብ ጀመሩ፡፡ ችካን ጠሩትና ‹‹ይሄን ፎቶ አውርድ›› አሉ

‹‹አላወርድም››

‹‹አታወርድም?››

‹‹አዎ››

‹‹ለምን?››

‹‹እወዳቸዋለሁ››

‹‹ምን አልክ? ››

‹‹አባቴ ናቸው››

‹‹ካላወረድክ እኔ በጠመንጃ አወርዳቸዋለሁ››

‹‹መንካት አትችልም››

‹‹እንዴት?››

‹‹አትችልም አልኩህ››

.....ችካን ለማሰር ለሁለት ያዙት ‹‹ኖ .ኖ...አይፈልጉም (አልፈልግም)... አይፈልጉም!!››እያለ ጮኸ፡፡ ባትፈልግም ትጠፈራለህ ብለው እጁን ጠምዝዘው አዙረው ሊያስሩ ሲሉ ወደ ግራና ቀኝ ገፍትሮ ጠላቸው፡፡‹‹ይህችን ይወዳል አብዮት ጥበቃ!!!›› ሁለቱ ከመሬት ተነሱ፡፡ ሌሎቹ መሳሪያ ደገኑበት፡፡ የአንዱን መሳሪያ አፈሙዙን ያዘና ሊነጥቀው ታገለ፡፡ ከኋላ ያለው ማጅራቱን ሲለው





ሉሉች ተረባረቡበትና ታሰረ፡፡ በጥላሁን ሞት ለገዳዮቹ መሸሸጊያ ሰጥተዋል ተባብረዋል ብለው የጠረጠሯቸውን ጃማይካውያን መግደል ይፈልጋሉ፡፡ዴዝማን ማርቲንና ችካን መርጠው ያዙ፡፡ጄእንም ከእነርሱ ጋር አብራ አለች፡፡እሷም እየተገረፈች ነው፡፡በጣም ያተኮሩት ዴዝና ችካ ላይ ነው፡፡ቆካንም ይፈልጋሉ፡፡ቆካና ዴዝማን በከተማው ታዋቂ የሆነው የገሞራው ቡድን ተጫዋች ናቸው፡፡ዴዝማን ፈጣንና ምቱ ጠንካራ ነው፡፡ ሲጫወት ኳስ ይዞ ስለሚደንስ ጉረኛ ነው ይሉታል፡፡ ዴዝማን በ1972 የኢትዮጵያ 100 ሜትር ሪከርድ የሰበረ ሯጭ ነው ፡ ለገሞራው ቡድን በግራ ክንፍ ሲጫወት በፍጥነቱ ማንም አይደርስበትም፡፡ የገሞራው ቡድን ማሊያው ቀይ ነው፡፡ይሄንን የማሊያ ቀለም የመረጡት ኢህአፓ አርማ ቀይ በመሆኑ ከዚያ ጋር ለማመሳሰል ነው ይላሉ፡፡ብዙዎቹ ተጫዋቾች ወታደራዊ መንግስትን ስለማይደግፉ የኢህአፓ አቀንቃኝ ናቸው በሚል የከተማው ካድሬዎች ፈርጀዋቸዋል፡፡(ከሁለት ወር በኋላ ተጫዋቾቹ ከኢህፓ ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው ታስረዋል፤ ተገድለዋል)እነዚህም ሁለት ጃማይካ ከቡድኑ ጋር በተያያዘ የኢህአፓ አባልና ተባባሪ እንደሆኑ የቀበሌ 10 አብዮት ጥበቃዎች አምነዋል፡፡ደግሞም በድፍረት የንጉሱን ፎቶ ሰቅለው አናወርድም ማለታቸው አናዷቸዋል፡፡የጥላሁን መሞት እያንገበገባቸው የበቀል ርምጃ ለመውሰድ ወደ ጫካ እየነዱ ወሰዷቸው፡፡ዴዝማን እየተቃወመ ነው፡፡‹‹ወዴት ነው የምትወስዱን?››አለ

‹‹ዝም ብለህ ሂድ››

‹‹ምን አጠፋን? ››

‹‹ወንጀለኛ ናችሁ››

‹‹ካጠፋን ወደ ህግ ቦታ ውሰዱን››

‹‹ምን አልክ ?››

‹‹ፖለስ ጣቢያ ውሰዱን››

‹‹እናንተ ፖሊስ ጣቢያ መታሰር የለባችሁም››

‹‹እና››

‹‹እኛ ነን የምናውቀው››

‹‹እንሄድም››

በያዙት ስደፍና ዱላ እየመቱ ወደ ጫካው ይዘዋቸው ሄዱ።ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያውቃሉ። የአዋሾ ቀበሌ ሰዎች ከሀሌሉ በመጡት አብዮት ጠባቂዎች ውሳኔ መቃወም እየጀመሩ ነው። ይሄ ደግም የታሰበውን ርምጃ ላይ እንቅፋት ሊፈጥርበት ይችላል።በብዙ ወንጀል የተጠረጠሩት ሁለቱ ሰዎች ምንም አልተገኘባቸውም።ይሄን የአዋሾ ሰዎች አረጋግጠዋል።አሁን ሌላው ነገር ቀረና ትልቁ አጀንዳ የጃንሆይ ፎቶ ጉዳይ ሆነ። ‹‹..ጃንሆይ ተመልሰው ይመጣሉ ››በሚል በአካባቢው እየሰበኩ። ገበሬው በወታደራዊ መንግስትላይ እምነት እንዳይኖረው እያደረጉ ነው በሚል ማዋከብ ተጀመረ።ጉዞው ቀጥሏል። ወደ ጫካው እየተነዱ።እንደገናም ያሰቡበት እስኪደርሱ መግረፋቸውን አልተውም።አንድ ቦታ ደረሱ። የከብቶች በረት ነው። ውስጥ የነበሩት ጥቂት ከብቶች ወደ ውጭ አወጧቸው።ወደ እስረኞቹ እያዩ‹‹እዚህ ግቡ››አሏቸው

‹‹ለምን?
‹‹ግቡ ብለናችኋል››
‹‹አንገባም››
‹‹ብትገቡ ይሻላል››
‹‹እምቢ››

በግርፊያ ወደ ውስጥ አስገቧቸው። እጃቸው እንደታሰሩ መቀጥቀጥ ጀመሩ። ዴዝማን ነገሩን እንዲህ ያስታውሳል ‹‹....የሚመራቸው አንድ ሰው ነው። እሱ ከበረት ውጭ ሆኖ እዚህ ጋር ምታው፣ ጣለው ፣እርገጠው ፣ፈንክተው እያለ ቀጠቀጡን። እኔ ዱላ ሲበዛብኝ ብዬ የማላውቀውን የውጭ ዜጋ ነኝ አልኩ

‹‹ብትሆንስ?››
‹‹ልትመቱኝ አትችሉም››
‹‹እንዴት ነው የማንመታህ?››
‹‹አትነኩኝም››
‹‹እናሳይሀለን››

እንደገና ግርፊያው ተጀመረ። በእልህና በንዴት ነው የሚገርፉን›› ይላል። ጬኸቱና ግብግቡ ቀጠለ። ከግርፊያ ውጭ ምንም ለማድረግ አልቻሉም። ምክንያቱም በተወነጀሉበት ነገር ማስረጃ ስለሌላቸው የአዋሾ ሰዎች ለግድያ የሚያበቃ ነገር አላገኙባቸውም።





የቀበሌ 10 ሰዎች እነዚህን ጃማይካ እነርሱ ቀበሌ ክልል መውሰድ እንደነበረባቸው አምነዋል። አዋሾ ውስጥ ከመግረፍ በስተቀር ለጥይት እራት የሚሆን ነገር አላገኙም። ሌላ ቀን አዘናግተው እነርሱ ቀበሌ መውሰድ እንዳለባቸው ተስማምተው ለዛሬው መግረፉን አጠናክረው አቆሳስለው ተመለሱ።

ከአብዮት ጥበቃዎቹ አንዱ በሁለተኛው ቀን ወደ ከተማ ሲሄድ ሙክታርን አገኘው። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ‹‹ጃማይካ ሰፈር መጥተህ ነበር አይደል?››አለው

‹‹መቼ?››
‹‹ሰሞኑን››
‹‹አልሄዱኩም››
‹‹አይቼሀለሁ››
‹‹ምን ሳደርግ?››
‹‹ከዳካ ጋር ቆመህ››
‹‹ከሌላ ቦታ ስመጣ እግረመንገዴን ነው››
‹‹ጥላሁን መሞቱን ታውቃለህ?››
‹‹አዎ››
‹‹ገዳዮቹ እዛ ሰፈር የመሸጉ ነበሩ››
‹‹የት?››
‹‹ጃማይካዎቹ ጋር››
‹‹እንዴት አወቅክ?››
‹‹ጥላሁን ነግሮን ነበር››
‹‹እና››
‹‹እዛ ሰፈር በሄድክ ጊዜ የተለዩ ሰዎች አይተህ ነበር?››
‹‹እኔ እኮ እዚያ አላዘወትርም››
‹‹ምናልባት ዳካ ነግሮህ ከሆነ››
‹‹እየመረመርከኝ ነው?››
‹‹እንደሱ ማለቴ አይደለም››

ሰውየው ከሙክታር ጋር ተጨቃጨቁ። የሙክታር አድናቂ ቢሆንም ከእሱ የሆነ ፍንጭ አገኛለሁ የሚል ተስፋ ነበረው።ጥላሁን ስለ አንደኛው ልጅ የነገረው ገጽታ አሁን እየተመሳሰለበት ነው። ጥላሁን የነገረው አቋምና ሙክታርን አተኩሮ ሲያይ ተመሳሰለበት። አሁን ሁሉም ነገር ግልጽ እያለለት ሄደ።

## ምእራፍ 22

### የመሸሸጊያ ከተማ

ከተከራየችበት ቤት አልፎ አልፎ ወደ ከተማ የምትወጣውን ልጅ ብዙም ትኩረት የሰጣት የለም።በጎረቤቶቿ በጣም የምትወደድ ሲሆን ለችግራቸው ደራሽ ነች። ጎረቤቶቿ የት እንደምትሰራ አያውቁም። ደግሞም ይሄ ነገር አያሳስባቸውም። ብቻ እሷ ትስማማቸው እንጂ። በኋላ ግን ከይርጋለም ተቀይራ የመጣች የመንግስት ሰራተኛ መሆኗን ሰሙ። አልፎ አልፎ አንድ ሰው ወደ ቤቷ ብቅ ይላል። ወጣቱ የሀዋሳ ሀይቅ ቡድን ተጫዋች ነው። ወንድሟ መሆኑን ነግራ ለጎረቤቶቿ አስተዋወቀችው።

በር ዘግተው ብዙ ሰዓት ይቆያሉ፡ወጣቱ ችኩልና ፈቱ ላይ ድንጋጤ ብጤ የሚታይበት ቢሆንም ሰው አክባሪ ነው።ብዙ ግዜ ኮፍያ ያደርጋል። ራሱን ለመደበቅ ይሞክራል። ወጣቱ ብዙም ሳይቆይ ተገደለ።ሀዋሳ የነበረው እንቅስቃሴ ሀይቅ ቡድን ላይ ነገሩ እንዲያተኩር ተደረገ።የቡድኑ ተጫዋቾች እየታደኑ ተያዙ።ግማሾቹ አመለጡ።ሻሸመኔ ተደብቆ የነበረ አንድ የቡድኑ ተጫዋች አራዳ በሚገኘው ሜዳ ልምምድ ሲሰራ ከተማውን ሲያስሱ የነበሩት የሀዋሳ ካድሬዎች ጠልፈው ወሰዱት። ይሄ ከሆነ ከወር በኋላ ልጅቷ ወደ ግቢ ስትገባ በአቋራጩ ያልፉ የነበሩ ከተቻኮሉ አብዮት ጠባቂዎች ጋር ተገጣጠሙ። ‹‹ደህና ዋላችሁ››አለች

‹‹ደህና››

‹‹ስራ እንዴት ነው?››

‹‹ጥሩ ነው››

ሰላምታው ከዚህ የዘለለ አልነበረም ።ወደ ጉዳያቸው እየሄዱ የነበሩት አብዮት ጠባቂዎች ስራቸውን ጨርሰው ወደ ጽህፈት ቤታቸው ተመለሱ።ከመሀላቸው አንደኛው ‹‹ይህች ልጅ››አለ

‹‹የቷ?››





‹‹ሰላም ያለችን››

‹‹የቅድሟ ልጅ?››

‹‹አዎ››

‹‹እና››

‹‹ታውቃታለህ?››

‹‹ነግረውኛል››

‹‹ምን?››

‹‹ተቀይራ የመጣች ነች››

‹‹ከየት ?››

‹‹ከይርጋለም››

‹‹ምንድነው የምትሰራው?››

‹‹እንጃ!! ግን አስተማሪ መሰለችኝ››

‹‹ለምን አንጠይቃትም? ››

‹‹ምን ብለን?››

‹‹ዝም ብለን እናናግራት››

‹‹ፈልገሀታል እንዴ? ››

‹‹ስነስርዐት››

አሁን ያነሳው ነገር አላስደሰተውም። ‹‹እንዴት ፈልገሀታል ትለኛለህ?›› በሚል አኮረፈ። በኩርፊያ ብቻ አልቀረም። በከባዱ አጨቃጨቃቸው። ከጾታ ጋር በተያያዘ አብዮት ጥበቃና ካድሬዎች ሴቶችን እያስገደዱ ይተኛሉ በሚል ወቀሳ በተለያየ ግዜ ይቀርባል። ከዚህ በመነሳት ልጅቷ ላይ አተኩሯል ወደሚለው ነበር የወሰዱበት። የተወቀሰው ሰው በድጋሚ ‹‹እንዴት እንዲህ ትለኛለህ?›› ብሎ አከረረው።

‹‹ስታተኩርባት ነው››

‹‹ባተኩርስ?››

‹‹የመሰለኝን ተናግሪያለሁ››

‹‹እንላቀቅም››

‹‹ይቅርታ!! እንዲህ የሚከፋህ አልመሰለኝም››

ይቅርታውን ቢቀበልም ነገሩ ግን ከንክኖታል። ይሄ አብዮት ጠባቂ በሴቶች የሚጠረጠር ነው።አሁን ሊፈጽም ያሰበው በፖለቲካ የተነሳ ወደ ልጅቷ እንዳይቀርብ ነበር።ይሄን መንገድ እየዘጉበት በመሆኑ ሌሎቹ ተስማምተዋል። ተጠርጣሪው ሰው ለዚህ ጉዳይ ያለመሆኑን ለማሳየት ‹‹አብረን ሄደን ልጅቷን እናናግራት›› አለ

‹‹እስፈላጊ ነው?››

‹‹ቀበሌያችን ውስጥ እንግዳ ሰው ሲመጣ መርምሩ ተብሎ ነበር››

‹‹ተመርምራለች ››

‹‹መቼ?››

‹‹ሰሞኑን....ደግሞ››

‹‹ደግሞ ምን?››

‹‹ጎረቤቶቿ መስክረዋል››

‹‹ምን ብለው?››

‹‹ሰላማዊና አብዮታዊ መሆኗ››

‹‹ቢሆንም በጋራ እንመርምራት››

ሰውየው ነገረኛና የማይለቅ እንደሆነ ያውቃሉ። ወደ ቤቷ ተመልሰው መሄድ አልፈለጉም። ግን ስለጨቀጨቃቸው ሄዱ።ውጭ ሆነው አስጠሯት።‹‹መቼ መጣሽ እዚህ?››አለ

‹‹አመት ሆነኝ››

‹‹የትነው የምትሰሪው?››

‹‹መምህር ነኝ››

‹‹የት?››

‹‹አጼ ናኦድ››

‹‹ስንተኛ ክፍል››

‹‹አሁን ለጊዜው ትቻለሁ››

‹‹ለምን ?››

‹‹በጤና ችግር››

‹‹እውነትሽን ነው?››

‹‹አዎ››





ሰዎቹ ጥርጣሬ አልነበራቸውም ።ሆኖም ሰውየውን ለማስደሰት ወደ ቀበሌ ይዘዋት ሄዱ። ነገር ግን እዚያ ሳይደርሱ ተኩስ ተከፈተባቸው።ተኳሹ ማን እንደሆነ ባያወቁም ከልጅቷ ጋር ግንኙነት እንዳለው አልጠረጠሩም።እንደኛው አብዮት ጠባቂ ‹‹ ሰሞኑን ቤቷ ሲገባ ያየሁት ሰው ነው የተኮሰው››በማለት ልጅቷ ላይ አጠበቁባት። ወደ እስር ቤት ተወሰደች።ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከአዲስ አበባ በመጡ የህዝብ ደህንነት ሰዎች በጣም የምትፈለግ የከፍተኛ ኢህአፓ አመራር ሆና በመገኘቷ ወደ ደርግ ጽፈት ቤት ሄደች።እዚህ ከተማ ውስጥ የኢህአፓ ትልልቅ ሰዎች እንዳሉ ጥርጣሬ አሳደረ። ከእስር ቀን በኋላ አንዲት ሴት ተያዘች።ምንም ስለሌለባት ተለቀቀች።ነገር ግን ምሽት ላይ መልሰው ያዟት።ብዙ ተመረመረች ።በቂ መረጃ ባይገኝም ተራ የኢህአፓ አባል ናት በሚል ታመነ።

ነገር ግን እሷም ከፍተኛ አመራር አባል ውስጥ እንደነበረች በመረጋገጡ ወደ አዲስ አበባ ተወሰደች። አሁን ደርግ ሻሸመኔን ላይ መረቡን ዘረጋ።በእርግጥም ዋና ዋናዎቹ የኢህአፓ አመራርና ስኳዶች እንደመሸጉ ተረጋገጠ።እዚህ መኖራቸው የታወቀው ደርግ እስሶና አጥንቶ አልነበረም።በኢህአፓ ውስጥ የተፈጠረው አንጃ ያሉበትን ለደርግ ስለጠቆመ መሆኑን ብዙዎቹ ይናገራሉ።በእርግጥ ኢህአፓ ዋና ዋናዎቹን ሰዎች ሻሸመኔ አስቀምጦ ነበር። የኢህአፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረው ክፍሉ ታደሰ‹‹ያ ትውልድ ››በሚለው መጽሀፉ በቅጽ ሶስት በገጽ 229 ላይ ይሄን ነገር እንዲህ ይገልጻል‹‹.....በደቡብ የሀገሪቱ ክፍል የኢህአሰን እንቅስቃሴ ለመጀመር ከተፈለገባቸው ምክኒያቶች አንዱ ለሚሳደዱ የኢህአፓ አባላት መጠጊያ ስፍራዎች ማዘጋጀት የነበረ ቢሆንም ይህ ሽንፈት በከተማ ውስጥ የነበረውን የድርጅቱ መዋቅር አባላቱን ለአደጋ አጋለጠ።የሲዳሞ በይነ ቀጠና ኮሚቴ ለመሳሪያ ትግል ሲያደርግ የነበረውን ጥረት ትቶ ትኩረቱን ወደ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ እንቅስቃሴ አዞረ። የበይነ ቀጠናው ኮሚቴም ለሶስት አመት ትግሉን ሲመራ ከነበረበት ከወላይታ ሶዶ ከተማ ማዕከሉን ወደ ሻሸመኔ አዛወረ ››ይላል።

በሻሸመኔ ከተማ ውስጥ የተሸሸጉት የኢህአፓ ዋና ዋና ሰዎች በአካባቢያው የደርግ ካድሬዎችን ብቻ ሳይሆን ሰርገው የገቡትን

የመኢሶን ሰዎች ማጥራት ጀምረዋል።በጥርጣሬ የደረሱበትን አንድ ወጣት ሀሴሉ ቀበሌ ተገደለ።ሌላው ትልቁ ችግር የአንጃ ሰዎች አሳልፈው እንዳይሰጧቸው በተለያየ ዘዴ እየተከላከሉ ነው።እዚህ ከተማ ላሉ ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ ጥበቃ ማድረግ አስፈልጓል።ይሄ ብቻ አይደለም ቀጣይ ስራ ምን ሊሆን እንደሚችል መመሪያ ይተላለፋል ተብሎ እየተጠበቀ ነው።ይሄንን ለመወሰን አንድ ትልቅ ስብሰባ ይደረጋል።ለተደበቁት የድርጅቱ ዋና ሰዎች እንዴት ከለላ መስጠት እንዳለበት ይመከራል።ይሄ ውይይት ለተደበቁት ሰዎች ብቻ አይደለም።የኢህአፓ ቀጣይ ጉዞና ርምጃዎች ምን መደረግ እንዳለበት የሚወስን ነው።ከታች በተዋረድ አባላት የዚህን ስብሰባ ውሳኔ በእስቸኳይ ይፈልጋሉ ።ቀጣይ እርምጃ የሚወሰደው ከዚህ ስብሰባ ከሚመጣው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ነው። ዋና ማዕከሉን ሻሸመኔ ላይ ያደረገው የኢህአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት ስብሰባቸውን የት ማድረግ እንዳለባቸው ተወያዩ።

ሻሸመኔ ለማድረግ ሰሞኑን አመቺ አይደለም ።ሁለት አባላቶቻቸው ተሰውረዋል። አንድ ሰው ደግሞ ባጋጣሚ ተያዘ። የአብዮት ጥበቃዎች መታወቂያ ጠይቀው አሳያቸው። እዚህ ከተማ በተደጋጋሚ ስላዩት ለምርመራ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱት።ለጥያቄ ወደ ውስጥ ሲያስገቡት የሚመጣውን ነገር ስላወቀ ይመስላል አጥር ዘሎ ለማምለጥ ተንደረደረ።በፍጥነት አጥሩን ተንጠላጥሎ ወጣ። ጫፍ ደረሰ ። ነገር ግን ወደ ውጭ ዘሎ መሄድ አልቻለም።ጫፍ እንደደረሰ ፖሊሶች ጥይት አርከፈከፉበት።ከነጥይቱ ግቢው ውስጥ ወደቀ።ሰውየው ማንነቱና ከየት እንደመጣ አልታወቀም ።ነገር ግን ቆይቶ የከፍተኛ አመራር አባል መሆኑን ተደረሰበት።ኢህአፓ ማዘዣውን እዚህ ከተማ ቢያደርግም ወሳኙን ስብሰባ ሻሸመኔ ውስጥ ማካድ ለጊዜው አስቸጋሪ ነበር።

ዋና ዋናዎቹ ሰዎች የሚሳተፉበትን ስብሰባ ከከተማው አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ኩየራ ከተማ ለማድረግ ስምምነት ላይ ተደረሰ።የዛሬው ስብሳባ ወሳኝ በመሆኑ የሚመለከታቸው ሰዎች በተለያየ ምክኒያት እዚያ ትንሽ ከተማ ተገኝተዋል።እዚህ አካባቢ ያለው የነዋሪው ቁጥር አነስተኛ ነው።





ከተሜው እርስ በእርስ ስለሚተዋወቅ ጸጉረ ልውጥ ሰው በቀላሉ ይለያል።አመቺ የሚሆነው ሆስፒታል ውስጥ ህመምተኛ ለመጠየቅ ሰው በሚበዛበት ቀን ነው የተመረጠው።በዚህ ቀን ጸጉረ ልውጥ ሰው ቢታይ ለምን እንደመጣ ስለሚታወቅ የሚያተኩርበት የለም።ደቡብ ካሉ ከተሞች ከፍተኛ ሆስፒታል ከሚባሉት አንዱ ‹‹ኩየራ ሆስፒታል›› ነው። ብዙ አልጋ ስላለ ራቅ ካሉ ከተሞች ሳይቀር እዚህ የሚገለገሉ በሽተኞች በርካታ ናቸው።

በዚያን ግዜ ኩየራ ሆስፒታል ውስጥ የኩባ ሀኪሞች ይበዙ ነበር።ወቅቱ የኢትዮ ሶማሌ ጦርነት የተፋፋመበት በመሆኑ ሆስፒታሉ አብዛኛውን አግልገሎት የሚሰጠው ለወታደሩ ነው።እነዚህ የኩባ ሀኪሞች የወታደር በሽተኛ ስለሚበዛባቸው ፋታ የላቸውም። ለምሳ እንኳን ወደ ውጭ በብዛት አይወጡም።እዚያው ባሉበት ይቀርብላቸዋል።ሄሊኮፕተሮች እያመጡ ቁስለኛውን ያራግፉላቸዋል። የቁስለኛው ብዛት እየጨመረ በመሄዱ ከክፍሎቹ ውጭ ድንኳን እየተከሉ እስከማስተናገድ ደርሰው ነበር። እዚህ ሆስፒታል ውስጥ ከእነዚህ የኩባ ሀኪሞች ጋር ስማቸው የሚነሳውና ትልቁን ስራ ያከናውኑት ኢትዮጵያዊ ሰው አሉ። ዶክተር ሀጎስ ይባላሉ።ዶክተር ሀጎስ የሰራዊቱ የህክምና ሰራተኛ ናቸው። በተለይ በኢትዮ ሱማሌ ጦርነት ለተጎዱት ወታደሮች የቀዶ ጥገና ህክምና በማድረግ ትልቅ ሚና የተጫወቱ ናቸው።ከኩባ የመጡት ሀኪሞች ለዶክተሩ ትልቅ አክብሮት አላቸው ።ወታደራዊ መንግስትም ቢሆን ሰውየው በችግር ጊዜ ሳይሰለች እየሰጡ ለነበረው ህክምና አድናቆቱን እየገለጸ ነው። ለሙያቸው ታላቅ አክብሮት ስለነበራቸው ሽልማት ተሰጧቸዋል።

የኩባ ዶክሮች ከኢትዮጵያ ወታደሮች ጋር በቋንቋ ስለማይግባቡ ትልቅ ችግር እየታየ ነበር። የዶክተር ሀጎስ እዚያ ቦታ መኖር ይሄን ችግር በመፍታት ትልቅ ሚና ነበራቸው።ዶክተሩ ከህክምና ጋር በተያያዘ አዲስ አበባ ስብሰባ ስላለ ዛሬ ይሄዳሉ። ስለመሄዳቸው ሰራተኛውም ያውቃል።ወታደሮቹ ሰውየው ከሆስፒታል ሲርቁ ደስ አይላቸውም ።ቢሆንም ቶሎ እንዲመለሱ ይፈልጋሉ።ዶክተሩ ከሰራተኞች ጋር ያላቸው ቅርበት የቤተሰብ ያህል

በመሆኑ ሁሉም ይደሰትባቸዋል።ማንም ቢሆን ዶክተሩ ከግቢው ርቀው እንዲቆዩ አይፈልግም። ዶክተሩ የተሰጣቸው መኖሪያ ቤት የተሻለ ቢሆንም ብዙ ግዜ ስራ ቦታ ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ በማለፋቸው ሆስፒታሉን እንደመኖሪያ ቤት ነበር የሚጠቀሙት።

ዛሬ ኢህአፓ እዚህ ከተማ በምታደርገው ስብሰባ የሚወሰነው ነገር ጥልፍልፍ ላለበት ለድርጅቱ ሰዎች ምላሽ እንደሚሰጥ ይጠበቃል።ስብሰባው እየተካሄደ ነው።ቦታው አስተማማኝ በመሆኑ ማንም ወደዚህ የሚመጣ የለም።ለነገሩ እዚህ ከተማ የኢህፓ እንቅስቃሴ ስለሌለ ካድሬዎች የሉም። ማንም አያተኩርም።ስብሰባው እየተካሄደ ወደ መፍትሄ እየሄዱ ሳለ ታጣቂዎች ሰብረው ገቡ።በሩ ሲንኳኳ የተጠራጠሩት ተሰብሳቢዎች ማምለጥ ጀመሩ ።ነገር ግን አካባቢው ተከቦ ነበር።ቤቱን ሰብረው ሲገቡ ስብሰባውን ሲመሩ የነበሩት ዶክር ሀጎስ ነበሩ።ውስጥ የነበሩት ለማምለጥ መተኮስ ጀመሩ ።ነገር ግን አልተሳካም ።አገሬ አዲሱ ወዲያውኑ ተገደለ።ይህ ሰው በኢህአፓ ውስጥ ቁልፍ ሰው ነበር።ትልቁን ሚና የተጫወቱት ከሀዋሳ የመጡት ካድሬዎች ነበሩ።

ለመሆኑ እንዴት ነው እነዚህ ሊያዙ የቻሉት? የሚለው ጉዳይ አነጋጋሪ ቢሆንም አንደኛው ወገን የዶክተሩ ወንድም በሀዋሳ ካድሬዎች ተፈላጊ ስለነበር ኩየራ እንዳለ መረጃ ደርሷቸው መጡ።እሱ እንዳያመልጥ በር ሰብረው ሲገቡ ከውስጥ ሲተኮስባቸው በክበባ እንደያዟቸውና እጅ አልሰጠም ያሉት እንደተገደሉ ተወርቷል ።እዚህ ውስጥ ያሉት በመያዛቸውና አንዳንዶቹ በመገደላቸው ለኢህአፓ ትልቅ ኪሳራ ነበር።በሌላ በኩል ደግሞ ከተሰብሳቢዎች መሀል አንጃ ስለነበር በጥቆማ መያዛቸው ይነገራል።ዶክተር ሀጎስ የኢህአፓ አባል ሆነው በመገኘታቸው ደርግ በጣም ተናደደ።የኢህአፓ አባል ይሆናሉ ብሎ ደርግ በፍጹም ጠርጥሮ አያውቅም ።ብዙ ድብደባ አደረሰባቸው። እንዲገደሉም ተወሰነ።ሆኖም የኩባ ዶክተሮች በጣም ስለሚወዷቸው በነርሱ አማላጅነት ለጊዜው ሳይገደሉ ቀሩ። ደርግ ለህክምና ከጦርነት ከሚመጡ ወታደሮች ጋር በተያያዘ ትልቅ ችግር ነበረበት።ዶክተሩን በአጃቢ ከእስር ቤት እያስወሰደ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረግ ነበር።





ሻሸመኔ ተደብቀው ከነበሩት ውስጥ አስፈላጊ የተባሉት የኢህአፓ ሰዎች ኩየራ ላይ ርምጃ ቢወሰድባቸውም ድርጅቱ ምላሽ አልሰጠም።የበቀል ርምጃ አልወሰዱም።ሌሎች የድርጅቱ ቁልፍ ሰዎች በየስርቻው ስላሉ እነዚህን መጠበቅ ነበረበት።

ለነገሩ ኢህአፓ ሻሸመኔን ለመሸሸጊያ እንጂ ለትግል አይፈልግም እየተባለ ይታማል። ቢፈልግ ኖሮ 19ኙ ሰዎች ተወስደው ሲገደሉ የአጸፋ ርምጃ ይወስድ ነበር። በባንክ ኦፕሬሽን ሰሉ ከተማ ሲገደሉ... ለተገደሉት ሰዎች የበቀል በትሩን ያሳርፍ ነበር።አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተሞች በኢህአፓ አባል ላይ እርምጃ ሲወሰድ ወዲያውኑ ፈጣን ምላሽ ይሰጥ ነበር።በሻሸመኔ ግን ይሄ አልታየም። ሌላው ቢቀር ሻለቃ አሊ ሙሳን በቀለ ሞላ በግላጭ አግኝተውት እርምጃ ሳይወስዱበት የቀሩት እዚያ ከተማ ኮሽታ ላለማሰማትና የኢህአፓ እንቅስቃሴ እንደሌለ ለማሳየት ነው።በርግጥም ትላልቅ የኢህአፓ ሰዎች በድብቅ የመሸጉበት በመሆኑ የነርሱን ደህንነት ለመጠበቅ ነው፡ አብዛኛዎቹ ሰዎቻቸው የመሸጉት ሀሌሉ ቀበሌ እንደነበረና አካባቢው ከከተማው የራቀ ከገበያ ቀን ውጭ ብዙ እንቅስቃሴ የሌለበት ለመደበቅ አመቺ ስፍራ ነበር።የቀበሌው ሊቀመንበር ጥላሁን ግዛው አሳሳ በማድረጉ የተደበቁትን ሰላም እየነሳቸው ነበር፡ አንዳንዶቹ የጥላሁን መገደል ከእዚህ አሰሳ የተያያዘ እንደሆነ ያምናሉ።

## ምእራፍ 23

### የቤት ሰራተኛዋ

ሻሸመኔ ውስጥ ጀማሉ ከተመስገን ጋር በተለያ ጊዜ ተገናኝተዋል። መጀመሪያ ላይ ጥርጣሬው ነበረው። እምነት የጣለበት ግን በኋላ ላይ ነበር። ተመስገን ሶስት ቤት ነው የተከራየው። በአንደኛው ቤት አካባቢ አሰሳ ካለ ወይም ጥርጣሬ ካደረበት ወደ ሌላኛው ቤት ይሄዳል። ጀማሉ እንዲህ ይላል ‹‹ ተመስገን በጣም ተጠራጣሪና ንቁ ነው። እንቅስቃሴዎችን ቀድሞ ነው የሚረዳው።

እራሱን የመቀያየር ትልቅ ችሎታ አለው። ለእዚህ ነው ለብዙ ጊዜ ሳይያዝ የቆየው።በተገናኘን በሶስተኛው ቀን አስቸኳይ መልዕክት ደረሰኝ።የገጠመውን ችግር ሊነግረኝ ነው።ተመስጌን እዚህ ከተማ እንደሚገኝ በአንጃዎች ጥቆማ ደርሶበታል።ይሄን ቀድሞ ነግሮኛል። የቀጠረኝ በግ ተራ ነው።››ይላል

ተመስጌን ለጀማሉ በግ ተራ እንገናኝ ብሎ መላእክት ላከበት እንጂ የት ጋር እንደሚቆም አልነገረውም።ጀማሉ ሄዶ ፈለገው። ሊያገኘው አልቻለም።እዚያ ዝም ብዬ መቆሙ ሌላ ነገር ሊያስመስል ይችላል።‹‹ዝም ብዬ ከምቆም›› በሚል በግ የሚገዛ መስሎ ሊፈልገው ተንቀሳቀሰ ።ወደ አንደኛው በግ ነጋዴ ሲሄድ በቅርብ የነበረው በግ ሻጭ ወደ እሱ ጠራውና‹‹በግ ፈልገህ ነው?›› አለው

‹‹አዎ››

‹‹ምረጣ!!››

‹‹የበግ አይነት አላውቅም››

‹‹ይሄኛው አረፍ ነው።ደግሞም ትልቅ ነው››

‹‹ስንት ነው ዋጋው?››

‹‹አስራ ስምንት ብር ብቻ››

‹‹ውድ ነው››





ጀማሉ በግ የሚገዛ መስሎ ተመስገንን ዞር እያለ እየተመለከተ ነው። ግን የለም። ሰዓት አክባሪ እንደሆነ ያውቃል። ደግሞም ሰዓት ማክበር እንደሚገባው አስጠንቅቆታል። ቶሎ ባለመምጣቱ ምን ችግር ገጥሞት ይሆን ብሎ አሰበ። ወደ ሌላ ቦታ ሊሄድ ተንቀሳቀሰ። ከበግ ተራው ራቅ ብሎ መጠበቅ ፈለገ። ራመድ እንዳለ በግ ነጋዴው እጁን ጎተት አድርጎ። ‹‹ጥሩ በግ ነው ። ላቱን እየው››አለው

‹‹ዋጋው ውድ ነው አልኩህ››

‹‹አንድ ብር ቀንስልሀለሁ››

‹‹ምን አላት አንድ ብር?››

‹‹እቃው መጣ?››

‹‹የቱ እቃ?››

ጀማሉ ተጠራጠረ። ወዲያውኑ እሱ መሆኑን በምልክት ነገረው። ኮፍያው ገጠር እንዳሉት ሰዎች ነው። ሻርፑን አፉ ድረስ ሸፍኗል። ቦት ጫማ ነው ያደረገው። ዱላ እያያዙና አለባበሱ ከገጠር በግ እያመጡ የሚሸጡትን ሰዎች ነው የሚመስለው። ሲሄድ ደግሞ ያነክሳል። አነጋገሩም እንደነሱ ነው።

ድምፁን እንደፈለገው ነው የሚቀያይረው። ሁለት በጎች ነው የያዘው።በጠዋት አምጥቶ እንዳገባደደ ነው። ጀማሉ አወቀውና መነጋገር ጀመሩ ‹‹አልገባኝም የቱ እቃ ነው››አለ

‹‹ትላንት የተነጋገርነውን››

‹‹ታውቀኛለህ?››

‹‹ችግር ላይ ነኝ››

‹‹ምን?››

‹‹የሆኑ ሰዎች ትላንት ተከታተሉኝ››

‹‹የት ?››

‹‹የሆነ ቦታ››

‹‹እንዴት ሆንክ?››

‹‹በመርፌ ቀዳዳ አመለጥኩ››

‹‹አሁን ታዲያ ምን ልርዳህ?››

‹‹የፈለግሁህ ለዚህ ነው››

‹‹ምን ላድርግ? ››

‹‹ስለ እኔ ለሰዎች ነግረሀል?››

‹‹በፍጹም››

‹‹እርግጠኛ ነህ?››

‹‹በጣም››

‹‹ይሄን ነው ማወቅ የፈለግሁት››

ተመስጌን ጀማሉ ላይ እምነት ጥሏል፡፡ እሱም እንዲጥልበት ይፈልጋል፡፡በአብርሀም በኩል ስለመጣ ትልቅ እምነት አለው፡፡ ትላንት የተፈጠረውን ጉዳይ ለጀማሉ በዝርዝር ነገረው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነበር፡፡

ኦፕሬሽኑ ሊካሄድ ሶስት ቀን ሲቀረው ከአዋሳ የመጡ ካድሬዎች በጥቆማ ተመስጌን ያለበትን ቤት አገኙት፡፡ አብዮት ጥበቃዎች አብረዋቸው ነበሩ፡፡ ቤቱን ከጓሮውና ከፊት ለፊቱ መከበብ ጀመሩ፡፡ ጊዜው ወደምሽት ተቃርቦ አስራ ሁለት ሰዓት ይሆናል፡፡ ለአይን ያዝ ብሏል፡፡

መጀመሪያ ተመስጌን የት ጋር እንዳለ ማጣራት አለባቸው፡፡ ግቢው ትልቅ ነው፡፡ ውስጡ ሌሎች ተከራዮች አሉ፡፡ ተመስገን የትኛው ክፍል እንዳለ ካረጋገጡ በኋላ ዘለው ገብተው ያንቁታል ፡፡ ሊያመልጥ ከሞከረ ተኩሰው ይይዙታል ወይም ይገሉታል፡፡ ባሉበት አካባቢ ጥናት እስኪያደርጉ ጥቂት ቆይተዋል፡፡ አካባቢውን በመከበብ ቦታዎችን ሲሸፍኑ የተወሰነ ግዜ ወሰዱ፡፡ ወደ ቤቱ እየተጠጉ እያለ የቤት ሠራተኛዋ ከግቢው በር ከፍታ ወጣች፡፡ ቅርብ ካለው ጉልት ለመሸመት ዘንቢል ይዛ እየሄደች ነው፡፡ በሩን ከፍታ ስትወጣ ታጣቂዎቹ አገኟት፡፡ ፈጠን ብላ ስትሄድ አንደኛው ካድሬ ጠራት፡፡ ፊቷን የተከናነበችውን አሮጌ ነጠላ ትንሽ ዝቅ አድርጋ ‹‹አቤት!!››አለች

«እዚህ ግቢ ነሽ?»

«አዎን»

«የቤቱ ልጅ ነሽ?»

«ሠራተኛ ነኝ»

«ግቢው ውስጥ የተከራዩት ሰዎች አሉ?››

«አዎን»

«ታደለ የሚባል ልጅ ታውቂያለሽ?»





«አውቀዋለሁ»

«ውስጥ ነው?»

«አዎን»

«የትኛው ክፍል ነው?»

«የመጀመሪያው ቤት»

«ምን እያደረገ ነው?»

«ሊወጣ ነው››

‹‹በየት?››

‹‹በጓሮ በር»

ካድሬው ተጣደፈና ሠራተኛዋን ማናገሩን ትቶ ከጓደኞቹ ጋር ወደ ውስጥ ለመግባት ተዘጋጁ፡፡ ካድሬው ‹‹ታደለ አለ?›› ሲላት ሰራተኛ ተብዬዋ ‹‹አዎን›› ብላ ስትመልስለት መጠርጠር ነበረበት፡፡ ስሙ ታደለ መሆኑን በምን አወቀች? እሱ ስሙን ይቀያይራል፡፡ ስሙ ታደለ መሆኑን በምን አወቀች? እሱ ስሙን ይቀያይራል፡፡ አሁን የትኛው ስም ላይ እንዳለ የሚያውቀው ጠቋሚው እንጅ ሰራተኛዋ አይደለችም፡፡ እነሱ ግን ቶሎ ለመግባት ስለፈለጉ ይሄንን ነገር መመርመር አልቻሉም፡፡ ሠራተኛዋ እንደሄደች ቤቱ ውስጥ ገብተው በፍጥነት ፈተሹ፡፡

ታደለ ግን የለም፡፡ አምልጦ ከወጣ በሚል በጓሮ የሚጠብቁ ታጣቂዎች ነበሩ፡፡ እነርሱም አላገኙትም፡፡ የቤቱ በር ክፍት ነው፡፡ እናም እዚያ አካባቢ ይሆናል ብለው ገመቱ፡፡ የግቢው ልጅ ከታደለ (ተመስጌን) ጋር ይግባባል፡፡ግን የኢህአፖ አባል አልነበረም፡፡ አብረው አልፎ አልፎ ኳስ ይጫወታሉ፡፡ ግቢ ውስጥ አንዳንዴ ካርታ ላይ ይሰየማሉ፡፡ ልጁ የመኢሶን አባል ቢሆንም ታደለን ምንም ውስጥ የሌለበት እንደሆነ ነው አድርጎ የሚገምተው፡፡ እናም ቤቱ በከባድ ሁኔታ ሲፈተሽ ታደለ ቀንደኛ ኢህአፖ ነው ተብሎ ሲታደን ልጁ ግራ ገባው፡፡ ሰዎቹም ግቢውን ፣ጓሮውን፣የእከራዮቹን ቤት ፈተሹ፡፡

ሳጥን ውስጥ እንኳን ሳይቀር በረበሩ፡፡ታደለ ግን የለም፡፡ ምን አልባት ጣራ ላይ ወጥቶ ይሆናል ብለው እዚያም ፈለጉት፡፡ ይሄን ሁሉ አሰሳ የሚያደርጉት እርሱ የተከራየበት ክፍል በሩ በመከፈቱ ነው፡፡በሩ ከተከፈተ ደግሞ እዚያ አካባቢ አለ ማለት ነው፡፡ ደግሞም

ከደቂቃ በፊት ክፍሉ ውስጥ እንዳለ የቤት ሰራተኛዋ ነግራቸዋለች። ግን ተፈላጊው የለም። ካድሬዎቹ የቤቱን ባለቤት ማናገር ጀመሩ። ‹‹ልጁ (ተመስገን) መቼ ነው የተከራየው?›› አሉ።

«አንድ ወር ይሆናል»

«ትግባባላችሁ?»

«እኛ ከሁሉም ተከራዮች እንግባባለን»

«ጓደኞች አሉት?»

«ሁለት ልጆች አልፎ አልፎ ይመጣሉ»።

ካድሬዎቹ የቤቱን ባለቤት ብዙ ነገር ጠየቋቸው። እዚህ ይመጣሉ የተባሉትን ሁለት ልጆች መልካቸውንና ቁመናቸው ጠየቋቸው። ታደለ (ተመስገን) ስላመለጣቸው በጣም ተናደዋል። እንደገና ባለቤቱን መጠየቅ ጀመሩ።‹‹ቤቱ እንደምታዩት ክፍት ነው›› አሏቸው።

«አዎን»

«አሁን እዚህ ነበር አይደል?»

«እኔ አላየሁትም»

«ሠራተኛዋ እኮ ነግራናለች»

«የማን ሠራተኛ?»

«የእናንተ»

«እኛ ሠራተኛ የለንም»

«ምን አሉኝ!!!!!»

«ሠራተኛ የለንም»

«የቤት ሠራተኛ የላችሁም?»

«አዎን! ሴት ልጆቼ ናቸው ቤቱ ውስጥ የሚያገለግሉን››

‹‹የታሉ እነርሱ። ››

‹‹ጠዋት ዘመድ ሊጠይቁ እንደሄዱ እስካሁን አልመጡም »

ሰዎቹ ግራ ተጋቡ። የሆነ ነገር እንደተፈጠረ ገምተዋል። አንድ ነገር ተሸውደዋል። የእነሱ ችግር ሠራተኛዋን ትኩር ብለው ያለማየት ነው። ሐሳባቸው የሚፈልጉትን ሰው ቶሎ ለማግኘት ነበር። ከመጣደፋቸው የተነሳ በችኮላ ሠራተኛዋን በደንብ አላነጋገሯትም።





ትኩር ብለው ሳያይዋትና ሳይጠርጥሯት ተመስገን ውስጥ እንዳለ ስለነገረቻቸው ተጣድፈው ወደ ግቢው ዘለቁ።

ሠራተኛዋ ወደ ጉልት የምትሄድ አስመስላ ዘንቢሏን የሆነ ቦታ አስቀምጣ ወደ ወንዝ ሄዳ ከዘንቢሉ ውስጥ ያወጣችውን ልብስ ቀሚሷን ቀይራ ሱሪውን አድርጋ ‹‹ተመስገን አባላለሁ›› በሚል ወደ ትክክለኛ ማንነቱ ራሱን መለሰና ወደ ሌላኛው ቤት ተሻገረ። ምሽቱን ወደ ቤት ደወለና ጓደኛውን (የተከራየበትን ቤት ልጅ) አገኘው። ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ልጁ‹‹ ዛሬ ሰዎች ፈልገውህ ነበር››አለው

‹‹ማናቸው?››

‹‹ካድሬዎች ናቸው››

‹‹እኔን ነው የፈለጉት?››

‹‹እንደዚያ ነው ያሉት››

‹‹አይመስለኝም››

‹‹አንተ ጋር ችግር አለ እንዴ?››

‹‹አይደለም....እኔ ጋር የሚመጡት ጓደኞቼን ታውቃቸዋለህ አይደል?››

‹‹አዎ››

‹‹አንደኛው ኢህአፓ መሆኑን ዛሬ ነው የደረስኩበት››

‹‹እርሱን ነው የፈለጉት?››

‹‹አዎ››

‹‹ታዲያ አንተን ለምን በጥብቅ ፈለጉህ?››

‹‹እነርሱን እንዳሳያቸው መሰለኝ......ግን ቤቱን እንዴት አወቁት?››

‹‹እርሱ እንኳን ስህተት አለው››

‹‹እንዴት?››

‹‹የቤት ሰራተኛችሁ......አለኝ››

‹‹ሰራተኛ አላችሁ እንዴ?

‹‹የተምታታባቸው ነገር ነበር››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹እኛን ሊያሳምኑን ስለፈለገ ሰራተኛችሁ ነግራናለች አለ››

ጓደኛው ካድሬዎቹ መጥተው ያደረጉትንና የተነጋገሩትን ሁሉ በስልክ ነገረው:: በመጨረሻ‹‹ዛሬ ትመጣለህ?››አለው
‹‹እህቴ ጋር ነው የማድረው››
‹‹የት ነው?››
‹‹አርብ ገበያ››
‹‹ታዲያ መቼ ትመጣለህ?››
‹‹ስሞኑን››


ከዚያ በኋላ ተመስገን ወደ ቤቱ አልሄደም:: ማን እንደጠቆመበት ማጣራት ጀመረ::ጀማሉን በአስቸኳይ ጠራና ስለጉዳዩ ነግሮት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ተወያዩ::ለኦፕሬሽኑ የቀረው ሁለት ቀን ስለሆነ አዲሱን እቅድ ነደፉ::ባንኩ ተዘርፎ ጀማሉ አብላጫውን ገንዘብ ለተመስገን አቀበለው ግን ተያዘና ታሰረ:: ታስሮም ሞት ተፈረደበት::

## ኢህአፓና ስፖርት ቁጥር 4 ይቀጥላል







## ሱማሌ

በተጧጧፈ ጦርነት ውስጥ ያሉት ኢትዮጲያና ሱማሊ ድንበር ላይ እየተተጋተጉ ነው። ሞቃዲሾ ላይ ደግሞ ሶማሊያና ኒጀር ለአለም ዋንጫ ማጣርያ ጨዋታ አላቸው። ፊፋ ለዚህ ጨዋታ የኢትዮጵያን አልቢትር መድቧል። የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ዚያድባሬ ሳይቀር ይሄ አልቢትር ሀገራችን ክገባ በህይወቱ ላይ ለሚደርሰው አደጋ ሀላፊነት እንደማይወስዱ ለፊፋ አሳውቁ። የኢትዮጲያው መሪ ሻለቃ መንግስቱ ሀይለማርያም ወደ ሞቃዲሾ የሚሄደውን አልቢትር ጠርተው ሊገድሉት እንደሚችሉ ስጋት ስለገባቸው እንዳይሄድ መመሪያ ሰጡ። በኋላ ግን የኢትዮጵያ መንግስት ጦርነቱን በሚመለከት ወደ ሱማሊ ውስጥ ገብቶ የሚሰልልላቸው ሰው ይፈልጉ ነበር። አጋጣሚውን ጥሩ በመሆኑ አልቢትሩን ሊጠቀሙበት ፈለጉ። ...ፊፋ የሱማሊን ጥያቄ ከተቀበለ እግር ኳስ ከፖለቲካ የጸዳ ነው የሚለው የራሱን ምርህ ሲጥስ ነው። ስለዚህ ለሱማሊ የማያዳግም ደብዳቤ ጻፈ። ሱማሊ ደግሞ የኢትዮጵያ አልቢትር የእኔን መሬት ከረገጠ ሞቱ አገኛለሁ አለች

## የአሚና ቦሳ

የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ትምህርት መጽሀፍ የያዘው መምህር ማስተማሩን እንደቀጠለ ነው። ከገለጸው ገጽ ውስጥ «...ባቡሩ እየተንቀሳቀሰ ነው። አሚና ባቡሩ ላይ ለተሳፈረው ሰውዬ ፍራፍሬውን በመስኮት አቀብላው ሳንቲሙን ስላልሰጣት እየተከተለች ‹ሽልንጌን!!!!!› ‹ሽልንጌን!!!!!› እያለች ትጮህ ጀመር...» እያለ ሄዶና መምህሩ አንድ ጥያቄ አነሳ። ‹‹አሚና ሳብ አደር ነች ወዛደር?›› አለ። የብሄራዊ ... ብረኛውን (በኋላ) ተካበ ዘውዱ እጁን አወጣና ‹‹ሳብ አደር ነች››አለ። ክስአቱ ግቢውን የወረሩት ወታደሮች እያጣዳፉ ወደ እስር ቤት ወሰዱት፤ ወስደውም ዝም አላሉትም። ስምንት ቁጥር ገልብጠው መግረፍ ጀመሩ። ወንድሙ በኢህአፓነቱ ተፈርዶ ተገድሏል። አንደኛው ደግሞ እየተፈለገ ነው። እሱ ደግሞ በአሚና የተነሳ ኢህአፓነቱን አረጋግጠውታል። ተባባሪዎቹ የት እንዳሉ በዱላ ሁሉንም ያውጣጡታል . . .

## ጣቷን ፍለጋ

ሰውየው ዛሬም ቀጥሎ መጥቷል። ሰማንያ 3 ጣቷን ቆርጦ ወስዶታል። ወስዶም እዛው ግድግዳ ላይ በክር እንጠልጥሎታል። ዛሬ ከቀጠለ ሁሉንም ጣቷን ቆርጦ ሊጨርሰው ነው። አራተኛው ጣቷን አስተካከለ። መቁረጫውን ጣቷ ውስጥ አስገባ። ቀና ብሎ ተመለከታትና ‹‹ፋንታ›› ብሎ ጉባሬ፤ በጥንቃቄ ‹‹አቤት›› አለች ‹‹ወንድምሽ የት እንዳለ አትናገሪም?›› አላት። ወንድሟ የቀበሌውን ወሳኝ ሰው ገድሎ ተሰውሯል፤ እሱን ለማግኘት ያልገቡበት ጉድጓድ አልነበረም፤ ግን አላገኙትም። እሷ የት እንዳለ ታውቃለች። ጣቷ መቁረጫው ውስጥ ገብቷል፤ ወንድሟን በጣም ትወደዋለች። አንድ ያላት እርሱ ነው። ያለበትን ከነገረቻቸው ይገድሉታል፤ ካልተናገረችም ጣቷን ሊከታተፉ ነው። ከቆራጩ ጋር ፊት ለፊት ተያዩ። ሰውየው ጣቷን ይዞ አሻቅቦ በተቀደደው ሸሚዟ ውስጥ ጡቷን ሲመለከት አየችው፤ ያን ጊዜ በጣም ደነገጠች። ልትጮህም ተንደረደረች። አሁን ግን ጣቷ ሊሄድ ነው። ስቃዩ ስለበዛ ወንድሟ የት እንዳለ ለመናገር ተዘጋጀች ግን የሆነ ነገር በሀሳቧ መጣላት. . .

(ከመጽሐፉ ገጾች የተወሰደ)

እታፍዘር አታሚዎች 011 849 53 81

ዋጋ 162.00 ብር
USD 15